# እሱና እበ ነገ



በማሞ ውድነህ

# አሉላ አባ ነጋ

## ታሪካዊ ልቦለድ

በማሞ ውድነህ

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
፲፱፻፹፱

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
Kuraz Publishing Agency

ስልክ ቁጥር / Tel. 112719

ፖስታ ሣ. ቁ. / P. O. Box [illegible]

አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ADDIS ABABA
ETHIOPIA

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው ።
All Rights Reserved

የሽፋን ሥዕል — [illegible]

[illegible] ማተሚያ ቤት

# ለዶጋሊ ድል

## መቶኛ ዓመት መታሰቢያ

## የተዘጋጀ

# ምስጋና

ለዚህ መጽሐፍ ጥናትና ዝግጅት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ 'የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ኢንስቲቲዩት' ፣ እንዲሁም የዩኒቨርሲቲዉ የታሪክ መምህር የሆኑት ዶክተር መርዕድ ወልደ አረጋይ ላደ ረጉልኝ ትብብር ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ።



# እንዲህ አለ አሉላ ።

ተሻገረ ቢሉት ቀይ ባሕርን ጠላት ፤
አሉላ ተቆጣ ነደደ እንደላት ።
'ማን' አለ 'ፈረሴን ወልውል ጕራዴዬን ፤
አውርድ ከግድግዳ ጦርና ጋሻየን ፤
ማንም አይረግጣትም ውዲቱን አገሬን ።
ምታ ፤ ነጋሪቱን ንፋ መለከቱን ።
ጀግናው ሁሉ ይከተት ይሰለፍ ይታጠቅ ፤
አገር መደፈሩዋን. ይነገረው ይወቅ ።'
ሰማ ሠራዊቱ የጠላትን ድፍረት ፤
ጥቃቱ ሆነበት የመረረ እሬት ።
'እንሒድ እንዝመት ጠላትን እንውቃ ፤
ክንዳችንን ይየው ትዕግሥታችን ይብቃ !'
በረብረቡ ገደል በጊንዳ ቁልቁለት ፤
የዳማስን ሜዳ የሰሐጢን ኸረት ፤
የአሉላ ሠራዊት ተርመሰመሰበት ።
አገኘው ጠላቱን ተድአሊ ላይ ሠፍሮ ፤
ምሽጉን ገንብቶ መድፉን አነጣጥሮ ።
'በለው !' አለ አሉላ 'ግባ ተደባለቅ ፤
አባየው ክንድህን ማንነትክን ይወቅ ።'
አልቀረም አንጀቱ ጢሶ እንደ ነደደ ፤
የጠላቱን አንገት እያወራረደ ፤
ጣለው በጕራዴ አጨደው ከመረው ፤
ተድዓሊ ዕልል አለች ፤ አሉላን ደስ አለው ።
ከዚያ በኋላ ነው ፤
አሉላ እንዲህ ያለው ፤

'አንድ ጊዜ ከንዱን አቅምሻቸዋለሁ ።
ደግሞ ብቅ ካሉ እደግማቸዋለሁ ።
ራሱ ቀይ ባሕር ድንበር ነው ያገሬ !
የኖረ ነውና ከጥንት እስከ ዛሬ ።
'እኔ የሔድኩለት ሮማን ልገዛ !
ያን ምናልባት ቢበዛ ቢበዛ !
ባሊያንም ሰሐጢ ሊመጣ ይችላል !
ከዚህ አልፋለሁ ቢል ከንዱ ይደግመዋል ።
የኢትዮጵያ ጀግና ይሰባብረዋል ።
ይህ ነበር ምኞቱ የቆራጥነቱ !
አሉላ አባ ነጋ የታገለበቱ ።
«አገሬን የነኩ የደፈሩ ሁሉ !
በኢትዮጵያ ጀግና ክንድ ይዳሸቃሉ»
ስመ ጥሩ ጀግና አሉላ አባ ነጋ !
ጠላት በጉራዴ ሲነዳ ሲያንጋጋ !
በአውሮፓ ጺሑፈ ያስመሰከረ ነው ።
የአሉላን ጀግንነት ማነው አሉ እሚለው
ኤርትራን ሲጠብቅ !
በምዕራብ በምሥራቅ !
በደቡብ በሰሜን !
'አንትኩ' ይል ነበር 'አትድፈሩ አገሬን !'



# ማውጫ

አርእስት ገጽ


መግቢያ ........................ ፱
ወይ ያች ዕለት ........................ 1
ትኩር ጥምድ ........................ 16
ንጉሥ ማራኪ ........................ 40
የጉራው አንበሳ ........................ 45
የማስፈራሪያው ዱላ ........................ 75
«ማሩኝ አለ» ........................ 86
ቁርጠኛው አሉላ ........................ 94
አሉላና እንግሊዞች ........................ 115
ባለሟሉ ተጠረጠሩ? ........................ 123
«ነጭ ወታደር ምፅዋ ገባ» ........................ 131
የኩፊት ጦርነት ........................ 148
አሉላ አሥመራና ምፅዋ ........................ 162
አሉላና ኢጣሊያኖች ........................ 167
መለማመጡ በቃን ........................ 180
እንግዶቹ ........................ 190
ጊንዳዕ ........................ 207

## አርእስት

ገጽ

ጦርነቱ .................................... 237
ችሎቱ .................................... 253
አማላጅነቱ .................................... 263
ማሕፈሰቶች ፣ አሉላና መረብ ምላሽ .................. 280
ምኒልክና ጣሊያኖች ፣ ትግራይና ሁለቱ ራሶች ........ 311
መንገሻ አሉላና ምኒልክ ........................ 362
አሉላ በዐድዋ ጦርነት .......................... 394
የሁለቱ ራሶች ፍጻሜ ............................ 403



# መ ግ ቢ ያ ።

ሆን ተብሎ በልጅነት አእምሮአችን ውስጥ የጀግኖች ገድል እንዲተረጽና የእነርሱን ፈለግ እንድንከተል እንዲያደርጉ ፣ የታዘዙና የሠለጠኑም ይመስል ፣ የመንደር ሽማግሌዎች እርስ በርሳቸው ሲጨዋወቱ ከአባቶቻቸው በፊት የነበሩትን ጀግኖች ስምና ዝና እያነሱ መጣል ያዘወትሩ ነበር ። በቴዎድሮስ፣ በዮሐንስ፣ በምኒልክ ዘመነ መንግሥት ፣ በማይጨው ጦርነትና በአርበኝነቱ ወቅት የነበሩ ታማኝ ጀግኖች ዝና ፣ በኢትዮጵያ ተወልዶ ያደገ ሁሉ የጭውውት መጀመሪያ መሆኑን ያውቀዋል ።

ገና በልጅነቴ ወራት በመንደሬ ሽማግሌዎች አንደበት የንግግር መጀመሪያ ከሆኑት ጀግኖቻችንም አንዱ አሉላ አባ ነጋ ነበሩ ።

«አጼ ተክለ ጊዮርጊስን የማረኩ ፣ ቱርክን (በዚያን ጊዜ ግብፅም ቱርክ እየተባለ ይጠራ ነበር) ፣ ድርቡሹን (ሱዳኖችን) ፣ ጣሊያንን ድል የመቱ ፣ አዩ ጀግና አዩ ወንድ ፣ እናት ወለደች እየተባለ ሲነገር በየጊዜው የምሰማው ታሪክ ነበር ።

ምንም እንኳን የልጅነት አእምሮ እንደ ነጭ ወረቀት ሁሉንም ቀለም ለመቀበል የሚችል ቢሆንም ፣ የራስ አሉላዉ ታሪክና ዝና በመላ አካላቴ የሠረፀ ብቻም ላይሆን ፣ እኔ በጉለመስኩ ቁጥር አብሮ የሚጉለምስ እየሆነ ሔዶ ።

የመንደራችን ደብር አለቃ የነበሩት የኔታ ትኩ እስከ ዳዊት ደገማው ቢያስተምሩኝም ፣ የአሉላን ታሪክ ሊያስነብቡኝ ወይም ሊያስተምሩኝ አልቻሉም ነበርና ፣ እርሳቸውን ከነትምህርታቸው እዚያው ትቼ ፣ ወደ ከተማ ኮብልዬ የዘመናዊዉን ትምህርት ግዕድ ተሳታፊ ለመሆን በቃሁ ። ከዚያም በልጅነቴ እንደ ቀረት ቀረት

በሰማው የነበረውን ታሪክ በአንዳንድ ያለፈርኝ መጻሕፍት ዐልፎ ዐልፎ አነግሁት ። ይሁን እንጂ የበዚያም ወቅት የነበሩት መምህራንና መጻሕፍትም ቢሆኑ የጀግኖቻችንን ገድል በሰፊው አብራርተው ሊያስተምሩ የሚችሉ አልነበሩም ።

ሆኖም ፣ ስለ ራስ አሉላም ሆነ ስለ ሌሎቹ ጀግኖቻችን የነበረኝ ዕውቀትና አድናቆት እየጎላ በይበልጥ እንድጠይቅ እንድመራመር መንገዱን እየከፈተልኝ መጣ ።

ያ ፣ ጉልህ ሥፍራ በአእምሮዬ እንደ ተቀረጸ ወደ ጋዜጠኝነቱ ዓለም ስገባ ፣ የአሉላን ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያንም ታሪክ በይበልጥ እንድከታተል የሚያደርግ ግፊት ሆነ ።

በ1957 ላይ በተመሠረተበት መንግሥት አስገዳጅነት የተገነጠለ ወደ ኤርትራ ከዋና ሀገር ከተዛወርኩ በኋላ ደግሞ ፣ ስለ ራስ አሉላ አባ ነጋ በልጅነቴ በሰማው ከነበረውና በትምህርት ቤትም ካነበብኩት የተቆራረጠ ታሪክ የበለጠና የላቀ ታሪክና ዝና መስማት ጀመርኩ ። ከዚያ በኋላ ስለእሳቸው ጀግና በይበልጥ ለማወቅ የነበረኝ ፍላጎትና ጉጉት በይበልጥ እያደገ መጣ ።

በሰሚ ስሚ ፣ በወሬ ወሬ ይጨዋወቱ ከነበሩት የመንደሬ ሽማግሌዎች ይልቅ ራስ አሉላን በአካል ያወቋቸው የነበሩ የዕድሜ ባለጸጎች ኤርትራ ውስጥ ለማግኘት ቻልኩ ። ራስ አሉላን እናውቃቸዋለን ፣ በዕድሜ ደርሰንባቸዋል ከሚሉት የዕድሜ ባለጸጎችም መካከል ፣ እምባዩርሆ በተባለው ከአሥመራ በስተምዕራብ ከሚገኘው መንደር ነዋሪ የነበሩት ፣ አቶ ጊላሚ ከሌል ተሰፋ ሚካኤል የአንድ መቶ ሰማር ዓመት ዕድሜ ላይ በ1963 ሲያጫውቱኝ ፣

«ራስ አሉላ በአሥመራ በነበሩበት ጊዜ ከእሳቸው ጋር አሥመራ እየሄድኩ የሚያደርጉትን ፍርድ እሰማ ነበር ። ራስ አሉላ ፍርድ በሚያስቀምጡበት ጊዜ ሕዝቡ ግር ፣ በግ ፣ ፍየል ይዞ ይሰለፋል ። ገንዘብም የሆነ እንደሆነ በዕንቁላት ወደ ላይ ከፍ አድርጎ ይዞ ይሰለፋል ። ከፍርድ በኋላ የረታው የወሰደውን ግርም ሆነ ገንዘብ ከፍሎ ይመለሳል ። የተረታው ግን ገንዘቡን ይዞ ይመለስ ነበር (ሥላሴ ቀኝ ጉዳት እንዳያደርስበት ይመለሳል) ። ራስ አሉላ የከር



ትራ አገሩ የሚ ሳሉ ብዙ ወታደር ነበሯቸው ፣ በመጋቢቸው የተርቢ ነበር ። ወታደሮቻቸው ወደ ዘመቻ ሲሄዱ በገቡ አለ ነበሩቸውም ። አንዳንድ ጊዜ ከገበሬዎች ስንቅ ተቀማቶ ሲበደሉ ፣ የተጣሀ እንደሆነም በዓመት አምስት ብር ብቻ ይከፍሉ ነበር ። ያላቸው የሆኑ እንደሆነ ደግሞ ፣ የተወሰደውን ስንቅ አመጋቢቸው ይዘዋቸው ነበር ። ራስ በአንደኛት ፣ በስሉጢ ፣ በሬ በብ ግርጌ ሰፈር ግርጌ ተይዞ በኩራት ዘምተው ግዛታቸውን በመቃኘት ብለውኛል ።

ከእርሳቸው ቀጥለው ደግሞ አመት ወርቁ ደግሞ የቀበሉ የአሥመራ ነዋሪ የነበሩ በአንድ መቶ ዘጠኝ ዓመት ዕድሜያቸው ሲያጫውቱኝ ፣

«ራስ ተቀማጩ እንደ መጡ መጀመሪያ ደባርቅ ተቀመጡ እዛ ተቀብለው ፣ ቀጥለው አሥመራ ሠፈሩ ። በእዛ ባርያ (የደብረ ቢዘን) ብዙ ቸገር ነበርና ራስ ግዛቱ እያሰሙት ለሕዝቡ ይሰሙት ስለነበረ ፣

ቀጣል ራሲ ሰላ

ከገበል ከኢሌኖ መገዲል ተብሎ ተገጠመላቸው ።

ራስ አሉላ ባርያ ዘምተው በሸፋ ዙሪው አሥመራ ሲገቡ ፈረሰኛ ማንዱ መጣሁ

ራሲ አትበሉኝ በሸፋ»

ተብለው ተዘፍኖላቸዋል ። ራስ አሉላ የቀይ ዳማ ፣ መካከለኛ ቁመት ነበራቸው ። ሽፋል መውረት ፣ መልክ ሰው ፣ መካከለኛ ቁመት ነበራቸው ። ሽፋል ይሠሩ ነበር ። በእንግሊዞቹ የወርቅ አክሊል ወርቀዘቦ ያደርጉ ነበር ።

አሥመራ ሲመጡ በዚያ ጊዜ አሥመራ ውስጥ ብዙ ቤቶች አልነበሩም ፣ ነጋዴዎች ትልቅ ግርግም አጠገብ የተሠሩ ቤቶች ነበሩ ። በመጀመሪያ ሲመጡ ብዙ ግብር ያስገቡ ነበር ። እንደ ዛሬው ግን አሥመራ ወታደሮቻቸው በየቤቱ የተሰፋ ይሠሩ ነበር ። እንደዚህ ባለ ጊዜ ሲያልፉ ወታደር በየቤቱ መመሪያ ተሰጥቶ ፈሰሰ ወደ መንገድ ሥነ እንዲቀበሉ አዘዙ ። በዚህም ነገር ሕዝቡ በጣም ተደሰተ

ጅግ ይወዱ ነበር ። የባለቤታቸውን የእቴጌ አምለሱን ተዝካር ያበሉትና ያጠጡት ለድሃና ለደካማ ነበር ።

ራስ አሉላ ፥ ቆራጥ ጀግና ፥ ፍትሕ ዐዋቂ ስለነበሩ እርሳቸው የፈረዱት ፍርድ ፈረንጅ ከመጣ ወዲህም አልተሻረም ።

እመት ወርቄ ኢግዎ ፥ ስለራስ አሉላ የሰጡትን ምስክርነት በማረጋገጥ እንግሊዛዊው ነጋዴ ኤ.ቢ. ዋይልድ «ከ83—87 በሉ ዳን ውስጥ »በተባለው መጽሐፉ ላይ ፥ «ራስ አሉላ ቁመታቸው አምስት ጫማ ከዘጠኝ ኢንች ይሆናል ። ደረታቸው ሰፋ ያለ ትከ ሻቸው የሞላ ስለነበረ ቁመታቸውን ውጦታል ። ጉበዝ ፥ ፈረስ መጋለብና ተኩስ የሚያዘወትሩ ነበሩ ። ፊታቸው ሞላላ ቀልጣፋ አ ፍንጫቸው ቀጥ ያለ ፥ አፋቸው ጠባብ ፥ ጥርሶቻቸው የሚያማምሩ ጸጉ ራቸው ወርቅማ ነበር ። በግል እንግዳ ሲያነጋግሩ ካልሆነ በቀር ከአሽከሮቻቸው ፊት አይስቁም ነበር ። ፈገግ ሲሉ ያስደስታሉ ተጫዋችነት የሚታይባቸው ቢሆኑም ፥ በቁም ነገር ንግግር ላይ ዝንፍ የማይሉ እንደ ሐውልት ድርቅ ያሉ ናቸው ። በጣም ዝነኛ ናቸው ። ፈጣንና የተመሰገኑ አዝማች ናቸው ። የውጊያ ስልት ያውቃሉ ። የሀገራቸውን ጉዳይ ቸል የማይሉ ነበሩና የግብጽ ችን ተንኮል ዐለ ደረሱበት ድል ሊያደርጉዋቸው ችለዋል»ሲል የራስ አሉላን ባሕርይ ያሳውቀናል ።

ከአሥመራ ወደ ምፅዋ በሚወስደው መንገድ ከሃያ አም ስተኛው ኪሎ ሜትር ላይ ከምትገኘው ነፋሲት የተባለችው መንደር በስተምሥራቅ የሚገኘው የደብረ ቢዘን ገዳም አበ ምኔት የነበሩት መምህር ተወልደ ብርሃን ከገዳሙ አግኝተው ከግእዝ ወደ አማርኛና ትግርኛ ተርጉመው በሰጡኝ ጽሑፍ ላይ ደግሞ ፥

«ራስ አሉላ በተፈጥሮአቸው ትሑት ፥ የዋህ ፥ ርኅሩኅ ሃይማ ኖታዊ ነበሩ ። በልዕልና ለሚመጣባቸው ግን በወሰኑት ነገር ጸጉ ወደኋላ የማይመለሱ ናቸው ። በመከራና በጭንቅ ጊዜ ደግሞ እውነተኛ አርበኛ ከመ—ጥሩ ጋ የማይሉ ኃይለኛ ነበሩ ።

ራስ አሉላ ፥ የጦርነት ጉዳይ ይወዱ ነበሩና በየጊዜው ሠራ ዊታቸውን ግብር እያበሉ ፥ ወታደሮች ሲያስጨክሩ ለባለሙያው



ሙያውን ያስቀምሩ ነበሩ ። ደግሞ በየጊዜው በሳምንት በወርም ሠራዊታቸውን እየሰበሰቡ ጠመንጃ ፥ ጕራዴ ፥ ሴፍ እያደሉ ፥ «ጠመ ንጃህን ተኩስበት ፥ ጕራዴህን ምዘዝ ፥ ባለሰይፍም ፋጭ» እያሉ ወታደሮቻቸውን መፈተሽ ልማዳቸው ነበር ። ስለዚህ «አሉላ መጣ» ሲባል ጠላት ሁሉ ይንሸቀሸቅ ነበር ።

ራስ አሉላ ፥ በተድአሊ ጣሊያኖችን ድል ከመቱ በኋላ የት ግሬ አቅራሪ እንዲህ አለ ።

«ሐሽከር ፈንቅል ዝበለ ንባሪ
ሐሽከር በዝብዝ ዝበለ ንባሪ
ጕይታ ሐማሴን ምድሪ ቀሪ
ጕይታ አሳውርታ ገምገም ባሕሪ
ወደረኛ ጣልያን በዓል ምስሪ
ወደረኛ ቱርክ በዓል ምስሪ
ወደረኛ ድርቡሽ ሐጂ ኑሪ
ሐጺርን ፥ ነዊሕን ብሐደ ዘመእራሪ
ይውሕጠና ዝብሉኻ ከምባሕሪ
የንድደና ይብሉኻ ከምኂሒሪ
የዓብጠና ዚብሉኻ ከምነብሪ
ከም አምበጣ እብ ጕቦ ሰፋሪ
መጋረጃ ሐበሻ መቁሀ ሰባሪ
ድፍእ የብሉኻ መነጸሪ ፥
ኩዒትካ ተእትዎም ትሀቲ ምድሪ
መሐር ኢሉሙኺ ዘይመሐሪ
ግብር ኢሉሙኺ ዘድይገባሪ
አብልብኺ ተጺሐፉ አታምክሪ
ከም አባነጋ መንጦ ፈጣሪ
ብእግዚአብሔር ጸአ ኩይኑ ብፈጣሪ
ክንሰምዮም ደሞ ነገ—ነጋ ጕይታና
ላእሊም ትግጠም ከምደመና
ንድኻ ትፀንሕዎ ብትሕትና
ንሐያል ትፀንሀዎ ብልእልና
ናይ ልቦም ዝገብሩ ከምእወረልና?

የጁ ተደፍሏል ዳም ከነገሬከም ዘና
ልርድ መንልዎም ገሃላ በና
የጁ ከሬት ደግም ከነገሬከም ዘና
ድርቡሽ መደሌት ከተመለሰ ደመና
የጁ ነጋ ወረደሬን ከበለምሌት ከዱና
ለብደን ደርሻት ተቩሌና
ርእስ በበርዓዶ ከምሸና
ዓጤሚ አለም ሰራዊቴ ከና
አፀ ፋሙድ አልደርሰዉ ዓትማን ጅዋናዬ

## ትርጉም

የፈንቅል አሽከር ካለ ዋሬ
የበዝበዝ አሽከር ካለ ዋሬ
የዲጋው አገር ያማሪን ጌታ
የበሉር ዋጥ ያስወርቃ
የባሊያን ፣ የዋበዕ አሳሳሪ
የቀርከ ፣ የደርቡሽ የሐበሻ ኩሬ
ፈጀም ከዋይ አስገዳል
ይፈተሃል አሉ ፣
እነዚያ ሁሉ ።
ዓሊር ነው ብለው የሚወቁ
አሳቅ ነው ብለው የሚለዋ
ነብር ነው ብለው የሚነቸላ
እንደ አንበሳ ብቅት ሲል ውፋራ
የአበባ እጥር ብሩት በባሬ
ይነከኩሀና ብለው ለመኪራ
ትርሺቸዋለሁ በበሳ መከራ ።
አትማሬቸው ቢለምኑ
ቢለማመጡ ቢማፀኑ
ግነው እንደአባ ነጋ ጊዮል ሄሬ
እግዜር ካለም ያው ሬሳ
ጌታዬን የአዩ ናቸውና



ከሰው በላይ እንደ ደመና
ደንገን በትህትና
ኃያሉን በለዕልና
የማስተዳደር ልምድ አላቸውና
ዳግም ሳውሬላቸው የደንቢን ዘና
ታሪክ አለ እኚያ እናባ ፀና
ዳግም ለንገሬቸሁ የመቅን ዘና
ድርቡሽ ተኮፍሶ መጣችና
ያሁ ነጋን ታሪክ ሳታውቀው
እንደ ቅጠል ረግፎ ሳበረው ።
በእሳም ልጅ አናንቅ ከብ ሥርተው
ዝጀት ኩሉ ዐመድ አርገው ።

ታላቁ ደራሲያችን ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ዋዜ ይመቅ ታሪክ» በሚል አርእስት በ1915 ዓመተ ምሕረት መጽሐፍ ስለ ራስ አሉላ ሲተርኩልን ፤

«ራስ አሉላ አባነጋ የሐማሴንና የአውራጃዎ ሁሉ ገዥ ነበሩ ። በጀግንነታቸውም እጅግ የታወቁና የተፈሩ ሰለሆኑ ፤ በሐማሴን በኩል የመጣውን የውጭ ጠላት ሁሉ ዘወትር ድል እያደረጉ ይመልሱት ነበር ። በጨዋታ ላይ የጀግንነት ሥራ በተነገ ጊዜ በጀዋ ራስ ጉበና ፣ በትግሬ ራስ አሉላ ፣ በጐጃም ራስ ደረሶ እየተባሉ ሲመሰገኑ ይኖራሉ» ብለዋል ።

እንዲሁም ብላታ መርስዔ ኀዘን ወ/ቂርቆስ የአማርኛ ሰዋሰው በሚል ርእስ በ1919 ዓመተ ምሕረት መጽሐፍ ሲጽፉ ወርቅ የአማርኛ ቅኔ» በሚለው ክፍል ፤ የሚታሉ ጎንጉ የገጠ ሙትን በመጥቀስ ፤

«አዋንቱን ለአቀመጥ መታበር ቀዳሬ
ጉበናን ከጀዋ ፤ አሉላን ከትግሬ
ለመኝ አድራለሁ ፤ ትግንትና ዛሬ
አሉላን ለግደት ጉበናን ለዋሬ
ተበበለና ተገግሎ ግላ
አሉላ ተትግሬ ጉበና ተጋላ ።

ጉበና ሴት ልጁን ሊያስተምር ፈረስ'
አሉላ ሴት ልጁን ጥይት ሊያስተኩስ ።
አገሬ ተባብራ ካልረገጠች እርካብ
ነገራችን ሁሉ የእምቧይ ካብ ፣ የእምቧይ ካብ።»
ብለው አስፍረውታል ።

ስፋትና ዝርዝር አይኑረው እንጂ ፣ ስለራስ አሉላ ማንነትና ዝና ብላቴን ጌታ ማኅተመ ሥላሴ ወ/መስቀል ፣ አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ፣ ኩሉኔል ይርዳው ልባርጋቸው ፣ አባ ገብረ የሱስ ኃይሉ ፣ ደጃዝማች አብርሃ ተሰማ በየመጻሕፍቶቻቸውና በየጋዜጦቹ ሲያስተዋውቁን ኑረዋል ።

በተለይም ደጃዝማች አብርሃ ተሰማ የተባሉ የኤርትራ ክፍለ ሀገር ተወላጅ በ1938 በአሥመራ ከተማ ይታተም በነበረው «ሰሙናዊ ጋዜጣ» ላይ በአሰፈሩት ጽሑፍ ፣

«እንዴት ነህ አሉላ አባ ነጋ
ለእሉም ቁቢ ልጅ የዘሪጋ
ሽበሽ ፈረስ የሚያላጋ
ትቆርጣቸዋለህ እንደ ሥጋ
ትሰነጥቃቸዋለህ እንደ ዱጋ
እንዴት አለህ አባ ነጋ አሉላ
በአሥመራ የነበርህ መዝጊያ ቡላ
በምጥዋ የነበርህ መዝጊያ ቡላ
ዐይኑ በእሳት ጉራዴ ተበላ
ጉራዴህ ጣሊያንን የሚበላ
የቦሬሳው አሽከር ብሉ ቢወጋት
ቱሚ ወእርምሚ ቢላት
ገምስ አለች ፣ ተሰነጠቀች ከሁለት
የቦሬሳ አሽከር የበለጥን ሥራ
ካንተ በኋላ ምርኩብ ተሻገራ
ጣሊያን እርድ ሠርቶ በአሥመራ
የቦሬሰ አሊጋ እግሩዋ ተሰበራ
እንዲሁ ልትጠፋ ብላ
አጠፋሀኮ እነንብላህ ንብላ ።»



ሲሉ የጠቀሱት ሕዝባዊ ግጥም አሉላን በደብልዋ እንደነበሩ ናቸው ተጨማሪ ቀንዲል ሆናልኛል ።

ከራስ አሉላ የልጅ ልጅ ከፊታውራሪ በየነ አብርሃ ጋር ስንጨዋወት ፣ «አያትዎ ራስ አሉላ ትግራይ ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ 'ወዲ ቁቢ' (የቁቢ ልጅ) እየተባሉ ነው የሚጠሩት 'ቁቢ ምን ማለት ነው' አልኳቸው ።»

«ቁቢ ማለትማ ያንበሳ ጭራ ማለት ነው» አሉኝ ።

«አባነጋ ማለትስ ?»

«አጼ ዮሐንስ የራሳቸውን ፈረስ ሲሸልሙዋቸው ያወጡላቸው የፈረሳቸው ስም ነው ።»

«እስቲ ስለ አያትዎ ስለ ራስ አሉላ የሚያውቁትን ያህል ያጫውቱኝ ።»

«ዛሬማ አርጅቼ ሰማኒያ ዓመት ሆናኝ ! ስንቱ ትዝ ይለኛል ልጄ? ገድላቸውን አልጻፍነው ፣ እንዲሁ የወሬ ወሬ ሆኖ ቀረ ። የወሬ ወሬ ሰትውልደ ትውልድ ሊተላለፍ ነው ፤ ቀደም ብለህ ሳላረጅ አግኝተኸኝ ቢሆን ኑር ብዙ ብዙ ነገር አጫውትህ ነበር ። ዛሬማ ሁሉ ተዘንግቶኝ ምኑን ተምን አድርጌ እነግርሃለሁ ?ፈረንጆች ይልቅ ጽፈውላቸዋል ሲባል ሰምቻለሁና ያንኑ ብታፈላልገው አይሻልም?» ብለው ጥያቄዬን ወደ ባሕር ማዶው ወረወሩብኝ ።

ቢሆንም ፣ እእምሮአቸው የደበቀው ትዝታ እንደማይታጣ በመተማመን ፣ «እንዲያው መቼም አንዳንድ ጊዜ የምትጨዋወቱበት ትዝታ ይኖር ይሆናልና የሆነውን ትዝ የሚለዎትን ቢነግሩኝ !» ብዬ አትኩሬ ስመለከታቸው ፣ እምቧይ ወደ ሰማይ ተወርውራ እስክትመለስ ድረስ የሚወስድባትን ያህል ጊዜ ቢያንሰላስሉ ቀዩና ጉረሮአቸውን አሰስለሰው እኔን ቅክ ብለው እያዩኝ ፣ «ደጃች ገዛኸኝ የእያቴን የራስ አሉላን የእኅት ልጅ አግብተው ይኖሩ ነበር ። ደጃዝማችነቱንም የሰጡዋቸው አያቴ ናቸው ። በኋላ ገዛኸኝ አያቴን ከድተው ለራስ መንገሻ ገቡ ።

ዓመት ወጣት ሲሆን ፣ ተከታዩ አምለሱ ደግሞ የዐሥራ አራት ዓመት ጉብል ነበረች ። ለሁለቱም መምህር ተቀጥሮላቸው በግቢያቸው ውስጥ ይማራሉ ። ምንም እንኳን እሉላ የባልገዳ እርሌያ ድምፁ አሽከር ቢሆንም ፣ እርሱ እንደ ተመኘው ምርጥ ጠመንጃ ይዞ ተከታይ ከመሆን ደረጃ አልወጣም ።

አሽከርነቱ ለደበበና ለአምለሱ ሆነ ። የሁለቱን እግር ያቀባል ፣ ሁለቱንም ይላላካል ፤ ሁለቱም ሲወጡና ሲገቡ ይከተላል ።

እርሌያ ድምፁ የቆቅ የስስና የድኩላ ሥጋ እጅግ አጥብቀው ይወዱ ስለነበረ ፣ ድኩላና ስስ አድኖ ገድሎ ወይም በወጥመድ ይዞ ለሚያቀርብላቸው አሽከር ልዩ ጉርሻና ሽልማት መስጠት ያዘወትሩ ነበር ። የአውሬ ሥጋ ጥብሱንና ቋንጣውንም ለሌላ ቀርቶ ለልጆቻቸው እንኳ «እንዳይሸታችሁ» እያሉ ከማጉረስ በቀር እንደ ልባቸው አያስጠጉቸውም ነበር ።

«ደበበ ተኳሽኮ ብትሆን ኖሮ ፣ የአውሬ ሥጋ ታጠግበኝ ነበር» ብላ አምለሱ ወንድሟን አንድ ቀን በተቀለደበት ፣ እሉላ ሰምቷት ኖሮ ይህችን ሲያምሰለስል ቆይቶ ከዕለታት አንድ ቀን ከአባቷ ቤት ወደ አክስቷ ቤት ስትሔድ ጠመንጃ ይዞ ሲከተላት ጠጋ ብሎ ፣

«የአውሬ ሥጋ ትወጃለሽ?» ብሎ ጠየቃት ።

«ምነው ገድለህ ልታመጣልኝ ነው?» ብላ መልሳ ጠየቀችው ፣ ከአሽሙራዊ አስተያየት ጋር ።

«መተኮስ አልችል መሰለሽ?»

«ተኩሱንማ ማንም ይተኩሳል አነጣጥሮ መጣሉ ነው እንጂ የወንዶች መለያው» አለችው ።

«ለመሆኑስ የምን አውሬ ሥጋ ነው የምትወጂው?»

«ያውም መርጠህ ነው የምታመጣልኝ?» ብላ እንደ ገና አሽሟጠጠችው ።

«ተኩሼ ብስትም በወጥመድ እይዛለሁ ።»



«ከሆነልህማ ቆቅና ስስ ነው የምወደው ፤ ያስለመዱኝም የእነርሱን ሥጋ ነው» አለችው ። ይህን ከተነጋገሩ ከሦስት ቀናት በኋላ ከረፋዱ ላይ እሉላ ስስ ገድሎ ልጅ አሽከርም ወስዶ ሰጣት ። ከዚያ በኋላ ቆቅ በወጥመድ ስስና ድኩላ በጥይት እያመረተ ማቅረቡን በመቀጠሉ አምለሱ ፣ ለአባቷ ነግራ ጠመንጃ አሸለመችው ። ባልገዳ እርሌያ የሸለሙት ጠመንጃ ደግሞ በዘመኑ ብርቅ የነበረችው መግሪያ ነበረች ። እርሷም ማለፊያ ኩታ ሸለመችው ።

በተኳሽነቱና በአዳኝነቱም ብቻ ሳይሆን ፣ እሉላ ለጌታው ቤት አሳቢ ተቆርቋሪና ታማኝ በመሆኑ ፣ በጌትየው ዘንድ እጅግ ተወዳጅ ባለሟል ሆነ ። ቆይቶም ከልጆች አሽከርነት ደረጃ ወጥቶ የራሳቸው የባልገዳ እርሌያ አንጋች ሆነ ።

እያደርም እሉላ የጌታው ምሥጢረኛ እየሆነ በመሔዱ ፣ አምለሱ ስትደለት ወንድሟ ደበበ በቅናት ልቡ እያበጠ ሔደ ። በየአውራጃዎችና ወረዳዎቹ እየተላከ ለጌታው አስፈላጊ የነበሩ ጉዳዮችን ማቀላጠፍ ጀመረ ። ሕዝቡ ለጌታው የሚያቀርበውን ጉዳይና ስጦታ ይቀበላል ፣ ወደ ምፅዋም ከነጋዴዎች ጋር እየሔደ የባሕር ማዶ ዕቃዎችን ጠመንጃና ጥይት መግዛት ጀመረ ። እነዚህም ሁኔታዎች የእሉላን ዕውቀት የአስተሳሰብ ኃይልና ልቀት እያስፋፉለት መጡ ። በተለይም ምፅዋ ደርሶ መርከቦችን ዐይቶ ፣ ጥቅማቸውን በመገንዘቡ ለዚያ የባሕር ዳር ለሆነው መሬትና ክብር በሕይወቱ ሙሉ ያልቀዘቀዘ ፍቅርና የጀግንነት ወኔ አደረበት ። በዚያ ዘመን ከልዩ ልዩ አገሮች በቀይ ባሕር ሲተላለፉ የነበሩ የንግድ መርከቦች ወደ ምፅዋ ወደብም ጎራ እያሉ ያራግፏቸውና ይጭኗቸው የነበሩ ሸቀጣ—ሸቀጦችና ጠመንጃዎችም ለባልገዳ እርሌያ ብቻ ሳይሆን ፣ ለመላዋ ኢትዮጵያ የቱን ያህል እንደሚጠቅሙና እንደሚያስፈልጉ ከልቡ ለማመን የቻለባትንም ዕውቀት ቀሰመ ። በዚያው ጊዜም ነበር ያን በር በጀግንነት መጠበቅ እንደሚገባ ሊገነዘብም የቻለበትን አጋጣሚ ለማየት የበቃው ።

እሉላ ፣ ከዚያ ቀበሌ ከመድረሱ ከብዙ ዓመታት በፊት አስቀድሞ ቱርኮች ያን አካባቢ ይዘው ፣ ወደ ደጋውም ቀበሌ እየ

አሉላ የሥራ ታሪክ በሩ አድርገው የጻፉት የእሥራኤላዊው የሐጋይ ፡ ኤሪክ ጥናታዊ ሥራዎች ለዚህ ጽሑፍ መሠረት ሆነውኛል ።

አሉላ በሌላው አንደበትና ብዕር ቀርቶ በመረሩ ጠላቶቻቸው ዘንድ እንኳ ከፍተኛ አድናቆትና አክብሮት ያተረፉ በመሆናቸው ታሪካቸውን ለልብወለድ ፡ ለትያትርና ለግጥም የአጻጻፍ ስልቶች እጅግ ምቹ ሆኖ እንዲገኝ አድርጎታል ።

በዚህ በእውነተኛ ታሪክ ላይ ተመሥርቶ የጸሐፊው የልብ ወለድ ሥራ ተጨምሮበት በቀረበው ጽሑፍ እንደሚታየው ፡ አሉላ ከዝቅተኛ ኑሮ ተነሥተው የአጼ ዮሐንስ (የግብፈራሪያ ዱላ ፡ የአጼ ምኒልክ የጦር ስልት አማካሪና ለዐድዋውም ጦርነት የመረጃ ሥራዎች አቀነባባሪና ኃይል አስተባባሪ እስከ መሆን በደረሱም ፡ ገና የራስ አርአያ ድምፁ የቤት አሽከር ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ የመረሩ ጠላቶችና ተፎካካሪዎች ነበሩዋቸው ።

በካርቱም ፡ በካይሮ ፡ በለንደንና በሮም ከነበሩት የአገሪቱ ጠላቶች ጀምሮ በአጼ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት ዙሪያ አሰፍስፈው እስከ ነበሩት ተቃዋሚዎቻቸውና ተፎካካሪዎቻቸው ሁሉንም በትዕግሥት ፡ በቆራጥነትና በዘዴ ተቋቁመዋቸው አልፈዋል ። በዚህም ጽሑፍ ውስጥ እነደጃዝማች ደበበ አርአያ ፡ እነባላምባራስ ክፍለየሱስ፡ እነደጃዝማች ወልደሚካኤል ፡ እነራስ ሐጐስ ፡ እነራስ ገብረመስቀል ፡ እነበጅሮንድ ስውጤና እነርሱን የመሳሰሉት ተቀናቃኞቻቸውና የመረሩ ጠላቶቻቸው ተራ—በተራ ሲወድቁና በመጨረሻም ለታላቁ ጀግና ለአሉላ አባ ነጋ ሕይወት አሳዛኝ ፍጻሜ ምክንያቶችም እስከ መሆን ሲደርሱ እናያለን ።

ታላቁ አሉላ ፡ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ ቁጥራቸው በትክክል ያልታወቀ ወላጆች ልጆቻቸውን «አሉላ» እያሉ ስም ያወጡላቸዋል ። ይህ ገናና ስም ፡ ወንዝና ጋራ ጎሣና ሃይማኖት የማይገታው በመሆኑም ፡ ከኢትዮጵያ መልክዓ ምድር ዐልፎ ባሕር ማዶም በፈጠረው ነጸብራቅ ከተማረኩት የታሪክ ሊቃውንት ሚስተር ሪቻርድ ፓንክረስት የተባሉ እንግሊዛዊ ልጃቸውን «አሉላ» ብለውታል ።



እኒሁ ሊቅ በምን ምክንያት ልጃቸውን አሉላ ብለው እንደ ሠየሙት ብጠይቃቸው ፡ «እንደሚታወቀው ሁሉ አሉላ ታላቅ ጀግና ለሀገራቸውም ከፍተኛውን አገልግሎት የፈጸሙ ናቸው ። የጀግንነታቸው አርአያነትና ምሳሌነት በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአፍሪቃና በእስያ የሚያንጸባርቅ ነው ። ከዚህም ሌላ ደግሞ አሉላ ከተራ ቤተሰብ የተገኙ ናቸው ። ይህን ስለማውቅና ለእርሳቸው ያለኝንም አክብሮት ለማስታወስ ስል ነው ልጄን «አሉላ» ብዬ የሠየምኩት ። ታዲያ ይህ ስም በእንግሊዝ አገር በተለይም በወጣቱ ትውልድ ዘንድ ብዙም የማይታወቅ በመሆኑ አንዳንድ ችግሮች አስከትሎ ነበር ። ለምሳሌ ለልጄ ከትምህርት ቤቱ ሊጻፍለት «አሉላ» የሚለውን ስም ካለማወቅ የተነሣ በእንግሊዝኛውም ፊደል «ኤ» የመጀመሪያውና የመጨረሻው ስለሆነ ፡ የሴት ስም እየመሰላቸው «ሚስ» (ወይዘሪት) እያሉ ይጽፉለት ነበር ። እየቆየ ግን ስሙ እየታወቀ ስለ ሔደ ከዩኒቨርስቲው በግዕዝ ቋንቋ ጥናት ተመርቆ ሲወጣ ፡ ዲግሪውም የተጻፈለት «አሉላ ፓንክረስት» ተብሎ ነው ። እርሱም ይህን ስም ከነታሪኩ በጣም ይወደዋል» ብለውኛል ።

በኢትዮጵያ ውስጥ የአሉላ አባ ነጋን ስም የሚያወሱ የኳስ ሜዳ ፡ ትምህርት ቤት ፡ ወታደራዊ ተቋሞች ቢኖሩም ፡ የአሉላንና የሠራዊታቸውን ታላቅ ታጋይነትና ጀግንነት በይበልጥ አጉልቶ ለትውልድ ለማስተላለፍ ሲባል ደግሞ ፡ ከአብዮቱ ወዲህ ፡ ታላቁን ጀብዱ በፈጸሙበት በዶጋሊ በሪሃግ ቀበሌ ሐውልታቸው እንዲሠራ መሠረቱ ተጥሏል ። ይህም በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በመላው አፍሪቃ ሲያንጸባርቅ እንደሚኖር አይጠረጠርም ።

እርግጥ ነው ፡ ስለታላቁ ጀግና ስለ ራስ አሉላና ስለሠራዊታቸው ብዙም እንዳልጻፍኩ ይሰማኛል ። ሆኖም ከልጅነቴ ጀምሮ በአእምሮዬ ለተቀረፀው ጥያቄ መጠነኛ መልስ ለመስጠት በመሞከሬ የመንፈስ እርካታ ይሰማኛል ።

ደራሲው

ማሞ ውድነህ ።

# ወይ ያች ዕለት

በመጀመሪያ የተኮሳት ጥይት ጊላግወን ሳተች ። ሁለተኛ ፉ·ከ የቀኝ ቀንድ መታች ፤ ሦስተኛዋ ባክኗች ፤ አራተኛዋም ተሠለበች ፤ አምስተኛዋ የግራ ቀንድ መታች ። የተሰጡት ጥይቶች አለቁ ። ወጣቱ በንዴት እየጨሰ ስናድሩን ከድግኑ ቀና አደረገው፤ በትልቁ ደትራ ሥር ተተክሎ የነበረውን የክብት ግንባር እየንት በጥላቻ ተመለከተው ። ሦስቱንም ጥይቶች አባክና እናቱን በከርከም ሊያስፈልሰው የተሰለፈ ጠላቱ ሆኖ ታየው ።

«እንዴትክ ፤ በምን የተነሣ ሦስት ጥይት ታባክናለህ?» ብለው ባሻይ ፈንጃ ስናድሩን ከጁ ነጠቁና ከንዱን ጥርቅም አድርገው ይዘው ፤ ይተናንቃቸው የነበረውን ቁጣ ከላዩ ላይ እያፈሰሱበት ፤

«ስትተኩስ ሆድህን ሸልገህ ምራቅህንና ትንፋሽህን ውጠህ ሰውነትህን አስቀጥተህ መንፈስህን ሰብስበህ ነው ፤ ታዲያ መሳብ አልነበረምን?» ብለው ከንዱን ለቀቅ አደረጉና እንደገና ጆሮውን ይዘው እንደ ማፍተልተል እያደረጉ ፤

«ከጊላግህ ላይ በታንጣጥር ትንፋሽህን ካላቀክ ፤ ሰውነትህን ካላላክ ትበታለህ ብትህ አልነበረምን ይህን ነገር አባትህ ቢሰማ ጭንቅላትህን በከርከም ነው የሚያፈልሰው ። ሁለተኛ እንኳን ከኔ ፊት ቀርተ ፤ 'ተኩስ ሳተ' የሚል ወሬ እንዳልሰማ» ብለው አንድ ጊዜ ከአናቱ ላይ ለኩፍ አድርገው ለቀቁት ።

ባሻይ ፈንጃ ፤ በጠዋት ተነሥተው ከቤታቸው አልፎ ብሎ በነበረው ሸንኮ ተቀምጠው ፤ ስናድራቸውን ከደንጋይ ላይ አጋድመው የጠዋቷን ፀሐይ ሙቀት በሰውነታቸው ውስጥ ሲያከማቹ በነበሩበት ሰዓት ፤ ወጣቱ አሉላ የዝቁሊ ሚካኤል መም

ሀር ወደ ነበሩት ፡ መምህር ወልደ ጊዮርጊስ ሲሔድ ነበር ፡ ጠር
ተው እርሳቸው ከነበሩበት ሸንጎ ራቅ ብሎ የነበረውን ነጭ
የከብት ግንባር አጥንት እንዲመታ ያስተኮሱት ።

ሸንጎጡ የመንደሪቱ ነዋሪዎች ጡዋትና ማታ እየተሰበሰቡ
የሚጫወቱበት የሚመከሩበትና የተጣላ የሚያስታርቁበት ብቻም
ሳይሆን ፡ አንዳንድ ቀንም በውርርድ እየተኮሱ ዒላማ የሚመቱ
በት ነው ። የተኳሾች መፈተኛ እንጂ መለማመጃ እንኳ አልነ
በረም ። በዚያች የቢጋ ወራት ስትሰለመለም የነበረችውን የፀ
ሐይ ሙቀት እየተሻሙዋት በነበረበት ሰዓት ፡ አሉላን ጠርተው
ያስተኮሱትም ከዚያ ዕለት በፊት ደጋግሞ ተኩሶ ፡ ዒላማውን
ማምታቱን ሰምተው ስለነበረ ነበር ለፈተና ያስተኮሱት ።
የመጀመሪያ ጊዜያቸውም አልነበረም ፡ ከመጀመሪያው ጀምረው
ተኩስ አስተምረውታል ። ብዙ ጊዜ ዒላማውን ሲስት አንዳ
ንድ ጊዜ በትክክል መትቶ ነበር ።

የባይሻን ኩርኩም በጡዋት የቀመሰው አሉላ ፡ በእልህ እየ
በገነ ከቤተ ክርስቲያኑ ዘንድ እንደ ደረሰ ከዘወትሩ በተለየ ሁኔታ
ጉንበስም ሳይል የቤተ ክርስቲያኑን ካብ እንደ ቆመ ተሳልሞ
ወደ መምህሩ ጉባኤ ሔደና ወንበራቸውንም ሳይሳለም ከጓ
ደኞቹ ጋር ተደባልቆ እያንዳንዳቸውን በንቀት ይመለከት ጀመር ።

በዕድሜው ከዐሥር ዓመታት በላይ የሆነው አሉላ ፡ የገበሬ
ልጅ በመሆኑ የሰኔ ወር ከገባ በኋላ ከብቶች ማገድ ፡ በእርሻ
ሥራዎች መሰለፍ ፡ ቀጥሎ በመኸር ከተታ መሠማራት ዋና
ተግባሩ ስለ ነበረ ፡ ለትምህርቱ ጉዳይ አጅግም ጊዜ አያገኝለትም
ነበር ። ከጥር እስከ ሚያዝያ መጨረሻ ግን ከግብርናው ጣጣ
ወደ ትምህርቱ ገበታ ያመራል ። በእነዚሁ ጊዜያትም ቢሆን
የእርሱን ጉልበት የሚጠይቅ የቤትና የግብርና ሥራ ጠፍቶ
አልነበረም ። አባቱ ግን ተምሮ የቤተ ክህነት አገልጋይ እንዲሆ
ንላቸው በሊተመኙ ነበር ፡ ታናናሾቹን ልጆቻቸውን ለሥራ
መድበው ፡ አሉላን ወደ መምህር ወልደ ጊዮርጊስ ይልኩት የነበ
ሩት ።

መምህር ወልደ ጊዮርጊስ የቤተ ክርስቲያን ጉዳያቸውን አከ
ናውነው ፀሐይ መግንተር ስትጀምር ወደ ጉባዔያቸው ሲያመሩ



ተማሪዎቻቸው እየተሯሯጡ ተቀበሉዋቸው ። ከወንበራቸው ላይ
እንደ ተሠየሙም ተማሪዎቻቸው ጉልበታቸውን እየሳሙ የዕለቱን
ትምህርት ለመጀመር በየመሥመራቸው ተሰለፉ ። አሉላ ግን
እንደ ቀፈፈው ነበር ። የየኔታን ጉልበትም እንደ ጓደኞቹ ተሻምቶ
አልተሳለመም ። ከጠፍርና ዕንጨት በተሠራው ወንበራቸው ላይ
ከተቀመጡ በኋላ ፡ ቀስ ብሎ ጉልበታቸውን በአገጩ ነካ አድርጎ
ተመለሰ ። ተማሪዎቹ በየገበታቸው ከተከፋፈሉ በኋላ ትም
ሀርቱ ተጀመረ ። ፊደል ፡ አቡጊዳ ፡ መልእክተ ዮሐንስ ፡ የወን
ጌል ቁጥር ፡ ውርድ ንባብ ፡ ሙሉ ንባብ ፡ መዝሙረ ዳዊት
ተጀመረ ። መምህር ወልደ ጊዮርጊስም «ውዳሴ አምላክ» የተባ
ለውን መጽሐፍ መመልከት ጀመሩ ። የተማሪዎቹ ጩኸት የአካባ
ቢውን ጸጥታ አተራመሰው ። አሉላም ውርድ ንባቡን ቀጠለ ።
ፊደል ቆጥሮ ለመጨረስ ሦስት ዓመታት ያህል ፈጅቶበታል ። ታዲያ
የዝቂሊ ሚካኤል ዲያቆናትና ቀሳውስት «የትዱስ ያሬድ ተከታይ»
እያሉ ይቀልዱበት ነበር ። መምህር ግን «አይዞህ ታላቁ ሊቅ ቅዱስ
ያሬድም ቢሆን ፊደል ቆጥሮ ለማጥናት ሰባት ዓመት ፈጅቶበታል
ይባላል» እያሉ ያጽናኑት ነበር ። «ለምን ተኩስህ ሳትከ» ብለው
አባቱ እንግዳ ቁቢ ከትምህርት ቤት ሲመለስ በአናቱ ላይ የሚያ
ወርዱበት ኩርኩም «መጣሁብህ» እያለ ያስጨንቀዋል ። በዚያ
ላይ እያለ ደግሞ ፡

«የኔታ ቅድምኮ አሉላ ወንበር አልተሳለመም» ብሎ ባል
ንጀራው ሐጐስ ክስ አቀረበበት ፤ ከመምህሩ ፊት ተገትሮ ። መም
ሀር ግን መልስ አልሰጡትም ፤ ከመጽሐፋቸው ጋር ጨዋታው
ጥሟቸዋል ።

«የኔታ ፤ አሉላኮ ወንበር አልተሳለመም» አለ ሐጐስ ደገ
መና ። መምህርም ቀልጥፎ መልስ የመስጠት ልማድ አል
ነበራቸውምና ፡ እርሱም ይህንኑ ስለሚያውቅ ደግሞ አቤት አለ።

«ወጅድ» ብለው መምህር ንባባቸውን ቀጠሉ ። ሐጐስ
አንገቱን ደፍቶ መለስ ሲል ፡ ሌላዉ የንባብ ተማሪ ሲሮጥ
ተተካና ፡

«የኔታ ትላንትና ከመንገድ ጠብቆ አሉላ ደብድቦኛል ።
ዛሬም ወንበር አልተሳለመምና ይጠይቁልኝ» ብሎ አመለከተ ።

መምህርና መጽሐፋቸው ግን ከዚህ ከግዞት ዓለም ርቀው ሚልተ ብለው ወደ ረቂቁና ሩቁ ዓለም በመንዝ ላይ ነበሩና፤ ለጥያቄ ቸውም ከሳሽ ፈተነው መልስ አላለጡም።

«የኔታ ትላንትና እሱላ ደብድቦኝ ዛሬም . . . »

"«ወጅድልኝ' አላልኩም!» አሉ መምህር ቆጣ ብለው። እሱን ያላስገረፉት ተማሪዎች እያዩቀንቁ ትምህርታቸውን፤ መምህርም የሰተኛ አሳቦች እንዳይጠጋቸው ግንባራቸውን አስቆ ጥተው ንባባዊ ምርመራቸውን ቀጠሉ። መምህር ወልደ ጊዮርጊስ ከውሳሴ እምሳከ ንባብ መለስ የሚሉበት ጊዜ ግኖ ነው። እርሱ ስልችት ሲላቸው ከአጠገባቸው ከሚገኘው መደርደሪያ ላይ ያስቀምጡና ትምህርታዊ ጥያቄ ከመጣ መልስ ሰጥተው ወደ ንባባቸው ይመለሳሉ። ውሳሴ እምሳከ ሲሰለቻቸው እር ጋኖን፤ እርሱም ሲጠጥርባቸው ፍትሐ ነገሥት፤ እርሱም ዘዝ ሲልባቸው ሃይማኖተ አበው ማገላበጥ የየዕለቱ ጥና ጥና ተግባራቸው ነው።

የዕለቱ ትምህርትና ንባብ ተግባራ ዕረፍት ሲጀመር ከሰች እያምጠው፤ ምስክር አስቀጥረው እውነት ከሆነ ወንበራቸውን ያልተሰለመውን እምቢት ኩርኩም፤ ጓደኛውን የመታውን እም ሰት አለንጋ ይፈርዳሉ። ክሱ በምስክር ካልተረጋገጠ ደግሞ ከሳሹ እጥፍ ቅጣት ይከናነባል። የመምህር ወልደጊዮርጊስ ትምህርትና ቅጣት ጠበቅ ያለ በመሆኑ የሰበካው ልጆች በሩቅ ይሸሹታል።

እሱላ፤ ዕለቱ ያመጣበትን ጣጣ እያምሰለሰለ ከመምህር ለበቅና የጆሮ ቁንጥጫ ወደ አባቱ ኩርኩም የሚሸጋገርባቸው ምክንያቶች ከፊት ለፊቱ ተደቅነው ብልጭ ድርግም በሚሉበት በዓተ-ፍጥነት የዕረፍቱ ሰዓት ተነገረና ተማሪዎቹ ጠብቶ እንደ ጠገበ አንበሳ እየዘለሉ ተበታተኑ።

ወዲያው ከሳሾች ከመምህር ፊት ከበቡ። የእሱላ ከሳ ሾችም እሉበት፤ መምህር ገና የቀደመ ከሳሾችን ቃል እዳም ጠው ሳያበቁ፤ አንድ አዛውንት ወደ ችሎቱ ሲገሠግሱ መምህር በሩቅ ተመለከቷቸውና ወደ እርሳቸው ሔደው ተቀበሏ



ቸው። በቅሎቀ ጥንዝ ሥር በተዘጋጀው ትምህርት ቤት ከተደ ረደሩት የድንጋይ መቀመጫዎች ሻል ባለው መቀመጫ ላይ እንግዳቸውን ከስቀመጡ በኋላ፤ «ምነው በደኅና መጡ?» አሉ መምህር።

አዛውንቱ ከነበሩበት ድንጋይ ሲነሡ መምህር እጃቸውን ይዘው ወደታች እየጐተቱዋቸው፤

«አይነሣም ምነው እርስዎን ያህል ሰው ይነሣል!» ብለው አስቀመጡዋቸው።

እኒያን አዛውንት እሱላም አይቷቸዋል፤ ገና ብቅ ሲሉ በደ ጎናቸው እንዳልሆነ ተረድቶታል። መምህር ተቀብለው ከአጠ ገባቸው ሲያስቀምጧቸው ደግሞ ሊፈረጥጥም ከጅሎት ነበር። ከአንደበታቸው የሚወጡት ቃላት ተራ—በተራ እየተወረወሩ እንደሚለበልቡት ተገንዝቦታል። አዛውንቱ በቀበሌው የታወቁ ናቸው።

«መቼም ከሳሽ ነኝ ብዬ ነዋ!» አሉ እኒያ አዛውንት ተደ ላድለው እንደ ተቀመጡ በሚላው ሲሾሹ ከነበሩት ልጆች መካከል በመምህር አለንጋ ሊያስመነድሩት ያሉትን ልጅ በዐይነ ሕሊናቸው ጭምር እየፈለጉ።

«ምነው ምን አጋጠመዎ!» አሉ መምህር ለቅጠኛ እንደ ገለት ብለው። «በበቀደም አደባባይ ሆኜ በቁሎዬ ከነ ኮርቻዋ በግር ታስራ ነበርና ወንዝ ወስዶ ውኃ አጠጥቶ እንዲያመጣት የዘመድ ልጅ ለምኜ ሰጠሁት። ልጅም በቁሎዋን እየጋለበ ወደ ወንዝ ሲወርድ የእርስዎ ተማሪ የሆነ ልጅ ተምትሞ ከኮ ርቻዬ ላይ ተቀምጦ፤ እስከ ወንዙ ከሔደ በኋላ እንደገና ተቀም ጦባት እያስገረ እምጥቶ ከበው አጥር አስሩዋት ሔደ። ሳስጠ ይቅም የባሻይ እንግዳ ልጅ መሆኑን ሰማሁ።

«ምገስ ቢጠግብ እንዴት ከኛ ከአባቶቹ ኮርቻ ላይ ይተመጣል! ዛሬ የኛን በቁሎ ከተፈረረ ነገ ደግሞ የእናንተን የትልልቆቹን ወንበር መመኘቱ አይቀርም። ከዛሬ እንዲቀጡ ያስፈልጋል። ለአባቱ ከመንገር የእርስዎ ቅጣትና ተግሣጽ ይር

ሙ ይሆናል ብዬ ነው» አሉ አዛውንቱ ከወገባቸው በላይ ጭምር እየተናገሩ ።

መምህር ወልደጊዮርጊስ ፡ ትክዝ ብለው እንደ ቆላ ቅል የተንጨጠጠ ጭንቅላቸውን የተሸከመ ሰልካካ አንገታቸውን ወዲያና ወዲህ ሲያላጉት ቆይተው ፡ «ልጆች መማታቱ ፡ ለዲያቆናት አልታዘዝም ማለቱ ፡ የኔን ወንበር ያልመሳሙ መንገደኛ ማስቸገሩ አነሰውና ደግሞ ብሎ ብሎ በቁሉ ከነኮርቻዋ ለመቀማት ጀመረ? ጉድ ነው! ተሰምቶ የማይታወቅ ጉድ ነው! ወይ ጥጋብ ሆዬ! ግዴለዎትም አይቀጡ ቅጣት ነው የምቀጣው! እንኳን የነገሩኝ እግዚአብሔር ይባርክዎ!» ብለው ከወንበራቸው ተነሡና አንዱን ተማሪ ጠቅሰው አሉላን እንዲጠራላቸው አዘዙት ።

«ቶሎ ቶሎ አትመጣም ?» አሉና መምህር ፤ አሉላን በጭራቸው ጭምር ጠሩት ፡ ጆሮውን ይዘው ለማፍተልተል የመቸኰላቸውን ያህል የአሉላ ቀበታ አናደዳቸው ። ከሳሹን አዛውንት መምህሩንና ጓደኞቹን ቁራ በተራ እየተመለከተ ለመምህር ችኮላ ደንታ ሳይሰጠው እንደ ተጀነነ ቀረበ ። በጡዋት ሦስት ጥይቶች ያጣነበት ሦስት ከላቾችም የመረቀለት መናጢ ዕለት ደግሞ ለአለንጋና ለኩርኩም አሳልፎ ሊሰጠው ሆነ ። በጭራቸው መያዣ ደጋግመው ራስ ራሱን ወቀሩለት ፤ አልጠቀማቸውም ጆሮውን ይዘው አፍተለተሉት ፤ ይህም አንጀታቸውን አላራሰውም ። «አለንጋዬን አምጣ» ብለው አዘዙ መምህር ። አስንኳውም ሩቅ አልነበረም ። ብቻ ግን መምህር ልማዳቸው ነው ብዙ ጊዜ በገራ እጃቸው የያዙትን ጭራም ቢሆን «አምጣ» ብለው ይፎገላሉ ፤ በዚያች ሰንትም ቢሆን አለንጋቸው ከወንበራቸው ሥር ከተለመደ ቦታው ነው የነበረ ።

አሉላ ፡ ማልቀስ ቀርቶ ደንገጥ አላለም ። ከንፈሩን ነክሶ ዐይኖቹን አፍጥጦ ከከሳሹ አዛውንት ላይ አፈጠጠ ። የበቀል ስንዝርሽ እንደሚጠብቃቸው የአመለካከቱ ሁኔታ አስረዳቸው ። ከኮርቻቸው ላይ የተቀመጠውን ቂጡን በአለንጋ ቢያስለበልቡት እየወደዱ ፤ በአንድ በኩል ደግሞ ውሉ አድሮ የሚከተላቸው በቀል አሳስባቸውና ወደ መምህር ጠጋ ብለው ፡



«የዛሬን ይማሩልኝ የኔታ ለኔ ብለው ይማሩልኝ፤ ሁለተኛ እንዳይለምደው ግን ወንበርዎን መትቶ አለንጋዎን ጥሶ ይጥራልኝ» አሉና የከሳሽ አማላጅ ሆኑ ።

«የኔ ወንበር የሚዳኘው ፡ የኔ አለንጋ የሚያስደነግጠው ፡ የኔ ቁጣ የሚመልሰው መች ሆነ? ልቡ አብጦ የለም? ሙያ መስሎት ጥይት ሲተኩስ ነው የሚውል ። ጥፋቱ የእርሱም አይደል የዘመዶቹ ነው ። ፈረስ መጋለብ አልቅት ይመስል ውሃ ማንቦጫረቅ ነው ሙያው አይቀጡት! እኔ ቀጥቼ አስተምሬ ለቤተ-እግዚአብሔር አገልጋይ የምመኘውን ልጅ ይሸውና ሊያስኮበልሉት ነው ። ተዉ ብልም ሰሚ አጣሁ!» አሉና መምህር ጆሮውን ለቀው ራሱን ያሻሹት ጀመር ።

«ግዴለም እያደር ይመከራል ፤ የዛሬን ብቻ ለኔ ሲሉ ይማሩልኝ ፡ ደግሞስ የሰውን ዕድል ማን ያውቃል? በተኳሽነቱም ማለፊያ ጀግና ይሆን ይሆናል» አሉ አዛውንቱ ፤ 'የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ ፡ የሚያድግ ልጅ አይምታህ' በሚለው ምሳሌ መሸነፋቸውን እያምበለበሉ ።

«እንደ ቃልዎ ይሁን ፡ ከቃልዎ አላልፍም ፤ የዛሬን ለእርስዎ ስል ምሬልዎታለሁ ፡ ቢሆንም ጥስ ሳስጠራ አልቀውም» አሉና አንደገና ጆሮውን ይዘው እያፍተለተሉ ፡ «ሁለተኛ አይለምደኝም ፡ የየኔታ አለንጋ ትጥሰኝ በል» አሉና መምህር እስምለው ሲለቁት ፡ አሉላ ጉልበታቸውን ስሞ ሊመለስ ሲል «በል ደንጋይ ይዘህ ማሩኝ በል» ብለው የከሳሹን አዛውንትም ጉልበት እንዲስም መምህር አዘዙት ። አሉላ ከተኮለኮሉት ደንጋዮች አንዱን አንሥቶ ከአዛውንቱ ፊት ሲንበረከክ ፡ «ልብ ይስጥህ ልጄ ይባርክህ» አሉና አዛውንቱም ጉልበታቸውን ስሞ ቀና ሲል ቀበል አድርገው ጉንጮቹን ሳሙት ።

ምንም እንኳን እንግዳ ቁቢ ልጃቸውን አሉላን እየቀጡ እንዲያስተምሩላቸው መምህር ወልደ ጊዮርጊስን አደራ ቢሉዋቸውም ፡ በአሉላ ላይ የሚለበልብ ቅጣት ለመጣል የመምህር ሆድ ቆራጥ አልነበረም ። የፈደል እግርና እጅ ለመስበር የፈጀበት ጊዜ ከያሬድ ጋር ቢያነጻጽረውም ትሉ ፡ በንቁነቱና ተልጣፊ

«ግዴለም ፤ እንኳን የሰማሁት እንጂ ለወደፊቱማ አባቱ የሚያደርጉትን ያደርጋሉ» ብለው ወይዘሮ ገረዳ አሉላን እንደማይመቱት ለሴቶቹ ቃል ገብተው ሸኙዋቸው ።

«እስቲ ና አንተ አሉላ» አሉ ወይዘሮ ገረዳ እቤታቸው እንደ ተመለሱ ። ቂጣውንና ወተቱን በሽክና ይዞ ከጓዳው እንደ ወጣ «እደይ እኔኮ አይደለሁም ጥፋተኛው ፤ የሥላሴን እንስራ የሰበረችው ዐውቄ አይደለም ። ልጆች ጠብቀው ወረወሩብኝ ፤ እኔም ስወረውርባቸው ነው እንስራዋን የመታሁት ። የአደይ ኪሮስም ልጅ እየሰደበኝ ስችለው ስችለው ትላንትና ማታ ደግሞ ከመንገድ ጠብቆ ድንጋይ ወረወረብኝ ፤ ሩጬ ይዤ ገርፌዋለሁ ። ታዲያ ሸሽቼ ልመጣልሽ ነው? እኔ ፈሪ እንድሆን ነው የምትመኚው? ሸሽቼ ስገባ አባይ ቢሰማስ? ከለበቁ ታድኝኛለሽ?» አላቸው ።

«በል ሁለተኛ እንዳይለመድህ» ብለው ወደ ጓዳቸው ሲገቡ ሲሉ ደግሞ ፥ «ተመትተህና ሸሽተህስ እንዳትመጣ» ብለው ሲያጉረመርሙ ፤ «እሺ አደይ ሸሽቼና ተመትቼ እቤት አልገባም» አለ አሉላ ።

ቂጣውን በወተቱ እያወራረደ ጨራርሶ ሲወጣ ከበሩ ሲደርስ ወይዘሮ ገረዳ እንደገና ከጓዳቸው ወጡና ፥ «እንጀራ ይዘህልኝ ወደ ሥርጉ ቤት እንሔዳለንና እንዳትጠፋ» አሉት ። «የኔታን እጅበን ነው የምንሔደው እንድትመጣ ብለውናል» አለ አሉላ ለመሮጥ እያገረገረ ።

«ደግሞ እዚያ ሔደህ እንዳትደባደብ ነግሬያለሁ ፤ ወንድምህም እዚያው ሒዶአል» አሉ እናት ወደ ጓዳቸው እየገቡ ።

«ከነኩኝ መቼም እያለቀስኩ አልመጣም» አለና ሮጠ ።

መምህር ወ/ጊዮርጊስ ምርጥ ምርጥ ተማሪዎቻቸውን አስከትለው ከሥርጉ ዳስ በር ሲደርሱ የቤት ልጃቸውን አበባና ፍ[...] ለማዩት ወዳጅ ዘመድ ጠርተው ከወዲያወዲህ ሲዋከቡ የ[...] በሩት ፥ ገራዝማች ገረንኪኤል በአክብሮት ተቀብለው በተለ[...] ወደ አዘጋጁት መቀመጫ ወሰዷቸው ። መምህር በተዘጋጀ[...]ላቸው ወንበር እንደ ተቀመጡ ተማሪዎቻቸውም በስተኋላቸው በግራ ቀኝ መሥመር ተሰለፉ ።



ወይዘሮ ገረዳ ከነበሩበት አውራጃ ሆነው ከመምህር በስተኋላ የነበሩትን ተማሪዎች ሲመለከቱ ፥ ጠይም መልከ ስልክክ ቀጭን ፥ ረጅም ልጅ ከዐይናቸው አልገባ አላቸው «ከየኔታ ጋር ወደ ሠርጉ ቤት እሔዳለሁ » ያለኝ «እንጀራ ላለመሸከም ብሎ ነው? ወይስ የኔታ አስቀርተውት ይሆን? » እያሉ ሲያወጡ ሲያወርዱ በነበረበት ወቅት ምስለኔው በርከት ባሉ ባለብረቶች ታጅበው ገቡ ። ባሻይ ፈንጃም ስናድራቸውን ከነዝናራቸው አሉላን አስይዘው ወደ ዳሱ ሲገቡ ወይዘሮ ገረዳ ትኩር ብለው ሲመለከቱ ቆዩና የግራ እጃቸውን መዳፍ ከጉንጫቸው ላይ ለጥፈው ልጃቸው የያዘውን ስናድር ከእንግቱና ከባሻይ ጋር እያወዳደሩ ሲመለከቱ ቆዩና አንገታቸውን ደፉ ።

ከእርሳቸውና ከመምህርም ትእዛዝ ማፈንገጡን ተረዱት ። ሙሽራው ገብቶ ፥ ምግቡ ተበልቶ ጠጁና ጠላው በገፍ መውረድ ጀመረ ። ሚዜዎቹ ተራ በተራ እያቅራሩና እየፎከሩ በዳሱ ውስጥ በነበረው ዕድምተኛ መካከል ወዲያና ወዲህ እየተወራጩ ዐይኑ ሕሊናውን ሲሰቅሉት ሲያወርዱ ቆዩና እንደገና ወደ ሙሽራው ሲመለሱ እርሱም ረጅም ስናድሩን አጽምጦ ይዞ በብር የተሸቆጠቆጠ ካባ—ቀሚሱን ወርወር እየተወራጨ ወረደና ፉከራውን ሲያሽጎደጉደው ዕልልታው ተለጠ ። ቀጥሎም ከሁለቱም ሙሽሮች በኩል ወኔያቸው ያስፎገላቸው አዛውንት ተራ በተራ እየተነሡ እንደተደቁት ። ባሻይ ፈንጃም ስናድራቸውን ከአሉላ ተቀብለው ፎከረው ሲመለሱ ፥ አሉላ ስናድሩን ከእጃቸው ነጥቆ ተንደርድሮ ከዳሱ መካከል ገባና ፥

«ሩቅ ተመልካች አነጣጣሪ ፥
እንደ ቆላ አባብ ተወርዋሪ
ሩቅ ተመልካች ሩቅ አዳሪ
የጀግና ልጅ ጀግኖች አኩሪ»

ብሎ ፎከረና ፥ ስናድሩን አቋርጦ ይዞ ከዳሱ ወጣ ። ወይዘሮ ገረዳም ተከታትለውት ወጡ ። ዐሐይ በማዘቅዘቅ ላይ ስለነበረች ፥ አሉላን ይዛ የምትጠልቅባቸው የመሰላቸው ፤ እናቱ ቢፈልጉት ቢጠሩት የውሃ ሽታ ሆነባቸው ። «እንግዲህ ይህ ልጅ በቃው ፥ ትምህርት የሚሉ ነገር በቃው ፥ ዳዊቱን

እንኳ ደጋግሞ ሳይወጣው ማጿረጡ ነው ። ለማዕረገ-ቅስና ቀርቶ ለዲቁናም ሳይበቃ መቅረቱ ነው» ብለው መምህርም ከአጠገባቸው ለነበሩ ተሳውስት ያደረባቸውን ሥጋት እሚወቱዋቸው። «ትምህርት በልጅነት ነበር እንጂ ፤ ካረጀ ካፈጀ በኋላ መች ይሆናል?ያስጀመሩትኮ ካረጀ በኋላ ነው ፤ ታዲያ ይኸ ልጅ ጠመንጃ አንግቶ ቢነሣና ቢፎክር ምን ያስደንቃል?» አሉ ወዳጃቸውም።

«እሱስ እውነት ነው ፤ አንድ ጊዜ ካጉቱ አንድ ጊዜ ከአያቱ ቤት እየዘለለ ኑሮ ነው ጊዜው ያለፈበት ። አሁንም እንደ ሆነ ቢቻል ቢቻል እንዲያው ለዳዊት ደገመውስ እንኳ ቢበቃልኝ በወደድኩ ነበር ። ታልሆነም መቼስ ምን ይደረጋል? ማለፊያ ወታደር እንዲሆን ወደ አንዱ ጌታ ቤት ማስጠጋት ይሻላል እንጂ ።’’ አሉ መምህር የወጣቱ አሉላ የወደፊት ዕድል አሳስቧቸው ።

የአሉላ ፉከራ በዳሱ ውስጥ ሹክሹክታና ጉርምርምታ ፈጥሩዋል ።

«የማነው ልጅ?»

«የእንግዳ ቁቢ ።»

«እረግ እረግ እርሱ ነው? ለካ ይህን ያህልም ልጅ አለውና? እንግዳ ቁቢምኮ ጀግና ነው ። ተኩሱንም እርሻውንም አሳምሮ ያውቅበታል ፤ ከወለዱ አይቀር እንደዚህ ነው» እየተባለ ጨዋታው በደራበት ሰዓት ደግሞ በሩቅ ሦስት ጥይቶች ተከታትለው ተተኮሱ ። በዳሱም ውስጥ ትርምስ ሆነ ። ወዲያው ባሻይና ሌሎች ሰዎች ከየነበሩበት እየተደናገጡ ተነሥተው ተከታትለው ወጡ ። ባሻይ ፍንጃል ከሁሉም በተለየ ስሜት ተሸብረው ወደ ቤታቸው ሮጡ ፤ ከቤታቸው እንደ ገቡም ጠመንጃቸውን ከመደቡ በስተራስጌ ተሰቅሎ አገኙት ። አውርደው በአፈሙዙ በኩል አሸተቱትና ከቤት የነበረችውን የባለቤታቸውን ትንሽ እኅት ጠርተው ፣ «ጠመንጃውን ማነው ያመጣው?» ብለው ጠየቋት ።

«አሉላ ነው ለቅሎት የሔደ» አለች ። «ወዴት ሔደ?» «ዝምብሎ ነው የሔደ አልተናገረም ።» «ነፍስ አልፎበት ይሆን?



ተኩሶበታል እርሳሱ ይሸታል» አሉና ከቤታቸው ወጥተው ወደ እንግዳ ቁቢ ቤት ሔዱ ። በሁለቱ ቤቶች መካከል ያለው ርቀት ሁለት ምዕራፍ ቢሆን ነው ። ገና ከመንገድ ላይ እንዳሉ አሉላ በሩቅ አይቷቸው ኑሮ እየሮጠ ሔደና ከፊታቸው በልበሙሉነት ኮስተር ብሎ ቆሞ

«አቦይ ያን ነጭ የበሬ ግንባርኮ አከታትዬ በሦስት ጥይት መታሁት » አላቸው ። «ማን ይመሰክርልሃል? ጡዋት ስተኸው የለም?»

«ሚካኤልን ! እንግዳ ይሙት ! መትቼዋለሁ ። ካላመንከኝ አጥንቱን ሳሳይህ» ብሎ እየሮጠ ሔደና ዒላማውን ወስዶ አሳያቸው ። በእርግጥም በሦስት ጥይት ተበሳስቷል ። ባሻይ ፍንጃልም ፈገግ አሉና የአሉላን ራስ በጉጉት እየዳበሱ ፣

«እደግ ተባረክ ! በል ከእንግዲህ ወዲያ ተኩሰህ እንዳትስት ተጠንቀቅ» ብለው ወደ ዳሱ ተመልሰው ዜናውን አበሠሩ ። ከዚያ በኋላ በዳሱ ውስጥ የአሉላ ፉከራና ተኳሽነት የጨዋታ መጀመሪያና መደምደሚያ ሆኖ አመሸ ።

መምህር ወልደ ጊዮርጊስ እንደ ፈሩትም አሉላና ትምህርት እየተራራቁ ሔዱ ። እርሱም ጠመንጃ እያነገበ ወደ አደንና ወደ እርሻ አዘነበለ ። እያደገም በሔደ መጠን ከነጋዴዎች ጋር ወደ አክሱም ዐዱዋና መቀሌ መመላለስ አዘወተረ ።

አሉላ ፣ በአካልና በአእምሮ እየመጠቀ ሔዶ ከመንደሩም እየወጣ ወደ ከተማዎች መመላለስ ከመጀመሩ በፊት የመንደሩን ልጆች እየሰበሰበ ከመንደሩ አልፍ ብሎ በሚገኘው በገባ ወንዝ ቁብታ ላይ እየወጣ ፣

‘እኔ ፊታውራሪ ነኝ ፣ አንተን እንተን ፣ አንተን ቀኛዝማች`፣ አንተን ደግሞ ግራዝማች ብያችኋለሁ’ እያለ መሾም ማዋጋትና ማጊነት ይወድ ነበር ። ከዚያ ሌላ ደግሞ በቁርቁፍ ጨዋታና በውሃ ዋና ከመንደሩ ልጆች አውራ ነበር ።

ከዕለታት አንድ ቀን ከጓደኞቹ ጋር ሆኖ በገባ ወንዝ ሲጫወት ፣ ሴቶች ሞሰብ ሞሰብ ተሸክመው ጠላ በገንቦዎች እዝ

ሰው ወደ ሥርግ ቤት ሲሔዱ አሉላ ተጣራና ፡ «ይህን ሁሉ ድግስ የምትወስዱት ለማን ነው?» ብሎ ጠየቀ ። ከተሸከሙት ሴቶችም አንዷዋ ቆም ብላ የለበጣ ሣቅ እያሳየችው ፣

«ባራስ አሉላ ሰወዲ-ቁቢ ልንሰጥ ወደ ሠፈራቸው እየሔድን ነዋ?» አለችው ። አሉላም ነገሩዋን ቀበል አደረገና ፣

«እንተበኺ ኦ» አላት ።

መምህር ወልደ ጊዮርጊስ አሉላን አስተምረው ለማዕረገ ዲቁናና ቅስና ለማብቃት የነበራቸውም ምኞት እየከሰመ ሔደ።

«ከተማ ከለመደማ በቃው ለይቶለታል ፣ ከእንግዲህ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ አልሆነም ። ከእንግዲህ ወዲያ እኔም አል ደክምም ፣ ከውትድርናው ላይ ጠበቅ እንዲል ማድረጉ ነው የሚሻለው » እያሉ በእነባሻይ ፍንጃል ላይ የነበራቸውን ቅሬታ ማስማት አዘወተሩ ።

እንግዲህ ቁቢም ቀድሞውንም ቢሆን ወደ ውትድርናው እንጂ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ እንዲያተኩርባቸው ምኞት አልነበራቸውምና ፣

«ቀለሙ እምቢ ካለው ይተወው ፣ ድብትርና ምኑ ነው? እኔ ገበሬና ወታደር ! አባቴም ዘመዶቼም እንደኔው ገበሬዎችና ወታደሮች ናቸው ! ልጄም የኔን ጋሻ ነው መከተል ያለበት ። እንደ ዕቁበ ሚካኤል እንዲሆንልኝ ነው የምወደው » ማለት አዘውትረው ነበርና አሉላ ዳዊት እንኳ ሳይደርስ ትምህርቱን ተሰናበተው ።

አባቱ እንግዳ ቁቢ ከመረብ ወንዝ ማዶና ማዶ ከነበሩትና በዘመናቸውም ከሚያውቋቸው ጀግኖች ዕቁበ ሚካኤል ጠቋሬን በጣም ያደንቁት ነበር ። በጥንቱ ዘመን የቱርክ ጦር ከምፅዋ ተነሥቶ ሕዝብ እየፈጀ ንብረት እየዘረፈ ድባርዋ ከምትባለው መረብ ምላሽ ውስጥ ከምትገኝ ጥንታዊት ከተማ ደረሰ ። በዚህ ጊዜ የወገናቹ መዋረድና የመንደሩ መደፈር በጣም ያስቆጣው ዕቁበ ሚካኤል ጠቋሬ የተባለ ጀግና የመንደሩን ጀግኖች ሰብስቦ ስግ ሆ ራሱን ሁኖ ድባሩዋ ውስጥ መኖር የነበረውን የቱርክ ጦር



በሽምቅ ውጊያ ገጠመውና ፈጀው ። ከዚያ ጦርነት የተረፈውም የቱርክ ጦር ከድባሩዋ የፈረጠጠ ምፅዋ ገባ ። ዕቁበሚካኤልና ጀግኖቹም ቱርክን ድል ነሥተው የማረኩትን መሣሪያ ተሸ ሩፍለው አገራቸውን መጠበቅ ጀመሩ ።

ታዲያ እንግዳ ቁቢም የዚያ ጀግና ዝና በተነሣ ቁጥር ከል ጃቻቸው አንዱ ስመ — ጥር ጀግና እንዲሆንላቸው ይመኙ ስለ ነበር ፣ ልጃቻቸውን ከልጅነታቸው ጀምረው ተኩስ ማስተማር ይወዱ ነበር ።

እዎ አሉላም አነጣጥር ተኳሽ ሆነላቸው ፣ በዚህም ሙያው ነበር በጉልማሳነት ዘመኑ በባልገዳ አርአያ ድምፁ ቤት እጅግ ተወዳጅ ባለሟል ለመሆን የበቃው ።

# ትኩር ድምጥ

የአጼ ቴዎድሮስ እስረኛ ሁነው ጐንደር ይቀመጡ የነበሩ
ባልገዳ እርአያ ድምፁ እንግሊዞች ጐንደር እንደ ገቡ ሌሎቹን
እሥረኞች ሲፈቱ እርሳቸውም ነጻ ወጥተው ትግራይ ገብተ
ተንቤንን መግዛት እንደ ጀመሩ በወታደሮቻቸው ታጅበው በ
አውራጃው ሲዘዋወሩ ጐበዛዝቱ ሁሉ እየተከተለ አሽከርነ
ይገባላቸው ጀመር ። እርሳቸውም ዳግመኛ የቴዎድሮስም ሆ
የሌላ ጉልበተኛ ተግራኪ ላለመሆን ሲሉ የተከታዮቻቸው
ቁጥር ማብዛትና ምርጥ ምርጥ መሣሪያ መግዛት የወቅቱ ም
ኞቻቸው ሆነ ። ቢሆንም የሚገባላቸውን ተከታይም ከየት እን
መጣ የማን ልጅና የነማን ወገን እንደሆነ ማጣራቱም ተ
ዳሚ ተግባራቸው ነበር ። ይህ ጉዳይ ደግሞ ይበልጥ እያ
ናከራቸው ሔደ ።

የእርሳቸው ተከታይና አሽከር ለመሆን የሚመኙ ሁ
የእነማን ልጆችና የእነማን ወገኖች መሆናቸውን እያሳወ
ስለሚገቡ ፣ የወታደሮቻቸው ጥራትና ቁርጠኝነትም የሚተማመ
በት እየሆነላቸው ሔደ ።

እርአያ ድምፁ የትግራይን መንደሮች እየተዘዋወሩ በ
ሬጋጋትና መተያየም በመቀበል የአሽከሮቻቸውን ብዛት ብ
ሳይሆን እስባበስና ትጥቅም ማሳመር በመቻላቸው ለአሽከርነ
የሚቋምጠው ኮበሌ ብዛት ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ ሔ
ባልገዳ እርአያ ተንቤን ገብተው በሰነበቱባቸው ሰሞና
ወጣቱ አሉላም ከጓደኞቹ ጋር ተስማምቶ የእርአያ ድም
አሽከር ለመሆን ቆረጠ ።

ሐሳቡን ለአባቱ ቢነግር እንደሚስማሙለት ያውቃል
እናቱ ግን የመምህር ወልደ ጊዮርጊስን ሐሳብ የሚደግፉ መ



ናቸውን ስለሚያውቅ «ወታደር ልሆን ነኝ ቢላቸው ቢችሉ ይዘው በቡጢ ለመውቃት ያላዚያም የስድብና የእርግማን ነጐድጓድ እንደሚያወርዱበት ያውቃል ። ስለዚህ ለእናቱ ለአባቱም ሆነ ለእኅቶቹና ወንድሞቹ መናገሩን አልወደደውም ።

እንግዳ ቁቢ ከሦስቱ ወንዶችና ከሁለቱ ሴቶች ልጆቻቸው ይልቅ አሉላን ያቀርቡታል ። በንቃቱና በተኳሽነቱም ብዙ ጊዜ እየሳሙ ፍየሉችና በቅሉ ሸልመውታል ። ወታደር ሆኖ የእርሳቸውንና የዘመዶቻቸውን ጋሻና ጦር እንዲያነግ ከመመኘታቸው የተነሣ ሌላው ቀርቶ «ገብረ ሚካኤል» ተብሎ ለአሉላ የወጣለት የክርስትና ስም እንኳ «ወልደ ገብርኤል» ተብሉ እንዲለወጥ ከመምህር ወልደ ጊዮርጊስ ጋር ብዙ ጊዜ ተጨቃጭቀዋል ።

ምክንያታቸውንም ለመምህር ሲያስረዱ ፣

«ሚካኤል ገራገር ለስላሳ ነው ። ገብርኤል ግን ቁጡ ቀልጣፋ ነው ! እኔም ልጄ አሉላ ቁጡ ኮስታራና ቀልጣፋ እንዲሆን ነው የምመኝለት» እያሉ ነበር አንዳንድ ጊዜም «መብረቁ እሳቱ» እያሉ ያቆላድሱት ነበር ።

ወጣቱ አሉላ ፣ ወደ ባልገዳ እርአያ ሠፈር እየሔደ ባለሟሎችን ደጅ መጥናት ጀመረ ።

«አሽከርነት ፈልጌ ነው» እያለ ለባልገዳ እርአያ አሽከሮችና ባለሟሎች ነገር ወደ እርአያ ድምፁ ቀረበና የማን ልጅ መሆኑን አስረዳ ።

«ሲሆን ሲሆን ራሱ አባትህ አምጥቶ አሳድግልኝ ሥርዓት አስተምርልኝ ብሎ ይሰጠኝ ነበር ። አንተ ልጁ ለዚህ ወግ ደርሰህ መጥተህ ስትጠይቀኝ ደግሞ በደስታ እቀበልሃለሁ እንጂ ምን ከፋቶኝ ?» ብለው ባልገዳ እርአያም አሉላን ተቀበሉትና የቤት አሽከርነቱን ፈቀዱለት ። በዚያ ጊዜና በዚያም ቤት ነበር አሉላ በሕይወት ታሪኩ ውስጥ ደምቀውና ጐልተው ከሚታዩት ከደበበና ከአምለሱ ጋር የተገናኘው ፤ ሁለቱም የባልገዳ እርአያ ልጆች ናቸው ። በዚያን ጊዜ ደበበ የዐሥራ ስባት

ዓመት ወጣት ሲሆን ፥ ተከታዩ አምለሱ ደግሞ የዐሥራ አራት
ዓመት ጉብል ነበረች ። ለሁለቱም መምህር ተቀጥሮላቸው
በግቢያቸው ውስጥ ይማራሉ ። ምንም እንኳን አሉላ የባልገዳ
አርአያ ድምፁ አሽከር ቢሆንም ፥ እርሱ እንደ ተመኘው ምርጥ
ጠመንጃ ይዞ ተከታይ ከመሆን ደረጃ አልወጣም ።

አሽከርነቱ ለደበበና ለአምለሱ ሆነ ። የሁለቱን እግር ያቀ
ባል ፥ ሁለቱንም ይላላካል ፤ ሁለቱም ሲወጡና ሲገቡ ይከተላል ።

አርአያ ድምፁ የቆቅ የሰሰና የድኩላ ሥጋ እጅግ አድ
ብተው ይወዱ ስለነበረ ፥ ድኩላና ሰስ አድኖ ገድሎ ወይም በወ
ጥመድ ይዞ ለሚያቀርብላቸው አሽከር ልዩ ጉርሻና ሽልማት
መስጠት ያዘወትሩ ነበር ። የአውሬ ሥጋ ጥብሱንና ቋንጣው
ንም ለሌላ ተርፎ ለልጆቻቸው እንኳ «እንዳይሸታችሁ» እያሉ
ከማጉረስ በቀር እንደ ልባቸው አያስጠግቧቸውም ነበር ።

«ደበበ ተኳሽኮ ብትሆን ኖሮ ፥ የአውሬ ሥጋ ታጠግበኝ
ነበር» ብላ አምለሱ ወንድሟን አንድ ቀን ስትቀልድበት ፥ አሉላ
ሰምቷት ኖሮ ይህችኑ ሲያመሰለስል ቆይቶ ከዕለታት አንድ
ቀን ከአባቷ ቤት ወደ አክስቷ ቤት ስትሔድ ጠመንጃ ይዞ
ሲከተላት ጠጋ ብሎ ፥

«የአውሬ ሥጋ ትወጃለሽ?» ብሎ ጠየቃት ።

«ምነው ገድለህ ልታመጣልኝ ነው?» ብላ መልሳ ጠየቀ
ችው ፥ ከአሽሙራዊ አስተያየት ጋር ።

«መተኮስ አልችል መሰለሽ?»

«ተኩሰንማ ማንም ይተኩሳል አነጣጥሮ መጣሉ ነው እንጂ
የወንዶች መለያው» አለችው ።

«ለመሆኑ የምን አውሬ ሥጋ ነው የምትወጂው ?»

«ሆውም መርጠህ ነው የምታመጣልኝ ?» ብላ እንደ ገና
አሽሟጠጠችው ።

«ተኩሼ ብስትም በወጥመድ እይዛለሁ ።»



«ከሆነልህማ ቆቅና ሰስ ነው የምወደው ፤ ያበለመዱኝም
የእነርሱን ሥጋ ነው» አለችው ። ይህን ከተነጋገሩ ከሦስት ቀናት
በኋላ ከረፋዱ ላይ አሉላ ሰስ ገድሎ ልጅ አሽከሯ ወስዶ
ሰጣት ። ከዚያ በኋላ ቆቅ በወጥመድ ሰሰና ድኩላ በጥይት እያ
መረተ ማቅረቡን በመቀጠሉ አምለሱ ፥ ለአባቷ ነግራ ጠመንጃ
አሸለመችው ። ባልገዳ አርአያ የሸለሙት ጠመንጃ ደግሞ
በዘመኑ ብርቅ የነበረችው መሣሪያ ነበረች ። እርሷም ማስፈያ
ኮታ ሸለመችው ።

በተኳሽነቱና በአዳኝነቱም ብቻ ሳይሆን ፥ አሉላ ለጌታው
ቤት አሳቢ ተቆርቋሪና ታማኝ በመሆኑ ፥ በጌትየው ዘንድ እጅግ
ተወዳጅ ባለሟል ሆነ ። ቆይቶም ከልጆች አሽከርነት ደረጃ
ወጥቶ የራሳቸው የባልገዳ አርአያ አንጋች ሆነ ።

እያደርም አሉላ የጌታው ምሥጢረኛ እየሆነ በመሔዱ ፥
አምለሱ ስትደሰት ወንድሟ ደበበ በቅናት ልቡ እያበጠ ሔደ።
በየአውራጃዎችና ወረዳዎቹ እየተላከ ለጌታው አስፈላጊ የነ
በሩ ጉዳዮችን ማቀላጠፍ ጀመረ ። ሕዝቡ ለጌታው የሚያ
ቀርበውን ጉዳይና ስጦታ ይቀበላል ፥ ወደ ምፅዋም ከነጋዴዎች
ጋር እየሔደ የባሕር ማዶ ዕቃዎችን ጠመንጃና ጥይት መግ
ዛት ጀመረ ። እነዚህም ሁኔታዎች የአሉላን ዕውቀት የአስተ
ሳሰብ ኃይልና ልቀት እያሰፋለት መጣ ። በተለይም ምፅዋ
ደርሶ መርከቦችን ዐይቶ ፥ ጥቅማቸውን በመገንዘቡ ለዚያ የባሕር
ዳር ለሆነው መሬትና ክብር በሕይወቱ ሙሉ ያልቀዘቀዘ ፍቅ
ርና የጀግንነት ወኔ አደረበት ። በዚያ ዘመን ከልዩ ልዩ አገ
ሮች በቀይ ባሕር ሲተላለፉ የነበሩ የንግድ መርከቦች ወደ ምፅ
ዋእ ወደብም ጉራ እያሉ ያራግፉዋቸውና ይጭኑዋቸው የነበሩ
ሸቀጣ—ሸቀጦችና ጠመንጃዎችም ለባልገዳ አርአያ ብቻ ሳይ
ሆን ፥ ለመላዋ ኢትዮጵያ የቱን ያህል እንደሚጠቅሙና እንደሚ
ያስፈልጉ ከልቡ ለማመን የቻለባትንም ዕውቀት ቀሰመ ። በዚ
ያው ጊዜም ነበር ያን በር በጀግንነት መጠበቅ እንደሚገባ ሊገ
ነዘብም የቻለበትን አጋጣሚ ለማየት የበቃው ።

አሉላ ፥ ከዚያ ቀበሌ ከመድረሱ ከብዙ ዓመታት በፊት አበ
ቀድሞ ቱርኮች ያን አካባቢ ይዘው ፥ ወደ ደጋውም ቀበሌ እየ

ወጡ ሕዝቡን እየፈጁ ቤቱን እያቃጠሉ ፣ ንብረቱን እየዘረፉ
ሲፈጽሙት የነበረውን ግፍ ሁሉ በይበልጥ ለመረዳት የቻለ
ውም ምፅዋ ከደረሰ በኋላ ነበር ።

በዚያም ወቅት ነበር ከልጅነቱ ጀምሮ ሽማግሌዎች ሲጨ
ዋወቱ ሲያደንቁትና ሲያሞግሱት ስለነበረው ዕቁባ ሚካኤል
ጠቋሬ ስለ ተባለው ጀግና ታሪክ በይበልጥ ለመረዳትና የእር
ሱንም አርአያ ለመከተል በልቡ ቃል የገባው ።

በዚያ ዘመን የንግድ እምብርት በነበረችውና ድሆና እየተ
ባለች በምትጠራው መንደር ሠፍረው የነበሩት የቱርኮች ወኪ
ሎች ፣ ከደጋው አገር ሲሔዱ የነበሩትን ኢትዮጵያውያን ነጋዴ
ዎች እንዴት እያደረጉ ይዘርፉዋቸውና ያንገላቱዋቸው እንደ
ነበር አሉላ በሚገባ ለመረዳትና ያን ግፍ ፣ ያን የጥጋበኞች ድር
ጊት መልሶ በጉልበትና በኃይል መመከት እንደሚገባም ራሱ
ለራሱ በልቡ ማለ ።

ባልገዳ አርአያ በምፅዋ በኩል ሲደርሳቸው በነበረው
ጌጣ—ጌጥ የወግ ዕቃና በተለይም ጠመንጃና ጥይት ልባቸው
እየተማረከ በመሔዱ አሉላንም እየደጋገሙ ወደ ምፅዋ
ልከውታል ። በዚያም መልሱ ወቅት የአንገትና የእጅ ጌጦች
አንዳንድም የቤት ዕቃዎች ለአምለሱ ይወስድላት ስለነበረ ፣ ልዩ
ልዩ የሆነና ግልጽም ያልሆነ መቀራረብና መተሳሰብ በመካከ
ላቸው እየዳበረ ሔድዋል ።

አንድም ጥይት ሳያባክን አነጣጥሮ ተኩሶ የአውሬ ሥጋ
የሚያስቀርጥ ወደ ምፅዋ እየሔደ የባሕር ዕቃ ገጸ—በረከት
የሚያቀርብ የጠይም መለሎ በወንድነቱ የተማመነ የጉልማሳ
ልዩ ሥዕልና ስሜት በወጣቷዋ አምለሱ ዐይነ—ሕሊና ልበ—
ልቡና ውስጥ እየተቀረፀ ሔደ ።

በተለይም አንድ ጊዜ ከምፅዋ ሲመለስ ለባልገዳ አር
አያ ፣ ለባለቤታቸውና ለአምለሱ ከወሰደላቸው ባሕረ—መቀ
ዕቃዎች ማራኪነት ሌላ ከደብረ —ቢዘን አካባቢ የገደላቸው
ዝሆኖች ጥርስና የአንበሶች ለምድ ለዕለት ምግብ ከሚፈለ
ጉት የቆቅ የሰሱና የድኩላ ሥጋ ይበልጥ በቤተ—ሰቡና በመ



ንደሩ ልዩ ፍቅርና ሞገስ ቢያተርፍለትም ፣ በደበበ ልብና እነ
ምር ሲጤስ የነበረውን ንቀትና ጥላቻ ግን ወደ ነዲድነት
እየለወጠው ሔደ ። በዚያው ሰሞን ደበበ ከእናቱና ከእኅቱ ጋር
በእልፍኝ ውስጥ ሆነው አሉላ ከምፅዋዕ የወሰዳቸውን ልዩ
ልዩ ጌጣ—ጌጦች ሲመለከቱ ፣

«ሁሉን አሟልቶ የሰጠው ወንድ ነው» አለች አምለሱ ።

«በየትኛው ጦርነት ውሎ ነው? አውሬ መግደሉ ነው ወን
ድነቱ?» አላት ደበበ እኅቱን በጥላቻ እየተመለከተ ።

«አውሬ ለመግደልኮ አነጣጥሮ መተኮስም ያስፈልጋል ።
አሉላ'ኮ ለአንድ አውሬ ዝናር ሙሉ ጥይት አይጨርስም! አንተ
ምነው አንዲት ቆቅ እንኳ ገድለህ አታውቅ? ይልቅስ ከእርሱ ጋር
በረሃ እየሔድክ ተኩስ ብትማር ዱሩን ብታውቅ ይሻልሃል!»
አለችው በዐይናቿ ሙሉ እንኳ ለማየት ንቃው ።

ደበበ ከነበረበት ድኳ ብድግ አለና የአምለሱን ጠጉር
ሲይዝ ፣ እናትም እርሱን ጥርቅም አድርገው ያዙና ገላግለውና
ተቆጥተው ፣ «እውነቷን ነው ፣ መንደር ከመዋል ወጣ—ወጣ
ብትል ወንድ ወንድ ትሸት ነበር» ብለው አስወጡት ። ከዚያች
ዕለት በኋላ አምለሱና አሉላ በአንድ ፊት ደበበም በአንድ ፊት
ሆነው ፍጥጫው ቀጠለ ።

እንደ ተለመደው ፣ አሉላ ከዕለታት አንድ ቀን አደን ሔዶ
ውሎ ወደ ማታ አምስት ጅግራዎች ፣ ሁለት ቆቆችና አንድ
ድኩላ ገድሎ ፣ በሁለት የቤት አሽከሮች አሸክሞ ተመለሰ ።
ገና ከምድረ—ግቢው ሲገባ ደበበ ከበር ጠብቆና ፣

«አንተ የሴት ልጅ ማን ፈቅዶልህ ነው ፣ እነዚህን አሽከ
ሮቹን የወሰድካቸው?» ብሎ አፈጠጠበት ።

«እሜቴን ጠይቄ አስፈቅጃለሁ» አለ አሉላ የደበበን እኳ
ኋን ኮስተር ብሎ እየተመለከተው ።

«የሴት ልጅ! የሴት አሽከር ፣ ሴት አይደለህ? ሁል ጊዜም የም
ትነጋገረው ከሴት ጋር ነው» አለው ደበበ ፣ ከእግር እስከ ራሱ

ከፍና ዝቅ እያደረገ እየገረመመው ። "ሴትማ ከቤት ጉያ ሳይወጣ ከቤት የሚውል ነው! እኔማ ይኸውና የወንድነቱን እያበሠበሰርኩ ነው» አለ አሉላ ፈርጠም ፈርጠም ያሉትን ጡንቻዎቹን አሰቆጥቶ ።

«እኔ ነኝ ሴት፣ አንተ የሴት ልጅ!!» አለ ደበበ ለግላጋ አካሉን ለማስቆጣት ሰልካካ ፊቱን አኮስታተረ ።

«ከቤት ጉያ ከቤት እልፍኝ የማይወጣ ወንድ ሁሉ ሴት ነው» አለ አሉላ ይዞት የነበረውን ቆቅ አብሮት ለነበረው አሽከር ሰጥቶ ያነገተውን ስናድር አቅምጦ ይዞ ።

«እኮ እኔ ነኝ የሴት ልጅ!» አለ ደበበ ።

«እኔ አንተን ቀርቶ ማንንም የምሳደብ አይደለሁም» ብሎ አሉላ ፈንጠር ሲል፣ ደበበ ሩጦ ከወገቡ ላይ ሲጠመጠም አሉላ ስናድሩን ወርውሮ ዘወር አለና በሁለት እግሮቹ ቆልፎ ዘረረውና ሆዱን በአንድ እግሩ ረግጦ ዐይኖቹን አፍጥጦ ሰውነቱን ሥጋ እንዳየ አንበሳ አስቆጥቶ ሲመለከተው፣ የቤት አሽከሮች ተሩዋሩጠው ሁለቱንም ያዙዋቸው ። አሉላ የያዙትን ሰዎች ነጥቆ ስናድሩን አንሥቶ ዘወር አለ ። በምድሩ ግቢው ግርግር ሆነ ። እጋፋሪ ሰብሐት ነገሩን ሰምተው አሉላ ተይዞ እንዲታሰር አዘዙ ። እጋፋሪ እንኳንስ የባላባት እርስያ ልጅ ተደፍሮ ድቅርና የቤት እንስሳቸውን እንኳ የመጋደር ክብት ከወገባቸው «አገር ይያዝልኝ ሕዝብ ይታሰርልኝ» የሚሉ ናቸው ። በዚህም የተነሣ ከእርሳቸው የቤት እንስሳ ጋር የማንም መንደርተኛ ክብት አይጠጋም ።

አሉላም በፈቃዱ እጁን ሰጠና ከምድሩ ግቢው ጋር ተያይዞ በተሠራው እስር ቤት ተወስዶ በሰንሰለት ታሰረ ።

እምለሱ እርር ድብን ብላ ዋለች ። እጋፋሪ ሰብሐትን እጅግ ተጠየፈቻቸው፣ በመላው ተገቢን ከለው ሕዝብ ሁሉ እጅግ የከፋ አረመኔ መስለው ታዩዋት ።



«አሉላ የገደለውን ድኩላ በልተዋል፣ እንዴት በእርሱ ላይ ይጨክናሉ? ለዚህ የመንደር አውደልዳይ ሲሉ አሉላን እንዴት ያሰራሉ?» እያለች ስትጠፍ ዋለች ።

«አደይ አሉላኮ አይደለም ጥፋተኛው ደበበ ነው ለምን ጉበዝ ሆንክ? ለምን ጀግና ሆንክ? ለምን? ....» ብላ ተናግራ ሳታበቃ የእልህ እንባ ተናነቃትና ጸጥ አለች ።

«አይምሰልሽ፣ የዚያ የገበሬ ልጅ ጥጋብ ነው ። ምን ነው ጉብዝናው? አንበሳና ነብር የገደለ መሰለሽ? ድኩላና ሰሳ ማንም ይገድላል ። እንዲያውም አንቺ ነሽ ጉበዝ ጉበዝ እያልሽ ልቡን ያሳበጥሽው ። እንዴት ልጄን ደፍሮ ይነካዋል?» አሉ እናትዋ ወይዘሮ ሐጐሳ ።

እምለሱ ተስፋ አልቆረጠችም ። እናቷ የነፈጓትን ፍርድ ከአባቷ ለማግኘት እንደምትችል ተማመነችበትና፣

«ምንም እንኳን ደበበን ቢወዱትም በአሉላ አይጨክኑም» አለችና አባቷን አስተዛዝና የምትለምንበትን ስልትና ዕለት ስታምሰለሰል ቆይታ፣ ጊዜው ለዐይን መያዝ ሲጀምር በጥቦብ ፍትፍትና ጥበስ፣ በገንቦ ደግሞ ጠጅ ይዛለት ወደ እስር ቤት ሔደች ።

እስር ቤቱ ከዋናው ግቢ ጋር ተያይዞ ከውስጡ አጥር ውጭ የተሠራ ነው ። እርእያ ድምፁን፣ የሚያስቆጡ የቤት አሽከሮችና ቤተ—ዘመዶች የሚታሰሩበት ነው ። በአንድ ጊዜ እስከ ሠላሳ የሚደርሱ ሰዎች ገብተው ይታጎሩበታል ።

ምሶቧና ገንቦ ተሸክማለት የነበረችውን ሠራተኛዋን ወደ ውስጥ ልካ ጠባቂውን አስጠርታ፣ «ለአሉላ ራት ተልኮለታልና ጥራልኝ ልስጠው» አለች ።

«በእግረመቅኮ ታስሯል አይመጣም» አለ ዘበኛው ። «እንግዲያው እኔ ልግባ ዕቃውን ያዝልኝ» አለችና እምለሱ ወደ ውስጥ ገባች ።

በዕለቱ ከአሉላ ጋር ሦስት እሥረኞች ነበሩ ። በእግር ብረት የታሰረ ግን አሉላ ብቻ ነበር ፤ በጥግ በኩል ኩርምት ብሎ ተቀምጦል ። አምበሱ ቀረብ ብላ ከአንገቷ ጉንበስ ብላ ፤

«እንደ ምን ዋልክ?» አለችው ።

«እንደ ምን ዋልሽ እመቤቴ? ለምን መጣሽ?» ብሎ አሉላ ከተቀመጠበት ተነሥቶ ቆመ ። «ራትህ ተልኮልሃል» ብላ ከኋላዋ ከነበረው ጠባቂ ተቀብላ ስታቀርብለት ባንገቱ ሰጥ ብሎ እጅ ነሣና ፤

«ምነው አንች መምጣትሽ? አሽከሮች ሞልተው የለም?» አለና አንገቱን አቀረቀረ ። «እብልተሽ ተመለሺ የተባልኩት እኔ ነኝ » ብላ በማስመሰል ሸነገለችውና ሼብረክ ስትል ፤ መሬት ስታይ ጠባቂው ወደ ውጭ ወጣና ራሱ የሚቀመጥበትን ስስ ድንጋይ ከአጐዛ ጋር አቀረበላትና የሔደችበትን ምክንያት ሹክ ያለችው ይመስል ሌሎችን እስረኞች ይዞላት ወጣ አለ ። እዚያች ላይ ሼብረክ ብላ አሉላንም እንዲቀመጥ አድርጋ ሞሰቡን አቀረበች ።

«ሆዴን አሞኛል ፤ በዚህ ላይ ብበላበት ደግሞ በይብልጥ ያመኛልና ይቅርብኝ » አላት ።

«የተጣላኸውኮ ከደበበ ጋር እንጂ ከቤቱ ሰው ሁሉ ጋር አይደለም ። እሚቴ ልካልህ እኔ ይዥልህ መጥቼ አልበላም ብትል ሁላችንም እናዝንብሃለን ። ይልቁንስ እንካ» ብላ በመጀመሪያ በዋንጫ ቀድታ ጠጅ ሰጠችው ። ተንሥቶ ሊቀበላት ሲል ጉልበቱን ጫን አለችውና እንደ ተቀመጠ ተቀበላት ። ጠጁን እንደ ተጎነጨም አከታትላ ስታጉርሰው ምላሱ ጣቶቿዋን ሲነካባት ሰቅጠጥ አለና እንደገና ስታጉርሰው ሆን ብሎ ጣቶቿዋን ላሳቸው ።

ከምግቡ ይልቅ ጣቶቿዋ ሞቁትና ፈጥኖ ሰበሰባቸው ። ያች የዐሥራ አራት ዓመታት ዕድሜ ወጣት ትኩሳት እያደር በይበልጥ እየጋለ እንጂ እየበረደ ከሚሔድበት ወቅት ላይ አልነበረም ። እርሱም ከሃያ አንድ ዓመት ዕድሜው ላይ ስለነበረ ፤ የሁለቱ እንፋሎት ተቃጣዋሎ ከምላሱ ላይ ጠበሰው ።



ለመሆኑስ ደበበ ተጉድቷል ? ከደንጋይ ላይ ነበር የወደቀውኮ?» አላት ቀና ብሎ ለማየት ፈርቶ ።

«ያ ጋን ራሱ ሊፈነዳ ቀርቧል ። ወጌሻ ገብቶለታል ፤ እንኳን የጥጋቡን ዋጋ አገኘ ፤ ጥፋቱ የራሱ ነው» አለችና እንደገና ስታጉርሰው ትክ ብሎ ተመለከታት ። በቀይ ዳማ መልኳ ላይ የበቀሉት ዐይኖቿ እንደ ሕዋው ኮከብ እየተወረወሩ የሚወጉት መሰለውና መልሶ አቀረቀረ ። የአምበሱ ውበት ጐልቶ የሚታየው ፈገግ ስትል ነው ። ቁንጅናዋን የሚያጐሉት ደግሞ ጥርሶቿ ናቸው ። በሰልካካው መልኳ ላይ ከተደረደሩት የተፈጥሮ ስጦታዎች ችምችም ብለው የበቀሉት በረዶ መስል ጥርሶቿ ውበቷን ከነባሕርይዋ የመመስከር ኃይል አላቸው ።

ባልገዳ አርአያ ዘለአጼ ቴዎድሮስ ግዞትና እስራት ለመለየት ሳይችሉ ለብዙ ዓመታት በመቅረታቸው የአምበሱንም እጅ ፈጥነው ለወንድ ለመስጠት አላመቻቸውም ነበር ፤ በዚያ ወቅት ግን እርሷን ድረው ዓላማቸውን ለማዩት ፍላጐታቸው ዳብሮ ነበር ። እንደ እርሳቸው ያለ መኳንንት ከዐሥር ዓመታት በላይ ዕድሜ ያላት ልጅ ይዞ መቀመጥ ሊኖረው የሚገባውን ጠንካራ ጉልበት ማዳከም ነበር ።

ነገር ግን ፤ ያ ወቅትም ቢሆን አመች ሆኖ አልታያቸውም አለ ። የእኅታቸው ልጅ ደጃች ካሣ ዙፋኑን ከአጼ ተክለ ጊዮርጊስ ቀምተው መላውን ኢትዮጵያን ለመያዝ ከፍተኛ ትጉትና ዝግጅት የጀመሩበት ሰዓት ስለነበረ ፤ በበኩላቸው የእኅታቸውን ልጅ እጅ ለትግራይ ባላባት ከመስጠት ይልቅ ወደ በጌምድር ወይም ወደ ሐማሴን ያለዚያም ወደ ወሎ አሻግሮ መስጠት ለወደፊቱ ጥንካሬያቸው አስተዋጽኦ እንደሚኖረው በመረዳት በየወንዙ የነበረውን ጉልበተኛ የሚያበላልጡበት ዱላቸው ሆነ ። ይሁንና የአምበሱን እጅ ለመጨበጥ የሚመኙ በባልገዳ አርአያ አካባቢም ነበሩ ።

«ዛሬ ከጥዋት ጀምሬ ስንከራተት አንች የምትወጃትን ስስ አጥቼ ድኩላ በማምጣቴ ቅር ብሎኝ ነበር» አላት ያጉረሰችውን በጠጅ እያወራረደ ።

«ሊሰክ ዛሬ ብዙ አብልተኸኛል ! ወደፊትም ታበላኛለህ ፡ አት ሰብ ዛሬ ቢቀር ነገ ታመጣኛለህ» አለችው ። እንጀራ የለበሰ ትን አጥንቶች እየፈለፈለች ፡ እያወጣች ከፊቱ አስቀመጠችለትና ከአንዱ አጥንት ላይ ሥጋውን እንሥታ ልትጎርስ ስትል እጅዋን ያዝ አደርጎ ፡

«አይገባም ነውር ነው» አላት ።

«ምነው?»

«ነግሬሻለሁ በቃ ሒጅልኝ » አለ ዐይኖቹን መሬት ላይ እንደ ተከለ ። «ከእኔ ጋር መቀመጡ ፡ ከኔ ጋር መብላቱ ነውር ሆነ ብህ?» አለችው ያነሣችውን አጥንት እንደ ያዘች ።

«አዎ ነውር ነው ! እዚህ መምጣትሽንም ጌታችን እንዳይሰሙ ተጠንቀቂ» አለ ሙሉ ለሙሉ ለማየት ቢሸቀዳደሙ የነበሩትን ዐይኖቹን የተከለከለ ይመስል እያንቀዋለለ ። አምለሱ ነገሩን አልሳተችውምና ፡ «እኔ የገብሬ ልጅ አሽከርሽ ነኝ ፡ ከኔ ጋር ልትጫወችና ከኔ ጋር በአንድ ሞሰብ መሰለፍሽ ለወላጆችሽ ውርደት ነው ማለትህ ነው? ይህንኑ አይደለም የምታስበው?» ብላ አፋጠጠችው ።

«አዎ እንደ እርሱ ነው ።»

«ዳግመኛ ግን እንደዚህ እንዳትለኝ» ብላ በእጅዋ ከነበረው አጥንት ላይ ላጥ አድርጋ ጉራረሰችለትና ፡ «ዛሬን እዚህ ብታድር ነገን አትውልም» አለችው ።

«ደበበ ቶሎ እንዲድን ጸልይልኝ» አላት በዐይኖቹ እየተማፀናት ።

«ዓመት ቢጋደም ምን ቸገረህ!»

«ቁስሉ ከጠናበትማ አባትሽ ይሰቅሉኛል መሰለሽ !»

«ማን ይነካሃል! በረሃውን ታውቀው የለም?»



«የባልገዳ እርአያን ልጅ በአልጋ ላይ አስተኝቼ የትኛው በረሃ ነው እኔን ደብቆ የሚያዝ ? ቀድሞ ነገርስ ከዚህ እንዴት እወጣለሁ?» አላት ተስፋ በቆረጠ ስሜት ተውጦ ።

«ከዚህም ትወጣለህ ! ለማንም እጅህን መስጠት የለብህም ያገርህ በረሃ እንኳን አንተን ሌላም አቅፎ ይይዛል» ብላው ለቃዋን አሽከማ ወጣች ።

አምለሱ ፡ የአሉላ ተኳሽነትና ቁመና ከሐሳቡዋ ቢገባም በዘር ሐረጉና በደረጃው የመጨረሻው ተራ በመሆኑ፡ እጅዋን እጁ ሊጨብጠው እንደማይቻለው ታስብና ተስፋዋ ይሟሽሽባታል። ግን ያን ተስፋ መቍረጧን የሚያድስላትና የሚያለመልምላት ከመምህሩዋና ከዘመዶቿ የሰማችው ትረካ ትውስ ሲላት ነበር።

«ቋረኛው ካሣ የድሃ ልጅ ያውም የኮሶ ሻጭ ልጅ ቢሆኑም ፡ በወንድነታቸውና በጀግንነታቸው የራስ አሊን ልጅ ተዋበችን ለማግባት በቅተዋል» እየተባለ የሚነገረውን ትረካ ስምታለች ። ይህንም ታሪክ በልቡዋ ቀርፃ የሕይወት ጉዳናዋን ታስተያይበታለች ።

«ዛሬን ብታድር ነገን እዚህ አትውልም» የተባለውን እስረኛ ቀናት እየተሰናበቱት ሔዱ ። እርሷም ቃሉዋን መጠበቅ ባለመቻሉዋ እየራቀችው ሔደች ! ራት ምሳውን ግን ራሱዋ እያዘጋጀች ትልክለት ነበር ።

የደበበ መታመም ከፈረስ እንደ ወደቀ ተመስሎ አሉላም ታሞ እንደ ተኛ ሆኖ ለባልገዳ እርአያ ተነግሩዋል ።

«ከፍየሉች ጋር የሚውሉ አውሬዎች ገደልኩ ብሎ ይኸን ያህል የተንጠራራው ፡ አንበሳና ነብር ቢገድልማ የራስ ወርቅ ድቀልኝ ከማለት የሚመለስ አይሆንም! ለመሆኑስ ይህ የቤት ልጅ እንዴት ቢጠግብና ቢናጥጥ ነው ይህን ያህል የተንጠራራው ?» እያሉ የባልገዳ እርአያ አጋፋሪ የአሉላን እስራት እያጠበቁበት ሔዱ ። ከመናደዳቸውና ከጽናታቸውም የተነሣ ፡

«እርፋችሁ ተቀመጡ ፡ የማን ልጅ መሆኑን ፡ ዐቅሙንና ደረጃውን ላላወቀ መድኃኒቱ ይኸው ነው» ይላሉ አጋፋሪ ወብ

ሐት ለአሉላ ምሕረት እንዲያደርጉ ለሚያነሡባቸው ሁሉ ። አምለሱ የአጋፋሪ ስብሐትን ወዳጆችና ዘመዶች እየለመነች አጋፋሪን ለምነውና አለዝበው አሉላን እንዲፈቱላት ያደረገችው ጥረት ሳይሳካለት በመቅረቱ ፣ «ያሉትን ይበሉኝ» ብላ ራሱዋን ከአጋፋሪ ዘንድ ቀርባ ፣

«ጥሉን የጀመረው ራሱ ደበበ ነው ። ቁስሉም ሺርሏታል ፤ ስለዚህ አሉላን ለምን አይፈቱትም?» ብላ ኮስተር ብላ ጠየቀቻቸው ።

«እኔ እንደ ሰማሁሽ ጌቶቼ የሰሙሽ እንደሆነ የውስጥ ገላሽን ነው የሚያስገለብጡት ። ተጠንቀቂ! ሁለትና ሦስት አውሬ ገድሎ አምጥቶልሻል መሰል ወሮታውን የከፈልኩ መስሎሽ ነው ? ከተደፈረው ወንድምሽ ይልቅ የእርሱ መታሰር ነው የቆጨሽ?» ብለው አጋፋሪም ከፍና ዝቅ አድርገው ተመለከቷዋት ።

አጋፋሪ ራሳቸው ካልመሰላቸው በቀር እንኳንስ ለአምለሱ ልመና ለእናቷም ቢሆን አይመለሱ ። ራሳቸው ጌታቸው የሚያዙዋቸውንም እንኳ የሚፈጽሙትና የሚያስፈጽሙት እልሃቸውን ከአስጨረሱዋቸው በኋላ ነው ። ባልገዳ አርአያም በአጋፋሪ የሚጨክኑ አልነበሩም ። የቴዎድሮስ እስረኛ ሆነው ጐንደር ይኖሩ በነበሩበት ወቅት ቤታቸውን የሚጠብቁና ሰንቅም ያቀብሉ የነበሩ አጋፋሪ ስብሐት ስለ ነበሩ ውለታው ይከብዳቸዋል ።

«ደርሶ ሲመታው ታዲያ እንደ ሴት እጁን አጣምሮ ለምን አልተመታም ነው የሚሉት?» አለች አምለሱ ፡ ከአጋፋሪ ላይ እንደአራስ ነብር ልትከመርባቸው እየከጀላት ። «ይችን ልጅ ምን ነክቷታል? አሽከሩ ሁሉ ጌታው ሲመታው መልሶ ከተማታ ከምን ላይ ሆነ ልዩነቱ? የሚያበላውን የሚያጠጣውን ፣ የሚያለብሰውንና የሚያሳድረውን ጌታውን መማታት ቀርቶ ፣ ቀና ብሎ ማየትስ የጥጋብ ጥጋብ አይደለም? ይኸ ሁሉ አሽከር በተመታ ቁጥር መልሶ ተማትቶ ቢሆን ኑሮ አባትሽስ እስከዛሬ በሕይወት ይገኙ ነበር? በይ እኔ እንደ ሰማሁሽ ሌላ ሰው እንዳይሰማሽ !»አሉና አጋፋሪ በጠጅና ጠላ የበዙ ዐይኖቻቸውን



ሲያጉረጠርጡባት በጥላቻና በንቀት ገላምጣቸው መልስ ሳትሰጣቸው ጥላቸው ሔደች ።

ወንድሟ ፈጽሞ እስኪድን ድረስ እስረኛውን መንከባከቧን ቀጠለች ።

በምድረ ተንቤን ዐዋቂውና ወጌሻው ሁሉ እየተፈለገና እየተመረጠ ደበበን ከቅስፈት እንዲያተርፍ የባልገዳ አርአያ ቤተሰቦችና ባለሟሎች ያደረጉት ጥረትና ድካም ከፍተኛ ቢሆንም ፣ ደበበ ከአሉላ ጋር ግብግብ ቢገጥም ተንጋሎ ቢወድቅም የደረሰበት ጉዳት ቀላል በመሆኑ በእልፍኝ ውስጥ ታፍኖ የጠበት ሥጋና የግር እሽት ሲቀሰብ ሰነባብቶ ወደ ደጅ መውጣት ጀመረ ። በእርሱ መዳንም ታላቅ ደስታ በምድረ ግቢው ሠፈነ። ከዚያ በኋላ አምለሱ ፍጹም እፎይታ እየተሰማት ሔደ ። የወንድሟ መዳን ለአሉላ መፈታት ዋናው ምክንያት እንደሚሆን ታምንበት ነበርና ።

የደበበ ቁስል እየዳነ ቢሔድም ፣ የአጋፋሪ ልብ በአሉላ ላይ ከቋጠረው ጥላቻና ንቀት አልተፈታም ነበርና ፣

«የጌታውን ልጅ ጌታውን በመድፈሩ ሌላ ቅጣት መቀጣት ይገባዋል» እያሉ ማውጠንጠን ጀመሩ ።

አምለሱ ፣ ነገሩን ለአባቷም ሆነ ለእናቷ መንገር እንደማይገባት ብታምንበትም ፣ የአጋፋሪ ጭካኔና ጥላቻ ደግሞ ስለ አንገፈገፋት ፣ በዘወርዋራ ዘዴ ለማስከሰስ አሰበችና ቀደም ብለው ከአጋፋሪ ጋር ብርቱ ጥል አብቅለው ለነበሩት ለፊታውራሪ በርሄ ነገሩ እንዲደርሳቸው አደረገች ።

ነገር ግን ፣ በአሉላ ተኳሽነትና ከአምለሱም ጋር በነበረው መቀራረብ ልባቸው ከቆሰለው አሽከሮች አንዱም ፊታውራሪ በርሄ ስለነበሩ አሉላ በፈጸመው «ድፍረት» በደብልጥ እንዲቀጣ የሚመኙ በመሆናቸው እንዲያውም ሲካሰሱ ከነበሩት ከአጋፋሪ ስብሐት ጋር ዕርቅና ሰላም መሠረቱበት ። በዚህም የተነሣ ፊታውራሪ በርሄ ይባስ ብለው ፣

«ይህን ድሃ የድሃ ልጅ ለሌላውም መቀጣጫ እንዲሆን ማድረግ ነው ፤ ገበያ አውጥቶ ሕዝብ በተሰበሰበበት በርባ ገርፎ ማባረር ነው እንጂ እስር መቀለብማ እንደ እነርሱ ላለ የቆሩራ ልጅ ክብሩና ኩራቱ ነው» እያሉ የሚፎገሉ ሆኑ ።

«እንዲያውም ለኔ ይስጡኝና እንደ እርሱ ላሉ የድሃ ልጆች ሁሉ መቀጣጫ እንዲሆን ላድርገው» ብለው እስከ መጠየቅ ደረሱ ፤ ፊታውራሪ በርሄ በነገሩ እንደዚያ ያመረሩት በእጅ እዙር ቁርሾአቸውን የተወጡ መስሎአቸው ነበር ። የመጀመሪያቸውና የሦስት ልጆቻቸው እናት የነበሩትን ባለቤታቸውን ፈትተው የአምለሱን እጅ በጋብቻ ለመጨበጥ አመችውን ወቅት የሚ ጠባበቁ ነበሩ ።

አምለሱ ፤ የጀመረችው ጥረት ሁሉ እየተበላሸባት መሔዱን ከተረዳችው በኋላ ፤ እንደ ተለመደው አንድ ቀን ራቱን ይዛ ለት ሔዳ አብልታው ልትወጣ ስትል ፤ «እንዲያው የኔስ ነገ. ምን ሆነ?» አላት ሰርቆ እንደ ታሰረ ሁሉ አንገቱን አቀርቅሮ ።

«አንድ ጊዜ ደግሞ ሞክሬ የማይሆን ከሆነ ወጥተህ ወደ ፈለግህበት ትሔዳለህና አስብበት» አለችው ።

«ከዚህ እንዴት እወጣለሁ?»

«በነገሩ ከቆረጥክበት ለዚህ አታስብ ።»

«ለምን አልቆርጥም? ዛሬማ መቁረጥ አለብኝ እንጂ!»

«ዛሬ ምን የተለየ ምክንያት ደርሶብሃል?»

«ከመታሰር የበለጠ ውርደት ደርሶብኛል» አላት ከአቀ ረቀረበት ተቃንቶ እርሷንና እስር ቤቱን ተራ በተራ እየተመለከተ ።

«እንደምን ያለ ውርደት!» አለች ከእርሱ ይበልጥ ሰውነቷን አስቆጥታ ።

«መታሰርም መሞትም ለወንድ ልጅ ክብሩ ነው ። ስድብ ግን አጥንቱን ይሰብርበታል» አላትና የታችኛው ከንፈሩን ነክሶ አፈጠጠባት ።



«ማን ሰደበህ?»

«አጋፋሪ በነጋ በጠባ በአጥሩ ብቅ እያሉ 'ይህ የቤት ልጅ እስኪ የሚደርስበትን ይጠብቅ' እያሉ መሳደባቸው አንሶ ዛሬ ደግሞ እዚህ ድረስ መጥተው 'አንተ የቤት ልጅ! ጋን አተላ አሸከሚ መንደር ለመንደር ሳላዞርህ ብቀር ታዘበኝ' ብለውኝ ሔዱ» አለና በሆዱ ውስጥ ያመቀውን ትንፋሹንና ንዴቱን ደጋግሞ አስወጣው ።

«እኮ ታዲያ ውጣና የወንድ ልጅ ወንድ መሆንህን አሳየኝ!» አለችው ከፍና ዝቅ አድርጋ እየተመለከተችው ።

«ይህን ሁሉ አጥር ዘልዬ ከዚህ ሁሉ ጠባቂ አምልጬ የምወጣበትን ዘዴ ትነግሪኛለሽ?» አላት እርሱም ከሁለንተናዋ ላይ አፍጥጦ ።

«ለዚህ አታስብበት በየሃለሁ ።»

«እኮ እንዴት? እስከ መቼስ ልወጣ እችላለሁ? ነገ ጋን አተላ አሸክመው ካዞሩኝ በኋላ ግን ፤ የኔም የቤት ዘመዶቼም ወንድነት ማብቃቱን እንዳትዘነጊው» ሲላት እንባም እልህም ተጫጫኗት ።

«አተላም አትሸከምም ፤ ሁለተኛም እዚህ እስር ቤት ዐይን ህን አያዩም» ብላው ወጣች..... በዚያው ለጥን ደግሞ ባልገዳ አርአያ ታመው ስለነበር ፤ በቅዳሴ ጠበል እንዲጠመቁ ተብሎ ወደ አክሱም ተወሰዱ ።

ከቀናት በኋላ ፤ በግቢው ውስጥ ያልተለመደ ድንጋጤ ተወለደ ። አሉላ ከነጠባቂዎቹ ጠፋ ። አጋፋሪ ስብሐት የጌታቸውን ሠራዊት አሰልፈው መላዋን ትግራይን ሊያተራምሱዋት ቆርጠው ተነሡ ።

«የጌታዬ ልጅ ተደፍሮ ፤ የጌታዬን ልጅ ከአቧራ ላይ ጥሎ ፤ የጌታዬን ልጅ ደም አፍስሶ ፤ የጌታዬን አጥር ጥሶ ፤ የጌታዬን አሽከሮች አባብሎ እንዴት ያ የድሃ ገበሬ ልጅ እንዴት ያ የቤት ልጅ ያምልጠኛል? ይህን ጥቃትስ እንዴት መታገሥ ይቻ

ላል? ይህ ሁሉ አሽከርስ የጌታቸውን ጥቃት ሳይወጣ እንዴት ውሉ ያድራል? ነገ ከጂ ሳይገባ ከቀረ እውነት ወንድ አይደ ሁም? እርሱማ ተይዞ መቀጣጫ ካልሆነ የመኳንንቱ የባላባቱ ልጅና ዘር ማንዘር በማንም ውርጋጥ ክንድ ሲወቃ መኖሩ ነው፤ አይማረኝ የማርኩት እንደሆነ» እያሉ መደንፋት ጀምረዋል ። ተንቤንን በእግሩዋ ገብተው በእናቷ ለመውጣት አነጣጥረው ባታል። አጋፋሪ ስብሐቱ «የድሃ ልጅ፤ የገበሬ ልጅ፤ የቤት ልጅ» እያሉ ያሳዝኑት የነበረው ቋንቋቸው ደግሞ የባልገዳ አርአያን አሽከሮች እያስቆጣና እያስኮረፈ በየልባቸው ቂምና ጥላቻ እየመሠረተ ሔደ ። ሠላሳ የሚሆኑ የባልገዳ አርአያ አሽከሮች ወደ በረሃ ሔደው አሉላን አድነው እንዲይዙ ወይም እንዲገድሉ አጋፋሪ አዘመቱ ። ግን ሁሉም አጋፋሪ ከሚንቁትና ከሚሳደቡት «ድሀና ገበሬ» ቤተሰብ የተገኙ ስለ ነበሩ፤ ከመንደሩ ወጥተው በየኮረብታው ተኝተው ውለው የሚመለሱ እንጂ የተላኩበትን ግዳጅ ከልብ የሚያምኑበት ባለመሆናቸው፤ የአሉላን እጅ ቀርቶ የደረሰበትንም ፍንጭ የሚነግሩዋቸው አልሆኑም ።

ስነባብቶ ደግሞ፤ ‹በዚህች ምድር ላይ ወይ እኔ ወይ ስብሐት እንኖርባታለን እንጂ፤ ሁሊታችንም እንቀመጥባትም ብሎ አሉላ ዝቷል› የሚል ወሬ ደረሳቸውና ወደ መንደራቸው ብቅ ማስቱን ጠብ ርግፍ አድርገው ተዉት ።

«አሉላ በርከት ያሉ ተከታዮች አገኘ፤ አዳዲስ ጠመንጃ አስ ያዘ፤ አሉላ በዚያ ወጣ በዚያ፤ ወረደ» የሚል ወሬ ከዚያው ከግ ቢው እየመነጨ የአጋፋሪን ልበልቦና የፍርሃት ቋያ ይለቅበት ጀመር ። በሁኔታው እጅግ የተሸበሩት አጋፋሪ አንድ ቀን እሑድ ጡዋት ወደ ባልገዳ አርአያ የነፍስ አባት ዘንድ ሔደው፤ ከቅ ዳሴ ሲወጡ ጠጋ ብለው «እንደ እርስዎ ያለ ከመሬትና ከሰማይ የከበደ አባት እያለን እንዴት ይህን ነገር በዝምታ መመልከት ይገባል? መሳሳቱን መቼም ተሳስቷል፤ እኔም ድፍረቱ አሳዝኖኝ የወንድማችን ልጅ ነው ብዬ ተቀጥቼዋለሁ ። ታዲያ በዚህ አኩ ርፎ መውጣቱ የባሰ ጥፋት ስለሚሆን፤ እርስዎ ተጓልከው ያስ መጡት፤ በዚህ ነገር ጊዜ ማሳለፍ አይገባምና ያስቡበት» ብለው ለመኑ ።



ልመናውና ጥያቄው የቀረበላቸው መምህር ተበሩ ጽዮ ንም ለደቂቃዎች ያህል ትኩዝ ብለው መሬት መሬቱን ሲመ ለከቱ ቆዩና፤

«ነገር ነገሩ ሁላችንንም መቼም ሳያሳዝነን አልቀረም፤ በት ንሽ የተጀመረ ነገር እያደር እየከረረና እያሳዘነ መሔዱ ማሳ ሰቡ የማይካድ ነው፤ ደግሞ ስውን መናቅ ተገቢም አይደለም ። እግዚአብሔር አይወደውም ። የተናቁትን ከፍ ከፍ የሚያደርግ አምላክ የሚያነሣውንና የሚጥለውን ያውቃል ። አሁንም እንደ ሆነ ‹ተቆጡትና ይመለስ› ከተባለ ዋና ጉዳያችን ነውና ተላ ልከንም ሆነ ተሯሩጠን እንመልሰዋለን» አሉ ።

«እንግዲያው ጌቶቼ ከአክሱም ከመመለሳቸው በፊት ጉዳዩ ፍጻሜ እንዲያገኝና ሲመጡ እንድናስታርቀው ቀልጥ ፈው ቢያምሩት ይሻል ይመስለኛል» አሉ አጋፋሪ እየተፍነ ከነኩ ።

«ለመሆኑስ እንዴት ሊያመልጣችሁ ቻለ?»

«ያውስ ብቻውን መስለዎት?»

«ሌሎችም ይዞ ወጥቷል !» አሉ መምህር ያላወቁ መስለው በስሚ ስሚ የደረሱበትን የአሉላን መሸፈት ከአጋፋሪ ለማረጋገጥ ብለው ።

«የሚያንቅ ነገርኮ ነው የሆነው፤ ጌቶቼ ወደ አክሱም ሲሔዱ ጠብቆ ‹እንግዲህ እርሳቸው አይመለሱም ይሞታሉ› ብሎ አንድ ባሕታዊ ተናግሩዋል ፤» ንጉሡም ብዙ ሠራዊት አስከትለው አገሩን ሊያስገብሩ ይመጣሉና ከዚህ እንውጣ› ብሎ «ጠባቂዎቼን አባ ብሎ ገንዘብ ሰጥቶ ጥቂቶቹንም አስከትሎ ነው ያመለጠን» አሉ አጋፋሪ ጥርሳቸውን ነክሰው፤ አንገታቸውን እያወዛወዙ ።

«የተከታዮና የመሣሪያው ብዛትስ ታውቋል?»

«ቢበዛ ቢበዛ ከዐሥርና ከኻያ አይበልጥም «ይባላል» አሉ አጋፋሪ ንቀታቸውን እያሳዩ ። «ይህምኮ ቀላል አይባልም፤ ይኸን ሁሉ መሣሪያ ከያዘ ወንዝ ማስቸገሩ አይቀርምና ያለ መናቅ

ነው!» አሉ መምህር ተደግፈው ቁመውበት ከነበረው ካብ ወደፊታቸው እያዘገሙ አጋፋሪን ሸኝተው ወደ ደጀሰላም ለመግባት ብለው ።

«ለዚህስ ነው ፣ እኔም መጥቼ የማስቸግርዎ!»

«ይሁን እንግዲህ ከዛሬና ከነገ ሰው ይስጡኝና ተላልከ አስመጣዋለሁ» ብለዋቸው ተሰያዩ ።

መምህር ተሰፋ ጽዮን የአሉላ መምህር ከነበሩት ከመምህር ወልደጊዮርጊስ ጋር ሆነው በጉዳዩ ከመከሩበት በኋላ ፣ ሽማግ ሎች ልከው በእርቅ እንዲገባ አደረጉ ። በዚያ ወቅትም አሉላ እጁን ሲበጥ ሦስት ራሱን ብቻ ነበር ። ሁለቱ የባሻይ ፋንታ ልጆች ይሁኑ እንጂ ዘመዶቹ ናቸው ።

ሁለቱ መምህራን አሉላን ከአጋፋሪ ጋር ከአስታረቁ በኋላ ፣ ቀጥሎ ደግሞ ለባልገዳ አርአያ ተነግሮ ይቅርታ እንዲያደርጉ ለት ከደበበም ጋር 'ይቅር ፣ ይቅር' እንዲባባሉ አጋፋሪ ነገሩን እንዲጨርሱ ሆነ ። ይህም እስኪሆን ድረስ አሉላ በውጭ እንዲ ቆይ እንጂ ከባልገዳ አርአያ ቤት እንዳይገባ ተስማሙ ።

ባልገዳ አርአያ ፣ ከእክሉም ተመልሰው ከሰንባበቱ በኋላ በተዝናኑበትና ሳቅ ሳቅ ባሉበት ሰዓት አጋፋሪ ከጫማቸው ወድቀው ፤

"ጌታዬ መቼም ምሕረት ገንዘብዎ ነው ባጠፋን በተሳሳትን ይማሩን ጌታዬ! ያበበና አሉላ በዕለት ጠብ ተጋጭተው ሰን. ቢው እርስዎ እንዳይሰሙ ብለን ደበበን ከፈረስ ላይ ወድቆ ነው ብለን ነግረንዎ ነበር ። አሉላንም በእስር ቤት አስገብተ ነው ነበርና እርሱም የባሰ ነገር ይደርስብኛል ብሎ ፈርቶ ከእ ስር ቤት ወጥቶ ወደ ዘመድ ቤት ሔዶ ተደብቆ ነበር ፤ አሁን ግን 'ምሕረት ለምኑልኝ' ብሎ ቀሳውስቱን ልኳልና ይቅር ብለ ውት ጫማዎን እንዲስም ይፍቀዱለት" ብለው ለመኑለት ። "ከሆነ ከደረሰ በኋላ መደባበቁ ምን ጠቀሜታ ይሰጣል ብላ ችሁ ነው የደበቃችሁኝ? ለነገሩ ግን እናንተ ብትደባብቁትም ጫፍ ጫፉን ሳልሰማው አልቀረሁም ። እንኳን በቤቱ ውስጥ የሆ



ነውን ቢያገሩ የደረሰውንም ቢሆን ሳልሰማው የምቀር አይምሰ ላችሁ ። አሁንም እንደሆነ እንኳን ከባሰ ጉዳት ያወጣን እንጂ ፣ እኔስ ስለ ጽዮን ብዬ ይቅር ብያለሁ ። ደግሞም መጋጨት በየትም የኖረ ነውና ይቅር ብያለሁ" አሉ ባልገዳ አርአያ ።

ቀጥሉም አሉላን ሁለቱ መምህራን ይዘው ገብተው የባል ገዳ አርአያን ጫማ አስመው ፣ "ይቅር" አስኙለትና እንደ ተለ መደው አሽከርነቱን እንዲቀጥል ፈቀዱለት ። ቀጥሎ ደግሞ ከደ በበም ጋር ማስታረቅ ስላስፈለገ ፣ አጋፋሪ ደበበን ለምነው ለማ ስታረቅ ከነመምህር ጋር ይዘውት ሔዱና "በል ድንጋይ ተሸከ ምና 'ማረኝ' በል" ብለው አሉላን ጠየቁት ።

"ከልብ እንድንታረቅ ካላችሁ እንዲዚሁ እንታረቅ እንጂ ያለ በደሌና ጥፋቴ ድንጋይ ተሸክሜ ከጫማው አልወድቅም" አለና አሉላ አንገራገረ ።

"በደልክም ተበደልክም እኛ አዘንሃልና ድንጋይ ተሸክመህ 'ማረኝ' ብለህ ከእግሩ ውደቅ" አሉ አጋፋሪ በማስገደድና በመ ሥጋት ላይ ሆነው ።

"የበደልኩትኮ ነገር የለም!"

"በድለኸዋል እንጂ! ከድንጋይ ላይ ፈጥፍጠህ ደሙን አፍሰስህ አስተኝተኸው የለም? ከዚህ የባሰ ምን በደል ታደርስበት ኑሩ ዋል!" አሉ አጋፋሪ እነመምህር ጭምር እንዲረዱዋቸው በዓ ይን—ሕሊናቸው እየተማፀኑ ።

"ቢሆንም ነገሩን የጀመረው ራሱኮ ነው !"

"የጕዳኸውኮ አንተው ነህ!" አሉና አጋፋሪ ወደ መምህር ተስፋ ጽዮን መለስ ብለው ደግሞ ፣

መምህር ተስፋጽዮንም ወደ አጋፋሪ ጠጋ አሉና ፣

"ደበበን መቼም እናውቀዋለን ፤ እንኳን ለቤት አሽከር ለኛ ለኛም የሚመለስ አይደለም ፤ ከጌታችን በሥጋ እንጂ ፣ በባሕርይ አልተወለደም ። ቢመከር ቢዘከር የሚሰማ አይደለም ፤ ሁላችሁ

ንበ እንዴት እንደሚያዋርዳችሁ እናውቅ የለም? እንኳን በቀላሉ አደረገለት እንጂ ለጥጋበኝነቱ ለትዕቢተኛነቱ አንድና ሁለት የለበትም ፤ ይኸው ከፊቱ ነው የምናገረው ። ይኸም ልጅ የሚለው እውነቱን ነው ፤ ሳይበድለው ድንጋይ አሸከሞ ታረቅ ማለት የሚገባም ባይሆን ለጌቶቹ ስንል ብቻ እናስገድደው እንደሁ እንጂ በነገሩ እንኳ አልደሰትበትም ” አሉዋቸው ።

“ቢሆንም ቢሆንም ደሙ የፈሰሰው ደበበ ነው ፤ ይቅርታም ሊጠይቀው ይገባዋልና እርስዎ ይቆጡት” አሉ አጋፋሪ ሥልማን — ቁጣቸው እየገነፈለባቸው ።

“ይኸኛውስ ቢሆን መች የዋዛ ሰው ነውና? እርስዎን እምቢ ያለ ለኔ ምን ብሎ ይሰዝባል ብለው ነው?” አሉ መምህርም የአጋፋሪ ቁጣ እሳት ነበልባል ሆኖ እንዳይፈጃቸው ሥግተው መሬት መሬት እያዩ ።

“ታዲያ ለጌቶቹ ይነገር?” አሉ አጋፋሪ ። ,

“ምኑን ነው የሚነግሩዋቸው?”

“ሁለቱንም ተቆጥተው እንዲያስታርቋቸው ።”

“እሁንኮ ጥፋት በእርስዎም ላይ እያለሁ ። ደበበ እግሬ ካልተሳመ ድንጋይ ካልተሸከመ አልታረቅም አላለ ። ለምን እንደዚሁ አናስታርቃቸውም? ደግሞ በዚህ ጌቶቼን እናስቸግር ነው የሚሉት?” አሉ መምህር ከአጋፋሪ ላይ አፍጥጠው ።

“ብኋል እንጂ እንዴት ባይል ይሉኛል ትላንትና ማታ እንዲታረቅ ስለምነው ፤ ‘ድንጋይ ተሸክሞ እግሬን ካልሳመ አልታረቅም’ ብኋል ። እኔም እሉላ ይህነኑ እንደሚፈጽም አረጋግጬለት ነው ደበበ እርቁን እሺ ያለኝ” አሉ አጋፋሪ ፤

“ወይ ጥጋቢቱ! ወይ ልቢቱ!” ብለው መምህር ሲያጉረመርሙ ቆዩና ፤

“ለመሆኑ እንዲያውላ ለመሆኑስ እውነት ፈራጅ ተገኝቶ ፤ ‘ነገሩን የጀመርከ አምባጓሮውን ያስነሳህ አንተ ነህና ድንጋይ



ተሸክመህ አሉላን ‘ማረኝ’ ብለህ ከእግሩ ውደቅ ቢባል ያደርገዋል?” ሲሉ አጋፋሪ ቀጠል አድርገው ፤

“የባሰውን ነገሩን በቀሉት ፤ እንግዲህ የሚሻለው ጌቶቼ እንዲያስታርቋቸው መንገሩ ይመስለኛል” አሉ ። መምህርም እንደ መነሚነጭ እየቃጣቸው ፤

“እንዳሻችሁ አድርጉ እኔ ግን ለሕሊናዬ ደስ የሚለኝን ሠርቻለሁ። ልጅና ልጅ ቢጣላ ግራና ቀኙን ተቆጥቶ እንደማስታረቅ አንተ ድንጋይ ተሸከም ፥ አንተ እግርህን ተሳም” ብሎ ማንተት አልታየኝም ። አሁንም እንደ ወደዱት ያድርጉ” ብለው ተመለሱ።

አጋፋሪ ስብሐት ፤ ራሳቸው ያባባሱትን ራሳቸው የፈቱትንና ራሳቸው መልሰው ያቀዘቀዙትን ጉዳይ በውል መጨረሱ ቸግራቸውና ነገሩን ለጌታቸው ነገሩ ። ባልገዳ አርአያ ሁለቱን ጥለኞች አስቀርበው ፤

“ሁለቱኛ እንጣላም ፤ ሁለተኛ ብንጣላ ዐሥር ዐሥር ጅራፍ እንቀጣለን በሉና እጁን ምቱ” ብለው አስምለው ፤ አሳስመው አስታረቋቸውና ነገሩ ጊዜያዊ እልባት አግኝቶ ለጊዜው በረደ ። አሉላም የራሳቸው የባልገዳ አርአያ የቅርብ አሽከርና ባለሟል ሆነ ። በአምበሱና በአሉላ መካከል የነበረውም ድብቅ መተሳሰብ በድብቅነቱ ቀጠለ ።

የባልገዳ አርአያ ግዛት የነበረችውን ተንቤንን ከዳር-ዳር ያዳረሰ አሽከር ቢኖር አሉላ ብቻ ነበር ። አንድ መንደር ቀርቶ አንድ ገበሬ ሊከፍል የሚገባውን መዋጮና ግብር አውሎ ካሳደረ የሚላከው አሉላ ነበር። ጠጉረ-ልውጥ ሰው በአንድ ቀበሌ ታይቷል ከተባለ ገሥግሦ የሚደርሰው ተወርዋሪው ጦር አሉላ ነበር ። ለባልገዳ አርአያ አዳዲስ ጠመንጃዎችና የጌጣ-ጌጥ ባሕር-መጥ ዕቃዎች ለመግዛት ወደ ከበሳና ምፅዋ የሚላከው አሉላ ነበር ። በወሎ በጉንደርና በጉጃም ለነበሩ መኳንንት የባልገዳ አርአያን መልእክትና ገጸበረከት የሚያደርስ ያለ አሉላ ማንም አልነበረም ። ጌታውንም እየወከለ በየሠርጉ ፤ በየለቅሶውና በየበዓላቱ የሚገኘውም እርሱ ነበር ። በተለይም ወደ ምፅዋ ተልኮ ለመጀመሪያ ጊዜ በሔደበት ዕለት ባሕር ለማየትና በባሕሩም ላይ ሲንሳ

ሬፍ የነበረውን ኩራብታ የሚያክል መርከብ ለማየት በመቻሉ ፣
ያ መርከብም የሚሰጠውን አገልግሎት ለመገንዘብ በመቢተቱ
የባሕር በርን ጥቅም ለማወቅ ቻለ ።

በወቅቱ ምፅዋንና አካባቢዋን ሲቈጣጠሩ የነበሩት ግብ
ጾችም ከደጋው ሲወርዱ በነበሩት ነጋዴዎችና ገበያተኞች ላይ
ሲፈጽሙ የነበረውን ግፍና በደልም ሊገነዘብ ችሏል ። ቤጠቅ
ላላው የባልገዳ አርአያ ከተራ አሽከርነት ላቅ ያለ መለስተኛ
እንደራሴ በመሆኑ ፣ ትግራይን ብቻም ሳይሆን ሌሎቹንም አካባቢ
ዎች በሰፊው ለማወቅ አጋጣሚው ረድቲታል ። ታዲያ ያሁሉ
ጥረቱና ድካሙ ፣ ያሁሉ ታማኝነቱና ወንድነቱ ተዳምረው ተቀና
ቃኝና ምቀኛ እያበዛበት ሔደ ። ከራሳቸው ከባልገዳ አርአያና
ከአምለሱ በቀር 'ዐይንህ ላፈር ከሔድክበት አይመልስህ'' የሚ
ለው እየበረከተ ሔደ ።

በተለይም አጋፋሪ ስብሐት ፣ ደበበና አሉላን ከባልገዳ አርአያ
ግቢ ቀርቶ፣ ከመላዋ ትግራይ ቀርቶ፣ ከምድሪቱ ለማጥፋት ወጥመድ
መዘርጋት የተንኰል ከር መግመድ የዕለት ተዕለት ሥራቸው
ሆነ ።

"ለድሃ ልጅ ሁሉ መጥፎ ምሳሌ የሚሆን ጥጋበኛ ነው''
እያሉ ጡዋት ማታ ያላዝኑበት የነበሩት አጋፋሪ ፣ አሉላን ከቤያ
ግቢ ካላጠፉ እንቅልፍ የማይዛቸው ሆኑ ።

ተቀናቃኞቹ ለማጥመድ የሚዘረጉበት ወጥመድ ደግሞ
ከእርሱ ይልቅ አምለሱን እያሳለባት ሔደ ። ሌላው ቢቀር ለአባቷ
ከእርሱ የበለጠ ታማኝና ጀግና አሽከር እንደሌላቸው ስለምታ
ውቅ "ለክፉ ቀን ይሆናቸዋል'' እያለች ሁልጊዜም ለእናቷና
ለቅርብ ዘመዶቿ ስለምታጫውታቸው በሁኔታውም እየሠጋችበት
ሔደች ። እያደር እየጠለ በአሉላ ላይ የሚደረገውን ተንኰል አባ
ቷም እየተረዱት በመሔዳቸው በነገሩ ይቸገሩበት ጀመር ። ለአ
ሉላ ቢሉም ከሌሎቹ በተለይም ከአጋፋሪ ስብሐት ጋር ሆድና
ጀርባ ለመሆን አልፈለጉም ። የእርባቸውን በሐሳብ መጥላል
የተረዱት አጋፋሪ ደግሞ ነገሩን ለማባባስ ብለው ፣ "ይኽ ልጅ
ያሠጋዎታል ፣ ቤትዎ ጠንቅ ነው ፣ ልጅዎንም ለመድፈር አይመ



ለሙ ። እንዲያውም 'ተንቤንን እንደምገዛ ባሕታዊ ነግሮኛል'
እያለ ይናገራል ። አንዳንድ የበቁ ሰዎችም ከአጠገብዎ ራቅ
እንዲል ንገሩ ብለውናልና ሁኔታው አላማረንም'' ብለው
ለጌታቸው ሹክ አሉ ።

ምንም እንኳን ራሳቸው ባልገዳ አርአያም ቢሆኑ፣ "የሚሆነውን
ነገር የሚናገሩ ባሕታውያን'' ቢኖሩዋቸውም ቅሉ ፣ በዙሪያቸው
የነበሩት ቀንደኛ ቀንደኛ ባለሟሎቻቸው በአሉላ ላይ የነበራቸው
ጥላቻና ሥጋት ስለ አሳሰባቸው አሉላን ከቤታቸው ዘወር ሊያደር
ጉና ከትኩረታቸውም እንዲያመልጥ ለማድረግ የሚችሉበትን
ዘዴ ማቀድ ጀመሩ ።

## “ንጉሥ ማራኪ”

አጼ ፣ ቴዎድሮስ ከእንግሊዞች ጋር ጦርነት ገጥመው “እጄን አልሰጥም” ብለው የራሳቸውን ራስ በራሳቸው ሽጉጥ ከጨለሙት በኋላ የሥልጣን ተተኪያቸው የሆኑት አጼ ተክለ ጊዮርጊስ ነበሩ ። ይሁን እንጂ የእርሳቸውንም ሥልጣን የሚፎካከሩ በየወንዙ ማቆጥቆጥ ጀምረው ነበር ። ከእነርሱም አንዱና ጉልህ ብለው ይታዩ የነበሩት የባልገዳ አርአያ የእኅት ልጅ በፈረስ ስማቸው “አባ በዝብዝ” በመባል የታወቁት ደጃዝማች ካሣ ነበሩ ። አባ በዝብዝ ካሣ መላዋን ኢትዮጵያን ለመጨበጥ ሠራዊትና መሣሪያ ማከማቸት ጀምረው ስለነበረ ፣ ለዚያ አዲስ ጉልበትና የጋለ ምኞት እንደ አሉላ የመሳሰሉ ጀግኖች የበለጠ ሙያ ሊያበረክቱ እንደሚችሉ የታመነ ጉዳይ ነበር ። አሉላም ይህንኑ ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተውት ነበር ።

ባልገዳ አርአያ ፣ ባንድ በኩል አሉላን ከቤታቸው ላለማራቅ ቢፈልጉም በእርሱ ምክንያት ከባለሟሎቻቸው ጋር መኳረፉን አልፈለጉትም ። በሌላ በኩል ደግሞ ከእርሳቸው ከራቀ ለአንዱ ደጃዝማች ወይም ሹም አሽከርነት ገብቶ የእርሳቸውን ምሥጢር እንዳያወጣባቸው ብቻ ሳይሆን የእርሳቸው አሽከርና ባለሟል የነበረ ሎሌ ፣ ከሌላ ጌታ ገብቶ ማደሩን እንደ ብርቱ ጥቃት ገመቱት ።

ከእነዚህ የራሳቸው ስሜትና እምነት ከፈጠረባቸው ችግር ነጻ ለመውጣት ፣ ሲሉም አሉላን አስከትለው ወደ መቀሌ በሔዱበት ወቅት ፣

“ከኔ ቤት ምቀኛ ሊያኖረው አልቻለምና ለአንተ ይጠቅምሃል ። ከአጠገብህ አታርቀው ፣ ታማኝ ጀግና ነው ፣ ለቤትህ ምሰሶና አጥር ይሆናል” ብለው ለደጃዝማች ካሣ አስረከቡት ።



መቀሌም ሰንብተው ወደ ተንቤን ሊመለሱ በተነሡበት ወቅትም አሉላ ሊሰናበታቸው ጫማቸውን ሲስም ፣

“ካሣ የሚያደርገውን ሁሉ ላክብኝ ፣ እኔም በምፈልግህ ጊዜ ፈጥነህ እንድትመጣ ፤ ለጊዜው ነው እንጂ ከኔ አትለይም” ብለው አሰናበቱት ።

አፍለኛው ካሣ አባ በዝብዝ የአሉላን ጀግንነትና ታማኝነት በፈተና ውስጥ አላስገቡትም ፤ የአጐታቸው ምስክሬ በቂያቸው ስለሆነላቸው ከጥቂት ጊዜያት በኋላ አሉላን አልፍኝ አስከልካያቸው አድርገው ሾሙት ።

ያንጋ ጠባ በየቀበሌውና በየበረሃው መዝመት የለመደው አሉላ ፣ በአንድ ጥያት አንባብሮ መጣል የለመደው አሉላ ፣ በማለፊያ ማለፊያ ልብስ አጊጦ ቀጭን ኩታ አደግድጎ ለሚገባውና ለሚወጣው ቁጭ ብድግ እያለ እጅ መንሣቱ በጀሮ ማሾክሾኩ ፣ እጁ ከጠመንጃ መለየቱ በካሣ ቤት አምለሱን ባለማግኘቱ በዋሻ ውስጥ ብቻውን የተዘጋበት እንጂ ፣ ገና ዘውድ በሚመኝ አፍለኛ ጉልበታም ምድረግቢ የገባ አልመሰለው አለ ። ማገገኑንና መተከዙን የተረዱለት ካሣም ከአልፍኝ አስከልካይነት ወደ አጋፋሪነት ደረጃ ከፍ አደረጉት ።

በአዲሱ ሹመቱም መጠነኛ ደስተኛ ሆነ ፤ ሌላው ቢቀር ራሱ የሚያዛቸው ጭፍሮች ነበሩት ። በአጋፋሪነቱም ከመኳንንቱና ከጦር አለቆቹ ጋር በይበልጥ ሊቀራረብ ችሏል ። ከባልገዳ አርአያ አጋፋሪ ከአጋፋሪ ሐጐስም ልቋል ። ምክንያቱም ባልገዳ አርአያ ገና በማገገም ላይ የነበሩ የቴዎድሮስ ክንድ አድቅቋቸው ጉልበታቸው እንደሚሸሽ የነበሩ ሲሆን ፣ በዝብዝ ካሣ ግን በምፅዋ በኩል ለገባው የእንግሊዝ ጦር ከቴዎድሮስ ጋር ጦርነት እንዲገጥም ፣ የትግራይን በር ከፍተው በማስገባታቸው ይኸው ውለታቸው የከበደው የእንግሊዝ ጦር አዝማች የነበረው ጀኔራል ናፒየርም በርከት ያለ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ሰጥቷቸው ከነበራቸው ላይ ጨምረው ጉልበታቸውን አዳብረው ትግራይን ዐልፈው በመላዋ ኢትዮጵያ ላይ ለመንገሥ የተነሡ ስለነበሩ ደጀጠኞቻቸው የበዛ ምድረግቢያቸው የደመቀ ነበሩና ።

አፍለኛው ጉልበተኛ ደጃዝማች ካሣ ሠራዊታቸውንና መጣሪያቸውን ካደረጁ በኋላ ፣ ለአጼ ተክለጊዮርጊስ ሲገብሩ የቆዩትን ተገቢውን ግብር "አልከፍልም" ብለው በማመፃቸው በሁለቱ መካከል የተጧጧፈ የዛቻና የመልእክት ጦርነት ጀመረ ።

አጼው ትኩሱን ጉልበተኛ ደጃዝማቹን ለማስፈራራትና ለጉብጥ ብለው መገዛታቸውንና መገበራቸውን እንዲቀጥሉ ለመምከርም ሲሉ የሠራዊታቸው ብዛት የካማን ጭፍሮች ቀርቶ በመላዋ ኢትዮጵያ የነበረውን ተቃዋሚያቸውን ሁሉ ሊያጥለቀልቀው እንደሚችል ለማሳወቅ ሲሉ ከአንድ ስልቻ ጤፍ ጋር ፣ "የሠራዊቱ ብዛት በዚህ ልክ ነው" ብለው ላኩባቸው ። ደጃዝማቹም ፣ "ሠራዊትህ ይዘን ያህል ቢበዛም እንደዚህ አድርጊ ቆልቼ ነው የምልክልህ" ብለው ስልቻውን ሙሉ ጤፍ ቆልተው መልሰው ይልኩላቸዋል ። እርር ብሉ የተቆላው ስልቻ ሙሉ ጤፍ ከፊታቸው የተዘረገፈው አጤም ከጤፉ ይበልጥ እርር ብለው ኑሮ ፡

"ከዚህ ወዲያ ጥጋብ ከዚህ ወዲያ ድፍረት እንኳንስ በመፈተ ከበባቱ ሰማያትም ወዲያ ቢሆን አያደርስብኝምና ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት" ብለው ከነበሩባት ከዋግ አውራጃ ወደ ትግራይ ዘመቱ ።

የሁለቱ ዘውድ ተናጣቂዎች ሠራዊት ዐድዋ አጠገብ ከሚገኘው አሰም ከተባለው ወንዝ ላይ ሐምሌ 5 ቀን 1863 ጦርነት ገጠሙ ። አንዲት ዘውድ በአንድ ሰው ራስ ላይ ለማስቀመጥ የአንዲት አገር ልጆች ተላለቁ ። በዚያ የዘውድ ንጥቂያ ጦርነትም ያችኑ ዘውድ "ማን ይወስዳት ይሆን?" እያለ የትግራይ የዋግና የቤጌምድር ሕዝብ በሐሳብ ይዋልል ነበር ። አፍለኛው ጉልበተኛ ደጃዝማች ካሣ ከቤታቸው በራፍ ድረስ ሰተት ብሉ የገባላቸውን ጦር ዙሪያውን አስከብበው እንደ ስልቻው ጤፍ ሲቆሉት ዋሉ ። አጋፋሪ አሉላም ከራሳቸው አሽከሮች ሌላ በርካታ ወታደሮች ተጨምረውላቸው በአንድ አቅጣጫ አሰልፈው ሲዋጉ ዋሉ ። በመጨረሻም በለስ ቀናቸውና ራሳቸውን አጼ ተክለ ጊዮርጊስን ማርከው ለደጃዝማች ካሣ አቀረቡና ፣



"ንጉሥ ማረከ ከነዘውዱ
የዐድዋው አሽከር አሉላ ወንዱ!
ከነፋስ የፈጠነ
በወንድነቱ የተማመነ
ክንዱ ብርቱ እንዳንበሳ
ለጠላት ሠፈር የሚያገሳ
ሩቅ . . . ሩቅ . . አሳሬ . . ."

ብለው ፉከራውን ሳይጨርሱ ሲታ ተናንታቸውና ከጌታቸው ፊት እንደ ተንበረከኩ ዐይኖቻቸውን አፍጠው ዝም ሲሉ ፣ ጌታቸው በዝብዝ ካሣ አስጠርተው ቀሚሳቸውና የእንግሊዝ ጦር አዝማች የነበረው ጀኔራል ናፒየር ከሰጣቸው ሁለት ዲሞትሮር ጠመንጃዎች አንዱን ሸለሟቸው ።

አባ በዝብዝ ካሣ የእኅታቸውን ባል አጼ ተክለ ጊዮርጊስን እጅ ከጨበጡ በኋላ ፣ በድል አድራጊነት ወደ መቀሌ እንደ ተመለሱም አሉላን ከአጋፋሪነት የሻለቃነት ማዕረግና ደንገላ ፈረስ "አባ ነጋ" ብለው ሰይመው ሁለተኛ ሸለሟቸው ።

ከዚያ በኋላ የአሉላ ዝና ፣ የአሉላ ጀግንነት ከባልገዳ እርሲያ ጋቢ ወጥቶ ከአባ በዝብዝ ግቢ ዐልፎ በመረብ ምላሽ ከተከዜ ማዶ ከጥራሬ ወዲህ ዐባይን ተሻግሮ ማስተጋባት ጀመረ ። ከእረኛ እስከ መኳንንቱ አዝማሪዎች የአሉላን ጀግንነት ማወደስና ማሞገስ ሆነ ።

"ንጉሥ የማረከ ከነሠራዊቱ
እንደምን ብርቱ ነው አሉላ እሚሉቱ
የንጉሥ ሠራዊት ዐድዋ ድረስ መጣ
አሉላ ቢገጥመው ብትንትኑ ወጣ!
ዐይኑ እንዳሞራ እጁ ተወርዋሪ
አሉላ አይደለም ወይ? ንጉሥ አሳፋሪ
እንደምን ትኮራ አሉላ እናትህ
እንደምን ትኮራ አሉላ ሚስትህ
ንጉሥ በጨበጠው ባያሉ ክንድህ ።

እየተባለ በየሜዳው ፣ በየወንዙና በየሥርጉ ቤት ይዘፈን ጀመር ። በዝብዝ ካሣም አሉላ ከእጃቸው እንዳይወጣ ያተኩሩበት ጀመር ። የቅርብ ቤተ-ዘመድ ፈልገው እጅዋን ለአሉላ ሰጥተው ክንዱንና ወንድነቱን ለአልጋቸው ማጠናከሪያ ማድረግ ዋናው ምኞታቸው ሆነ ። በዝብዝ ካሣ የአሉላን ወንድነት በሚመኙበት ወቅት ደግሞ መምህር ወልደ ጊዮርጊስም የአሉላ ዘር ከተንቤን እንዳ ይወጣባቸው ሲሉ ከባሻይ እንግዳና ወይዘሮ ገረዳ ጋር ተመካከረው በግብርናቸው በመላው ተንቤን የታወቁ የነበሩትን የባሻይ ገብረ መስቀልን ልጅ ብትወጣ ገብረ መስቀልን አጋቡ ።

በአሉላ ጀግንነትና በማዕረግ እድገት የባልገዳ አርአያ ባለሟሎች የበሸቁትን ያህል የአምበሱ ሕሊናም በአሉላ ጋብቻ የተነካ ቆሰለ ።

ደጃዝማች በዝብዝ ካሣ ፣ አፍለኛው ጉልበታቸውን በአጼ ተክለ ጊዮርጊስ ላይ ሞክረው ያ-ሁሉ ሠራዊት የተፋለቀበትን ዘውድ ከደፉ በኋላ ፣ ሻለቃ አሉላንም የሊጋባነት ማዕረግ ሰጡቸው ። ቀጥለውም ሠራዊታቸውን በጉደለ አሟልተው ከደላደሉ በኋላ ግዛታቸውን ለማደላደል በየአውራጃው ሲነሡ የነበሩትንም ተቀናቃኞቻቸውን ለማንበርከክ በየአውራጃው በሚዘዋወሩበት ጊዜ ሊጋባ አሉላም በግንባር የሚሰለፉ የጦሩን ገፈታ ቀድመው የሚቀምሱ ሆኑ ። የአሉላ ክንድ መጠጠር አጼ ዮሐንስን የሚያስመካ እየሆነ ቢታይም ፣ የባልገዳ አርአያ ባለሟሎች ብቻም ሳይሆኑ ራሳቸው አርአያ ድምፁ ጭምር ጥላቸውን እያጠኑበት ሔዱ ።

ጀግንነት ፣ ቆራጥነትና ታማኝነት ለአሉላ ብርቱ ጠላቶች የማፍራታቸውን ያህል ፣ አጼ ዮሐንስም በሀገሪቱ ውስጥ ከተነሡባቸው ተፎካካሪዎች ሌላ የውጭ ጠላትም እጁን ይዘረጋባቸው ጀመር ። በዚህም ምክንያት ጥንካሬያቸውንና ቆራጥነታቸውን የሚያሳዩበት የንጉሠ ነገሥትነታቸውን ብርታትም ለውጭው ተጋፊና ለውስጡ ተቀናቃኝ የሚያረጋግጡበት ወሳኙ ወቅትና ምዕራፍም በአቅራቢያቸው እንደ ገና ተከፈተ ።



## “የጉራው አንበሳ”

በ19ኛው ክፍለ ዘመን ላይ በሰሜን ኢትዮጵያ ተደጋግሞ የደረሰው የባዕድ ወረራ አገሪቱን ከከፍተኛ ፈተና ላይ የጣለ ነበር ። በውስጥ የነበረው የእርስ በርስ መከፋፈል ለውጭው ወራሪ ምቹ በር እየከፈተ ከዐሥራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በመጀመሪያ ቱርኮች ቀጥሎም በ19ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ግብጾች ወደ ሀገሪቱ ለመግባት እንዲችሉ ረድቷቸዋል ።

በተለይም ግብጽ በዐባይ ወንዝ አዋሳኝ የሚገኙ አገሮችን በቁጥጥርዋ ሥር ለማድረግ በነበራት ምኞትና ዕቅድ ሁለት ጊዜ በጉንደር በኩል ያዘመተችው ጦር በጳረኛው አባ ታጠቅ ካሣ እጅ እየተወቃ ብትንትኑ ከወጣባት በኋላ የቴዎድሮስን ዘመነ-መንግሥት ፍጻሜ አድፍጣ ስትጠባበቅ ቆይታ ነበር ።

ቴዎድሮስ ሙተው ተክለ ጊዮርጊስና በዝብዝ ካሣ እርስ በርስ ተዋግተው በዝብዝ ድል አድርገው ከነገሡ በኋላ ደግሞ በሀገሪቱ ውስጥ ይታይ የነበረው የመኳንንት ፉክክር አመቺ ሆኖ ስለታያት ፣ ግብጽ እጅግ የታጠቀና የተጠናከረ የጦር ኃይል ወደ ኢትዮጵያ ለማዝመት ወሰነች ። በዚያ ዘመን ደግሞ ራሷዋን ግብጽን በበላይነት ይቆጣጠራት የነበረው የእንግሊዝ መንግሥት ስለነበረ ፣ የራሱን የቅኝ ግዛት ፍላጐት ከግቡ ለማድረስ ሲል ኢትዮጵያን ለመውረር ጽኑ ፍላጐት የነበራትን ግብጽን ማጠናከር ማደፋፈርና ማስታጠቅ ዋናው ጥረቱ ነበር ።

በዚህም መሠረት የግብጽ ጦር ከአውሮፓ አገሮች ልዩ ልዩ ዘመናዊ መሣሪያ ለማግኘት ከመቻሉም ሌላ ፣ ከአሜሪካ ፣ ከአውሮፓና ከቱርክም በተመረጡ የጦር ስልት ባለሙያዎችን የሠለጠነና የሚመራ ለመሆን ቻለ ። ከዚያም የላቀ ደረጃ ላይ

የደረሰ በመሆኑ ወደ ኢትዮጵያ ያዘመተውን ሠራዊት ይመራ የነበረው በጦር ሚኒስትሩና በአልጋ ወራሹ ነበር ።

የጉብኙ ቀዲል እስማኤል የሠራዊቱን መኮንኖች ሰብስቦ ስለኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ እየዘረዘረ ሲያስረዳም ፣
"በሐበሾች ንጉሦችና መኳንንቶች መካከል የነበረው ጦርነትና መናናቅም እሙች ስለሆነላቸው ፣ እንግሊዞች በጀኔራል ናፒየር የሚመራ ጦር አዝምተው እስከ ሀገሪቱ እምብርት ድረስ ለመግባት ችለው ቴዎድሮስ እስረኛቸው የነበሩትን ዜጎቻቸውን አስፈትተው ለመመለስ ችለዋል" ብሎ ከፊቱ የነበረውን ጽዋብን እንደገና ሲመለከት ቀዩና እንደ ጣኦታቸው ሲመለከቱት የነበሩትን ጭፍሮቹን እንደገና ገለማምጦ ንግግሩን በመቀጠል ፣
"እኛም በዚሁ አጋጣሚ የተነካ በቅርቡ በጉስና መተማ የሚባሉትን አካባቢዎች ለመያዝ ችለናል ። ገምግሚችንም በዚህ አይ ገታም ፤ ወደፊት ገፍተን የሰሜኑን ግዛት መያዝ አስፈላጊያችን ሆኗል ። ወዳጃችን ዋርነር መንዚንገርና የምፅዋው አገረ ገዥ አራኬል በይ እንደ ጻፉልኝ ፣ የሸዋው ንጉሥ ምኒልክና የጎጃሙ ንጉሥ ራስ አዳል ለዮሐንስ አንገዛም ብለዋል ። በዚሁ ሁኔታቸው እንዲተባበሩት እኛም እንገፋፋቸዋለን ። የጦር መሣሪያም እንደ አስፈላጊነቱ እንልክላቸዋለን ። በየቦታውና በየአገሩም እዚሁ እንገዛም የሚሉ ወይም እኔ ልንገሥ የሚሉ ባላባቶች እንደዚሁ አኩርፈው መሣሪያና ሰው በመሰብሰብ ላይ መሆናቸውን መንዚ ንገር ጽፎልኛል ።

"እንዳመለከቱት ከሆነ ፣ ይህ ሁኔታ የሐንስን ክብርቱ ፈተና ላይ ይጥለዋል ። ስለዚህ የንጉሦንቱን የበላይነት ለማረጋገጥ ሲል ወደ መሃል አገር መዝመቱ የማያጠራጥር ነው ።

"የኛ መልካም ዕድል ጉልቶ የሚታየኝና የሚጠራኝም ከዚሁ ላይ ይመስለኛል ። ይህን አጋጣሚ ማለፍ የለብንም ፤ ወደፊት መገፋትና ከመረብ ወንዝ ወዲህ ያለውን አገር በአስቸኳይ መያዝ አለብን ። ይህ ዕቅዳችን ሲሟላ የዐባይ ወንዝና የምፅዋ ባሕር በቁጥጥራችን ሥር ይሆናሉ ። ከዚያ በኋላ ሃይማኖታችንን ለማስ ፋፋትም ሆነ ሀብታችንን ለማጠናከር አመቺና ተገቢም ይሆን ልናል ።



"በተለይም በይዞታችን ሥር በሚገኙት ከላይ በጠቀስኳ ቸው ቦታዎች የሚገኘው ሕዝብ የሃይማኖታችን ተከታይ በመ ሆኑ ፣ ወደፊት ለመግፋት በምናደርገው ጉዞ ተባባሪያችን እንዲ ሆን ለማድረግ ያስችላል ። በሌላውም አካባቢ የሚኖረውን ሕዝብ የኛ ተከታይና ደጋፊ ለማድረግ ለባላባቶቹና ለሃይማኖት አለቆቹ የተቻለውን ያህል ስጦታ ማድረግና በወዳጅነትም ማቅ ረብ ተገቢያችን ይሆናል ። ስለዚህ የሐማሴንን አገረ-ገዥ በቀ ላሉ አቸንፈን የሰሜኑን ያበሻ ግዛት መያዝ እንችላለን" አለ ።

የቀዲቡን ንግግር ከሰሙት የጦር አለቆችም አንዱ ተነ ሥቶ !

"አሁን እንደ ሰማነው ከሆነ ንጉሡ ዮሐንስ ብቸኛ ሆኗል ማለት ነው ። ይህም ሁኔታው ለኛ በሩን ክፍት ሊያደርግልን ይች ላል ። ነገር ግን ከዚህ በፊት እንዳደረጉት አበሾች ሌላ የውጭ መንግሥት እርዳታ በተለይም ከክርስቲያን መንግሥት ጋር በምዕምነት ያደረጉ እንደሆነ ከብርቱ ችግር ላይ ይጥሉናል ። በቱርኮች ላይ የደረሰው ውርደት እንዳይደርስብን መጠንቀቅ ይኖርብናል..." ብሎ ንግግሩን ሳያጠቃልል ቀዲብ እስማኤል በቁጣ ጦፎ ፡

"ስማ አንተ ውሻ! የመተማን የምዕዋንና የደንከሉን አካባቢ ከያዝነው ከውጭ የሚኖራቸው ግንኙነት በየት በኩል ይሆናል! ብለህ ታስባለህ? የወታደር ወኔና ስልት የጐደለህ ወንድነትህ የማያስመካ እንዳንተ ያለ የጦር መኮንን በግብጽ ጦር ውስጥ መገኘት የለበትምና አንገትህን ለሰይፍ ዳርጌሃለሁ" አለና በወ ታደር አስይዞ ወዲያውኑ አንገቱን አስቀላው ።

ከዚያ በኋላ ፣ በዚያች የፍጥሜ ሰዓት ቃል የተነፈሰ አንድም የጦር መኮንን አልነበረም ። በተሰጣቸው ትእዛዝ መሠረት ሠራ ዊታቸውንና መሣሪያቸውን አዘጋጅተው ወደ ኢትዮጵያ ዘመቱ ። ቀዲብ እስማኤል ባወጣው ዕቅድና በሰጠው ትእዛዝ መሠረት የግብጽ የጦር መሪዎችና ባለሥልጣኖች ለሃይማኖትና ለጐሳ መሪዎች የማዕረግ ስም ገንዘብና ልዩ ልዩ ገጸ-በረከት እየሰጡ እስከ ዶጋው የሐማሴን ግዛት ደረሱ ። በዋርነር መዚንጋር የሚ መራ ጦር ደግሞ በአውሳ በኩል ዘመተ ። ይሁን እንጂ ሀገሪቱ

እጆቿን ዘርግታ አልተቀበለቻቸውም ። በወቅቱ የሐማሴን ገዥ የነበሩት ደጃዝማች ገብሩ የነበሩዋቸውን የግል አሽከሮችና ጭፍሮች እንደዚሁም የታወቁ ጀግኖች አሰልፈው በቆራጥነት ገጠሙዋቸው ። ዳሩ ግን ሩቡዋን ኢትዮጵያን ለመያዝ በሚገባ ተዘጋጅቶና ታጥቆ የመጣው ወራሪው ጦር አሸነፋቸውና በደቀመሐሪና በጉራዕ በሀዘሞ በኩል ወደ ጉንደት አምርቶ ጉንደትና አዲኳላ ድረስ ዘልቆ ገብቶ ምሽጉን አጠናክሮ ሠርቶ ለጦርነት አመቺ የሚሆኑ ቦታዎችን ያዘ ።

አጼ ዮሐንስ ፣ የግብጽን ጦር ድፍረት እንደ ሰሙ በዝምታ ሊጠባበቁት ቀርቶ ውለው ለማደር የማይቻላቸው ሆነ ። እርግጥ ነው በዚያ ወቅት በሸዋ ንጉሥ ምኒልክ ፣ በጐጃም ራስ አዳል በተቀናቃኝነቱ ጸንተውበት "ዘውድ ለኔ ለኔ" የሚባባሉበት ሰዓት ስለነበረ ፣ አጼ ዮሐንስም ከተቀናቃኞቻቸው ይልቅ ፊታቸውንና ሐሳባቸውን ያዞሩት ወደ ሀገሪቱ ጠላት ሆነ ። በዘውድ ፉክክር የኢትዮጵያ ክብር መደፈሩና ሕዝቡዋ በጠላት እጅ መግባቱ የሚያንገፈግፍ ጥቃት መሆኑን ስለአመኑበት ለጦርነት ተዘጋጁ ። በጎናቸውም በወቅቱ የታወቁት የጦር አለቆች እነ ራስ አርአያ ፣ ራስ ባርያው ገ/ጻድቅ እነደጃዝማች ገብሩና ወልደ ሚካኤል ተሰለፉ ።

የከተት ዐዋጅ አስነግረው ሠራዊታቸውን አስከትተው የጦር አለቆቻቸውንና መኳንንቶቻቸውን ሰበሰቡና ፣

"ልጆቼ ወዳጆቼ አዳምጡኝ!

አቅማችን መከፋፈሉን ፣ ሐሳባችን መዋለሉን ተረድቶ ይኸውና ግብጽ መላውን የመረብ ምላሽ አገራችንን ይዞታል ። የሀገሬን መደፈር አላይም ። አልሰማም ። ፊቴንም ወደ መኻል አገር አላዞርም ፣ ዛሬ እኔን የከዳው ሁሉ ነገ ዕዳውን እያንዳንዱ ለየብቻው ይሸከመዋል ። እንግዲህ ልጆቼ ወዳጆቼ ምን ትመክሩኛላችሁ? ሁላችሁም እንደ ታያችሁ ንገሩኝ" ብለው ምክርና ሐሳብ ጠየቁ ።

በዚህ ጊዜ ባልገዳ አርአያም ተነሡና ፣



"የምኒሊክንና የአዳልን ማፈንገጥ ቀደም ብለን በውቀነዋል ። ያኮረፉበትንም ምክንያት አላጣነውም ። ቢሆንም የሀገራችንን መደፈር ዘርዝረን ሁነኛ ሰው እንልክባቸውና ሲሆን ሲሆን ሁለቱም እንዲደርሱልን ፤ ያለዚያ የሚሆነውን ያህል እርዳታ እንዲልኩልን እንጠይቃለን ። የእነርሱንም ሐሳብ እስክናገኝ ልንዘጋጅበት ይገባል" ብለው ተቀመጡ ። ቀጥሎም ደጃዝማች ኃይለ ማርያም ተነሡና ፣

"አሁን ጌታ ባልገዳ የተናገሩት ማለፊያና ተገቢም ነው ። የንጉሥ ምኒልክንና የራስ አዳልን እርዳታ ብቻ ሳይሆን እነርሱም ራሳቸው ከነሠራዊታቸው መጥተው እንዲረዱን ጌታ ባልገዳን ብንልክባቸው የሚገባ ሆኖ ይታየኛል ፤ የእነርሱን መልስ ካገኘን በኋላ የመጣብንን ጠላት እንገጥመዋለን" ብለው ተቀመጡ ።

ከሁለቱ ታላላቅ መኳንንት ቀጥሎም ሌሎቹ እየተነሡ ሐሳባቸውን ከአሰሙ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ አጋፋሪያቸውን በጥቅሻ ጠርተው ትእዛዝ ሰጡት ። አጋፋሪውም ጮክ ብሎ ፣

"ሊጋባ አሉላ እርስዎም ሐሳብዎን ይናገሩ ይባላሉ" ብለው የንጉሠ ነገሥቱን ትእዛዝ አስተጋቡ ። ከዋና ዋናዎቹ መኳንንቶችና የጦር አለቆች በስተኋላ አደግድገው ቆመው የነበሩት ሊጋባ አሉላም ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ፊት ለፊት ጠጋ ብለው ፣

"እንዴት ለጠላት ጊዜ ይሰጣል? እኛ ወደ ሸዋና ወደ ጐጃም አማላጅ እስክንልክ ጠላት መደላደልና መከበብ ይጀምር የለም? የሀገራችንን መደፈር ሰምተን ውለን ማደርም አይገባንም ነበር ። ግብጽ ያን ሁሉ አገር አቋርጦ ከደጃፋችን እስኪገባም መቆየታችን ተገቢ አልነበረም ። ለነገር ለነገሩ ግን ወደ ንጉሥ ምኒልክና ራስ አዳል መልእክቱን እንስደድ ። አገር ተደፈረ ብለን እንላክባቸው ፤ ይህን ሰምተው ካስቻላቸው እኛ ምን ቸገረን ፤ አድረው ውለው ያገኙት የለም? እኛ ግን ዛሬውኑ ስንዘምት ይታየኛል" ብለው ለጥ ብለው እጅ ነሥተው ወደ ነበሩበት ተመለሱ ።

ደጃዝማች ኃይለማርያም እንደ ገና ተነሡና ፣

“ይኸ ችኩላ አይታየኝም ፤ ትላንትና ከወንዛችን ድረስ የመጣውን የአጼ ተክለ ጊዮርጊስን ጦር ድል አድርገናል ብለን ነገ በችኩላ ከባሕር ማዶ ከመጣውና ብዙ ሠራዊትና መሣሪያ ከያዘ ጠላት ጋር ብቻችንን ብንገጥም ፣ ለሀገር ታላቅ ውርደት ይሆናልና ይታሰብበት” ብለው እጅ ነሥተው ተቀመጡ ።

በዚህ ጊዜ ሊጋባ አሉላ ሲቁነጠነጡና ሲወራጩ አጼ ዮሐንስ ተመለከቷቸውና ፤

“አሉላ የምትሰጠው ምላሽ እንዳለህ ተናገር” ሲሉዋቸው አሉላ ፈጠን ብለው ከአጼ ዮሐንስ ፊት ቆሙና መላ አካላቸውን አስቆጥተው ፤

“ትላንትና የአጼ ተክለ ጊዮርጊስ ጦር ከወንዛችን ድረስ መምጣቱን ዐውቆ ነው የግብጽ ጦር ዛሬ ከበራፋችን ድረስ የመጣው ። እንግዲህ የምንታገሠውሳ ከአልጋችን ላይ እስኪወጣ ነው? ንጉሠ ምኒልክና ራስ አዳል አንመጣም ፣ እርዳታም አንልክም ቢሉ ልንሸሽ ነው? ወይንስ ጦርነት ልንገጥም ነው ! ዙሮ ዙሮ ዕዳው ዕዳችን መሆኑ ላይቀር ለጠላት ጊዜ መስጠት ትርፉ ምንድን ነው? እኔ ጌታዬን እከተላለሁ ። ከፈቀዱልኝና ከዘዙኝም ቀድሜ እዘምታለሁ ። የፈራ ይቅር ከፈለገም ሸዋ ሒዶ ይጮህ ይግባን ።

‘ሀገር ተደፍሮ ፣ ወገን በጠላት እግር ወድቆ ፣ ‘የወንድ ልጅ ያለህ! የወገን ያለህ!’ እያለ እየጮኸ ውሎ ማደር ይባስ ብሎ ደግሞ ጐጃምና ሸዋ ሒደን ርዳታ እናምጣ ብሎ ማሰብ የቁምነት መሆን ነው ። ዛሬውኑ መረብ ወንዝ ገብቼ ልደር እዘዙኝ ጌታዬ!” አሉና ራቅ ብሎ ቁሞ ከነበረ አሽከራቸው ላይ መግሪያቸውን ነጥቀው ከአጼ ዮሐንስ ፊት በርከክ ብለው ፤

“ተዚያ ተነሥተው እዚህ ቢደርሱ
የበዝብዝ አሽከር ይበቃል እሱ
ጥበጡ ቢመጣ አገር አቋርጦ
ነግ ይመለሳል ዐፈሩን ግጦ
አገር ተደፍሮ ወገን ያለቅሳል
ያስቆጣል እንጂ መች ያስመክራል



ትዕግሥቱ ይብቃ ተነስ ዮሐንስ
በጉበጡ ሠፈር ግባና ተድስ
ከሬትህ ልቅደም እዘዙኝ ግሬ
ቀሳይህ ግበጡን እንባብሬ
ነገ ዕልል ትበል ትኩራ አገሬ
ንጉሥ ማራኪ ከነዘውዱ
የበዝብዝ አሽከር አሉላ ወንዱ ።”

ብለው ፎክረው ከንጉሡ ነገሥቱ እግር ሥር ሲንበረከኩ፣ “ተነሥ ከዐይን ያውጣህ! ይባርክህ” ብለው ከኋላቸው የነበረውን እንግት ጠመንጃቸውን ከአሽከር ተቀብለው ሸለሟቸው ።

ከዚያ አከታትሎ የተነገረውን ፎከራ ሁሉ ፣ ዮሐንስ ከምንተ ፍሬት እንጂ ከልብ ፈንቅሎ የወጣ ስላልሆነባቸው ፣ ለአንድም መኳንንት በባሬ ሰንጥር ሳይሰጡ ቀሩ ።

አጼ ዮሐንስ ዝግጅታቸውን ከአጠናቀቁ በኋላ የጦርነት ዐዋጅ ሲያናግሩ ፤

“ያገሬ ሕዝብ ስማ!

በወሎ በቤገምድር ፣ በጐጃም ፣ በሸዋ ፣ በዳር አገር ያለህ ሁሉ ስማ! የእርስ-በርሳችንን መጋጨት አጥንቶ ጠላት እስከ በራፋችን ደርሷል ። እኔ እንደ ሆንኩ እምነቴ እንዲት ናት ። ነፍሴም እንዲት ናት ። በሕይወቴ ቁሜ የሀገሬን መደፈርና መጥፋት አላይም ፤ አልሰማም ። እኔን ጠልተህና ንቀህ አገርህን አስደፍረህ ዝም ብትል በሥጋህ ትወልድ ፣ በነፍስህ እግዚአብሔር እንደሚፈርድብህ ዕወቅ ፤

ሀገርህን ቤት ንብረትህን ርስትህንና ሚስትህን ፣ የሚያጠፋውን የግብጽን ጦር ልገጥም ሐሸለሙና ተከተለኝ ። እኔም ብወድቅ የጉብዝ እለታህን መርጠህ ተከላከል ። ይህን ቃል ሰምተህ እንዳልሰማህ የሆንክ ሁሉ አንተም ዘርህም ርጉማን ሁን” ብለው ነበር ።

እነሱም “ለሀገራችን ለሃይማኖታችንና ለንጉሡ ነገሥቱ ክብር የማይዘምት ርጉም ይሁን” ብለው አወጁ ። ከዚያ በኋላም አጼ ዮሐ

"እንግዲህ እንደዚህ የመሰለ የሚያኮራ ታሪክ ያለን የጀግኖች ልጆች ነንና የዛሬውንም ጠላት ወደ መጣበት ለመመለስ አይደለም የምንዘምተው ፤ እዚሁ ማስቀረቱ ነው የሚገባን ። የመፈረበትን አቅጣጫ ብዛቱን ወኃ የሚያገኝበቱን ለማምለጥ የሚችልበትን መንገድ ሁሉ ተመልክተው አጣርተውና መርምረው የሚነግሩኝ ታማኞች ሰዎች ልኬ ስለነበረ ፤ ዛሬ ተመልሰው ማነኛውንም ነገር ነግረውኛል ። የመረብን ወንዝ ከተሻገርን በኋላ ጠላትን በሁለት አቅጣጫ እንከበዋለን ። ባንድ በኩል በጊታ ደጃዝማች ወልደሚካኤል የሚታዘዝ ሠራዊት ሲዘምት ፤ ባንድ በኩል ደግሞ ባሻ ገብሩ አባጨቄን ከነሠራዊቱ ይሰለፋል ። ግንባር ለግንባር ደግሞ ራሴ እሰለፋለሁ ።

"በሩቅ ማቅራራት መንጫጫት ዘፈት ያለው ሲወድቅ መደናገጥና መሸሽ እንዳይታይብን ተጠንቀቁ ። ይህን የዘነጋን እንደሆን ጠላት በሩቅ በሚወረውር መሣሪያው ይጠምደናል ። ከዚህ በፊት አጼ ቴዎድሮስ የጉበዝ አለቃ ሆነው ገና በበረሃ በነበሩበት ዘመን ከዚሁ ከግብጡ ጦር ጋር በበጊምድር በኩል ጦርነት ገጥመው ድል ያደረጉትም በዚሁ ዘዴና ጥንቃቄ ነው ።

"ነገ ማታ በንጋዝ አድረን ሌሊት መረብ ወንዝ አድፍጠን እናድርና ጡዋት ሠፈሩን እንከበዋለን " አሉ ።

በዚሁ መሠረት የሊጋባ አሉላ ጦር በሦስት አቅጣጫ ተጉዞ መረብ ወንዝ ላይ አድፍጦ ጡዋት የመረብን ወንዝ ተሻግሮ አስቀድሞ በተወሰነው ስልት መሠረት የግብጽ ጦር የሠፈረበትን ምሽግ ከበበና ጦርነቱን ጀመረ ። የግብጽ ጦር ታጥቆት የመጣውን በወቅቱ ዘመናዊ የነበረውን መድፍና መትረየስ ያስጉራው ጀመር ። የምሽጉ አዛዥ የነበረው የዴንማርኩ ተወላጅ ኩሎኔል አርንድሩፕ በተማረው ወታደራዊ ስልት መሠረት በምሽጉ የነበረውን ተዋጊ አከፋፍሎ ወጊያውን ቀጠለ ። የአሉላ ሠራዊትም በስልቱ በጀግንነቱና በአርጊ ጠመንጃው የጠላቱን ምሽግ ከቦ ያጥቅበው ጀመር ። በአጭር ሰዓት ውስጥ ቁጥራቸው ስምንት መቶ የሚሆኑ የግብፅ ወታደሮች አለቁ ። የአሉላ ሠራዊትም ከመረብ ወንዝ ዳር የነበረውን ጠላቱን ከደመሰሰ በኋላ ፤ ወደፊት ገፍቶ በጉንዳጉንዲ ሸለቆ በምትገኘው



ጉንደት በተባለችው ቀበሌ መሽጎ ወደ ነበረው የግብጽ ጦር ገሠገሠ ። በዚያም ሥፍራ አንድ ሺህ ሦስት መቶ ወታደሮች ያንበሻ አርድ ይዘው ይጠባበቁ ነበር ። አሉላ ከታማኞቹ የመረጃ ሰዎቻቸው ባገኙት ፍንጭ መሠረት ወታደሮቻቸውን ከፋፍለው አሰልፈው ጦርነቱን ገጠሙ ። በዚያም ቦታ ከኢትዮጵያውያኑ ይልቅ የግብጽ ጦር እጅግ ምቹና የተሟላለት ነበር ። ይሁንና የግብጽ ጦር እንደገና ብትንትኑ ወጣ ።

እርግጥ ነው ። በዚሁ ጦርነት ከአምስት መቶ በላይ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች መሥዋዕት ሲሆኑ ፤ ከጠላት ወገን ደግሞ ያለቀው አልቆ ሦስት መቶ የሚሆኑ ሸሽተው አመለጡ ። በግብጽ ምሽጎችም እስከ ሁለት ሺህ አምስት መቶ የሚሆን ስናይደር ጠመንጃዎች ዐሥራ ስድስት ያህል መለስተኛ መድፎች፣ በርካታ ጥይቶች የኢትዮጵያ ሠራዊት አግኝቷል ።

በዚያ ወቅትና በዚያች ቦታ በተደረገው የትንቅንቅ ጦርነት ደጃዝማች ወልደሚካኤልም ከፍተኛ ጀብዱ ፈጽመዋል ። በተሰለፉበት ግንባር የግብፅ ጦር ምሽግ ሰብረው ከገቡ በኋላ በሽሽት ላይ የነበረውንም ጠላት እየተከታተሉ አስቀርተውታል ። ከሰባት መቶ በላይ የሚሆን ስናይደር ማርከዋል ።

በአሉላ አዝማችነት የተሰለፈው የኢትዮጵያ ጦር የግብፅን ምሽግ አጽድቶ ፣ ንጉሠ ነገሥቱን ተቀብሎ ተከራው የጦር መሣሪያ ምርኮውም ከንጉሠ ነገሥቱ ፊት ቀረበ ። ሊጋባ አሉላ በመጀመሪያ የጦር ልብሳቸውን ለብሰው ከአጼ ዮሐንስ ፊት በርከክ ብለው ፤

"ግብጡን ገዳይ ከነጥሩሩ
ከንዱ ብርቱ ልበ-ኩሩ
የጠላት ምሽግ አደባላቂ
ጠላት ከማረ ጠላት ወቂ
የበዝብዝ አሽከር የጦር ክተር
ነጭ ጦር ገዳይ በጡዋት ቀበር
ግበጥ ማራኪ ከነመድፉ
የበዝብዝ አሽከር አሉላ ወንዴ"

ብለው ፎክረው ሲነሡ ፣ አጼ ዮሐንስ ከተቀመጡበት ተነሥተው አሉላን አቅፈው ሳሙዋቸውና ታጥቀውት የነበረውን ሽጉጣቸውን ከወገባቸው ፈትተው ሸለሙዋቸው ።

ቀጥለውም ደጃዝማች ወልደሚካኤል የማረኩትን መሣሪያ ሁሉ አሸክመው ሰናድራቸውን አጳምጠው ይዘው ከአጼ ዮሐንስ ፊት ተንበረከኩና ፣

“ወዲ ሐማሴን የጀግኖች ጀግና
ባጭር ታጣቂ ባለጉተና
አልቀረም ጠላት አገሬን ደፍር
በሠራው ምሽግ አልዋለም አድር
የበዝብዝ አሽከር የበዝብዝ ወንድም
ግብጥ አባራሪ ግድም ለግድም
የበዝብዝ ታማኝ የበዝብዝ ሎሌ
ጠላት ሰባሪ እንደ ብርሌ”

ብለው ሲፎክሩ አጼ ዮሐንስ አቅፈው ሳሙዋቸውና የራሳቸውን እንግት፣ ሸለሙዋቸው ። ከዚያ በኋላ አጼ ዮሐንስ የጦር አለቆቹንና መኳንንቱን ሰብስበው ምክር አደረጉ ። የስብሰባውም ፍሬ ነገር በሠራዬና በሐማሴን ሠፍሮ የነበረውን ርዝራዥ የግብፅ ጦር ጠራርጎ ለማስወጣት እንዴት እንደሚቻል ስልት ለማውጣት ነበር ። በዚህ ጊዜም ሊጋባ አሉላ ፣

“በደጋው ክፍል የሠፈረው ጠንካራ ጠንካራ ምሽግ ሠርቷል። በሩቅ የሚከላከል መሣሪያም ጠምዷል። የውሃና የስንቅም ችግር የለበትም ። ስለዚህ አሁን ፊታችንን ወደ እርሱ ብናዞር ከጭን ቀቱ ብዛት የተነሣ አጠንክሮ ሊወጋን ይችላል ። ይሁንና መቼም ቢሆን ከእጃችን ሊያመልጥ አይቻለውም ። በበጉስና በምጽዋ የሚገኘውን የግብፅን ጦር ገሥግሠን ብንገጥመው ግን ሥሩን ነቃቅለን እንጥለዋለን ማለት ነውና የጀግኖቻችን ወኔ ሳይበርድ ወደዚያው ብናመራ የሚተካም ቢኖር ሳይጠናከር እንደር ስበታለን ። እንደኔ እንደኔ ከሆነ በዚህ ብንስማማና ጉዞውን በአስቸኳይ ብንጀምር ይሻል ይመስለኛል”፡ አሉ ።

“እግዚአብሔር ይባርክህ የሚደገፍ ሐሳብ ነው” አሉ ራስ ባርያውም ቀጠል አድርገው ። “ሲመሆኑስ በበጉስና በምፅዋስ



ምን ያህል ጦር እንዳስቀመጠ የታወቀ ነገር አለ?” ብለው ባል ገዳ አርአያም ጠየቁ ።

“ይኸ እያስቸገረንም በጥቂት ቀናት ውስጥ ልንደርስበት እንችላለን” አሉ ሊጋባ አሉላ ።

አጼ ዮሐንስ ፣ በዚሁ ጉዳይ ላይ ከየመኳንንቶቹና ከየጦር አለቆቹ የተሰነዘሩትን ሐሳቦች ከአዳመጡ በኋላ ፣ ግራ-ቀኙን እየተመለከቱ ፣

“ሐሳባችሁ ሐሳቤ ነው ። እንዳላችሁት በጉስንና ምጥዋን ነቅተን መጠበቅ ይገባናል ። በተለይም ምጥዋ ጉሮሮአችን ናት ፣ ፍጡር የሆነ ሁሉ ጉረሮውን ከታነቀ እስትንፋስ አይኖረውም። በዚያው ያልቅለታል ። ልብ-ብላችሁ እንደሆነ ጠላታችንም ዋናው ዓላማውና ሐሳቡ ይኸው ነው ፣ የኛን ጉረሮ ለማነቅ ነው ። ይህንኑ ሐሳቡን በመረዳታችንም ነው ፣ ይህ ሁሉ ትንቅንቅም ለዚሁ ነበር ። ዛሬ እንደ ተሞከረው ሁሉ ነገም እንዳይደግም ከወዲሁ ነው መሽቀዳደም ። እንግዲህ በዚሁ ሐሳብ ወደ በጉስም ሆነ ወደ ምጥዋ ብንዘምት የሚያርሰውንም ጉዳት አብሮ ማየት ተገቢ ነው ። ምክንያቱም በምጥዋ ስርኳታ የውጭ አገር ሰዎች ይኖራሉ ፣ ጠላት ስንፈልግ እነርሱንም አብረን መውጋታችን ነውና እስቲ ምከሩበት ፣ እንነጋገርበት” አሉ ።

በዚሁ ጉዳይ ምክክር ከተደረገበት በኋላ ፣ ወደ በጉስም ሆነ ምፅዋ የሚደረገው ዘመቻ ለሌላ ጊዜ ተላልፎ ሐማሴን ላይ አንድ ታማኝና ጠንካራ ሰው ተመርጦ የጦር አበጋዝ እንዲሾም ተባለ ።

አጼ ዮሐንስ በተደረገው ምክክር መሠረት ሊጋባ አሉላ ሹም እንዲሆኑ ሾሙዋቸው ።

በዚህም ሹመት የተነሣ በቤተ—መንግሥቱ ታላቅ ጉርምርምታ ተስተጋባ ። በተለይ ልጅ ደበበና ደጃዝማች ወልደሚካኤል ከቅሬታና ከጉርምርምታም ዐልፈው ተቃውሟቸውን በግልጽ አሰሙ ።

«ለአንድ የገበሬ ልጅ የጦር አበጋዝነትን ያህል ሹመት እንዴት ይሰጣል? ከመኳንንቱ የበለጠ ምን መርቷል ?» እነዚህ ቃላት ከቤተ—መንግሥቱ ግቢ ወጥተው ትንፋይን አልፈው በመላዋ ኢትዮጵያ እንዲያስተጋቡ ሆነው ንዝአቸውን ጀመሩ።

በተለይ ደጃዝማች ወልደ ሚካኤልማ ፤

«ለዚህ ነው እንዴ የታገልነውና የደከምነው ? ዘሬን እያወቁ ሥራዬን እያዩ እንዴት በአንድ ገበሬ ልጅ «ታዘዝ» ብለው በላዩ ላይ ይሾሙታል? በእርሱስ ሥር እንዴት ተቀርጦ ይሉኛል! ካሉም ከመሰሎቻቸውም መኼስ ምን ይደረጋል! የአገራችንን በረሃ እንደሙ ያደግሁበት ነው ፤ ዐውቀዋለሁ» ብለው ተነሡ ። ይህ ወሬ ከንጉሡ ነገሥቱ ጆሮ በመድረሱም የማረኩትን የጦር መሣሪያ ሁሉ ለጦር አበጋዙ ለሊጋባ አሉላ እንዲያስረክቡ ታዘዙ ። ከዚያ በኋላ ደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ከአጼ ዮሐንስ ጋር ሆድና ጀርባ ሆኑ ። ጉንደት ላይ መኸነ የነበረው የግብፅ ጦር በጥቅምት ወር ድል ከሆነ በኋላ በታኅሣሥ ወር ላይ ደግሞ የተዋረደ ክብሩን ለመመለስ ሲል እስከ ፲፭ ሺህ የሚገመት ጦር እጅግ ዘመናዊ መሣሪያ ታጥቆ ምፅዋ ገባ ። ምፅዋ እንደገባ በመጀመሪያም አጼ ዮሐንስ እጅግ ተናደዱ ። ምፅዋ ለንጉሡ ነገሥትነታቸው ጽናትና ብርታት የጦር መሣሪያ የሚያስገቡበት ዋናው በሬቸው ነበረችና ሊጋባ አሉላ ዝግጅታቸውን አጠናቀው ከመቀሌ ወደ ሐማሴን ከመሻገራቸውም በላይ በፊት ምፅዋ የደረሰው የግብፅ ጦር ንሥማሥ የመረብን ወንዝ አካባቢ ያዘ ። በዚህ ጊዜ አጼ ዮሐንስም ሌላ ወሬ ደረሳቸው ። «ደጃች ወልደ ሚካኤል ሁለት ሺህ ጦር አስከትለው ለግብፅ ጦር ገቡ ። » በዚህም ነገር እጅግ አዘኑ ። በጥቅምት ወር በተደረገው ጦርነት ለሀገሩ ነጻነትና ክብር ተሰልፎ የግብፅን ጦር ያርገበገበ እንደ ወልደ ሚካኤል ያለ ጀግና ወትሮ ሳይደር በታኅሣሥ ወር ከነሠራዊቱ ለጠላት እጁን ሲሰጥ በግብፅ ሠፈር ደስታ ፤ በዮሐንስ ቤተ—መንግሥት ደግሞ ቅሬታንና ሐዘን አስከተለ ።

«ከእንግዲህ ወልደሚካኤልን ለመመለስ ምን የሚደረግ ሥራ አለ? ምን ታስባላችሁ?» ብለው አጼ ዮሐንስ መኳንንቶቻቸውን ምክር ጠየቁ ።



«የዮሐንስን ካባና ላንቃ ወርውሮ የግብፅን ጥብቆ እጥልቆ፤ የዮሐንስን ግቢ ጠልቶ፤ ሆዱን ከድቶ ከሔደ በኋላ ትላንት የወጋውን ጠላት ዛሬ ማረኝ ብሎ ከገባለት በኋላ ምን የሚደረግ ነገር ይኖራል? እንዲያው ከትዝብቱ ያህል ግን የአባታችንን ቃል በታማኝ ሰው እንላክበት በኋላ ትውልድ እንዳያዝን ለማለት እንጂ ፍሬ የሚኖረው እንኳ አይመስለኝም» ሲሉ ባልገዳ አርአያ ፤

አሉላ ቱግ ብለው ተነሡና ቀጥ በተሟሟነው አነጋገር፤

«ይፈልድልኝ ዕረፍት እንጂ ጉዳትነት የለውም ፤ ከመካከላችን ሆኖ በንቀትና በጥላቻ ከሚመለከተን መሔዱ ይሻለናል ። አንድ ወልደሚካኤል ቢሔድ ሐማሴን እንደሆነች ሺህ ወልደሚካኤል ወልዳለች ፤ እርሱ ያሳዘናል ፤ እርሱ ለዘሩ ለትውልዱ ያሳፍራል እንጂ አገራችን ጀግና እንዳታጣ ነው! ከዮሐንስስ ቤት አሽከር እንዳይጠፋ ነው! ለሁሉም በሚያምንበት በጸጋን ይሁንብዎ ፤ ቅር አይበልዎ እኔም ልሒድና የጠላትዎን ክምር ላጥፋዎ!» አሉ ፉከራም እየተሟሟናቸው ።

«ለመሆኑ ምን ቀረብኝ፤ ምን ጉደለብኝ ብሎ ነው በዚህ በክፉ ቀን ከድቶን የሔደው፤ ምክንያቱ ታውቋል?» ብለው ጠየቁ ራስ ባርያው ።

«ዓመል ነው የጎደለው፤ ታማኝነትና ትዕግሥት ነው የጐደለው የአባቱን አገር አልነግሠውም ብለሽልማት አላስተረሁት፤ ምን ጉድለውበት? ምንስ ቀርቶበትን?» አሉ አጼ ዮሐንስ እንደ መተከዝ ብለው ።

«ድነት የማረኩትን መሣሪያ ለምን አስጠባ ተባልኩ ብሎ ቅር ተሰኝቶስ እንደሆነ?» አሉ ባልገዳ አርአያ ።

«ምን ያደርግለታል መሣሪያ ማከማቸት ለጠላት አልተነሣበት ፤ ሁለት ሺህ ጦር ሙች እንስጠውና ፤ ደግሞም እኔ ዮሐንስ የመግሬያ ደግ አይደለሁምን? አነሰኝ ይጨመርልኝ ቢለኝ እልከለከለው ነበር» ብለው ንጉሡ ነገሥቱ ራሳቸውን እየወዘወዙ ከጎረፉቸውን ሲነኩ ፤ አሉላ ከተቀመጡበት ተነሡና ፤

«የጅግና ድሃ አይደሉም ጌታዬ ፤ ወርቅ ትንፋሽምን ብቻ የሰሙኝ ዛሬውን ልገስግሰበት» ቢሉ ፤ ባልገዳ አርአያም እንደ አሉላ ቁጣቸው እየተናናነቃቸው ፤

«ቀስ ብል አትቸኩል ፤ በመጀመሪያ ወልደሚካኤልን ለመመለስ የሚቻልበትን ብልሃት ብንፈልግለት ይሻላል» አሉ በድሮው አሽከራቸው ላይ ዐይኖቻቸውን አፍጥጠው ።

አሉላም የባልገዳ አርአያን ፍጥጫ ገሸሽ አድርገው ፤

«በሀገር ላይ ጠላት ሠፍሮ መድፍ እነጣጥርብን የከዳና ያኮረፈ እንዴት እንለምናለን? ጀግና ሞልቶ መሣሪያ ተከምሮ ምን ችግርን ነው? ኢትዮጵያን ከድቶ ዮሐንስን አታልሎ ፤ ከጠላት የተወሸቀ ሰው ለምናና አባብሎ ለመመለስ ማሰብ ውርደት አይደለም? ወልደ ሚካኤል ረክሷል ከእንግዲህ ወዲያ ከዮሐንስ ግቢ ገብቶ ከኛ ጋር ማዕድ ሊቀርብ አይሆንለትም» አሉ የብስጭት መንፈስ እየተጫጫናቸው ። «ያኮረፈ ታርቆ ቢመለስ ጉልበት ይበረታና ጠላት ያፍራል ፤ አንድነት ይጠነክራል» አሉ አርአያ ድምፅም የድሮ አሽከራቸውን በአፈጠጡ ዐይኖቻቸው እየገረፉ ። «ብዙ ያኮረፈና የከዳ ለምኖ ጦርነትን ያህል ከባድ ጉዳይ ከመግጠም ታማኝ ወኔው የጋለ ጥቂቱ ይበቃል ጌታዬ» አሉ አሉላ በበኩላቸው ለመቆጣት እየከጀላቸው ። በዚህ ጊዜ አጼ ዮሐንስም ከላያቸው ላይ ሠፍኖ የነበረውን እርምም ገፈፉና ፤ «ጌታ ግዴለም የአሉላን ሐሳብ ችላ እንበለው ፤ ያኮረፉትንም ሆነ የከዱትን ኢትዮጵያ ትፋረዳቸው ። እኛ ግን በእምነታችን ጸንተኔን በቆራጥነት እንዝምታለን ። ፈጣሪያችንም አሳልፎ ለጠላታችን እንደማይሰጠን እንተማመናለን» ብለው ወደ አሉላ ደግሞ ዞር አሉና ፤

«ነገሩን ዐዋጅ ይነገራል ። ከዐዋጁም በኋላ ቀድመህ የምትዘምተው አንተ ነህና ተዘጋጅ» ሲሉዋቸው አሉላ ከንጉሠ ነገሥቱ ፊት በርከክ አሉና ፤ «እኔ አሽከርህ ፤ እኔ ታማኝህ ፤ እኔ ምንተ አሽከር አላሳፍርህም ፤ ለጠላቱ ጀርባዬን አላሳይም ፤ እጁንም አልሰጥም ፤ ክብርህን አላስደፍርም» ብለው የንጉሠ ነገሥቱን ቀልበት ስመው ሲወጡ ፤ «ትላንት የተወለደ ልጅ ፤ ትላንትና በእጃ



ቹን እያጉረስን ያሳደግነው ልጅ ይህን ያህል የአእምሮ ብሩህነት ፤ ይህን ያህል ቆራጥነት ፤ ይህን ያህል ወንድነት ለሰጠው የሚያስገርም ነው ። አሁንም እግዚአብሔር ቀኙን ይስጠው» ቢሉ ባልገዳ አርአያ ፤ ንጉሠ ነገሥቱ ደግሞ ቀበል አደረጉና ፤

«እግዚአብሔር ክንዱን ለማጠንከር ሲል የፈጠረልኝ ልጅ ነው ፤ ታዲያ ምን ይሆናል? ብቻውን ሆነ ። እርሱን የመሰሉ ሁለትና ሦስት ቢኖሩኝ ኑሮ በየሰበቡ የሚያኮርፍ ፤ የሀገሬን ዐፈሩዋን የሚቆነጥር ባልነበረም ነበር ። ታዲያ ምን ይሆናል? ለመድኃኒትነት የተፈጠረ እርሱ ብቻ ሆነ» አሉና አጼ ዮሐንስ ትክዝ ብለው ቆይተው ፤ «ዳሩ እርሱንስ ቢሆን ቀናተኛና ምቀኛ አላስቆም ፤ አላስቀምጥ ብሉት የለም?» ሲሉ ባልገዳ አርአያ ቀበል አደረጉና ፤

«ይኸውኮ ነው ያበረታው ፤ ያለዚያማ ዋዘኛ ፈዘዘኛ ይሆን ነበር ። ታዲያ እንዲህ የመሰለውን ባለሙያ ካልጠበቁት የከፋ አወዳደቅ ይወድቃልና እንተው ጠብቀው ። ጥንቱንም ላንተ ሳሳልፈው ከጠበቅሽው ይጠብቅሃል ብዬ ነው» አሉዋቸው ።

በጥቅምት ወር 1866 ጉንደት ላይ አንድ ሽክላ የተሰባበረበትን የጦር ኃይሉን ክብር ለማደስና እንክትክት ብሎ የወደቀውን የመንግሥቱን እቋም ለመጠገን ሲል ቀዲብ እስማኤል በዚያው ዓመት በየካቲት ወር ላይ ለሁለተኛ ጊዜ በልጁ ዘሙለይ ሐሰን ፓሻ ጠቅላይ አዛዥነትና በምርጥ ምርጥ አውሮፓውያንና ግብፃውያን የጦር መኰንኖች አዋጊነት የላከው ቁጥሩ ወደ ኻያ ሺህ የሚጠጋው ጦሩ ከአሥመራ በስተደቡብ ዐርባ ኪሎ ሜትር ጉራዕ ከተባለው ቦታ ደርሶ ምሽጉን በሁለት ቦታ ላይ አጠንክሮ ሠራና ሠፈረ ። በዘመኑ ግብፅ አምስት መቶ ሺህ ፓውንድ ስተርሊንግ ወጪ አድርጋ የላከችው ጦር በዘመኑም ተሻሽሎ የተሠራውን ልዩ ልዩ ከባድና ቀላል መሣሪያ የታጠቀ ነበር ።

አጼ ዮሐንስ ፤ በዐዋጅ ያስከተቱትን ሞፈር ሰቀል ጦር አዘጋጅተው በግንባር ቀደሙ አዝማች በሊጋባ አሉላ ያዘመቱት ጦር ጉራዕ ላይ ደረሰና ከመሸገው ጠላቱ ጋር ጦርነቱን ገጠሙ።

ምንም እንኳን ፤ ከቀበሌው አቀማመጥ በተጨማሪ የተሠራው ምሽግ እጅግ ጠንካራና በቀላሉ ለጥይትም ሆነ ለወታደር የማይደፈር ቢሆንም ፤ በዘመኑ ዘመናዊ የነበሩትን መድፍ ፤ መትረየስና ጠመንጃ በምሽጉ ውስጥ የጠመዱ ቢሆንም ፤ በዘመኑ ዘመናዊ የጦር ትምህርት የተማሩ አዝማቾች ቢኖሩትም የግብፅ ጦር የኢትዮጵያን ጀግኖች ወኔና ቅልጥፍና ሊመክት ባለመቻሉ በግንባር ቀደሙ በአሉላ ሠራዊት እንደገና ፍርክስ ክሱ ወጣ ። ዋናው የጦሩ አዝማችም ተማረከ ። የተረፈው ጥቂት ወታደርም መሣሪያውን እየጣለ የዘመናችንን ትሬንታኳትር በሚያስንቅ ፍጥነት እየተሽቀዳደመ አመለጠ ።

በዚህም ጦርነት ግብፅ ዐሥራ አምስት ሺህ የሚሆኑ ወታደሮቿን አጥታለች ። በጦር መሣሪያም በኩል ሠላሳ ዘጠኝ ከባድ መትረየሶች ፤ ዐሥራ አምስት ሺህ ልዩ ልዩ ጠመንጃዎች ሲማረኩባት አርባ አርባ ሺህ የሚሆኑ ግመሎችና በቅሎዎችም አልቀውባታል ።

በዚያ ዕለት በጦርነቱ ከወደቁትና ቁጥሩ እስከ ሁለት ሺህ ያህል ይሆናል ተብሎ ከተገመተው የኢትዮጵያ ሠራዊት መካከልም ፤ «የባዕድ መንግሥት ጦር አገሬን ሲረግጣት አላይም አልሰማም» ብለው ከጦሩ ጋር ተሠልፈው ሲያዋጉ ፤ የሚሸሸውን ሲገዝቱ የነበሩት አቡነ አትናቴዎስ ይገኙበት ነበር ። ሊጋባ አሉላ ፤ በግብፆች ምሽግ ዙሪያ እየተዘዋወሩ የጀግኖቹን ሬሳ ሲያሥሡም የታላቅ ወንድማቸውን የባሻይ ገብረ ማርያምን ሬሳም ከአንድ ዶጉራ ሥር በናድሩን ወደ ጠላቱ እንዳነጣጠረ ወድቆ አገኙት ። ብድግ አድርገው ተመለከቱት ። ግንባሩን ከሁለት ላይ ተመትቷል ። በደም የተበከለውን ጀግና ሬሳ ዕቅፍ አድርገው የዕንባ ዘለላዎቻቸውን ሲያወርዱ ወታደሮቻቸው ደርሰው ከሬሳው ጋር ሲያላቅቋቸው ፤

«ታሪካችን ይኸው ነው ። እየማሉ መውደቅ ነው ። የክብርና የመሥዋዕትነት ሞት ማለትም ይህ ነው ፤ በክብር ተደመኝ! እንኳን በጀርባው በኩል ተመትቶ አላገኘሁት!» ብለው በግል አሽከሮቻቸው አሸከመው ወደ ትውልድ መንደራቸው ወደ መንዊ አስወሰደው ቀበሩ ።



በዚያ ጦርነት የወደቁት ኢትዮጵያውያን ደምና አጥንት በዚያ ጦርነት በልበ—ሙሉነት የተዋጉት ኢትዮጵያውያን ጀግንነት ፤ በዚያ ጦርነት ላባቸውንና እንባቸውን ያፈሰሱ ኢትዮጵያውያን ድካምና ጥረት ፤ በዚያ ጦርነት ለዘመተው ሠራዊት በገንቱ የሰንቁ ኢትዮጵያውያን ደጀንነት ፤ በዚያ ጦርነት ለዘመተው ሠራዊት ምግብ ውኃው ወግ ተድተው ያቀበሉ ኢትዮጵያውያን ጭንቀትና ጥበት ፤ ሁሉ ተዳምሮ በግብፅ መዳፍ ልትገባ የነበረችውን ኢትዮጵያን ታድጎ በዘመናዊቱ ኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አንጸባራቂውን ምዕራፍ ለመክፈት የተቻለው በዚያ ጦርነት ውጤት ነው ።

ያ—ጦርነት በተለይ የአሉላን ማንነት በይበልጥ አጉልቶ አሳየ ። ከዚያ ጦርነት በኋላም ነበር አሉላ «ጥሩራው አንበሳ» የሚል መገላ ከጦር አበጋዝነቱ ላይ የተጨመረላቸው ።

«ለጌታ የጠላት ድግስ ማቆየት አይገባም» ብለው የግብፅን ጦር በመጀመሪያ ገጥመው እንደበታተኑት በራሳቸው በንጉሥ ነገሥቱ የሚመራው የኢትዮጵያ ጦር ከመድረሱ በፊት ባስገኙትም ውጤት በአጼ ዮሐንስ ዘንድ ልዩ ተወዳጅነትና ተደማጭነት አግኝተውበታል ።

አጼ ዮሐንስ ከጉራዕ ጦርነት በኋላ ፤ ሐማሴን ውስጥ ሰንባብተው ወደ ዐድዋ ተመልሰው መኳንንቶቻቸውንና የጦር አበጋዞቻቸውን ፤ በዐጥጂ የከተተውን ጭፈር ስቀል ሠራዊታቸውን ሰብስበው ፤

«ለዚህ ጦርነት ከወሎ ፤ ከቤጌምድር ፤ ከጐጃምና ከሸዋ የመጣችሁትን ጀግኖች ቆራጥነት ትውልድ የማይረሳው ነው ። ከእንግዲህ ወዲያ የአገራችን በሩቅ ሲደፈር እናገኘነም ልጆቻችንም ትጠራሳችና ችላ እንዳትሉዋት አደራ ! በመሬት አደራ በሰማይ» ብለው ኢትዮጵያን ለኢትዮጵያውያን አደራ ሰጥተው ሠራዊታቸውን አሰናበቱ ።

ምንም እንኳን ፤ አጼ ዮሐንስ ጉንደትና ጉራዕ ላይ የግብጽን ሠራዊት ሁለት ጊዜ ጦርነት ገጥመው ድል ቢያደርጉትም ፤ ግብፆች በምዕራባዊና በምሥራቃዊው ሰሜን ግዛት በአንዳንድ በታዎች ላይ ተበታትነው ይኖሩ ስለነበርና በወትሮም አውሮፓውያን

በኢትዮጵያ ላይ የነበራቸውን ልዩ ትኩረት ተረድተውት ስለ ነበረ ፣ የሀገሪቱን ዳር ድንበር በሚገባ ለመጠበቅ እንዲቻል «የትራውን አ/በሳ » «ራስ» ብለው የሐማሴን ገዥ አድርገው ሾሙዋቸው ።

አሉላ የራስነት ማዕረግ ባገኙበት ዕለትም ባደረጉት የሹመት ማስመረቂያ ግብዣ ላይ ከነበሩት አዝማሪዎች አንዱ ተጥሎ ያለውን ግጥም አበረከተ ።

«ዕልል ይሉ ነበር መረብ ጉንዳጉንዴ
በግብፅ አንገት ቢሰት ያሉላ ጉራዴ
ያሉላ ጉራዴ ይቀላል ስለቱ
ሐበሻ ጋሻን ማርኮ ሲያጠልቀው በንገቱ ።
አሉላ ስጊያው ለዮሐንስ አልጋ
ድል በቀኙ ነበር በነጋ በነጋ»

በዚህ ጊዜ አሉላም ለአዝማሪው አንድ ስናድር ጠመንጃ ሸለሙት ።

ራስ አሉላ ፣ በድል አድራጊው ሠራዊታቸው ታጅበው በታላቅ ግርማና አስፈሪነት አሸብርቀው በየደረሱበት ሆታና ዕልልታ እያስተጋባላቸው የመረብን ወንዝ ተሻግረው ድባርቅ ከተባለችው ጥንታዊት መንደር ሠፈሩ ። ሕዝቡንም ሰብስበው ግብር ካገቡ በኋላ ቀጥሎ ያለውን ዐዋጅ አናገሩ ።

«ጀግናው ያገሬ የሐማሴን ሕዝብ ስማ!

በድሮ ዘመን የቱርክ ጦር እስከዚህ ድረስ መጥቶ ያወረደውን ጥፋት ታውቃለህ! ቱርክ ቤትህን እያቃጠለ ሚስትህን እየቀማ እያረከሰ የፈጸመብህን ግፍና ያደረሰብህን ውርደት ታውቃለህ ። የሀገሩ መደፈር የሕዝቡ መዋረድ ያስቆጣው ስመጥሩው ጀግናው ዕቁበ ሚካኤል ጠጸሬ የተባለው ልጅህ ስማኒያ ጀግኖች አስከትሎ በመንገድ ሸምቆ ገፈኛውን የቱርክ ጦር ገጥሞ እስከ ምዕዋ እንዳባረረው ታውቃለህ ። ከዚያ በፊትና



ከዚያም በኋላ ነገሥታቱ ያደረጉትን ጦርነት ሁሉ ታውቃለህ ፤ ዛሬም የግብፅ ጦር እንደ ቱርክ ጦር ቤትህን ንብረትህን ሚስትህን ሊቀማ መጥቶ የደረሰበትን ውርደት ይኸው አይተኸዋል ፤ ሰምተኸዋል ።

«በር እንዲጠብቅ ፣ ሀገርና ሕዝብ እንዲያስከብር ከንጉሠ ነገሥቱ አደራና ሹመት የተቀበለው ደጃዝማች ወልደሚካኤል አገሩን ከድቶ ከጠላትህ ከግብፅ ጋር ተሰልፎ ወግቶን ጌቶቹን ለናስቀራቸው እርሱ ፈርጥጦ አምልጧል ። ይህም ሳይበቃው ንጉሠ ነገሥቱ የሾሙዋቸውን ደጃዝማች ኃይሉን ከመንገድ ላይ ሸምቆ ገድሏቸዋል ።

«አሁንም በሐልሐልና በበጐስ ውስጥ ሆኖ ሕዝብ እያስጨነቀ የግብፅን ጦር ለማስመጣት የሚሠራውን ግፍ ሁሉ የምትሰማውና የምታየው ነው ። እኔም እርሱን ለመያዝ በገባበት እገባ ለሁና ገበሬም ሆንክ ነጋዴ ፀርፈህ ረግተህ ሥራህን ሥራ ። ወልደ ሚካኤልን የተከተልክ የኔም ፣ የዮሐንስም ፣ የአገርህም ጠላት መሆንህን ዕወቀው » አሉ ።

የራስ አሉላን ዐዋጅ የሰማው ሕዝብም በዕልልታ ተለያየ። ደጃዝማች ወልደሚካኤልም በበኩላቸው የራስ አሉላን ዝናና ዐዋጅ ከምንም የማይቆጥሩት መሆናቸውን ለማሳወቅ ከቆላው ቀበሌ ወደ ደጋው ሐማሴን ወጥተው ሕዝቡን መዝረፍ ጀመሩ።

ራስ አሉላ ፣ የሕዝቡን ሁኔታ እየተከታተሉ ወታደራቸውን እያዘጋጁ ወልደሚካኤልም በእርቅ እንዲገቡላቸው ውስጥ ውስጡን እየተላላኩ ፣ ሕዝቡ በእርሳቸውና በንግዱ ሥራው ላይ ብቻ እንዲያተኩር እያደፋፈሩና እየመከሩ ቆዩ ። መቀመጫቸውንም ከድባርዋ ወደ አዲ ተክላይ አዛወሩ ። ደጃዝማች ወልደሚካኤል በየወረዳውና በየመንደሩ እየተዘዋወሩ ከሚፈጽሙት ዘረፋና ቅሚያ የተነሣ ሕዝቡ በመቸገሩ ከያለበት እየነቀለ ወደ ራስ አሉላ ሰፈር መከማቸት በመጀመሩም ራስ አሉላ በይበልጥ እየተቸገሩ ሔዱ።

የደጃዝማች ወልደሚካኤልንም አድራጎት ለመግታት ዋና ዋናዎቹን የጦር አለቆቻቸውን ሰብስበው ፣ «በአሁኑ ወቅት ያጋጠመን ችግር የተደራረበ ነው ። በዚህ በኩል ወልደሚካኤል

በሕዝቡ ላይ የሚያደርሱትን ችግር ታውቃላችሁ ። ጉዳያችን ምዕዋ ላይ ሆነው እርስትንና ሌሎችንም ባላባቶች እያታለሉ መሬቱንና ገንዘብ እየሰጡ የሚያሰሩ ጅሙበን ግፍ እየበዛ መጥቷል። በዚህ በኩል ያለን ችግር ይህ ሲሆን፥ በንጉሡ ነጋሪቱም በኩል ሌላ ችግር አለባቸው ። ንጉሥ ምኒልክ «ሌሼ አትብሩሉ ወይ አልገባም » ብለው ያልጠቁት ነገር ባለመኖሩ ጉዳዩ አሳሳቢ እየሆነ ተገኝቷል ። ምናልባት ወደ ሸዋ የምንሔድ ከሆነ ደግሞ፥ በዚህ በኩል ያለውን ችግር እንዳለ ትተነው መሔድ አይቻለንም። ጉባያችን በምዕዋ ወልደ ሚካኤልን በሐማሴን አስቀምጠን ብንሔድ ያው የትላንቱ አልቂት ለምስተኛ ጊዜ መድረሱ የማይቀር ነው ። እንግዲህ በየ በኩላችሁ የሚታያችሁን ሐሳብ እንድትነግሩኝ ብዬ ነው የጠራኋችሁ» አሉ ።

ስደቲታዎች ያሀል ዝምታ ሆነ ። የጦር አለቆቹ የእርስ በርስ መተያየትና መጠቃቀስ ጋብ ሲል ብላታ ገብሩ አባ ጨቀን ተነሡና፥

«ደጃች ወልደ ሚካኤል በሕዝቡ ላይ ይሆን ሁሉ ግፍ እያስፈጸመ በዝምታ የምናየው ለምንድን ነው? ይኸውና ሕዝቡ ከየመንደሩ ጀኸቶ እዚሁ ሠፍሯል ። የንጉሥ ምኒልክ ሁኔታ ቁርጡ እስኪለይ ድረስ ትላንትና አባቶቻችን ከቱርክ ጋር ዛሬ ደግሞ እኛ ከግብፅ ጋር ይሆን ሁሉ ደም ተፋሰናል ። ታዲያ አሁን ደግሞ ደጃች ወልደ ሚካኤል ይሆን ሁሉ ግፍ ሲሠሩ እያየን መዝግየቱ አግባብ ስላልሆነ፥ ከደጃች ወልደ ሚካኤል ጋር ጦርነት ብንገጥም ይታየኛል» አሉ ።

ብላታ ገብሩ አባ ጨቀን የራስ አሉላ የጦር አበጋዝ ናቸው። ከአዴ ተክለጊዮርጊስ ጋርም ሆነ ከግብፅ ጦር ጋር በተደረገው ጦርነት ባላቸው ጀግንነትና ባስቆጠሩት ምርኮ «የአሉላ ቀኝ እጅ» እየተባሉ መጠራት ጀምረዋል ። በዚያች ዕለትና በዚያም ስብሰባ ያቀረቡትን ሐሳብ የጦር አለቆቹ ስለተስማሙበት፥ ራሳቸው በቲ ጦር ይዘው ደጃዝማች ወልደ ሚካኤልን እንዲከታተሉ ታዘዙ ።

በዚያ ወቅት ደጃዝማች ወልደ ሚካኤልም በበጉዑና በምዕዋ የነበሩት ጉበኞች በሚሰጡዋቸው ድጋፍ እየተረዱ ከየመ



ንደሩ የዘረፉት ቀጥሩ ከአምስት ሺህ በላይ የሚሆን የእርድ ከብት አከማችተው በጊንዳዕና በምዕዋ መካከል በሚገኘው አይለት ከተባለው ቀበሌ መፍረው ነበር ።

ራስ አሉላም በዚያ ወቅት ከዐሥር ሺህ በላይ የሚሆን ሠራዊት ነበራቸውና ከዚሁ ጦር ላይ አንድ ሺህ የሚሆን ባለበናድር ጦር በብላታ ገብሩ አዝማችነት ደጃዝማች ወልደ ሚካኤልን እንዲወጋ ወደ አይለት አዘመቱ ። ተገለውም ወልደ ሚካኤል ወደ በጉስ ሸሽተው እንዳያመልጡዋቸው ሲሉ መንገዱን ራሳቸው ራስ አሉላ ዘጉባቸው ።

በብላታ ገብሩ የሚመራው ጦር በጊንዳዕ በኩል አድርጎ ወደ አይለት ሲወርድ ደጃዝማች ወልደሚካኤል ተመልክተውት ኑር አትግማቸውን ገመዱና ጓዛቸውን ጥለው ያረት ጦር ብቻ አስከትለው አመለጡ ። ብላታ ገብሩም ከደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ሠፈር እንደ ደረሱ የተከማቸውን ንብረትና የተሰበሰበውን የእርድ ከብት እንደዚሁም ኻያ የሚሆኑ ግብየውያንና አንድ ለበንስ ሚቸል የሚባል አሜሪካዊ ጭምር ነድተው ወደ አዲ ተክላይ ተመለሱና ለራስ አሉላ አቀረቡ ። በዚህ ጊዜ በምዕዋ የነበረው የግብፆች ወኪል አትግማን ፓሻ የሚባል የራስ አሉላ ጦር እስከ አይለት መውረዱና ግብፃውያንንም ማርኮ መውሰዱ አለአግባብ መሆኑንና፥ «የግብፅንም ግዛት እንደ ደፈሩ ይቆጠራል» ብሉ ቢልክባቸው አሉላ እጅግ ተቆጥተው፥ «እንኳን አይለት ራሱዋ ምዕዋና ባሕሩ ጭምር የኢትዮጵያ አካል መሆኑን እንዴት ዘነጋህ? አሁንም ወንድ ከሆንክ ከምዕዋ ወጥተህ አይለት ድረስ እንገናኝ» ብለው ላኩበትና ጦር አዝምተው አይለት ላይ አሠፈሩበት ። በዚያው ሰሞን ራስ አሉላ አዲ ተክላይ ውስጥ ከአሥሩዋቸው መጠነኛ እልፍኝ ከአዳራሽ ቤታቸው ታኅ ላይ በወንበር ተቀምጠው ከደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ሠፈር የተማረከውን አሜሪካዊ አስጠርተው፥

«ይኸ ሁሉ ጓዝህ ምን የምትሠራበት ነው?» ብለው ጠየቁት በጥርጣሬ እያስተዋሉት ። «እኔ የመሬትን የተፈጥሮ ጠባይ በውስጡ የሚገኘውን ማዕድናት ዐይነቱን የማጠና ስለሆንኩ ለዚሁ ሥራዬ የሚረዳኝ ነው» አላቸው በፍርሃት ተውጦ ። «ታዲያ

ለግብፅ ወታደሮች እንደምን አጋዣቸው ሆነህ መጣህ?» አሉት ቆፍጠን ብለው ።

«የእነርሱ አጋዥ ሆኘ አይደለም የመጣሁት ፣ ተቀጥሬ ጥቅም እየሰጡኝ ነው» አለ አሜሪካዊዉ ፈገግ እያለ ።

አገርህ ከእነርሱ አገር እጅግ ሩቅ ነው ፣ ለጥቅም ስትል ብቻ እንዴት እዚህ ድረስ ትመጣለህ?» አሉት ጥርጣሬያቸውን በአመለካከታቸው ጭምር እየገለጹት ።

«አገሬ እርግጥ ሩቅ ነው ፣ ዋናው ጉዳይ ደግሞ እስከዚህ ያመጣኝ ጥቅሙ ብቻ ሳይሆን የዚህችን ሀገር መሬት ሁኔታ ለማጥናትና ለማወቅ ፈልጌ ነው ። እኔን የመሰሰሉ ዕውቀት ፈላጊዎች ሁሉ በየአገሩ ይሔዳሉ ። እኔም ወደዚህ አገር ስመጣ በምፅዋና በአይለት ብቻ ሳይሆን በዚህ በእርስዎ አገርም ያለውን ሁሉ ለማወቅ እንደሚረዳኝ ተማምኘ ነው የመጣሁት» አላቸው ፈገግታውን ወደ ሣቅ ለማሸጋገር እየተጣጣረ ።

«ከዚህ ላይ ተሳስተሃል» አሉና ራስ አሉላ እንደ መቆጣትም ቃጣቸውና ለደቂቃዎች ያህል ዝም ብለው ቆይተው ንግግራቸውን እንደ ገና በመቀጠል ፣

«ተሳስተሃል ማለቴ በሌላው ሳይሆን በአገሩ ጉዳይ ነው ። ምፅዋም ሆነ አይለት የኢትዮጵያ ግዛትና ርስት ነው ። ግብጾች በጉልበታቸው ተማምነው ነው የሠፈሩበት ። ለወደፊቱም ሲሆን በኔ ክንድ ካልሆነም በትውልድ ክንድ በጉልበት የያዙትን አገራችንን በጉልበት ይለቃሉ» አሉት ቁጣቸው መላ ገጽታቸውን እያላበሰው ።

«ይሁን ራስ ይሁን» አለና ሚችል የራስ አሉላን ቁጣ ለማብረድ ፈገግ ፈገግ እያለ ንግግሩን ቀጥሎ ፣

«እኔ አገሩ የማንኛችሁ እንደሆነ ብዙም አላወቅሁም ፤ ግን በመጣሁበት ነገር ከሆነ» ብሎ ንግግሩን ሳያጠቃልል አሉላ እንደገና አቋረጡትና ፣

«ታዲያ በምፅዋና በአይለት ምድር ምን ምን ነገር አገኘህበት? ወርቅ የለውም?» አሉት ።



«በቅርቡ ነው የመጣሁት ፤ ጥናቱንና ምርምሬን ገና በሚገባ አልጀመርኩም ። ግን በመጠኑም ቢሆን እንደ ተረዳሁት ብዙ ሀብት ሳይኖርበት አይቀርም» አላቸው ።

«በል እውነቱን ንገረኝ በምፅዋ ያሉት ግብጾች ብዙ መድፍና ጠመንጃ እንዳላቸው እሰማለሁ ፤ እውነት ነው? ሐሰት?» ብለው ጠየቁት ዘና ብለው ።

ሚችል ዐይኖቹን እያስለመለመ ሲያስብና ሲተክዝ ቆየና ፣

«በሠፈራቸው ውስጥ ብዙ አልቆየሁም ፤ ግን እንደ ተረዳሁት ከሆነ ብዙ መሣሪያ ያላቸው አይመስለኝም» አለ ።

«የወታደራቸው ብዛትስ ምን ያህል ይሆናል?»

«ከጦርነቱ ወዲህ ብዙም ወታደር አላስመጡም ፣ ያላቸው ጥቂት ነው ።”

“ሐሳባቸውንስ አልነገሩህም? ወደዚህ ወደ ደጋው ሊወጡ አይመኙም?»

«ሁለተኛስ የሚመጡ አይመስልም ።»

«ምን ሁለተኛ ትላለህ? ሦስተኛ በል እንጂ! ሁለተኛማ መጥተው የጀግኖች ክንድ ቀምሰዋል» አሉት ኮራ ብለው ።

«አዎ ልክ ነዎት ፣ እውነትዎን ነው ።»

«እንግዲህ እናንተ ፈረንጆች ግብፆችን ስትረዱ እኛን ለምን አትረዱንም?»

«በምን በምን እንድንረዳችሁ ትፈልጋላችሁ?»

«አሁን አንተ ለእነርሱ የምትሠራውን ሥራ ለኛስ ብትሠራልን እንጠላ ይመስልሃል? ሌላም ሌላም ጥበብ አላችሁ፤መድፍ፣ ጠመንጃ ፣ መነጽር ፣ ሌላም ብዙ ብዙ ጠቃሚ ጥበብ አላችሁ ። ከጥበባችሁስ ብታካፍሉን እንጠላ ይመስልሃል?» አሉት ።

«እርግጥ ነው ፣ ብዙ ብዙ የጥበብ ሥራዎች እንችላለን ። ታዲያ እርስዎና ፣ ንጉሥዎ ከፈቀዳችሁ የምትጠይቁንን ልንሠ

ራሳችሁ እንችላለን» አለ አሚሪካኑ ፤ «ጥበብ ከፈለግ በኔ ላይ ሊጠቀሙብኝ አይችሉም» በሚል ስሜት እየተዝናና ።

«ግለፈያ ነው» አሉና ራስ አሉላ አሚሪካኑን በተዝናና ሁኔታ ተመለከቱት ራት ብሉ ደግሞ በሠፈራቸው ውስጥ ይተረማመስ የነበረውን ሕዝብ በዐይናቸቸው ቃኙተው ፤ ወደ ሚችል ዘወር አሉና ፤

«ሊንግዲህ ወደ አጼ ዮሐንስ እስድህና ሐሳብህን ትነግራቸዋለህ ። የምትችለውን ሁሉ ብትሠራልን ዋጋህን እንከፍልሀለን ። ለንብያች የምትሠራላቸውንም ሁሉ ለኛም እንድትሠራልን በእጅጉ እንፈልጋለን ። አንድ ነገር ግን ላስጠንቅቅህ እወዳለሁ» ብለው ፈገግታቸውን ለገሙለትና ፤

«ከዚህ ከኔ ግቢ እስካለህ ይህን የምታጨሰውን ትንባሆውን አልከለክልህም ። በጾም ቀንም ቢሆን ያፈቀደህን ደስ ያለህን ብላ ። አጼ ዮሐንስ ግን አይወዱምና ሳይፈትዱልህ እንዳት ነካው» አሉና ፈገግታቸውን ገቱበት ። ተጥለውም የመግራያ ምቹን አጠቃተምና ሁኔታ እንዲያሳያቸው ጠየቁትና እሲሉን ጥበብ በመጠኑ ሲያጠኑ ሰነበቱ ። በዚያም አጋጣሚና በዚያም ምክንያት የተነግ ራስ አሉላ ከፈረንጆች ጥበብ ጋር እየተዋወቁ መሔድና ከመኳንንቶቻቸውም ጋር መወያየት እያዘወተሩ ሔዱ ።

«የአውሮፖችን ጥበብ ወደ ሀገራችን ማስገባት አስፈላጊ ያችን ነው ። ለዚህም እንዲረዳን ምጥጥን ከንብያች አስለትቀን በእጃችን ማስገባት ይኖርብናል ። ስለዚህ በነገሩ ሁላችሁም አስቡበት ፤ ምከሩበት ፤ ጥበብ አይናችም» እያሉ መኳንንቶቻቸውን ማስረዳት ያዘወትሩ ጀመር ። ጥበብንና ጥበበኞችንም በይበልጥ ለመተዋወቅም ሆነ ለማቅረብ ይረዳል ብለው ከግመናቸው የተነሳም ነጋዴዎች ያለ ችግር ወደ ምፅዋ እንዲመላለሱ አስፈላጊውን ርዳታ ማድረግ ጀመሩ ።

«ቱርክና ግብፕ በጥበባቸው ተመክተው አይደለም እስከ ቢታችን በራፍ የመጡት፤ ጥበቡ እኮ ከኛም ጋር ጥንት ነበረ ፤ አሁንም ፈታችንንና ልዩናችንን ካዞርንበት እስከ እነርሱ በራፍ



በመዝለቅ ምን ያገደናል ፤ ወንድነቱ እንደሁ ከኛ ወዲያ ላሳር ነው» ራስ አሉላ ሁልጊዜም ለመኳንንቶቻቸው የሚናገሩት [illegible] ታቸው ሆነ ። አሉላ ከሚችል ብዙ የጥበብ ዜናዎችን በ[illegible] ታቸው ፤ «ለሀገራችን የሚጠቅም ዕውቀት ያለው ሰው [illegible] ጃንሆይ ይቀበሉትና በሚገባ ያነጋግሩት» ብለው ወደ መቀሌ ላኩት ።

ምንም እንኳን ግብፅ ሁለት ጊዜ የላከችው የጦር ኃይል ሁለት ጊዜ ሙሉም ድል ቢሆን የአጼ ዮሐንስ እምነትና ጥረት የነበረው ግን ከግብፅ ጋር በወዳጅነትና በሰላም ለመኖር ስለ ነበረ ይህንኑ እምነታቸውን የሚገልጽ ደብዳቤና መልእክተኛ ወደ ካይሮ ልከው ነበር ። ግብፅ ግን በነ መንሊስ ማሳሳቻ ቀርቶ የኢትዮጵያን መልክተኛ ይዛ አሠረች ። አጼ ዮሐንስም በጉዳዩ አዝነውና ተበሳጭተው ቀርጠው የሀገራቱን አንድነትና ኃይል ማጠናከራቸውን ቀጠሉ ።

ይህንኑ ዓላማቸውን በሚገባ የሚያውቅላቸው አሉላም ከመረብ ማዶ የነበረውን ሁኔታ በሚገባ ለመቆጣጠር ሲሉ አበተዳደራቸውን እያሻሻሉ የጦር ኃይላቸውንም እያጠናከሩ መሔዳቸውን የተረዳችው ግብፅ በመጀመሪያ ጊታው የነበረችውን የወዳጅነትንና የመግባባት ጥሪ እንደገና ልታተኩርበት ተገደደች ። በዚህም የተነሣ ከኢትዮጵያ ጋር እርቅና ሰላም ሊመሠረትልኝ ይችላል ብላ የተማመነችበትንና የደርቡር አገረ ገዥ የነበረውን ኩሉኔል ቻርልስ ጎርደን የሚባለውን እንግሊዛዊ መርጣ ወደ ምፅዋ ላከችው ።

ኩሉኔል ቻርልስ ጎርደን ምፅዋ ከደረሰ በኋላ ለራስ አሉላ የሚከተለውን ደብዳቤ ጽፎ ሰንሂት በሚባለው ቦታ የግብፅ ምሽግ አዛዥ የነበረውን ሐሰን ፓሻ አስይዞ ላከው ።

ደብዳቤውም ፤ «ታላቁ ጀኔራል ሆይ!
ክርስቲያናዊ ሰላምታዬን አቀርባለሁ ።

«በግብፅና በሀገርዎ መካከል የተፈጠረውን ያለመግባባት በሊ ርቅ ለመጨረስ የሚቻልበትን ነገር ለመነጋገር ለመምጣት ተዘ

ጋጀቻለሁ ፡፡ ንግግራችንም በስድስት ነጥቦች ላይ የተመሠረተ ይሆናል ፡፡ ነጥቦቹም ፤

አንደኛ ፤ በመካከላችሁ ግጭት እንዳይደረግ ፤

ሁለተኛ ፤ አሁን ያለው የግዛት ወሰናችሁ የተጠበቀና የታወቀ እንዲሆን ፤

ሦስተኛ ፤ ኢትዮጵያ በምፅዋ በኩል ንግድ ለማካሔድና ለመላላክ እንድትችል ፤

አራተኛ ፤ ንጉሠ ነገሥቱ በዓመት እስከ ሃምሳ ሳጥን የሚሆን ጥይትና አሥር አሥር ሚስኬቶ ጠመንጃዎች በምፅዋ ወደብ ለማስገባት እንዲችሉ ፤

አምስተኛ ፤ የግብፅ ቀዲብ ወደ ኢትዮጵያ ጳጳስ እንዳይላክ የከለከለውን እንዲያነሣ ፤

ስድስተኛ ፤ ደጃዝማች ወልደሚካኤል በሁለታችሁ መካከል የሚገኝ የግዛት ድንበር ሆና ኢትዮጵያን ከማስቸገሩ እንዲገታ ከወሰናችሁ ማበረር ይሆናሉ ፡፡ በእነዚህ ነጥቦች የሚስማሙልኝ ከሆነ ለመምጣትና ለመነጋገር ዝግጁ ነኝ» የሚል ነበር ፡፡

ራስ አሉላ የጐርዶንን ደብዳቤ ይዞላቸው የሔደውን የግብፅን የጦር መኰንን ሲያነጋግሩ ፤

«ለመሆኑ ኰሎኔል ጐርዶንን የዳርፉር አገረ ገዥ አድርጎ የሾመላችሁ ማነው?» ብለው ጠየቁት ፡፡

«የእንግሊዝ ንግሥት ናቸው» አለ ሐሰን ፓሻ ፡፡

«ታዲያ እናንተ አገራችሁን በእጃችሁ ሳትይዙ ያገራችሁ ባለቤቶች ሳትሆኑ ባንድ በኩል ቱርክን እንይዛለን ብላችሁ የመጣችሁትና ያን ሁሉ ሕዝብ ያስፈጃችሁት ተገቢ ነው? አሁንስ በአገሬ ላይ ሁናችሁ ወልደሚካኤልን እንደ ውሻ «ያዝ ያዝ» እያላችሁ እየላካችሁ የሐማሴንን ሕዝብ የምታስቃዩትስ ትክክል



ነው? የኔን አገር ከመመኘት አገራችሁን በመጀመሪያ በእጃችሁ አታደርጉም?» ብለው አፈጠጡበት ፡፡

«ታላቁ ጀኔራል ሆይ!» አለ ሐሰን ፓሻ በፍርሃት ተውጦ ፡፡

«አሁን የተናገሩት ሁሉ ትክክለኛ ነው ፤ አገራችን ምሥር እንደ እርስዎ አገር ጥንታዊት ናት ፡፡ እንደ እርስዎም አገር ታላቅ ታሪክ ያላት ናት» ብሎ ንግግሩን ሳይገታ ራስ አሉላ አቋረጡትና ፤

«የኔ አገርኮ ዛሬም ቢሆን ጥንታዊነቷን ታሪኳንና ዋናነቷን እንደ ያዘች ናት ፡፡ ለማንም አልተገዛችም ፤ እኔን የሾሙኝ አጼ ዮሐንስ እንጂ የእንግሊዝ ንግሥት አይደሉም ፡፡ ስለዚህ ከኛ ጋር ለመስተካከል የምትችሉት እንደኛው የሀገራችሁ ባለቤቶች ስትሆኑ ነው» ሲሉት ሐሰን የበለጠ ተደናገጠና ፤

«ታላቁ የንጉሥ ጀኔራል! እውነትዎን ነው ፤ እላህ የቀባዎት ፤ እላህ የሚጠብቅዎት ፤ እላህ እውነትና ሐቅ የሚያናግርዎት ነዎት» አለና አንገቱን አቀረቀረ ፡፡ ራስ አሉላም የሐሰንን መደናገጥ ተረድተው ለዘብ ባለ አነጋገር ፤

«ስማህ ወዳጄ! ምሥርና ኢትዮጵያን ለማስማማት የፈረንጅ አማላጅ መፈለጋችሁ የሚያሳዝን ነው ፡፡ አጼ ዮሐንስ ግን ከጦርነቶቹ በኋላ በወዳጅነት አብረን እንድንኖር ብለው ደብዳቤ አስይዘው ብላታ ገብረ እግዚአብሔርን ወደ አገራችሁ ቢልኩ የቁም እስር አድርጋችሁ አስቀመጣችሁት ፡፡ ይህም የሚያሳዝን ነው ፡፡ በኋላም እንግሊዞችና ፈረንሳዮች በመካከል ገብተው አስለቀቁት ፡፡ ይህም የሚያሳፍር ነው ፡፡ እኛን እምቢ ብላችሁ የእንግሊዝ አማላጅና አስታራቂ ከመፈለግም ደረሳችሁ ፡፡ ይህም የሞት ሞት ነው! የእናንተ አልበቃ ብሎ ወልደሚካኤል የሚባል ከሃዲ እያባበላችሁ መሣሪያ እየሰጣችሁ ጥግ እየሆናችሁ ይኸውና በአገሬ ላይ ሕዝቤን ታስጨንቃላችሁ» አሉና ትኩረታቸውን ከእርሱ ላይ ነቅለው ወደ ቀይ ባሕር አቅጣጫ አዙረው ራሳቸውን እያነቃነቁ ፤

«የግዱለም ባሕሩንም የአገሬንም ጠላቶችና ከሃዲዎች በመዳፌ ሳላስገባ አልቀርም» አሉና እንደገና ደግሞ ሐበሻን እየተመለከቱ ፤

«አሁን ወደ መጣህበት ጉዳይ ልመለስና ፤ አገረ ገዥችሁ ያቀረበው ፍሬ ነገር ግለፈያ ይመስለኛል ። ምንም እንኳን ጳጳስ እንልካለን የተባለውን ጉዳይ ብንቀበለውም ፤ ለአንድ ግዛት ጥጋ ትና ለዐሥር ጠመንጃ ሲሉ አጼ ዮሐንስ የአገራቸውን ድንበር ይለቃሉ ብዬ አላምንም ። ቢሆንም ይህንኑ መልእክት ይዘህ ወደ እርሳቸው እንድትሔድ አደርጋለሁ ። ፈቃዳችሁ ከሆነ አገረ ገዥአችሁም እንዲመጣ አደርጋለሁ ።

በምፅዋ በኩል ንግድ ማድረጉ ተገቢ ነው ፤ ከሁሉም ከሁሉም ደግሞ የወልደሚካኤልን እጅ የምታስረክቡኝ ከሆነ እንስማማ ይሆናል ። እናንተ ካለሰማችሁኝም እኔ ሕይወቱ ቁጣ ወልደሚካኤል አገሬን እየበጠበጠ ሕዝቤንና ወገኔን እያስጨነቀ አይኖርም ። አንተም ነገ ወደ ዐድዋ ትሔዳለህ» አሉትና ለግን ምቱ ደብዳቤ አስይዘው እጅቢና ስንቅ ሰጥተው ሰደዱት ።

አጼ ዮሐንስም የግብፁን መኰንን ተቀብለው ደብዳቤውን ተመለከተው ፤

«የኢትዮጵያ ወሰን ግልጽና የታወቀ ሆኖ ሳለ እነዴት በዚህ ጉዳይ ላነጋግራችሁና ላስማማችሁ ይለኛል? ዓለም የሚያውቀውን የአገሬን ድንበር ለማንም አሳልፌ አልሰጥም ። ሁለተኛም በዚህ ነገር ከግብፅ ጋር ንግግርም ስምምነትም የለኝም» ብለው መልእክተኛውን መለሱት ።



## የማስፈራሪያው ዱላ

ንጉሥ ምኒልክ እየጐለበቱ ትከሻ እያሳዩ ከማስቸገር ዐልፈው ፤ ጐንደርን ለመያዝ እስከ ደብረ ታቦር ድረስ መዝለቃቸውን አጼ ዮሐንስ ሲሰሙ በዝምታ ቀርቶ በሽምግልና ነገሩን ለማብረድ እንኳ የማይሞከሩት ሆነባቸው ። ኃይላቸውን ማሰባሰብና ከንዳቸውን ማስቆጣት የማይቀርላቸው መሆኑን አመኑበት ። በዚህም ጊዜ ፤ "ጦርህን አስከትተህ በፍጥነት ድረስ" ብለው ወደ አሉላ መልእክት ሰደዱ ።

ከዐሥር ሺህ በላይ የሚሆን ሠራዊት ይዘው አሉላ ዐድዋ ሲደርሱ አጼ ዮሐንስ እጅግ ተደሰቱ ። የአሉላ ዝና የአሉላ ጦር የምኒልክን ቅስም እንደሚሰብርላቸው ተማመኑበት ። ሲጠሩት ፈጥና የሚደርስ ትእዛዛቸውን ሳያወላውል የሚፈጽም ፤ ዘውድ የማይቀናቀን በዮሐንስ እጅ ተነሥቶ ከዮሐንስ ትከሻ መድረሱን ያለ ዮሐንስ ጋሻ ሌላ መከታ የሌለው መሆኑን ያመኑ በየጦሩ ግንባር ሳያፍር የሚመለስ "ዮሐንስ ይሙት" ካለ የማይመለስ አሽከራቸውን ፤ ከነበሩዋቸው ራሶች ሁሉ ለማላቅም ሙሉ ፈቃዳቸው ሆነና ፤

"ከዙፋኔ በቀር ሁሉን ሰጥቼሃለሁ ። ከኔ ቀጥለህ ግዛ ንዳ ፤ እዘዝ ፤ ከዛሬም ጀምረህ "ቱርክ ባሻ" እየተባልክ እንድትጠራ ፈቅጃለሁ ። "የራሶችም ራስ" ብዬሃለሁ" ብለው በይፋ ተናገሩ ።

ይህ ሹመት ደግሞ ፤ በአጼ ዮሐንስ አካባቢ በነበሩ መኳንንት ዘንድ የመረረ ተቃውሞ አስነሣ ። መኳንንቱ ወደ ራስ አርአያ ድምፁ ዘንድ ሔደው ፤

"ስንት መኳንንት ሞልቶ ፤ ስንት ባላባት ሞልቶ ፤ ያንድ ገበሬ ልጅ ይህን ያህል ከሁላችን የሚልቅበት ምክንያት ምንድን ነው?

አጼ ዮሐንስ ፣ ከአጼ ተክለ ጊዮርጊስና ከግብፅ ጋር የተዋጉት
ከአሉላ ጋር ብቻ ነው? በመላዋ ትግራይ የተወለደው ባላባትና
የጨዋ ልጅ ሁሉ ለአጼ ዮሐንስ ታማኝ አይደለም ማለት ነው!
ከእንግዲህ ወዲያስ የኛን አገልጋይነት አይፈልጉትም ማለት ነው?”
ብለው በደጃዝማች ሐጐስ አፈ ቀላጤነት አመለከቱ ።

ነገሩ ራስ አርአያንም ቢሆን የሚያሳስብ ሆነ ። ትላንት
የአሽከራቸው ጭፍራ የነበረ ያንድ ድሃ ገበሬ ልጅ ከሐማሴን
የጦር አበጋዝነት ልቆ ‘የራሶች ራስ’ ሲሆን የመላዋን ትግ
ራይ መኳንንት ደም እንደሚያፈላ ተገነዘቡት ። አቤቱታውን
ከአዳመጡም በኋላ ወደ አጼ ዮሐንስ ዘንድ ሐደው ፣

“ለመሆኑ በምኒልክ ላይ መዝመቱን ቀርጠህበታል ማለት
ነው?” ብለው ከረር ባለ ቃል ጠየቁ ። አጼ ዮሐንስ የአጐታቸውን
ጥያቄና የደም ፍላት ገጽታ ተመልክተው ለማለዘብ ፈለጉና ፣

“እስቲ እግዚአብሔር ያሳየዎ? ምኒልክ የሚሠራውን ይመል
ከቱት? ‘አልገብርም’ ማለቱ አንሶ ከጣሊያን ጋር ውስጥ ውስጡን
እየተላላከ መሣሪያ ማስመጣቱ አንሶ ጳጳስም እስከ ማስመጣት
ደረሰ ። አሁንም ቤገምድር ገብቶ ጕልበቱን ለማሳየት ይኸውና
ደብረ ታቦር ሠፍሩዋል ። ታዲያ ይህን ሁሉ ድፍረት እንዴት
ልታገሠው? እርስዎስ ምን አድርግ ይሉኛል?” ብለው ጠየቁ ፣
ከፍ ባለ ትሕትና ።

ራስ አርአያ በዝምታ ተሸብበው ቆዩና ፣ “እኮ ታዲያ አሉ
ላን ፊታውራሪ አድርገህ ልታዘምተው ነው?” ብለው ፊታቸውን
ኮስተር አድርገው ጠየቁዋቸው ።

“ያለ እርሱ ትእዛዜን የሚፈጽምልኝ የልቤን የሚያውቅልኝ
ስለሌለኝ እርሱን ነው የማስቀድመው” አሉ አጼ ዮሐንስም የማ
ንባራቸውን ቆዳ ሰብሰብ አድርገው ።

“ከእርሱ የበለጠ ሰው አጣህና ነው ለአሉላ ይህን ሁሉ
ማዕረግና ጦር የሰጠኸው? ምነው የታወቁ ባላባቶችና መኳንንት
ሞልተው የለም?” አሉ ራስ አርአያም የእኅታቸውን ልጅ እንደ
ንጉሠ ነገሥት ሳይሆን በንቀት እየተመለከቱ ።



“መኳንንትማ ሞልቷል ። ለኔ የልቤን የሚያደርስልኝ ያለ
ርሱ የለኝም እንጂ! ሌላውማ ውስጥ ውስጡን ነገር ሲጸጥርብኝ
አይደል የሚኖር? እኔን ለማደናቀፍ አይደለም የሚመሳጠረው?
ሌላውን ይህን አደራ ብሰጠው ከምኒልክ ጉን ተሰልፎ እንዴ
ሚወጋኝ አልጠራጠርም ። ሁሉንም ደርሼበታለሁ ፤ ዘውድና መን
ግሥት የማይፈልግ መኳንንት የለኝም” አሉ አጼ ዮሐንስ
አጐታቸውን ጭምር በጥርጣሬም እየተመለከቱ ።

“አገር ምድር ተጠራጥረህ በአንድ ሰው ላይ መተማመኑ አያ
ዋጣም ። በዚህ ነገር መኳንንቱም አዝነዋል ፣ ተከዘዋልና አስብ
በት” ብለዋቸው ወጡ -

የአጼ ዮሐንስ ማስፈራሪያ ዱላ የሆኑት ፣ “ቱርክ ባሻ ራስ
አሉላ” የንጉሠ ነገሥቱ ቀዳሚ ጦር ዋና አዝማች ሆነው ተከ
ዜን ተሻግረው ጉዞአቸውን ወደ ጐጃም አቀኑ ። ቀደም ብሎ
ንጉሥ ምኒልክ ዐባይን ሲሻገሩ ከእርሳቸው ጋር መተጣጠን
ጠልተው በረሃ ገብተው የነበሩት የጐጃም ራስ አዳልም ከመሸ
ጉበት በረሃና ተራራ ተሰያይተው እጃቸውን ለአሉላ ሰጡ ።
አጼ ዮሐንስም ዋናውን ሠራዊታቸውን ይዘው ወደ ጐጃም
ሲዘልቁ የሁኔታውን ክባድነት የተገነዘቡት ምኒልክ ወደ ሸዋ
ተመለሱ ። አጼ ዮሐንስ ምኒልክን ተከትለው ወደ ሸዋ በመዝ
መት ፈንታ ወሎ ገብተው ፣ በዚያ ዘመን መሐመድ አሊ በኋላ
ግን ራስ ሚካኤል ከተባሉት ጋር ተገናኝተው ከሰነባበቱ በኋላ፣
የማስፈራሪያ ዱላቸውን በወሎና በሸዋ መካከል አሥፍረው
ራሳቸው ወደ ደብረ ታቦር ተመልሰው በሀገር ሽማግሌዎች አግ
ባይነት ከምኒልክ ጋር መላላክ ጀመሩ ።

የአጼ ዮሐንስን ንጉሠ ነገሥትነት የጐጃሙ ራስ አዳልና
የወሎው መሐመድ አሊ አምነው ተቀብለው ገብተዋል ። በዚ
ህም የተነጣ የሰሜን ኢትዮጵያ ጦር በአጼ ዮሐንስ ዙሪያ ተከ
ማችቷል ። ከዚህ ሌላ ደግሞ ፣ የቱርክ ባሻ አሉላ ዝና ከዳር እስከ
ዳር ያስተጋባል ። ሠራዊታቸው የያዘው መሣሪያ ጥራትና ብዛት
ከሆነው በላይ ሆኖ ይወራለታል ። ያ ሁሉ ሠራዊት ወደ ሸዋ
ጉዞ የጀመረ እንደሆነ ሊያደርስ የሚችለውን ጥፋት ምኒልክ
እንደ ተገነዘቡት እርቅ ፈለጉ ።

የምኒልክ እርቅ መፈለግ በንጉሡ ነገሥቱ ዘንድ ተቀባይነት በማግኘቱ ቦሩ ሜዳ ላይ እንዲገናኙ ተስማሙ። የሁለቱ ጦር ተራርቆ እንዲሠፍር ከተደረገ በኋላ ምኒልክ ከአጼ ዮሐንስ ዘንድ ቀርበው ፣

'ባጠፋሁ ይማሩኝ' ብለው ሲጉነበሱ አጼ ዮሐንስም ከተቀመጡበት ተነስተው፣ ምኒልክን አስተርበው አቅፈው ሳሟቸው። በዚያም እርቅ ምክንያት አስገምግሞ የነበረው የደም ደመና ከሀገሪቱ አየር ላይ ገፈፈ። በግራና ቀኝ አሰፍስፎ የነበረውም ጠላት አፈረ። ከሁሉም ደግሞ አሉላ እጅግ ተደሰቱ። በመሐል ኢትዮጵያ ዳግመኛ በእጃቸው ደም ባለመፍሰሱ ከፍ ባለ ደስታ ተዋጡ።

የሁለቱ ዘውድ ተናጋቂዎች ፉክክር በዕርቅ በርዶ ሰላም ወርዶ አጼ ዮሐንስ፣ ንጉሥ ምኒልክ፣ ራስ አዳልና ንጉሥ ሚካኤል ወሎ ውስጥ ሆነው በሃይማኖት ምክንያት በሀገሪቱ ውስጥ ስላለው ልዩነትና ስለጠቅላላው ጉዳይ ምክክር ይዘው በነበረበት ወቅት ከሐማሴን አስቸኳይና አስደንጋጭ መልእክት ደረሰ።

በምፅዋና በቦጎስ ከነበሩት ግብፆች ጉያ ተወትፈው ወደ ደጋው ሐማሴን እየወጡ መንደር እየዘረፉ ሕዝብ ሲያስዉንቁ የነበሩት ደጃዝማች ወልደሚካኤል አመች ጊዜ አጋጥማቸውና ሐማሴንን ይዘው ወደ ትግራይ ለመዝመት በመዘጋጀት ላይ መሆናቸውን የሚያረዳ መልእክት ነበር የተላከው።

አጼ ዮሐንስ፣ ያ መራራ መልእክት እንደ ደረሳቸውም አልጋቸውን እንዲጠብቁ መቀሌ ላይ ትተዋቸው የነበሩት ራስ ባርያው ወደ ሐማሴን ተሻግረው ደጃዝማች ወልደሚካኤልን ወግተው አገሩን እንዲያደላድሉ ላኩባቸው። ራስ ባርያውም በፍጥነት ጉዞ ጀመሩ።

“ከዛሬ የተሻለ ጥሩ አጋጣሚ አናገኝምና በእጃችን ሊገባ በሩ የተከፈተው አገር እንዳያመልጠን አደራህን” ብለው ግብፆች በቂ መሣሪያ አስታጥቀው ያዘመቱቸው ደጃዝማች ወልደሚካኤልም ተዘጋጅተው ወታደሮቻቸውን ቦታ ቦታ አስይዘው ሲጠባበቁ፣ ራስ ባርያው የመረብን ወንዝ ተሻግረው ሲገሰግሱ የወልደሚካኤል ወታደሮች ካደፈጡበት ቦታ ሲገቡ ተኩስ



ተጀመረባቸው። በዚያም ጦርነት ራስ ባርያው ሞቱ። ጦራቸውም ተበታተነ። ወልደ ሚካኤልም በነበራቸው ጦር ላይ ከራስ ባርያው የማረኩትን መሣሪያና ወታደር ጨምረው በይበልጥ ጎለበቱ።

በሁኔታው አጼ ዮሐንስ እጅግ ተበሳጩ። ግብፅን ሲያሸንፉ ምኒልክ አኮረፉ። ከምኒልክ ጋር ሲታረቁ ደግሞ ወልደ ሚካኤልም በተራቸው አኮረፉ። እንዲያውም ሐማሴንን እጅ አድርገው ትግራይን ለመውረር መዘጋጀታቸው የሚቀጠቅጥ ቁስል ሆነባቸው። ያን ቁስል የሚያሽር፣ ያን ጥቃት የሚበቀል የፈሰሰውን ደም የሚመልስ ዱላ መሰንዘር ደግሞ አስፈለጋቸው።

“ያ የግብፆች አሽከር የሠራውን ሰምተኸው የለም?” አሉ አጼ ዮሐንስ ለራስ አሉላ መርዶውን ሲነግሩዋቸው።

“አዎ ጌታዬ ስለአሽከርነትስ መች በታና ተላዋሚቸው ነው እንጂ” አሉ አሉላም የደረሰውን ነገርና የተጠሩበትንም ምክንያት ያወቁት መሆናቸውን ሲያረጋግጡላቸው።

“እውነትህን ነው ቀላዋጭ ነው” ብለው ትክዝ ብለው ቆዩና ከሆዳቸው ውስጥ ገብቶ የሚፈጃቸውን ነበልባላዊ ብስጭት በትንፋሻቸው ለማስወጣት ሲሉ ደጋግመው ተነፈሱና ፤

“ታዲያ አሁንስ ምን ታስባለህ?” አሉና ጠየቁ። እኒያን ንጉሥ ምኒልክን አስፈርተው ለእርቅ ያንበረከኩላቸውን ያበሻው ማዕረግ እንዷቸው ቱርክ 'ፓሻነት' የደረቡላቸውን የጦር ገፈታ ቀማሻቸውን በጉጉት እየተመለከቷቸው።

“ነገውኑ ልሒድ ሌላ ምን ሐሳብ ይኖረኛል ጌታዬ!” አሉ አሉላም ቆፍጠን ብለው።

“እንደ መልእክተኛው አነጋገር ከሆነ ግብፆች በርከት ያለ መድፍና መትረየስ ሰጥተውታል ፤ በዛ ያለ ሰውም አሰልጥኗል ይባላል። ስለዚህ አብረን ነው የምንሔደው” አሉ አጼ ዮሐንስ።

“ምነው ጌታዬ! ምን በደልኩ? ምን አስቀየምኩ? ምንስ ተገኘብኝና እኔ እያለሁ ወልደሚካኤልን ቅም—ነገር ብለው ከሰቀትረው ልዘምት ማለትም?” አሉ ራስ አሉላም ትክዝ ብለው።

“ማየትክ ያለብህ ወልደ ሚካኤልን አይደለም ፤ ዋነኞቹ ባለ ጉዳዮች ግብፆች ናቸው ። ከኋላው ሆነው ያዝ ያዝ የሚሉት የፈለገውን የሚሰጡት ፣ የፈለጋቸውን የሚያሠሩት እነሱ ናቸው ። አብረን እንሒድ የምልህም በዚሁ የተነሣ ነው” አሉ አጼ ዮሐንስ ትክዝ ብለው ።

“ቢሆንስ ጌታዬ? ቢሆንስ? ግብፆችንስ እናውቃቸው የለም? ወልደሚካኤልንስ እናውቀው የለም? የግንኙቸው ወንድነት ነው የእርስዎን ነጋሪት የሚያስመታው? የእርስዎን ሠራዊት የሚያስከትተው? ወልደ ሚካኤል በኔ ፊት ነፋስ እንደሚያላጋው ሸንበቆ ነው ። ይፍቀዱልኝ ጌታዬ ይዘዙኝ አላሳፍረዎትም” አሉ አሉላ እልህ እየተናነቃቸው ።

አጼ ዮሐንስ ትክዝ ብለው በዝምታ ተውጠው ቆዩና አሉላን በዐይናቸው ሙሉ እንኳን በማየት እየጨነቃቸው ፣

“ለመንግሥቴ ጽናት ክንዴ ለቤቴ ምሰሶዬ ነህ ፣ ርቀኸ ብትሔድ ደግሞ ይጨንቀኛል ። አንተ ካልሔድክበት ደግሞ ወልደሚካኤልን የሚያንበረክክልኝ የለኝም ። የልቤን የሚያደርስልኝ የለም ። በታማኝነትና በእውነተኝነት የሚመክረኝስ ማነው?” ብለው እንደገና በሐሳብ ተውጠው መናገር ሲያቅታቸው ራስ አሉላ ቀረብ አሉና ፣

“የወልደሚካኤል ጦር እኔን መክቶ የሚያቆይ እንደማይሆን ይመኑኝ ! ውሎ ካደረ ደግሞ ግብፆች እርሱን ያሳብጡትና እነዚህ ዛሬ እርቅ የጠየቁትን መልሰው አሻፈረኝ ለማለት ይቃጣቸዋልና መርቀው ይላኩኝ ጌታዬ” አሉ አሉላ ።

አጼ ዮሐንስ ተበሳጭው ተወራጩና ፣

“የወልደሚካኤል አብጠትና ድፍረት ዛሬ እርቅ የጠየቁንን መልሶ ያሳብጣቸዋል” ያልከው እውነትህን ነው ። አሁንም እንኳን የራስ ባርያውን ሞት ሰምተው ማጉረምረም ጀምረዋል የሚሉ ነገር ሰምቻለሁ ። ግን ደግሞ አንተንስ ያሳጣኝ እንደሆን ባንተ ላይ ክፉ ነገር የደረሰ እንደሆነ ክንዴ መዛሉ አይደለም? ብለው እንደገና በዝምታ ታፍነው ቆዩና ፣



“እንዲያው ጉሮአችንና ሥራችን መሸሸግ ብቻ ሆና መቅረቱ ነውን?” አሉ ትክዝ ብለው ።

“እረ ጌታዬ በዚሁ በቃችሁ ቁለኝ!”

“የሐማሴን ልጅ የዮሐንስ ወንድም” ብሎ በተናገረበት አንደበቱ የግብፅ አሽከር ይሁን? የአባቶቹን ማዕረግ በተጉና ጸፈበት ትከሻው የባዕድ ቀሚስ ያጥልቅበት? እኔስ በድየው ብሆን በአባቶቼ በታላላቆቼ ወንድሞቼ ፊት አይከሰኝም? አይወቅሰኝም ነበር? እኔን ቢጣላኝስ አገሩን ይክዳት? ኢትዮጵያን እናቱን ከግብፅ ጋር ሆኖ ይውጋት?” ብለው አጼ ዮሐንስ እንደገና በትካዜ ተዋጡ ።

“ወልደሚካኤል ሔዶ ብለው ነው እንደዚህ የሚተከዙ ጌታዬ እርሱኮ የግብጾች ቀላዋጭ የሆነው ዛሬ አይደለም? ልጁን ወደ ምሥር የላከው ጊዜ ነው ዮሐንስን የከዳው፤ አሁንም መድኃኒቱ ከነጌቶቹ መውቃት ነው ። ውሎ ካደረ ተከታዩ ይበዛል፣ የሚያሳስበው ደግሞ የእርሱና የጌቶቹ ወንድነት ሳይሆን የሐማሴንን ሕዝብ እንዳያስተው ነውና...” ብለው አሉላ ተናግረው ሳያበቁ ፣

“ምናልክ? ሕዝቡን እንዳያስተው አልክኝ? እውነትክ የእርሱ አሳፋሪነት እንኮ የእርሱ ዘር አሰዳቢነት እንኮ ደጉንና ጀግናውን የሐማሴንን ሕዝብ አባብሎም ሆነ አስገድዶ ተከታዩ እንዳያደርገው ፍጥነህ ድረስለት ። እኔ እስከመለስም ትግራይንም ጠብቅ የኢትዮጵያ አምላክ ይጠብቅህ ፣ ያባቶቼ ጸሎት ይከተልህ” አሉና አጼ ዮሐንስ የማስፈራሪያ ዱላቸውን ከመኻል ኢትዮጵያ እንደገና ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ መሰሱት ።

አሉላ ፣ ከወሎ ገሥግሠው ዐድዋ ሲገቡ ከዚያ በፊትና ከዚያም በኋላ ተደርጎላቸው የማያውቅ አቀባበል ተደረገላቸው ። የትግራይ ሕዝብ ከየመንደሩ እየጎረፈ ዐድዋን አስጨነቃት ። ራስ ባርያውን የገደሉትና ትግራይን ለመውረር ይዘጋጁ የነበሩት ደጃዝማች ወልደሚካኤል “ መጣሁ ፣ መጣሁ” እያሰኙ ስለነበረ የትግራይ ሕዝብ በወልደ ሚካኤል መሪነት በግብፆች መዳፍ የገባ እንደሆነ የጉራዕ ብድር መመለሻ እንደሚሆን ተረድቶት

በጭንቀትና በመዋለል ላይ በነበረበት ወቅት አሉላ ሲደርስለት ልባዊ ደስታ፣ ልባዊ ዕረፍት፣ ልባዊ ኩራት ፈነቀለው!

አሉላም ሕዝቡን የሚያረጋጋ ዐዋጅ አናገረው የራስ ባርያውን አሽከሮችም ከየተበታተኑበት ሰበሰቡ። ከራሳቸው ሠራዊትም ጋር ሲዳመር በትእዛዛቸው ሥር የነበረው የሠራዊታቸው ብዛት እስከ ሃያ ሺህ ደረሰ። ይሁን እንጂ ከወልደሚካኤል በስተኋላ የተሰለፉት ግብፆች የቱን ያህል እንደ ተዘጋጁና በየት በየት በኩል እንዳተኮሩ እስኪያጣሩ ድረስ ትግራይ ውስጥ መሰንባበት ግዴታ ሆነባቸው።

የትግራይን ሕዝብ አረጋግተው ከመረብ ወንዝ ማዶ ለሚጠብቃቸው ግዳጅ በመዘጋጀት ላይ እንዳሉም ትግራይ ውስጥ ሌላ ተቀናቃኝ ተነሣባቸው።

የራስ ባርያው ልጅ ደጃዝማች ገብረመድኅን ባርያው ያባታቸውን ግዛት ለማግኘት ባለተስፋ ነበሩና፣ "ለሐርሲታይ ልጅ አልታዘዝም" ብለው ተነሡ። ያም ግጣ ደግሞ ለአሉላ ተጨማሪ ሸክም ሆነባቸው። ከጉዳ ተፎካካሪ ከወንዝ ማዶ ትግራይን አሸባሪ ከወደ ምፅዋዕ በኩል አገር ወራሪ ሦስት ጠላቶች መደዳውን አነጻጸረውባቸዋል። ከየትኛው ጋር ይፋለሙ? ችግሩን ዘርዝረው ወደ አጼ ዮሐንስ አመለከቱ። መልሱም፣
"ከቤቱ ውስጥ እንደዚህ ያለ ነገር ከተፈጠረ በይበልጥ እየከፋ እንዳይሔድ በቀስታ እያስታመምክ ቆየኝ። ገፍቶ ከመጣብህ ግን የወንድነትህን ሥራ ፈጽም፣ የሚያመች ከሆነ ደግሞ ወልደሚካኤል አገር እንዳያበላሽ ጦር ላክበት፣ አንተ ግን ዐድዋን ለቀህ እንዳትሔድ" የሚል ሆነ።

ከራስ ባርያው ልጅ ቀጥሎ ደግሞ የራስ አሉላ የመጀመሪያ ባለቤታቸውና የሦስት ሴቶች ልጆቻቸው እናት የነበሩት ወይዘሮ ብትወጣም በቤታቸው ውስጥ ሸፈቱባቸውና ችግራቸውን አባባሱት።

"በቃኝ ልቀቁኝ፤ የሰማሁትን ሰምቻለሁ፤ ከእንግዲህ ወዲያ እኔና እርሳቸው ባልና ሚስት ሆነን አንኖርም በቃኝ" ብለው ቀሳውስትና ሽማግሌዎች እንዲያፋቱዋቸው ለመኑ።



ወይዘሮ ብትወጣ ሰባት ዓመታት ከኖሩበትና ሦስት ልጆች ከወለዱበት ቤት ለመውጣት ምክንያት አላጡም ነበር። ከዚያው ትግራይ ውስጥ ሰለዋ—ሲሐርቲ ከተባለው መንደር ተወላጅ ከነበሩት ወይዘሮ ስምለም ከተባሉ ሴት ራስ አሉላ ልጅ ማስወለዳቸውንና ከራስ አርአያ ልጅ ከወይዘሮ አምለሱም ጋር መልእክተኛ በየጊዜው መመላለሱን ሰምተው ነበር። ወሬውንም ከያለበት ለቃቅመው የነገሩዋቸው በአሉላ የማዕረግና የሹመት ዕድገት በቅናትና ምቀኝነት ተቃጥተው የነበሩት እነደበበ እነሐጐስና ገብረመድኅን ነበሩ።

"በትግራይና በሐማሴን የተነሡባቸው ጠላቶች መች አነሡዋቸውና ነው እርስዎ ደግሞ ከቤት ውስጥ የተነሡባቸው? አባክዎ ይለመኑን? በሀገር ላይ ጠላት ተነሥቶ ከቤት ደግሞ ብጥብጥ ማስነሣት ምን ይባላል? ማንንስ ለመጥቀም ነው? ከዚህ ወዲያ ክብር፣ ከዚህ ወዲያ ክብረት፣ ከዚህ ወዲያ ምቾት ምን ይምጣ ብለው ነው እንደዚህ የሚያስቸግሩ?" ብለው የነፍስ አባታቸው ቢለምኑዋቸውም፣

"የሁሉንም አልፈልግም በቃኝ" ብለው አሻፈረኝ አሉባቸው።

"የውስጥና የውጪ ጠላቶች ባስጨነቁኝ ወቅት የችግሬና የብስጭቴ ተካፋይና ረዳት መሆንዋን ትታ ከሚጋፋኝ ጋር ተባባሪ ሆና እሔዳለሁ ካለች ምን አደርጋለሁ? ተዋት ትሒድ መንገዱን ጨርቅ ያድርግላት" ብለው አሉላም ቆረጡ።

ሁኔታውም ከአጼ ዮሐንስ ዘንድ ደረሰ። ግራ ቀኙን ተቆጥተው የፈረሰውን ትዳር ለማደስ አልፈለጉም። "ካልተስማሙ ምን ይደረግ" ብለው የሆዳቸውን በሆዳቸው ይዘው ዝም አሉ። ከመጀመሪያውም ቢሆን የአሉላን ክንድ በጋብቻ ለመያዝ ተመኝተው ነበር። ታዲያ አንዳንዶቹን ዘመዶቻቸውንና የቅርብ ባለሟሎቻቸውን በጠየቁ ቁጥር ያገኙት መልስ፣ "ለወዲ ቁቢ ለወዲ ሐረሲታይ" የምትሆን ሴት ከኛ እንዴት ይመኙብናል!" የሚል ትሬታ ስለነበረ፣ አሉላን በጋብቻ ክር ለመያዝ ሳይመቻቸው ቀርቶ ነበር።

አሉላ፣ በገበሬ ልጅነታቸው የተነሣ በትግራይ መኳንንት አካባቢ እየተናቁና እየተጠሉ ሲሔዱ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ደግሞ "የራሶች ራስ" የሚለው ማዕረግም እንዷቸው በሀገረ-ቱርክ የታወቁትን "ቱርክ ፓሻ" ያሉዋቸውን የማስፈራሪያ ዱላቸውን መኳንንቶቻቸውም አክብረውና ፈርተው እንዲታዘዙላቸው ከማ ድረግ አልተቆጠቡም ነበር ።

ንጉሠ ነገሥቱ ያላቁትንና ያከበሩትን የአሉላን ጀግንነት ታማኝነትና ፈላጭ ቆራጭነት ያልተቀበሉ መኳንንትም አሉላን ጠልፈው ለመጣል ወጥመድ ሲዘረጉባቸው መኖራቸውን አጣ ርተው የሚያውቁት አጼ ዮሐንስ፣ "አሉላ ሳይጠየቅ፣ አሉላ ሳይስማማበት፣ አሉላ ይሁን ሳይል አይሆንም" እያሉ መኳንንቶ ቻቸውንና ባለሟሎቻቸውን ማሣፈር ያውቁበት ነበር ።

የአሉላ ወንደ-ላጤነት ያሳሰባቸው ንጉሠ ነገሥት ያለ ምንም ማመንታት የአምለሱን እጅ እንዲጨብጥላቸው ምኞ ታዊ ትእዛዝ ላኩባቸው ። ራስ አርአያም ቢሆኑ ከራሳቸው በላይ ራስ ለሆነው የገበሬ ልጅ አሽከራቸው 'የልጃቸውን የአምለሱን እጅ አልሰጥም' ለማለት ከማይቃጡበት ጊዜ ላይ መድረሳቸውን አምነዋልና!! "ምንም እንኳን ክኔ አብራክ ብትወጣም የዮሐንስ ልጅ ናት ። ከርሱ ፈቃድ እኔም ሆንኩ እርሷ እንወጣም ። አሉ ላም ቀደም ብሎ ይመኛት እንደነበረ ዐውቃለሁ ። ስለዚህ ከጊዜው ፈቃድ መውጣት የሚችል ማንም የለምና ፈቅጃለሁ" ብለው የአምለሱን እጅ ለድሮ አሽከራቸውና ለኋለኛው "ቱርክ ባሻ አሉላ" አስረከቡ ።

የጠቅላላው የሀገሪቱ ጉዳይ ከንጉሠ ነገሥቱ ቀጥሎ ያረፈው በአሉላ ላይ ቢሆንም፣ ከሁሉም ከሁሉም ደግሞ የደጃዝማች ወልደሚካኤል 'ማን አለብኝነት' ለገናናው ጦረኛ አሉላ አባ ነጋ ከሬት የመረረ ቢሆንም፤ ከዚያ በፊት ከማንኛዋም ሴት ያላገኙትን ፍቅርና ሰላም ከአምለሱ ለማግኘት በመቻላቸው የደረሱበትን የማዕረግና የጸጋ ልቀት ለማጣጣም ችለዋል ።

ይሁን እንጂ፣ ለፍቅራቸው ማጣጣሚያ የሚሆን ልጅ ለማ ግኘት ሳይችሉ ቀሩ ። ይህም ብቻ ሳይሆን ጀግንነታቸውና ታማ ኝነታቸው ያስገኘላቸውን ታላቅ ማዕረግና ዝና ይዘው ወደ ታላቅ



ቤተሰብ ቢገቡም፣ በትግራይ መኳንንት ዘንድ ልባዊ ተቀባይነት አላገኙበትም ። እንዲያውም የራስ አርአያን ልጅ በማግባታቸው "ምን ቢያስብ ነው? እንዴ ቴዎድሮስ ቢጋብቻ ተንጠልጥሎ ለመ ንገሥ ነው?" የሚል ጥርጣሬ በመኳንንቱ አእምሮ ተቀረፀና የተቃዋሚዎቻቸውን አንድነት እያጠናከረባቸው በመሔዱ የአዲሲቱ ፍቅረኛ ባለቤታቸው ወንድም የድሮው ጥሰኛቸው ደበበ አርአያ የአሉላ ተቃዋሚዎች ቀጠሪ ሆኑ ።

## "ማሩኝ አለ"

ራስ አሉላ ፣ ዐድዋ ገብተው ጦር በማዘጋጀት ላይ መሆናቸውን ደጃዝማች ወልደሚካኤል እንደ ሰሙ ፣ ትግራይን ለመውረር የነበራቸውን ዝግጅት ትተው ፀአዘጋ ከተባለችው መንደራቸው ላይ ሆነው ለመከላከል የሚያስችላቸውን ምሽግ ማጠናከር ጀመሩ ። ግብፆችም በወልደሚካኤል ምርጫ በመስማማት ተፈላጊውን መሣሪያ ሁሉ ማቀበሉን ቀጠሉ ። የሱዳን ጠቅላይ ገዥ የነበረው እንግሊዛዊው ጐርደን ፓሻ ግን በግብፆችና በወልደ ሚካኤል መካከል የነበረውን ሐሳብና ዕቅድ አጥብቆ ተቃወመው ። የእርሱ ሐሳብ ፣ 'ደጃዝማች ወልደሚካኤል የራስ አሉላን ጦር ድል ለማድረግ ስለማይችሉ ፣ ራስ አሉላ ድል ያደረጉ እንደሆነ በቦጐስና በምፅዋ ያሉትን ግብፆች ያጠፏቸዋል ። ከዚያም በኋላ ነገሩ ለግብፅ ብቻም ሳይሆን ለኛም አስቸጋሪ ይሆናል' የሚል ስለ ነበረ የወልደሚካኤልና የግብፆች የመቀራረብና የመተባበር ክር እንዲበጣጠስ አደረገው ።

ከግብፆች ጉያ በጐርደን ዘዴ ተፈልቅቀው የወጡት ወልደ ሚካኤል በፀአዘጋ መንደር የሰበሰቡዋቸውን ወታደሮቻቸውን ለመመገብ ስለ ተቸገሩ ፣ እንደ ለመዱት ወደ አይለት ወረዱና ምፅዋ የነበረው ወዳጃቸው አላዲን ፓሻ እህል እንዲልክላቸው ወታደሮች ላኩበት ። በዚያን ጊዜ የእንግሊዝ የጦር መርከብ ምፅዋ ላይ ነበረችና ለወልደሚካኤል ምንም ነገር እንዳይላክና ምንም ዐይነት መቀራረብ እንዳይደረግ አላዲን ፓሻን የመርከብ አዛዡ አስጠነቀቀው ። ወልደሚካኤልም ምፅዋ ወርደው እርዳታ ለመጠየቅ ቢሞክሩ የማይቻል ሆነባቸው ።

ወልደ ሚካኤል በዚያ ሁኔታ ላይ በነበሩበት ወቅት ራስ አሉላ ከሸያ ሺህ በላይ የሚሆን ሠራዊታቸውን አስከትለው



ሐማሴን ደረሱ ። አከታትለውም የአንድ ፊታውራሪ ጦር በበጐስና በሐማሴን መካከል እንዲሠፍርና ደጃዝማች ወልደሚካኤል እንዳያመልጡ መንገዱን አዘጉባቸው ። ወልደሚካኤል ከባርቱ ችግር ላይ ወደቁ ። የሠፈሩበት የአይለት ቀበሌ ከነሠራዊታቸው ሊሸከም የሚችል ምንም ነገር የለውም ። ምግብ ሊገኝ የሚችልበትን ደጋማውን ቀበሌ ደግሞ የአሉላ ሠራዊት ሠፍሮበታል። የግብፆችን ፊትም እንግሊዞች ጋርደውባቸዋል ። ከረኃብ ላይ ሥጋት የተጫጫናቸው አሽከሮቻቸውም ቀስበቀስ ወደ ራስ አሉላ መግባት ጀመሩ ። በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የወልደ ሚካኤል ምርጫም ሆነ እንቅስቃሴ እየጠበበ መጣ ።

ሁኔታዎቹን ሁሉ ከገመገሙ በኋላ ፣ የደብረ ቢዘን ገዳም መነኮሳትና ቀሳውስት ከዚያ ጭንቅ እንደሚገላግሉዋቸው ተማመኑባቸው ። በዚህም መሠረት በእነርሱው አማካይነት ፣

"ጌታዬ ራስ አሉላ ፣

ዝቅ ብዬ እጅ እነሣለሁ ። ዛሬም ሰይጣን አነሳሥቶ አሳሥቶኝ ንጉሠ ነገሥቱንና እርስዎን በድያለሁ ። ስለዚህ ጀግንነትና ምሕረት ገንዘብዎ የሆነት ጌታዬ የምሕረት ትንፋሽዎን እንዲልኩልኝና ከንጉሠ ነገሥቱ እንዲያስታርቁኝ እግዚትነ ማርያምን አማላጅ ይዤ እለምንዎታለሁ" የምትል ልመናቸውን አስይዘው ላኩ ።

'ወልደ ሚካኤል ማሩኝ አለ?' ብለው ራስ አሉላ በሆዳቸው ውስጥ ታምቆ የኖረውን የንዴት ክምችት ለማስወጣት ያጋግመው ተንፈሱና በዝምታ ታፍነው ከቆዩ በኋላ ፣ ዐይናቸውን በአደራሹ ዙሪያ ቁመው ከነበሩት ቀሳውስት ላይ ተራ በተራ እየወረወሩ ፣

"ባያድለው ነው እንጂ እጼ ዮሐንስ በርሱ ልክ ያቀፉት ፣ በርሱ ልክ ይቅር ያሉት በርሱ ልክ ያከበሩት ፣ ማንም የለም ። የአባቱ ግዛት ቀረብኝ ብሎ አኩርፎ ብቻውን በረሃ ቢገባ ኑሮ ባላዘንኩበት ነበር ። እንዴት ትላንትና በጦር ግንባር ካርገበገባቸው ግብፆች ጫማ ሥር ይወድቃል ? ምንስ ቢሆን እንደምን ብሎ ግብፆች ፣ 'ያዝ ያዝ' ብለው እንደሚልኩት ውሻ

ይሆናል ? እንደምንስ ብሎ የሐማሴንን ሕዝብ ያኖርደዋል ? አሁን መጠጊያ ሲያጣ የሚበላው ሲቸግረው ጊዜ 'ማረኝ' አለ? መቼስ ምን ይደረጋል ! የት ይጣላል ! ይሁን ምን ይደረግ ? እና ንተን አስቸግሮ የላከውስ ቢጨንቀው አይደለም ? እንደማል መልሳችሁ ዐውቆ አይደለም ? ይሁን ከቃላችሁ አልወጣም ። ግን በዚያው ባለበት በኩል ወደ ዐድዋ ይሒድና እኔም እዚያው ሔጄ ከተገናኘን በኋላ ለአጼ ዮሐንስ አመልክቼ ነው መታረቅ የምንችለው'' አሉ ሲተናነቃቸው የነበረውን ቁጣ ለማስወገድ እርሳቸውም እየተናነቁት ።

አማላጆቹ የራስ አሉላን ሐሳብ ለደጃዝማች ወልደ ሚካ ኤል ሲያደርሱ ራስ አሉላም ጉዳዩን ዘርዝረው ለአጼ ዮሐንስ አስተላልፈው ወደ አክሱም ሔዱ ። ደጃዝማች ወልደ ሚካኤል በሃረብና እርዛት ሲሠቃዩ የነበሩትን ሦስት መቶ የሚሆኑ አሽከሮቻቸውን ሰብስበው ወደ ትግራይ ተሻግረው ከራስ አሉላ ጋር ተገናኝተው ፣ 'ይቅር ለእግዚአብሔር' ተባብለው ሁለቱ ከታረቁ በኋላ ከአጼ ዮሐንስ ጋር ለማስታረቅ ደግሞ ራስ አሉላ ከደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ጋር ወደ ደብረ ታቦር ሔዱ ።

"'ወንድምህ ቢበድልህ ሰባት ጊዜ ሰባም ቢሆን ይቅር በለው' ብሏልና ጌታ በበኩሌ 'ይቅር ለእግዚአብሔር' ብያለሁ ። ከባለ ደምህ ግን ታረቅ ፤ አገርህንና ወገንህንም ከልብህ ማሩኝ በል'' አሉ አጼ ዮሐንስ ድንጋይ ተሸክመው ከበራፋቸው ላይ የወደቁ ትን ደጃዝማች ወልደ ሚካኤልን ሲታረቁዋቸው ።

የእርቁ ጉዳይ ግን በመኳንንቱ ዘንድ የተለያየ አስተሳሰብ ፈጠረ ። ገሚሱ 'ጠላት ጉያ ተሸጉጦ ለወንድማማች ደም መፋ ሰስ ምክንያት የሆነውን ሰው መታረቁ የጠላትን ቅስም ለመስ በርና ለማሳፈር ይረዳልና ተገቢ ነው' ሲል ፣ ገሚሱ ደግሞ 'አገሩንና ንጉሠ ነገሥቱን ከድቶ ከግብፅ ጦር ጉን ተሰልፎ የወጋንንና የሐማሴንን ሕዝብ ሲያስጨንቅ የነበረውን ራስ ባር ያውን ያህል ሰው ሸምቆና አዘንግቶ የገደለ በደለኛ እንዴት ይቅር ይሉታል?' እያለ ማጉረምረም ጀመረ ።

አጼ ዮሐንስ በቤተመንግሥታቸው ዙሪያ የተነጣውን ጉር ምርምታ እንደ ሰሙ ዋና ዋናዎቹን መኳንንትና የጦር አለቆች ሰብስበው ፣



"ልጆቼ ወዳጆቼ!

"ሐሳባችሁን ደርሼበታለሁ ፤ ወልደሚካኤል እኔን ብቻ አል በደለም ። ሁላችሁንም አሳዝኗል ። ከሁላችሁም ጋር ደም ተቃብ ቷል ። ትውልድ የማይረሳው በደል በድሏል ፤ የራስ ባርያውን ያህል አዛውንት ደም አፍስሷል ። ቀደም ሲልም ደጃዝማች ኃይሉን ያህል ሰው ገድሏል ። እንግዲህ የሾምኳቸውን ሁሉ ከመግደል የበለጠ ምን ድፍረትና በደል አለ? ይህም ሁሉ አልበቃው ብሎ መሐላውን አፍርሶ ጭፍራውን ሁሉ ሰብስቦ ከግብፅ ጉን ተሰልፎ ኢትዮጵያን ወጋት ። እናቱን በደላት ። በደሉ መቼም ታይቶ ተሰምቶም አይታወቅም ።

"ለአገራችን አንድነት ስንል ግን ምሕረትንና ትዕግሥትን ገንዘባችን ማድረግ ተገቢ ነው ። የአጼ ቴዎድሮስ ኃይል እንኩት ኩት ብሎ ብቻቸውን የወደቁት መኳንንቱ በየፊናቸው በመነ ጣጠሉ ነው ። እኛም ብዙ ጠላት አለብን ። የውጪ ጠላት ገና በበጐስና በምጥዋ እንደ ሰፈረ ነው። ከዚህ ሌላ ደግሞ በውስጣ ችንም ያለውን ነገር ታውቁታላችሁ ።

"አሁን ወልደ ሚካኤልን ምሕረት ብንነሣው አገር መለያየት ይጀምራል ። ያኮረፈ ሁሉ በዚያው ይቀራል ። የኛ መነጣጠልም በዳር ሆኖ ለሚጠባበቀው ጠላት የሚጠቅም ይሆናል ። አሁንም ሁላችሁም ብትሆኑ ወልደሚካኤልን 'ይቅር' በሉት ፣ ታረቁት ፣ አቅርቡት ። እኔም 'ይቅር' ያልኩት ፣ እናንተም ይቅር ብላችሁ እንድትታረቁት ብዬ ነውና ምከሩት'' ብለው ጠየቁ ።

መኳንንቱም ነገሩ ከልባቸው የገባና የሚያምኑበትም መሆ ናቸውን ስላረጋገጡላቸው ፣ ደጃዝማች ወልደ ሚካኤልን አስቀርበው ከመኳንንቱና ከጦር አለቆቹ ጋር አስታረቁ ።

ከእርቁ በኋላ መኳንንቱና የጦር አለቆቹ ሲወጡ ራስ አርአያ ወደ አጼ ዮሐንስ ቀረብ ብለው ።

"ምሕረት ማድረጉና መታረቁ ተገቢ ነው ። ታዲያ ስለ መቶ ዳደሪያውስ ምን አስበሀለታል?'' ብለው ጠየቋቸው ።

"እርስዎ ምን ያስባሉ? ወደ አገሩ ይግባ? ወይስ ከዚሁ ይሰንብት?" ብለው መልሰው ጠየቋቸው ።

"አገሩን ብትሰጠው መልካም ነው ። ለጊዜው ከአሉላ ሥር ሆኖ አሉላን እየጠበቀና እየረዳው ቢቆይ የሚሻል ይሆናል" አሉ ራስ አርአያ ።

"አሉላን ከምንድን ነው የሚጠብቀው?" አሉ አጼ ዮሐንስ በመጠራጠር ስሜት ሆነው ።

"ሁልጊዜ የዋህነት አያዋጣም ፤ አሉላም ቢሆን ከቤታቸው ከገባ በኋላ የእምለሱን እጅ ከሰጠነው ወዲህ የምስግበት አንዳንድ ጉዳይ አለና ከኛ ርቆ ብቻውን ሆኖ የሚሠራውንም የሚመለከት ያስፈልገዋልና ወልደ ሚካኤልን ራስ ብለህ ከአሉላ ሥር ሆኖ እንዲጠብቀው ቢደረግ ይሻላል" አሉዋቸው ።

አጼ ዮሐንስ የአጐታቸውን ምክር በልባቸው አሳደሩዋት ። ወልደ ሚካኤልን 'ራስ' ብለው ወደ መረብ ምላሽ ቢልኩ ለጊዜው በዚያ በኩል አገሩ ከተደላደለላቸው የማስፈራሪያ ዱላቸውን በእጠገባቸው አስቀምጠው ወንዝ የወለደውን እፈንጋጭ ቅስመን ለመስበር ፣ አገር ለማደላደልና ለማስገበር እንደሚያመቻቸው አመኑበት ። በዚሁ መሠረት ደጃዝማች ወልደ ሚካኤልን 'ራስ' ብለው በራስ አሉላ ሥር ሆነው ሐማሴንን እንዲገዙ ሾሙዋቸው ።

ራስ ወልደ ሚካኤልም ለአጼ ዮሐንስ ብቻ ሳይሆን ለራስ አሉላም ፍጹም ባለውለታና ፍጹም ታማኝ መሆናቸውን በመሐላ አረጋግጠው ወደ መረብ ግዶ ሲሻገሩ አሉላም በሸዋና በወሎ መካከል ሠፍረው እንዲቆዩ ታዘዙ ። ራስ ወልደ ሚካኤል ሐማሴን ደርሰው ከዋና ከተማቸው ፀጋ ከገቡ በኋላ በሥልጣን ተፎካካሪያቸው በነበሩትና ወኪደባ ላይ ሸምቀው በገደሉዋቸው በደጃዝማች ኃይሉ ቤተሰቦች እንደዚሁም እርሳቸው ኢትዮጵያን ከድተው ለግብፅ ጦር እዛዥ መግባታቸውን ሲታወሙ በነበሩ ካህናትና ባላባቶች ላይ ጥቃት ማድረስ በመጀመራቸው ተቃዋሚዎቻቸው ወደ ዐድዋ እየገቡ ፣ 'ቂም በቀል ፈጸሙ



ብን ፤ ራሳቸውም ከግብፆች ጋር በምስጢር መላላክ ጀምረዋል' የሚል አቤቱታ ወደ አጼ ዮሐንስ አስተላለፉ ።

ይህም አቤቱታ ፣ ንጉሠ ነገሥቱን ዐብርቱ የሚያሳስብ ሆኑ ። አሉላን እንዲቆጣጠሩ ተብለው የተሾሙት ሰውዬ እንደገና ከባድ ችግር ሊያስከትሉ እንደሚችሉ አጼ ዮሐንስ ወዲያው ተረዱት ።

'ወልደ ሚካኤል ከግብፆች ጋር ተስማምቶ ወደ ሐማሴን ካስገባቸው እንደገና መልሶ ለማስወጣት ያስቸግረናል' ብለው ፣ በመኻል ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩትን እምቢተኞች ችላ ብለው በሰሜን ኢትዮጵያ በኩል ስለ ነበረው ሁኔታ ከራስ አሉላ ጋር ሲመካከሩበት ፤

"ነገሩ ግልጽ እየሆነ ነው ፤ በጉስና ምፅዋ የግብፆች ይዞታ እንደሆኑ እንዲቀሩ እንግሊዞች ይፈልጋሉ ። ሁለቱ መንደሮች በግብፆች እጅ መቆየታቸውን ከተስማማንላቸው ጥይትና የአጼ ቴዎድሮስን ዘውድም ጨምረው እንደሚልኩልን ፈቃደኞች መሆናቸውን ልከውብኛል ። ለአንድ ግጥን ጥይትና ሰርቀው ለወሰዱት ዘውድ ስል የአገሬን ርስት አሳልፌ የምሰጥ አይደለሁምና ፣ እንግዲህ በእነርሱ በኩል ያለው ሐሳብ ይህ ከሆነ ወልደ ሚካኤልን እንደ ለመዱት አትሬው እሳት ሊያስጭኑብን እንደሚችሉ መገመት አይሳነንም ። በመካከላችን ያለው የእርስበርስ ጉዳይ ጐድቶ አይጐዳንምና የሚበቃህን ያህል ወታደርና ስንቅህን አዘጋጅተህ ወደ ሐማሴን እንድትሔድ ፈቃዴ ነውና ሐሳብህን ንገረኝ" አሉዋቸው ።

"ከዚህ ሌላ ምንም ሐሳብ የለኝምና ፣ መርተው ይላኩኝ ጌታዬ?" አሉ ራስ አሉላም ።

ከዚህ በኋላ ራስ አሉላ ከሻያ ሺህ በላይ የሚሆን ሠራዊት አስከትተው መረብን ተሻግረው ጉራዕ ሠፈሩ ። ራስ ወልደ ሚካኤልም ሐዶው ተቀበሉዋቸው ። በምፅዋና በቦጐስም እስከ እምስት ሺህ የሚደርስ የግብፅ ጦር ሠፍሮ ስለ ነበረ ሁኔታው እጅግ የሚያሠጋ ሆነ ። በዚያ ዘመን በሐማሴንና በምፅዋ የነበሩ የውጪ አገር ተወላጆች ወደ ራስ አሉላ እየቀረቡም ሐሳባቸውን ለማወቅ ጥረት ጀመሩ ። አሉላም ከእነርሱ ጋር ሲን

ጋገሩ፣ "ምፅዋን ከግብፆች እጅ ነጻ አወጣታለሁ ። ፈረሴ ከቀይ ባሕር ውሃ ሳይጠጣ ከቶ አልመለስም" እያሉ በመናገራቸውና ባለሟላቸውም፣

"ምፅዋን ከግብጾች ነጻ ሊያወጣት
ወደ እናት አገሩዋ እንዲመልሳት
አዞታል ዮሐንስ በጥብቅ አስጠንቅቆ
የኢትዮጵያን ወኔ ጀግንነት አስታጥቆ
ከቀይ ባሕር ውሃ ፈረሱ ሳይጠጣ
አይቀርም አሉላ የመጣው ቢመጣ"

እያለ በማስተጋባቱ በግብጾችና በደጋፊዎቻቸው ዘንድ ከፍተኛ ሥቀቀን ፈጠረ ። የውጪ አገር ተወላጆችም፣

'ከአሉላ እንደዚህ ያለ ቃል ከወጣ ነገሩ ከባድና በተግባር ላይ የሚውል ነው ፤ ሰውዬው ቆራጥና ፈጣን ስለሆኑ በግብጾች ላይ ብቻ ሳይሆን በሁላችንም ላይ እጃቸውን መስንዘራቸው የማይቀር ነው' እያሉ ጭንቀታቸውን ማስተጋባት ጀመሩ ።

በዚያን ጊዜ በጉስ በተባለችው ቀበሌ ሠፍረው የነበሩ ሚሲዮናውያን ስብከታቸውን አጼ ዮሐንስ የማይፈቅዱት ከመሆኑም በላይ፣ በዐዋጅ የተከለከለውን የትንባሆ ተክል በእርሻ ዘርተው አልምተውትና ሕዝቡንም አስለምደውት ስለ ነበረ፣ ራስ አሉላ በጉስን ከያዙ በሚሲዮናውያኑና በተባባሪዎቻቸው ላይ ብርቱ ቅጣት ያደርሳሉ ብለው እጅግ ፈሩ ።

በተለይም እንግሊዝ በምፅዋ በኩል የነበሩትን የግብፅ ወታደሮች የአሉላ ሠራዊት የደመሰሰው እንደሆነ የነበራትን የበላይነት እንደምታጣ በመገንዘብ ራስ አሉላ ወደ ምፅዋ እንዳይወርዱና ነገሩን እንዲነጋገሩበት መወትወት ጀመረች ።

ራስ አሉላ ግን 'ለግብፆች ጥቅምና ክብር እንግሊዞች ቢቆረቆሩም፣ ለኢትዮጵያ ክብርና ጥቅም ደግሞ እኛ አለንላት' አሉና በራስ ወልደ ሚካኤል ትእዛዝ ሥር የነበረው ሠራዊት ወደ በጉስ እንዲዘምት አዘዙ ።



በከንቲባ ሻዊት የሚመራ የራስ ወልደ ሚካኤል ጦር በጉስ ገብቶ ሠፈረና ሕዝቡን ማስገበር ጀመረ ። በከረን ምሽግ አድፍጠው የነበሩት የግብፅ ወታደሮችም እንድም ተቃውሞ ሳያሳዩ በጽሞና ነገሩን ተቀበሉት ። ነገር ግን ይህ ጦር የግብፆችን ምሽግ ባለመንካቱ ራስ ወልደ ሚካኤል 'ከግብፆች ጋር ምሥጢራዊ ስምምነት አድርገው ይሆናል' የሚል ጥርጣሬ በራስ አሉላ ልብ ተሰነቀረ ።

ከዚያ በፊትም 'ራስ ወልደ ሚካኤል በምፅዋና በጉስ ከሚገኙት ግብፆች ጋር መላላክ ጀምረዋል' ተብሎ ለአጼ ዮሐንስ ከደረሰው ማስጠንቀቂያ ጋር ሁኔታውን ማገናዘብ ጀመሩ ። በመካከሉ ታዲያ የራስ ወልደ ሚካኤል አጐት ከንቲባ ኃይሉ ከራስ አሉላ ዘንድ ቀርበው ራስ ወልደ ሚካኤል ከግብፆች ጋር በምሥጢር በመላላክ ላይ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ ። ከእርሳቸው ቀጥለው ደግሞ ደጃዝማች መሸፍን፣ ልጅ ኃይለ መለኮትና ባላምባራስ ክፍለ ኢየሱስ ቀርበው ነገሩ እውነት መሆኑን በመሐላ ያረጋግጣሉ ። ከዚህ በኋላ ራስ አሉላም ራስ ወልደ ሚካኤልን ከነልጃቸው አስይዘው በታማኞቻቸው አሳጅበው ወደ አጼ ዮሐንስ ሰደዱዋቸው ። ንጉሠ ነገሥቱ ግን በራስ አሉላ መልእክት ብቻ በራስ ወልደ ሚካኤል ላይ ለመፍረድ ባለመፍቀዳቸው ራስ አሉላን አስጠርተው ሁለቱንም ግራና ቀኝ አቁመው ካከራከሩዋቸው በኋላ፣ ራስ ወልደ ሚካኤል እንዲታሠሩ ስለ በየኑባቸው፣ ከነልጃቸው በአባ ሰላማ ተራራ እንዲቀመጡ አዘዙ ።

# ቁርጠኛው አሉላ

የራስ ወልደ ሚካኤል መታሰር በጣብያች ዘንድ ያሳሰቡት ዱላ ሆነ ። «ዮሐንስ ካስቸገረ ወልደ ሚካኤልን ማደርጀት ነው» እያሉ ሲተማመኑባቸው ስለ ነበረ ፣ ወልደ ሚካኤል ከፊታቸው ሲሰወሩ እንበለ መጋረጃ ከአሉላ ጋር መፋጠጡ በይበልጥ አሳሳቢ ሆነባቸው ። የአሉላን ብርቱ ክንድ ሊመክት የሚችል ጉልበት ከማጠናከር ሌላ አማራጭም አልነበራቸውም ።

የአሉላ ጦር ከረን የሚገኘውን የግብፅ ምሽግ ከያዘ ወደ ምፅዋም ሆነ ወደ አሰላ ሊወረወር እንደሚችል በይበልጥ የተረዱት ደግሞ እንግሊዞች ነበሩ ። በእርግጥም አሉላ ያን እጅግ አስፈላጊ የነበረ ምሽግ ከያዙ እንግሊዝ በግብፅ ላይ ታዝባ ይዛው የነበረውን ጥቅምና ክብር ወደ ማጣቱ ልትደርስ ሆነ ። ስለዚህ ከዚያ ውድቀት ላይ ከመድረሱዋ በፊት ፣ ነገሩን በዲፕሎማሲ ማለዘቡን ሁለቱም ወገኖች ስለ አመኑበት ፣ የሱዳን ጠቅላይ አገረ ገዥ የነበረው ጐርደን ከራስ አሉላ ጋር ለመነጋገር እንዲችል ፈቃድ የሚጠይቅ ደብዳቤ ጻፈላቸው ። እርሳቸውም ፈቃደኝነታቸውን ስለ አስታወቁት እርሳቸው ወደ ነበሩበት ጉራዕ ወደ ተባለው መንደር ሔደ ።

ራስ አሉላ ጐርደንን ተቀብለው ሲያነጋግሩት ፣

«ምንም እንኳን ንጉሠ ነገሥቱ የከለከሉም ቢሆን ትግባ ሆዎን ቢሞት ቅር አይለኝም» አሉት ፈገግታቸውን ጭምር እየጋበዙት ።

«ስለ ነጻ አስተሳሰብዎና በሱሰኛነቴም እንዳልቸገርብዎ ስለ አሰቡልኝ ከልብ አመሰግናለሁ» አለ ጐርዶንም ከፍ ባለ ትሕትና ።



«እንግዲህ ወደ ዋናው ወደ መጡበት ጉዳይ ከመግባታችን በፊት ፣ አመጣጥዎ ከእንግሊዝ መንግሥት መሆኑን እንዲያረጋግጡልኝ እፈልጋለሁ» አሉትና ጥቂት ቆይተው ደግሞ ፣ «እንደ ተረዳሁት የእንግሊዝ መንግሥት ባለሥልጣን ነዎት» ብለው አተኮሩበት ። የጐርደን ድንጋጤ ከፊቱና ከሁኔታው ላይ በጉልህ መከሰት ጀመረ ። «ይሰነዘርብኛል» ብሎ ያላሰበበት ጥያቄ ነበር ። ለደቂቃዎች ያህል አንገቱን አቀርቅሮ ቆየና ፣

«የለም የእንግሊዝ መንግሥት መልእክተኛ አይደለሁም ፣ የመጣሁት የቀዲብ ኢስማኤል መልእክተኛ ሆኜ ነው» ብሎ መለሰላቸው ።

የአሉላ ፍላጐት ደግሞ ከቀዲቡ ጋር ሳይሆን ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ለመነጋገር ነበር ። ከዚህ ሌላ ደግሞ ጐርደን ቀደም ሲል በግብፃዊው መኰንን እጅ የላከላቸውን ሐሳብ ያልተስማሙበት ነበር ። የእንግሊዝ መንግሥት መልእክተኛ ያለመሆኑን ካረጋገጡለት በኋላ ፈገግታቸው ቅጭም እያለ መንፈሳቸው እየቀዘቀዘ ሔደ ። «የቀዲብ መልእክተኛማ ሆነው ከመጡ ምን ቁም ነገር ሳገኝበት ነው የምንነጋገረው?» ብለው ፊታቸውን ኮስተር አደረጉበት ። እንዲያውም የጥርጣሬ መንፈስ እየወረራቸው መጣ ። ጐርደን ሊሰልላቸው እንደ ሔደም አድርገው ተመለከቱት ። በመካከላቸው ከባድ ዝምታ ገብቶ ፈንታቀላቸውና ሐሳባቸውን አራራቀው ።

«ለነገር ነገሩ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ለመነጋገር የሚፈልጉ ከሆነ ወደዚያው እልክዎታለሁ ። በበኩሌ ግን እስከ አራትና አምስት ወራት ድረስ ወደ ምፅዋ ወታደር የማላዘምት መሆኔን አረጋግጥልዎታለሁ ። እስከዚያ ድረስ ነገሩ በሰላም የሚያልቅ ከሆነ ግብፅ ጉልበት አለኝ ብላ የያዘችባትን ግዛቷን ለማስመለስ ኢትዮጵያ ደጂ ጠኝ አትሆንም» አሉት ።

ነገሩ በዚሁ አበቃ ። ጐርደንም ቢቸግርው አጼ ዮሐንስን ደግሞ ለማነጋገር ወደ ደብረ ታቦር ተሻገረ ። በቂ ስንቅና ጠባቂም ተሰጥቶት ነበር ። ራስ አሉላ ጐርደንን ከሸኙ በኋላ ዋና ዋናዎቹን የጦር አለቆች ሰብስበው ለሚደረገው ጦርነት መመካከር ጀመሩ ።

ብላታ ገብሩ ። «እም ግብፆች ሰብከውና አስፈራርተው የእነርሱ ረዳቶች ያደረጉዋቸውና ሃይማኖታቸውንም ያስካዱዋቸው መናራቸው ባይከድም ፣ በእነርሱ ወጥመድ ያልገቡና አገራቸውን የሚወዱና ያልበደሉ እስላሞችም በብዛት አሉ ። በተለይም እዚህ ከገባን ወዲህ በጭንቀትና በችግር የተነካ ከእምነቱ ተዛብቶ የነበረው ሁሉ ተረጋግቷል ። መንግሥት ጠንክር ሲል ሕዝቡም ይተባበራልና ይህን ያለ መዘንጋት ነው ። የሆነ ሆኖ ልዩ ተመልካች የመላኩን ጉዳይ በመጀመሪያ የምናስብበትና በቅድሚያም ውጤቱን የምንፈልገው ነው» አሉ ራስ አሉላ ።

ከዚያ ቀጥሎ በጐስንና ምፅዋን ከግብፆች እጅ ፈልቅቀው ለማውጣት የሚያስችላቸውን ስልትና ዝግጅት ማቀለጣጠፍ እንደ ጀመሩ ፣ ቀደም ብሎ ጅዳ ውስጥ በቆንሲልነት ሲሠራ ቆይቶ በኋላ በንግድ ሥራ ላይ ተሠማርቶ የነበረ እውግስቶስ ዋይልድ የተባለ እንግሊዛዊ ራስ አሉላን ለማነጋገር ስለ ፈለገ እንዲገባ የፈቃድ መጠየቂያ ደብዳቤ ላከላቸው ።

ዋይልድ የኢትዮጵያን ሁኔታ በሚገባ ያወቀና ደጋፊም ስለ ነበረ ፣ በዲፕሎማቲክ ሙያው ላይ የሚሠራ እንጂ በንግድ ተግባር ላይ የተሠማራ መሆኑን ስላላወቁ ፣ ጥያቄውን ተቀብለው ቢያነጋግሩት ነገሩን በሰላም ለመጨረስ እንደሚረዳ በመተማመን የጠየቀውን ፈቃድ ሰጡትና ገዛግሮ እዲ ተክላይ ድረስ ሔደ ። እርሱም የኢትዮጵያን ጉዳይ በቀጥታ ለእንግሊዝ ንግሥት ቪክቶሪያ ሊያስተላልፍ እንደሚችል ስላረጋገጠላቸው ውይይቱን ሲጀምሩ ፣ ራስ አሉላ ፣ «ግብፅ በሀገራችን ውስጥ ጦር አሥፍራ በሕዝብ ላይ ግፍ መሥራቷን እንደ ቀጠለች ናት ። የክርስትናንም ሃይማኖት እያጠፋች ነው ። ወደ ኢትዮጵያም ጳጳስ እንዳይመጣ ከልክላለች ። በዚህ የተነካ ከግብፅ ጋር መነጋገሩንና መዋዋሉንም ትተነዋል እና . . .» ብለው ራስ አሉላ ንግግራቸውን ሳያጠቃልሉ ዋይልድ ጣልቃ ገባና ፣

«አገርዎ የሚገባትን ካሣ ተቀብላ በጐስን ብትለቅስ?» ብሎ ንግግር ሲጀምር ራስ አሉላም ሐሳቡን ተቃወሙ ፣

«እስቲ አንድ ነገር መልሼ ልጠይቅህ?» አሉና የሰፊውን ንግግራቸውን ቆዳ ሰብስበው ዐይኖቻቸውን ተከሉበትና ፣



«ቻይና ከሕንድ አገር አንዱን ግዛት ይዛ ግምቱን ገንዘብ ልክፈል ብትል አገርህ እንግሊዝ ትስማማለች?» አሉት ።

ዋይልድ መልስ አልነበረውምና አንገቱን ደፍቶ ዐይኖቹን ከወለሉ ላይ ተከሉ ዝም አለ ።

«ኢኮ እንግሊዝ ይህን ጉዳይ ትስማማበታለች?» አሉ ራስ አሉላም እንዳፈጠጡበት ።

«ገባኝ ነገሩ ገብቶኛል» አለ ዋይልድ እንዳቀረቀረ ።

«ታዲያ ይህንኑ ለመንግሥትህ ልታሳውቅልኝ ትችላለህ?" አሉ ራስ አሉላ ።

«የማውቀውን ያህል ሐሳብዎን አብራርቼ ወደ መንግሥት አስታውቃለሁ» አላቸውና ለንባብቶ ተመለሰ ። ዋይልድ ጉዳዩን ወደ ለንደን ቢያስተላልፍም ፣ መንግሥት ሳይወክለውና ሳይፈቅድለትም የገባበት ጉዳይ ስለ ነበረ ተቀባይነት አላገኘም ። እንዲያውም ሁለተኛ እንደዚያ የመሳሰሉ የመንግሥታት ጉዳዮች ውስጥ እንዳይገባ ተከለከለ ። ከዚያ በኋላ ግን የሰሜን ኢትዮጵያ ጉዳይ ለእንግሊዝ መንግሥት ጭላንጭሉ የተዘጋበት ሆነ።

ግብፆች በጐስና ምፅዋ ከእጃቸው እንዳይወጡባቸው በተከላካይነቱ መድበዋቸው የነበሩት ራስ ወልደሚካኤል ከነልጃቸው ከታሰሩባቸው በኋላ ነገሩን በዲፕሎማሲ ለማስታመምና ይዞታቸውን ለማጠናከር አቅደውት የነበረው ደግሞ በእንግሊዞች ላይ ነበር ። ግን በጐርደንና በዋይልድ አማካይነት ተጀምሮ የነበረው ጥረት በመክሸፉ ግብፆች ሌላ መጠለያ በማጣታቸው ለጦርነት መዘጋጀቱ ግዴታቸው መሆኑን አመኑበት ። ምንም እንኳን ለጦርነቱ ራስ አሉላ ቢዘጋጁበትም ቅሉ ፣ በመኻል ኢትዮጵያ የነበረው የሥልጣንና የዘውድ ሽኩቻ አጼ ዮሐንስን ከቤጌምድርና ከወሎ አካባቢ እንዳይርቁ ስለ አስገደዳቸው ፣ ራስ አሉላም ወደ ደብረ ታቦር መመላለስና ትግራይም ውስጥ ሆነው የንጉሠ ነገሥቱን እልጋ የመጠበቅ ኃላፊነትም ስለነበረባቸው ሐማሴንን በጦር አበጋዞቻቸው እያስጠበቁ እርሳቸው በዐድዋና በመቀሌ ተቀማጭ ለመሆን ተገደዱ ።

ሠራዊታቸውን በየቦታው ከሰፈሩ በኋላ ፣ «ማንኛውም ሰው የአገር ተወላጅም ሆነ ባዕድ የኢትዮጵያን የበላይነት አምኖ ግብሩን እንዲከፍል» ሲሉ ትእዛዝ አስተላለፉ ። እንደ ታዘዘውም ሕዝቡም ሆነ ሚሲዮናውያኑ ቀጥ ብለው ግብሩን መክፈል ጀመሩ ።

በዚህ ጊዜ በከረን ምሽግ ውስጥ የነበረው የግብፅ ጦር አዛዥ ራሺድ ፓሻ ፣ «ሕዝቡን ከሚያስገብሩ ለምን እስከ ምሽጉ ድረስ መጥተው ከኔ ጋር ጦርነት አይገጥሙኝም?» ብሎ ላከባቸው ።

በዚህ መልእክት አሉላ አልተበሳጩም ፤ አላዘኑም ፤ እንዲያውም ከትከት ብለው ሣቁና ፣

«አገሩና ሕዝቡ የግብፅ ግዛት ነው እያልክ ስትፎልል የኖርከው አንተ አይደለህም? ሕዝቡ ኢትዮጵያዊነቱን ዐውቆ ግብር እንዳይከፍል ስትከለክለው የኖርከውስ አንተ አይደለህም?አሁን ደግሞ እንደ ምስጥ መሬት ውስጥ ገብተህ ከምታደፍጥ ወንድነቱና ወኔው ካለህ ለምን ወጥተህ አትከላከልም? እጠብቅሃለሁ ብቅ ብለህ ወንድነትህን አሳየን» ብለው ላኩበት ።

የራስ አሉላ ሠራዊት የሠፈረበት ቦታና የርሳቸውም ቆራጥነት የማያንቀሳቅሰው መሆኑን የተረዳው ግብፃዊው የጦር አዛዥ ምፅዋ ከነበረው የግብፅ ጦር አዛዥ ጋር ተላልኮ ቁጥሩ ሰባት ሺህ የሚሆን በሚገባ የሠለጠነና የታጠቀ ጦር ለዕርዳታ እንዲላክለት አደረገ ። ያንም ጦር ቀደም ብለው አኩርፈው የሸፈቱት ባሕታ ሐጎስ እየመሩ ይዘውለት ከደረሱ በኋላ በአንሰባ ሸለቆዎችና ተራራዎች እንዲሰፍር ተደረገ ። የግብፅ ጦር በእነዚያ ቦታዎች እንዲሰፍር የተደረገው ራስ አሉላ ከምዕራባዊው ቆላ አካባቢ ወደ ደጋው ሲወጡ ከቦ ለመግጠም ነበር ።

ራስ አሉላ ግን ፣ የግብፅን ጦር እንቅስቃሴና ሁኔታውን የሚከታተሉ ልዩ ተመ[illegible]ኞች አሰማርተው ነበርና የደረሳቸውን ጥቆማ ከሁኔታው ጋር አገናዝበው ከምዕራባዊው ቆላ ወደ ደጋው



ሐማሴን ሲመለሱ የግብፅ ጦር ባልጠረጠረበት አቅጣጫ ተጉዘው ፀአዘጋ ላይ ሠፈሩ ።

ራስ አሉላ ፣ ከደጋው ሐማሴን ተነሥተው የአንሰባን ወንዝ ተሻግረው ከረንን ዐልፈው ከሐልሐል ተራራዎች ላይ ሠፈረው ሕዝቡን አረጋግተውና አስገብረው ፣ በከረን ምሽግ የነበረው የግብፅ ጦር የዘረጋባቸውን ወጥመድ ተራምደው እንደገና ወደ ፀአዘጋ የተመለሱበትን ዘዴና ቀልጣፋነት የተመለከቱ አውሮፓውያን ፣ እጅግ ሲያደንቁዋቸው የግብፅ ጦር አዛዥ ግን አንጀቱ አረረ ። ናላውም ዞረ ። በዚያ ወጥመድ አሉላን ከፈጠረቀ በኋላ ሐማሴንን ሙሉ በሙሉ ለመያዝ ጓጉቶ ነበርና !

ራስ አሉላ ከግብፅ ወጥመድ ካመለጡም በኋላ ሠራዊታቸውን በልዩ ልዩ አቅጣጫዎችና ስልቶች ወደ ምዕራባዊ ቆላ እያዘመቱ ከመቈጣጠርና ከማስገበር አልተገቱም ። የግብፅ ጦርም ከምሽጉ ውስጥ ተቀብሮ ሁኔታውን ከመመልከት በቀር ምንም ሊያደርግ አልተቻለውም ነበር ። ራስ አሉላ በከረንም ሆነ በምፅዋ የነበረው የግብፅ ጦር ከምሽግ ወጥቶ ለመግጠም እንደማይደፍር ካረጋገጡ በኋላ ደግሞ ፣

«ግብፅ በስርቆት ከሠፈረችበት ግዛት ካልወጣች ምፅዋንና ከርቱምን በጦር ኃይል እይዛለሁ» እያሉ ማስፈራራት ጀመሩ።

እንዲያውም ይባስ ብለው ከከረን ከተማ በስተምሥራቅ በኩል ወደምትገኘው የደብረሲና ገዳም ሒደው ዐዋጅ አስነገረው ሕዝቡ ለመንግሥት የሚከፍለውን ግብር ለገዳሙ እንዲከፍል ወስነው ለገዳሙ መነኮሳትም አስፈላጊውን ድጋፍና ርዳታ አድርገው ወደ ፀአዘጋ በመመለሳቸው በከረን ምሽግ የነበረው የግብፅ ጦር የመቈጣጠሩ ኃይሉ ፣ ቅስሙ መሰበሩን ሕዝቡ በመገንዘቡ በኢትዮጵያዊነቱ ኮራበት ።

ከግብጾች መስረግ በፊት በጐሰንና አካባቢውን ቱርኮች ከመያዛቸው ቀደም ብለው ፣ ምዕራባዊው ቆላ ማለትም ከረን፣ ሳህል ባርካና ከሰላ የሚባሉት ወረዳዎች የክርስትናን ሃይማኖት የሚከተል ሕዝብ በብዛት ነበረባቸው ። በተለይም ቢለን ማርያ ቤት 'ታውቀ ቤት ታርቀ' የሚባሉት ጐሳዎች ከሥር ከመ

ሠራታቸው ክርስቲያኖች ነበሩ ። በዐሥራ ሦተኛው መቶ ክፍለ
ዘመን መጨረሻ ላይ ፣ ቱርኮች የቀይ ባሕርን አካባቢ መያዝ
ከጀመሩና ከሰሜን ኢትዮጵያም መግባት ከጀመሩ ወዲህ ግን
የእስልምናን ሃይማኖት ለማስፋፋት ቆይሰውት በነበረው ስልትና
ባወጡትም ጥብቅ ትእዛዝ የተነሣ ከላይ በተጠቀሱት አካባቢ
ዎች ሠፍረው የነበሩት ጐሳዎች የእስልምናን ሃይማኖት መከ
ተል ጀመሩ ።

የቱርክ መንግሥት ኃይል እየደከመ መጥቶ በቁጥጥሩ ሥር
የነበሩትን አገሮች እየለቀቀ ሲሔድ በቀይ ባሕርም ሆነ በም
ዕራባዊው ቆላ በኩል ግብጾች መግባት ጀመሩ ። ወዲያውም በቁ
ጥጥራቸው ሥር የገባው ሕዝብ ሃይማኖቱን እንዲለውጥ በማስ
ገደዳቸው በአካባቢው የነበረው የተከታያቸው ወገን ቁጥር እያ
ደገ ሔደ ። ቢሆንም ራስ አሉላ ደብረ ሲና ከተባለችው ገዳም
ድረስ ሔደው ያሰሙት ዐዋጅና የሰጡትም ድጋፍ የክርስቲያ
ኑን ሕዝብ እምነት እያጠነከረው መሔዱን ግብጾች ስለ ተረዱት
ቅስሙን ለመስበር ሲሉ በራስ ወልደሚካኤል ምትክ ከጉያቸው
ተወትፈውላቸው የነበሩትን ባሕታ ሐጐስን በቂ ወታደር ሰጥ
ተው የደብረ ሲናን ገዳም እንዲያጠፉላቸው ላኩዋቸው ።

ባሕታ ሐጐስም እንደ ታዘዙት ወደ ገዳሙ ሔደው ገዳ
ሙን አቃጥለውና ዘርፈው ቀሳውስቱ ፤ ፈጅተው ተመለሱላቸው ።
ራስ አሉላ ነገሩን እንደ ሰሙ ፣ «አገር በንቲን ታፈራሰችን!»
ብለው ምርር ብለው አዘኑ ። ነገሩም ግብፆችን እጅግ ስላስደሰ
ታቸው ፣ «ከአሉላ ጋር ከመፋጠጥ በሸፍቶች ማስጨነቅ » የሚል
ስልት ቀየሱና በምፅዋ በኩልም እንደ ደጃዝማች ወልደሚካ
ኤል ወይም እንደ ባሕታ ሐጐስ የመሳሰሉ ያኮረፉ ባላባቶ
ችና የሃይማኖት ተጠሪዎች መሰብሰብ ፣ ማሠልጠንና መርዳት
ጀመሩ ።

ራስ አሉላ የራስ አርአያ ድምፁ የቤት አሽከር በነበሩበት
ጊዜ በዕለት ጥል ግብግብ ገጥሟቸው ከመሬት የደባለቁት የድ
ሮው «የጌታቸው ልጅ» ደበበ አርአያ ፣ አጐቱ አጼ ዮሐንስ
የፊታውራሪነት ማዕረግ እንጂ ከዚያ ላቅ ያለ ሹመት ስላልሰ
ጡት ፣ በዚሁ አኩርፎ ኮብልሎ አሳውርታ ውስጥ ገብቶ ፣



«እኔ የራስ አርአያ ልጅ ነኝ ። ወንድሜ አጼ ዮሐንስ የአባ
ቴን ግዛት ስለቀማኝ ፣ በዚሁ ተጣልቼ መጥቻለሁ ። የኔን መሸ
ፈት የሰሙ መኳንንትና ባላባቶችም ወደኔ እየመጡ ናቸው ።
ከንጉሡ ነገሥቱ ጋር የሚቀር አንድም መኳንንት አይኖርምና
እናንተ እንድትረዱኝ መጥቻለሁ» ብሎ ምፅዋ ለነበረው የግብፅ
ወኪል መልእክተኛ ሰደደ ። ይህም ነገር ለግብፆች ታላቅ የም
ሥራች ሆነ ።

ለደበበ አርአያ የሚፈለገውን ሁሉ እየሰጡ ራስ አሉላን
መቋቋምና ማስቸገር የሚፈልጉትን ውጤት እንደሚያስገኝላቸው
የተረዱት ግብፆች ፣ በወቅቱ ያሰቡትን ሁሉ በተግባር ለማዋል
አመች ሆነላቸው ። ባሕታ ሐጎስና ደበበ የሚሠሩትን አሳፋሪ
ሥራ ራስ አሉላ እንደ ሰሙ ፣ «ግብፆች ዛሬም አንድ አውራ ዶሮና
አንድ ቡችላ አገኙ!» ብለው ተካከዙና ፣

«ግዴለም አውራ ዶሮውን በጥሬ ፣ ቡችላዋን በወተት አባ
ብዩ እይዛቸዋለሁ » አሉ ።

ሁለቱን ከጠላት ጉያ የተሸጎጡትን «አውራ ዶሮና ቡችላ»
ለመያዝ በሚያውጠነጥኑበት ወቅት በረድ ብሎ የነበረው የመ
ኻል ኢትዮጵያ ደግሞ እንደገና መገንፈል ስለ ጀመረ ፣ አጼ ዮሐ
ንስም የማስፈራሪያ ዱላቸውን ከሰሜን ወደ መኻል አገር
አዛወሩ ።

የችግሩም መነሾ እንዲህ ነበር ። ቀደም ብሎ አጼ ዮሐንስ
የጐጃም ራስ አዳልን «ተክለ ሃይማኖት» ብለው ሠይመው የን
ጉሥነት ማዕረግና ጐጃምን ሰጥተዋቸው ሁኔታው ተረጋግቶ
ነበር ። በመካከሉ ንጉሥ ምኒልክ እንደገና አሻፈረኝ ብለው
ተነሡና ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጋር እምባቦ ላይ ጦርነት ገጥ
መው አሸንፈው ገሚስ ጐጃምን ያዙ ። ይህም ነገር አጼ
ዮሐንስን እጅግ ስለ አሳሰባቸው ፣ መኳንንቶቻቸውንና የጦር አለ
ቆቻቸውን ሰብስበው ፣

«ምኒልክ የገባውን ቃል እያፈረሰ ከትእዛዜም እየወጣና
እየጎለበተም መጣ ። ከዚህ ቀደም ባሳየው አሻፈረኝነት ፈጥኖ
ጦር አላዘመትኩበትም ነበር ። ለከፋ ቀን የሚሆን ፣ የውጭ ጠላት

ሲመጣ የሚመክሩ ጀግኖች ፡ በኔና በርሱ ወገን ሆነው እንዳይ ተባለቁ የጀግኖች ደም በከንቱ እንዳይፈስ በማለት የሃይማኖት አባቶች በመካከላችን እንዲገቡ አድርጌ ፡ ነገሩ ደስ በማያሰኝ መንፈስ እልባት አግኝቶ ነበር ።

«አሁን ደግሞ ይኸውና እንዲህ ያለ ድፍረት ፈጸመ ። የጠላ ሁት የአንዲት እናት ልጆች ደም በከንቱ መፍሰስ የማይቀር ሊሆን ነው ። እንግዲህ እናንተም ምከሩበትና የሚሆነውን አመ ልክቱኝ » ብለው አስታወቋቸው ።

«እንደዚህ የሆነበት ምክንያቱን ታውቋል?» አሉ ራስ አር ኢያ ።

«አከረፍኩ ብሎ ነዋ!» አሉ አጼ ዮሐንስ ።

«በምን የተነሣ ?»

«ግዛቴ ተቀርጦ ለተከለ ሃይማኖት ለምን ተሰጠብኝ ብሎ!»

«እህ እወይ ምኝነት» ብለው ራስ አርአያ ለጥቂት ጊዜ በዝምታ ታፍነው ቆዩና ፡

«ይህስ ቢሆን መች የሚያስከርፍ ነበር? ለሁላችንስ ቢል ክብሩን በእርጋታ ሊሆን ይችል አልነበረም? አሁንም እንዳልከው የአንዲት እናት ልጆች ደም ከምናፋስስ እነዚያኑ የፊተኞቹን ሰዎች መልሶ መላክና ነገሩ በእርቅ እንዲያልቅ ማድረግ ነው ። ደም ለማፋሰስ ያለ መቸኮሉ ተገቢ ነው» አሉ ።

ቀጠል አድርገው ደግሞ ራስ አሉላ ተነሡና ፡

«የእርስ በርሳችን መበጣበጥ ነው ለጠላቶቻችን በር ከፍቶ ይኸውና በጉስንና ምፅዋን ያስያዘብን ። አሁንም በመካከላችን ደም መፋሰሱ ከቀጠለ ጠላት እንደ ለመደው እስከ በራፋችን ለመ ምጣት ይጠባበቀናል ። ንጉሥ ምኒልክ በርካታና ጠንካራም ሠራ ዊት እንዳላቸው እናውቃለን ። አሁን ደግሞ የጉጃምን ጦር ሲጨ ምሩ የበለጠ እንደሚጠነክሩ አያጠራጥርም ። ከዚያ በኋላ ጦር ነት ብንገጥም የግራ ቀኛችንም ሠራዊት ይተላለቅና አገሪቱ ፈጽማ



ባዶ እጇዋን ቀርታ ጠላቶቻችን ሰተት ብለው የሚገቡባት ትሆ ናለች ።

«እንግዲህ ለዚህ የሚታየኝ ከዚሁ ሆነን ብንላላክ ፡ ንጉሥ ምኒልክ ጦራቸውን ለማዘጋጀት ጊዜ ያገኙና በኋላ እምቢ ሊሉን ያመቻቹዋል ። ለዚህ መድኃኒቱ ሳንውል ሳናድር ወደዚያው ቀረብ ብለን ብንላላክ የደከመው ፈረሳቸው ከማንበራራቱ በፊት ልና በፈራራቸውና አቅማቸውን ዐውቀው ሊመለሱልን ይገደዳሉ» ታዲያ ለዚህ ለዚህ የሚረዳው ፈጥኖ መሔድ ነው» ብለው ተቀመጡ ። አጼ ዮሐንስ መኳንንቱን ምክር ጠይቀው እሱላ ከተናገሩ በኋላ ፡ ሌላ ምክር መስማት ጎደል እንደ መግባት ሆኖ ስለሚታያቸው ፡ በዝያ ዕለትና ስብሰባም ሌላ ተናጋሪ ሳይጠብቁ ፡

"ነገርህ ከልቤ ገብቷል ፤ ሌላ መጨመር አያስፈልገም ፤ ነገውኑ ጉዞ እንዲጀመር ይሁን" አሉና ወሰኑ ።

በዚሁ መሠረት ከደብረ ታቦር ተነሡና ወደ ወሎ ተጉዘው ወረኢሉ ሠፈሩ ። እጅግ አሥግቶ የነበረው የወንድማማቾች መተላለቅም እንደገና ሊወገድ የሚችልበት ዕድል ተፈጠረ ። ንጉሥ ምኒልክ አቅማቸውን ገምተው በፊት የማሉትን መሐላ አስታውሰው ፡ ለንጉሠ ነገሥቱ መልእክተኞች ሰደዱና ቁጣቸውን አብርደው ለእርቁ ተዘጋጁላቸው ።

አጼ-ዮሐንስ ምኒልክን ብቻ ይቅር ብለው ከመታረቅ ሁለ ቱን ንጉሦች ማስታረቅም የበለጠ ውጤት እንደሚያስገኝ በማ መዛዘን ወረኢሉ ድረስ እንዲመጡ ላኩባቸው ። ከዚያ በኋላ ምስቱም እርቃቸውን በመሐላ አጸደቁ ።

አጼ ዮሐንስ ፡ የሁለቱን ንጉሦች ግጭት መርምረው የየግዛ ታቸውን ክልል አከፋፍለው አደላድለው ከአስማሙ በኋላ ፡ ከን ጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሠራዊት ይበልጠውን እጅ ቀንሰው ለማ ሰፈራራያ ዱላቸው ጨምረው ከምኒልክም ጋር ሁለተኛ ለድብድብ ላለማሰላለፍ ቢሉ ልጃቸው ራስ አርአያ ሥላሴን ከንጉሥ ምኒልክ ልጅ ከወይዘር ዘውዲቱ ጋር እንዲጋቡ እንደ ባህሉና እንደ ወጉም «ልጅህን ለልጄ» ብለው ወደ ምኒልክ ሽማግሌ ላኩ ። በጋብቻው ምኒልክም ተስማሙና ድግሳቸውን ሊደግሱ ወደ

ሽዋቸው ተመለሱ ። የአጼ ዮሐንስ መኳንንቶች በተደረገው እርቅና በጋብቻው መስማማታቸውን ሲገልጹ በዓለም ላይ የተደነቀችውን ቆንጆ በክንዳቸው መፈርጠም ድል አድርገው ለራስ አርአያ ለማቅረብ ይመኙ የነበሩት አሉላ ብቻ ፤

«በጋብቻ መተሳሰሩ ሰላም ሊያወርድልን ፤ አንድነታችንን ሊያጸናልን መቻሉ ማለፊያ ነው ። ግን እንዲያው ግን . . . . .» ብለው ሲናገሩ ያሰቡትን ዋዋ ሲያደርጉት ፤ አጼ ዮሐንስ አዩዋቸውና ፤

«ተናገረው እንጂ? ከመች ወዲህ ነው ነገር መዋጥ የለመድከው ?» ብለው አፈጠጡባቸው ።

«እንደ ሰማሁት ዘውዲቱ ቆንጆ ናት ፤ ለኛ ልጅ ትገባዋለች ተብሎ ነው?» ብለው የልባቸውን ተናገሩ ። ንጉሡ ነገሥቱም ፊታቸውን ዘወር አድርገው ፈገግ ብለው እንደ መሣቅ አሉና ፤

«ስማህ ልጄ ሁለት ወዶኮ አይሆንም ፤ አንድነት ፈልገን ሰላም ፈልገን ፤ መልክ መርጠን አይዘለቅም» አሉዋቸው ።

ከዚያ በኋላ ራስ ቢትወደድ ገብረ መስቀል ቱርክ ፓሻ ራስ አሉላ ፤ ራስ ገብረኪዳንና ሌሎችም መለስተኞች መኳንንት ሆነው ወጣቱን ከሙሽራ ራስ አርአያ ሥላሴን አጅበው የነገር አባትና ሚዜ ሆነው ምኒልክ ግቢ ሆ ! ብለው ገብተው ሙሽሪት ዘውዲቱን አዝለው ወደ መቀሌያቸው ተሻገሩ ።

በመኻል ኢትዮጵያ ገንፍሎ የነበረው ትኩሳት በርዶ ዳግመኛም እንዳያገረሽበት በጋብቻ ተጠልፎ ሲያዝ በስሜኑ በኩል የነበረው እንቱሉት ደግሞ እየተነነ ማበቸገሩን በመቀጠሉ እንደ ተመለመደው የማስፈራሪያው ዱላ ወደ መረብ ተወረወረ ።

ራስ አሉላ ፤ በመኻል ኢትዮጵያና በትግራይ ውስጥ ከንጉሥ ነገሥቱ ጋር ይቀመጡ በነበረበት ጊዜም ቢሆን በመረብ ምላሽ ግዛታቸው ኃላፊነትና አደራ ሰጥተዋቸው የነበሩት ወኪሎቻቸውና የጦር አበጋዞቻቸውም ቢሆኑ ፤ በበጉሉስና በምፅዋ የነበሩት ግብጾች ወደ ደጋው አካባቢ እንዳይወጡ መከላከል



ብቻ ሳይሆን አመች ጊዜ እየፈለጉም ለማጥቃት ይሞክሩ ነበር ። ግብፆች «የኛ ግዛት ነው» በሚሉት ወረዳና ጉሳም መካከል እየገቡ የኢትዮጵያን የበላይነት እያሳጡ ግብር እያስከፈሉ ሁኔታውን ይቆጣጠሩ ነበር ። ይህም ሁኔታ ካይሮን እጅግ እያሳሰባት በመሔዱ «የኔ ግዛትና ድንበር» ስትለው በነበረው ቀበሌ ሁሉ የኢትዮጵያ ወታደሮች እንዳይደርሱ ለማስድረግ የሚያስችላትን ስልት መቀየስ ጀመረች ። በዚህም መሠረት ስልቱን የሚነድፉላትን ባለሙያዎቿን ወደ ከረንና ምፅዋ ሰደደች ። ባለሙያዎቹ ባቀረቡት ሐሳብም ላይ ፤

1ኛ. በምፅዋ በከረንና በሌሎቹም በቁጥጥሩዋ ሥር በነበሩት ቀበሌዎች የተጠናከሩና በንስለት ምሽጎች በአስቸኳይ እንዲሠሩ ።

2ኛ. የግዛቶቹ አማካይ የአስተዳደር ሰፈር ምፅዋ እንዲሆን፤

3ኛ. ከዐሥር ሺህ በላይ ለሚሆን ወታደር ማስፈሪያ የጦር ወረዳዎች ሠፈሮችና ቤቶች እንዲዘጋጁ ።

4ኛ. ከአጼ ዮሐንስ ጋር በልዩ ልዩ ምክንያት የሚጣሉና የሚጋጩ ፤ እንደዚሁም የእስልምና ሃይማኖት ተጠሪዎች እየተመረጡ ሕዝቡን እንዲሰብኩላቸውና መሣሪያ እየተሰጣቸው የኢትዮጵያን ወታደሮች እንዲወጉ ፤

5ኛ. በመሠራት ላይ የነበረው ከከረን ወደ ከሰላ የሚወስደው መንገድ እንዲፋጠንና ከካርቱም ጋር የማያቋርጥ ግንኙነት ለመዘርጋት እንዲቻል እንዲደረግ» ማጠቃለያ ይገኝበት የሚል ነበር ። በዚህም ጥናታቸው መሠረት በመጠኑ ለመሥራት ሙከራው ቀጠለ ። በጥናቱ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች አሟልቶ ለመሥራት ግን ግብፅ የነበረችበት ሁናቴ የማያስችላት ሆኑ።

ባለሙያዎቿ ያቀረቡላትን ጥናት በሥራ ላይ ተርጉማ ኢትዮጵያን ለመቋቋም የራሷ አቅም ባይፈቅድላትም ፤ የኢትዮጵያን ልጆች እያባበለችና እያስታጠቀች ራሷን ኢትዮጵያን እንዲወጉላት የማድረጉን ስልቷን ግን ቀጠለችበት ። እንዲያውም የተሻለ ዘዴ መሆኑን አመነችበት ።

«እዲሱ ቡችላ» ደበበ አርአያ አሳውርታ ውስጥ ሆኖ እስከ አምስት መቶ የሚደርሱ እጋሚዶችን የሚያስታጥቀው መሣሪያ ግብፅ ሰጠችው ። የወር ደመወዝም ቆረጠችለት ። ከዚያ በኋላ ደበበ የተከታዮቹንም ቁጥር እያበዛ ሔደና ከየአቅጣጫው ወደ ምፅዋ የሚሔደውን ነጋዴ ሁሉ መዝረፍ ጀመረ ። እንዲያውም አንድ ጊዜማ የፈረንሳይ ቆንሲል የነበረውን ሀብት ዘርፎ በምፅዋና በሐርጊጎ ገበያዎች ሲያሸጠው በምፅዋ የነበሩት ግብጾች ነገሩን ሰምተው «ቁራጩ ጀግና» እያሉ አሞጋገሱት ።

የእጼ ዮሐንስ ተቃዋሚዎች ናቸው ብለው ያመኑባቸውን ሁሉ ሰብስበው ካስታጠቁ በኋላ ፣ ከዶጋሊ ወደ ምፅዋ ይመላለስ የነበረው ንግድም እንዲቋረጥ ማድረግ የግብጾች ዋናዉ ጥረታቸው ሆነ ።

ቀጥለውም ዙላ ወደ ሚባለው የጠረፍ መንደር ወታደሮቻቸውን ሰደው ራስ አሉላ አስገዝተው ሊጫን ተዘጋጅቶ የነበረ ከስምንት መቶ በላይ የሚሆን ጠመንጃና ከሃምሳ ሣጥን በላይ የሚሆን ጥይት ዘረፉ ። ነገሩም ራስ አሉላን እጅግ የሚያስቆጣ ስለሆነ ፣ «የዘረፋችሁትን መሣሪያ ካልመለሳችሁ ደበበንም ይዛችሁ ካልሰጣችሁኝ ምፅዋን መውጋቴን እንድታውቁት» ብለው በምፅዋ ለነበረው የግብጽ ወኪል ላኩበት ። ጉዳዩ በግብጾችም ዘንድ እጅግ አሳሳቢ ስለ ሆነባቸው ፣ ደበበን ከዚያ አካባቢ ዘወር እንዲል አደረጉና ያስዘረፉትን መሣሪያ በሙሉ አስጭነው ወስደው አስረከቡዋቸው ። ከዚያ ቀጥለውም አሉላ ሁለተኛ የእርሳቸውን ንብረት እንዳይነካ ማስጠንቀቂያ ልከው በምፅዋ የነበረውን ኒኮላ ጆርጅ ካሊጅ የሚባለውን ግሪካዊ ነጋዴ አስጠርተው ሁለት ሺህ ጠመንጃዎች በግዥ እንዲያስመጣላቸው አዘዙት ።

ምንም እንኳን ፣ ግብጾች ደበበን ከምፅዋ ከተማ ዘወር እንዲል ቢያደርጉትም ፣ «ግዛታችን ነው» ብለው ወታደር አስፍረውበት እንበረው ተበሌ አድፍጦ ስለነበረ ፣ ከሐማሴን ወደ ምፅዋ ሲመላለሱ የነበሩትን ነጋዴዎች መዝረፍ አላቋረጠም ነበር ። ከዕለታት አንድ ቀንም እጅግ ብዙ ዕቃዎች የጫኑ መንገደኞች ደረሱበት ። የራስ አሉላ ባለቤት ወይዘሮ አምለሱ አስገዝተው ያስጫኑት ንብረት ነበር ። የእርሳቸው ብቻም አልነበረም ፣ ራስ



አሉላ ለጠመንጃ መግዣ ብለው የላኩት ከሦስት ሺህ በላይ የማርትሬዛ ብርም ነበረ ፣ ደበበ ያን ሁሉ አዘረፈ ።

ንብረቱ የእኅቱና የራስ አሉላ በመሆኑም ዕጥፍ ድርብ ደስታ ተሰማውና ፣ «ክቡር ጌታ ራስ አሉላ ሆይ! እኅቴና ባሏ ይህን ያህል ስጦታ ስለ ላካችሁልኝ ምስጋናዬን አቀርባለሁ» ብሎ የፌዝ መልእክት ሰደደላቸው ። ከዝርፊያውና ከፌዙም አከታትሎ በራስ አሉላ ቤት ከባድ ኀዘን ደረሰ ። ለብዙ ጊዜ ታመው የነበሩት ባለቤታቸው ወይዘሮ አምለሱ ዐረፉ ። ራስ አሉላም እጅግ ምርር ብለው አዝነው ስለነበረ እንዲህ ብለው አንጐራጐሩ ።

«አምለሱ ነበረች የራሴ ጌጥ ክብሬ
የትካሻዬ ልብስ ፣ ጋሻዬና ጦሬ ።
የቤቴ ምሰሶ የቤቴ ብርሃን
ዛሬ ፈረሰና ጨለመኝ እኔን ።
አፈረ ልባኔ ፣ ታሰረ አንደበቴ
ከንደም ሄደሽልሽ ፣ ደከመ ጉልበቴ»

በራስ አሉላ ላይ በደረሰው መሪር ኀዘን አጼ ዮሐንስም እጅግ አዘኑ ። «ከቤተ—ሰቦቹ ሁሉ ለሀገር የምታስብ ሀገሩን የሚያገለግለውን ሁሉ የምትወድ መንፈስ ጠንካራ ነበረች ። ለዚህም ነበር አሉላን እንድትረዳው ያደረግሁት ። ሁላችንንም ባያድለን ነው እርሷን የተሠፈብን» ብለው የኀዘን ተካፋይነታቸውን ገልጸው ነበር ።

የወይዘሮ አምለሱ እርአያን የግል ዕቃዎችና ንብረት ወንድማቸው ደበበ አርአያ ከምፅዋ አካባቢ ሸምቆ ከዘረፈባቸው በኋላ ፣ እኅቱንና አማቹን ለማናደድ ሲል የላከላቸው ወረቀት ፣ በነበረባቸው ሕመም ላይ ተጨምሮ በይበልጥ ስላናደዳቸው «እኔን እንዳናደደኝ እርሱንም የሚያናድድ ወንድ ይዘዝበት» ብለው ሲናገሩ ፣ ባለቤታቸው ሰምተው ስለነበር ፣ «አንጀትሽ እንዳረረ አይቀርም» አሉዋቸውና የደበበን እጅ የሚይዙበትን ወይም በግንባሩ አረር የሚያስገቡበትን ዘዴ መቀየስ ጀመሩ ።

በመጀመሪያ ግንኛውም ሸቀጣ ሸቀጥ ወደ ምፅዋ እንዳይወርድና ከምፅዋም ወደ ደጋው እንዳይወጣ ከለከሉና ምፅዋ ለነበረው የግብጾች ወኪል ለሙክታር ቤይ ፣

“በደበበ ምክንያት ሸቀጥ ወደ ምፅዋ እንዳይመጣ ከልክያለሁ። ደበበ ከነልጆቹ ሐርጐ ውስጥ ከናይቡ ጋር መኖሩን እንተምታውቃለህ ፤ እንጂን ካስረከብከኝ ነጋዴዎቹም እንዲመላለሱ አደርጋለሁ” ብለው ላኩለት። እንግዲህ ከጉራዕ ጦርነት በኋላ በሁለቱ ወገኖች መካከል የነበረው ያለመግባባት እየተባባሰ የሔደውም በእነዚህ ምክንያቶች ሆነ። ምንም እንኳን ግብጽ በበጐስና በምፅዋ አካባቢ በነበሩዋት ምሽጎች ወታደሮቿን አሥፍራ “በዐይን የሚታየው ሁሉ ግዛቴ ነው” ብትልም ቅሉ የኔ ይዞታና የኢትዮጵያ አካል የምትለው ክልል በደንብ የታወቀና በውል የጸደቀም አልነበረም። ንጉሠ ነገሥቱም ሆኑ ራስ አሉላ ፣ “ግብጽ ሰርቃ ከሠፈረችበት መሬታችን ትውጣልን” ከማለት በቀር ፣ “ከዚህ እስከዚህ” ብለው የተካለሉት ግዛት አልነበረም።

ይህንንም ለማረጋገጥ ሲሉ ነበር ራስ አሉላ ግብጽ ፣ “የኔ ነው” ስትል በነበረው አቅጣጫ ሁሉ ራሳቸውም ሆኑ ወታደርቻቸው እየተዘዋወሩ የሕዝቡን አስተዳደር ሲከታተሉና ግብርም ሲያስከፍሉ የነበሩት። ያም አድራጐታቸው ጠቃሚ ሆኖ ተገኝቷል። ምክንያቱም ግብጽ የበላይነት እንዳይሰማትና ሕዝቡም በኢትዮጵያዊነቱ እንዳይናቅ ለማድረግ በመቻሉ ነበር።

ግብፅ ራሱዋ በአንድ በኩል በእንግሊዝ ጦር ተይዛ ቅኝ ግዛት ሆና በሌላ በኩል ደግሞ ግብጽ በሱዳን ላይ የነበራት የበላይነት መወዳደቅ መጀመሩን አጼ ዮሐንስ እንደሰሙ የግብጽን ጦር ከሀገራቸው ለማስወጣት የሚያመችበት አጋጣሚ መድረሱን በመረዳት የጦር ኃይላቸውን ማዘጋጀትና ማንቃት ጀመሩ። ምናልባትም ደግሞ እንግሊዝ ስለግብጽ ሆና ትዘምትብኝ ይሆናል የሚል ጥርጣሬም ስለገባቸው ፣ ፈጣን ርምጃ መውሰድ እንደሚኖርባቸው ተገንዝበው ንጉሥ ምኒልክ ሠራዊታቸውን አስከትተው ወደ ወሎ ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ወደ ቤገምድር ፤ ራስ ሚካኤል ወደ ትግራይ እንዲዛወሩና ተዘጋጅተው



እንዲጠባበቁ ትእዛዝ አስተላለፉ። በመኻል ኢትዮጵያ እንደዚያ የመሰለ ወገን አኩሪና የጠላት ቅስም ሰባሪ የሆነ የአንድነት እንቅስቃሴ በመታየቱ ፣ በሰሜን ኢትዮጵያ ጫፍ የነበረው የአሉላ ኃይል መጠናከር ጀመረ። ያን የመሰለ ኅብረት በመታየቱም ግብጽ የኔ ነው ስትለው የነበረውን ቀበሌ ሁሉ ነጻ ለማውጣት የዮሐንስና የአሉላ ቁርጠኛ ውሳኔ ሆኖ ቀረበ። ግብፅም የበኩሏን የመጨረሻ ሙከራ ለማሳየት ዝግጅቷን ቀጠለችበትና ከምፅዋ ከተማ በስተምዕራብ በኩል ከሚገኘው ስሐጢ ከሚባለው ቀበሌ ጠንካራ ምሽግ ማሠራት ጀመረች።

የግብጽ ወታደሮች ከምፅዋ ከተማ ወጥተው ያን ያህል መሬት ዐልፈው የኢትዮጵያን ግዛት ዘልቀው ገብተው ፣ ምሽግ ሠርተው መሥፈራቸውን ራስ አሉላ እንደሰሙ መሬቱ የኢትዮጵያ ርስት መሆኑንና የግብጽ ወታደሮች ያለአግባብ የሠፈሩበት በመሆኑ በአስቸኳይ ለቀው እንዲወጡ ለግብጹ ተጠሪ ጻፉለት። እርሱ ግን ፣ “የኢትዮጵያን ነጋዴዎች ሽፍቶች እንዳይዘርፉዋቸው ለመጠበቅ ነው” ብሎ መለሰላቸው። ይህ መልስ ደግሞ አሉላን እጅግ የሚያስቆጣ ሆነ።

“ሌባውንና ቀማኛውን ከጓዳህ ደብቀኸው የለም? ደግሞስ የግዛቴን ሰላም ራሴ መጠበቅ አቃተኝና ነው አንተ እምታስጠብቅልኝ? ነገሩን አላጣሁትም ፤ ምፅዋ እንዳልገባ በሩቅ ለመከላከል ስትል ነውና ስሐጢ ላይ ያሠፈርካቸውን ወታደሮች በአጣዳፊ ካላስወጣህ ወዮልህ!” ብለው ላኩበት። እርሱ ግን ፣ “ከአፋፍ ላይ ሆኖ ይጮህ” ብሎ የስሐጢን ምሽግ አጠናከረ። ያ ውሳኔው ደግሞ አሉላን እጅግ የሚያስቆጣ ሆነና ሠራዊታቸውን በሦስት አቅጣጫ አሰልፈው ስሐጢ ወርደው ገጠሙት። በዚያም ጦርነት ከሃምሳ በላይ የግብጽ ወታደሮች ሲሞቱ ፣ የተረፉት እየሸሹ ምፅዋ ገቡ። ዐሥራ አምስት ግብጻውያን ወታደሮችም ተማረኩ።

ራስ አሉላ ያን ድል እንደ ጨበጡም “እንደዚህ የመሳሰሉ አዳዲስ ጠመንጃዎች ስለላክህልኝ አመሰግንሃለሁ” ብለው ለግብጽ ወኪል ላኩበት። የስሐጢው ጦርነት እንደ ጉራው ጦርነት እዚያው ከአሸዋው ውስጥ ተቀብሮ አልቀረም። ውሎ ሳያድር ከዓለም አቀፍ ሁኔታዎች ጋር የሚገናዘብበትና በኢትዮጵያም

ታሪክ ውስጥ አዲስ ምዕራፍ ያቀፈበት አጋጣሚ ደረሰ ። ይኸ ውም በግብጽ ላይ የበላይነት የነበራት እንግሊዝን በጉዳዩ ጣልቃ ለመግባትና ከኢትዮጵያ ጋር በቀጥታ ለመነጋገር ስላስገደዳት ነበር ።

ራስ አሉላ ከሰሐጢ ጦርነት ሲመለሱ ባለሟላቸው እን ዲህ ብሎ አንጐራጐረ ።

“መቼ ዘመቱና አሉላ ሰሐጢ
ከግጽብ ወታደር ጋር ተጋጠሙ ቡጢ?
ሲነሡ አልተሰሙ ፣ አልታዩም ሲዘምቱ
ከምን ጊዜው ደርሰው አሉላ ተግቱ
ካግቤን ተነሥተው ሰሐጢ ቢረግጡ
የመኪታር ወታደር ወጣ ዝርጥርጡ
አሉላ አባ ነጋ ነፋስ ነወይ መብረቅ!
ድንገት ተወርውሮ ጠላት የሚያስጨንቅ!”



# አሉላና እንግሊዞች

የሰሐጢው ግጭትና ውጤት ግብጽ ‘ግዛቴ ነው’ ስትላ ቸው በነበሩት ወረዳዎች ላይ የኢትዮጵያን የበላይነት ፣ የአሉላንም ክንደ—ብርቱነት ፣ የአጼ ዮሐንስን ግልጽ ዓላማ እያረጋገጠው ሔደ ። በበጐስ የነበሩት ጉግዎች ሁሉ ኢትዮጵያዊነታቸውን አምነው የተቀበሉበት ሌላው ማረጋገጫ የሆነው ደግሞ ግብጾች ከከረን እስከ ምፅዋ ዘርግተውት የነበረውን የቴሌግራፍ መሥ መር የአሉላ ወታደሮች መቆራረጣቸው ነበር ።

በግብጽ ወታደሮች ላይ የኢትዮጵያ ወታደሮች ደጋግመው ያገኙት ድል በሱዳን ውስጥ ደግሞ ሌላ ወኔ ለማነቃቃት ምክን ያት ሆነ ። በተለይም ሰሐጢ ላይ መሽገው በነበሩት የግብጽ ወታ ደሮች ላይ የአሉላ ጦላ ያስገኘውን ውጤት የሱዳን ማሕዲስቶች (ደርቡሾች) ከሰሙ በኋላ እነርሱም የአሉላን ስልት በመከተል በሀገራቸው ውስጥ በነበሩት የግብጽ ወታደሮች ላይ ክንዳቸውን አነሡባቸው ። ይህ የተያያዘው እንቅስቃሴ ከግብጾች ይልቅ እን ግሊዞችን በይበልጥ እየከበዳቸውና እያሳሰባቸው ሔደ ።

የማሕዲስቶቹ እንቅስቃሴ በምሥራቅ ሱዳን እየተስፋፋ ሕዝ ቡም እያቀፈው የግብጽን ወታደሮች የበላይነት እያገለለው ሔደ። በዚያ አስቸጋሪና ፈጣን ግሥጋሴ ለንደንና ካይሮ እየተጨነቁበት በመምጣታቸው ፣ ቀደም ሲል ተዘግቶ የነበረውን የአጼ ዮሐንስን በር ለመክፈት እንግሊዞች ስልታቸውን ማቀነባበር ጀመሩ ።

የዮሐንስን በር ለማስከፈት ደግሞ ፣ የበሩ ጠባቂ ከነበረው ሰውዬ ጋር አስቀድሞ መገናኘትና መነጋገር አስፈላጊ ሆኖ ቀረበ ። ያበረኛም ቀደም ብሎ እንግሊዞችን ያውቃቸዋል ።

እርግጥ ነው ፣ በዚያ ወቅት ከአጼ ዮሐንስ ጋር በመነጋገር ምንም ውጤት ሊገኝበት እንደማይችል ቀደም ብሎ የሚያውቃ

ቸው ጐርደን ከለንደን የቀረበለትን ይህንኑ ሐሳብ ቢቃወም
ዐይንና ጥርሱን አግጥጦ የመጣባቸውን አስፈሪ ሁኔታ ብቻውን
መጋፈጥ ሊኖርበት ነው ። ስለዚህ የኢትዮጵያን ድጋፍ ማግኘት ፤
ከሚደርስባቸው አስከፊ ውድቀት ሊታደጋቸው እንደሚችል፤
የለንደን የፖለቲካ ጠበብት ያመኑበትንና የቀየሱትን ስልት ጐር
ደንም ዐይኑን ሳያሽ ለመቀበል ግዴታው መሆኑን ስላመነበት
ለዲፕሎማቲኩ ጥረት ደግሞ ራስ አሉላ ዋናው ቁልፍ መሆና
ቸውን ሳይውል ሳያድር ተረዳው ።

ስለዚህ በተቻለ መጠን የተደረገው ተደርጎ አሉላን መቅረብና
ማለዘብ እንግሊዞች የተገደዱበት ምዕራፍ ሆነ ።

ወደ ኢትዮጵያ ለሚላከው የእንግሊዝ ቡድን ሬር አድሚ
ራል ሰር ዊሊያም ሒዊት ኃላፊ እንዲሆን ተሾመ ። ቀጥሎም
ጀኔራል ቤከር ወደ ምፅዋ ሔዶ ከራስ አሉላ ጋር መላላኩን
እንዲጀምር ተላከና ከረን እንደ ደረሰ ‘ቡችላውን’ ደበበ አርአ
ያን ይዞ ምፅዋ ገባ ። ምፅዋም እንደገባ የግብጽ ተጠሪ የነበረውን
ሙክታርን ሽር ማሶን ቤይ የተባለ አሜሪካዊ ሾመ ። ዋይልድ
የተባለውንም እንግሊዛዊ ነጋዴ የፈቃድ ጉዳይ ኃላፊ እንዲሆን
ሾመው ።

ጀኔራል ቤከር እንደዚህ አድርጎ ሁኔታዎችን ካመቻቸ
በኋላ ለራስ አሉላ ደብዳቤ ጻፈላቸው ። በደብዳቤውም የደበበን
ተከታዮች እያሳደደ እንደሚለቃቅማቸው ካረጋገጠ በኋላ ፤ በሁ
ለቱ አገሮች መካከል ወዳጅነትና ንግድ ለመመሥረት እንዲቻል
በቅርብ ጊዜ የሚመጡትን የእንግሊዝንና የግብጽን መልእክተ
ኞች ለመቀበል ፈቃዳቸው እንዲሆንለት ጠየቀ ። ከጀኔራል ቤከር
ቀጥሎም ዋይልድ የተባለው እንግሊዛዊ ቀደም ባሉት ዓመታት
የነበራቸውን ወዳጅነት ጠቅሶ ፤ እርሱም የደበበን ተከታዮች
እየተከታተለ ለማጥፋት እንደማይቸገረውና ከምፅዋም ጋር የን
ግድ ግንኙነት እንዲደረግ ከልቡ የሚጥርበት መሆኑን ገለጸላ
ቸው ።

ኢትዮጵያ የተወሰዱባት ግዛቶቿ እንዲመለሱላት አጥብቃ
የምትፈልግና በምፅዋም ወደብ በኩል የንግድ ሸቀጣ—ሸቀ
ጦች እንዲገቡና እንዲወጡ ፤ እንደዚሁም የጦር መሣሪያዎች



እንዲገቡላት የራስ አሉላ ጽኑ ፍላጐት መሆኑን ዋይልድ የሚ
ተማመንበት ጉዳይ ስለነበረ ፤ ለጻፈው ደብዳቤም አጥጋቢ መልስ
እንደሚያገኝበት ባለሙሉ እምነት ነበር ።

የእንግሊዝ እጅ ግብጽን ይዞ ከአጼ ዮሐንስና ከራስ አሉላ
ዘንድ ከስምምነት ለመድረስ የጀመረውን ስልት የፈረንሣይ
ዐይን ደግሞ በቅናት ይመለከተው ጀመር ። ስለዚህ እንግሊዞች
ከአጼ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት ቀርቶ ከራስ አሉላ በር እንኳ
እንዳይደርሱ ለመከላከል የፈረንሳይ መንግሥት ጥረት ጀመረ ።

በምፅዋ የነበረው የፈረንሣይ ቆንሲል ፍራንቧ ሱማኝ የሚ
ባለው ሁኔታውን ሲከታተለው ስለነበር ፤ ለራስ አሉላ በጻፈው
ደብዳቤ ፤ ከእርሱ ጋር ሳይነጋገሩ የእንግሊዝን መልእክተኞች
ተቀብለው ፤ ምንም ነገር እንዳይወስኑና ከእንግሊዞች ወጥመድ
እንዳይገቡ አስጠነቀቃቸው ። ለአጼ ዮሐንስም ፤ ተመሳሳይ ውክልና
ካገኘ ፤ የፈለጉትን ያህል የጦር መሣሪያ ከፈረንሣይ ሊያስመጣላ
ቸው እንደሚችል አረጋግጦ ፈቃዳቸውን ጠየቀ ። ንጉሠ ነገሥ
ቱም ቀደም ሲል በነበራቸው ግንኙነት ከእንግሊዞች ጋር ከስ
ምምነት ለመድረስ እንዳልቻሉ በመገንዘብ ፤ እንግሊዝ አዲስ
በቀየሰችውም የመቀራረብ አዝማሚያ ጥርጣሬ አድሮባቸው ኑሮ
የፈረንሣዩ ወኪል ፤ ወኪላቸው እንዲሆን መፍቀዳቸውን ላኩበት ።
ስነባብተው ደግሞ እንግሊዞችና ግብጾች ከመድረሳቸው በፊት
ሉሲንላቦስ የተባለው የፈረንሣይ መልእክተኛ እንዲመጣላቸው
ጠየቁ ። የአጼ ዮሐንስ ዝንባሌ ወደ ፈረንሣዮች ያጋደለ ቢሆንም ፤
የፈለጉትን ያህል የጦር መሣሪያ ከፈረንሣይ ለማግኘት የሚችሉ
መሆናቸውን ቢያውቁትም ፤ እንግሊዝ ደግሞ የግብጽና የይዞታ
ዎቿ ሁሉ የበላይ ስለ ነበረች ፤ በመጀመሪያ መልእክተኞቹን ማነ
ጋገርና ሐሳባቸውን ማወቅ ከተቻለም ወደ ስምምነት መድረስ
ቅድሚያ ሊሰጡት የሚገባ ጉዳይ መሆኑን ተረድተው የፈረን
ሣዮቹን ጥያቄ በሁለተኛ ደረጃ ያዙት ።

አድሚራል ሒዊት ምፅዋ እንደ ደረሰ ስለ ራስ አሉላ ባሕ
ርይና በአጼ ዮሐንስም ዘንድ ስለነበራቸው ታማኝነትና ተደማ
ጭነት እየጠየቀ ሲያጠና ሰነበተ ። ከዚያ በኋላ ለእርሳቸው
ባሕርይና ክብር በሚስማማ ሁናቴ ደብዳቤ ጽፎ የመቶ አለቃ

የሊተር ገረሐም የሚባለውን መኮንን አስይዞ ወደ አዲ ተኽላይ ሰደደው ። ራስ አሉላም የሙቶ አለቃውን በወዳጅነት መገረስ ካነጋገሩት በኋላ ፣ አድሚራል ሒዊትንም ለመቀበል ፈቃደኛ መሆናቸውንና ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ነበሩበት አሸንጌ እስከሚገባ ለው መንደር እንደሚልኩት ደብዳቤ ጽፈው መኮንኑን መለሱት ።

ጉዳዩ ግን ፣ በእንግሊዞች ዘንድ ሌላ ጥርጣሬ ፈጠረ ። ንጉሠ ነገሥቱ የነበሩበት አሸንጌ ከምፅዋ በጣም ሩቅ በመሆኑ ፣ አድሚራሉ እዚያ ለመድረስ በርካታ ሳምንታት እንደሚጠይቁትና ከዚያም ሌላ ደግሞ ምናልባት እንደ አጼ ቴዎድሮስ አጼ ዮሐንስም በአንድ ምክንያት ተበሳጭተው አድሚራሉንና ተከታዮቹን ያስሩዋቸው እንደሆን ለማስፈታት ደግሞ ከፍተኛ ጥረትና ትንቅንቅ ስለሚያደርስ ፣ ንግግሩ ከቀይ ባሕር አካባቢ በማይርቅ ቀበሌ እንዲሆን ስለፈቀዱ ይህንኑ ጉዳይ በለዘብታ እንዲያስረዷቸው ኮማንደር አርነስ ርልፍ የተባለውን የባሕር ኃይል መኮንን ወደራስ አሉላ ላኩት ። ኮማንደሩ አዲ ተኽላይ ደርሶ የተላከበትን ጉዳይ ሲያስረዳ ፣

“አድሚራሉም አሸንጌ ድረስ ለመላክ በኛ በኩል አንዳንድ ችግሮች አሉብን ! ምክንያቱም የቀበሌው ርቀትና አድሚራሉም ያለባቸው ብርቱ የሥራ ኃላፊነት ብዙ ጊዜ ለማባከን የማይፈቅድላቸው ስለሆነብን ነው ። በጤንነታቸውም በኩል እንደዚሁ ችግር አለባቸው” ሲል ራስ አሉላም ቀበል አደረጉና ፣

“መቼስ እየሀ ወዳጄ! ንጉሠ ነገሥቱ እስከ ባሕሩ ጠረፍ እንዲመጡላችሁ ለማዘዝ አልችልም ። ለነገር ለነገሩ ግን ለእርሳቸው የተላከውን ደብዳቤ ለመቀበልና አስፈላጊም ሆኖ ከተገኘ ለማ የጥል እችላለሁ ። አስፈላጊያችሁም ከሆነ እስከ ምፅዋ ልሔድላችሁ ፈቃደኛ ነኝ” አሉት በትሕትና አነጋገር ።

“እኛን ለመቀበልና ለመርዳት ስለአሳዩን በጐ ፈቃድ ከልብ እመሰግንዎታለሁ ። አድሚራሉ ግን ለንጉሠ ነገሥቱ የተጻፈውን ደብዳቤ ለራሳቸው ካልሆነ በቀር ለሌላ ሰው እንዲሰጥ የሚፈቅዱ አይመስለኝም” ብሎ ኮማንደሩ ትክ እያለ ተመለከታቸውና ቀጠል አደረገም ፣



“ለመሆኑስ የግብጽ ይዞታ ስለሆኑት ቀበሌዎች እርስዎ ያለዎት አስተያየት እንዴት ነው?” ብሎ ጠየቃቸው በአመለካከቱም ጠንቀቅ ብሎ ።

“በዚህ ጉዳይ የእኔም ሆነ የአጼ ዮሐንስ ሐሳብ አንድ ነው ። ኢትዮጵያ በጉልበትም ሆነ ወደቡን ለማንም አሳልፋ አትሰጥም!” አሉት ኮስተር ብለው ።

“በዚህ ጉዳይ ላይ መቼም እኔ የምሰጠው መልስም ሆነ ውሳኔ የለኝም ። አድሚራሉ የተላኩበት ጉዳይ ስለሆነ የእርሳቸው ድርሻ ነው ። ግን አሸንጌ ድረስ ለመሔድ የሚኖርባቸው ችግር ነው የሚያሳስበኝ” አለ ኮማንደሩ በግራ እጁ አፍንጫውን ነካ ነካ እያደረገ ።

“ታዲያ እንግዲህ እኔስ አድሚራሉ አሸንጌ ድረስ እንዳይደንግ ቱባችሁ ምን ማድረግ እችላለሁ ! ባይሆን እዚህ ድረስ ከመጡልኝ ራሴ ይዣቸው ንጉሠ ነገሥቱ እስከሚገኙበት አሸንጌ እሔድላችኋለሁ ። ነገሩንም አብራርቼ ወደ አጼ ዮሐንስ እልካቸውና ምናልባትም ከአሸንጌ ወደ መቀሌ ወይም ዐድዋ የሚመለሱበትን ጊዜም ያስታውቁን ይሆናል ። በቶሎ የሚመለሱ ከሆነም ችግራችሁ ተቃለለ ማለት ነው” አሉት ለዘብ ባለ አነጋገር ።

ጉዳዩ በዚሁ አበቃና ኮማንደሩ ወደ ምፅዋ ሲመለስ ራስ አሉላም ጉዳዩን አብራርተው ወደ ንጉሠ ነገሥቱ መልእክተኛ ሰደዱ ።

በመካከሉ ግን ፣ ሱዳን ውስጥ የተነሣው የማሕዲስቶች ንቅናቄ እየገፋ የእንግሊዝንም ወታደሮች እያጠቃ በመምጣቱ የሁኔታውን ክብደት የተገነዘበው አድሚራል ሒዊት ፣

“ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ሔጄ ብነጋገር ይሻላል” ብሎ ወሰነና እንግሊዛዊውን ማሰን ቤይንና የግብጽን ተወካዮች አስከትሎ አሥመራ ሲደርስ ፣ ራስ አሉላም ከአዲ ተኽላይ አሥመራ ድረስ ሔደው በወግ በማዕረግ ተቀበሉት ። ከቀናት በኋላም ጉዞአቸውን ወደ ትግራይ ቀጠሉ ።

አጼ ዮሐንስ ፣ የራስ አሉላ መልእክት ከደረሳቸው በኋላ በጉዳዩ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ስለነበራቸው ከአሸንጌ እንደሚ መለሱና እስከዚያው ድረስ ግን ስለጉዳዩ ከእንግዳው ጋር እየ ተመካከሩ ዐድዋ ላይ እንዲጠብቁዋቸው ለአሉላ ላኩባቸው ። ራስ አሉላና እንግዳው እንግሊዛዊ ዐድዋ ደርሰው ለወራት ያህል ከጠበቁዋቸው በኋላ አጼ ዮሐንስ ደረሱ ።

በአሉላ አማካይነት አድሚራል ሒዌት ከአጼ ዮሐንስ ዘንድ እንደ ቀረበ ፣ ተገቢውን ሰላምታ ካቀረበ በኋላ ከእንግሊዝ መንግሥት የተላከውን ደብዳቤ አቀረበ ።

ንግግር ሲጀምሩም አድሚራሉ ፣

"ግርማዊነትዎ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ሲመኙው የነበረው የግዛት ጥያቄ ከእንግዲህ ወዲህ ከአንድ ግብ እንደሚደርስ ተስፋ አለኝ" አለ በፈገግታ ተውጦ ። "የራሴን የባሕር በር መልሼ ብወስድ ትርፍ ነገር ፣ ያልነበረኝን ነገር እንዳገኘሁ ሆኖ መታሰብ አይገባውም ። ከሰላም ቢሆን የኢትዮጵያ መሬት ነው ፣ በግብጦች እጅ ቢገባም መልሼ እወስደዋለሁ" አሉ አጼ ዮሐንስ ቆጣ ብለው ።

ከዚያ በኋላ ንግግሩ ቀጥሎ ከስምምነት ላይ ስለደረሱ ሐምሌ 17 ቀን 1876 በኢትዮጵያ በኩል ንጉሠ ነገሥቱ ፣ ራስ አርአያ ሥላሴ ፣ ራስ ሚካኤልና ራስ አሉላ ቢገኙ ፣ በእንግ ሊዝ በኩል ደግሞ አድሚራል ሒዌትና ማሶን ቤይ ሆነው ቀጥሎ ያለውን ውል ተፈራረሙ ።

1ኛ. በምጥዋ በር የሚወጣና የሚገባ ዕቃ ሁሉ የነጋዴም ዕቃ ቢሆን የጦር መሣሪያም ቢሆን ከግብር ነጻ ይሆናል ።

2ኛ. በእንግሊዝ ጠባቂነት ከመስከረም መባቻ ጀምሮ በ1876 በኢትዮጵያ ቁጥር በእንግሊዝ ቁጥር በ1884 ቦጐስ የሚባለው አገር ለጃንሆይ ለንጉሠ ነገሥት ይመለ ሳል ። የምስር ኬዲው ወታደሮችም ከሰሳን አመዲብን ስንሒትን ለቀው ሲወጡ በመሻል ያሉት የኬዲቪ ቤቶች ዕቆች ፣ የጦር መሣሪያቸውም ሁሉ በነዚህ ስፍሮች የሚ ቀር ለጃንሆይ ይሁን ።



3ኛ. ጃንሆይ ንጉሠ ነገሥት በከሰላ በአመዲብ በሰንሒት ያሉት የኬዲቪ ወታደሮች ምጥዋ ሲመለሱ ረድተው በኢትዮጵያ በደኅና አሳልፈው ሊሰዱዋቸው ተስማሙ ።

4ኛ. የምስር ኬዲቪ ለጃንሆይ ለንጉሠ ነገሥት ይፈቅዳሉ ። ጳጳሳቱን ወደ ኢትዮጵያ ለመስደድ ።

5. ጃንሆይ ንጉሠ ነገሥትና የምስር ኬዲቪ ቅጣት ፈርተው ካንዳቸው ግዛት ወደ አንዳቸው ግዛት የሚሸሹ በደለኛና በደለኞችን አሳልፈው ሊሰጡ ተስማሙ ።

6ኛ. ይህ ቃል ኪዳን ከታተመ በኋላ ፣ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገ ሥትና በምስር ኬዲቪ መካከል ጠብ ቢነሣ ለእንግሊዝ ንግሥት ሊነግሩ ሊአሰሙ ውል አደረጉ ።

7ኛ. ይህ ቃል ኪዳን ወረቀት በታላቋ ብርታንያና በአየርላንድ ንግሥት በህንደኬ ቄሳርይት ደግሞ በምስር ኬዲቪ ዘንድ ታይቶ ታትሞ ቶሎ ይመለሳል ።

ለዚህም ምስክርነት ሪር አድሚራል ሰር ውሊያም ሒዊት የታላቋ ብርታንያና የአየርላንድ ንግሥት የህንደኬ ቄሳርይት ምስለኔ ሁኖ ጃንሆይም ንጉሠ ነገሥት ፣ ከቡር ሚሶን ቤይን የምስር ኬዲቪ ምስለኔ ሁነው ይህን ቃል ኪዳን በየማኅተማቸው አተሙ ። አጼኑ ።

ግራ ቀኙም ፈረሙበት ። እንግዶቹ ወደ ዐረፉበት ቤት ሲሔዱ ራስ አሉላ ሸኙተዋቸው ተመለሱና ፣

"ተንኮላቸውን እግዚአብሔር አፈራርሶ መሬታችንን በሰላም ለማግኘት በቃን ፤ እንኳን ደስ ያለን" አሉ በጥ ብለው የደስታ መግለጫ እንዲሆናቸው እጅ እየነሡ ።

"ና ሳመኝ! ያንተው ትጋትና ልባምነት ነው ለዚህ ያደረሰን ፤ ና ሳመኝ" ሲሉ አጼ ዮሐንስ ራስ አሉላም የጌታቸውን ጫማ ሊስሙ ሲያጐነብሱ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ቀበል አድርገው አቅ ፈው ሳሙዋቸው ። ቀጠል አድርገውም ፣

“ስለ ፈረንጎቹስ ምን ይታይሃል? ‘እንግሊዞቹን አትመኑቸው፤ መሣሪያም እኛ እናስመጣለን’ ነው የሚሉን” ሲሉ ጠየቋቸው። “ጃንሆይ! እነርሱም ቢሆኑ መሬት ስጡን ባዮች ናቸው። ጣሊያ እነርሱንስ ቢሆን እንዴት ማመን ይቻላል? እንደኔ እንደኔ ግብጾች ይዘዋቸው የኖሩትን ቀበሌዎች በእጃችን ካደረግን ሁሉንም በሩቅ ከመዛመድ በቀር ማስጠጋቱ እያደር የሚያመጡት ጣጣ እንደዚሁ ከችግር ላይ ችግር የሚያመጣብን ነው፤ የሚሆነው” አሉ፤ “ግለፊያ ነው እስቲ ስለእነሱም ቢሆን ወደፊት እንመከርበታለን” አሉ አጼ ዮሐንስ።

ራስ አሉላ፤ አጥብቀው ይመኙዋት የነበረችውን ቦጎስን መልሰው ለመውሰድ የሚችሉበት፤ እንደዚሁም የከዳተኞቹን የደበበን፤ የከፍለ ኢየሱስንና የባሕታ ሐጎስን እጅ የሚይዙበትን ውል አገኙተዋል።

የውስጥ ጉዳዩዋን በሰላምና በአንድነት ያጠናከረችው ኢትዮጵያ እንደዚያ ሆና ስትጎለብት ተጻራሪ ግብጽ ተጣከመችና የአሉላ ጥረትና ስልት ከታላቋ ብሪታኒያ ጋር ለመዋዋል ቻለ። ግን ከግብጹ ከዲብ ትክሻ ላይ ቁመው የተፈራረሙት አሉላና ሒዊት እንደገና የተጋጩበት ምዕራፍ ደግሞ ደረሰ።

አድሚራል ሒዊት ከዐድዋ ተነሥቶ ምፅዋ እንደ ደረሰ፤ “የዚህች አገር ሰዎች ወዳጅነታቸው እጅግ አስገራሚና ተፈላጊም ነው። አሉላም ታላቁ የአብሲኒያ ታላቅ ጀኔራል ናቸው፤ በሀገራቸውም ውስጥ በራሪ መንፈስ ናቸው” ብሎ ለሥራ ጓደኞቹ አጫውቷቸዋል።



## ባለሟሉ ተጠረጠሩ!

ራስ አሉላ፤ ወደ ግዛታቸው እንዲሻገሩና በሙሉ መሠረትም ሥራቸውን እንዲቀጥሉ አስፈላጊ ሆና በመገኘቱ፤ ጉልበታቸውም የተጠናከረ እንዲሆን ስላስፈለገ በራስ ሚካኤል ሥር የነበረው ከሃያ ሺህ በላይ የሚሆን ሠራዊት ተጨመረላቸው። አሉላ ይህን ያህል ሠራዊት ከያዙም ግብጾች “የኛ ነው” ብለው ይዘዋት የነበረችውን ከሰላን መልሰው እንዲይዙ የንጉሠ ነገሥቱ ፍላጎት ስለነበረ፤ ምንም እንኳን በአጼ ዮሐንስና በራስ አሉላ መካከል የነበረው ጽኑ ምኞትና ፍላጎት የተወሰዱትን ቀበሌዎችና ጉባዎች ወደ ኢትዮጵያዊነታቸው ለመመለስ ቢሆንም፤ የራስ አሉላ ጽኑ ተቀናቃኞች የነበሩት መኳንንት አሉላን ማስናከልና መጣል ግባቸው አድርገው ተነሡ።

እነ ደጃዝማች ሐጎስ፤ እነራስ ገብረ መስቀልና ሌሎችም መለስተኛ መኳንንት በአሉላ ዕድገትና ሥልጣንም ላይ ዐይናቸውን ተከሉ።

“ንጉሠ ነገሥቱን ከፈረንጆች ጋር ያዋዋላቸው ለብልሃቱ ነው። እነርሱን ታዝሎ ከእነርሱ ጋር ተባብሮ ከእነርሱ ዘንድ የሚፈልገውን ካገኘ በኋላ አሻፈረኝ ለማለት ነው” እያሉ ደጃዝማች ሐጎስ ያሰራጩት ስብከት የአሉላን ተቀናቃኞች ይበልጥ አስተቃቀፈ።

ከዚያ በኋላ መኳንንቱ አንድ ግንባር ፈጠሩና ከንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ቀርበው በራስ ገብረ መስቀል አፈቀላጤነት፤

“ከዚህ ይህን ያህል ሠራዊት ሰጥተውታል። ሐማሴን ከደረሰ በኋላ ደግሞ በሙሉ መሠረት የፈለገውን ያህል መሣሪያ እያስገባ በይበልጥ ይጎለብትና ነገ አልገዛም አልገብርም” ቢሉ

ምስ? ከሁሉም ከሁሉም ትልቁ ውርደትም ከአንድ የገበሬ ልጅ ጋር ጦርነት መግጠምዎ ይሆናል ። ይህንም የምንናገረው የሰማ ነውን ሰምተን ነው ። ከሚገባው በላይ ሊሸከመውና ሊቀበለው ከሚችለው በላይ ነው የተሰጠውና ያበጠው ፤ አሁንም መድኃኒቱ ሳይጠረጥር መንቃትና ማንነቱን እንዲያውቅ ማድረግ ነው'' አሉ ።

ራስ ገብረ መስቀል ፣ ይህን በሚያስረዱበት ወቅትም አብረዋቸው የነበሩት አድመኞች እንባና ንዴት ይተናነቃቸው ነበር ።

የእንግሊዞች ወዳጅ የሆኑት አሉላ በሀገሪቱ ውስጥ ከነበረው የጦር መሣሪያ ሩቡን ያህል ይዘዋል ። ከዚያ ላይ ደግሞ የፈለጉትን ያህል ቢጨምሩ የሚቆጣጠራቸው የለም ። ውሉ አድር 'አሻፈረኝ ባይነት' የመጣ እንደሆነ ንጉሠ ነገሥቱ የማስፈራሪያ ዱላ ከጃቸው ከወጣ ጉልበታቸው መሟሸሹ ለጥ ሰጥ ብሎ የንጉሠ ነገሥቱን የበላይነት አምኖ ሲገብር የኖረው ሁሉ እነደገና አፈርጥሞ ሲነሣባቸው አጼ ዮሐንስ ይታያቸው ጀመር ። ከንዴት ከብስጭትና ከእንባ ጋር የቀረበላቸውን አቤቱታ ሲያዳምጡ ቆዩና ፣

"ታዲያ ምን ሐሳብ አላችሁ ?'' ብለው ጠየቁዋቸው ።

"አካለ ጉዛይን ለሌላ ታማኝ ሰው መስጠት ነዋ ፤ ይህ የሆነ እንደሆነ ለእርስዎ የሚመጣው መሣሪያ በቀጥታ ወደዚያ ሊመጣና ከአሉላ ተመልካችነትና ተቆጣጣሪነት ሊያመልጥ ይመቸቃል ። ያለዚያ አካለ ጉዛይ የእርሱ ግዛት እንደሆነ ከቀየ ለራሱ የሚሆነውን መሣሪያ ከመሰብሰቡም በላይ ፣ ወደ እርስዎ የሚመጣውን ሁሉ ሊመለከትና ሊቆጣጠርም ያመቸዋል ። ከዚያ በኋላ ኃይሉ ምን ገምቶ እምቢ ሊል ይነሣል ። ከተሰጠው ጦርም በገሚስ ሙቀነስ ይገባል'' አሉ መኳንንቱ ።

"ማለፊያ ነው ። በበኩላችሁሳ አካለ ጉዛይን ለማን ይሰጥ ትላላችሁ'' አሉ አጼ ዮሐንስ ።

"ከእርሱ እጅ ከወጣ ጃንሆይ ለመረጡትና ለአመኑት ሰው ይሰጥ'' አሉ ሐጐስ ።



"በኔ ግምት ግን ለባሻይ ገብሬና ለብጀሮንድ ለውጤ ቢሰጥ እስማማለሁ'' አሉ ራስ ገብረ መስቀል ደጃዝማች ሐጐስን እየገረመሙ ።

ይህነኑ ሐሳብ አጼ ዮሐንስም ተስማሙበትና አካለ ጉዛይ አውራጃ ለሁለት ተከፍሎ ለሁለቱ ዐድመኞች እንዲሰጥ ተወሰነ ።ሁለቱም ሰዎች በራስ አሉላ ላይ ሲያድሙና ሲያሳድሙ የኖሩ ነበሩ ።

ከዚያ አከታትሎ ለአጼ ዮሐንስ የሚላከው የጦር መሣሪያ ሁሉ በአካለ ጉዛይ አውራጃ በኩል እንዲላክ ምፅዋ ተቀማጭ ለሆነው የንጉሠ ነገሥቱ ወኪል ለነበረው ፈንሣዊ ተላከበት ። እርሱም ይህንኑ መሠረት አድርጐ ከሦስት ሺህ በላይ የሚሆን ጠመንጃ አካለ ጉዛይ ውስጥ በምትገኘው አክሩር በምትባለው መንደር በነበሩበት ኢጣሊያውያን ሚሲዮኖች አማካይነት ወደ አጼ ዮሐንስ ሰደደ ።

ነገሩን ራስ አሉላ እንደ ሰሙ ፣ "ማንኛውም ነገር ከምፅዋ ወሐማሴን በኩል እንዲገባ ንጉሠ ነገሥቱ ያዘዙትን ችላ ብለህ በሌላ አቅጣጫ እንዲገባ ማድረግህ ትክክል አይደለምና ምክንያትሁን እንድታሳውቀኝ'' ብለው ላኩበት ። የሚሲዮኑ ኃላፊ የነበረው ቄስ ኩልቦም ጥያቄያቸውን ለአዲሱ ባለሥልጣን ለብጀሮንድ ለውጤ አስተላለፈ ። ለውጤም በበኩላቸው ፣

"መሣሪያዎቹ በዚህ በኩል እንዲያልፉ ያደረግሁት እኔ ነኝ። ያዘዙኝም ራሳቸው ንጉሠ ነገሥቱ ናቸው'' ብለው ለራስ አሉላ ላኩባቸው ።በዚህም የተነሣ አሉላ ከሆዳቸው ነገር ገባ ።

"እውነትም ለውጤ ከኔ ይበልጥ ታማኝ ሆኖ ነው እኔን ያስለወጠ? እስቲ ይሁና ! አገር ለነሱ ሲሰጥ አይደለ ነገሩ የቀረው? አዩ አጼ ዮሐንስ አላሳቻቸው መብዛቱ !''አሉና አሉላ ተከዙ ።

ይሁንና ለዚያ ቅሬታ ሳይሸነፉና መንፈሳቸውንም ሳያስጨንቁ ከስላን እንዲይዙ የተጨመረላቸውን ሠራዊት እየመሩ ወደ በጐስ አመሩ ። ከዚህም ላይ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በሐሳብ የተራራቁበት ጉዳይ ነበረ ።የአጼ-ዮሐንስ ትልቁ ጉጉት ከሰላን መያዝ

ቢሆንም፣ አሉላ ደግሞ እጅግ ያበሳጨበት የነበረው ከአካባቢያቸው ስለነበረችው በጉስ ነበር። ያችን ቀበሌ ከያዙ የአስተዳደር አቅማቸው እንደሚጠናከር ተገልጦም ቱርኮችና ግብጾች የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ እንዲሆን ያስገደዱትን ሕዝብ ወደ ተደ ምት ክርስቲያናዊነቱ ለመመለስም አስቸጋሪ ቢሆንም ለኢትዮጵያዊነቱና ለአንድነቱ እንዲቆም ለማድረግ እንደማይሳናቸው ቆራጥ ዓላማ ነበራቸው።

በጉስም እንደ ደረሱ ዕቅዳቸውን በሥራ ላይ ለማዋል ቢጀምሩ በአካባቢው ከነበሩት የግብጽ ወታደሮች ጋር ግጭት ተነሣ። እርግጥ ነው፣ ያን ቀበሌ ለመረከብ ከአድሚራል ሒዊት ጋር በተደረገው ስምምነት መሠረት ጥቂት ሳምንታት ቀርተዋቸው ነበር። በዚህም የተነሣ በእንግሊዞችና ግብጾች ዘንድ ሁኔታው ያልታሰበ ትርምስ አስነሣ። በአካባቢው የነበሩ ጎሳዎችም እርስ—በርሳቸው ተፋጠጡ። ኢትዮጵያዊነታቸውን እንደ ጠበቁ በቆዩት የበኒዓምር ጎሳዎችና የነእርሱ ተቃዋሚዎች በነበሩት ጎሳዎች መካከል የተካረሩ ሁኔታዎች እየተባባሱ በመሔዳቸው ራስ አሉላ የሐባብ ጎሳ ባላባት የነበሩትን፣ ከንቲባ ሐሚድን የቀበሌው ኃላፊ እንዲሆኑ ሾሙዋቸው።

አሉላ ሳይታሰብ በጉስ ገብተው ከግብፅ ወታደሮች ጋር ያስነሡት ግጭት፣ የአካባቢውንም ሕዝብ ግብር በማስከፈላቸውና ወኪልም በመሾማቸው፣ የሚቀጥለው ርምጃቸው ደግሞ ከሰላ ከደረሰ ለግዛታቸው ተቃራኒ እንደሚሆን የተረዱት እንግሊዞች ወደ አጼ ዮሐንስ አቤቱታቸውን ሰደዱ።

ንጉሠ ነገሥቱ ደግሞ በሁኔታው በይበልጥ ማተኮር ጀመሩ። የአሉላ ተቀናቃኞች የነበሩ መኳንንት ያቀረቡላቸው ሐሳብ እንደ ከነከናቸው ነበሩ። ቀጥሎ የእንግሊዞቹ አቤቱታ ቀረበ። ከእነዚህ ነጥቦች ሌላ ደግሞ ፈጥነው ከሰላን አልያዙላቸውም። በእነዚህ ሁኔታዎች የተነሣ በቅሬታ ላይ ቅሬታ በመጨመሩና በሐሳብና በሥራም ስለ ተራራቁ፣ "ስለ ፈጸሙት ነገር የምትቀጡን ኃላፊ ግልጽ ቢሆንና የሻምበል ዐርም የተባለውን እንግሊዛዊ ይቅርታ ልትጠይቃቸው ይገባል" ብለው ላኩባቸው።



"አገሬ ላይ ተንሰራፍተው ተቀምጠው ሕዝብ እየበዘበዙ እርስ—በርሳችን የሚያበጣብጡን እነርሱ፣ እኔ ምን በበደልኩ ነው ይቅርታ በሉኝ የምትሉኝ? አዝማሚያውን ተረድቼዋለሁ። የፈረንጆች እጅ የማይሠራው ነገር የለም፤ የጌታቸውን አሽከሮችና ባለሟሎች ይዘዋቸዋል ማለት ነው?" ብለው ራስ አሉላ ሁለተኛ ቅሬታ በልባቸው አሳደሩ።

አጼ ዮሐንስና ራስ አሉላ እንደዚሁ ሆነው በሐሳብና በአመራር በመራራቃቸው ደግሞ እንግሊዞች ያተኮሩበት አንዲት ጭላንጭል ታየች። ማሕዲስቶች ሱዳን ውስጥ ያነሡት ዐመፅ እየገፋ ሔደ። መተማ የነበረውን የግብጽ ጦር ከበበው። ከምሽጉ በቀር አካባቢው በማሕዲስቶቹ ቁጥጥር ሥር ዋለ። ሁኔታውን ያጠኑት እንግሊዞችም ያ የተከበበ የግብጽ ጦር እንደሚደመሰስ ወይም እጁን ከመስጠት እንደማይተርፍ ተረዱት። ይህን ከአመኑበት በኋላ ነበር፣ እንግሊዝ አመዲብና ሰንሒት በተባሉትም ቀበሌዎች የነበረው የግብጽ ጦር ተመሳሳይ ውድቀት እንዳይደርስባቸው ሲሉ ዐድዋ ድረስ ሔደው ከአጼ ዮሐንስ ጋር የተዋዋሉት። ነገር ግን መተማ ላይ በተለይ ጋላባት በተባለው ምሽግ የነበረው የግብጽ ጦር ዙሪያውን በማሕዲስቶቹ ቢወጠርም ያለ መደምሰሱን ወይም እጁን ያለ መስጠቱንና በተጠናከረም ሁኔታ ላይ መሆኑን እንግሊዞች እንዳረጋገጡ፣ "ቢከፋኝ በመለስ" የሚባለውን የገበጣ ጨዋታ ምሳሌ ለመከተል ፈለጉ።

የኢትዮጵያ መራዊት ወደ ከሰላ እንዳይዘምት በጋላባት በኩል ከበባ እንዲደረግ አዲስ ስልት እንግሊዞች መትለም ጀመሩ። የቀይ ባሕርና የአካባቢው አገር ገዥ ሆኖ በዚያው ወቅት ተሹሞ የነበረው ኰሎኔል ቺርቦርት ኪርሚሊ ከረን የሚገኘውን የግብጾች ምሽግ የማሠልጠኛ ማዕከል አድርጎ ከአካባቢው ጎሳዎች ወታደሮች እየመለመለ የሱዳንን ማሕዲስቶች ለመቋቋም ዕቅድ አወጣ። በዚህም መሠረት በጉስ የሚባለው ቀበሌ ለኢትዮጵያ በሚመለስበት ጊዜ ምሽጉ እንዳይለጣት ለማድረግ የሚቻልበትን ዘዴ ማውጠንጠን ጀመረ። ይሁን እንጂ ይህንኑ አዲሱን ዕቅዱን ወይም የክፋት አዝማሚያውን አጼ ዮሐንስም ሆኑ ራስ አሉላ እንዳያውቁበት የተቻለውን ያህል ይጥርበት ጀመር።

እንግሊዞች የራሳቸውን ስልት በምሥጢር አጠናቀው ከጨረሱ በኋላ የምፅዋው አገሬ ገዥ በማሶን ቤይና የሻምበል ስፒዲ ጉዳዩን ለራስ አሉላ ለማስረዳት ወደ አዲተኸላይ ሒደው በከሰላና በአመዲብ የሚገኘው የግብጽ ጦር ተጠቃሎ እስከሚወጣ ድረስ የከረን ምሽግ በእንግሊዝ ተቆጣጣሪነት የሚቆይ መሆኑን ሲነግሩዋቸው ፣

“ከተዋዋልነውና ከተስማማነው ውጪ የጠየቅናችሁ አንድም ነገር የለም ። ውሉን የፈለጋችሁት እናንተው ነበራችሁ ። አሁን ደግሞ ማፈግፈግ የጀመራችሁበት ምክንያት ይገባኛል ። የሀገሬን ክብር በክንዴ እጠብቀዋለሁ” ብለው ንግግሩን አቋርጠው እንግሊዛዊውንና አሜሪካኑን አሰናበቱ ።

ከዚያ ቀጥለው እንግሊዞች ሐሳባቸውን መለወጣቸውን ዘርዝረው ለአጼ ዮሐንስ ላኩ ።

“ድሮውንስ ከእንግሊዞች እጅ መሬት እናገኛለን ብለን መተማመንስ መቼ ይገባን ነበር ?” አሉ አጼ ዮሐንስ መልእክቱ እንደ ደረሳቸው ቀጥለውም ወደ እንግሊዞቹ ፣

“የስምምነቱን ጉዳይ ያዘጋጃችሁት ራሳችሁ ናችሁ ! የምታፈርሱትም ራሳችሁ ናችሁ ።ግን ራስ አሉላ ስሕተት ሠርተዋል እያላችሁ ታመካኛላችሁ ፣ አሉላ የፈጸመው ስሕተት የለም ።በከረን የሚገኙት የከዲቭ ወታደሮች ለመስከረም አንድ ቀን ምሽጎቹን እንደሚለቁ በውላችን አልተጻፈምን ? በውሉስ ላይ ሁላችን አልፈረምንበትም ? በቃል የሆነ ነገር ምናልባት ይረሳ ይሆናል ። በጽሑፍ የሆነ ነገር ግን ሊለወጥ ከቶ አይችልም ።የሆነ ሆኖ ዘማይታችሁም የምትለቁ ቢሆን አገሩን የኔ ሹም መረከብ ይኖርበታል ። በገባነው ውል መጽናት አይገባንም ነው የምትሉ?” ብለው ላኩ ።

በምሽጉቹ ምክንያት የተነሣው ውዝግብ እልባት ከማግኘቱ በፊት አጼ ዮሐንስ ከሰላን ማሕዲስቶች እንዳይዙባቸው ለመዝመት መዘጋጀት ጀመሩ ። አስቀድመውም ራስ አሉላ እንዲዘምቱ ላኩባቸው ።እንግሊዞች ደግሞ አሉላ ወደ ከሰላ እንዳይዘምቱ ለማደናቀፍ የተቻላቸውን ያህል ጥረታቸውን ቀጠሉ ።



በዐድዋው ውል መሠረት የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች የሆኑትን ሽፍቶችና ከዳተኞች እየያዙ ለኢትዮጵያ ለማስረከብ ሁለቱም ወገኖች ተፈራርመዋል ። ውሉ የተፈረመበት ቀለም ከመድረቁ በፊት የዮሐንስንና የአሉላን በጐ አመለካከት ለማትረፍ የቸኮሉት እንግሊዞች ፊታውራሪ ደበበን አባብለው ይዘው ምፅዋ ውስጥ አሰሩት ። ነገር ግን የውንብድና ዓላማው ደጋፊዎች የሆኑ ግለሰቦች ፣ ከእስር ቤት አስወጥተው አሣውርታ ገብቶ እንዲያደፍጥ አደረጉ ። እርሱም ዘረፋውን ቀጠለ ። አጼ ዮሐንስ ሁኔታውን እንደሰሙ ፣

“ለይስሙላ ያህል የሆነ ጉዳይ መሆኑን አላጣሁትም ። ከእነርሱ እስር ቤት ቢያመልጥ ከኔ እጅ የሚያስጥለው ማንም የለም” አሉና በጀሮንድ ለውጤና ራስ ጉብረኪዳን ወደ አሣውርታ ገብተው ደበበንና ተከታዮቹን እንዲይዙላቸው አዘዙ ። እነለውጤ ግን የአሣውርታን መንደሮች ዘርፈው የዙላን ቀበሌ አተራምሰው ተመለሱ እንጂ ደበበን ሊያገኙት አልቻሉም ።

ደበበ ፣ ከአሣውርታ መንደር አምልጦ ሐባብ ከተባለው ቀበሌ ገብቶ ሽፍቶች ሰብስቦ ራስ አሉላን ለመዳፈር ተዘጋጀ ። የእርሱ ሐሳብና ዝግጅት የማረካቸው ባሕታ ሐጐስና ክፍለ የሱስም ተቀላቀሉትና ክንዳቸውን አስተባብረው አሉላን ለማጥቃት የሚችሉበትን ስልት ማቀነባበር ጀመሩ ። የሦስቱ መጠናከር ደግሞ የሐባብን አካባቢ በከሰውና በጐሣዎች መካከል ግጭት አስነሣ ።

ሁኔታው ራስ አሉላን እጅግ የሚያሳስብ በመሆኑ ፣ በድንገት ከረን ደርሰው ሠራዊታቸውን በሦስት አቅጣጫ አሰልፈው እነደበበን ማደን ጀመሩ ። እነርሱ ግን ተከታዮቻቸውን በታትነው ደብዛቸውን አጠፉ ። ቢሆንም አሉላ ከረን ላይ ሆነው ሕዝቡን አረጋግተው ጸጥታውን ራሳቸው መከታተል እንደ ጀመሩ ወደ አዲተክላይ ፈጥነው የሚመለሱበት አስገዳጅ ሁኔታ አጋጠመ ። ሱዳን ውስጥ የተነሣው ዓመፅ የእርሳቸውንም ግዛት ከሚዳፈርበት ደረጃ ላይ ደረሰ ። የከረንን አካባቢ ሁኔታ በታማኞች ጐሳዎችም ጭምር እንዲጠበቅ አድርገው ወደ አዲተክላይ ተመለሱ ።

የማሕዲስቶቹ ግፊት ከራስ አሉላ ይበልጥ እንግሊዞችን እንደገና የሚያስጨንቅ እየሆነ በመሔዱ፣ ቀደም ሲል ራስ አሉላ ወደ ከሰላ እንዳይዘምቱ ልዩ ልዩ ተንኮል ሲያውጠነጥኑ የነበሩት እንግሊዞች ከ'ቢከፋኝ ብመለስ' ሐሳባቸው እንደገና ወደ ዐድዋ ውል አስገዳጅነት ተመለሱና አሉላ ወደ ከሰላ ወርደው ከማሕዲስቶች ወረራ እንዲከላከሉ ለማግባባት ሞከሩ። አሉላ ደግሞ 'ከእናንተ ወዳጅነት የማሕዲስቶቹ ጠላትነት ይሻላል' ብለው የእነርሱን ውትወታ ችላ ብለው የአስተዳደር ተግባራቸውን ቀጠሉ። እሥመራን የቆረቆሩዋትም በዚሁ ወቅት ነበር። ከሰላ ወርደው ማሕዲስቶቹ እንዳይዙዋት ለመከላከልም ሆነ አዲሲቱ ከተማቸውን ለአስተዳደርና ለንግድ የሚኖራትን አስፈላጊነት ለአጼ ዮሐንስ ለማስረዳት አሉላ መቀሌ ገብተው ውለው እንዳ ደሩ እንደ ገና አስቸኳይና አጣዳፊ መልእክት ደግሞ ከመረብ ማዶ ደረሳቸው።



## "ነጭ ወታደር ምፅዋ ገባ"

ከመረብ ማዶ የገሠገሠው መልእክተኛ ወደራስ አሉላ ሔዶ የ'ነጭ ወታደር ምጥዋ መግባቱን-ነገር ተብሎ ነው የመጣ ሁት' አላቸው። መልእክተኛውም የተላከው የራስ አሉላ ወኪል ከነበሩት ከፊታውራሪ ዓለማየሁ ነበር።

ራስ አሉላ፣ እጅግ ተቆጡ፤ ዐይኖቻቸውን ከመልእክተኛው ላይ አፈጠጡበት።

"ይኸ ነገር ከታመነ ሰው የተገኘ መሆኑን አረጋግጣች ኋል?" ብለው እንደ ተቆጡ ጠየቁት።

"አዎን ጌታዬ! ምጥዋ የሚኖሩት ወዳጆችዎ ናቸው መልእ ክተኛ የሰደዱት" አለ መልእክተኛው።

"ገዶለም የነርሱን ተንኮል ዱሮውንም አላጣነውም፤ እኔ በሕ ይወቴ ቁሜ ካገሬ ድንበር ውሉ አያድርም እንገናኛለን" ብለው ወደ ቤተ መንግሥቱ ሐደው መርዶውን ለንጉሠ ነገሥቱ ነገሩ።

"በማን ፈቃድ ነው እዚያ የሠፈሩት? እንግሊዞቹ ፈቅደውላ ቸው ይሆናል!» አሉ አጼ ዮሐንስ።

"ሳይሆን አይቀርም፣ ፈረንሣዮች ወደዚያ እንዳይጠጉዋቸው ሲሉ እንግሊዞች የፈጸሙት ደባ መሆኑ አያጠራጥርም" አሉ ራስ አሉላ።

"እንግሊዞች እንደዚህ ሠሩን? ጉሮሮአቸው ሲያዝ 'እኛን እርዱን' እያሉ ይወተውታሉ፤ ትንፋሻቸው ሲመለስላቸው ደግሞ እኛን ከድተው ወደ ወገኖቻቸው ማድላታቸው ነው? እንዴት እንደዚህ ያደርጋሉ? በእግዚአብሔር ስም እናምናለን እያሉ እኛን እያ

ሞች በጕን እንደዚህ ያለ ክህደት ይሠራሉ ? ሐሳባቸውን አላባ
ሁትም ። ጣሊያኖች በደንከል በኩል በሩን ይዘው ከምኒልክ ጋር
ተወዳጅተው ፥ እኔን እንዲወጋላቸው የፈለገውን መሣሪያ ሲያቀ
ከበሉት መኖራቸው አንሶ ፥ አሁን ደግሞ የኔን ጕሮሮ ለመዝጋት
እጅና እግሬን ለማሰር ምጥዋን ያዙ ? !''

''መልካም ነው ፥ እኔ ለእንግሊዝ ንግሥት እልክባቸዋለሁ ።
አንተ ግን ኀስግሠህ ድረስና ምጥዋ የሠፈሩት በማን ፈቃድ እን
ደሆነ ? ሐሳባቸውም ምን እንደሆነ አረጋግጠህ ላክብኝ ። ጣሊያ
ኖቹ እዚያ የሠፈሩት በፈቃዳቸው ከሆነም እንዲለቁ አስጠንቅቃ
ቸው ። ያ-በር ያገሬ ጕረሮ ነውና ነቅተህ ተዘጋጅተህ ጠብቅ''
አሉ አጼ ዮሐንስ ለማስፈራሪያው ዱላቸው ትእዛዝ ሲሰጡ ።

''ሕይወቴ እያለች ያገርዎ ዐፈር አትቆነጠርም ። በመጣበት
እግሩ ይመለሳታል ። እምቢ ካለም በጀግኖችዎ ኃያል ክንድ ይወ
ቃል'' ብለው አሉላም ጌታቸውን ተሰናብተው ወደ ግዛታቸው
ገሠገሡ ። አሥመራ እንደ ደረሱም ምርጥ ምርጥ ጥቂቶች ወታደር
ቻቸውን በምሥጢር አስጠርተው ከፊታቸው አስቀምጠው በግ
ለፊያ ሞሰብ ፥ ግለፊያ ራት አብልተው ፥ ግለፊያ ጠጅ አጠጥተው
ምርጥ ምርጥ ጠመንጃዎች ከሸለሙዋቸው በኋላ ፥

''ጀግኖቼ! ልጆቼ!

እስከ ዛሬ ድረስ በታዘዛችሁበት ቦታና ግንባር ሁሉ የሚያ
ኮራ ሥራ እየሠራችሁ ተመልሳችኋል ። ዛሬ ደግሞ በጣም ለበ
ለጠ አደራና ተግባር መርጫችሁአለሁ ። የነጭ ወታደር ምጥዋ
መግባቱን ሰምቻለሁ ። እናንተን የፈለግኋችሁም ወደዚያው ልል
ካችሁ አስቤ ነው ። የዛሬዋ ጨረቃ ትነጋለች ። ስንቃችሁ ከዚሁ
ተዘጋጅቶላችኋል ። እኩለ ሌሊት ላይ ከዚህ ወጥታችሁ እስከ
ጥዋት ድረስ ትገሠግሡና ከደረሳችሁበት ቦታ እንደሆናችሁ
ድምጻችሁን ሳታሰሙ አድፍጣችሁ ትውላላችሁ ።

ነገ ማታ እንደገና ጕዞአችሁን ትቀጥሉና ሲነጋ ከደረሳችሁ
በት ትውላላችሁ ። ማታም ጕዞ ትቀጥሉና በምጥዋ አካባቢ ከደ
ረሳችሁበት አድፍጣችሁ ከመካከላችሁ ሁለትና ሦስት ሁናችሁ



በተለያየ መንገድ ወደ ምጥዋ ትገቡና የጣሊያኑን ጦር የሚሠራ
ውን ተመልክታችሁ ትመለሰላችሁ ።

ምናልባት የጣሊያን ወታደሮች አገር ለመቃኘት ከምጥዋ
ወጥቶ ወደላይ ኀብቶም ካገኛችሁት የጀግንነታችሁን ሙያ ፈጽ
ማችሁ መመለስ ነው ። የዮሐንስ ጸሎት ይጠብቃችሁ'' ብለው
ለያንዳንዳቸው ሦስት ሦስት ብር ሰጥተው አሰናበቱዋቸው ። ለዚያ
ግዳጅ የተመረጡት ሦስት ታማኞችም የአሉላን ጉልበት እየሳሙ
ወጡ ።

የተላኩት ምርጥ ምርጥ ወታደሮች እንደ ታዘዙት በምፅዋ
አካባቢ ሆነው ስለ ጣሊያን ወታደሮች ማጠያየቅ ጀመሩ ። በዚያ
ላይ እንዳሉም የግብጽ ወታደሮች በጠቋሚ እየተመሩ ደርሰው
ከበቡዋቸው ። እነዚያ የአሉላ ወታደሮች ዐሥር ግብጻውያን ወታ
ደሮች ገድለው መሣሪያቸውን ገ[illegible]ው ከእነርሱ አንዳቸውም ሳይ
ነኩ ወደ አሥመራ ተመለሱ ።

አሉላ ጀግኖቻቸውን ደስ ብሏቸው ተቀበሉዋቸው ። ከግብጽ
ወታደሮች የማረኩትንም አዳዲስ መሣሪያ ለጀግኖቹ መረቁ
ላቸው ። በምፅዋ የሠፈሩት ጣሊያኖች ከግብጾች ጋር በወዳጅነት
መቀራረባቸውን ከባሕሩም ዳር ዳር ቤት ሥራ መጀመራቸውን
መድፎችም መትከላቸውን ከወደ ደጋው የሚወርደውን መንገ
ደኛ ሁሉ እያያዙ የሚጠይቁ መሆናቸውን አስረዱ ። ''የእንግሊ
ዞች ተንኮል መሆኑን አላጣሁትም ። በግብጾች ላይ ታዝለው
እሽሩሩ በሉን'' ሲሉ የኖሩት አንሶ ዛሬ ደግሞ በጣሊያን ላይ
ተቀምጠን እንጋልብ ነው የሚሉት ? እንኳን በጣሊያን በሰይጣ
ንም ላይ ቢፈናጠጡ በኔ አገር ላይ እኔ ቁሜ አይጋልቡም''
አሉ የሰላዮቻቸውን ማብራሪያ ከሰሙ በኋላ ቁጣቸውን ለመዋ
ጥም እየታገሉት ።

''በሉ ልጆቼ የድካማችሁን ዋጋ አምላክ ይክፈላችሁ ! እኔም
የሚቻለኝን አዝላችኋለሁ'' ብለው ጀግኖች ወታደሮቻቸውን አጕ
ራርሰውና ሸላልመው ካሰናበቱ በኋላ ሲተክዙ ቆይተው ፥ ''ግብጽ
ወጥታ እንግሊዝ ቢገባ ፥ እንግሊዝ ለቆ ጣሊያን ቢገባ ምንድ
ነው ልዩነቱ ? ሁሉም አገር ፈላጊዎች ፥ ሁሉም ጠላቶች ፥ ሁሉም

ሕዝብን ባርያ አድርጉ ለመግዛት የተሰለፉ ናቸው ። ከረንና
ከሰላን መልሰን በእጃችን እንዳናስገባ ሲሉ አይደለም እንግሊ
ዞች ይህን ተንኮል የሠሩት?" ብለው አጉረመረሙ ።

አሉላ የመረብ ምላሽ ግዛታቸውን ለማደራጀት ያወጡትን
ዕቅድ በሥራ ለማዋል በሚጣጣሩበት ወቅት የምፅዋ መያዝ
አጅግ ከበዳቸው ።

አንድ ከተማ እንደ ምን ሊሰፋፉ እንደሚችል ሐሳቡን ደር
ሰውበታል ። ንግድም የሚያስገኘውን ሰፊ ጥቅም በሚገባ ተረ
ድተውታል ። የመረብ ምላሽ ግዛታቸው በንግድ በልጽጎ ከዚያ
በሚገኘው ገቢ ምፅዋ በሚኖረው ግሪካዊ ወዳጃቸው አግካይ
ነት ምርጥ ምርጥ ጠመንጃ አስገዝተው ፣ ሠራዊታቸውን አደራጅ
ተው ፣ የመረብ ምላሽ ግዛታቸውን በወራሪዎች እንዳይደፈር አስ
ከብረውና ጸጥታውን አደላድለው ለማስተዳደር ትልቁ ግባቸው
ነበር ።

በዚሁ የተነግም ትካዜና ብስጭት የሚፈራረቁባቸው ሆኑ ።
በዚያ ላይ እንዳሉ ደግሞ ጣሊያኖች የአጼ ዮሐንስንና የእርሳቸ
ውን ሐሳብ ለማወቅ ስለፈለጉ መልክተኞች ሰደዱ ። እነዚያው
መልእክተኞች ምፅዋ ከደረሱ በኋላ ፣ "ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ስለ
ምንሔድ ፈቃድ እንዲሰጠንና እንድንመጣ" ብለው ላኩባቸው ።
"የሀገሬን ጉረር ካነቁ በኋላ ደግሞ ምን አድርጉ ሊሉን ነው
የሚመጡት!" አሉ አሉላ የጣሊያኖቹን ጥያቄ ያደረሰውን መል
እክተኛ ከፍና ዝቅ እያደረጉ እየተመለከቱት ። መልእክተኛውም
በድንጋጤ ተውጦ ዐይን ዐይናቸውን ከመመልከት በቀር አንዲት
ቃል ለመተንፈስ አልደፈረም ነበር ።

"የሆነ-ሆኖ ይምጡና ሐሳባቸውን እንወቀው" ብለው ፈቃ
ዱን ላኩላቸው ።ጣሊያኖቹ አሥመራ ደርሰው ከራስ አሉላ ዘንድ
እንደ ቀረቡ ኃላፊው ነገር ያሳመረ መስሎት ፣ "ዝናዎን ስንሰማ እንደ
አንድ ትልቅ ጋራ ይመስሉን ነበር እንጂ እንደዚህ ልከኛ ቁመ
ትና ወርድ ያለዎት አይመስሉንም ነበር" ሲል ንግግር ጀመረ—
የልቡ ተንኮል ፊንቅሎ ወጥቶ የሚታይበት መስሎት በፈገግታ
እየሸነገለ ።



አሉላ እንደ ተቆጣ አንበሳ ጸጉራቸው ቆመ ። ዐይናቸውም
ገርሽጥ ለመምሰል ተቃረቡ ፤ ግንባራቸውን ኮስተር ፣ ትከሻቸውን
ለጠጥ አደረገው ፤

"ከምድር በላይ ያለኝ ቁመቴ እንደዚህ ቢሆንም ቅሉ ከአገሬ
በታች በምድሬ ውስጥ ያለኝ ሥር ጥልቀቱ እነዚያን ጋራዎች
የሚያክል መሆኑን ዕወቅ" አሉ ። በአኳኋናቸውም ጣሊያናዊ
ተደናገጡ ። ቪሽንዞ ፌራሪ የጨዋታውን አርእስት መለወጥ እን
ደሚሻል ወዲያው ተገነዘቡና ፣

"ከአገሬዎ ጋር የጠበቀ ወዳጅነትና ንግድ ለመመሥረት በንል
ለተወሰነ ጊዜ ምፅዋ መፍረናል ። ለዚህም ፈቃድ እንጠይቃለን"
አለ ፣ ኮስተር ብሎ የነበረውን የአሉላን ገጽ ለመግለጽ እየሞከረ ።

"ስለምጥዋም ሆነ ስለበጉስ ጉዳይ ከእንግሊዞች ጋርኮ ያደረግ
ነው ስምምነት አለን" አሉ ራስ አሉላ በአኳኋናቸው ቅጭም
እንዳሉ ።

"በሁለታችሁ መካከል የተደረገውን ስምምነትም ቢሆን
የኢጣሊያ መንግሥት የሚያከብር መሆኑንም ላረጋግጥልዎ
እወዳለሁ" አላቸው ።

"ሐሳብዎን ተረድቼዋለሁ ። እኛ መቼም ቃላችንን እናከብራ
ለን ። መንሸራተትና ጫወላወል የሚታየው ግን በእናንተ በባሕር
ማዶ ሰዎች ነው ። የሆነ ሆና ይህንኑ ጉዳይ ራሳችሁ ቀርባችሁ
እንድታስረዱዋቸው ወደ ንጉሠ ነገሥቱ እንድትሔዱ እረዳች
ኋለሁ" አሉት ።

"ግዴለም በኛ በኩልም መንሸራተት የለም ። እኛም እንደ
እናንተው ቃላችንንና ውላችንን እናከብራለን" አለ መል
እክተኛው ፤ በዚሁ ነገሩ ከስምምነት ላይ ተደረሰበትና ራስ አሉላ
ሸኝና ስንቅ ሰጥተው እንግዶቹን ኢጣሊያኖች ወደ መቀሌ ሰደ
ዷቸው ።

እንግዶቹ ከራስ አሉላ ጋር በተነጋገሩበት ሰዓት የመልእክ
ተኞቹ ኃላፊ ቪሽንሶ ፌራሪ የአሉላን ገጽታ ፈገግ ለማድረግ
ሲል ቁመታቸውንና ወርዳቸውን ከጋራ ጋር አነጻጽሮ የተናገረ

ውና እርሳቸውም የሰጡት መልስ በአካባቢው ተሰምቶ ኑሮ በዘመኑ የታወቀ አንድ ማሲንቆኛ እንዲህ ሲል አንጐራጕረበት ።

"ኮረብታም ባያክል ቁመቴ ደረቴ
ከምድር ውስጥ ነው ያለው ወንድነቴ
ከተራራው በታች ዘልቆ ገብቷል እግሬ
ጽኑ መሠረት ነው ላገሬ ለክብሬ
እጥር ነው እሾህ ነው ለዳር ለድንበሬ
ፈንቅሎ ይወጣል ከተራራው ላይ
አገሬን በሚመኝ ባገሬ ጠላት ላይ ።"

የኢጣሊያ ወታደሮች ምፅዋ ከሠፈሩ በኋላ የእንግሊዞች አስተያየትና አስተሳሰብም እየተለወጠ መሔድ ጀመረ ። ሱዳን ውስጥ የተነሣው የማሕዲስቶች እንቅስቃሴ ፥ በኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩትን ደጋፊዎቹን እያስተባበረ ከከሰላ እስከ ምፅዋ የተስፋፋ እንደሆነ በእንግሊዝ ድጋፍ ምፅዋ ለሠፈሩትም ጣሊያኖች አስቸጋሪያቸው እንደሚሆን በመረዳት በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ጐሳዎች 'ከራስ አሉላ' ጋር ተባብረው ማሕዲስቶችን እንዲወጉ እንግሊዞች መወትወትና ማስታጠቅም ጀመሩ ።

እንግሊዞች አዲስ ለቀየሱት ብልጠታቸው ማስተማመኛ እንዲሆንላቸው ሲሉም ቀደም ብሎ ከአድሚራል ሒዊት ጋር በተደረገው ስምምነት መሠረት በከረንና በአመዲብ ምሽጐች የነበረው የግብጽ ጦር ወጥቶ ወደ ምፅዋ ሲሔድ ምሽጐቹን የራስ አሉላ የጦር አበጋዝ ለነበሩት ለብላታ ገብሩ አባ ጨቄን እንግሊዞች አስረከቡ ።

አሉላ እነዚያ ምሽጐች በእጃቸው ከገቡ የምዕራባውያን ቀላጸጥታ ለመጠባበቅ አስተዳደራቸውን ለማስተካከልና ሕዝቡን ለማስገበር እንደሚችሉ ተማመኑበት ።በሌላ በኩል ደግሞ "ምፅዋስ!" የሚለው ደወል ዕረፍት አላጣቸው ። ከሹማምንቶቻቸውና ከጦር አለቆቻቸው ጋር በተነጋገሩ ቁጥር ፥

"ምፅዋ ላይኮ ጉሮሮአችንን የሚያንቅ ጠላት መቀመጥ የለበትም ፥ ምፅዋ ከጃችን እንደወጣች ከቀረች ትንፋሻችን መቆሙ" እያሉ መናገር አዘወተሩ ።



በዚያው ሰሞን ደግሞ የከረንን ምሽግ ያስረከበው የግብጽ ጦር ወደ ምፅዋ እንዳያልፍ የማሕዲስቶች ተባባሪ የነበረውና የሱሐኪም ባላባት አብዱል ቃድር የሚባለው ወንበዴዎች ሰብስቦ በአሥመራና በምፅዋ መካከል በሚገኘው አይለት በሚባለው ረባዳ መሬት ላይ ቆድቦ መቀመጡን ራስ አሉላ ሰሙ ።

"የባሕር እስትንፋሳችንኮ መቼም ጊዜ ቢሆን በወስላቶች ቀርቶ ከባሕር ማዶ በመጡ ወራሪዎችም ቢሆን መደፈር አይገባውም" ብለው ራሳቸው አዝማች ሆነው በጠፍ ጨረቃ ዘምተው ጦርነት ከወንበዴዎቹ ጋር ገጠሙ ።በዚያ ጦርነት የወንበዴዎቹ አለቃ አብዱል ቃድር ተሹለክሉኮ ሲያመልጥ ግብረ-አበሮቹ በሙሉ አለቁ ።አሉላ በዚያ ድል ብቻ አልተመለሱም ። ከአሥመራ ወደ ምፅዋ የሚወስደው መንገድ ሌትና ቀን ጸጥታው የተረጋጋ ሆኖ ነጋዴዎች ያለምንም ችግር እንዲመላለሱ ሲሉ አካባቢውን ከወንበዴዎች ለማጽዳት አሰሳቸውን ቀጠሉበት ። ባዕዳን እየሰበኩ መሣሪያም እየሰጡ በዚያ ወረዳ አሠማርተዋቸው የነበሩ የማሕዲስቶች ደጋፊዎች ነዋሪውንም ሆነ መንገደኛውን ሁሉ አስቸግረው ነበሩና አሉላ ባደረጉት አሰሳ ተጠራርገው በቀበሌው ታላቅ እፎይታ ሆነ ።

የግብጽ ወታደሮች የከረንን ምሽግ ለራስ አሉላ የጦር አበጋዝ ባስረከቡበት ዕለት በምፅዋ የነበረው የኢጣሊያ ጦር አዛዥ ኰሎኔል ሳሉታ ደግሞ ፥ አረፋይሌ የሚባለውን መንደር ወታደሮቹን ልኮ አስያዘው ። አከታትሎም ሕርጊጐ የተባለውን መንደር ያዘ ። በዚያም አላበቃም ። የግብጽ ወታደሮች ሠፍረውበት የነበረውን የሰሐጢን ምሽግ ለመያዝ ደግሞ ዝግጅቱን ጀመረ ። የኢጣሊያኑን ዝግጅት ግን እንግሊዞች አልደግፉትም ነበር ። የግብጽ ወታደሮች ሰሐጢ ላይ እንደ ሠፈሩ እንዲቆዩ አጼ ዮሐንስ ከአድሚራል ሒዊት ጋር የተስማሙት ከአሥመራ ወደ ምፅዋ የሚመላለሱት ነጋዴዎች በወስላቶች እንዳይቸገሩ ለመከላከልና ለማስጠበቅ ሲሉ ነበር ። ስለዚህ ግብጾች ቀበሌዎቹን ከለቀቁላቸው አሉላ ራሳቸው ጦር አሥፍረው ለማስጠበቅ እንደማይቸገሩ የተረዱት እንግሊዞች በቀበሌው ኢጣሊያኖች ቢሠፍሩ ራስ አሉላ በዝምታ እንደማይመለከቱ ተረዱት ።

ከዚህ ሌላ ደግሞ ፣ የከረንን ምሽግ ኢትዮጵያ ተረከባለች ። የማሕዲስቶች ንቅናቄም እየገፋና እየተስፋፋ ሔዷል ። ራስ አሉላ ብቻ ሳይሆን አጼ ዮሐንስም አጥብቀው በሚመለከቱትና በሚከታተሉት በቀይ ባሕር አካባቢ እንደዚያ የመሰለ ሁኔታ ሲታይ ደግሞ አሉላ ወደ ከሰላ ሊያደርጉ ያሰቡትን ዘመቻ ትተው ወደ ምፅዋ ፊታቸውን ሊያዞሩ እንደሚችሉ በእንግሊዞችና በግብጾች ዘንድ የታመነበት ጉዳይ ሆነ ።

የማሕዲስቶቹ ግፊት እንግሊዞችንና ግብጾችን ብቻም ሳይሆን በምዕራባዊ ቆላና በምፅዋ አካባቢ የነበሩትንም የክርስትና እምነት ተከታዮችና የማሕዲስቶች ተቃዋሚዎች የሚያሳስብ ሆኖ በመታየቱ የሁሉም እምነት በራስ አሉላ ላይ ያረፈ ሆነ። በዚህም የተነሣ አሉላ ወደ ከሰላ እንዲዘምቱና ማሕዲስቶችን እንዲወጉ የሚወተውቱት እየበረከቱ ሔዱ ። ራስ አሉላ ግን የከሰላውን ዘመቻ እያዘገዩ ወደ ምፅዋ ማትኮር እያዘወተሩ ሔዱ። ይህ ትኩረታቸው ደግሞ እንግሊዞችን በይበልጥ እያሳሰባቸው ሔደ ።

ምንም እንኳን ምፅዋ የሠፈሩት ጣሊያኖች በመልእክተኞቻቸው በኩል ፣ "የማሕዲስቶችን እንቅስቃሴ አብረን እንዋጋለን" ብለው ቢልኩባቸውም ቅሉ ፣ አሉላ በዚህ ቃል ሙሉ እምነት ሊጥሉበት አልቻሉም ነበር ። የእንግሊዞች ሁኔታ በቂ ትምህርት ሆኗቸው ነበርና ።

እርግጥ ነው እንግሊዞች ከፈረንሣዮች ጋር በነበረባቸው የቅኝ ግዛት ሽሚያ የኢጣሊያኖችን ተባባሪነት ፈልገውት ስለነበረ ምፅዋ ላይ እንዲሠፍሩላቸው አድርገዋል ። ከምፅዋ ወጥተው ሌሎች ቀበሌዎችን መያዝ ከጀመሩ ደግሞ ሁኔታው እየተበላሸ እንደሚሔድ ተረድተዋል ። ምፅዋ ላይ ጣሊያኖች መሥፈራቸውን አጼ ዮሐንስ በጥብቅ ተቃውመው ለንግሥት ቪክቶሪያ ጥብቅ ደብዳቤ ጽፈዋል ። በዚያ ላይ እንዳሉ ደግሞ የሌሎቹን ቀበሌዎች ጣሊያኖች ቢይዙ ነገሩ እየተለወጠና እየተበላሸም እንደሚሔድ ግልጽ ሆነ ።

ሮማ ከነበሩት አለቆቹ ጋር በሐሳብና በአሠራር ርቆ የነበረው ኩሉኔል ማሌታ የእንግሊዞችን ሥጋትና ምክር አሽቀንጥሮ



ጣልና እምባ የተባሉትን መንደር ለማስያዝ የላካቸውን ወታደሮች በአካባቢው የነበሩ የማሕዲስቶች ደጋፊዎች ከበው ፈጁ[illegible]ሉት ፤ ይህም ደግሞ እንግሊዞችን በይበልጥ አስደነገጣቸው ። የማሕዲስቶቹ ደጋፊዎች ባገኙት ድል ይበልጥ እያበጡበት ስለሔዱ ከአንድ ሺህ በላይ የሚሆኑ ኢጋሚዶዎች ሰብስበው አብደልቃድር የሚባለውን የወንበዴ አለቃ አዝማች አድርገው ተነሥተው ከአሥመራ ወደ ምፅዋ የሚወስደውን መንገድ እንደገና ይዘው ራስ አሉላንም ሆነ ጣሊያኖችን ለመገጠም ተነሡ ። በዚያው ጊዜ ደግሞ ሐባብ ውስጥ የነበረውና የራስ አሉላ የመረረ ተቃዋሚ የሆነው ክፍለየሱስ እንደዚሁ ጦር ሰብስቦ ራስ አሉላን ለመውጋት እንዲነሣና ማሕዲስቶች ቀበሌውን ሲይዙ አገረ ገዥ እንዲሆን ከማሕዲስቶች ጋር መስማማቱን አሉላ ሰሙ ። እነዚያ ሁለት የወንበዴ አለቆች የግዛታቸውን ጸጥታ ማወካቸው እንደ ለማሕዲስቶች አገራቸውን አሳልፈው ለመስጠት መዘጋጀታቸው እጅግ ያስቆጣቸው አሉላ ራሳቸው ሠራዊታቸውን እየመሩ ዘምተው በመጀመሪያ አብዱልቃድርን ከነወንበዴዎቹ አጠቁት ። ክፍለ የሱስም ይህን ሲሰማ ወደ ሱዳን ጠረፍ ፈረጠጠ ።

ራስ አሉላ ፣ በማሕዲስቶቹ ላይ ያገኙት ድል የጣሊያኖቹንም ሁኔታ ለመገመት አጋጣሚ ስለሆናቸው ፣ "አገራቸውን ከድተው ከኢትዮጵያዊነታቸው ይልቅ ደርቡሾች (ማሕዲስቶች) ነን የሚሉትን አሳፋሪ ወንበዴዎች አጥፍቻቸዋለሁ ። አንተንም ደስ እንደሚልህ አምናለሁ ። ስለዚህ ሌላ ደግሞ በምፅዋ በኩል ያለጣሁት ጠመንጃ ስላለ ያለምንም ችግር [illegible]ሊላክልኝ እንድታደርግ አሳስብሃለሁ" ብለው ለኩሉኔል ማ[illegible] ላኩበት ።

ኩሉኔል ማሌታም ምፅዋ በነበረው ግሪካዊ ወዳጃቸው በኩል ያስገዙት ጠመንጃና ጥይት ያለምንም ችግር እንዲሔድላቸው የሚያደርግ መሆኑን ገልጾ ቀጥሎም ፣ "አካባቢውን የሚጠባበቁ ወታደሮች ስሐጢ ላይ ለማስፈር ስለፈለግሁ ቤቶች እንዲሠሩ ይፍቀዱልኝ" ብሎ ላከባቸው ።

ይህ መልእክት ደግሞ አሉላን ወደ ጥርጣሬ የሚመራ ሆነ ። ከምፅዋ ወጥቶ ስሐጢ ለመሥፈር የፈለገበትን ምክንያት አላወቁትም ነበርና ፤

“መሣሪያውን ተረክቦ እንዲያመጣ ሻለቃ አርአያን ልኬዋለሁ። ያንተ ወታደሮች ሰሐጢ ድረስ ከሸኙት ይበቃቸዋል። ከዚያ በኋላ ወደ ምፅዋ ይመለሱ እንጂ በዚያ መቆየታቸውን አልፈቅድም” ብለው መለሱለት። ከዚያ በኋላ በሁለቱ መካከል የነበረው ሁኔታ በመጠራጠርና በመጠባበቅ ላይ ያተኮረ ሆኖ ለወራት ያህል ቆየ።

አጼ ዮሐንስም ኢጣሊያኖች ከምፅዋ እንዲወጡላቸው ለእንግሊዝ ንግሥት ደብዳቤዎች መስደድ ቀጠሉ።

ኰሎኔል ሣሌታ ፣ የራስ አሉላ ክብደት የማይገፋ ብቻውን ሊቋቋመው የማይቻለው መሆኑን ስለተረዳው ፣ እርሳቸውን ሊያዳክምለት የሚችል ሁኔታ ማመቻቸት እንደሚሻል በመገንዘብ ለእርሳቸው ተቃዋሚዎች በእጅ አዙር መሣሪያ ማቀበልና ከማሕዲስቶች ጋር በምሥጢር የወዳጅነትና የመረዳዳት ስምምነት ማድረግ ጀመረ። በዚሁም መሠረት ከምፅዋ ምግብና ሸቀጣ-ሸቀጥ እንዲደርሳቸው ማድረጉን ራስ አሉላ ሰሙ።

ባንድ በኩል ወደ ከሰላ ወርደው ማሕዲስቶቹን መግተው አገሩን እንዳይዙና እንቅስቃሴውን እዚያው ላይ እንዲገቱት እንግሊዞች ይወተውቷቸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ፣ ኢጣሊያኖች ከማሕዲስቶች ጋር አዲስ ሽርክና ጀምረዋል። ሁለቱ አውሮፓውያን ኃይሎች ሁለት አቅጣጫ በመያዛቸው ፣ ዙረው ዙረው የት ላይ እንደሚገናኙና ድርሻቸውን እንደሚከፋፈሉ አሉላ ማነጣጠር ጀመሩ።

“እኔን ወደ ከሰላ ገፋፍተው አዝምተው አሥመራ ላይ ጉብ ሊሏት አስበው ይሆን ?ከኔስ ጠላቶች ጋር ለምን በምሥጢር መረዳዳት ጀመሩ ? የግብጽ የበላዮችንም ጣሊያኖችንም ምፅዋ ያስገቡ እንግሊዞች ናቸው። አሁን በእነርሱው አማካይነት ከሐባብ ጐሳዎችና ድርቡሾች (ማሕዲስቶች) ጋር የጀመሩት ምስጢር ውጤቱና ትርጉሙ አሥመራንና ከረንን ለመያዝ ይሆን ?”እያሉ ማሰላሰል ጀምረዋል።

ሁኔታው በይበልጥ እንዲብራራላቸው ስለ ፈለጉም ለኰሎኔል ሣሌታ በሰደዱለት መልእክት ፣



“እስላሞች ድርቡሾች ነን እያሉ መነሳሰት ይዘዋል። በሐባብ የሚገኙት ሽፍቶችም በዚሁ መንፈስ ተሰብስበው መሣሪያ በመቀበል ላይ ናቸው። መሣሪያውንም የሚያገኙት ከምፅዋ መሆኑን ደርሼበታለሁ። በእናንተ በኩል እየታወቀ እንዳልታወቀ ተመስሎ ይህ ነውር ነገር መሠራቱ አሳዝኖኛልና ሁለተኛ እንዳይደገም እንድታደርግ። ከእርሱ ጋር ወዳጅነትና አንድነት ለማድረግ ፈቃዳችሁ ከሆነም ቁርጡን አሳውቀኝ” ብለው ነበር። ኰሎኔል ሣሌታ ግን የራስ አሉላን ጥያቄ ችላ ብሎ እንዲያውም “ይግረመዎ ብሎ” ወታደሮቹን ሰሐጢ ላይ አሰፈረ።

በራስ አሉላ ፣ በእንግሊዞችና ጣሊያኖች መካከል እንደዚያ የመሰለ ሁኔታ ተፈጥሮ ሦስቱም በየፊናቸው ጉዞ በጀመሩበት ሰዓት የማሕዲስቶቹ ግፊት እየበረታ ሔደ። ከሰላ ውስጥ የተከበቡትን ግብጻውያንና የእንግሊዝ ጥገኞች ያለ ራስ አሉላ የሚታደጋቸው እንደሌለ የተረዱት እንግሊዛውያን ደብዳቤና ሰው እየላኩ አሉላን መወትወት ቀጠሉ። በተለይም ከእንግሊዞችና ግብጾች ጋር የጠበቀ ወዳጅነት መሥርተው የነበሩ አሥመራ ድረስ እየሔዱ ራስ ወደ ከሰላ እንዲዘምቱ ልመናቸውን ደጋግመው ከማቅረብ ችላ አላሉም ነበር።

አሉላ ግን ፣ እንደ ዐይናቸው ብሌን በሚመለከቱዋቸው በበጐስና በምፅዋ አካባቢ ፣ የሐባብ ጐሳዎች ማሕዲስቶች የተፈራሩት ግብጾችና አዲሶቹ ጉልበተኞች ጣሊያኖች ያን ሁሉ ጥልፍልፍ እየዘረጉባቸው ወደ ከሰላ መዝመትና የድሮ ጠላቶቻቸውን ለመበቀል ጦርነት መግጠሙ አጣዳፊና አስፈላጊም ሆኖ አላገኙትም ነበርና “መጣሁ መጣሁ” እያሉ ብቻ አሥመራ ላይ ሆነው በምዕራብና በምሥራቅ የተደቀነባቸውን ቀስት ሲመለከቱ ማሕዲስቶች ከሰላን ያዙዋት።

የከሰላን መያዝ ፈጥነው ያልደረሱበት እንግሊዞችም የራስ አሉላ ዝንባሌ ወደ ምፅዋ ማጋደሉን በመረዳት አሉላ ፈጥነው ወደ ከሰላ እንዲዘምቱ ለማድረግ ሲሉ ዙላ የተባለውን ቀበሌ ለኢትዮጵያ ለመመለስና ለሚስረከብ ማቀዳቸውን ከምፅዋ ወደ ለንደን መልእክት አስተላለፉ። ያን አሉላን ሊያስፈነጥዝ ለኢጣሊያኖች ግን የራስ ምታት ሊሆን ይችል የነበረውን ዕቅድ ግን

ለንደን የነበሩት ባለሥልጣኖች ተቃወሙት ። ይሁን እንጂ በም ፅዋ የነበረው የእንግሊዝ መንግሥት ተጠሪ ኰሎኔል ክርምቢይድ በነገሩ ተስፋ ሳይቆርጥ ሃምሳ ሺህ የማሪትሬዛ ብር እስይዞ የፈለጉትን ያህል ጠመንጃና ጥይትም እንደሚልክላቸው በፍጥነት ወደ ከሰላ የሚዘምቱ ቢሆን እስከ ሦስት መቶ ሺህ የማሪትሬዛ ብር የሚልክላቸው መሆኑን በማብራራት ግብጻውያን መልእክተኞች ሰደደ ።

የእንግሊዞችን ጎጸ-በረከትና የልመና ደብዳቤ ይዞ ወደ አሥመራ የሔደው ማርክ ቢይ የተባለው ግብጻዊ ከራስ አሉላ ዘንድ ቀርቦ የወሰደላቸውን ሁሉ ካበረከተ በኋላ ፣ “ወደ ከሰላ ሲዘምቱ የሚረዳዎ ደግሞ በቅርብ ቀን ውስጥ አንድ ሺህ ጠመንጃዎች እንልክልዎታለን” አላቸው ።ራስ አሉላም ከፊታቸው የቆመው መልእክተኛና የበላዮቹ የሆኑት እንግሊዞች በአገራቸውና በእር ሳቸው ላይ ሲያስፈጽሙት የኖሩት ተንኮል ሁሉ ከፊታቸው እየ ተደቀነ ቁጣቸውንም እየቀሰቀሰባቸው በመሔዱ ፣

“ያሁኑን ጭንቀታችሁን ተረድቼላችኋለሁ ። በበኩሌ ደግሞ አንድ ነገር ልጠይቃችሁ ነው ። ምንም እንኳን እኛ ባንስማማ በትም መቼም ምጥዋን ይዛችሁ ወጭና ገቢውን ትቆጣጠራላ ችሁ ። ታዲያ ጣሊያኖች ምጥዋ ሲገቡ ለምን ዝም አላችኋቸው፣ ከምጥዋም አልፈው ሰሐጢ ላይ መሥፈር ጀምረዋል ። በዚህ ነገር ላይ ከእናንተ ቁርጥ ያለ ሐሳብ ለማግኘት እፈልጋለሁ ። ይህን ሳላውቅ ወደ ከሰላ አልዘምትም ፣ እንስማማ የትምሉ ከሆነ ጣሊያኖቹን አስወጡ” ብለው አትኩረው ተመለከቱት ።

“እንግዲህ ይህንንም ጉዳይ ቢሆን ምፅዋ ተመልሼ ለአለቆቼ ላስረዳና ቁርጡን እንልካለን” አለ መልእክተኛውም የአሉላ ቁጣ የለበለባቸውን ፀይኖቹን እያስለመለመ ።

የራስ አሉላና የከሰላው ዘመቻቸው ጉዳይ በዚያ ላይ እን ዳለ ኢትዮጵያዊነታቸውን በምንም ስለምንም ያልተለወጡት የበኒዓምር ጐሳዎች ከማሕዲስቶች ደጋፊዎች ጋር ግጭት እስ ነው ። በተለይም የሐደንደዋ ጐሳ ተጠሪ የነበሩት ታዋቂው ጦረኛ ሼህ ባክርኤል ምርቃኒ የማሕዲስቶችን አድራጐት በጥ



ብቅ በመቃወማቸው በቀበሌው የተቀሰቀሰው ግጭትና ትርምስ እየተባባሰ ሔደ ። ከዚህ ሌላ ደግሞ ፣ “ራስ አሉላ ወደ ከሰላ ለመዝመት በዝግጅት ላይ ናቸው” የሚል ወሬ ለማሕዲስቶች መሪ ስለደረሰው ፣ አስቀድሞ በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ለመጀ መር ወስነና ሠራዊቱን ወደ ኩናማዎች ቀበሌ አዘመተ ። የጦሩ አዛዥ የነበረው ለራስ አሉላ ፤

‘ከሰላን ለመውረር እንደምትመጡ ሰምተናል ። ይህን ነገር የአሚሮች አሚር ኡስማን ዲግና ሰምተው ሠራዊታቸውን አሠል ፈው ይመጣሉ ፤ ጉዞም ጀምረናል ። ከሰላም ገብተናል ። እንግዲህ ቆራጦች ከሆናችሁ ኑና እንጋጠም ። የማትመጡ ከሆናችሁ ግን እኔ እመጣላችሁአለሁ ። እናንተንም በአላህና በነቢዩ የማያምኑ ትንም ሁሉ በሰላው ሰይፌ እቆራርጣችኋለሁ ። ነፍሳችሁም በቀ ጥታ ወደ ገሐነመ-እሳት ትወርዳለች” ብሎ ላከባቸው ።

የማሕዲው ጦር አዝማች ኡሱማን ዲግና ይህን መልእክት ወደ ራስ አሉላ በመላኩ አለቃው ከሊፋ አብደላ ሰምቶ ኑሮ ፣ “ወደ ኢትዮጵያ መዝመትህን ሰማን ። በከሰላ በኩል ያለው ችግር እንደነበረ መሆኑንም ሰምተናል ። ያ በሱዋኪን በኩል ያለው ችግርም እንደዚያው እንዳለ ነው ። ይሁንና በጣም አስፈላጊ ለሆኑ ጉዳዮች ቅድሚያ መስጠት ይኖርብሃል ። ኢትዮጵያውያንን አትንካቸው ፤ ወደ አገራቸውም አትግባ ፤ ሰዋኪንን ብቻ ከያዝክ በቂያችን ነው ። የምንፈልገውም እርሱን ብቻ” ብሎ ልኮበት ነበር ።

ይሁን እንጂ ኡስማን ዲግና የመሪውን ትእዛዝ አልተቀበ ለም ። መስከረም 3 ቀን 1878 ጦሩን እየመራ ኩፊት ከተ ባለው ቀበሌ ሠፈረና ምሽጉን አጠናክሮ ሠርቶ ጦሩን አዘጋጅቶ ከከናወነ በኋላ “መጣሁብህ ጠብቀኝ” ብሎ ለራስ አሉላ ላከባ ቸው ። የሠራዊቱም ብዛት ከስድስት ሺህ እስከ ዐሥራ ሁለት ሺህ ይደርስ ነበር ።

ኢትዮጵያ የከረንን ምሽግ ከተረከበች በኋላ ፣ ብላታ ገብሩ አባ ጨጓን የአገሩ አስተዳዳሪና የምሽጉም ኃላፊ እንዲሆኑ ራስ አሉላ ሹመዋቸው ስለነበረ ፣ ብላታ ገብሩም በአካባቢው እየተ

ስፋፋ ይሔድ የነበረውን የማሕዲስቶች ኃይል ለመቋቋም ሲ
ኢትዮጵያዊነታቸውን በምንም ስለምንም ሳለመለወጥ ሲታገ
ከነበሩት ከበኒዓምር ጐሣዎች ምርጥ ምርጥ ተዋጊዎች መር
ውና በቂ መሣሪያም ሰጥተው ከራሳቸው ወታደሮች ጋር ከ
ለት ሺህ በላይ የሚሆን ጦር በምሽጉ ውስጥና አካባቢ አሠፈሩ

ከዚያ በኋላም ብላታ ገብሩ ወደ ከሰላ እንዲዘምቱ ራ
አሉላ ትእዛዝ አስተላለፉ ። በዚሁ መሠረት ብላታ ገብሩ
መስከረም 11 ቀን 1878 የመጀመሪያውን ተዋጊ ጦር አዘመቱ
ግን ምሽግ ሠርቶ አጥቂም መሬት ይዞ ሲጠባበቅ የነበረው የ
ሕዲስቶች ጦር ድል አደረገ ። ይሁን እንጂ ብላታ ገብሩ ሌ
ጦር ማዘጋጀት ደግሞ ቀጠሉ ።

በምሥራቅ ሱዳን የተነሣውን የማሕዲስቶች ንቅናቄ እጅ
የፈሩት እንግሊዞች 'ያለ አሉላ ከንድ የሚገታው የለም' ብለ
ወሰኑ ። ስለዚህ አሉላ ፈጥነው እንዲዘምቱ ውትወታቸውን ቀ
ሉበትና ከስድስት መቶ በላይ የሚሆን ጠመንጃ አስይዘው ግ
ኮፖሎ ቤይ የተባለውን ወዳጃቸውን ለአማላጅነት ከምፅዋ ወ
አሥመራ ሰደዱት ። አማላጁም ጭኖ የወሰደውን መሣሪያ
ሌላም ገጸ-በረከት ከራስ አሉላ ፊት አቅርቦ ፣

"እባክዎ ከሰላን ከአሠቃቂው እልቂትና ውድቀት ፈጥነ
ያትርፉልን" ብሎ ጠየቃቸው ።

"ወደ ከሰላ እዘምታለሁ ። ግን ለእናንተ ገጸ-በረከት ሳይሆ
የተጨነቁትን ለመርዳት ስል መሆኑን እንድትረዳልኝ አደራህን
ብለው ትኩር ብለው ተመለከቱትና እንደገና ንግግራቸውን ቀ
ለው ደግሞ ፣

"ግን በቅድሚያ አንድ ነገር ልጠይቃችሁ እወዳለሁ
ኢጣሊያኖች ምጥዋ ላይ ምንድን ነው የሚሠሩት ? ወደ አገ
ቸው ፈጥነው ቢመለሱ ይሻላቸዋል ። ከደበበስ ጋር ምንድነ
ያመሣጠራቸው ። ስሐጢ እንሥፈር ማለታቸውስ ምን ለማድረ
ነው ? ከዚያስ በኋላ ወደየት ሊያተኩሩ ነው ? ምጥዋም ሆነ ስሐ
የኢትዮጵያ መሬት መሆኑን አጥተውት ነው ? ወይስ ግን ይ



ናል ብለው ነው ? ይህን ድፍረታቸዉን በቸልታ ወይም በፍርሐት ተውጠን የማንመለከተው መሆናችንን እርስዎም ለጣሊያኖቹም ሆነ ለእንግሊዞቹ እንዲያስታውቁልን አደራ እለዎታለሁ" አሉ ።

"ጣሊያኖቹ 'ለጊዜው ነው እንጂ ወደ አገራችን እንመለ ሳለን' ብለዋልና እስተዚያው...." ብሎ ተናግሮ ሳያበቃ አሉላ አቋረጡትና ፣

"ለጊዜውስ ቢሆን ማን ፈቅዶላቸው ነው የሠፈሩት ? ወይስ በደንከል ውስጥ ካንድ ወስላታ ሰው እንደ ገዙት መሬት ምጥዋ ንም የሸጠላቸው አለ ? ግብጾች ሸጡላቸው ? ወይስ እንግሊዞች ሸጡላቸው ? ለጊዜውስ ቢሆን ምንድነው የሚሠሩበት ! እይሆንም ኋላ ያጋጩናል ። ከእንግዲህ ወዲያ አገሬ ድንበሩዋን የሚዳፈሩ ትን በቸልታ አትመለከትም ። ያለፈው ድፍረት ይበቃል"አሉና አንገታቸውን ወደ ምፅዋ አቅጣጫ መለሱ ።

"እሺ ጌታዬ እንደ ተመለስኩ ይህንኑ አስረዳለሁ" አለ መልእክተኛው አንገቱን ደፍቶ ።

ካንደዬም ሁለተዬ ይህን ቁርጠኛ አነጋገር የሰማው ፣ ማርኮ ፖሊ ወደ ምፅዋ ተመልሶ ሁኔታውን በምፅዋ ለነበረውና ራስ አሉላ ወደከሰላ ዘምተው ማሕዲስቶችን እንዲወጉለት በገጸ-በረከ ትና በአማላጅ ሲወተውት ለነበረው ኩሉኔል ከርምሳይድ ለተ ባለው እንግሊዛዊ አስረዳው ።

"ገንዘብም መሣሪያም እየሰጠን ብንለምናቸውም ለውዬው ዐይኖቻቸውን ከጣሊያኖች እንቅስቃሴ ላይ ሊያነሡ አልቻሉም ማለት ነው ? ሐሳባቸውንም እግሮቻቸውንም የተከሉት ምፅዋ ላይ ነው ማለት ነው ?"ብሎ ኩሉኔሉ ሲተክዝ ቆየና ፣

"አሁንም እንደገና ወደ አሥመራ ልትመለስ ነው ። በምፅዋ በኩል እርሳቸውንም ሆነ አገራቸውን ሊያሠጋ የሚችል አንዳ ችም ነገር ሊኖር እንደማይችል አስረዳቸው ። ደበበንም ሆነ ሌሎቹን ሽፍቶች ከገቡበት ገብተን እንደምንይዛላቸው አስረዳ ቸው" ብሎ እንደገና ማርኮ ፖሊን ወደ አሥመራ ሰደደው ።

ኰሎኔሉ ቃሉን ለመጠበቅም ሲል ወታደሮቹ ሽፍቶችን እንዲያሳድዱ አመገራቸው ።

ማርቆ ፖሊ እንደገና ወደ አሥመራ ተመልሶ እንደ ታዘዘው የኰሎኔሉን መልእክት ለራስ አሉላ አደረሰ ። አሉላ ግን የእንግሊዞችን ቃል ሊተማመኑበት ከማይችሉበት ወቅት ላይ ደርሰው ስለነበረ መልእክቱ ከአንጀታቸው ጠብ አላለ አላቸውና ፡

“እነርሱን እንኳን ማመኑን ትቸዋለሁ” ብለው እንግዳውን መለሱት ። በዚያው ወቅት ደግሞ የማሕዲስቶቹ እንቅስቃሴ እየገፋ መጣ ። አዝማቹ ለራስ አሉላ የላከው የዘለፋ ቃልም ከልባቸው ገብቶ ዕረፍት እየነሣቸው ሔደ ።

“እንደ ተለመደው የጦር አለቆቻቸውንና ባለሟሎቻቸውን ሰብስበው ፡ “ልጆቼ ወዳጆቼ ! ጊዜው ፈተናዎችን እያደራረበብን ነው ። አገራችንን ፈላጊ አሰፍስፎብናል ። በባሕሩ በኩል ግብጾችና እንግሊዞች በረድ ሲሉልን ጣሊያኖች ደግሞ ተተክተውብናል ። በከሰላም በኩል የደርቡሽ ጦር እየገፋ መጥቷል ። አጥንት የሚሰብር ፡ ጋብቻ የሚከለክል ስድብም ይልኩብን ጀምረዋል ።

“ምንም እንኳን ከሰላን መልሰን እንድንይዛት ንጉሠ ነገሥቱ ቀደም ብለው ቢያዙኝም ፡ ሠራዊቱ እንዲያርፍና እንዲያርስ መሣሪያም እስኪዘጋጅ ብዬ ፈጥኜ አልዘመትኩም ። የጣሊያኖቹንም ነገር ማጻመጡን ፈልጌው ነበር ። እንግሊዞች ደጋግመው የላኩብኝ የጣሊያኖቹ ነገር አያሳስብም እያሉ ነው ። እኔ ግን ሁሉንም አላመንኳቸውም ። ድርቡሾች ይኸውና እንደምትሰሙት ከከሰላም አልፈው ሕዝቡን እየዘረፉ ምሽግም እየሠሩ ነውና ፈጥነን ካልዘመትንባቸው ዙሪያችን መከበባችን የማይቀር ስለሆነ ፡ ወደ ደጋው ሳይወጡ እዚያው ከቆላው እንዳሉ ማስቀረት ይኖርብናል ። ብላታ ገብሩም በቅድሚያ እንዲወርድ አድርጊያለሁ ። ፈጥነን ካልዘመትን ደግሞ ወንዞቹ ይደርቁና የውሃ ችግርም ሆነ የወባው በሽታ የማይቻለን ይሆናል ። ስለዚህ ነገር ሐሳባችሁን እንድትነግሩኝ ብዬ ነው ዛሬ ያስጠራኋችሁ” አሉ እያንዳንዳቸውን በተራ እየተመለከቱ ።



በዚህ ጊዜ ፊታውራሪ ኃይለ ሥላሴ ተነሥተው መኳንንቱን አንድ ባንድ ከተመለከቱ በኋላ ፡

“ባባቶቻችን ያልደረሰ አልመጣብንም ። አባቶቻችንም ‘ትውልድ ይወጣው’ ብለው ጠላት አገራችን ውስጥ አስገብተው አላቆዩንም ። በሚቻላቸው ታግለውታል ፤ እኛም ለልጆቻችን ጠላት ማቆየት አይገባንም ። ነገሩን ተረድተነዋል ። ቀኑ ይቆረጥና እንዝመት” ብለው ተቀመጡ ። በዚሁ ሐሳብ ሁሉም የሚስማሙ መሆናቸውን አስታወቁ ።

በምፅዋ በኩል የነበረውን የጣሊያኖች ትኩረትና እንቅስቃሴ ማለዘብ ደግሞ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ሆኖ ተደቀነባቸው ። ለጊዜው “በሰላምና በወዳጅነት” የቀረቡትን ኢጣሊያኖች ማለዘብም አስፈላጊ መሆኑን አመኑበትና ፡

“ከዚህ ቀደም” በወዳጅነትና በስምምነት ለመኖር ሙሉ ፈቃደኞች ነን” ብለህ የላክህልኝን ነገር ከመኳንንቶቼና ከብርቱዎቼ የጦር አለቆች ጋር መክርክሬበት ፤ ሐሳብህ ማለፊያ ነው ። የኛም ምኞት ይኸው ስለሆነ ፡ ከከሰላ በመለስ ፍሬ ፍሬ ነገሩን እንመካከርበትና ለንጉሠ ነገሥቱም እናመለክታለን ። እስከዚያው ድረስ ግን ወደ ምፅዋ የሚወርዱና ከዚያም የሚመጡ ነጋዴዎችና መንገደኞች በሆነ-ባልሆነው ምክንያት መጉላላት እንዳይደርስባቸው አደራህን” ብለው ምፅዋ ለነበረው ለጣሊያን ኰሎኔል ላኩለት ።

በምፅዋ በኩል የነበሩትን ጣሊያኖች በዚህ ስልት አቀዝቅዘው ፡ የእንግሊዞችንና የግብጾችን ሰፊ ርዳታ አግኝተው በግዛታቸው ውስጥ የነበሩትን አቀራርበውና አስተባብረው ፡ ሠራዊታቸውን አዳዲስ መሣሪያ አስታጥቀው ፡ ስንቁን አዘጋጅተው መንገዱን አስጠርገው ፡ ንጋ-ጠባ ሲፎክሩባቸውና ሲዝቱባቸው ለነበረው ለማሕዲስቶች ጦር አዝማች ለነበረው ፡

“እኔ ወዳለሁበት ለመምጣት አትቸገር ። እኔው እመጣለሁ ። እኔንም ንቀህ አገሬን ደፍረህ ገብተሃል ! በል ተዘጋጅተህ ጠብቀኝ” ብለው ፈረሰኛ አስቀድመው ልከው ቁጥሩ እስከ ዐሥር ሺህ የሚደርስ ሠራዊታቸውን እየመሩ ወደ ኩፊት ዘመቱ ።

# የኩፊት ጦርነት

ብላታ ገብሩ ፣ አባ ጩቁን ከረን ላይ ሆነው ጦር ልከው ሲከላከሉት የነበረው የማሕዲስቶች ጦር ከከሰላ ተነሥቶ ኩፊት ከምትባለው ቀበሌ ሠፈረ ። ወዲያውም ምሽጉን ሠርቶ ጦሩንና ስንቁን አስገብቶ ካበቃ በኋላ ፣

"እዚህ ድረስ እንደማትመጣ አረጋግጫለሁና ካለህበት ድረስ መጣሁብህ !" ብሎ ድጋሚ መልእክት ለራስ አሉላ ሰደደ ። አሉላም ፣

"ኩፊት ድረስ መምጣትህን ሰምቻለሁ ። እንኳን ወደፊት መጥተህ ወደ ኋላህም ብትፈረጥጥ አታመልጠኝም!" ብለው ላኩበትና ከአሥመራ ከረን ገቡ ።

ራስ አሉላ ከረን ሆነው ሠራዊታቸውን በዐዋጅ አስከትተው ካዘጋጁ በኋላ ፣ የማሕዲስቶችን ሠፈርና አሠላለፍ አጥንተውላቸው የሚመለሱ ዐሥር የሚሆኑ ፈረሰኞች አስቀድመው ሰደዱ ። እነዚያም ፈረሰኞች ኩፊት ደርሰው ሁኔታውን አጥንተው ፣

"ኩፊት ላይ ፣ የመሸገው የድርቡሽ ጦር ከሦስት ሺህ እንደማይበልጥ አረጋግጠናል"ብለው ሲነግሩዋቸው ራስ አሉላም የለበጣ ፈገግታ አሳዩዋቸውና ፣

"እንዴት ቢንቀኝ ነው ሦስት ሺህ ጦር ብቻ ይዞ የመጣው ? ቢሆንም የጠላት ትንሽ የለውምና እንዳመጣጡ እንሒድበታ!" አሉ ። ከዚያ ቀጥለውም ሠራዊታቸውንም በሦስት ዘርፍ ከፈሉት ።

በአንደኛዉ ዘርፍ ፣ ብላታ ገብሩ አባ ጩቁን ፈረሰኛውን ጦር ይዘው በግንባር ፣ በሁለተኛዉ ዘርፍ ፣ ራሳቸው ቱርክ ባሻ ራስ



አሉላ አግረኛ ተዋጊ ይዘው ደጀን ፣ ሦስተኛዉ ዘርፍ ደግሞ ፣ ወራሪና በጉን አጥቅቶ ወደ ምሽጉ እንዲገባ ሆኖ ተሰለፈ ።

በዚህ አሰላለፍ የዘመተው የኢትዮጵያ ሠራዊት መስከረም 13 ቀን 1878 ኩፊት ደረሰ ። በኦቶማን ዲግናና በሙስጠፋ ሐደል አዝማችነት ዘምቶ የነበረው የማሕዲስቶች ጦር በወጣ ገባው ቦታ ላይ ግራና ቀኝ ምሽግና እርድ ሠርቶ በሸለቆ ሥፍራ የነበረውን ዛፍ ተገን አድርጐ አድፍጦ ሲጠባበቅ በግንባር ቀደምትነት የተሰለፈው የብላታ ገብሩ ጦር በመካከሉ ገባ ። ብላታ ገብሩ ሁለት ስሕተቶች ፈጸሙ። አንደኛዉ፣ የቦታው የተፈጥሮ አቀማመጥ በርከት ያለ ሠራዊት ሊይዝ እንደማይችል ያለመገንዘባቸው ሲሆን ፣ ሁለተኛው ደግሞ ፣ አንድ ጊዜ አጥቅተው ወደኋላቸው እንዲያፈገፍጉና መልሰው ቦታ ይዘው ጠላት ከእርዱ ወጥቶ እንዲገጥም ማስገደድና ማባበል ዋናው ስልታቸው እንዲሆን ከራስ አሉላ የተሰጣቸውን ትእዛዝ ችላ ብለው ፊት ለፊት እርድ ውስጥ ገብቶ ከሚጠባበቅ ጦር ጋር መግጠማቸው ነበር ።

የጉራዕ ጦርነት ጊዜ ፣ በአጼ ዮሐንስ ይመራ የነበረው ዋናዉ የኢትዮጵያ ሠራዊት ከጦርነቱ መሥመር ከመግባቱ በፊት በራስ አሉላ አዝማችነት ዘምቶ የነበረው ጦር ጠላትን ድል አድርጐ ምሽጉን ይዞ ንጉሠ ነገሥቱን እንደጠበቃቸው ሁሉ፣ ብላታ ገብሩም የማሕዲስቶችን ጦር ድል መትተው ሠፈሩን ይዘው ራስ አሉላ ሲደርሱ ምርኮኛና ምሽግ ለማስረከብ ብቻ ነበር ቁርጥ ዓላማቸው።

ጦርነቱ ተጀምሮ በተጋጋለበት ወቅት የኢትዮጵያ ሠራዊት ባንድ ክንፍ የነበረውን የጠላት ጦር አጥቅቶ ሲገባ ፣ በሁለተኛዉ ክንፍ በኮረብታማ ሥፍራ ላይ እርድ ይዞ የነበረው የማሕዲስቶች ጦር ገጠመው ። የኢትዮጵያ ሠራዊት ከሥር ሆኖ ከኮረብታው ላይ የነበረውን የጠላቱን ኃይል ጥሶ ለመውጣት ቀርቶ ለመከላከልም ከአልቻለበት ሁኔታ ላይ ወደቀና ወደፊት መግፋትም ሆነ ወደ ኋላው መመለስ ከማይችልበት መሥመር ውስጥ በመግባቱ በነበረበት አለቀ ። አዋጊውና ስመጥሩው ጀግና ብላታ ገብሩ አባ ጩቁንና የኢትዮጵያ የማያወላውል እምነትና ፍቅር የነበራቸው የበኒዓምር ፈረሰኞችም "እንግረከም" እያሉ ትውልድ የሚያኮራ ሙያ እየሠሩ እዚያው ላይ አለቁ ።

የብላታ ገብሩ ጦር ድል መሆኑንና ራሳቸውም እዚያው ላይ መውደቃቸውን አሉላ እንደ ሰሙ እጅግ አዘኑ ።

“ገብሩ ሞተ! ገብሩ ቀደመኝ? ገብሩ ከዳኝ! ‘ጠላትክን እኔ ጣብሬ ሠፈሩን ይዤ እጠብቅሃለሁ’ ብሎኝ አልነበር? ቃሉን ጣሰ? እርሱም ድል ሆነ? የልጂን የወዳጂን የታማኝን የገብሩንና የጀግኖቹን ወታደሮቼን ደም ሳልመልስ ብቀር መሬት ትከዳኝ፣ ትውልድ ይታዘበኛል!” ብለው አሉላ ሠራዊታቸውን አሠልፈው ከጦርነቱ ገቡ ። ስልት አልለወጡም ፣ የቦታውንም የተፈጥሮ አቀማመጥ ፤ ልብ አላሉም ፤ ብላታ ገብሩ የፈጸሙትን ስሕተት ራሳቸውም ደገሙት ።

ምርጥ ምርጥ ተዋጊዎቻቸውን በግንባር አሠልፈው ሲዋጉ በከፍተኛ ኮረብታዎች ላይ የነበረው የማሕዲስቶች ሠራዊት በከፍተኛ ቆራጥነትና ሲቃ ማጥቃት ጀመረ ። የራስ አሉላም ጦር ድል ሆነና ተበታተነ ። ፈረሳቸው በጥይት ተመትቶ ራሳቸውም ወደቁ። ወዲያው ከታማኝ አሽከሮቻቸው ጋር ሆነው ከተጋጋለው ውጊያ ወጥተው አልባሌ ሰው መስለው ለመጀመሪያ ጊዜ ሸሹና ከአንድ’ ኮረብታ ላይ ወጡ ።በሠራዊታቸውም መካከል “ራስ ሞቱ’ የሚል ወሬ ተሰራጨበትና በየአቅጣጫው ተበታተነ ። እርግጥ ቆስለው ነበር ። ፈረሳቸው መሞቱን እርሳቸውም መቁሰላቸውን የተመለከቱ “ሞቱ” ብለው በማውራታቸውና በመደናገጣቸው ሠራዊታቸው ተበታተነ ። ራስ አሉላ ከጦርነቱ መሥመር ራቅ ብላ በነበረች ተራራ ላይ ከወጡ በኋላ እራፊ ጨርቅ ከጭናቸው ላይ አስረው ሲፈስ የነበረውን ደማቸውን አቆሙት ። ቀጥለውም እንግሊዞች በሸለሙዋቸው የሩቅ መመልከቻ መነጽር የጠላትን ወረዳ ተመለከቱት ።

“ለካ ተሳስተናል? ለካ ድል ያደረገን የኛው ስሕተት ኑሩዋል? በዚያ ቦታ ላይ የመሸገው ጠላት ብዛቱ ከሰማነው በላይ ነው የሚሆነው ፤ ከላይ እስከታች ከወዲህም ከአግድመቱ ጀምሮ ወታደር ከሠፈረበት ብዛቱ እጥፍ ነው የሚሆነው! ሦስት ሺህ ብቻ አይሆንም ይህን ሳናጠና ነው ከመካከሉ የገጠምንለት!” ብለው መነጽሩን ከዐይኖቻቸው ነቅለው ከኋላቸው ለነበረ ጋሻ ጃግሬ ሰጡና ከንፈራቸውን ነክሰው ራሳቸውን እያወዛወዙ ፣



“አገሬ ላይ ጠላት ሠፍሮ ቀኝ እጄ ገብሩ ወድቆ ጀግኖች ወታደሮቼ ረግፈው ፣ እኔ የዮሐንስ አሽከር ፣ እኔ የዮሐንስ ባሪያ ከድርቡሽ ሸሽቼ በሕይወቴ ቆሜ ልታይ ነው? አበሾች ድል ሆነው ሸሹ ብሎ ዓለም ሊታዘበኝ ነው? አይታሰብም! ብለው ተቀም”ጠውበት ከነበረው ድንጋይ ላይ ተነሡ ።

“ገብር ገብር ገብር ብር.. ብር—ብር—ርር” ነጋሪቱ ተጎሰመ ። “ክተት! ክተት! ክተት ት—ትት” መለከት ተነፋ ። ከዚያ በኋላ የተበታተነው ሠራዊት ወደዚያች ኮረብታ ተሰበሰበ። በወደቁት አዋጊዎች ፈንታ ሌሎች ተመረጡ ።

የማሕዲስቶች ጦር የመሸገበትን ወረዳ አሉላ ከአጠኑ በኋላ ፊት ለፊት መግጠሙ ቀርቶ በጎንና በጎን እንዲወጥር እንዲያዝ ስልት አወጡ ። ከምሽጉ በሚመጣበት ጊዜ ደግሞ በግንባር የሚገጥመውና አፈግፍጎ ከደጀን ጦር ጋር እንዲጋጠም የሚያባብለው ዘርፍ አሰለፉ ፤ ከእርሳቸው ቀጥሎም የበኒዓሚር ተወላጅ ሙሳኤልፈል ናዚር አዛዥ እንዲሆኑ ሾሙዋቸው ። በየዘርፉ በተሠለፈው እግረኛ ጦር ጀርባ ፈረሰኛ እንዲሠለፍና ወደ ኋላው የሚሸሸውን የወገን ጦር ያለ ምሕረት እንዲቀጣው አዘዙ ።

አሉላ ድል በተመቱበት ዕለት ሠራዊታቸውን አስከትተው በአዲስ ስልት ካዘጋጁት በኋላ ፣ እንደገና በማግሥቱ ጧት ጦርነቱን ገጠሙ ። ራሳቸው በፈረስ ላይ ሆነው በየግንባሩ እየተዘዋወሩ ፣

‘ወደ ኋላህ ፊትህን ያዞርክ ሥጋህን ለአራዊት ፣ ነፍስህን ለገሃነመ እሳት ዳርጌዋለሁ’ እያሉ እያሳወጁ ተዋጊ በሳሳበት በኩል ጦር እየጨመሩ ፣ አቅጣጫውን የሳተውን ሥፍራ እያስያዙ ወደ ፊት ሲያስገፉ ፣ አጥቂውን የጠላት ክንፍ በእግረኛና በፈረሰኛ እያስከበቡ ጦርነቱን መሩ ። ሠራዊታቸው ከበስተኋላው የራሱ ፈረሰኛ ፣ ከወደፊቱ በጠላት ጦር እንደ ተከበበ ካረጋገጠ በኋላ ጥርሱን ነክሶ መንፈሱን አስቆጥቶ ተዋጋ ። እኩለ ቀን ድረስ ሲፋጭ ራሳቸው አሉላ ከፈረሳቸው ወርደው ከተዋጊው ሠራዊት መካከል ገቡና ፣

“ምሽትን ካልያዝን እዚሁ ማለቅ ነው! ወደኋላ ማየት የለም ፤ የሁላችንም ዕጣ-ፈንታ ከዚህ አያልፍም” እያሉ ራሳቸው እየጮሁ ቁርጠኛ ውሳኔያቸውን አስታወቁ ።

ወደ ማታ የኢትዮጵያ ሠራዊት የጠላትን እርድ እየጣሰ መግባት ሲጀምር ፣ ሺህ አረይ የሚባሉት ፈረሰኛ ጦር ይዘው መድረሳቸውን ራስ አሉላ ሰምተው ሺህ አረይ ከጠላት በስተጀርባ እንዲገቡና ጠላት እንዳያመልጥ መንገዱን እንዲዘጉበት ከከሰላም የሚመጣ ደጀን ጦር እንዲከላከሉት ትእዛዝ አስተላለፉላቸው ። በሦስት አቅጣጫ ተሠልፎ ወደፊት ሲገፋ የነበረው የራስ አሉላ ሠራዊት ወደ ጠላቱ እርድ መግባት ሲጀምር ጠላት ከምሽጉ እየወጣ በጨበጣ ተጋጠመ ። የኢትዮጵያ ሠራዊት በቅልጥፍናና በአመካከት እጅግ በመላቁ እየጠቃ ወደፊት ሲገባ ጠላት ከእርዱ እየወጣ ወደ ኋላው መፈርጠጥ ሲጀምር ደግሞ የሺህ አረይ ፈረሰኛ ጦር እየተቀባበለ አስቀረው ።

ራስ አሉላ ፣ የሺህ አረይ ፈረሰኛ ጦር መንገድ እንዲዘጋ የሰጡት መመሪያ ሌላ ታላቅ ውጤትም አስገኘላቸው ። ለእርዳታ ከከሰላ ሲገሠግሥ የነበረውን የጠላት ጦር ከሁለት ቆራርጦ በመካከሉ ገባና በታተነው ። የማሕዲስቶቹ ጦር አዝማችና አዋጊ የነበረው ራሱ ኦቶማን ዲንካ ተሹሉክልኮ አመለጠ ። ከእርሱም ጋር አንድ መቶ ሃምሳ ያህል ወታደሮች በየአቅጣጫው እየፈረጠጡ ሲያመልጡ ዐሥር ሺህ የሚሆን ሠራዊት ግን ከዚያው ላይ ወድሟል ። ከኢትዮጵያም በኩል እስከ አንድ ሺህ አምስት መቶ የሚገመቱ ሲወድቁ ፣ እስከ አምስት መቶ የሚደርሱ ቆሰሉ ።

አሉላ ራሳቸው ፣ ከጦርነቱ ከመግባታቸው በፊትም በብላታ ገብሩ አዋጊነት ከወደቁት ወታደሮች ጋር ከሠላሳ በላይ የሚሆኑ እጅግ የተመሰገኑ ጀግኖች ከጦርነቱ ላይ ወድቀዋል ። ከእነርሱም መካከል ከብላታ ገብሩ ቀጥለው በአዝማችነትና በአዋጊነት እጅግ ስመ-ጥሩ የነበሩት ሐጎስ ወረታ የተባሉት ጀግና ይገኙበታል ። የማሕዲስቶቹ ግሥገሣ በዚያ ጦርነት ቅስሙ ባይሰበር ኑሮ ምዕራባዊው ቆላ ፣ ከረንና ምፅዋን አካቦ ለመያዝ የማያወላውል ዕቅዱ ነበር ።



ራስ አሉላ ፣ በዚያ ጦርነት ቀድመዋቸው የወደቁትን የታማኝ የጦር አበጋዛቸውን የብላታ ገብሩን አስከሬን አስፈልገው ባያገኙትም ፣ ደማቸውን በመመለሳቸው የኢትዮጵያን ክብር ባለማስደፈራቸው ጽጉራቸውን ሹርባ ተሠርተው ቅቤ ተቀቡ ። በጦርነቱ ሜዳ የወደቀውንም የወገንና የጠላት ወታደር ሬሣ አሰብስበው አስቀብረው ፣ የተማረከ መሣሪያ አስቆጥረው ምርኮኞች አስቀድመው ከኩፊት ቀበሌ ወጥተው ራቅ ካለ ሥፍራ ላይ ሠፈሩ ።

ከኩፊት ጦርነት የተረፈው ሠራዊታቸው በልዩ ልዩ ችግሮች እንዳይጠቃባቸው በጥንቃቄ እየተጓዙ ከረን ደረሱ ። የምሥራቹንም ወደ አጼ ዮሐንስ ፣ “አረመኔውን የድርቡሽን ጦር ድል አድርጌያለሁ” ብለው በጉዞና በሕመም የተዳከመው ሠራዊታቸው በመጠኑ ዕረፍት ካደረገና ቁስለኛውም ሁሉ ማገገም እንደ ጀመረ በብላታ ገብሩ ሞት እጅግ የተከፉትና ያዘኑት ራስ አሉላ ፣ የጦር አለቆቻቸውን ሰብስበው ስለ ጦርነቱና ስለ ወደፊቱም ጠቅላላ ጉዳይ በተወያዩበት ሰዓት ፣

“ልጆቼ ወዳጆቼ!

ኢትዮጵያ በድርቡሽ ጦር እንዳትወድቅ የሚጠብቃት አምላክ ታድጓት ከተዋረድን በኋላ አሳይቶ ግሬን እንጂ የሠራነው ስሕተት ከፍ ያለ ነው ። የድርቡሽን ሠራዊት ብዛት ተመልክተው እንዲነግሩን የላክናቸው ፈረሰኞቻችን ፣ ‘ሦስት ሺህ ብቻ ይሆናል’ ብለው የነገሩንን እንደገና ሳናጣራ ሰተት ብለን ገብተን ብዙ ጀግኖች አለቁብን ። ገብሩም የሰጠሁትን ትእዛዝ ሁሉ ዘንግቶ ቃሌን ጥሶ ሠርቶት የማያውቅ ጥፋት አጥፍቶ ጀግኖቹን ይዞ ጠፋ ። ነፍሳቸውን አምላካችን ይቀበልልን ፣ ተስካራቸውንም እናወጣለን ። ዛሬ ድል ብናደርገውም ድርቡሽ መምጣቱ አይቀርምና ጦር አዘጋጅተን እንደገና ወደ ከሰላ እንዝመት ወይስ ወደ አሥመራ እንመለስ ?በዚህ ጉዳይ የታያችሁን ያመለከታችሁን እንድትነግሩኝ ነው ያስጠራኋችሁ” ብለው ራስ አሉላ ምክር ጠየቁ ።

የጦር አለቆቹና የየቅላው ተጠሪዎች እርስ-በርሳቸው ከተ ነጋገሩበት በኋላ ባሻይ ደባሳ የተባሉ የጦር አለቃ ተነሥተው፣

"ጌታዬ ራስ አሉላ!

ጠላት አገራችንን መመኘት የጀመረው ዛሬ አይደለም "ቱርክም ግብጽም ሞክረዋል ። ድርቡሽም ይኸውና እስከዚህ ድረስ ዘልቆ ገባ ። በዚሁ ይቀራል ማለትም ሞኝነት ነው ። ከሌላው አገር በፊት የቱርክንም ሆነ የግብጽን ግፍ የቀመስነው እኛ ሐማሴ ኖች ነን ። የጠላትን ግፍ የቀመስን በመሆናችንም እነሆ ዛሬም ጉብዛዝቱ ሁሉ ወጥቶ ተዋግቷል ። ከእንግዲህ ወዲያ ጠላት መሬ ታችንን አይረግጣትም ። የሐማሴን ውርደት የመላው የአገር ውርደት ነውና በቶሎ ወደ ከሰላ ዘምተን ከዚያው ላይ ካላቆም ነው እንደገና ደግሞ ወደላይ መዝለቁ አይቀርምና ስንዘምት ይታየኛል" ብለው ተቀመጡ ።

ቀጥለው ሻለቃ አርአያ ተነሡና፣

"ከኩፊት መመለሳችንንም ቢሆን አልወደድኩትም፣ ድርቡሽን ነካ ነው እንጂ አላደቀቅነውም ። ከሰላንስ ዛሬ ከለቀቅነው መች ልን መለሰው ነው? ደግሞም ወደ ከሰላ የምንዘምት ከሆነ እንግሊ ዞችም ቢሆኑ ሳይደግፉን አይቀሩም ። ለዚህ ለዚህ ባንነካው ይሻል ነበር ። አሁን እንግዲህ ብድሩን ለመመለስ ሲል ጓዙን ጠቅልሎ ይመጣና ከቆላው ፀልፎ ወደ ደጋው ማንጋጠጡ የማ ይቀር ነው ። አሁንም ሠራዊታችን ካለፈ ስንቅ ይዞ ጋጅና እን ደገና ወርደን ከሰላን መልሰን በእጃችን ስናስገባ ነው የሚታ የኝ" ብለው ተቀመጡ ።

ፊታውራሪ ኀይለ ሥላሴ ደግሞ ተነሥተው፣

"ጌታዬ ጠላት ከታዛ አስተምሮ በርን ካልጠበቁና ካልዘጉ ዘሎ መግባቱ አይቀርም ። በትላንትናው ጦርነት የሚያስደስት መያ ለሙሉ ሹመትና ሽልማት ሰጥቶ፣ የከዳን ቀጥቶ ጠላት ሳይታጠቅ መድረስ ይገባልና እዚህ ውለን ማደሩ አይታየኝም" ብለው



ቢናገሩ፣ የጦር አለቆቹ እርስ-በርሳቸው ተያዩ ። በዚህ ጊዜ ባሻይ ባራኪ የተባሉ የጦር አለቃ ከአጠገባቸው ወደ ነበሩት ጓደ ኛቸው ዘወር አሉና፣

"ጌታችን እንኳን እንዝመት ብለዋቸው እንዲያውም ጦር ማን ማለት ይቀናቸዋል ። ዛሬን ቢውሉ ነገን አይደግሙትምና መዝ መታችን የማይቀር ስለሆነ ፣ ሌላ ሐሳብ መናገር አያሻ ችም" አሉዋቸው ። ይህችው ሐሳብ ውስጥ ለውስጥ ከተሰሙ ተች በኋላም ፣ "እንዝመት ፣ እንውረድ ፣ እንበለው" የሚለው ሐሳብ እስተጋባ ።

ራስ አሉላ ፣ የሁሉንም ንግግር በጽሞና ሲያዳምጡ ቆዩና ፣ በሐሳብና በትካዜ ተውጠው በዝምታ ተሸብበው ቆዩ ። ብላታ ገብሩ ቢኖሩ ኑሮ ሐሳባቸውን ይናገሩላቸውና ሌላው ሰው ሳይና ገር ነገሩ ያልቅ ነበር ። በዚያች ለት ግን ገብሩ የሉም ። የአሉላን ሐሳብ ተርጉሞ ፍሬ ነገሩን ፍርጥርጥ አድርጎ የሚናገር አልተ ገኘም ። ሁሉም "እንዝመት" አሉ ! ግን ሁሉም ከልባቸው ነበር?

በኩፊት ጦርነት በርካታ ጀግኖች ወድቀዋል ። ከዚያ ሌላ ደግሞ ቀበሌው ሞቃት ነው ፣ ከመስከረምና ከጥቅምት ወራት በኋላ ወንዞች ማግጠጥ ይጀምራሉና ። ወባው ተናዳፊ ነው፣ ስንቅ እንደልብ አይገኝም ። ከደጋውና ከወይና ደጋው ቀበሌ የወረደው ሠራዊት ያን ሁሉ ችግር እስከ መቼ ይችለዋል ! ታዲያ ይህን ሁሉ እያወቁ የጦር አለቆቹ እንዝመት ማለታቸው ከልባቸው ነበር ? ይህን የመሳሰሉትን ጉዳዮች እያነሡ ሲጥሉ ቆዩና ራስ አሉላ የብላታ ገብሩን ቁመና ከፊታቸው ፣ የብላታ ገብሩን ትዝታ ከአእምሮአ ቸው የብላታ ገብሩን ፍቅር ከአንጀታቸው ይፍቅላቸው መስሏ ቸው ፣ ያለ-የሌለ ትንፋሻቸውን ተጫጭነው አሰሙና ፣

"ለማችሁ ወዳጆቼ! ወንድሞቼ!

ሐሳባችሁን ሰማሁት ! ነገራችሁም ከልቤ ገብቷል ። ለጠላት ጊዜ መስጠትና ለትውልድም ማስተላለፍ እንደማይገባ የታመነ ነው ። ድርቡሽ ብድሩን ለመመለስ ብቻም ሳይሆን ኢትዮጵያንም መቆ ምጀቱ የማይቀር ነገር ነው ። ዛሬ ብንገፋውም ነገ ብቅ ማለቱ አይቀርም ። ግን ሌላ አስቸኳይ ጉዳይም አለብን ።

ከሰላ ገብተን የተከበቡትን ጭፍሮቻቸውን ነጻ እንድናወጣቸው እንግሊዞች ይወተውቱናል ። ለነገሩ ግን ለእነርሱ ጉትጎታም ሆነ ውለታ ብለን ሳይሆን ከሰላም ከጃችን ወቶ ውሎ ባያድር ተገቢ በሆነ ነበር ። ግን በባሕሩ በኩል የተፈጠረው አዲስ ነገር ደግሞ በጣም አሳሳቢያችን ነው ። ከከሰላ ይልቅ ምጥዋ ትቀርበናለች ። ከከሰላም ደግሞ ምጥዋ በቅድሚያ ታስፈልገናለች ። የምጥዋ መያዝ በጣም ከንክኖኛል ፤ በገዛ ምድራችን በገዛ ዐፈራችን ፣ በገዛ ባሕራችን ይኸውና ግብጦች ፣ እንግሊዞችና ጣሊያኖች ይሻኮቱበታል ። ይመሳጠራሉ ይናኮራሉ ። እኛ ከሰላ ከወረድንላቸው ደግሞ ምጥዋን ዐልፈው ሐማሴን ላይ ብቅ ይላሉ ፤ ከዚያ በኋላ እነርሱ ደገኞች እኛ ቆለኞች መሆናችን ነው።

ከዚያ በኋላ ከዚህ መቀመጫችን ብቻ ሳይሆን አንገታችን ከተያዘ በኋላ ፣ ድርቡሽም በከሰላ አካባቢ የሚገኙትን ሕዝቦች አስተባብሮ በከበባ ይፈጀናል ። ከዚያ በኋላ ያገራችን ነገር ያለቀለት ይሆናል ። ኢትዮጵያም ከብርቱና አወዛጋቢ ከሆነ ቀንበር ውስጥ ትገባለች ።

ስለዚህ ዛሬ የጨበጥነውን ድል ካገኘን ጉሳዎቻችን ሁሉ ተባብረው የድርቡሾች ደጋፊዎች የሆኑትን እንዲቋቋሙልን ኃላፊ ኃላፊ ሰጥተን ወደ ሐማሴን ብንመለስና በባሕሩ በኩል አዲስ የመጡትን ጣሊያኖች ሐሳብ ብናዳምጥ አይሻልም ይመስላችኋል ?” ሲሉ ያቀረቡትን ሐሳብ የጦር አለቆቹና ባለባቶቹ ከተመካከሩበት በኋላ በሐሳቡ ተስማሙበት ።

ራስ አሉላ ፣ በከረን በአቆርዳትና በምጽዋ በኩል የሚኖሩት ጉሳዎች ተባብረው በድርቡሾች ላይ እንዲነሡ በዐዋጅ ነግረው ሺህ ሙሳኤል ፊሊ የተባሉት የበኒዓምር ተጠሪ የአካባቢው ዋና ሆነው እንዲያስተዳድሩ ሾሙዋቸው ። ከእርሳቸው ቀጥሎም ሺህ አረይ የተባሉት የባርያ ጉሳ ተጠሪ ሆነው ተሾሙ ።

በዚህ ጊዜ ከኢትዮጵያዊነታቸው ዓላማና ስሜት ነቅነቅ ሳይሉ ሲታገሉ የነበሩት ጉሳዎች እየተበራቱ ስለሔዱ ፣ የማሕዲስቶቹ ደጋፊዎች ከነበሩት ጉሳዎች ጋር ግጭት ማስነሣት ጀመሩ። በተንሣውም የእርስ-በርስ ትርምስ ሺህ አሊ ኑሪ የተባሉት የራስ



አሉላ ባለሟል የመንደራቸውን ጀግኖች አሰልፈው ከማሕዲስቶች ደጋፊዎች ጋር ጦርነት ገጠሙና ሼህ አልሐሳምኪን ሼህ መሐመድ አዋድና ሌሎቹንም በርካታ የማሕዲስት ቀንደኞች ማርከው ለራስ አሉላ አቀረቡ ።

ሼሆቹ ኢትዮጵያዊነታቸውን ከደው የማሕዲስቶች ተጠሪዎች ሆነው በሕዝብ ላይ የፈጸሙት ግፍ አመዝኖ በመገኘቱ በስቅላት እንዲቀጡ ተፈረደባቸው ።

ራስ አሉላ ፣ ከኩፊት ጦርነት ተመልሰው ከረን ላይ ሹምሽር ፣ ሽልማትና ቅጣት ሲሰጡ ቆይተው የወታደሮቻቸውንና የራሳቸውን ቁስል ከጠጋገኑ በኋላ ወደ አሥመራ ጉዞ ጀመሩ ። በጥንቱ ዘመን “አርባዕተ-አሥመራ” በሚል መጠሪያ በአራት መንደሮች ተከፋፍላ ነዋሪዎችዋ እርስ-በርሳቸው ሲጋጩባት የነበረችው መንደር የአሉላ መዲና ከሆነች በኋላ ፣ የእርስ-በርሱ ግጭት ቀርቶ አንድነቷንና ልማትዋን የመሠረቱላትን ፣ የማሕዲስቶችን ወራሪ ኃይል እንኩትኩት አድርገው የሰባበሩትን አውራዋንና ሠራዊታቸውን በታላቅ ክብርና ፈንጠዝያ ተቀበለች ።

ቱርክ ባሻ ራስ አሉላ ጉፈሪያቸውን ቀጭን ሹርባ ተሠርተው በቀይ ሻሽ ደገፍ አድርገው ፣ ከግብጽ ጦር አዝማች ማርከው በለበሱት የማዕረግ ልብስ ላይ የአንበሳ ለምድ ደርበው አሽሟጣጭ ጐራዴያቸውን አገንድረው በድንጉላ ፈረስ ላይ ተቀምጠው ግራና ቀኝ ፊትና ኋላ ቁመናው ከስቶ ልቡ እንደ ዳልጋ አንበሳ ባበጠ ሠራዊት ታጅበው ብቅ ሲሉ የአሥመራ ሕዝብ ድብልቅልቅ ባለ የደስታ መንፈስ ተዋጠ ።

መስንቆኛዋም ቀጥሎ ያለችውን ገጸ-በረከት አቀረበ ።

“ከም መንደላይ ተመን ተውርዋሪ
ከም አንበጣ አብ ግድም ሰፋሪ
ከም አንበሳ ብቅልጽም ለባሪ
ሰብአይ ከሰላ ውሽማ ባሕሪ”

ት ር ጉ ም

"እንደ መርዘኛ እባብ ተወርዋሪ
እንደ አንበጣ ግድም ላይ በፋሪ
እንደ አንበሳ ቅልጥም ሰባሪ
ከሰላ ባለቤቱ
ባሕር ዕቁባቱ"

ከመረብ ወንዝ ማዶና ማዶ ሰሙጥር ዘፋኞች መሰንቆኞችና የነበሩ በነቂስ ወጥተው ጉሮሮአቸውን ቀርቶ የመሰንቆቻቸው ጅማቶች እስኪበጣጠሱ አቀባበሉን አድምቀውት ዋሉ። ከብት አረኛው ሁሉ መንጋውን እንዳሰማራ ወደ ሠልፉ እየተሯሯጠ በመሔዱ በአሥመራ አካባቢ የነበረ የእርሻ ሰብል እንደዚያ ዕለት የከብት ሲሳይ ሆኖ አያውቅም ነበር ።

እንጀራው ከምንነው ቂጣውና ጥራጥሬው ከምጣድ ሳይላቀቅ፣ ከወንጠፍቱ ላይ ድፍድፉ እንደተቆለለ፣ እንዝርቱ ከነጥጡ እየተወረወረ፣ ቡናው እንደ ተንተከተከ፣ ሊጡ እንደ ተከፈተ ቤቱ ዕልል ዕልል እያለ ሲወጣ በሕይወት የተመለሰ ዘማች ዘመድ ቀርቶ የማያውቀው ሁሉ እያቀፈ ሲስመው፣ ዘመዳቸውን ያጡ ቢላቀሱ ከዚያ በፊት በአሥመራ መንደር ያልታየና ያልተሰማ ትርምስ ሆነ ።

ራስ አሉላ ከነሠራዊታቸው ሕዝቡ ወደ አዘጋጀላቸው ዳስ ገቡ ። ሕዝቡ በየቡድን በየቡድን እየተመደበ ሲዘፍን የሊቀ መኳሶች ሊቀ መኳስ የተባሉትና በጉንደር ከተማ በዘመኑ የተመሰገኑት ሊቀ መኳስ ስጦታው የኩፊትን ጦርነት ውጤት እንደ ሰሙ ከአክሱም ወደ አሥመራ ሔደው ነበርና ከራሶች ራስ ፊት ቀርበው፣

"ድርቡሽ ገባ ሲባል ሾልኮ በቀዳዳ
አሉላ የሚሉት ወረደበት ናዳ

"መጣሁ" ብሎ ላከ ድርቡሽ ከከሰላ
ተቀበለው ወርዶ አባ ነጋ አሉላ



ምነው ባጠየቀው ግብጡን በጸንጸው
ጉራዕ ድረስ ገብቶ ምን እንዳገኘው !

ድርቡሽ አልጠየቀም ?አልሰማም ወይ ወሬ
ግብጡ መግቢያ ሲያጣ ባሉላ ጉፈሬ

ኩፊት ላይ የታየው ያሉላ ጉራዴ
ያገሬ መከታ የኔ ጋሻ ከንዴ"

ብለው ሲያንጉራጉሩ፣ የራስ አሉላ የልፍኝ አሽከር ቀረብ ብሎ በከረጢት የታሰረ ብር አሸከማቸው ። ዘፈኑ ቀረርቶው፣ ፉከራው፣ ዕልልታው ሳያቋርጥ ከሳምንት በላይ ሲያስተጋባ ሰነበተ። ራስ አሉላም በዚያ ሕዝባዊ ዳስ እየተገኙ ግብር ሲያበሉ ግዳይ እየተቀበሉ ሲሸልሙ፣ ከድቶ የተያዘውንና የሸሸውን ሲቀጡ ሰነበቱ ። ወደ አጼ ዮሐንስ የላኩት የምሥራችም መልሱ በዚያ ሰሞን መጣላቸው ።

"ልጄ ወዳጄ ቱርክ ባሻ ራስ አሉላ

የላክህልኝ የምሥራች በደረሰኝ ጊዜ ሰውነቴን ደስታ ወረረው። በጉልበቱና በመግሪያው ተመክቶ የመጣብህን አረመኔ ድል ንሥተህና አሳፍረህ እንኳን በደኅና ገባህ ፤ ለሀገራቸው ሲሉ በጦርነቱ ለሞቱት ጀግኖች ተዝካራቸው እንዲወጣ የሚቻለውን ነገር ሁሉ እልክልሃለሁ ። እግዚአብሔር ከንድህን ያበርታልህ" ይላል መልእክቱ ።

የኩፊት ጦርነት የአሉላን ማንነትና የጦር ስልት ችሎታ አመዛዛኝነት፣ ታጋሽነትና ታላቅነት ያስመሰከረ ሆነ ።ይህን የተገነዘቡት እንግሊዞችና ግብጾች የአሉላን ወዳጅነት በኢጣሊያኖች ላለመለወጥ መጠንቀቅ ጀመሩ ። የአሉላን ፊት ወደ ከሰላ አዙረው ጣሊያኖችን ወደ ሐማሴን ለማስገባት ያደረጉት ተንኮል የተደረሰበት እንደሆነ ከምሥራቃዊው ሱዳን እየፈለሱ በከረን በኩል ወደ ምፅዋ ሲጓዙ ለነበሩት ግብጻውያን እጅግ አስከፊና አስቸጋሪ ጉዳይ ሊደርስባቸው እንደሚችል ስለ አመኑበት ባለፈው ጊዜ ስለፈጸሙት ተንኮል ልባዊ ይቅርታቸውን ለማግ

ኘት መጣጣር ጀመሩ ። በስዚህ ኢጣሊያኖች በነበሩበት እንዲቆዩ እንጂ ወደፊት እንዳይራመዱ ማገባበት የእንግሊዞችና ግብጾች ዋናው ተግባራቸው ሆነ ። ራስ አሉላም ምንም እንኳን እንግሊዞች እርሳቸውን መሣሪያ አድርገው ማሕዲስቶችን ለማስደብደብ ያደረጉትን ጥረት ቢረዱትም ፥ የወዳጅነታቸውን ገጸ-ፈገግታ አላዞሩባቸውም ። እንዲያውም የእንግሊዞችን ባሕርይና ስልት በሚገባ ለማጥናት የቻሉት ከዚያ ወዲህ ሆነ። በዚያን ጊዜ የነበረውን ሁኔታና በእንግሊዞችም ላይ አድሮባቸው የነበረውን ቅሬታ ፍጻሜ ሕይወታቸው በተቃረበበት ወቅት ዋይልድ ለተባለው እንግሊዛዊ ሲያጫውቱት ፥ “እስቲ አንድ ነገር ልጠይቅህ !ስለምንድን ነው የድሮ ወዳጆቻችሁን ችላ እምትሉት ? እንግሊዝ አድሚራል ሒዊትን ልካ ያደረግነውን ስምምነት ሁሉ ገሸሽ አድርጋ ፥ ከጣሊያን ጋር ተመሳጥራ ፥ አገሬን ስትሰጥ ትንሽም ቅር አላላትም ? ይህን ምን ትርጉም ትሰጠዋለህ ? ምንስ ማለቷ ነው ? እንግሊዝ የገባችውን ውል አታከብርም?” ብለው ተቀምጠውበት ከነበረው ድንክ አልጋ በትራሱ በኩል ተጠቅልሎ ተቀምጦ የነበረ ወረቀት አወጡና ፥ ንግግራቸውን በመቀጠል ፥

“ይህ ውል ዛሬም ድረስ በእናንተም ዘንድ ይገኛል ፤ ለመሆኑስ ውል ብቻ ማስቀመጡስ ምን ይሠራል ? እስቲ በመጀመሪያ የተጻፈውን ቃል ተመልከተው ? ምጥዋን አሳልፋችሁ ለጣሊያኖች በመስጠታችሁ ንጉሠ ነገሥቱ በዚያ በኩል መሣሪያ ለማስገባት የማይቻላቸው ሆነ ። ይህን ማድረግ ይገባችሁ ነበር ? በውላችንስ መሠረት እኔ ግብጾችን ከበጐስ እውጥቼ ምጥዋ አላደረስኩላችሁም ? ምንም እንኳ ለሀገሬ ስል ቢሆን ወደ ቆላው ዘምቼ አልተዋጋሁም ? የዚያስ ጦርነት ውጤት እናንተን አልጠቀመም? እናንተ የምትፈልጉትን ከሠራንላችሁ በኋላ እኛን ገሸሽ አድርጋችሁ ወደ ወገኖቻችሁ ዘወር አላላችሁም ? ከገባችሁት ውል የፈጸማችሁት ነገር ቢኖር ጳጳስ መላክ ብቻ ሆኖ ቀረ ? በእርግጥስ ዋናው ፍላጐታችንና ችግራችንስ ይህ ብቻ ነበር ? እስቲ አንተ መልስልኝ?” ብለው አፋጠጡት ።



“መቼም ስሕተት ተፈጽሟል ። ባለሥልጣኖቻችን በልዩ ልዩ ምክንያቶች የተነሣ ችግር ፈጥረዋል” አለ አንገቱን አቀርቅሮ ዐይኖቹን እያስለመለመ ።

“ስሕተት አይደለም፥ ክዳት ነው!” አሉ አሉላም ቆጣ ብለው።

“መቼም ያሳዝናል፤እንደ ተመለስኩ ሁኔታውን ለባለሥልጣኖች ለማስረዳት እሞክራለሁ” አለ ዋይልድም እጅግ ግር ብሎት።

“ሳያውቁት ቀሩ ብለህ ነው? ልባቸው ቢከዳኝ ነው እንጂ! ግዴለም ትውልድ ይፈርዳል!” ብለው አሰናበቱት ።

# አሉላ አሥመራና ምፅዋ

ራስ አሉላ፣ዋና ከተማቸውን ከአዲ ተክላይ ወደ አሥመራ ካዛወሩበት ምክንያቶች አንዱም ከባሕሩ በኩል ወደላይ የሚወጣውን ጠላት ለመከላከል ብቻም ሳይሆን፣ከእርሻ ገቢ ብቻ በሚገኝ ገቢ ለማስተዳደር የከበዳቸውን ሠራዊታቸውን ከንግድና ቀረጥም በሚገኝ ገቢ ለመደጎም ሲሉ ነበር። በአራት አነስተኛ መንደሮች ተከፋፍላ የነበረችው አሥመራ በ1876 ላይ የአሉላ መዲና ከመሆኑዋ ከሃምሳ ዓመታት ቀደም ብላም እንደ ዚያው እንደ ተበታተነች መጠነኛ የንግድ እንቅስቃሴ ነበራት። የአራቱ መንደሮች ቁርቁራ ግን እጅግ ራቅ ያለ ነው። ከሃምሳ ዓመታት በፊት ግእነዚያ መንደሮች ከሦስት መቶ የማይበልጡ ቤቶችና ወደ ሁለት ሺህ የሚጠጉ ነዋሪዎች እንደ ነበሩዋት ይተረከላታል።

አሥመራና ምፅዋ በንግድ ገመድ እንዲተሳሰሩላቸው በአይሉትና በሰሐጢ አካባቢ የነበሩትን ሽፍቶች ማጥፋት ብቻም ሳይሆን የአሥመራ ከተማ እንድትሻሻልና በሥርዓት እንድትመራ ለማድረግ ሲሉ፣በመጀመሪያ ነጋድራስ ብርሃኑ ሐጎስ የተባሉትን የሸዊአተ አንበሳ ተወላጅ ሾሙላት።

ራስ አሉላ በሃይማኖታቸው ጽኑ ክርስቲያን እንደ ነበሩ የማያጠራጥር ቢሆንም፣የእስልምናን ሃይማኖት በማክበር ረገድ ደግሞ ከንጉሠ ነገሥቱ የተለዩ ነበሩ። አጼ ዮሐንስ እስላሞች ክርስትና ካልተነሡ ካገር እንዲወጡ ኢትዮጵያም የክርስትና ሃይማኖት የሚከተሉ ብቻ እንዲኖሩባት ዐዋጅ ሲያወጡና ዐዋጃቸውንም በሥራ ላይ ለማዋል ያን ሁሉ ጥረት ሲያደርጉ፣የራስ አሉላ አስተሳሰብ ደግሞ ከዚህ የተለየ ነበር። የራስ አሉላ ትልቁ ጥረትና ፍላጎት በንግድ ጉዳይ ላይ ያረፈ በመሆኑ፣በጸዋታቸው መታወክ



የተነሣ ሲንከራተቱ የነበሩትን የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች፣ አሥመራ እየገቡ እንዲሠፍሩ ቦታ በመስጠት በንግድ ሥራው እንዲሠማሩ በማበረታታት ይደግፏቸው ስለ ነበረ፣ በተቀናቃኞቻቸው ዘንድ 'የክርስቲያኖች ጠላት' እያሉ ያስወሩባቸው ጀመር። እርሳቸው ግን ለተቀናቃኞቻቸው ስብከት ሳይሸበሩበት እምነታቸውን በልባቸው ይዘው ሥራቸውን ቀጠሉ። ከመረብ ወንዝ ማዶ የነበሩት የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮችም በራስ አሉላ ላይ ልባዊ እምነትና አክብሮት ስለ አደረባቸው በንግዱ ሥራ በሙሉ ፈቃደኝነት ተሳታፊዎች ሆኑ። የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በአሉላ ላይ ያሳዩትን እምነት ራሳቸው አሉላም ስለ ተረዱላቸው፣የንግዱ እንቅስቃሴ በአስተማማኝ ይዞታ እንዲቀላጠፍ ስለ አመኑበት የኪንዳዕ መንደር እንዲስፋፋ መንገዱ እንዲጠረግና እንዲሻሻል፣ዱሩ እንዲመነጠር ለመንገደኞች አስቸጋሪዎች የነበሩት እንደ አንበሳና ነብር የመሳሰሉት አራዊት እንዲታደኑ አደረጉ።

ራስ አሉላ፣በመረብ ምላሽ ግዛታቸው የርስት ጉልት ሥርዓት መሥርተው በውትድርናው ግዳጅ የተሰለፉ ሁሉ እንዲተዳደሩበት ለማድረግ ያወጡት ዐዋጅ እምብዛም ውጤት የማይሰጣቸውና ሕዝቡም ያልወደደላቸው መሆኑን ከተገነዘቡት በኋላ፣ በንግድ በቀረጥና በግብር ከሚገኘው ገቢ ወታደሮቻቸውን ለማስተዳደር የወር ደመወዝ ለመስጠት ወሰኑ።

በተለይ ከመረብ ወንዝ ወዲህ ማለትም ከትግራይ አብረዋቸው ለሔዱ በየጦርነቱ ሊዋደቁ ለነበሩ ከሁለት ሺህ በላይ ለሚሆኑ ወታደሮቻቸው መተዳደሪያ መስጠት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን አመኑበት። ያመቸውንና የተቻለውንም ያህል በእርሻ ሥራ እያረሱና እያሳረሱ እንዲተዳደሩላቸው ለማድረግም ጥረት አድርገውላቸዋል። ቢሆንም በቂና አስተማማኝ ሆኖ አላገኙትም። እርሳቸውን አምነው ተከትለዋቸው የሔዱትም ቢሆን እንደገና ወደ ትግራይ ለመመለስ ከባሰ የኑሮ አረንቋ ውስጥ ለመዘፈቅ አይችሉም ነበር። በየአገር ቤቱ ተበትኖ የሚኖርና በጦርነት ሰዓት ብቻ በክተት የሚጠራ ሠራዊትም አስተማማኝ ሊሆን እንደማይችል የተረዱት አሉላ፣ቀዋሚ የሆነና በደመወዝ የሚተዳደር ወታደር አስፈላጊ መሆኑን አምነውበታል። እንደ

ዚያ የሆነ በአጠገባቸው በቀዋሚነት የሚሠፍር ተወርዋሪ ጦር
ክፍላቸው ደግሞ የግዛታቸውን ጸጥታ ለመጠበቅና በተለይም
የአሥመራ - ምፅዋን የንግድ መሥመር አስተማማኝ ለማድረግ
እንደማይችሉ ተማምነውበታል ።

በዚህ መሠረት ለመጀመሪያ ጊዜ ከአንድ ሺህ የማይበ
ልጡ ቀዋሚ ወታደሮች በወር አንዳንድ ኲንታል ጤፍና በዓ
መት ደግሞ አምስት አምስት የማሪትሬዛ ብር ደመወዝ መከፈል
ጀመሩ።የቀዋሚው ወታደራቸው ቁጥር እየበዛ መሔድ ሲጀ
ምር ደግሞ ደመወዙ የማይበቃው እየሆነ በመቸገሩ በእርሻ ከሚ
ገኝ ገቢ መደጐምም አስፈላጊያቸው ሆነ ።

በአሥመራ ከተማ በምትገኘው ኮረብታ ላይ ሦስት አዳራ
ሾች ለራሳቸው ከአሠሩ በኋላ በዙሪያቸው ደግሞ ለሁለት ሺህ
ቀዋሚ ወታደሮች መኖሪያና ከዐሥር ሺህ በላይ ለሚሆኑ
ወታደሮች ደግሞ ጊዜያዊ መሥፈሪያ የሚሆኑ ቤቶች አሠሩ ።

በኮረብታዋ ላይ ከተሠሩት ሦስት ታላላቅ አዳራሾች ትልቁ
የግብርና የምክር ቤት ፣ ሁለተኛው የእንግዳ መቀበያ ፣ ሦስትኛው
ራሳቸው የራስ አሉላ መኖሪያ ቤቶች ነበሩ ። ከዚያ በኋላ ለመ
ረብ ምላሽ ግዛት በመዲናነት ደምቀው የኖሩት እነ-ድባርዋ ፣
ፀአዘጋና ሐዘጋ የተባሉት መንደሮች ጊዜያቸው እያለፈ ድምቀ
ታቸው እየቀዘቀዘ ሔደ ። የራስ አሉላ የቅርብ አማካሪዎችና
ባለሟሎች የነበሩትና ከትግራይ አብረዋቸው የሔዱት እነብላታ
ገብሩ አባጭቁን ፣ እነደጃዝማች እንግዳ ፣ እነደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ
እነቫለቃ አርአያ ፣ እነ ልጅ ፈንታ ፣ እነ ባሻይ ተድላ (ወዲ ባሻ
ፈንታ) እነባሻይ ተድላ (ወዲ ምላሉ) እነባሻይ መርሻ ፣ እነባሻይ
ደስታ አባጋዲ ፣ እነባሻይ አስረበላ እና ሌሎችም በራስ አሉላ
ዙሪያ ቤት እየተሠራላቸው ከተሰባሰቡ በኋላ ከመረብ ምላሽ ተወ
ላጆች ከነባሕረ-ነጋሲ ጕደፋ ፣ ከነባሻይ ብኩሩ ፣ ከነዘጊየርጊስ
ጊላ ጊዮርጊስ ፣ ከነገብረማርያም ዘካርያስ ፣ ከነተስፋ ጽዮን አልመ
ዶም ፣ ከነከንቲባ አዲ-አድስግዶ ፣ ከነፍሬሆሐንስ ፣ ከነከንቲባ በሂት
ተወልደመድኅን ፣ ከነከንቲባ ሐጐስ ፣ ከነደጃች ኃይሉ አበራ ፣ ከነ
ሐድገንበስግልበት ፣ ከነመንገሻ አስገዶምና ከሌሎቹም መኳንንቶች
ጋር እጅግ የሚያስደስት ወንድማማችነት መሥርተው ጠላት



የሚያሟሽሽ አንድነት አጽንተው 'አንተ-ትብስ ፣ አንተ-ትብስ'
ተባብለው ሕዝቡና አስተዳደሩ የሚቀራረቡበትንና የሚተማመ
ኑበትን ስልት እየቀየሱ አሉላን እንደ ወንድማቸው ቆጥረው ፍቅ
ራቸውንና እምነታቸውን ሳይቀንሱ የመረብ ምላሽ ግዛት አስተ
ተዳደርና ጸጥታ አስተማማኝ አድርገውት ኖሩ ።

ራስ አሉላ ፣ በመረብ ምላሽ ግዛታቸው ጉዳይ እነዚሁ የጦር
አለቆች ባለሟሎችና ባለባቶች እየመከሩበት እንዲመራ በማድ
ረጋቸው የመረብ ምላሽን ሕዝብ ለማስተባበር አንድነቱና ጸጥ
ታው እንዲጠበቅ ለማድረግ ቻሉ ። በግዛታቸው ውስጥ የሚሾ
ሙት ሹሞች ጕልት ወይም ጭቃ ሹም እየተባሉ ይመደቡ
የነበሩትንም ሆነ ምስለኔዎቹን ራሳቸው ራስ አሉላ በቅርብ የሚ
ከታተሉትበና የሚቆጣጠሩበት ስልትም ነበራቸው ።በቅርብ የሚያ
ውቋቸውንና የሚያምኑዋቸውን እየመረጡ በየቀበሌው እየተዘ
ዋወሩ አስተዳዳሪዎቹን የሚቆጣጠሩላቸውና ግብርም የሚያስገቡ
ላቸው፣ መልእክትም የሚያስተላልፉላቸው ፈረሰኞች ነበሩዋቸው።

አስተዳደራቸውን ይመሩትና ይቆጣጠሩት የነበሩት የሕዝ
ቡንም የዕለት ተዕለት ጉዳይ ይከታተሉ የነበሩት እንደዚያ
የመሰለ የአስተዳደር መዋቅር ከዘረጉ በኋላ ነበር ። የመረብ
ምላሽ ሕዝብም ከፍቅሩና ከጽኑ እምነቱ የተነሣ ፣

"ጽድቅ እንደላሊበላ
ፍርድ እንደ አሉላ"

እያለ ያሞግሳቸው ጀመር ።

ራስ አሉላ የሕዝባቸው አስተዳደር በሥነ-ሥርዓት የሚመ
ራና ፍትሕ እንዳይጓደልበት የሚከታተሉትና የሚቆጣጠሩት በፈ
ረሰኞቻቸው ብቻ አልነበረም ። ከአጥር ግቢያቸው በስተውጭ
በኩል ከረጅም ገመድ ጋር የተያያዘ ደወል ነበራቸው ። የደወሉ
ገመድም ከካቡ ላይ የተንጠለጠለ ነበረ ። ራሱ ደወሉ የተንጠ
ለጠለው ደግሞ ከእልፍኛቸው በራፍ ላይ ነበር ። ፍትሕ የተጓደ
ለበት ሁሉ 'ፍርድ ተጓደለ ፣ ድሀ ተበደለ' የሚል ባለጉዳይ ከግ
ቢው ውጪ ሆኖ ገመዱን ሲነካው ደወሉ ይንቃጨላል ። በዚህ ጊዜ
ራሳቸው የቤት ልጅ ይልኩና ደዋዩን አስቀርበው ይጠይቁታል ።

ራስ አሉላ አሥመራን የአስተዳደር ፣ የጦር ፣ የንግድና የኢኮኖሚ ጠቅላይ ሠፈራቸው ከማድረጋቸው በፊት በመረብ ምላሽ የታወቁትን የፀአጋን ፣ የንጉደፈላሲንና የአዳጋ-ሐሙስን ገበያዎች አስዘግተው በአሥመራ ብቻ ገበያ እንዲከፈትና በሹም እንዲስተዳደር አደረጉ ። ከዚያ በፊት ግን በግዛታቸው ውስጥ በነበሩበት ገበያዎች ሥርዓትም ሆነ ቀረጥ አልነበረም ።

በአሥመራ ገበያ "ሹም አዳጋ" ከተከፈተበት በኋላ ቀረጥ እንዲሰበሰብና በሥርዓትም እንዲመራ በማድረጋቸው ፣ የባሕር ግዶ ሸቀጣ-ሸቀጥ በአሥመራ ከተማ በብዛት መግባት ጀመረ ። ቀረጡም እያደገ መጣ ።

ለምሳሌ ፣ አንድ ነጋዴ በበቅሎ ሁለት ብር ፣ አንድ ገበሬ ደግሞ በጥማድ ዐሥር ብርና ከአዝመራው ሲሶ እህል በዓመት ይከፍል ነበር ። የቀረጡንና የግብሩን አከፋፈል ያሳደጉበትም ዋናው ምክንያት ወታደሮቻቸውን በደመወዝ ለማስተዳደር ብቻ ሳይሆን ራሳቸውም ለማዕከላዊ መንግሥት በዓመት የሚያስገቡት ገቢ ስለ ጨመረላቸው ነበር ።

ለማስረጃም ያህል ፣ ከ1871—1872—1881— 1882 ድረስ አንድ መቶ ሃምሳ አምስት ሺህ ብር ግብር ለማዕከላዊው መንግሥት ከፍለዋል ። ከእርሳቸው በፊት ግን ይከፈል የነበረው በዓመት አምስት ከፍ ቢልም ስድስት ሺህ ብር ብቻ ነበር ። ራስ አሉላ የምዕራባዊውን ቆላ ግዛታቸውን ጸጥታ በሚገባ አረጋግተው አስተዳደሩንም በሚገባ መያዝ ስለቻሉ የሐባብ ፣ የበጐስ የማርያ የበኒዓምር ወረዳዎች ግብራቸውን ያለምንም ችግር ማስገባት በመቻላቸው የመረብ ምላሽ ግብር ገቢ ለአሉላም ሆነ ለአጼ ዮሐንስ ጉልበት ማጠናከሪያ ድጋፍ ለመሆን በቅቷል ።

ራስ አሉላ ፣ እንደዚያ አድርገው በጥንቲቱ የመረብ ምላሽ በዛሬዋ ኤርትራ እጅግ አስተማማኝ የነበረ የአስተዳደር መዋቅርና የንግድ መሥመርም ዘርግተው ፣ ሕዝቡ ጸጥታውን ራሱ ተቆጣጥሮ አንድነቱን አጠንክሮ እንዲመራ በማድረጋቸው ፣ በዳርና ዳር አስፍስፈው የነበሩትን ባዕዳን ቅስም ለመስበር ችለዋል ።



# አሉላና ኢጣሊያኖች

"ፈረንጅና ቁንቁን አንድ ናቸው ።"

ከጀግንነት ጋር ማስተዋልና አርቆ መመልከት የባሕርይ ገንዘባቸው የነበሩት ታላቁ አፍሪቃዊ ጀኔራል ባንድ ጊዜ በሁለት ግንባር ጦርነት ለመግጠም የማይቻላቸው መሆኑን ተረድተው በባሕሩ በኩል ብቅ ያለውን አዞ አስገዝበው በምዕራብ በኩል አስገምግሞ ወደ መጣባቸው የማሕዲ ወፈፌ ፊታቸውን አዞሩ ። በዚያም ያገኙት ድል ለጠላቶቻቸው ራት ሆነ ። ከዚያ ድል በኋላም ደግሞ ዐይኑ-ሕሊናቸውን ወደ ባሕሩ አካባቢ መወርወር ጀመሩ።

ጣሊያኖች ምፅዋ ከመሥፈራቸው በፊት ስለራስ አሉላ ሁኔታ ለማጥናት ባደረጉት ጥረት ባአንድ ሐቅ ላይ ደርሰው ነበር ። ያም ሐቅ እንዲህ የሚል ነበር ።

"በዛሬይቱ አቢሲኒያ ምዕራፍ ውስጥ አሉላ የሚባለው ሰውዬ ቁምነገረኛ ፣ ጠንቃቃ ፣ ተሰሚነት ያለውና ቀጥተኛ ሰው መሆኑን አረጋግጠናል ። በንጉሡ ዘንድ ያለው ተሰሚነትና ተቀባይነትም ከሁሉም ያመዘነ ነው ። እርሱ የተስማማበት ከሆነ በንጉሡ ዘንድም ተፈጻሚነት አለው ። አሉላ 'ይሁን' ካለ የማይሆን ምንም ነገር የለም ። ይህ ብርቱና ከባድ ሰውዬ የአብሲኒያ ጠረፍ ኃላፊ እንደመሆኑ መጠን ፣ እኛም መተዋወቅ የማያቋርጥም ወዳጅነትና ንግግር ማድረግ ያለብን ከእርሱ ጋር መሆን ይኖርበታል። የእርሱን ወዳጅነት ለማግኘት ስንልም ማንኛውንም ነገር ሁሉ መፈጸም ይገባናል ።"

ይሆን እውነት የተገነዘቡት ኢጣሊያኖች መልሰው ችላ ለማለትና ለመናቅም ደረሱ ። በመጋቢትና በሚያዝያ ወራት በ1877

ላይ የግብጽ ወታደሮች በለቀቁባቸው ቦታዎች ላይ ሰመሥፈርና ከራስ አሉላ ተቃዋሚዎች ከነበሩት ጋር ምሥጢራዊ ሤራ በመጀመራቸው እምነውበትና ፈልገውትም የነበሩትም የ"አሉላን ወዳጅነት" አሻከረባቸው ።

በተለይም የራስ አሉላ የመረረ ጠላት የነበረው ደበበ አርአያ ፣ የኢጣሊያ ወታደሮች ሠፍረውበት በነበረችው ሕርጊጐ በምትባለው መንደር ከናይቡ ቤት ተቀምጦ ይሠራው የነበረውን ወንጀል እንዲገፋበት ኢጣሊያኖችም መሣሪያና ሌላም ርዳታ ሲሰጡት እንደነበረ አሉላ ሰሙ ። እርሱም በኢጣሊያኖች ድጋፍና "አይዞህ" ባይነት ተደፋፍሮ ወንበዴዎች ሰብስቦ ከሕርጊጐ ወጥቶ ወደላይ ወጣና አሣውርታ ውስጥ ገብቶ በርካታ ወንበዴዎች መልምሎ ከአሥመራ ወደ ምፅዋ የሚመላለሱትን ነጋዴዎች መዝረፍ መጀመሩን አሉላ ሰምተው ከአሥመራ ተንደርድረው ሲወርዱበት ከመሸገበት ወጥቶ ፣ ፈርጥጦ ከጣሊያኖች ጉያ ገባ ። እርሳቸውም የእርሱና የማሕዲስቶች ደጋፊዎች የነበሩትን የተወሰኑ አሣውርታዎች ቀጥተው ወደ አሥመራ ተመለሱ ።

የኢጣሊያ ወታደሮች አለቃ የነበረው ኰሎኔል ማሴታም አድራጐታቸውን በመቃወም ፣ እንደዚደ የመሰለ ርምጃ ቢወስዱ ግን በምፅዋ በኩል የሚያስገቡትን የጦር መሣሪያ ሁሉ እንደሚያግድባቸው መልእክተኛ ሰደደ ።

ራስ አሉላ ግን "በኛ ጉዳይ እርሱን ምን አገባው?" ብለው ችላ አሉት ። ማሴታ ከዚያ አከታትሎ ደግሞ ፣ "በሚመጣው ክረምት ለወታደሮች መጠለያ የሚሆኑኝ ቤቶች ሰሐጢ ላይ ለመሥራት ስለአሰብኩ ይፍቀዱልኝ" ብሎ ድጋሚ ላከባቸው። እርሳቸው ግን በሰጡት መልስ ፣

"ከዚህም በፊት ይህን ነገር ጠይቀኸኝ የማይሆን መሆኑን አሳውቄህ ነበር ። ዛሬም አይሆንም ፤ መሬቱ ግዛትነቱ የንጉሠ ነገሥቱ ስለሆነ በአስቸኳይ እንድትለቁ ይሁን" ብለውታል ።

ኰሎኔል ማሴታ ፣ ሰሐጢ ላይ ቤት ቢሠራና ወታደሮች ቢያሠፍር አሉላ በዝምታ እንደማይመለከቱትና ከኩፊት የተመለ



ሰውን ዱላቸውን እንደሚያሣርፉበት ተረድቶ ፣ በነበረበት መቆየቱ እንደሚሻልና የእርሳቸውን ተቃዋሚዎች እየሰበሰበ ማሳደሙና እርሳቸውን ማበሳጨቱ እንደሚሻለው አመነበት ።

በዚያ ላይ እንዳለ የማሕዲስቶች ዋና ተጠሪና ተላላኪያቸውም የነበረው ባላምባራስ ክፍለየሱስ ወደ ምፅዋ ሔደና ከማሴታ ጋር ተገናኝቶ ሲነጋገሩ ፣

"አሉላን እኔም ሆንኩ እናንተ ብቻችንን አንችለውምና በአንድነት ብንነሣበት ይሻላል" ሲል ሐሳብ አቀረበ ።

"እኛ እንኳን ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር እንዳያጋጨን አሰበን ነው እንጂ የአሉላ ጉልበት የሚያቅተን አይደለም" አለ ኰሎኔል ማሴታ ።

"ለማናቸውም ቢሆን አሉላን ከዚህ ማስነሣት ይሻላል" አለው ባላምባራሱ ።

"በምን ዐይነት ዘዴ ?" አለ ኰሎኔሉ ።

"ነገሩን ካሰባችሁበትና ለኔ ርዳታ ካደረጋችሁልኝ በቀላሉ ከአጼ ዮሐንስ ጋር ማጋጨትና ማስነሣት ይቻላል" አለ ባላምባራበ ።

"በኛ በኩል የሚቻለውን ሁሉ እናደርጋለን ። ግን አሉላን አንሥተው የባሰ ሰው የላኩብን እንደሆንስ ?" አለ ጣሊያኑ ።

"ይመኑኝ ጌታዬ እንደ አሉላ ያለ ብርቱ ሰው የላቸውም ፤ ቢሆንም አሉላ እንደ ተነሡ ፣ እናንተ ፈጥናችሁ ወደ ንጉሡ ትልኩና የዚሁ የሐማሴን ተወላጅ የሆነ ሰው ቢሾም ይሻላል ብላችሁ መልእክተኛና ገጸ-በረከት ትሰዳላችሁ ። እኔም 'ምሕረት ይደረግልኝና አገሩም ይሰጠኝ' ብዬ ገጸ-በረከትም አስይዤ እልክባቸዋለሁ " አለ ክፍለ የሱስ ።

"የሃይማኖትና የባላባቶችንስ ድጋፍ እንዴት ሊያገኙ ይችላሉ?" አለ ኰሎኔል ማሴታ አዲስ የቀረበለት ሐሳብ ግቡን መትቶለት በክፍለየሱስ ላይ ተጭኖ አሥመራን ሲይዝ በሐሳቡ እየታየውና በፈገግታ ተውጦ ።

“ለዚህ እያስቡ ገዱለዎትም ። የአሉላ ተቃዋሚዎች የሆኑትን ቀርቶ ደጋፊዎቹን እንኳ ወደዚህ አምጥቼ ከእርስዎ ጋር እንዲገናኙና እንዲስማሙ ለማድረግ እችላለሁ” አለ ክፍል የሱስ ።

“ይህን ማድረግ ከቻሉማ በኛ በኩል አስፈላጊያ የሆነውን ነገር ሁሉ እንዲሟላልዎ እናደርጋለን ። እርስዎም የሀገርዎ ገዥ ሆነው ከተሾሙልን ከአሉላ የበለጠ ሠራዊትና መሣሪያ እንዲኖረዎ ለማድረግ እንችላለን” አለ ጣሊያኑ በጉጉት እየተመለከተው ።

የሤራው ጅማሬ በዚሁ አለቀና ፣ ባላምባራስ ክፍል የሱስም ወደ ሐባብ ሔዶ ስብከቱን ጀመረ ። በስብከቱም እነክንቲባ ሐሚድ እነሼህ ሐሰን ሐዳድና ሌሎቹም የጎሳና የሃይማኖት ተጠሪዎች ገቡስትና ሰብስቦ ወደ ምፅዋ ይዞአቸው ሔደ ፣ ከኮሎኔል ማሴታ ዘንድ አቀረባቸው ።

“የእናንተ ፈቃድ ከሆነ አሉላን ማሻርና ባላምባራስን ማሾም እንችላለን ። እስከዚያው ድረስም የአሉላ ወታደሮች እንዳይደርሱባችሁ የኛ ወታደሮች ሊጠብቁዋችሁ ይችላሉ ። ብቻ በመጀመሪያ የእናንተን ፈቃድና ፊርማ ማግኘት ይኖርብናል” አለ ኮሎኔል ማሴታ ፣ ከመንደራቸው ተነድተው ከፊቱ የተቀመጡትን በክፍል የሱስ የማረካቸውን የዋሆች ስብከት አንድ ባንድ እየተመለከተ ።

“የጌታ የባላምባራስም ሆነ የእርስዎ የጌታችን ሐሳብ ይስማማናል ። ለአሉላ ከመገበር ለእርስዎ ብንሰጥ እንወዳለን ። የአሉላ ወታደሮችም እንዳይመጡብን እርስዎ እንዲያስጠብቁን እንፈቅዳለን” አሉት ከንቲባ ሐሚድ ከተቀመጡበት ተነሥተው ።

በዚሁ ሐሳብ ከስምምነት ላይ ደረሱና የሃይማኖትና የጎሳ ተጠሪዎቹ ፣ “የኢጣሊያ ወታደሮች እንዲጠብቁን እንወዳለን” ብለው ፈረሙ ። ከዚያም በኋላ ለእያንዳንዳቸው ገንዘብ ጠመንጃና ልዩ ልዩ ሽልማት ከጣሊያኑ ኮሎኔል እጅ ተቀብለው ወደየወረዳቸው ተመለሱ ።



ሤራውን አሉላ እንደ ሰሙ እጅግ ተቆጡ ። ኮሎኔል ማሴታ ግን ሤራውን ያልደረሱበት መስሎት እርሳቸውንም ለማታለል ፈለገና ፣

“በኩፊት ጦርነት የቆሰሉትን ወታደሮችዎን የሚያክሙልዎ ሐኪሞች ከአገሬ ስላስመጣሁልዎ ልኬልዎታለሁ” ብሎ ሰደደላቸው ።

በነገሩ ደግሞ አሉላ በይበልጥ ተናደዱበት ። የተላኩላቸውን ሰዎች ሲያነጋግሩዋቸውም ፣

“የኢትዮጵያ ወታደሮች ከጠላታቸው ጋር ጦርነት እየገጠሙ ሲሞቱና ሲቆስሉ ኩፊት የመጀመሪያቸው አይደለም ። አገራችንን የሚመኙ ከመጡም እንደለመዱት ይዋጋሉ ። መስዋዕትነቱና ጀግንነቱ ይቀጥላል ። ሐሳባችሁን ደግፌላችኋለሁ ። ነገር ግን በመካከላችን የተጀመረው የልብ ቁስል እየተባባሰ ጥይት የነካውን የሥጋ ቁስል “እናክማለን” የምትሉት ምክንያት ከልብ እንዳልሆነ ተረድቼዋለሁ ። የወታደሮቼ ቁስል በአገሬ ዐዋቂዎች ታክሟል ። የእናንተ መድኃኒት አይስማማቸውምና ነገውኑ በመጣችሁበት እግራችሁ ወደ ምጥዋ እንድትመለሱ” ብለው ዝም ብለው እያንዳንዳቸውን ተራ በተራ ይመለከቱዋቸው ጀመር ። ጣሊያኖቹም በዝምታ ታፍነው የአዳራሹን ጣራ ሲመለከቱ ራስ ቀጠል አድርገው ፣

“የኔን ወዳጅነት ከልባችሁ የፈለጋችሁት ከሆነ በመጀመሪያ አገሬን ልቀቁልኝ ። የሰበሰባችኋቸውንም ከዳተኞች አስረክቡኝ ፤ እነክፍለየሱስና እነ ደበበን መሣሪያ እየሰጣችሁ ሕዝብ ማስቸገራችሁ አንሶ ፣ ደግሞ ብላችሁ ብላችሁ ከንቲባ ሐሚድን በተንኮላችሁ ውስጥ አስገባችሁት አይደለም ? እንግዲህ ከዚህ ተንኮላችሁ ካልታረማችሁ ምን ብዬ ነው ከእናንተ ጋር የልብ ወዳጅነት የምመሠርተው ?” አሉዋቸው ።

“እስቲ እንግዲህ ችግርዎን ለኮሎኔል ማሴታ እናስረዳለን” ቢል አንዱ ጣሊያን ፣ አሉላ ቀበል አደረጉና ፣

"ችግሩ የሚብሰው በኰሎኔላችሁ ላይ ነው ። እኔ እንደ ሆንኩ በሀገሬ ውስጥ ሆኜ የሀገሬን ዳር ድንበር ማስከበር አያቅተኝም" አሉት ።

ጣሊያኖቹ በማግሥቱ ከአሥመራ ወደ ምፅዋ ወርደው ሁኔ ታውን ለግሌታ ነገሩት ። ግሌታ የአሉላን ቁጣ ያበረደ መስ ሎት ፤ "ለኢትዮጵያ ወዳጅነት የሚቻለኝን ሁሉ ለማድረግ እንደምጣጣር ላረጋግጥልዎ እወዳለሁ" የሚል መልእክት ሰደደ ላቸው ። እርሳቸው ግን ፤ "የእነርሱ ክርስቲያንነት አገር እየያዙ ሕዝብ እርስ-በርስ እያጋጩ በሰው አገር መኖር ማለት ነው?" ብለው ለተላከላቸው መልስ ሳይሰጡት ቀሩ ።

በዚያ ወቅት ደግሞ ኢጣሊያ ውስጥ ሹም ሽር ሆነና ኮንት ካርል ሮሊስንት ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነ ። ወዲያውም በኢትዮጵያ በኩል የጀመሩትን ግፊት በስልት ለማካሔድና በአሰቸኳይም ከውጤት ላይ እንዲደርስበት ሲል አልኽኛውንና ችኩሉን ኰሎ ኔል ግሌታን እንሥቶ በትዕግሥተኛነቱና በዘዴኛነቱ የተማመነ በትን ሜ/ጀኔራል ካርሎ ጀኒን በምፅዋ ለነበረው ጦር አዛዥ አድርጐ ሰደደው ። ጀኔራሉም ምፅዋ እንደደረሰ የወዳጅነት ሰላ ምታውን በመግለጽ በምፅዋ በኩል የሚያስገቡትን የጦር መሣሪ ያና ዕቃ ሁሉ በተቻለው መጠን በአስቸኳይ እንዲደርሳቸው እንደሚያደርግ ላከባቸው ። እርሳቸውም ፤

"ኰሎኔሉ አገሬን ለቆ ይወጣል እያልኩ ስጠባበቅ ጀኔራል ተተካ! ይህ ነገር እየገፋ መምጣቱ አልቀረምና ከክንዳችን በቀር የሚገላግለን አይኖርም" ብለው ምፅዋን የጦር ሜዳ ለማድረግ የሚችሉበትን ስልት ማውጠንጠን ጀመሩ ።

ኢጣሊያኖችም የምፅዋን ከተማ በምሽግ ከከበቡ በኋላ ኅዳር 24 ቀን 1878 የምፅዋን ወደብ በአስተዳዳሪነት መያዛቸ ውን በይፋ አስታወቁ ። አጼ ዮሐንስና ራስ አሉላም ያን አድራ ጐት በጥብቅ የሚቃወሙት መሆኑን ለጣሊያኖችና እንግሊዞች አሳወቁ ። ሁኔታው እየተካረረ ሔደ ። ከዚያ ደረጃ ላይ መድረ ሱን ፈረንሣዮች ከአጠኑ በኋላ በመካከል መግባት ፈልጉና ምፅዋ በነበረው ወኪላቸው አማካይነት በመጀመሪያ ከራስ አሉላ ጋር



ቀጥሎም ከንጉሡ ነገሥቱ ጋር ለመቀራረብና እጃቸውን ለማስ ገባት የሚያስችላቸውን መንገድ ለመጥረግ ተነሡ ። በዚሁም መሠረት የምፅዋው ወኪላቸው አሥመራ ሔደ ። ከራስ አሉላ ጋር ተገናኙ ። እንግሊዞች የከዱዋቸው ፤ ጣሊያኖች አገራቸውን የያዙባቸው አሉላም የተሻለ አማራጭ ዘዴ ለማግኘት ብርቱ ፍላጐት ስለነበራቸው የፈረንሣዩን ቆንሲል በደስታ ተቀብለው ሲያነጋግሩት ፤

"እንግሊዞችና ጣሊያኖች እንደሚያውቁት በተንኮል ላይ ተን ኮል በክህደት ላይ ክህደት እየደራረቡበት ሔዱ ። ብለው ብለው ደግሞ ለአገሬ እኛ አስተዳዳሪዎችና ኃላፊዎች ሆነናል ብለው ዐወጁ ። እንግዲህ እኛም የአገራችንን ክብር በክንዳችን እንጠብ ቃለን ። ይህን ነገር በእናንተስ በኩል ምን ትሉታላችሁ?" ብለው ጠየቁት ።

"በኛ በኩልማ ይህ ሁሉ ነገር እንዲያውም ከዚህ የባሰ በደል ሊደርስባችሁ እንደሚችል አስቀድመን ተረድተነው እንድት ጠነቀቁ አሳስበናችሁ ነበር ። በእናንተ በኩል ቁርጥ ያለ ነገር ባለማግኘታችንም እነሆ እንግሊዞች ምፅዋን አሳልፈው ለጣሊ ያኖች ሰጡባችሁ ።በአድራጐታቸውም አዝነናል ። በእውነቱ አሳፋሪ ሥራ ነው ። አሁንም ቢሆን እናንተ የምትፈቅዱ ከሆነ በኛ በኩል ማንኛውንም ርዳታ ልናደርግላችሁና ይህንኑም በውል ልናረጋግጥላችሁ እንችላለን" ብሎ መለሰላቸው ።

"እንግዲያው ማለፊያ ነው ። በኔ በኩል ያለኝን ሐሳብ ከእናን ተም ጋር ለመስማማት የምችልበትን መንገድ ሁሉ ዘርዝሬ ለአጼ ዮሐንስ እልካለሁ ። ከዚያ በኋላ መልሱን አሳውቃለሁ" ብለውት ወደ ምፅዋ ተመለሰ ።

ራስ አሉላ ፤ የፈረንሣዩን ቆንሲል ከአሰናበቱ በኋላ ፊታ/ ዓለማየሁንና ሻለቃ አርአያን አስጠርተው ፤

"እንደምታውቁት እንግሊዞች ምጥዋን ለጣሊያኖች አሳል ፈው ሰጥተውብናል ። እዚያም ድረስ ወርደን ጦርነት እንዳንገጥም ሕዝቡን ማስጨረስና ሠራዊቱንም ለብርቱ ጉዳት የሚጥልብን

ይሆናል ። እንደደረሰኩበትም ጣሊያኖች ለምጥዋ ባሕር መድፍ የነጣጠረ መርከብ ጠምደዋል ። የምጥዋንም መዳረሻ በምሽግና በመድፍ አጥረውታል ። እኛም ባለን መሣሪያ ብንሰለፍ ሕዝቡ ይጐዳብናል ። ለዚህ የሚሻለው ከምጥዋ ወጥተው ወደላይ እስቲወጡ መጠባበቅ ነው ።

እስከዚያው ግን ፤ በምጥዋ በኩል የሚመጣልንን መሣሪያና ዕቃ እንዳይከለክሉብን ዙላ ላይ ፈረንሣዮች እንዲሠፍሩ አድርገን በእነርሱ በኩል ማነኛውንም ነገር ማከናወን ይሆናል ። ከዚህ ሌላ ደግሞ ፈረንሣዮች ዙላ የሠፈሩ እንደሆነ አማውርታ ውስጥ ተደብቀው ሕዝብ የሚያስቸግሩትን ደበበንና ወንበዴዎቹን ሊቆጣጠሩዋቸውም ያመች ይሆናል ። እንግዲህ የፈረንሣዩ ወኪል የመጣው ይህን ይህን ለመነጋገር ነበር ። በኔ በኩል ያለኝ ሐሳብ ይህ ነውና እናንተም የሚታያችሁን እንድትነግሩኝ ብዬ ነው" አሉ ።

"መቼም ጌታዬ" አሉ ፊታውራሪ ኃይለሥላሴ ፤ "መቼም ሐሳብዎ ረቂቅ ምሥጢር ያዘለ ነው ። ነገር ግን እንግሊዞችን አምነን አስጠግተንና ተዋውለን እነርሱ እኛን ችላ ብለው ወደጣሊያኖች ዘወር ብለው አገራችንን አሳልፈው እንደ ሰጡብን ሁሉ እነዚህኞችስ በተራቸው ሌላ ነጭ አስመጥተው አገራችንን ቢሰጡብንስ ምን ዋስትና አለን ?" ብለው ጠየቁ ።

"ግስፈያ አስበሃል ፤ ነገሩ እንዳልከውም የሚያሳስበን ነው ። ዳሩ ግን በአሁኑ ጊዜ እንግሊዞችና ፈረንሣዮች በብርቱ ፉክክር ላይ ናቸው ፤ በየዓለሙ ሁሉ አገር እየተሻሙ ነው ። እንግሊዞችም ምጥዋን ለጣሊያኖች አሳልፈው የሰጡት ከፈረንሣዮች ጋር ባበቀሉት ፉክክር ረዳት ለማግኘት ሲሉ ነው ።

ፈረንሣዮችም በበኩላቸው ረዳት ፍለጋ መሔዳቸው የማይቀር ነው ። እንግዲህ እርስ-በርሳቸው እንደዚህ የሚተናነቁ ከሆነ አንድ ቀን በአንዱ አገር ላይ ትልቅ ጠብ ያስነሡና ይለይላቸዋል ። ከዚያ በኋላ እኛም ሆን እንደኛው አገራቸውን የተቀሙ ሁሉ ተጣጥረው የአገራቸው ባለቤቶች ሊሆኑ የሚችሉበት አጋጣሚ ይኖራቸዋል ።



ፈረንሣዮችም እንደ እንግሊዞች የሚከዱን የሆነ እንደሆን መስኮቦችም ሰው ልከውብኛል ። ከእነርሱም ጋር የምንስማማበትን ብልሃት እንፈልጋለን ። መቼም ጊዜውን እያየን ለኛና ለሀገራችን የሚበጀውን ብልሃት ከመፈለግ ሌላ ምን እናደርጋለን ?" አሉ ትክዜ እየተጫጫናቸው ።

በዚሁ ሐሳባቸው ከተስማሙላቸው በኋላ ነገሩን አብራርተው ወደ አጼ ዮሐንስ ላኩ ። ንጉሠ ነገሥቱ የእሉላን ሐሳብ ደግፈው የምዕዋ በር እንዳይዘጋባቸው የሚያስችለውን ስምምነት ከፈረንሣዮች ጋር እንዲያደርጉ ላኩላቸው ። እሉላም ወደ ምዕዋ መልእክተኛ ልከው ወደ አሥመራ እንዲመጣ አስጠሩትና ፈረንሣዩም ያቀረበው ሐሳብ ግቡን እንደ መታለት በመተማመን ገሥግሦ አሥመራ ደረሰና ከራስ እሉላ ጋር ተገናኘ ።

ራስ እሉላ መኳንንቶቻቸው በተገኙበት ሲያነጋግሩት ፤ "ዙላ ላይ እንድትሠፍሩ ያቀረባችሁት ሐሳብ ደስ አሰኝቶናል ። ነገር ግን አሁን እናንተ ዙላ ስትገቡ ምጥዋ ላይ ካሉት ጣሊያኖች ጋር ግጭት ሊነሣ ይችላል ብለን ስለሠጋን ፤ ጣሊያኖችም ከሀገራችን በሰላም እንዲወጡልን ከእንግሊዝ ንግሥት ጋር በመላላክ ላይ በመሆናችን ንጉሠ ነገሥቱም አሁን አሽንጌ ስላሉ ወደ መቀሌ ተመልሰው የጣሊያኖቹ ጉዳይ እልባት እስከ ተደረገበት ድረስ ዙላ መሥፈራችሁ ቆይቶ እዚያው ምጥዋ ላይ እንደሆናችሁ ንጉሠ ነገሥቱ የሚያስገቡትን የጦር መሣሪያ ወደዚህ እንድትልኩልን ከዚህ በፊት በተሰጠህ ውክልና መሠረት ከእንግዲህ ወዲህም እንድትቀጥል ንጉሠ ነገሥቱ ፈቅደዋል" አሉት ።

"ዙላ የመሥፈራችን ጉዳይስ እስከመቼ ይወሰናል?" አለ ፈረንሣዊው ቆንሲል ።

"ትንሽ ጊዜ ይጠይቃል ። በመጀመሪያ የእንግሊዝን ንግሥት ቁርጠኛ ሐሳብ ለማወቅ እንወዳለን ። ከዚያ በኋላ ጣሊያኖች በሰላም አገራችንን እንዲለቁ ከመንግሥታቸው ጋር እንላላክበታለን ። ይህን ሁሉ አድርገን የማይሆን ከሆነ እናንተም ዙላ

ልትሠፍሩ ትችሉ እንደሁ ስምምነቱ ምን እንደሚሆን ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ትነጋገሩበታላችሁ'' አሉት ።

የፈረንሣዩ ወኪል በዚሁ ተስማምቶ፣ የንጉሠ ነገሥቱ ወኪል በዚሁ ተስማምቶ፣ የንጉሠ ነገሥቱ ወኪል ሆኖ የጦር መሣሪያ ሊልክላቸው ተስማምቶ ወደ ምፅዋ ተመለሰ ።

ምንም እንኳን ራስ አሉላ ያፋጠጡዋቸውን ችግሮች በዲፕሎማቲክ ስልታቸው ከፍጻሜ ለማድረስ ጥረት ቢያደርጉም፣ ዙላንም አሳልፈው ለፈረንሣዮች መስጠቱን በመጨረሻጊዜ ከብዶአቸው ቆንስሉን ተስፋ ስጥተው በመሣሪያ አቀባይነቱ ብቻ እንዲቆይላቸው ከስምምነት ላይ ቢደርስም፣ ጊዜ አዝሎ ያመጣባቸው ችግሮች ግን ባሰቡትና በሚደከሙበት መንገድ ሊጓዙላቸው አልቻሉም ። የፈረንሣዩ ቆንሲል የንጉሠ ነገሥቱ ወኪል ሆኖ የጦር መሣሪያ እንዲልክላቸው ያደረጉትን ስምምነት ዐይኖቿን አፍጥጣ ጥፍሮቿን አሹላ የሰማችው ሮማ ሌላ አቅጣጫ ደግሞ አሠመረች ።

በዚህም መሠረት ምፅዋ የነበረው የጣሊያን ጦር በተቻለ መጠን እንዲጠነቀቅ፣ ከኢጣሊያ ወደ ኢትዮጵያ የሚላኩ መልእክተኞችም ከራስ አሉላ ጋር ሳይገናኙ በቀጥታ ወደ አጼ ዮሐንስ ሔደው እንዲነጋገሩ፣ ራስ አሉላ ከመረብ ምላሽ ገዥነት እንዲነሡ የእርሳቸው ተቃዋሚዎች የሆኑ ሽፍቶችና የጉሳ ተጠሪዎች በተቻለ መጠን እየተጠናከሩ እንዲወጉዋቸው ስልቱ ተቀነባበረ ።

ይህን ሁሉ በሥራ ለማዋልም ተወስነና በመጀመሪያ የኢጣሊያ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበረው በቀጥታ ለአጼ ዮሐንስ ደብዳቤ ጽፎ ፈቃዳቸው ቢሆን መልእክተኞች ለመላክና ከአድሚራል ሒወት ጋር ያደረጉትን ስምምነት ለማደስና የኢጣሊያም ጥቅም ሊጠበቅ የሚችልበትን ሐሳብ ለማቅረብ የሚችል በጀኔራል ፓዚሊኒ ኃላፊነት አንድ ቡድን መላኩን ገልጾ ላከባቸው።

አጼ ዮሐንስ ደግሞ በጣሊያኖች ላይ ያደረባቸው ቅሬታ መልስ የሚያስጥና መልእክተኞችንም እስከመቀበል የሚያስች



ላቸው አልነበረም ። እንዲያውም ስለ ኢጣሊያኖች የነበራቸው እምነት፣

"ኢጣሊያኖች ተንኮለኞች ናቸው ። ወደዚህ የመጡትም ለክብት ርባታ አይደለም፣ አገሬን ለመያዝ ነው ። በእግዚአብሔር ቸርነት ግን አንድ ቀን ተዋርደው በዓለም ፊት አፍረው ከገሬ ይወጣሉ'' የሚል ነበር ።

ምንም እንኳን የአጼ ዮሐንስን መልስ ባያገኙም፣ ጣሊያኖች ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር መልካም ወዳጅነት መሥርተው ራስ አሉላን ለማቫር ቆርጠው ተነሥተውበት ነበርና በጀኔራል ፓዚሊኒ የሚመራው ቡድን ምፅዋ ገብቶ የአጼ ዮሐንስን ፈቃድ መጠባበቅ መጀመሩን አሉላ ሰሙ ።

በዚህ ጊዜ ነበር አሉላ ማንነታቸውንና ቆራጥነታቸውን ለጣሊያኖች ለማሳየት ደግሞ በይበልጥ የተነሡት ። ምፅዋ ከነበሩት ጣሊያኖች ጋር በምሥጢር እየተገናኙና እየተዋዋሉ የጦር መሣሪያና ጉርሻ እየተቀበሉ በየቀበሌው እየተዘዋወሩ ሕዝቡን ቡተለይም ከአሥመራ ወደ ምፅዋ ይመላለሱ የነበሩትን ነጋዴዎች ሲያስቸግሩ የነበሩትን ቀንደኞች ወንበዴዎች እጃቸውን ለመያዝ እምቢ ካሉም በየነበሩበት ለመደምሰስ ወታደሮቻቸውን በየአቅጣጫው እየላኩ ማሳደዱን አጠነከሩ ። በተለይም በሐርጊጐ፣ በዙላና ሐባብ የነበሩትን የጣሊያኖች ተባባሪዎችና ተላላኪዎች እየመነጠሩ ሕዝቡም ከኢትዮጵያዊነቱ ንቅንቅ እንዳይል በጐበዝ አለቃው አማካይነት ወሰላቶችን እንዲቋቋም ግብሩንም በወቅቱ እንዲያስገባ ጠበቅ ያለ አስተዳደራዊ ርምጃቸውን ማፋጠን ጀመሩ ።በዚያ ርምጃቸውም ጣሊያኖች መደናገጥ ጀመሩ ። በሕርጊጐና በሐባብ ቀበሌዎች የሚገኙት ነዋሪዎች በቀጥታ በኢጣሊያ የበላይነት የሚስተዳደሩ መሆናቸውን በመግለጽ የራስ አሉላ ወታደሮችም ሆኑ አስተዳደር እንዳይገቡ በመቃወም መልእክተኛ ወደ አሥመራ ስደዱ ።

አሉላም፣ "እንኳንስ ከባሕሩ ወዲህ ያለው መሬት ቀርቶ ራሱ ባሕሩም ቢሆን የኢትዮጵያ መሬትና ግዛት ነውና፣ በግዛቴ ውስጥ በማደርገው ሥራ እናንተን የሚያገባችሁ አይደለም''

ብለው መልስ ሰጥተው፣ እንዲያውም ይግረማችሁ ብለው ወታደር ሲልኩባቸው ወደ ነበሩት ቀበሌዎች ራሳቸው እየሔዱ ከዳተኞችን እየቀጡ ጸጥታውን ራሳቸው መቆጣጠር ጀመሩ።

ምፅዋ የነበረው የጣሊያን ጦር አዛዥና ከርማ ወደ መቀሌ ተልከው የነበሩት የኢጣሊያ መንግሥት ባለሥልጣኖችም በአሉላ ፈጣን ርምጃ እጅግ ተበሳጩ። የአሉላን ቁራጥነትና አስደናቂም ስልት ጣሊያኖቹ ከተገነዘቡት በኋላ፣ ስልታቸውንም መለወጥ እንደሚገባቸው አመኑበት። እርሳቸውን ተቃውመውና እርሳቸውንም ዐልፈው በቀጥታ ወደ መቀሌ ለመሔድም ሆነ ከአጼ ዮሐንስ ጋር ለመነጋገር የሚፈልጉትንም ውጤት ለማግኘት እንደማይችሉም አመኑበት። ከዚያ በኋላ አሉላን ማለዘብና መልካም ወዳጅነታቸውን ማግኘት ስለፈለጉ፣ በመጀመሪያ ዶክተር ነራዚኒ የተባለውን መልእክተኛ ወደ አሥመራ ሰደዱ።

ራስ አሉላ ያንኑ መልእክተኛ ተቀብለው ሲያነጋግሩትም፣ "በመጀመሪያ ምጥዋ ስትመጡ የኢትዮጵያን ሕዝብና መንግሥት ወዳጅነት ለማትረፍና በንግድም ነገር አብረን ለመሥራት ነው ብላችሁ ነበር። አገር ለመያዝ ግን ሐሳብ የለንም ብላችሁ ነበር። አሁን ግን ምጥዋንም እያለፋችሁ አንዳንድ ቦታዎችን መያዝና ሕዝቡንም ከኢትዮጵያዊነቱ አስክዳችሁ የእናንተ ባሪያ ለማድረግ መመኘታችሁን ተረድቼዋለሁ። እኔ በሕይወቴ ቆሜ ደግሞ ይህ ሐሳባችሁ አይሳካም። እንግዲህ የወዳጅነታችሁን ልክ አይተንላችኋልና አሁንም በወዳጅነታችሁ የምጠይቃችሁ በአስቸኳይ ከሠፈራችሁባቸው ቦታዎች እንድትለቁ ነው" አሉት መላ አካላቸውን አስቆጥተው።

"ንግዱንም ለመጀመር ከባሕሩ ወጣ ያለ መሬት ስላስፈለገን ነበር ከአንዳንድ ቦታዎች ላይ ለማረፍ የፈለግነው። ይህንኑ ሐሳባችንንም ለአጼ ዮሐንስ ለማስረዳትና ለመስማማትም ስልን ነበር ከመንግሥታችን ተልከን የመጣነው" አለ ነራዚኒ ዐይኖቹን እያስለመለመና እጆቹን እያወናጨፈ።

"ምነው ምጥዋ ለሸቀጥ ማራገፊያ አልበቃችሁ አለ? አጼ ዮሐንስስ ቢሆኑ እንኳን ሌላ መሬት ሊሰጡዋችሁ ምጥዋንስ ልቀቁ



እያሉ በእንግሊዞች በኩል አስጠይቀዋችሁ የለም ? እሱንም ከእርሳቸው ጋር ለመነጋገር ከፈለጋችሁ በመጀመሪያ ከምጥዋ ወጭ ወደ የሥፍራው ወሰናችሁ ያሠፈራችኋቸውን ወታደሮቻችሁን ሰብስባችሁ ምጥዋ ላይ ከሠፈራችሁ በኋላ ላኩብኝና እንነጋገርበታለን። ያለዚያ ግን ወዳጅነታችሁ በቅቶኛል" አሉት።

"መልካም ነው። ይህንኑ ሐሳብዎን ለላኩኝ ባለሥልጣኖች አስረድቼ መልሱ እንዲደርስዎ አደርጋለሁ" ብሎ ወደ ምጥዋ ተመለሰ።

ምጥዋ የነበረው የኢጣሊያ መልእክተኞች ኃላፊ የራስ አሉላን ቁርጠኛ ሐሳብ በነራዚኒ አማካይነት ከተረዳ በኋላ፣ የኢጣሊያ ወታደሮች ከሠፈሩባቸው ቀበሌዎች እንዲነሡ ለማድረግ የማይሆንና ከአጼ ዮሐንስም ጋር ለመገናኘት እንዳልቻለ ከተረዳ በኋላ በመጣበት እግሩ ወዳገሩ ተመለሰ።

ራስ አሉላም የመልእክተኞቹን መመለስ እንደ ሰሙ፣ "ፈረንጅ ምኞቱም የባሕር ማዶ ዕቃ ብቻ የሚያቀብል አይደለም። በጥበቡና በገንዘቡ ሕዝብ እያጋጨ አገር ሊይዝ ሌትና ቀን ከመጣር አይቦዝንም" አሉ።

# መለማመጡ በቃን

የኢጣሊያ መንግሥት መልእክተኞች ከምፅዋ መመለስ እጅግ ያንገበገበው ደግሞ በምፅዋ የነበረውን የኢጣሊያ ጦር አዛዥ ሆነ ። ጀኔራል ጅኔ ምፅዋ ገብቶ ሁኔታዎችን ካጠና በኋላ በራሱ ውሳኔ የተላከበትን ዒላማ ለመምታት ፈለገ ። በዚህም መሠረት ዕቅዱን በሥራ ላይ ለማዋል ወስኖና ከዕለታት አንድ ቀን ረዳቱ የነበረውን ኰሎኔል ዶ ክርስቶፎርስን ጠርቶ ፤

“ሌሎች የአውሮፓ መንግሥታት ማንኛውንም አገር በጦር ኃይላቸው ሲይዙ እኛ ከዚህ ሐሩር ላይ ሠፍረን አንድ ጥቁር አንጋጠን እየተመለከትን መለማመጣችን የውርደት ውርደት ነው ። ትውልድንም ጭምር ያሳፍራል ። በቀጥታ ዒላማችንን መምታት ወይም መመለስ እንጂ የአንድን ጥቁር ወዳጅነትና ስምምነት በመለመን የአውሮፓ መሣቂያ መሆን የለብንም” ብሎ ዝም አለና አንገቱን ወደ ምዕራብ አቅጣጫ አዙሮ በጽሕፈት ቤቱ መስኮት ምፅዋን እዘቅዝቀው የሚያሳዩትን ኮረብታዎች መመልከት ጀመረ ። ኰሎኔሉ ሁኔታው ደስ አላለውም ። ከአጼ ዮሐንስም ጋር ሆነ ከራስ አሉላ ጋር የተጀመረው መላላክ መልካም ፍጻሜ እንዲደርስ በትዕግሥት መጠባበቅ እንደሚያስፈልግ ለጀኔራሉ ሲያስረዳ ሰንብቷል ። በዚያች ዕለትም የገነፈለውን የጀኔራሉን ቁጣ ቱግ ለማድረግ የሚችልበትን ዘዴ እያምሰለሰለ ቃላት ከመናገር ተቆጥቦ ነበር ።የእርሱ ዝምታ ደግሞ ጀኔራሉን በይበልጥ የደም ግፊቱን ጨመረበትና ፤

“በዝምታ ልትመለከተኝኮ አይደለም ከሮማ የመጣኸው ፤ ሐሳብህን አትናገርም !” አለ ጀኔራሉ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ አዙሮት የነበረውን አስተያየቱን ከእርሱም ላይ አሳርፎ ። “እስቲ አሁንም ተስፋ ሳንቆርጥ አንድ ጊዜ እንሞክር ፤ ከዚያ



በኋላ....” ብሎ ኰሎኔሉ ንግግሩን እንደ ጀመረ ጀኔራሉ አቋረጠውና ፤

“ሺህ ጊዜ ብንሞክርም ውጤት አይኖረውም ። የላክናቸውን ሐኪሞች አዋርዶ መልሷቸዋል ። እንደገናም ከመንግሥታችን የመጡትን መልእክተኞች አላነጋግርም ወደ ንጉሡም አያልፉም ብሎ መለሰ ። ከዚህ የበለጠ ትዕግሥት በማንም ላይ አልታየም። ከዚህም የበለጠ ውርደት በማንኛውም የአውሮፓ መንግሥት ላይ አልደረሰም ። ኢጣሊያም አይደርስባትም! ልምምጡ ቢቃን ከእንግዲህ ወዲያ ግን አንድ እርምጃ ማሳየት አለብን ገባህ!” አለና ከተቀመጠበት ተነሥቶ በመስኮቱ ወደ ኮረብታዎቹ ፊቱን አዞረ ።

ኰሎኔሉ በማስታወሻው ላይ ሲጽፍ ቆየና ፤

“ምን ዐይነት ርምጃ ማሳየት እንችላለን ?” ብሎ ጠየቀ ።

“ጀግኖች ወታደሮቻችን እነዚያን ኮረብታዎች አልፈው ባንዲራችንን መስቀል አለባቸው!” ብሎ ጀኔራሉ ወደ ወንበሩ ተመልሶ ከፊቱ በነበረው ወረቀት ላይ በርሳስ ዝግዛግ መሥመር መንደፍ ጀመረ ።

“በእርምጃችንስ አለቆቻችንና እንግሊዞች ይስማማሉ ብለው ያስባሉ ጌታዬ!” አለ ኰሎኔሉ ።

ጀኔራሉ ሲነድፈው የነበረውን መሥመር ጨረስና በመጀመሪያ ራሱ ትክ ብሎ ሲመለከተው ቆይቶ በእርሳሱ ኰሎኔሉን እያመለከተ ፤

“ወታደሮቻችን ከዙላ በስተምሥራቅ የምትገኘውን ቡሬ የምትባለው መንደር መያዝ አለባቸው ፤ ከዚያ ከደረሰን በኋላም ቢሆን ርምጃችንን እንቀጥላለን” አለ ።

“ግንኮ ጌታዬ ግን...” ብሎ ኰሎኔሉ ተናግሮ ሳያበቃ ፤
“‘ግን ግን ምን!’ በየት በኩል አድርገን ወደ ቡሬ እንዝመት ብለን አለቆቻችንን እንጠይቅ’ ልትለኝ ነው?” አለ ጀኔራሉ በምፀት አነጋገር ።

"እንግሊዞችስ በነገሩ ይስማማሉ ወይ ለማለት ነው?" አለ ኩሉኔሉ ከአለቃው የተሻለ አስተሳሰብ ያለው መሆኑን ለመግለጽ ያለቃውን የፌዝ አነጋገር አሽቀንጥሮስት ። ጀኔራሉ ከመቀመጫው ተነሥና በስተምሥራቅ በኩል በነበረው መስኮት የባሕሩን አካባቢ እየተመለከተ ፣

"እንግሊዞች ይስማማሉ ወይ ? አልከኝ?" ብሎ ጥያቄውን ደገመውና ንግግሩን ቀጥሉ ፤

"እንግሊዞችማ ለጥቅማቸው ሲሉ ተስማምተውማ ከዚህ ደርሰናል ። ከእንግዲህ ወዲያ እኛን እያዘሉ በየኮረብታው እያሥፍሩንም። እነርሱ ከሜዲትራኒያ ባሕር ወዲህና ወዲያ ያለውን የአፍሪቃንና የእሲያን እህጉር እያካለሉ ይዘው ያውና ሕደን ገብተዋል ። እኛ በዚህ አገር የምናደርገውን ርምጃ ሊገቱ ወይም ሊቆጣጠሩ የሚችሉበት ምክንያት አይኖርም" ብሎ ከመስኮቱ ወደ ኩሉኔሉ ተመልሰ ፣

አሁን በቀጥታ ከመኮንኖቹ ጋር ተነጋገርበትና ነገውኑ ቡሬ በተበለችው መንደር ላይ ጦር እንዲሠፍር" ብሎ ትእዛዝ ሰጠና ከወንበሩ ላይ ሲቀመጥ ኩሉኔሉም ወታደራዊ ንቃቱን አሳይቶ ወጣ ።

የጀኔራሉ ትእዛዝ ተፈጸመ ። ወታደሮቹ ቡሬ ሠፍረው ባንዲራቸውን ሲሰቅሉ ሕዝቡ ተደናገጠ ። በዚህ ጊዜ ሼህ ኑርሑሴን የተባሉ አዛውንት ከመንደሩዋ ጠፍተው ወጡና ወደ አሥመራ ሐደው ሁኔታውን ለራስ አሉላ ነገሩ ።

"እግዚአብሔር ይስጥልኝ እንኳን የነገሩኝ የእነርሱ ምኞትኮ ሌላ ነው ፣ በምጥጥና በቡሬ ብቻ የሚገታ እንዳይመስልዎ ! የሆነ ሆኖ ዛሬ ቡሬን ከያዙ እንግዲህ ወደ ትግራይ ለመዝለቅ መንገድ መጥረጋቸው ነው" ብለው ሼህ ኑር ሁሴንን ሸልመው አሰናብተው ወደ አካለ ጉዛይ ሐደው ሰንዓፌ ላይ ዕርድ አሠርተው ወታደሮች አሥፍረው ተመለሱ ።

የጣሊያኖቹ መረማመድ ከአሉላ ጋር ግጭት ሊያስነግ እንደሚችል የተገነዘቡት እንግሊዞች በመካከል ጣልቃ ገብተው



ለማስታረቅ ፀላሰቡ ሐሪስን እስሚዝ በተባለው ወኪላቸው አግካይነት መልእክተኞች ወደ አጼ ዮሐንስ ለደዱ ። መልእክተኞቹ በመጀመሪያ ከራስ አሉላ ዘንድ እንደተረቡ ፣

"በእርስዎና በጣሊያኖች መካከል መግባባትና ሰላም እንዲመሠረት የሚቻልበትን ጉዳይ ከእርስዎና ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ለመነጋገር ነው የመጣነው" ብሎ የመልእክተኞቹ መሪ ሐሳቡን አስረዳ ።

ራስ አሉላ ፣ ለመልእክተኛው ሐሳብ መልሱን ለመስጠት የቸኮሉበት ጉዳይ ነበርና እርሱ ተናግሮ እንዳበቃ ፣

"ጣሊያኖችን ያመጣችሁና ተመሳጥራችሁ ምጥዋ ላይ ያስፈራችሁ እናንተው ናችሁ ። አሁንም ተስማሙ የምትሉ እናንተው ናችሁ ። አንድ ሰው ለንግድ ጉዳይ ወደ አንድ አገር ሲሔድ እዚያው እስፈረበት ሆኖ ነው የንግዱን ጉዳይ ማከናወን ያለበት ። ቀስ —ቀስ እያለ ወደሌላ ሰው ቤት በር መቃረብ ተገቢው አይሆንም ። ኢጣሊያኖችም ለንግድ ሥራ ነው የመጣን ሲሉ ቆይተው አሁን ይኸውና ቡሬንና ሌሎች ቦታዎችን ይዘዋል ። ታዲያ ይህ ተገቢ ሥራ ይመስላችኋል ? የሚያጥጣቸው አይመስለኝምና ምክሩዋቸው ፤ በሕይወቴ ቆሜ ያገሬን መሬት እንደ ማሳስንካ ይወቁት" ብለው ከአጠገባቸው የነበረችውን ከዘራ አንሥተው መሬቱን እየቆረቆሩ ተጫጭናእቸው የነበረውን ትካዜ በግሬት ለማስወጣት ደጋግመው ተንፍሰው ፣

"እናንተ በንሰለት አሥራችሁበት የነበረውን ደበበን ፈትተው አግውርታ ውስጥ በጉልበቱ አዳሪ አድርገው "አንተ ነጋዴ ዝረፍ ፣ እኛ ደግሞ ጸጥታውን ለመጠበቅ ነው እያልን አገር እንይዛለን ብለው ጣሊያኖች የሚሠሩትን እጉል እጉል ነገር የምታውቁት ነው ። ከዚህ ተንኮላቸው ካልተቆጠቡ በሀገሬ ላይ ሲጫወቱ ማንንም አፍሬና ፈርቼ በቸልታ የምኖር አይደለሁም" አሉና በዐይናቸቸው እየገራረፉ ተመለከቱዋቸው ።

"መልካም ነው ፤ ሐሳብዎን ተረድቼዋለሁ ። እንግዲህ በንጉሠ ነገሥቱ በኩል ያለውን ሐሳብ ከተረዳን በኋላ የሚቻለውን ሁሉ ።

ምኒግንዱ ላይ ሆነው የሚጠባበቁ በርከት ያሉ ወታደሮች ሰፍ
ረዋል ። እነርሱም ፊት በዚያው ከነበሩት ከቫሊያ አርአያ ወታ
ደሮች ጋር ሆነው በመጠባበቅ ላይ ናቸው አሉ ደጃዝማች ።
“ግለሩያ ነው ሁላችንም እንግዲህ መሔዳችን የማይቀር ነው!
አሉ ራስ ።

ደጃዝማችም ቀጠል አድርገው፤ “በጣሊያን አገር የሚኖሩ
ክርስቲያኖች የላኩን መልእክተኞች ነን ። የመጣነውም ሀገርምን
ለማለማት ነውና ወደ አሥመራ መጥተን ከእርስዎ ጋር እንድ
ንነጋገር ይፍቀዱልን ብለው ጣሊያኖች ይህን መልእክት ሰጥ
ዋል” ብለው ወረቀት አቀረቡ ። “የእነርሱን ክርስቲያንነትማ
ልኩን አየነው! አወቅነው! ለወዳጅነትና ለንግድ መጣን እያሉ
አገር መያዝ ፡ ሕዝብ መፍጀት አይደል ? ለመሆኑ ወረቀቱ ምን
ይላል?” አሉ ራስ አንገታቸውን እያወዛወዙ ።

ደጃዝማች ኃይለ ማርያም ወደ ውጭ ወጣ ብለው ከበሩ የነ
በሩትን እሌታ ምሀረተአብን ጠቀስ አድርገው አስገቡዋቸውና ፡

“ከምጥዋ የመጣውን ወረቀት አንብበው” አሉ ። ወረቀቱም
እንዲህ የሚል ነበር ።

“ይድረስ ለታላቁ ጌታ ራስ አሉላ

በየሱስ ክርስቶስ ስም ሰላምታችንን እናቀርባለን ። ከዚህ ቀደም
ጉጃም ድረስ ዘልቀን ደንበጫ በተባለው አገር ለንጉሥ ተክለ
ሃይማኖት ሀገርና ሕዝብ የሚያገለግል ድልድይ መርተናል ።
አሁንም ቢሆን ለእርስዎና ለንጉሡ የሚጠቅሙ ድልድዮች
መገንባት ፡ ቤተክርስቲያኖች ለመሥራት ከእርስዎና ከሀገርዎ
ጋር በክርስቲያንነት ወንድማማችነት ላይ የተመሠረተ ወንድም
ነትና መተሳሰብ ለመመሥረት በጣሊያን አገር የሚገኙ ክርስ
ቲያኖች ልከውን መጥተን ምህየ መፍረን ፈቃድዎን እንጠባ
በቃለን ። የድካማችንንና የሥራችንንም ዋጋ ሁሉ ከየሱስ እናገ
ኛለን ። ይህንኑ በቃል አስረድተን ሥራችንንም ለመጀመር
ከኔ ጋራ አምበት ሆነን እንመጣለን”

የመገረስ ቅዱስ ወንድምዎ
አውገበቶ ጣሊቢኒ ።



እሌታ ወረቀቱን አጣጥፈው ይዘው ቢቆሙ ራስ አሉላ ወደ
ደጃዝማች መለስ ብለው ፤ “እውነት ይመስልሃል ? ምን ታስ
ባለህ ?” ብለው ጠየቋቸው ።

“እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል እንደሚ እንደዚያ መጣ
ተው ብናያቸውና ብናነጋግራቸው አይከፋም ይመስለኛል ።
ቢሆንም ጌታዬ ያውቃሉ” አሉ ደጃዝማች ።

“እውነት ብለሃል! ለማንኛውም ቢሆን ቢመጡ አይከፋም።
ምናልባትም “ክርስቲያኖች ነን” ብለዋልና ተጋበኛውን ጀኔራላቸ
ውን መክረው ወታደሮቹን ከአሥፈረበት ቦታ ያስወጡልን ይሆ
ናል ። ይህም ባይሆን ከእጃችን ከገቡ ይዘን እውነቱን እንዲያ
ወጡ እናስለፈልፋቸዋለን ። ለማንኛውም መምጣታቸው አይከ
ፋም ፡ በኔ ቃል አድርገህ ላክባቸው” አሉ ራስ ።

መልእክተኛ ቢገሠግሥ ሔዶ መልሱን አደረሰ ። በአወጋ
ቡት ጊሊቢኒ ኃላፊነት የሔዱት ጣሊያኖች ልዩ ልዩ የሕንፃ መሣ
ሪያዎች የስጦታ ዕቃዎች መድኃኒቶችና የምግብ ዐይነቶች አስ
ጭነው ወደ አሥመራ ተጓዙ ።

የተጠሩት ሰዎች እየገቡ እጅ እየነሡ እንደ ተቀመጡ ራስ
አሉላ መሬት መሬት እያዩ ቆይተው እንደገና ዐይናቸውን
ወደ መኳንንቱ እየወረወሩ ፤

“አንድ ጉዳይ ስለ አጋጠመኝ የታያችሁን እንድትነግሩኝ ብዬ
ነው ። ጣሊያኖች ይኸውና በፊት በደንከል በኩል የባሕሩን በር
“ገዛነው” ብለው ይዘውታል ። በዚያ አልተወሰኑም ፤ ምጥዋ
ላይ ከሠፈሩ በኋላ ፤ አሁን አሁን ደግሞ ወደላይ ወደ ደጋው መገ
ፋተት ጀምረዋል ። ወደ ከሰላ ከመሔዳችን በፊት “ወጌሻዎች
ነን መድኃኒትም ይዘን መጥተናልና ወታደሮችዎን እናክምልዎ”
ብለው መጥተው የነበሩትን መልሰናቸው ነበር ። አሁን ደግሞ
“በጣሊያን አገር የሚኖሩ ክርስቲያኖች የላኩን ነን ድልድይና
ቤተክርስቲያን ልንሠራላችሁ መሬት ልናለማላችሁ ተልከናልና
ፍቀዱልን” ብለው ልከውብኝ እንዲመጡ ፈቅጄላቸዋለሁና
አስቲ አስቡበት ምን ይመስላችኋል ? እንደዚህ አጥብቀው የተ

መላለሱበት ምክንያት ሳይናገሩቸው ይቀር ይመስላችኋል ?" ብለው ምክር ጠየቁ ።

"ለመሆኑስ የመጡት እንግዶች የሚታወቁ ናቸው ?" አሉ ሻለቃ አርአያ ።

"ወረቀቱን የጻፈውና እመጣለሁ ብሎ የላከው ማሊቤኔ የተባለ ጉሻም ድረስ ዘልቆ ድልድይ ያሠራ ነው" አሉ ደጃዝማች ኃይሉ ለሥላሴ ።

"ዋናው ሐሳባቸውስ ምንድን ነው ?" አሉ ዘጊዮርጊስ የተባሉ ባለሟል ።

"አገር እናለማለን ፤ ድልድይና ቤተ ክርስቲያን እናሠራለን" ነው የሚሉት" አሉ ደጃዝማችም "ምነው እኛ በሠራነው ቤተ ክርስቲያን የምናደርሰውን ጸሎት እግዚአብሔር አልሰማም አለ ? መሬቱስ እንሥራለን የሚሉትስ ለምናችን ብለው ነው ? ተዚህ ቀደም እንግሊጣሮች ወደ ደጋው ገብተው ከአጼ ቴዎድሮስ ጋር ለመዋጋት እንዳመቻቸው ሁሉ እነዚህም ወደ መኻል አገር ለመግባት አስበው እንዲያመቻቸው ይሆናል እንጂ ለሀገራችን ሕዝብና እንስሳ አዝነውለት ይመስላችኋል ? መቼም ለሁሉም ጌታዬ ያውቃሉ ?" አሉ አንገታቸውን ደፋ ቀና እያደረጉ ።

"የእናንተንም ሐሳብና ምክርኮ አስፈልጎኝ ነው ያስጠራኋችሁ " ሲሉ ራስ ዘጊዮርጊስም ቀበል አደረጉና ፤ "መቼም ፈረንጅ ሲባል ጠላትነቱም ወዳጅነቱም ረቂቅ ነው ። ከኋላቸው ጦር ጭነው ለደግ ሥራ ነው የመጣነውና ተቀበሉን ማለታቸው 'እሺ' ቢሉ በፈገግታ 'እምቢ' ካሉ በግዴታ መሬቱን "እንይዛለን" ብለው ነው ። አባቶቻችን "ጠላትን በጦር ፤ አባትን መጦር ጠላት ይቀበል ጥላት" እንዲሉ አሁንም እንደሆን የእነዚህኞቹ ቀድሞ መምጣት ለብልሃታቸው ነውና የአመጣጣቸው ምክንያቱ በጥብቅ እንዲታይ ይገባል" አሉ ።

"ነገር ነገሩ ያጠራጥራል ፤ ቢሆንም ለመልካም ሥራ ነው የመጣነው ካሉ ይምጡና ሥራቸውን እንየው ፤ ከዚያ በኋላ የሚሆነውን እንመከርበታለን" አሉ ባሻይ በኩሩም ።



"ግለፊያ ነው ፤ ወዳጅነታችሁን ተረድቼዋለሁ ፤ በዚህ ጉዳይ ላይ ከእናንተ ጋር እንድንመካከርበት የፈለግሁትም ወረቀቱን የጻፈው ሰውዬ አገራችንን የሚያውቀው በመሆኑ ፤ ደግሞም በጣሊያን አገር የሚኖሩ ክርስቲያኖች ልከውናል ስላለ እምቢ ብንለው ከሌሎቹ ክርስቲያኖች ጋር እንዳያቀያይመን ስለጠነቀቅሁ ፤ ከዚህም በቀር የጣሊያን መንግሥት ያልበደላቸው ከሆነ ምንም ስለሠፈረው ጦርም አንዳንድ ነገር ለመረዳት ያመችን እንደ ሆነ ለመጣጣር ይጠቅመን እንደሁ በማለትና ለምናልባቱ ደግሞ በሁለታችን መካከል ያለው ነገር እየከረረም ከሔደ እነዚህኞቹ በመካከል ይገቡና ነገሩን ያበርዱት ይሆናል ብዬ ነው ። ወዳጅነታችንን ከልባቸው ፈልገው ከመጡ የልብ ወዳጆች እንሆናለን ፤ ተንኮል አዝለውም ከሆነ እንደርስበታለን ፤ ነቅተን መጠበቁ የኛ ፈንታ ነው ። እውነቱን የሚያመለክተን ደግሞ አምላካችን ነው" አሉና ራስ ነገሩ በዚሁ ተወሰነ ።

# እንግዶቹ

በአውግስቶ ግሊቢኒ የሚመሩት እንግዶች የሕንፃ መሣሪያዎች በግመሎች ጭነው ከምፅዋ ተነሡ ። ቆላማውን መሬት አጋምሰው ወደ ደጋው ሲጠጉ ቀኑ መምሸት ጀምሮና ምቹ ቦታ መርጠው ሠፈሩ ። የተከተሉዋቸው አሽከሮቻቸው ሠፈሩን ማጽዳትና እሳት ማንደድ ጀመሩ ። እነርሱ ከሠፈሩበት እልፍ ብሎ ደግሞ ወደ ምፅዋ የሚወርዱ ነጋዴዎች ሠፍረዋል ። ከመካከላቸውም አንዱ ዋሽንት እየነፋ እያቅራራና እየዘፈነም ጓደኞቹን ያጫውታል ።

"ምንድነው ከዚያ ማዶ የሚሰማው?" ብሎ ቫለታ ፒያና ከተከታዮቹ ተኽሌ የተባለውን ጠየቀው ። የቀረርቶውንና የዋሽንቱን ጩኸት ምክንያትና ትርጉም ነገረው ።

"ሒደህ አምጣውና ያጫውተን" አለ ፒያና ። ተኽሌ እንደታዘዘው ወደ ነጋዴዎቹ ሠፈር ሔዶና ባለዋሽንቱን ወስዶ ከጣሊያኖቹ ፊት አቀረበና ፣

"እጅ ንሣ" ብሎ እንደ ማስጐብደድ አደረገው ።

"ለእግዚአብሔሩ ሰላምታ ጤና ይስጥልኝ እላለሁ እንጂ እጅ መንሣቱ እንኳ ይቅርብኝ" አለ ያ-ዋሽንተኛ ጠጠር ብሎ ።

"እስከ መቼ ነው የሚቆየው?" አለ ተኽሌ ።

"የእነርሱን ማንነት እስካውቅ "አለ ባለዋሽንቱ ።

"ወደ ራስ አሉላ የሚሔዱ ሰዎች ናቸው፤ ደግሞም ግብጦች እይምሰሉህ ፈረንጆች ናቸው" አለ ተኽሌ የጣሊያኖቹን ኃያልነት ለማስተዋወቅ ብሎ ።



"ታዲያ ወደ ራስ ለሚሔዱ ፈረንጆችን ሁሉ" እጅ ንሡ ያለውስ ማነው?" አለ ዋሽንተኛው ። በዚህ ጊዜ ግሊቢኒ ወደ ሰዎቹ ጠጋ ብሎ ፤

"ወደየት ልትሔዱ ነው?" ብሎ በትርጁማኑ አማካይነት ጠየቀ ።

"ወደ ምጥዋ" መለሰ ዋሽንተኛ ።

"እዚያ ምን ጉዳይ አላችሁ?"

"ነጋዴዎች ነን ።"

"ከየት ነው የመጣችሁት?"

"እህ? እንዴት ነው ነገሩ? ብጥሰው ገለበጠኝ" የሚባለው ለካ እንደዚህ ያለ ነገር ሲያጋጥም ነው ። እናንተ ከየት መጣችሁ እንጂ እኛማ በሀገራችን ውስጥ ነው ያለነው" አለ ነጋዴው ።

በዚህ ጊዜ ግሊቢኒ በእነጋገሩ ተገርሞ ሰላምታ ሊሰጠው ጠጋ ብሎ እጁን ሲዘረጋለት ፣ ዋሽንተኛው ፊንጠር ብሎ ዱላውን አስተካክሎ ያዘና ፣

"ምን ሊሆን ነው?" አለ ።

"አይዞህ አትፍራ አገርህን ለማልማት የመጣን ነን" አለ ግሊቢኒ እየፈገገለት ።

"አገሬቱ ለምለም ናት ፣ የፈረንጅ አልሚ አያሻትም" አለ ኮስተር ብሎ ።

"እኛኮ አገር የምናለማው መንገድ፣ ድልድይ፣ ቤተክርስቲያን ማለፊያ ማለፊያ ቤቶች በመሥራት ሕዝብ ለማሠልጠን እንጂ መሬቷማ በጣም ለምለም ናት ። ጎጃም ድረስኮ ሔጄ አይቻታለሁ ፤ በክፉ ዐይን አትመልከተን" አለ ግሊቢኒ ።

"እረ ምን በወጣችሁ! በክፉ የምንመለከታችሁ! መቼም መጠርጠር ይገባል ብዬ ነው እንጂ!" አለ ዋሽንተኛው ።

“የምትጠራጠሬው ምን እንዳይመጣባችሁ ነው ?”

“የሚያጠራጥርግ ሞልቷል!!”

“በምን ነገር?”

“እንደዚሁ እንደ እናንተ የመሰሉ የሰው አገር ሰዎች በዚሁ በኩል ገብተው ፥ አገር እየሰለሉ ሕዝብ እየፈጁ አስቸግረው ነበርና ተዚያ ወዲህ የሰው አገር ሰው ስናይ እንጠራጠራለን ፥ እንዲያው ውቃቢያችን እሽ አይለንም” አለ ።

“ተዚህ ቀደም አገራችሁን የሰለሉ ሰዎች አጋጥሞሃል?” አለ ማሊቢኒ ።

“እኔን ባያጋጥመኝም መቼም በታሪክ እንሰማለን ።”

“አገራችሁን የሰለሉ የውጭ አገር ሰዎች ታውቃለህን ?” ብሎ ጠየቀ ማሊቢኒ በመጠራጠር ስሜት ተውጦ ።

“አዎን ብዙ ሰምቻለሁ ።”

“እስቲ አንዱን ትዝ የሚልህን ንገረኝ ።”

“በጥንት ዘመን ነው ይላሉ ፤ ተምድረ-ምሥር ሰዎች ተንጉሡ ተልከው ወደዚህ ሲመጡ ፥ ንጉሣችን ተጠራጥረው አስይዘው ያሣሥሩዋቸዋል ። የምሥሩ ንጉሥም በዚህ ነገር ይናደድና ጦሩን አስከትቶ ወደኛ ይዘምታል ። የሠራዊቱም ብዛት እስከ አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ይደርስ ነበር ይባላል ።

“የሱዳንን በረሃ አቋርጦ ወደኛ ሲገሠግሥ ዓውሎ ነፋስ ይነሣና ገሚሱን ጦሩን ጠራርጐ ያወድምበታል ። የተቀረውን ደሞ ውሃ ጥምና ረሃብ ይፈጅበታል ። ተዚያ የተቀረውንም የተቅማጥ በሽታ ይጨርስበታል ። በዚህ ጊዜ የምሥሩ ንጉሥ“ለካ የእበሻ ንጉሥ እንደዚያ አድርጐ የደፈረኝ አንድ የተደበቀ ኃይል አገሩን እንደሚጠብቅለት ስለሚታመን ነው ። በውነት የአበሻን መሬት የሚጠብቃት ኃይል አለ ብሎ ከመቅሠፈት የተረፉትን ወታደሮች ይዞ ወደ አገሩ ተመለሰ ይባላል” አለ ዋሽንተኛ ።



“ስለዚህ ነገር የሚያስረዳ መጽሐፍ አለህ? ” አለ ማሊቢኒ ።

“የወንጌል ትእዛዝ አይደለምኮ ምኑ ይጣፋል ! ቢሆንም ሊቃውንቱ ጽፈውት ይሆናል ፤ እኛ ግን ከአባቶቻችን እንደበት ነው የሰማነው” አለ ዋሽንተኛው እየሣቀ ።

“ለመሆኑ ወደ ምፅዋ ሁልጊዜ ትመጣለህ ? ” አለ ማሊቢኒ ።

“መቼም ዐልፎ ዐልፎ እንመጣለን ።”

“ታዲያ በመንገድስ ችግር ያጋጥማችኋል ?”

“አራዊቱን ፥ ወበላታውን ፥ ደጋውንና ቆላውን ዐልፈን ምጥዋ ስንደርስ ደግሞ ድር ግብጦች አሁን ጣሊያኖች ያስቸግሩናል” አለ ዋሽንተኛው ።

“ምን እያሉ ነው የሚያስቸግሩዋችሁ” አለ ማሊቢኒ ።

“እኛ ሳንፈቅድላሁች አትምጡ ፥ ቀረጥ ክፈሉ እያሉ ያስቸግሩናል” አለ ዋሽንተኛው ።

“ታዲያ ይህን ነገር መንግሥታችሁ ሰምቷል ?”

“ሰምቷል ይባላል ፤ ነጋዴ እንዳያስቸግሩ አገሩንም እንዲለቁለት ለጣሊያኑ ጦር አለቃ ራስ አሉላ ጥፈውለታል ይባላል” ሲል ፒያና ጠጋ ብሎ ፥

“ጣሊያኖቹ አገሩን አንለቅም ቢሉስ ምን ይመጣ ይመስልሃል ?” ብሎ ጠየቀው ።

“የሚመጣውን የሚያውቅ እንኳ ፈጣሪ ብቻ ነው ፤ ግን በሰው አገር ገብቶ አልወጣም ካለ በቱርኮችና በግብጦች የደረሰው ይደርስበታል” አለ ዋሽንተኛው ።

“በእነርሱ ላይ ምን ደርሷል” ብሎ ጠየቀው ፒያና ።

“የነፍጠኛ ጉራዴ ለሽልጂቸዋል” ብሎ መለሰለት ።

“ጦርነት ይሆናል ማለትህ ነው?”

"እንዴታ ! የት ይቀራል ?"

"አንተ ነጋዴ ነህ ፣ ጦርነት እንደሚሆን እንዴት ታውቃለህ ?" አለ ግሊቢኒ ።

"የሀገሬን ሕዝብ አማውትና ነው ? ያለፈቃዱ መሬቱን ሲነካ ከብት አይወድም ! እንደንብ ነው እውውው ! ብሎ እሚነግ ። እንግዲህ ወደ ሥፈሬ መሔዴ ነውና ከፈለጋችሁ ወደ ዚያው ኑና ዳቦ ቆሎና አምባሻ እናትምሳችሁ" ብሎ ሊሔድ ሲል ፣

"በል አሥመራ ስትመለስ እንፈልግሃለን" አለ ግሊቢኒ ።

"በደኅና ለመፈለግ ያብቃን" ብሎ ሔደ ዋሽንተኛው ። ግሊቢኒና ፒያናም እርስ በርሳቸው ተያዩና አንገቶቻቸውን እያወዛወዙ በበይኑ ሕሊናቸው ተከተሉት ።

ከቀናት በኋላ በእመጋቢት ግሊቢኒ የሚመሩት እንግዶች አሥመራ እንደገቡ በተዘጋጀላቸው ግሬሪያ ሁለት ቀናት ከቆዩ በኋላ ወደ ራስ አሉላ ቤት ተወሰዱ ።

ራስ አሉላም ከመኳንንቶቻቸው ጋር ሆነው በታላቅ አዳራሽ ተቀበሏቸው ። ግሊያናኛ እየገቡ መደዳውን ሲቆሙ ግሊቢኒ ወደ ራስ ቀረብ አለና ፣

"ታላቁ ጀኔራል ሆይ !

ከዚህ ከገባንበት ጊዜ ጀምሮ ስለ ተደረገልን መስተንግዶና ዛሬም እርስዎ ስለ ተቀበሉን ከልብ እናመሰግናለን ። እኔ ለሀገርዎ እንግዳ አይደለሁም ቀደም ብሎም እስከ ጎጃም ድረስ ዘልቄ ለንጉሥ ተክለሃይማኖት ድልድይ ሠርቼላቸዋለሁ ። መንገዶችም አስጠርጌያለሁ ፤ ለእንስሳት ጤንነት የሚጠቅም ሥራ ሠርቻለሁ ። ዛሬም የመጣነው ለእርስዎና ለሀገርዎ ጠቃሚ ሥራዎችን ለማከናወን ነው ። ይህንኑም በጻፍኩት ደብዳቤ አረጋግጫለሁ ። እነዚህ ጓደኞቼም የሥራ ረዳቶቼ ናቸው" ብሎ ተከታዮቹን አስተዋወቀ ።



"እኔም እንኳን ደኅና ገባችሁ እላለሁ ። ዝርዝሩን ጉዳይ እያደር እንመካከርበታለን ፣ ተቀመጡ" አሉና ራስ አሉላ እንግዶቹን መቀመጫ እያመለከቱ ራሳቸውና መኳንንቱም ተቀመጡ ።

ሰዓቱ የምሳ ሰዓት ነበርና ምግቡ በሞሶብ በሞሶብ ጠላውና ጠጁ በገንቦ በገንቦ እየሆነ ፣ ግምጃ እየተሸፈነ ቀረበ ። ለራስና ለመኳንንቶቻቸው ለብቻ ፣ ለኢጣሊያኖቹም ለብቻ በየዋሰቡ ቀረበ ።

"ለሀገሩ እንግዳ ስላልሆኑ ለምግቡም እንግዳ አይደሉምና ባለ ደረቦችዎንም ይጋብዙልኝ" አሉ ራስ ግሊቢኒን እየተመለከቱ ።

"አዎ ርግጥ ነው ፣ የሀገርዎ ምግብ ይጣፍጣል ፣ ሲናፍቀኝ ነበር ። ዛሬ ስለ አገኘሁትም ደስተኛ ነኝ" አለ ግሊቢኒ ።

"ይህ ነገር ሻምፓኝ ነው ?" አለና አንዱ ጣሊያን ግሊቢኒን ጠየቀ በዋንጫ የቀረበለትን መጠጥ ደጋግሞ ከተጎነጨው በኋላ ።

"ከማር የሚሠራ ጠጅ የሚባል መጠጥ ነው" ብሎ ግሊቢኒ መለሰለትና ወደ ራስ መለስ ብሎ ደግሞ ፣

"ጎጃም ከጠጣሁት ጠጅ ይኸ ይበልጣል ፤ ጓደኛዬማ ሻምፓኝ ነው ወይ ነው የሚለኝ ፣ ለመሆን የስንት ዓመት ነው" ብሎ ጠየቃቸው ።

"የጠጅን ጣዕም ለይተው እስቲያውቁ ድረስ ጎጃም ከቆዩማ ጎጃሜ ሆነዋላ!" አሉ ራስ በቀልድ አነጋገር ።

የግሊቢኒ ምክትል የነበረው ፒያናም ጠጁን ደጋግሞ ተጎነጨና ፣

"ታላቁ ጀኔራል ሆይ ! አውሮፓውያን ያልሠለጠኑ ሕዝቦች ናቸው እያሉ ሲነግሩን እኛም እውነት መስሎን ተሳስተን መኖራችንን ያወቅሁት አሁን ነው ። ከማር ብቻ እንደዚህ የመሰለ መጠጥ መሥራት ከቻላችሁማ በጣም ሀብታሞችና የሠለጠናችሁ መሆናችሁ አያጠራጥርም" አላቸው ።

"ሰማህ ወዳጄ" አሉ ራስ አሉላ እጃቸውን በለምለም እንጀራ እያባበሱ ።

"ፈረንጆች እኛን ያልሠለጠኑ ናቸው ቢሉንኮ አያስገርመንም። እኛም እነርሱን እንደዚሁ ነው የምንለው ። ሁለታችንም ሠልጥ ነናል የምንለው በየራሳችን አስተያየት ፍላጐትና ዝንባሌ ነው። እነርሱ አገራቸውን እንውረር እናንተንም ባሪያ አድርገን እን ግዛ ሲሉን ፣ እኛ ደግሞ አገር እናስደፍርም ለእናንተ አንገዛም ስንል ፣ ሁለታችንም ሥልጣኔ የሚባለውን ነገር እንደ እየምን ታችን እንተረጉመዋለን" አሉት ።

"ልክ ነዎት ጌታዬ" አለና ግሊቢኒ ይዞት የነበረውን ዋንጫ ተጐንጪለትና ከሞሰቡ ሥር ካስቀመጠ በኋላ አንገቱን እያወ ዛወዘ ፣ "መቶ በመቶ ልክ ነዎት የአውሮፓ መንግሥታት በተለ ይም እንግሊዝ ፣ ፈረንሣይ ፣ ፖርቱጋልና ጀርመን የአፍሪቃን ሕዝቦች በሥልጣኔ ስም በባርነት ቀንበር አስገብተዋቸዋል ፤ ይኸ ሥልጣኔ አይደለም ሰይጣናዊነት ነው" አለ ።

ወዲያው የልፍኝ አሽከሩ አለቃን አስገባና "ስብሐት" ከተባለ በኋላ ማዕድ ከፍ ሲል ብር ቅብ በሆነ ማህን የጣት ውሀ ሲቀ ርብ እንደ መጀመሪያው እንግዶቹን እንዲያስታጥብ ራስ አስታ ጣቢውን አዘዙትና እንግዶቹ መታጠብ እንደ ጀመሩ ፣ "እዎ ይህን የመሳሰለውን ወረራ ነው እኛ የምንቃወመውና አልሠለ ጠናችሁም የምንለው ። የባሕር ማዶ ሰዎች ደግሞ ካልገዛናችሁ አልሠለጠናችሁም እንላችኋለን ትሉናላችሁ" አሉና ከፈረንጆቹ ቀጥለው ታጠቡ ።

ወዲያው ግሊቢኒ አንዱን ጣሊያን ጠቅሶ አንድ ነገር አዘ ዘውና ወጣ ። በዚህ ጊዜ ራስ አሉላም ፣

"ምነው ምን ያስፈልገዎታል !" አሉት የተቸገረበት ጉዳይ የደረሰበት መስሏቸው ።

"ዕቃ እንዲያመጣልኝ ብዬ ነው ፤ ከውጭ ያስቀመጥነው ዕቃ አለን" አለ ግሊቢኒ ራስ አሉላም ጥውውቱን ቀጠሉና ፣ "እኛ ሥልጣኔ የምንለው የአዳም ልጆች ሁሉ በፍቅር ፣ በመደ



ጋገፍና በመግባባት ለመኖር ሲችሉ ነው እንጂ በእጅ ሥራቸው ሲመኩና ሌሎቹን ሲገዙበት አይደለም" አሉት ።

በዚህ ጊዜ ወደ ውጭ የተላከው ፈረንጅ በሸራ የተጠቀ ለለ ዕቃ ይዞ ሲገባ ግሊቢኒ ተነሥቶ ተቀበለውና ከጥቅሉ እያወጣ ፣

"ታላቁ ጀኔራል ሆይ! ይህ የአውሬ ማደኛ በቅርቡ አገራችን ውስጥ የተሠራና ለእርስዎ መታሰቢያ እንዲሆን ያመጣሁለዎ ነው" ብሎ ሲያቀርብላቸው እርሳቸውም ከመቀመጫቸው ቢነሡ መኳንንቱም ተነሡ ። ጠመንጃውንም ተቀብለው እያገላበጡ ተመለከቱና ፣ "እግዚአብሔር ይስጥዎ! ግለፈያ መጣሪያ ይመ ስላል ፤ አስበው ይህን ያህል መታሰቢያ በማምጣትዎ አመሰግን ዎታለሁ" አሉና አጋፋሪውን ጠቀስ አድርገው ትእዛዝ ሰጡና ወደ ፈረንጆቹ ዞር ብለው ደግሞ ፣ "ይህን መጣሪያ በመንገድ ሞክረውታል ?" ብለው ግሊቢኒን ጠየቁት ።

"የለም አዲስ ነው አልተሞከረም" አላቸው ።

"ምናልባት እርስዎ ሳያውቁት ተተኩሶበት ይሆናል ባሩድ ባሩድ ይሸታል" አሉት ደጋግመው ካሸቱት በኋላ ።

"እውነት ነው በመርከብ ላይ ሠራተኞች ለሙከራ ተኩሰው በት ይሆናል" ሲላቸው እርሳቸውም እንደገና እያሸተቱ ፣

"በቅርብ ቀን የተተኮሰበት ሳይሆን አይቀርም ፤ ሽታው ያስ ታውቃል" ሲሉት ግሊቢኒም ወደ እርሳቸው ተጠጋና ጠመንጃውን ተቀብሎ አሸትቶ ፣ "አዎ ምናልባት ባርቆ ይሆናል" አላቸው ። ወዲያው አጋፋሪው ሦስት ጠመንጃዎችና ሁለት ጐራዴዎች አስ ይዞ ገባ ። እርሳቸውም ከአጋፋሪው እየተቀበሉ ፣

"ይኸ ቤልጅግ የተሠራ የአውሬ ማደኛ ነው" ብለው ለግሊ ቢኒ ሰጡትና ቀጠል አድርገውም ፣ "ይህ ደግሞ እንግሊዝ አገር የተሠራ ነው" ብለው ፒያና ለሚባለው ምክትሉ ሰጡት ። "ይህ ደግሞ ጀርመን አገር የተሠራ ነው" ብለው ለሦስተኛው ጣሊ ያን ሰጡትና ለቀሩት ሁለት ጣሊያኖች ደግሞ ጐራዴዎች አበረከቱላቸው ።

በዚህ ጊዜ ፒያና የተባለው ደስታ ፈንቀለውና ፡ “ምስጋን የሚገባው አለቃችን ሲኞር ግሊቢኒ ቢሆንም ፡ ደስታ ስለፈንቀለኝ ነውና ቀድሜ በመናገሬ ይቅርታ እጠይቃለሁ ። ታላቁ ጀኔራል ሆይ! ልባዊ ስጦታ ነው አመሰግናለሁ” አለ ። በዚህ ጊዜ ሁሉም ማሊያኖቹ “እናመሰግናለን! እግዚአብሔር ይስጥልን” እያሉ እየተረቡ ሰላምታ ሰጡ ።

ራስ አሉላም አጋፋሪያቸውን ጠቀስ አደረጉና ፡ “መሣሪያዎቹን እንድንሞክራቸው ዒላማ አስተክሉ” ብለው አዘዙና ወደ እንግዶቹ መለስ ብለው ደገሙ ፡

“መሣሪያዎቹን ለመፈተን ያህል ዒላማ ስለ ተዘጋጀ እንውጣና እንሞክራቸው ?” ብለው ነገሩዋቸውና ሲነሡ ሁሉም አብረው ወጡ ።

በመጀመሪያ ራሳቸው ሸብረክ ብለው አዲስ በመጣላቸው ጠመንጃ ሦስት ጊዜ ተኩሰው በሦስቱም ጥይት የተተከለውን ነጭ መጓሪያ አጥንት መቱ ። ቀጥለውም ለግሊቢኒ ለፒያናና ለማይበርስ ሦስት ጥይት እያጐረሱ ያንኑ ጠመንጃ ሰጡዋቸው ። ሁለቱም እያከታተሉ ተኮሱ ። አንዳቸውም ዒላማውን አልመቱም ። በዚህ ጊዜ ማሊያኖቹ ኃፍረት ሲይዛቸው ራስ ተመለከቱና ፡

“የመንገዱ ጠመን ያልወጣላችሁ ሆና ነው ። ተኩስ ረጋ ያለ ልብ ይጠይቃል ፤ ዛሬ ብትስቱ ሌላ ጊዜ ትመቱ ይሆናል” ብለው ወደ ቤት ሲያመሩ ፡

“በጥናው ተኩስ ዕለት እንገናኛለን ፤ ያን ጊዜ የሚመታውንና የሚስተውን ዒላማ የሚሆነውንም እናያለን” ብሎ ፒያና ለግሊቢኒ ሹክ አለው ።

ራስና እንግዶቹ እንዲሁም መኳንንቱ በየነበሩበት ቦታ ከተቀመጡ በኋላ ፡ በጥልፍ ቀሚስ ያሸበረቀች ወጣት ቡና ይዛ ገብታ ተዳችና ከእንጨት በተሠራ መደርደሪያ ስታቀርብ ፡ ፈረንጆቹ ግን ሁሉን ትተው ልጅቱን አፍጥጠው ሲመለከቱ ፡ ራስ በንቀትና በትዝብት ፊታቸውን ዘወር አደረጉባቸው ።



ቡና ከተጠጣ በኋላ ራስ እንግዶቹን ይዘው ወደ ሁለተኛው አዳራሻቸው ገቡ ። ያ አዳራሽ ከእንግዶች ጋር የሚነጋገሩበት ነው ፡

“እንግዲህ ወደ መጣችሁበት ጉዳይ እንመለስና የተላካችሁት ከመንግሥታችሁ ሰዎች መሆን ነው” ብለው ጠየቁ ።

“የለም ፡ የለም እኛ ሦስታችንም ከአንዳንድ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ነው የተላክነው ፤ ሙያችንም መሐንዲስነት ነው” አለ ግሊቢኒ እየተርበተበተ ።

“እነዚህ ሁለቱስ?” ብለው ራስ ጠየቁ ።

“እነሱማ የኛ ረዳቶች ናቸው” አለ ግሊቢኒ ።

“በጻፉልኝ ወረቀት ላይ እንደ ተረዳሁት ሀገር ለማልማትና እኔን ለመርዳት ነው ሐሳባችሁ ፡ አይደለም ?” አሉ ራስ ።

“ልክ ነው ታላቁ ጀኔራል ልክ ነው” አለ ግሊቢኒ ።

“ለምትሠሩት ሥራስ የምትጠይቁት ክፍያ ምንድነው?” አሉ ራስ ።

“ከመንፈስ ደስታና ሀገርዎ ስትለማ ከማየት በስተቀር የምንጠይቀዎ ምንም ነገር አይኖርም” ብሎ መለሰ ግሊቢኒ ።

“እንግዲህ ዓላማችሁና ሐሳባችሁ ይህ ከሆነ እናንተ ኢጣሊያኖች ሀብታሞች ናችሁ ማለት ነዋ?” አሉ ራስ ።

“እርግጥ ነው ፡ በጣም የዳበረ ሀብትና በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ብር አለን ። ሀገራችን ለምለም ፡ መንግሥታችንም በጦር ኃይል የዳበረ ነው ። ይህን ሁሉ ሀብት አከማችተን የምንሠራበት ጉዳይ ነው የቸገረን ። ስለዚህ ያከማቸነውን ሀብት ከእናንተ ጋር ለመካፈል ነው የመጣነው ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለ ታሪክና የተመሰገነ መሆኑን ስለ ምናውቅ የልብ ወዳጅነትን ፈልገን የመጣን ነን” አለ ።

በዚህ ጊዜ ራስ አሉላም ጣሊያኖቹን አንድ ባንድ ተመለካከቱና ፣ "ማለፊያ ነው ፤ ለዚህ ታላቅ ተግባር የመጣችሁ ከሆናችሁ ምንም የሚቸግራችሁ አይኖርም ። ስለዚህ ለወዳጅነቱ ምስክሩ አምላካችን ነው" አሉና ራሳቸውን እየነቀነቁ አመልካች ጣታቸውን ቀሰረውባቸው ፤ "ይሁን እንጂ አስቀድሜ ላስጠንቅቃችሁ የምፈልገው በመካከላችሁ አታላዮችና ሰላዮች ቢገኙ ይቅርታ የማይገኝለት ቲም በቀል ይመሠረታል ፤ ቁጣዬና ቅጣቱም የበረታ ይሆናል" አሉ ።

የእንግዶቹ ገጽ ተለወጠ ። ድንጋጤ ወረራቸው ፣ ወዲያው ፒያኖ እንደ ምንም ተበረታታና ፣

"ወዳጅነታችንን ሊጻረር የሚችል ምንም ነገር አይኖርም ፤ በመካከላችን ሰላይም አታላይም የለም፤ የእርስዎን ወዳጅነት አግኝቶን ሥራ ሠርተን ለመጥቀምና ለመጠቀም የመጣን ነን" አለ ።

"ማለፊያ ነው ፣ የነገራችሁኝ ሁሉ እውነት ለመሆን መስቀል እየመታችሁ ትምሉልኛላችሁ ?" አሉ ራስ ባገነገነ ስሜት ።

"ይህ ነገር እውነት ለመሆኑ በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ልንምልልዎ እንችላለን" አለ ፒያኖ። በዚህ ጊዜ ራስ በተረጋጋ መንፈስ ሲያጨበጭቡ አጋፋሪው ገባ ።

"እባክህ አባ መስቀል ይዘው እንዲመጡ ንገርና መኳንንቱንም አስገባቸው" አሉ ።

"እያችሁ ወዳጆቼ ! እኛ ኢትዮጵያውያን ወዳጅነትና ፍቅርን በእምነት ምስክርነት ላይ ነው የምንመሠርተው ! ባለፉት ጊዜያት ብዙዎቹ የባሕር ማዶ ሰዎች ለልዩ ልዩ ጉዳያቸው እየመጡ ብዙ ችግሮች ስለ ፈጠሩብን ፣ የወዳጅነታችን እምነት የምናውቀው በመሐላ ነው ። ስሆንም ስለምናስምላችሁ ቅር እንዳማትሰኙ እተማመናለሁ" አሉዋቸው ።

"እኛ ቅሬታ አይኖርብንም ባህላችሁ ከሆነ እንምላለን" ፒያኖ ።

"ባህላችን ብቻ ሳይሆን እምነታችንም ነው" ብለው ራስ



አሉላ እንደ መለሱለት ቄሱ ትልቅ መስቀል ይዘው ገቡ ። ራስ ተነሥተው መስቀሉን ተሳለሙ ። ቀጥለው መኳንንቱ ገቡ ፤ ቄሱ መኳንንቱንም መስቀል አሳለሙ ።

"እኛም እንሳለም?" አለ ማሲቢኒ ።

"እንደ ሃይማኖታችሁ ነዋ! እኛ ኦርቶዶክሶች ነን ፤ እናንተ መቼም ካቶሊኮች ናችሁ። ስለዚህ በማታምኑበት ሃይማኖት መስቀል ተሳለሙ ብለን አናስገድዳችሁም ፤ ግን ትምሉበታላችሁ" አሉት ራስ ።

"እሺ እንምላለን" አለ ማሲቢኒ ።

"ይበሉ አባቴ ያስምሉዋቸው" አሉ ራስ ። ቄሱ የጣሊያኖቹን እጆች ተራ በተራ ከመስቀሉ ላይ ሲያስቀምጡ ራስ ቃለ መሐላውን ነገሩ ።

"የመጣንበት ጉዳይ የተናገርነው ሁሉ እውነት ነው ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብና መሬት ወዳጅነት ከልብ እንመኛለን ። ሸርና ተንኮል ፣ ደባና ዓመፅ አስበን ከመጣን መስቀሉ ይፍረድብን ፣ አምላካችን እጅና እግራችንን ይሰረን" ብለው እንግዶቹ ማሉ ።

"ማለፊያ ነው በእርግጥ ወዳጆቼ ለመሆን እንደመጣችሁ ቁረዳሁት ። ሥራችሁን ስትጀምሩ በየቦታው ከእናንተ ጋር የሚዘዋወሩ ሰዎችም ይታዘዙላችኋል ፤ የሚጉድልባችሁ አንድም ነገር አይኖርም" አሉና እንግዶቹን እያስቀመጡ ራሳቸውም ተቀመጡ ። ወዲያው ራሳቸውን ንግግራቸውን ቀጥለው "እንግዲህ መቼም ወዳጆቼ ሆናችኋልና አንድ ነገር ልጠይቃችሁ እወዳለሁ ። የአገርና የሕዝብ ጉዳይ ስለገጠመኝ ሰሞኑን ወደ ጊንዳዕ እወርዳለሁ ብዬ አስቢያለሁ ፣ ፈቃደኞች ከሆናችሁ አብራችሁኝ ብትሔዱ አልጠላም" አሉ ራስ ።

"እኛ ልንረዳዎ የምንችለው ነገር ይኖራል ?"

"እንደምታውቁት የመንግሥታችሁ ጦር ቀደም ሲል ደንከል ላይ ሠፍሮ ቆይቶ ደግሞ ይኸውና ምፅዋ ገባ ። አሁን ደግሞ ዊአና

ሰሐጤ መሥፈር ጀምሮዋል ይባላል ። በመካከላችን ገብታችሁ ነገሩን ብታዩት አይከፋም" አሉ ራስ ።

"በዚህ ጉዳይ ታዲያ እኛ ያገባናል? የኛ ሥራ ከመንግሥት ጋር ምንም ዐይነት ግንኙነት የለውምኮ!" አለ ፒያና ትከሻውን ከፍና ዝቅ እያደረገ ።

"እርግጥ ነው ፤ ከወታደሮቹም ጋር ሆነ ከአዛዡ ጋር የሥራ ግንኙነት ባይኖረንም ፤ ያለመግባባት እንዳይፈጠር በመካከል ብንገባ መቸም ክርስቲያናዊ ተግባር ይመስለኛል" አለ ማሊቢኒ ።

"ገባኝ ገባኝ በዚህ መንገድ ከሆነ መልካም ነው ። ምናልባትም መግባባትና መፈቃቀር ከተመሠረተ ታላቁ ጀኔራልም ወደ ምፅዋ ወርደው ምፅዋን ጐብኝተው ከኢጣሊያ የጦር አዛዥ ጋር በመነጋገር ሠፈሩንም ሆነ መርከቡን ሊጐበኙለት ይችላሉ" አለ ፒያና ።

"መቸም በነገሩ እናንተ ገብታችሁበት ያለመግባባት እንዳይጠፈር ከተደረገና ያለፈቃዳችን በመሬታችን ላይ የሠፈረው ጦር ከተነሣ ከጦር አዛዡ ጋር ለመነጋገርና ለመግባባት እንችላለን" አሉ ራስ አሉላም ።

"እንግዲያው በጉዳዩ እንስማማለን ፤ ከእርስዎ ጋር ለመሐድ ፈቃደኞች ነን" አለ ማሊቢኒ ። "ማለፊያ ነው አሁን እንግዲህ ወደ ተዘጋጀላችሁ ቦታ ሒዱና ዕረፉ ። ሰሞኑን አብረን እንወርዳለን" አሉ ራስ ።

እንግዶቹ ሲነሡ ራስና መኳንንቱም ተነሡና ሰላምታ እየሰጡዋቸው ወጡ ። ራስ ተመልሰው ተቀመጡና "እንግዲህ ነገሩን ሰማችሁት አይደለም? ሰዎቹ እውነተኞች ይመስሏችኋል?" አሉ ራስ አሉላ ።

"ሰይጣን ሰው ሲያታልል 'ስለ ፍቅር በስመ አብ ይትር' እያለ ይባላል ፤ ማይሙት በምጥዋ ካለው ጦር ጋር ሳይገናኙና ሳይመካከር እዚህ ድረስ መጣ?" አሉ አቶ ዘጊዮርጊስ በጋቢያቸው ጫፍ ዐይናቸውን እየጠራረጉ ።



"እመኑን ብለው መስቀል መትተው ምለዋል ። ከእንግዲህ ወዲያ መቸስ ልብ-ዐውቃንት የለን? ምን ይደረጋል ከመመልከት ሌላ?" አሉ ባሻይ በኩሩ ።

"እንግዲህ የሚሆነውን ጌታ ያውቃል ። ነገራቸው አጥግቦኛል ይስማሙኛል ካሉም ማለፊያ! ድልድዩ ፤ ቤተ-ክርስቲያኑ ሲሠራ እናያለን ። ሰውነትዎ ከተጠራጠረም ሕሊናዎ የሚያመለክተዎን ይሥሩ" አሉ ዘጊዮርጊስ ።

"ማለፊያ ነው ፤ መቸም እንደታያችሁ ተናግራችኋል ፤ እኔም ልብ ብየዋለሁ ። አስቀድሜ ተጠንቅቄበታለሁ ። ከእውነተኛው ጉዳይ ላይ እደርስበታለሁ ። ለማንኛውም እስቲ ሁላችሁም ተዘጋጁ ። ጊንዳዕ ከወረድን በኋላ ቁርጡ ይለያል ። ለጣሊያኑ የጦር አለቃም የሠፈረበትን ቦታ እንዲለቅ እልክበታለሁ' አሉ ራስ ።

ራስ አሉላ ፤ መኳንንቶቻቸውና ኢጣሊያኖች በዚህ ሁኔታ በነበሩበት ወቅት ደግሞ ከምፅዋ አንድ ደብዳቤ ደረሳቸው ። የጻፈላቸውም ኢጥርስ የሚባል ኢትዮጵያዊ ነበር ። ይህ ሰው ቀደም ብሎ ወደ ምስር ሔዶ በአሌክሳንድርያ የሚኖርና ስምንት ልዩ ልዩ ቋንቋዎች የሚችል ነበር ። ኢጣሊያኖች ፤ ምፅዋን ለመያዝ ባቀዱ ጊዜ ኢጥርስንም አስተርጓሚያቸው ሆኖ ወደ ምፅዋ እንዲመጣ ይጠይቁታል ። እርሱም ጥያቄያቸውን ይቀበልና ነገር ግን የእነርሱ ተቀጣሪ ከሆነ በኋላ ምንም ነገር ቢያጠፉ ወይም ቢበድል የኮንትራት ሥራውን አቋርጦ ወይም ሰርዞ ወደ አሌክሳንድርያ ከመመለስ በቀር በኢጣሊያኖቹ ዳኝነት ሊከሰስ ፤ ሊያዝና ሊቀጣ የማይገደድ መሆኑን በውል እንዲያረጋግጡለት ካደረገ በኋላ አብሮአቸው ምፅዋ ገባ ።

ኢጥርስ የኢጣሊያኖችን ፍላጐትና ዕቅድ በሚገባ ከተረዳ በኋላ ለራስ አሉላ የሚከተለውን ደብዳቤ ጻፈላቸው ።

"ይድረስ ለክቡር ራስ አሉላ
ዘውእቱ ቱርክ ባሻ ።

መድኃኔ ዐለም ሰላምና ፍቅር ያውርድልዎ ፤ የዮናታን ጋሻ በክንድዎ ይሁን ። ምናልባት ታሪክ አላነበቡ ይሆናል እንጂ ፤ ፈረን

ጅና-ቁንቁን አንድ ናቸው ። ቁንቁን ከትል ሁሉ ያንሳል ። ነገር ግን ታላቁን ግንድ በልቶ አድርቆ ይጥለዋል ።

እነዚህም ጣሊያኖች መጀመሪያ በንግድ ጥቂት በጥቂት እየገቡ የሰውን አገር ይወርሳሉ ። ስለዚህ አሁን ቶሎ ይደብድቧቸው ፤ አለዚያ አገርዎ መጥፋቱ ነው ።

አሁን እነሆ በምሳሌ እጽፍልዎታለሁ ፤ ዛፍ ሳያድግ በእግር ጣት ይነቃነቃል ፤ ከአደገ በኋላ ግን ብዙ መጋዝና መጥረቢያ ያስፈልገዋል ። እንደዚሁም ሁሉ የአሞራ ግልገል ከንፉ ሳያድግ የስድስት ዓመት ልጅ ከዛፍ አውርዶ ሲጫወትበት ይውላል። ክንፉ ከጠነከረ በኋላ ግን ከሰው እጅ ሥጋ ነጥቆ እስከ አየር ይወጣና የሚያገኘው የለም ።

እንደዚሁም እነዚህ ጣሊያኖች ናቸውና ለአገርዎ ፥ ለግዛትዎ ፥ ለጠጅዎ ፥ ለሎሚዎ ፥ ከሁሉም ይልቅ ለታላቁ ክብርዎ ይሞክሩ ። እኔ ያለኝን ምክር ነገርኩዎት ።ጥይትና ካባ ምንጣፍ ጥሩ የሆነ ጐራዴ ስድጀልዎታለሁ ። የኢትዮጵያ አምላክ ከእርስዎ ጋር ይሁን አሜን ።

ቅኑይ ለፍቅርከ
ጴጥሮስ ኢትዮጵያ
ጥር 10 ዘን 1888
ተጻፈ ምፅዋ ።

ራስ አሉላ ፥ ይህ ደብዳቤ ከደረሳቸው በኋላ ከኢጣሊያኖች ጋር ጦርነት መግጠም የማይቀርና አስፈላጊም መሆኑን ከተረዱት በኋላ ሠራዊታቸው በጊንዳዕና በአይለት አካባቢ እንዲሰፍር ትእዛዝ ሰጥተው ምፅዋ ለሰፈረው የኢጣሊያ ጦር አዛዥና ለጴጥሮስ የሚከተሉትን ደብዳቤዎች ሰደዱላቸው ።

የተላከ ከራስ አሉላ
ዘውእቱ ቱርክ ባሻ
ይድረስ ወደ ጀኔራል ጅኒ ።

እጅጉን እንዴት ሰንብተሃል ፤ እኔ ደኅና ነኝ እግዚአብሔር ይመስገን ። ከባሕረ ኤርትራ ወዲያ ማዶ የአንተ አገር ነው ።



ከእርሱ ወዲህ ግን ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የኛ ነው ። ስለምን ነው ለንግድ እያላችሁ ሰዉን እየአደራጃችሁ የምታመጡ ይህነን ወሬ ጃንሆይ የሰሙ እንደሆነ ታላቅ ጠብ እንደሚሆን የታወቀ ነውና ሠራዊትህ ከምጥዋ አሰብ እንዲመለስ ይሁን ፤ አለዚያ ውርድ ከራሴ ።

ተጻፈ ጥር 1879 አሥመራ ከተማ

ይድረስ ለወንድሜ ለወዳጄ እውነተኛ

የሐበሻ ልጅ ጴጥሮስ

እንዴት ሰንብተሃል ፤ ጥር 10 ቀን የተጻፈ ደብዳቤህ ደርሶኛል ። የእግዚአብሔር ምክር ደረሰኝ ። ጊንዳእ የነበረውን ሠራዊቴን ዛሬ ሌሊት ስሐጢ እንዲሔድ አዝዣለሁ ። እኔም ቶሎ እነሣለሁ ፥ እንኳን መካረ አግኝቼ ለብቻዬ እንኳን በጦርነት አልታማም ፤ የጻፍክልኝንም ደብዳቤ የእኔን ጨምሬ ወደ ጃንሆይ ስድጀዋለሁ ። የላክልኝ ዕቃም ሁሉ ደርሶኛል ።

እግዚአብሔር ወሮታህን ይመልስልሃል ። አሜን

ጥር 18 79 አሥመራ ።

ምንም እንኳን ፥ ራስ አሉላ ጴጥሮስ በላከላቸው ማስጠንቀቂያ መሠረት ለጣሊያኑ ጦር አዛዥ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ቢጽፉና ሠራዊታቸውን ቢያዘጋጁም ጸሐፊያቸው ጠንቃቃ ባለመሆኑ ለጴጥሮስ የተላከውን ደብዳቤ ለጀኔራል ጅኒ ከተጻፈው ደብዳቤ ጋር በአንድ ፖስታ ውስጥ አስገብቶ ላከው ።

ጀኔራል ጅኒ የተላከለትን ፖስታ ቀዶ ሁለት ባለማኅተም በአማርኛ ቋንቋ የተጻፉ ደብዳቤዎች አወጣና ሁለቱም ደብዳቤዎች በኢጣሊያ ቋንቋ ተተርጉመው እንዲሰጡት ለጴጥሮስ ላካቸው።

ጴጥሮስም ለእርሱ የተጻፈለትን አስቀርቶ የጀኔራሉን ደብዳቤ ብቻ ተርጉሞ ቢልክለት ፥ ጀኔራል ጅኒ ጴጥሮስን አስጠርቶ ፥

"ተርጉመህ እንድትሰጠኝ የላኩልህ ሁለት ደብዳቤዎች ነበሩ አንዱ ወዴት ሔደ ?" ብሎ ጠየቀው ። ጴጥሮስም ፥

“አንዱ ከዘመዶቼ የተላከልኝ የኔ ነው” ብሎ ይመልስለታል።

“ክፉ ነገር የሌለበት ከሆነ አላየኸና እመልስለሃለሁ” ይላል ጀኔራሉ ።

“ለእርስዎ ከዘመዶችዎ የሚላክልዎትን ደብዳቤ ያሳዩኛልን?” ብሎ ያን ደብዳቤ ከፊቱ ብጭቅጭቅ አድርጐ ቀዳዶ ጣለው ። ጀኔራሉም ተናደደና ጴጥሮስን አስይዞ አሳሰረውና ተቀዶ የተበታተነውን ወረቀት ቁርጥራጭ አሰሰቀመና አገጣጥሞ አስነብቦ ቢያስተረጉመው ራስ አሉላ ለጦርነት የሚዘጋጁ መሆናቸውን ይረዳዋል ። ከዚያም በኋላ እርሱም በበኩሉ የጦር ሠራዊቱን ማዘጋጀት ይጀምራል ።

ራስ አሉላም የኢጣሊያኖችን ዝግጅትና ከምፅዋ ወጥተው ወደ አሥመራ በሚወስደው መንገድ በሰሐጢ አካባቢ መስፈርና እርድ መሥራቱን እንደ ሰሙ ቀጥሎ ያለውን ሁለተኛ ደብዳቤ ጻፉለት ።

የተላከ ከራስ አሉላ ዘውእቱ ቱርክ ባሻ

ይድረስ ለጀኔራል ጀኔ !

ለጤናህ እንደምን ትሆናለህ ፤ እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ ።እንግሊዞች በጠባቂነት እንዲቆዩበት ብንፈቅድላቸው ምፅዋን ለእናንተ አሳልፈው በመስጠታቸው አዝነናል ። እናንተ ደግሞ ምፅዋንም ዐልፋችሁ ወደ ላይ መዝለት መጀመራችሁን ሰምቻለሁ ። ሀገራችንን ለመያዝ ከሆነ የመጣችሁት ከእሬት የመረርን ነንና እንቀመስም ። የሠፈራችሁበት ቦታ የኢትዮጵያ መሬትና ግዛት መሆኑን እምነህ ከንጭፍራህ ለቀህ እንድትወጣ በንጉሥ ነገሥት ዮሐንስ ስም አሳውቅሃለሁ ”...

ለዚህ ደብዳቤ የተላከላቸው መልስ ባለመኖሩ ራስ አሉላ ወደ ጊንዳዕ ወረዱ ።



## ጊንዳዕ

ጊንዳዕ የምትባለው መንደር በአሥመራና በምፅዋ መካከል ትገኛለች ። ዙሪያዋን በተራራዎችና ኮረብታዎች የተከበበችው ጊንዳዕ በመካከሏ ታላቅ ወንዝ አላት ። ከጥቅምት እስከ መጋቢት መጨረሻ ድረስ በቀይ ባሕር የአየር ጠባይ ትወረርና ዝናብና ልምላሜ ይሸፍናታል ። የአዝመራዋ ወቅትም እነዚሁ ወራቶች ናቸው ። ከሚያዝያ እስከ መስከረም ድረስ ባሉት ወራት ደግሞ የጊንዳዕ የአየር ጠባይ እጅግ የሚሞቅና የሚያቁነጠንጥ ነው ። ይሁን እንጂ የቀይ ባሕርን የአየር ጠባይ በትክክል ለማወቅ ስለሚያስቸግር ፤ የቆላውም የደጋውም አየር ጊንዳዕን እንዳመቻቸው ይሻሙዋታል ።

የጊንዳዕ መንደር እየተስፋፋችና እየደመቀች የሔደችውም ፣ ራስ አሉላ ጠቅላይ ሠፈራቸውን አሥመራ ላይ አድርገው ከምፅዋ ጋር የጠበቀ የንግድ ግንኙነት ከመሠረቱ በኋላ ነበር ። መንገዱ ተጠርጎ ፣ አራዊቱ ከአካባቢው ተባርሮ ፣ ወስላታ ነጋዴዎች እንዳያስቸግሩ ጸጥታው በወታደር እንዲከበር ከተደረገ በኋላ ፣ ጊንዳዕ እየተስፋፋች መጥታ ነበርና ፣ ራስ አሉላ ከነሠራዊታቸው ጊንዳዕ ሲገቡ ነዋሪዎቹ በዕልልታና በሆታ ተቀበሏቸው ። ልባዊ የሆነ መስተንግዶም በጊንዳዕ ሕዝብ ስም ሽማግሌዎች አቀረቡላቸው ።

ራስ አሉላ ፣ በካኪ ልብስ ላይ ለስ ነጠላ ደርበው ከበቅሎዋቸው ወርደው ከተዘጋጀላቸው ድንኳን ሲገቡ ፣ አሽከር በገበታ ውሃ ይዞ ገባና እግራቸውን አጥቦ እንዳበቃ የግራ እግራቸውን አውራ ጣት ስሞ ዕቃውን ይዞ ሲነሣ ፣ “ተባረክ እንጀራ ይውጣልህ” ብለው መረቁት ።

እጋፋሪውም የጊንዳዕን ሽማግሌዎች እያስገባ እጅ ማስነሣት ሲጀምር ፣ ከቆሙት ሽማግሌዎች ራስ ገናድ አእምር የሚባሉትን አዛውንት ጠቀስ አድርገው ሰላምታ ሰጡዋቸውና እንዲቀምጡ በእጃቸው ወንበር አመለከቱዋቸው ።

የጊንዳዕ ሽማግሌዎች እጅ እየነሡ ከወጡ በኋላ ራስ ወደ ገናድ ዘወር ብለው ፣

"የዘንድሮው ወራት ማለፊያ ዝናም የሰጣችሁ ይመስላል፣ አገሬውስ በሚገባ አርሷል?" ብለው ጠየቁዋቸው ። ገናድ አእምር ተንሥተው ሊናገሩ ሲሉ ራስ ካስቀመጡዋቸው በኋላ ፣ "ልምላሜው ማለፊያ ነው ፤ ሕዝቡም አርሷል ፤ የእርስዎ መምጣት ደግሞ ያጠግበናል፣ ያስደስተናል ፣ ግን የዛሬው አመጣጥዎ በድንገት ስለ ሆነብን የተገኘውን ቤት ያፈራውን ነው ያመጣነው" አሉ ።

ራስ ቀበል አደረጉና ፣ "የዛሬው አመጣጤ በድንገት የሆነው አስቸኳይ ጉዳይ ስለ አጋጠመኝ ነውና ፣ የአገሩ ሽማግሌዎች እንዲሰበሰቡ ይሁን ፤ የማነጋግራቸው ጉዳይ አለኝ ። ቤት ያፈራውን ያህል በማምጣታችሁም ፣ የሚታየው ማሰባችሁ ነውና እግዚአብሔር አዝመራችሁን ይባርከው ። ውለን ማደራችንም ስለማይቀርና ሠራዊትም ገና የሚመጣ ስለሆነ የሚቻላችሁን ያህል ስንቅ እንድትረዱ" አሉ ራስ ።

"ምን ከፉን ፤ የሚቸግረን አይሆንም ! ይዘጋጃል" አሉና ገናድ አእምር ተሰናብተው ወጡ ።

ወዲያው እጋፋሪው ገቡና ፣ "ግብር ተዘጋጅቷል ጌታዬ" ብለው አስታወቁ ።

"መኳንንቱና ሽማግሌዎቹ ሁሉም ገብተዋል?" አሉ ራስ ።

"ሁሉም ገብቷል ፤ ተዘጋጅቷል" አሉ እጋፋሪ ።

"ለሠራዊቱስ በቂ ድግስ ተደግሷል?" አሉ ራስ ።

"እምን በቂ ነው ፣ ከታሰበበትና ሥራው ከተጀመረ እኮ ውሎ አድሯል ! ጌታዬ ምን ጠፍቶ ፤ ከሐማሴን ፣ ከአካለ ጉዛይና ከሠራዬ በቂ እህልና ሠንጋ እንዲመጣ ተደርጓል" አሉ እጋፋሪ ።



ራስ አሉላ ፣ ከድንኳን ወጥተው ገሚሱ በግር ፣ ገሚሱ በቅጠል ተሸፍኖ ወደ ነበረው ግብር ቤት ገቡና መኳንንቱ ፣ የጦር አበጋዞቹና ሽማግሌዎቹ እንደየማዕረጋቸው ከተቀመጡ በኋላ ግብሩ ቀጠለ ።

"ለእንግዶቹስ ተልኮላቸዋል?" ብለው ራስ እጋፋሪውን ጠየቁ። "ደከምናል እንረፍ ብለው ከድንኳናቸው ተኝተዋል" አለ እጋፋሪ ።

"እንግዲያው አስፈላጊውን ሁሉ እዚያው ላኩላቸው፣አንድም ነገር እንዳይቀርባቸው" አሉ ራስ ።

ግብሩ እንደ ገባ ፣ አንድ አዝማሪ በዳሱ መካከል ቁመው በዘለሰኛ ፣

"ነጮችና ግብጾች የኛ እንግዶች ናቸው
ያሟውታችዋል ጉራዴህ ለምዷቸው ።
ነጭ በሬ አይግጥም ወይ ገብቶ ባገርዎ
በጦር በጉራዴ ምነው መጣልዎ
ያን አጭር ጦርህን እሉላ ስጣቸው
ረጅም ነውና ነጮች ሽመላቸው
የመጡት እንግዶች እውን ሰዎች ናቸው
በማላውቀው ነገር በል እስቲ አልማቸው
መጥተዋል ይላሉ ነጮች ብርድ ይዟቸው
ከጢስ ቤት አግብተህ ዕወቅ አፍናቸው
ከቤትህ ያሉትን ነጮች ጠብቃቸው
እንዳያዝኑ ባንተ ገረድ ጢስ አጥናቸው
ፈረንጆች መጥተዋል የለህም መስኳቸው
እባክህ እሉላ መዘህ አሳያቸው ።
አትችልም ይላሉ ጦር ሰብቀህ መወርወር
እየመሰከሩ ግብፆች ሔደው ካገር

ኩሬት ላይ የታየው ጉራደህ እንደ ጫይ
በለቱ አልበረደም ነገም ነገም ጫይ"

ብለው ሲያንጎራጉሩ ፣ ራስ ከፊታቸው የነበረውን ዋንጫ ል
ቸው ። ፊታቸውን አዙረው ጨለጡትና ዋች ባለ ሰገት ወዲያ
ወዲያ እየተወራጩ በፉከራ ፣

"አይደፈርም ያንተ በራፍ
እንበሳው ከንድህ ሳይታጠፍ
ምዕዋ ላከው ጀግናው ይውረድ
የባሕር መጤው ይፍራ ይራድ
ምጽዋ ጉራዴ ይውጣ ካርቱ
በባሕር መጤው ይታይ ሰለቱ
የጉራዴህን አርት ሰውጠው
ምፅዋ ሞልቷል የባሕር አዘው
ሥርግ ደግሳ ያበሻ እናት
የነጭ አስከሬታ ልታይ ሲያምራት
ላከች አሉላን እንዲያወራርደው
ተድአሊ ወርደህ ገብተህ ጉማምደው
ጉዞ ጀምረዋል መጥቷዋል ወደላይ
ያንተን ጉራዴ ነው በሬ ሊያይ
አስተምራቸው የጦር ውርወራ
ሐድ አሳያቸው የጀግኖች ሥራ
ግብፁ ያየውን ጣሊያኑም ያውራ
የጀግኖች ጀግና የጀግኖች አውራ
እንገብግቦኛል የውሃ ጥም
ዋንጫውን ሳልደግም ዛሬ አልወጣም!"

ራስ አሉላ እንደገና ዋንጫቸውን እንሥተው ሰጡ ።

ሰብሐት ከተባለ በኋላ ፣ መኳንንቱና ሽማግሌዎቹ እጅ እየ
ነሡ ወጡ ። ራስም ከእልፍኙ ወጥተው ወደ ድንኳናቸው ገቡና



አጋፋሪያቸውን ጠርተው ፣ "ወደ ማታ የጦር አለቆቹ እንዲመጡ
በር በሩንም ወታደር እንዲጠብቅበትና ጥንቃቄ እንዲደረግ ንገር"
አሉና ትእዛዝ ሰጡ ።

ራስ አሉላ ወደ ምፅዋ እየተመላለሱ ልዩ ልዩ የሸቀጣ
ሸቀጥ ዕቃዎች የሚያመላልሱ ብዙ ባለሟሎች ነበሩዋቸው ።
ከእነርሱም አንዱ ከብርም ወልደኪኤል ነበር ። ከብርም በእ
ሥመራ ፣ በከረን በአይለትና በምፅዋ የታወቀ ነጋዴ ነበር ። ተሚ
ዋች ፣ በየቦታው የሚገባና የሚወጣ ፣ ከትግርኛ ቋንቋ ሌላ ዐረብኛ
አሳርፉ የሚችል ፣ ከዐረብኛና እንግሊዝኛም ቋንቋዎች በቀጥር
ያህል ቃላት ጣል ጣል ማድረግ የሚችል ነበር ። ራስ አሉላ ጊን
ዳዕ በገቡበት ማግሥት እርሱም ከምፅዋ ጊንዳዕ ገባና ወደ ሠፈ
ራቸው ሔዶ ራስን እጅ ለመንሣት እንዲችል አጋፋሪን ጠየቀ ።

"እንዴ በበቀደም አሥመራ ላይ በቆይታ አነጋገርኻቸው
የለም? ዛሬ ደግሞ ምን አገኘህና ንገሩልኝ ትላለህ?" አሉ አጋፋሪ ።

"ውሉ የማያድር ጉዳይ አለኝና ንገሩልኝ" አለ ከብርም
ድርቅ ብሉ ።

"በል ጠብቅ ፣ የሚመች ከሆነ ልንገራቸው" አሉና አጋፋሪ
ወደ ራስ ድንኳን ገብተው ነገሩ ።

"የኔ ወዳጅ ከብርም መጣ? በል አስገባውና ሰው ከልክ
ልልኝ" አሉ ራስ ።

ከብርም ገብቶ ሰጥ ብሉ እጅ ሲነሣቸው ፣

"ወዳጄ ከብርም ደኅና መጣህ!" አሉት ።

"እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ" አለ ከብርም ።

"የሔድክበት ጉዳይስ ተሳካልህ ?"

"ጌታዬ እንዳዘዙኝ ምፅዋ ወርጄ ወዳጆቼንና ሸቀጣ ሸቀጥ የም
ወስድላቸውን አበሾች ግሪኮችና ዐረቦች ጠይቄ እንዳረጋገጥኩት
ወደ እርስዎ የመጡት ጣሊያኖች ልዩ ተመልካቾች ናቸው ።

አንዱ ፒያና የሚባለውማ ሻለቃ ነው ። ምፅዋ ካሉት የኢጣሊያ ወታደሮች የእርሱ ጭፍሮችም አሉበት ። አንዱ ደግሞ የመቶ አለቃ ነው ። ሐሳባቸውም አገሩን ለማየትና ለማጥናት ካመቻቸው ደግሞ እርስዎን አታለው ወደ ምፅዋ ወስደው ፣ ከአለቃቸው ጋር ካገናኙዎ በኋላ ፣ መርከባቸውን እንዲመለከቱላቸው ከመርከብ ያስገቡዎትና ከዚያም ወደ አገራቸው ሊወስዱዎ ነውና ይጠንቀቁ'' አላቸው ።

"ይህን ነገር ከታመነ ሰው ነው የሰማኸው'' አሉ ራስ በተረጋጋ መንፈስ ፤

"ጌታዬ ይህ ነገር እውነት ነው ። ያ—ግሪክ ወዳጅዎም በምሥጢር ንገር ብሎኛል ። ካላመኑኝም አንድ ታማኝ ሰው ይስጡኝና ይዘው ልውረድ ፤ ለኔ ከነገሩኝም ሰዎች ጋር ላገናኘው'' አላቸው ።

"ለታማኝነቱ ካንተ የበለጠ ታማኝ የለኝም ፤ ጣሊያኖቹ ምፅዋ ከሠፈሩበት ጊዜ ጀምሮ እርምጃቸው አሳሳቢ ስለሆነብኝ ነበር አንተን የላክሁት ። ግን አንተን አሳስተው ከወዳጆቻችን ጋር እንዳያጣሉን ወይም ራሳቸው ጣሊያኖቹ ከኛ ላይ ጉድፍ ለማግኘት አስበው በእጅ አዙር የፈጠሩት ተንኮል እንዳይሆን ብዬ ነው እንጂ ፣ አንተንማ የማላምንህ ቢሆን ኑሮ መጀመሪያውንስ መች እልክህ ነበር ? ለመሆኑስ ተደአሊ ላይ የሠፈረው ጦር ምን ይሠራል?'' አሉ ራስ ።

"ውሃ ይቆፍራሉ ፤ ግንብ ይሠራሉ ፤ ምሽግ የሚሆንም ቦታ ያዘጋጃሉ'' አለ ከብሮም ።

"የወታደራቸውስ ብዛት ምን ያህል ይመስልሃል ?''

"በግምት እስከ ስድስት መቶ ይደርስ ይሆናል ።''

"በተድአሊ ያለው ጦር አሰፋፈሩስ እንዴት ያለ ዘርፍ አለው?''

"ከወንዙ ማዶ ያለው ከሦስት ቦታዎች ላይ ሠፍሯል ፤ ከወንዝ ወዲህ ያለው ግን በሁለት ሥፍራዎች ላይ ነው የሠፈረው ።''



"ሕዝቡንስ ያስቸግሩታል ?''

"ወደ ከተማው የሚገባውን በየቦታው እየያዙ ለምን መጣህ? ማን ፈቀደልህ? ቀረጥ ክፈል ፣ ዋስ ጥራ እያሉ ያስጨንቁታል ።''

"አንተንስ አልያዙህም ?''

"ስንገባ ይዘው መርምረው ለቀቁን ፤ ስንወጣ ግን ብዙም አላስቸገሩንም ።''

"እነዚሁ ጣሊያኖችስ ከጦር አለቃው ጋር ነው የነበሩት ?''

"እንደ ሰማሁት ማሊቢኒና ሁለቱ ረዳቶቹ በኋላ ነው የተላኩት ፣ ሻለቃውና የመቶ አለቃው ግን ከወታደሩ ጋር ነው የመጡ ። ምፅዋ ብዙ ቆይተዋል።''

"መልካም ነው ፣ የኔው ስጦታ እንኳ ፍሬም የለው እምላክ በስፈው ይስጥህ'' ብለው ሲያጨበጭቡ አጋፋሪው ገቡ ፡ "በል እባክህ አጋፋሪ ለከብሮም ማረፊያና የሚገዛው ዕቃም ስላል መቶ ብር ስጠው'' አሉ ።

"እነዚህ ሰይጣኖች እኔን ለማታለል መጡ ? ሀገሬን ለመበለልና ለመያዝ መጡ ? ሀገሬን ለመውረር ወገኖቼን ባርያ አድርገው ለመግዛት መጡ ? የእነርሱ ሃይማኖት ትርጉም ይህ መሆኑ ነው ? ሰውን እየሰበኩ አገር መስለል ፣ ሕዝብ ማታለል ፣ ሕዝብን ባርያ ማድረግ ይኸው ነው ሃይማኖታቸው ? በጂ ገብተዋል ፣ ያታላይነት ዋጋቸውን ያገኛሉ ። ደማቸው ደመ—ከልብ ነው ። የነደደው ልቤ በእነርሱ ደም ይርሳል'' እያሉ ሲበሳጩና ሲተክዙ ቆዩና ሲያጨበጭቡ አጋፋሪው ገባ ።

"እነዚህ ጥልያኖቹ ቅድም ወደ አደን ሔደን እንምጣ ብለውኝ ነበር ሔደዋል ?'' አሉና ራስ ጠየቁት ።

"አዎ ሔደዋል ጌታዬ !''

"ወታደሮች ላክባቸውና በፍጥነት አስመጣልኝ ! እነዚህ ሰይጣኖች አገሬን ማየት የለባቸውም ! መኳንንቱንም አስገባ !'' አሉ ራስ ።

ኢንትራዉ ወጣና መኳንንቱን አስገባቸው ። ራስ እንዳዘኑ እንደ ተከዙ ነበርና መኳንንቱም ነገሩ ከበዷቸው እንደ ተጨነቁ ነበሩ ።

"ወዳጅነታችሁን ፈልገን መጣን ያሉት እንግዶች የመረሩ ጠላቶቻችን ሆነው አገኘናቸዋል። ጣሊያኖች ደንከልንና ምፅዋን ብቻ አይደለም የተመኙት ፤ መላዋን አገራችንን ነው ። በተድአሊ አካባቢም ምሽግ መሥራት ቀጥለዋል ፤ እንግዲህ በነገሩ ምክሩበትና የታያችሁን ያሳባችሁን ንገሩኝ" አሉዋቸው ።

የጦር አለቆቹና መኳንንቱ ለጥቂት ጊዜ ያህል እርስ በር ሳቸው ሲተያዩ ቆዩና ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ፤

"ያልተረጋገጠ ነገር ይዞ ወደ ጌታ ፊት መቅረቡን ጠል ተነው ነው እንጂ ፤ ጣሊያኖቹማ ወደላይ ለመዝለቅ ማሰባቸውን ሰምተናል ። አሁንም እንደሆነ ፤ ትድም አዝማሪዉ ፤

"ያን እጭር ጦርህን አሉላ ስጣቸው

ረጅም ነውና ነጮች ሽመላቸው"

ብሎ ሲያጉረመርም ነገሩ ከልቤ ገብቷል ። ነገሩ ከቀለ ካደረ ይጉመዝዛል ፤ በቶሎ ይላኩንና ማንነታችንን እናሳየው" ብለው ተናገሩ ። ከእርሳቸው ቀጥለው ደግሞ ባሻይ በዙሩ ፤

"ንቆን ሀገራችን ውስጥ ገብቶ ፤ እግሩን ዘርግቶ ማን አለብኝ ብሎ ተቀምጧል ። ከየቤታችን እስኪገባ ነው የምንጠብቀው ? ወንድነትና ቆራጥነት ሳያንሰን ፤ ብዙ ጀግና ወታደር እያለን ምንድን ነው ይህ ሁሉ ጣጣ ?ይላኩንና ልኩን እናሳየው" አሉ።

"እንኳንስ ሀገር የሚቀማ ጠላት ሲመጣ ይቅርና ለክርስትና ድግስ እንኳ ምክር ያሻዋል ። ዝግጅትና ጥንቃቄም ያስፈልገዋል ። ነገሩንም በያገሩ እናስማና ሠራዊቱ ይዘጋጅ" አሉ ዘጊዮርጊስ ።

ደጃዝማች ኃይለሥላሴም ቀጠል አድርገው ፤ "እኛ እስክ ንመካከርና እስክንዘጋጅ ያንድ ፊታውራሪ ጦር ይላክበትና ጉል በቱን ይሞክረው ፤ ካልሆነም ሁላችንም ወርደን እናሳየዋለን" አሉ ።



"ጥናው ሐሳቡን ደርሰህበታል ፤ ገፍቶ ከመጣ በሚገባ መ ከት እንድንችል ሠራዊታችንን ማስከተት ፤ ስንቅ ማዘጋጀት ያስ ፈልገናል ። እስተዚያው እርምጃውን ለማደናቀፍና ጉልበቱን ለመ ፈተን የባሻይ ተድላ ጦር ይዝመትበት" አሉ ራስ ።

ወዲያው ባሻይ ተድላ እመር ብለው ተነሡና ፤ "እዘዘኝ ጌታዬ! እዘዘኝ ዛሬውኑ ልውረድና ላሳየው" አሉ ።

"አምንሃለሁ ከነገ ጀምረህ ተዘጋጅ" አሉ ራስ ፤

"እነዚህ መሠሪዎቹ እንግዶችስ ለምን ዝም ይባላሉ ?" ብለው ዘጊዮርጊስ ጠየቁ ።"ራሴ መርምሬ ፤ ራሴ ከታላቸው እውነቱን እስካገኝ ድረስ ብዬ ነው እንጂ ፤ አገሬን የደፈሩ ጠላቶቼን እንዴት ዝም እላቸዋለሁ ?" አሉ ራስ አንገታቸውን እያወዛወዙ ።

የጦር አለቆቹንና መኳንንቱን ተገቢውን ዝግጅት እንዲያ ቀላጥፉ መክረውና አስጠንቅቀው ሲያበቁ ፤ ራስ አሉላ ጊንዳዕን ከከበቡዋት ተራራዎችና ኮረብታዎች መካከል ለጦር ሠፈርነት የሚያገለግል ኮረብታ ለመምረጥ ወጡ ። በመጀመሪያ በስተምሥ ራቅ በኩል ካሉት ከፍተኛ ኮረብታዎች ላይ ወጡና የቀይ ባሕ ርን አቅጣጫ ተመለከቱ ። የደግስ ሜዳ ፤ የአይለት መንደር ወለል ብለው ይታያሉ ።

እዎ ! በጥንቱ ዘመን ንጉሥ ኢዛናም ደብረ ቢዘን ላይ ሆነው ነበር ቀይ ባሕርንና አካባቢውን ይመለከቱ የነበረው ! ከዚያ በፊትም ሆነ በኋላ ፤ የኢትዮጵያ ነገሥታት ያን አካባቢ ያን በዚያች በዓት በአሉላ ዐይን—ሕሊና ውስጥ ገብቶ የነበረ ውን አካባቢ እንደ ዐይን—ብሌናቸው ይጠብቁት እንደ ነበሩ ትዝ አላቸው ። በአጼ ሠርፀ ድንግል ዘመን መንግሥትም ቱርክ በዚያ አካባቢ ገብቶ እስከ ደባርዋ ዘልቆ የገባበትን መንገድ ሁሉ ተመለከቱት ። ደባርዋ ድረስ የገባውንም የቱርክ ጦር ዕቁባ ሚካኤል የተባለ ጀግና ሰማኒያ ራሱን ሸምቆ በቱርክ ጦር ላይ አደጋ ጥሎ እስከ ቀይ ባሕር የነዳበትን ዳገት ፤ ቁልቁለ ትና ሜዳ ተመለከቱት ። ዕቁባ ሚካኤል የቱርክን ጦር በነዳበት ቁልቁለት እርሳቸውም የጣሊያኖችን ጦር እየነዱ ምፅዋ ባሕር ውስጥ ሲጨምሩት ታያቸው ።

ከጊንዳዕ በስተምሥራቅ ከ ጊገኙት ኮረብታዎች ተመልሱና በስተምዕራብ ከሚገኙት ኮረብታዎች ላይ ደግሞ ወጥተው አካባቢውን ተመለከቱ። በስተምሥራቅ በሚገኙት ተራራዎች ላይ ተመልካች ማስቀመጥና ፣ ከአይለትም ሆነ ከማይጭሆት አካባቢ ወደላይ የሚወጣውን ጠላት ከዳገቱ ላይ ጠብቆ ማጥቃት እንዲቻል ስልት ካወጡ በኋላ ፣ ምናልባት በሌላ አቅጣጫ ተጉዞ ላይ ታይ ጊንዳዕ የሚገባ ጠላት ቢመጣ ደግሞ በስተምዕራብ ከሚገኘው ኮረብታ ላይ ሆኖ ለመጠራረግ እንዲያመች ፤ እንዲያውም ከሐባብ የተነሣ ጠላት በስተሰሜን ፣ ከደግስ የተነሣ ጠላት ደግሞ በስተምሥራቅ በኩል በሚገኙት ረባዳ ቦታዎች ተረማምዶ ጊንዳዕን እንዳይዝ ለመከላከል ብቻም ሳይሆን ለማጥቃት ጭምር ምዕራባዊው ተራራና ኮረብታ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ተረዱ። የምዕራባዊው ኮረብታና ተራራ ሌላው ጥቅሙ ደግሞ በግራና ቀኝ ከሚገኙት ወንዞች ውሃ በቀላሉ ለማግኘት እንደሚቻልና ፣ ምናልባትም ወደ ኋላ ለማፈግፈግ ቢፈለግ ፣ ተራራ ለተራራ ተጉዞ አሥመራ መግባት እንደሚያመች አረጋግጠው ወደ ሠፈራቸው ሲመለሱ ፣ እነማሊቢኒ ከሔዱበት አደን ተመልሰው አገኙዋቸው።

ወዲያው ጣሊያኖቹ ወደ ራስ ድንኳን ገቡና ፣ "እንዴት ነው ነገሩ ?የእርስዎ ወዳጆችና እንግዶች መሆናችንን ወታደሮችዎ እያወቁ ፣ አውሬ ማደን ስንሔድ ከኋላችን ጥይት እየተኮሱና እየተሯሯጡ ደርሰው እያንገላቱ አመጡን ። እንዴት እንዲህ ያለ ድፍረት ይሠራል ?" አለ ማሊቢኒ ።

ከርሱ በባሰ ሁኔታ ተናዶ የነበረው ፒያና ደግሞ ፣ ንግግሩን ከማሊቢኒ ነጠቀና ፣"እንዴት ነው ባህላችሁ ? እንግዳ እንደ መጣ አክብሮ መቀበል ፣ ስንባብቶ ደግሞ ማዋረድ ! እንዚህ ያልሠለጠኑ አሽከሮችዎ ክፉ ያለ ድፍረት ፈጽመውብናል ። ምክንያቱን ሳይነግሩን መሣሪያችንን ቀምተው እያዳፉ ነው ያመጡን። ሁለት ጊዜ እንኳ በወድቅ ይጣጣቁብኝ ነበር እንጂ ለመርዳት አልሞከሩም ። እንደዚህ የመሳሰለ ተለዋዋጭ ጠባይ በመሬት ላይ ይገኛል ?እንደዚህ መዋረዳችንና መንገላታችንን ታላቁ መንግሥታችን ቢሰማው በሀገርዎ ላይ የሚደርስ ቅጣት ብርቱ እን



ደሚሆን እነዚህ ያልሠለጠኑ አሽከሮችዎ ሊገምቱት ይችላሉ ?" ብሎ ደነፋ ።

ራስ አሉላም ለዘብ ባለ አነጋገር ፣ "በክብር ተቀብለን ፣ በክብር አስተናግደን ፣ በክብር የምንሸኘውኮ በጠባይና በሥራው የታመነውን ነው ፤ እናንተ ግን...." ብለው ተናግረው ሳይጨርሱ ማሊቢኒ አቋረጣቸውና ፣"እኛ እንዴት ታማኞች አይደለንም? እንዴትስ የተከበርን አይደለንም ? ምንድነው የሚጐድለን እባክዎ? ራሳችንን ዝቅ አድርገን እዚህ ድረስ በመምጣታችን ነው እንጂ የተዋረድነው ምን የሚጐድለን ነገር አለ ?" አላቸው ።

"መንግሥታችን ኃያል ፣ ሕዝባችን የሠለጠነና ሀብታም ፣ በቆዳችን እንደሚያዩት የመላእክት ዘር የመሰልን ፣ በምን ምክንያት ይህ ሁሉ ክብራችን ይነካል ?" አለና ፒያኖም ጨፈረ ። ራስ አሉላም ከተረጋጋ መንፈሳቸውና አነጋገራቸው ንቅንቅ ሳይሉ ፣

"ለመሆኑ እናንተስ የማንብና የድልድይ ሥራ ጥበበኞች ነን ብላችሁ አገሬን ለማገልገል አይደለም የመጣችሁት?" ብለው ጠየቋቸው ።

"እኮ በዚህ አይደለም የተዋረድነው?" አለ ፒያኖ ።

"ተዋርደናል የምትሉት ይጣራል" አሉ ራስ ።

"ብዙ ምርመራም አያስፈልገውም ፤ ያዋረዱንን አሽከሮችዎን እናውቃቸዋለን ። አሁኑኑ ተገርፈው፣ አሁኑኑ መስቀል አለባቸው ፤ ያለዚያ ለተፈጸመብን ድፍረት አገርዎን በኃላፊነት እንጠይቃለን" አለና ፒያኖ ደነፋ ።

"ይህም ቅጣት አሁኑኑ ባይፈጸም ያውሮፓ መንግሥታት እንዲያውቁት የተደረገ እንደሆነ ከፍተኛ ችግር በአገርዎ ላይ ሊደርስ ይችላል" አለ ማሊቢኒ የፒያኖን ንግግርር ሲያጠቃልልለት።

"ለመሆኑ እናንተስ እውነተኞች የጥበብ ባለሙያዎች ብቻ ለመሆናችሁ አሥመራ ላይ በመስቀል እንደ ማላችሁልኝ ዛሬም ደግማችሁ ልትምሉልኝ ትችላላችሁ ?" ብለው ራስ ጠየቁ ።

“ከገርዎ ከገባን ወር እንኳ አልሞላንም፤ በየሳምንቱ መበቀል ጠፍቶት የምንባልበት ምክንያት አልገባኝም ። እንግዲህ ጎመት ብንቆይ ዓመቱን ሙሉ መስቀላችሁንና የቄሶቻችሁን እጅ ስንደበድብ ልንኖር ነው ?” አለ ፒያና በሚጠራጠር ስሜት ።

“እንደበትህን ተቆጣጠረህ ፣ ምላስህን አለዝበህ ብትናገር አይሻልህም?” አሉ ራስ ቆፍጠን ብለው ።

“ምን እንዳይመጣብኝ ፤ ከዚህ ሌላ መቼስ እጄን እያሲዙኝ ፤ እያሳሰሩኝ ምን እንሆናለን ?” አለ ፒያናም እጆቹን እያወራጨ ።

“በውል እንድንነጋገር እነዚያ ደፋሮች አሽከሮችዎ በመጀመሪያ መያዝ አለባቸው” አለ ማሊቢኒ እርሱም እንደ ጓደኛው እጆቹን እያርገበገበ ።

“አሽከሮቼን የምቀጣው እውነተኞቹን እንግዶች ሲደፍሩና ሲያንገላቱ ነው” አሉ ራስ ቆጣ ብለው ።

“የእርስዎ እውነተኞች እንግዶች እንደ ምን ያሉ ናቸው?” አለ ማሊቢኒ በምፀት አነጋገር ።

ራስም እንገታቸውን እያወዛወዙ ፣ በአመልካች ጣታቸው ወደ መሬት እያመለከቱ ፣ “የአገሬን የወገኖቼንና የኔን ወዳጅነት ከልብ የሚመኙ ፣ ከተንኮልና ከማታለል ነጻ የሆኑ ናቸው የኔ እውነተኞች ወዳጆቼና እንግዶቼ” አሉት ።

“ለሀገርዎ ሕዝብማ ብለን ነውኮ መጥተን ይህ ሁሉ የደረሰብን” አለ ፒያና ።

“ለጉጃም ሕዝብ ያን ድልድይ ልሠራ ስሔድ ንጉሥ ተክለ ሃማኖት አክብረው ነው የተቀበሉኝ ፤ ምክንያቱም ለሕዝባቸውና ለወገናቸው የሚያስቡ በመሆናቸው ነበር” አለ ማሊቢኒ ራስ አሉላን በአሽሙር ሊሰድብ ፈልጎ ።

“ጉጃም ገብተህ አንድ ድልድይ በመሥራትህ ተመክተህክ ነው ፣ ዛሬ ይህን ሁሉ ድፍረትና ተንኮል ለመሥራት የመጣኸው” አሉት ።



“ምነው ምለንልም፤ እንዴት እንደዚህ ይናገራሉ ?” አለ ማሊቢኒ ።

“ዛሬስ ደግመህ ትምላለህ?” አሉት ራስ ።

“ከእንግዲህ በኋላስ መግለ የሚገባዎ እርስዎ ነዎት ፤ እኛስ ምለንም ለመልካም ተግባር መጥተንም አልታመንም ፤ እኛም ልና ምነዎ እንችላለም” አለ ፒያና እጁን ወደላይ እየወረወረ ።

በዚህ ጊዜ የታላቁ ጀኔራል ትዕግሥት ወደ ቁጣ ተለወጠና ፣ “ዝምበል አገሬን ለመሰለል ፣ እኔን ለማታለል ነው የመጣችሁት ፤ ከይሁዳ የከፋችሁ ከዳተኞች ናችሁ ። አንተ ራስህ ምጥዋ ከሠፈረው ጦር ጭፍሮች አሉህ አይደለም ? ማስረገህም ቀላል ነው ፣ ይህን ትክዳለህ?” ብለው አፈጠጡበት ።

“ልክ አይደለም ፣ የጦር አለቃም አይደለሁም” አለ ፒያና ተደናግጦ ።

ራስ አሉላ ፣ የእርሱን ሁኔታ ሲመለከቱ ደግሞ በይበልጥ ጦፉ ። ማሊቢኒም የራቱ ውሃ እየጠወለገ ፣ ትላቱ እየነጣ እየነጣ ሔደ ። ሌሎቹም የድንኳኑን ጣራና ግድግዳ መግመጥ ጀመሩ ።

“ዝምበል ቀጣሬ ! ሌላው ቀርቶ ወታደርነትህንስ እንኳ ለመካድ ትፈልጋለህ ? ጀግና ወታደር አይዋሽም ። ይህን ግወቅ ነበረብህ ፣ አንተ ግን ዋሾና አታላይ ነህ ፤ የአታላይነትህን ዋጋ ታገኛለህ ፤ እኔን ነው የምታታልለው ? አገሬን ነው የምትሰልለው ? ኢሥመራ ተወስዳችሁ ፍርዳችሁን ትቀበላላችሁ ፤ ወደ ምጥዋም ሔጄ አገሬን የደፈረውን አለቃህን መቀጣጫ አደርገዋለሁ!” አሉ ።

“ስሐጢን ሲያልፉ አይችሉም ፤ በዚያ የሠፈረው ጦራችን አያንቀሳቅስዎትም” አለ ፒያና እንደ ምንም ተንጠራርቶ ።

“አንተ ደንቆር የኢትዮጵያን ወታደሮች አታውቃቸውም ! እንደ ወፍ ይበራሉ ፤ እንደ አንበሳ ጠላታቸውን ይሰብራሉ ፤ ወደ ጠላታቸው ምሽግ ለመገሥገሥ ከቶ አያመነቱም ፤ የኢትዮጵያ ወታደር ትዕግሥቱ ሲያልቅ ጠላቱን ይሰባብራል ። ይህን ሳታውቅ

ነውና የመጣሽው ነገ ታገኝዋለህ" አሉ ራስ አሉላ ከፒያና ላይ እንዳፈጠጡ ።

"ጌታዬ ይህን ነገር በሚገባ እንዲጠነቀቁበት ያስፈልጋል ፤ ለሀገርዎ ለማበርከት ያሰብነው ልግትና ሀብት ሁሉ እንዲበላሽ ጠላቶችዎ የፈጠሩት ተንኮል ሊሆን ይችላልና ያስቡበት" አለ ማሲቢኒ ቁጣውና ማስፈራራቱ ሲያልቅበት ።

"ማንን ነው 'ጌታዬ' የምትለው እባክህ ! ጥቁር የነጭ ጌታ ሊሆን አይችልም!" አለ ፒያና ።

"ኢጋፉሪ ውሰደውና በእግረ ሙቅ ቀፍድድልኝ!!" አሉ ራስ በከፍተኛ ቁጣ ተውጠው ።

"እባክዎ ይህን ነገር ያስቡበት ፤ ከባድ ጥፋት በሀገርዎ ላይ እንዳያስከትል" አለ ማሲቢኒ ።

"ትላንት በቴዎድሮስ ላይ የደረሰው፥ ነገ ደግሞ በእርስዎ ላይ እንደሚደገም ይወቁ" ብሎ ፒያና እንደ ተናገረ አጋፉሪ እያዳፋ ወሰደው ።

"አይሄሂ! 'ቴዎድሮስ' አለ፣ መቼ በእሱ ርኩስ አንደበት የሚጠራ ስም ሆነና" ብለው አሉላ ራሳቸውን ነቀነቁ ፤ ተከዙ ።

"እዎ አዎ እውነቱን ነው ፤ አዬ ታላቁ ጀኔራል አዬ ጌታዬ የልብ ወዳጅትዎ ለመሆናችን ማስረጃው ይሄ ነው ። ሀገርዎ ጥፋት ላይ እንዳትወድቅ ይጠንቀቁላት ። ደግሞም በኛ ላይ የደረሰውን ሁሉ ዘርዝሬ መልእክተኛ ወደ ጀኔራል ጅኒ እንድሰድ ይፍቀዱ ልኝ" አለ ማሲቢኒ ።

ራስም በንቀት እየተመለከቱት አንገታቸውን ወደፊት ገፉ ገፉ እያደረጉ፥ "ለምጻሙ ጻፍለት ፤ ፈቅጄለሁ ። ሀገሬ ከጥፋት ላይ የምትወድቀው መርዛችሁን ካላረከስነው ነው ፤ የጣብያች ዕድል ነው በእናንተ ላይ የሚደርሰው" አሉና እንደገና ቆጣ ብለው፥ "አጋፉሪ እነዚህን ሁለቱንም ውሰድና በእግረሙቅ ቀፍ ድድልኝ" አሉ ። ማሲቢኒና መቶ አለቃ ሜይሾርከስም በእግር ብረት ታሰሩ ። ራስ ሁለቱን ያልታሰሩትን ጣሊያኖች አስቀርበው፥



"አይዟችሁ ፥ እነዚህ ሰይጣኖች ናቸው ያሳሳቷዋችሁ ። አትፍሩ ነገውኑ ወደ ዘመዶቻችሁ ሔዳችሁ ትቀላቀላላችሁ ። እባክህ አጋፉሪ ለስንቃቸውና ለልብሳቸው የሚሆን መቶ ብር ስጣቸውና ከሸኚ ጋር አድርገህ ነገ ወደ ምፅዋ ሰደዳቸው" ብለው ሲያዙ ጣሊያኖቹ መሬት እየሳሙ፥

"ጌታ ግራሴ— ግራሴ! ማርያም ግራሴ ግራሴ! እዜግሔር ይምጣልዎ ግራሴ" እያሉ እጆቻቸውን እያርገበገቡ መረቁ ።

"ለመሆኑ ፒያና ሻለቃ አይደለም" ብለው ራስ ሲጠይቋቸው፥ "አዎ ጌታ ! አዎ ነው" አሉ ሁለቱም ባንድ ቃል ።

"ለሰላ አይደለም የመጣችሁት ?" አሉ ራስ ።

"አዎ ለዚሁ ነው ይቅርብን ብንል አይሆንም ብለው ነው" አለ አንደኛዉ ጣሊያን ።

"ከመንግሥታችሁ ነው ወይስ የምጥዋው ጀኔራል ነው የላካ ችሁ?" አሉና ራስ ጠየቁ ።

"ከሮም ነው ፥ ሮማኖች የላከችን" አለ ሁለተኛዉ ጣሊያን ።

"በሉ አትፍሩ ወደ ዘመዶቻችሁ ሒዱ" አሉና አሰናበቷቸው ።

"በርስ በርሳችን ተከከር በር ከፍተን መንገድ መርተን አስገብ ተን ነው ይህችን አገር በእንግሊዞች ያስደፈርናት ። ከእንግዲህ ወዲያ ግን ማንም ጠላት አይረግጣትም ! እዛው ከባሕር ሳይወጣ ጉረሮውን ይታነቃል" አሉ ራስ በእግራቸው መሬት እየተመ ተሙ ።በዚያ ሁኔታ ላይ በነበሩበት ሰዓት ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ፥ ባሻይ በኩሩ ፥ ባሻይ ተድላና አቶ ዘጊዮርጊስ ገብተው ሲቆሙ "ተቀመጡ" አሉና ራስ በእጃቸው መቀመጫ አመለከቷቸው ። ቀጠል አድርገውም፥

"የመጡት ጣሊያኖች አታላዮችና ሰላዮች መሆናቸውን ስለ ደረስኩበት ፥ ሦስቱ እንዲታሰሩ ፤ ሁለቱ ግን ወደ ምጥዋ እንዲ ሔዱ አዝዣለሁ" አሉ ራስ ።

"እረኛ ምን አለ ! አዝማሪስ ምን ብሎ ዘፈነ ? የሚባለውኮ ያለ ነገር አይደለም ። በእነዚህ ጣሊያኖችም ላይ ብዙ ብዙ ነገር ሲነገር ሰንብቷል ። አሁንም ፈጣሪም በእጅዎ ጥሎልዎታል ፤ ግዘን መተከዝዎ ተገቢ አይደለም" አሉ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ። ባሻይ በኩሩም ተጠል አደረጉና ፤

"እንግዲህ ለማንኛውም ባሻይ ተድላ ጦር ተጨምሮለት ይውረድና ይጠባበቅ" አሉ ።

"ምንድን ነው የምጠብቀው ? እገጥመዋለሁ እንጂ" አሉ ባሻይ ተድላ ተነሥተው ለመፎከርም እየቃጣቸው ። ራስ ከድንኳናቸው ሲወጡ መኳንንቱም አብረው ወጡ ። እንደገናም ከጊንዳዕ በስተምሥራቅ በኩል ወደሚገኘው ኮረብታ ሲሔዱ የጦር አለቆቹና መኳንንቱ ተከተሉዋቸው ።

የጊንዳዕ በር ከሆነችው ኮረብታ ላይ ወጡና ከተራራው ሥር ያለውን ሜዳ እየተመለከቱ የባሻይ ተድላን ትከሻ ይዘው፤ "ተመልከተው መንገድህን ሜዳውን ጨርሰህ ያለውን ኮረብታ አልፈህ ፤ ደፋታውንና ሸለቆማውን ቀበሌ ተሻግረህ ከሚገኘው ሜዳ ከመድረስህ በፊት አድፍጠህ ትውላለህ ። ከዚያም ሆነህ ተመልካቾች ትሰድና ጣሊያን ያለበትን አካባቢ ካስጠናህ በኋላ ወታደሮችህን በዘርፍ በዘርፍ ትከፋፍልና ፋምታ ታስተኩስና የጣሊያኖቹን አተኳከስ ካስተዋልክ በኋላ፤ እንደገና ታደፍጣለህ። ጣሊያን ከምሽት ከወጣልህ እያባበልክ መንገድ ትሰጠውና ሲከተልህ ትከበዋለህ ። ከምሽት የማይወጣልህ ከሆነ ከበስተጀርባው አስከብበህ ትገጥመዋለህ ። ከዚህም ስትወርድ ጦርህ በሁለት ረድፍ ተከፍሎ አንዱ ረድፍ በአይለት ፤ አንዱ ጦር በማዳበ ሸለቆ ወርዶ ተራራውን በስተግራ እየተወ እንዲያመራ ታደርጋለህ ።

"እንግዲህ ልብ በል ፤ የምትጓዘው ሌሊት ሌሊት ነው ። መንገዱን የሚመሩህ ሰዎች አሉ ። ቀን ቀን አድፍጠህ ትውላለህ። ሰውህ በየደረሰበት እሳት እያነደደ የጢስ ምልክት እንዳያሳይ ድምፅ እንዳይሰማ በየሰበቡ ጥይት እንዳይተኩስ ከልክል " አሉዋቸውና ፤



ራስ በአካባቢያቸው ተራራዎች ላይ እየተዘዋወሩ ቆይተው ወደ ሠፈራቸው ተመለሱ ።

ባሻይ ተድላ የራስ አሉላ እኅት ልጅ ናቸው ። የግብርና ሥራቸውን ትተው አጎታቸውን ተከትለው በየጦርነቱ ሜዳ ሲካፈሉ የኖሩ ናቸው ። በጉራዕ፤ በኩፊትና በአይለት ጦርነትም ተዋግተዋል ። ወደ ሰሐጢ የሚያመራውንም መንገድ ያውቁታል ።

ራስ አሉላ በጊንዳዕ አዳራሻቸው የጦር አለቆቻቸውንና መኳንንቶቻቸውን ሰብስበው መመካከራቸውን ጀምረዋል ። ሠራዊታቸውም ከየነበሩበት ወደ ጊንዳዕ እየወረደ ዙሪያውን መሥፈር ቀጥሏል ።

ባሻይ ተድላ ከሦስት መቶ በላይ የሚሆኑ ምርጥ ምርጥ ተዋጊዎቻቸውን አዘጋጅተው እንዳበቁ ለመሰናበት ወደ ራስ አሉላ ሠፈር ሔዱ ። ሌሎቹም የጦር አለቆች ገብተው ከራስ ጋር በመመካከር ላይ ነበሩ ።

"እንግዲህ ጊዜው መጨላለም ሲጀምር የምሽት ጨረቃ እስክትወጣ ጠብቀህ ጉዞህን ትጀምራለህ ። የምትገጥመው ጦር ፤ ኃይለኛ ጦር ነው ። ከዚህ ቀደም ከምታውቃቸው ከግብጾችና ከድርቡሾች የተለየ ነው ። መሣሪያውም ዘዴውም የተለየ ነውና ከመጠንቀቅ እንዳትዘነጋ" አሉና ራስ ለእኅታቸው ልጅ ስንብት ሲሉ ራት እንዲቀርብም ለአጋፋሪው ነገሩና ባሻይ ተድላንም ፤

"አብረዉህ ከሚዘምቱት ዋና ዋናዎቹን አስጠራቸው" አሉዋቸው ። ባሻይ ተድላም ምክትሎቻቸው ሆነው እንዲዘምቱ የመረጡዋቸውን ሰብስበው ይዘው ቀረቡ ።

ምንም እንኳን ቀን ከሠራዊቱ ጋር አብረው ግብር ቢገቡም ትሉ ፤ የራስን ልዩ ጉርሻና ዋንጫ የለመዱት የወታደር አለቆች የጌታቸውን ራት አይተው ጫማ ስመውና የፉከራ ቃል ኪዳን ሳይገቡ መዝመቱ እንደ ተጠሉና እንደ ተጋዙ ያህል ሆነው ስለሚቆጥሩት ቅር ተሰኝተውበት ነበር ። "በል ላንበሶቹ ከኔይቱ ምሰብ አምጣላቸው" አሉና ራስ አዘዙ ።

በሁለት ሞሶቦች ፍትፍቱና ቁርጡ ተቆልሎ፣ ገንቦው በቀይ ጨርቅ ተሸፍኖ ቀረበ ።

እንበሶቹ ኮመኮሙ ፤ የገንቦው ጠጅ ከተደጋገመ በኋላ እንበሶቹ ቀረርቶና ፉከራ ጀመሩ ።
አቅራሪው፣

"ብንታገሥ እንጂ ወዳጅነት ፈርተን
ነጩ በሬ እስከዚህ መች በተዳፈረን ።

መልካቸው ቀይ ቢሆን ልባቸው ሳይጠን ነው
የሰው አገር መያዝ አማራቸው ምነው ።

ገሩ ያገሬ ሰው አወይ ሞኛ ሞኙ
ወዳጅ መስለው ገብተው አገርከን ተመኙ ።

ይመስላል እንጂ በመጣበት መንገድ
በጀግና አገር ገብቶ ስንዝር አይራመድ ።"

ሲል፣ ፎካሪው ደግሞ፣ ስናድሩን አቋምጦ ይዞ ከራስ ፊት በርከክ ፣አለና፣

"ወኔው ተነሣ ያገሬ ጀግና
ጠላቱን ሊሰብር ሊያደርገው መና

ጨለማ አይጋርደው፣ ወንዝ አያግደው
ጠላቱን ደርሶ ዐፈር ሲያስግጠው
በአሉላ አገር ላይ ሠፋሪው ማነው?

ጠላቱን አይቶ አያድርም ውሎ
ጀግናው ወታደር የጦር አለሎ

ደፍረው ገብተዋል በጀግና አገር
ዛሬንም ቢውል ነገን አያድር ።"

ብሎ ብድግ ሲል ባሻይ ተድላ እጐታቸው የሸለሙዋቸውን ዲሞትፈር ከሸከር ተቀብለው፣ ከእጐታቸው ፊት በርከክ አሉና፣

"በርከህ መርቀህ ላከኝ ጌታዬ
ልሒድ አሁኑን ከነጀግናዬ



ላንተ ላንበሳው እታዘዛለሁ
ያገሬን ጠላት አጭደዋለሁ

በጠላትህ ደም ነገ ባልዋኝ
ያንቀኛል ሙግው ያበላኸኝ" ብለው ሲፎክሩ ራስ ከመቀመጫቸው ተነሥተው የእጎታቸውን ልጅ ከተንበረከኩበት እንሥተው ጉንጮቻቸውን እያገላበጡ ሳሙዋቸውና፣

"የኢትዮጵያ ሕዝብ አምላክ ይርዳህ ፤ የመሬቷ ክብር ቀኝን ይስጥህ፣ የዮሐንስ ጸሎት ይጠብቅህ ፤ በየቀኑ ያጋጠመህን ሁሉ ላክብኝ" አሉዋቸው ባሻይ ከነጭፍሮቻቸው የራስን ጉልበት እየሳሙ ሲወጡ፣ መኳንንቱም እየመረቁ አሰናበቷቸው ።

ባሻይ ተድላ ተሰናብተው ከወጡ በኋላ፣ ራስ አሉላም ከመኳንንቶቻቸው ጋር ምክክሩን ቀጠሉበት ።

"የስንቁን ጉዳይ አገሬውም እንዲያውቀውና እንዲረዳ ቢደረግ አይሻልም!" ብለው ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ሐሳብ ሲሰነዝሩ ራስ አሉላ ቀበል አደረጉና "ጩኸት የምታበዛ ድመት አይጥ አትይዝም" ይባላል ፤ ከባሕር ማዶ ከመጣ ጦር ጋር ጦርነት ለመግጠም እያሰብን አስቀድመን ዐዋጅ ብናውጅ ለጠላት እጅ መስጠት ይሆናል ። ስንቁም ቢሆን ከዱጋው እንዲመጣ ዛሬውኑ መልእክተኞች ይውጡ ። የተገኘውንም ያህል የእርድ ከብት እንዲሰበሰብ ይደረግ" አሉ ።

"ከሁላችንም ጦር ባለብረቱና ጀሌው ተለይቶ ተቆጥሮ ዘማቹ በረድፍ በረድፍ ቢመደብና አለቃ አለቃውን ቢያውቅ የሚሻል ስለሆነ፣ ሁላችሁም ሐሳባችሁንና የጦራችሁን ልክ አስታውቁን" አሉ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ። የጦር አበጋዞቹም ተራ በተራ እየተነሡ ጥቅሉ ያለውን ሁኔታ አስረዱ ።

ባሻይ በኩሩ፣ "በኔ ውስጥ ያለው ያካለ ጉዛይ ጦር ከትቶ መጥቷል ፤ ሦስት መቶ የጠራ ባለ ብረት፣ ሁለት መቶ ያህል ጀሌ አለኝ ። በስንቅ ረገድም አላባሰብም፣ በቂዬ ነው ። ለሀገራችን ክብር ስንል ጦርነት ስንገጥም የመጀመሪያችን ባለመሆኑ ተዘጋጅተን መጥተናል ። ይልቁንስ ስንታችን ሳይገባደድ ባሻይ ተድላን

ተከትለን እንውረድ” አሉ ። ከንቲባ አድሰገድ “የሐማሴንም ጦር በመከተት ላይ ነው ። ግን ባለመገሬያውን ሁሉ ከማሰለፍ በተቂቱ መርጦ ማዝመት የሚበጅ ይመስለኛል” አሉ። ቐለታ አርአያም “መርጦ ማሰለፉ ይበልጣል ፣ የሁላችንም ጦር ቢደመር እጅግ ብዙ ነው ። ኩፊት ላይ የደረሰው ጉዳት እንዳይደርስብን አሁን መርጠን ብናሰልፍ የሚበጅ ይሆናል ይታሰበበት” አሉ ።

“እንዲያውም የእርስዎ ጦር ስመ—ጥር ስለሆነ ፣ በመጠኑ ተወምርርልዎት በርከት ቢል ይመረጣል” ሲሉ ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ፣ ቐለታ አርአያም ቀበል አድርገው ፣ “ወታደር ቢከ ማች ሐምቱ ከፈሰስ ትርፉ የራስ ብዛት ነው ፤ ያለኝ ጦር ይበቃ ኛል ፤ ሰው ሲበዛ ሜችም ይበዛል” አሉ ።

“ግለፈያ ነው ፣ እንግዲህ በነገው ቀን የከተተው ጦር ተቀጥር ባለብረቱና ጀሌው ተለይቶ በየዘርፉ እንዲመደብ ይደረጋልና ጦርነቱን እንድንጀምር የሁላችንም ፈቃድ ስለሆነ ጌታዬ ፣ ፈቃ ድዎ ይሁን” አሉ ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ።

“ሁኔታው መች የናንተ ፈቃድ የሚጠይቅ ሆነ? የፈቀደችው እገ ራቱ ፣ የሚያዝዘንም ንጉሡ ነው ፤ አሁን እንዳልከው በነገው ቀን የሠራዊቱ ድምር ታውቆ በንቁም እንዲሰናዳና በየኃላፊው እን ዲመደብና እንዲጠባበቅ ይሁን” አሉ ራስ ።

በተባለው ቀን የከተተው ጦር ልኩ ከታወቀ በኋላ በየአዝ ማቹ ተደለደለ ። ራስ አሉላ ሠራዊታቸውን አስከትተው በንቅ አደላድለው ወደ ሰሐጢ ለመውረድ የባቸይ ተድላን መልእክት በሚጠባበቁበት ሰዓት ከኢጣሊያ ጦር አዛዥ መልእክት ደረሳ ቸው ።

መልእክቱም እንዲህ የሚል ነበር ።

“ይድረስ ለራስ አሉላ

የሐማሴን ገዥ

ምፅዋንና የያዝነውንም ቀበሌ ሁሉ ለቀን ለመሔድ ከመንግ ሥታችን አልታዘዝንም ። ስለዚህ ጉዳይ መነጋገር የሚገባም ከኔ



ጋር ሳይሆን ከኃያሉ የኢጣሊያ መንግሥት ጋር መሆኑን እና ውቃለው ።

ጀኔራል ካርሎ ጌኔ

የኢጣሊያ ጦር አዛዥ

ምፅዋ ።”

“ወንድነቱን የተማመነ ሰው ይመስላል ። ሀገርሆን ይዘዋል ሁና በመንግሥቱ አቤት ባለ አለኝ! የእርሱን መንግሥት ለለ ምን ርግ ልሔድበት ነው? እንግዲህ ከዚህ ሌላ ምን እንጠብቃለን? እስቲ ወረቀቱን ያመጣውን መልእክተኛ ጥሩው” አሉ ራስ ፣ አጋፋሪው መልእክተኛውን ሲያስገቡት ራስ አሉላ በችኩላ ፣ “በማህ ወዳጂ ትውልድህ የት ነው?” ብለው ጠየቁት።

« ምፅዋ ነው ፤ የናይብች ዘር ነኝ» አለ ።

«በመንገድህስ ምን ነገር አይተሃል» አሉ ራስ ።

«ተዚህ የሔዱ ነው መሰለኝ ብዙ ሠራዊት ወርዷል »

«የት ላይ ደርሷል»

«በጣም ተርቷል ፤ ከጣሊያኖ ጦር ጋር ያለው ርቀት ብዙም አይደል »

«የጣሊያኖ ጦርስ ነገሩን ሰምቷል ?»

«የሰማ ይመስለኛል »

«ምሽግስ ሠርቷል»

«አዎን ብዙ መድፍ ጠምዷል ። »

«ስንት ቦታ ጠምዷል»

«እኔ እንዳየሁት ካራት ቦታ ላይ ጠምዷል »

«በየት በየት በኩል ነው የጠመደው»

«ከወንዙ ወዲህ ከየኮረብታዎቹ ላይ ጠምዷል »

«ግለፈያ ነው ፣ አጋፋሪ ለስንቁ ሃምሳ ብር ስጠውና ነገውን ይሒድ» አሉ ራስ ።

«የምወስደውስ መልስ ይኖራል?»

«አዎ ጢት ይሰጥሃል ።»

ራስ አሉላ ፣ ለመጠነኛ ጊዜ ያህል ሲተክዙ ቆዩና በአጠገባቸው ወደ ነበሩት የጦር አለቆች መለስ ብለው ፣ «እንግዲህ ሰማችሁት አይደለም? ምን ይታያችኋል?» ብለው ጠየቁ ።

«ይህንኑ ገልጸን ወደ ንጉሠ ነገሥቱ እንላክ?» አሉ ዘጊዮርጊስ ። ይህን ሲሰሙ ራስ አሉላ ቆጣ ብለው ፣

«እንዲህ አድርጎም ታማኝነት የለ ! አስተዳደር ጠብቆ ግዛ ብለው በሰጡኝ አገር ላይ ጠላት ሰፍሮበታልና እባክዎ ይርዱልኝ ፣ ያለዚያም ይድረሱልኝ ብዬ ነው የምልክባቸው? አላደርገውም!!» አሉ ።

«ከታሰሩት ጣሊያኖች አንዱ ፣ አቅርቡኝ ይላል» አሉ ኢጋፋሬ ።

«ያን ደፋር ባለጌ ፒያኖ የሚሉትን እንደሆነ ዐይኑን እንኳ ላየው አልፈቅድም» አሉ ራስ ።

«ሽማግሌው ነው» አሉ ኢጋፋሬ ።

«ዋናው ደፋሩስ እርሱ አይደለም? ብቻ አስገባው ።» ሳሊቢኒ እጆቹን እንደ ታሰረ ገብቶ ሲቆም ፣

«ምን ጉዳይ አገኘተሃል?» ብለው ራስ ጠየቁት ።

«እርስዎ በፈቀዱልኝ መሠረት የደረሰብንን ሁኔታ ገልጠው ሕይወታችንን እንዳተርፍ በማለት ወደ ኋላው እንዲመለስ ለጀኔራል ካራሎ ጽፌለት ነበር ። እንዲያውም መታሰራችንን ሰምቶ በጣም ተቆጥቷል አሉ ። ስለዚህ . . . . » ብሎ ተናግሮ ሳይጨርስ ፣

«ምን ይሆን ያሰቆጣው ወዳጄ?» ብለው ራስ አሉላ ጠየቁት ።

«የኛ መታሰር ነዋ» አለ ሳሊቢኒ ።
ራስ ከት ከት ብለው የለበጣ ሣቅ ሣቁና ፣



«እንዲህማ ከሆነ የቁጣ ትርጉሙን አታውቁም ማለት ነዋ! ሀገሬ ውስጥ ገብታችሁ የሰለላችሁና ጦር ያሰፈራችሁ እናንተ ፣ የተደፈረች የኔ አገር ፣ የርሱ ቁጣ ከምን የተነሣ ሊሆን ነው?» አሉት ።

«ይህን ነገር እባክዎ ደጋግመው ያስቡበት ፤ በኛ መታሰር የተነሣ ተቆጥቶ ጦር እንዳያዘምት መጠንቀቅ ይገባዎታል» አለ ሳሊቢኒ ።

«የእናንተን መታሰር የሰማው የእናንተ ጄኔራል ዳግማዊ ናፒየር መሆኑ ነዋ! እናንተን በጦርነት ሊያስፈታ ሊመጣ ነዋ! እዚህ ድረስም መድከም አያስፈልገውም ፤ እናንተን አስቀድሜ አወርድስታለሁ ፤ የኔን ሠራዊት ካሸነፈ እራሴ እናንተን ፈትቼ አስረክበዋለሁ» አሉ ራስ በከፍተኛ ቁጣ ተውጠው ።

«ለምን ደም በከንቱ ይፈስሳል? ወታደሮችዎ ለምን ይለቁ? የሰፈረበትን ቀበሌ ቢተዉለትና እኛን ፈትተው ቢለቁ ጦርነት ላይነሣ ይችላል ?» አለ ሳሊቢኒ ።

«ለኔ ሠራዊት አታስብ የሀገሩን ክብር ለመጠበቅ ምንጊዜም እንደ ተዘጋጀ ነው ። ታያለህ የሚዋረደውን የእውነት አምላክ እውነት ላለው ይፈርዳል» አሉት ራስ ።

«ይተዉ አገርዎንና ሠራዊትዎን ከጥፋትና ከውርደት ላይ እንዳይጥሉ ይመከሩ» ብሎ ሳሊቢኒ ሲናገር ራስ በይበልጥ ተናደዱና ፣

«ንባ ኢጋፋሬ ሆስቴም እንደ ታሰሩ ከጦሩ ፊት ፊት እንዲሔዱ ። አሁን አስወጣልኝ!» አሉ ራሲ ። ተወራጭተው ተነሡና ተንጉራደዱ ። ሠራዊታቸውን ግብር ያገቡበት ዳስ ጠበባቸው ።

“የተደፈረችውን ያገሬን ክብር የነደደው ልቤ ይበቀልላታል ። በማን አገር ላይ ፣ በማን መሬት ላይ ነው የርሱ መንሰራፋት” አሉና እንደገና ከወንበራቸው ላይ ተቀመጡና ፣

«ሰማችሁ ጀግኖች ልጆች!ከዚህ የመረረ ጽዋ መቼም የለም፤ በሀገር ላይ ጠላት ሠፍሮ ባንዲራውን ሰቅሎ ተንሰራፍቶ ማን

አለብኝ ብሎ በጽሞና መመልከትና ውሉ ማደር ይገባል?» አሉና የሕሊና ፍርድ የጦር አለቆቻቸውን ጠየቁ ።

"የሞቱት ዐይኖቻቸው ፥ ያሉት ከብረቶቻቸው ይወቅሰናል ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ይፋረደናልና ውለን ማደር የለብንም ፤ ዛሬውኑ እንውረድና ቅርጡ ይለይ» አሉ ቸለታ አርአያ ። ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ለጠቅ አድርገው ፥ «ምነው ጌታዬ እንዲዚህ መናደድዎ ? እስከ ዛሬ ያልታየብዎትን ጠባይ ለምን ያሳያሉ? ሁሉንስ በትዕግሥትና በቆራጥነት አይደለም ችለውት የኖሩ? ሀገሩችንን የደፈሩ የአርበኞን ከንድ የሞከሩ እነዚህ ብቻ አይደሉም ። ስለዚህ መዝመት እንጂ መናደድን ምን አመጣው? እንዝመት ይልቀቁን ፥ ይዘዙን !» አሉ እየተወራጩ ።

«እንግዲህ ለማንኛውም ቢሆን ለማሊያኑ ጦር አለቃ የመጨረሻውን ማስጠንቀቂያ እንልክለታለንና አለቃን ጥሩልኝ» አሉና ራስ አሉላ አጋፋሪያቸውን አዘዙ ።

አለቃ የመቃ ብርዓቸውንና ስስ የብራና መጻፊያቸውን ይዘው ገቡና ቆሙ ።

«እንዲህ ብለህ ጻፍለት» አሉ ራስ ።

«በዊሊ በስሐጢና በዙላ የሰፈሩት ወታደሮችህን በአጭር ቀናት ውስጥ እንድታስወጣ አስጠንቅቅሃለሁ ። የዚህንም መልሱን በቶሎ እንድትልክልኝ ፤ መልስህ ውሉ ካደረ የወዳጅነቱ ፍጻሜ መሆኑን ዕወቀው» ብለው ለአለቃ ነገሩና የሚጻፈውንም ደብዳቤ የፓንሬላ ካርሉን መልእክት ይዞላቸው የመጣው መልእክተኛ እንዲወስድ አዘዙ ።

ባሻይ ተድላ ፥ ስሐጢ ወርደው ከኢጣልያ ጦር ጋር የመጀመሪያውን ግጭት ከለኮሱ በኋላ መልእክት ወደ ጊንዳዕ ሰደዱ ። መልእክተኛው ሲገመገም ከራስ አሉላ መረር ደረሰና ፥

«በቆይታ የምናገረው ጉዳይ በላ ንገሩልኝ» ብሎ አጋፋሪውን ጠየቀ ።



«ምን ብሎ ነው የላከህ?» አሉ ራስ አሉላ መልእክተኛው ገብቶ እጅ እንደነሣ ።

«ስሐጢ ላይ የመሸገው የጣሊያን ጦር ገና በሩቅ ባለን ተመልክቶን ኑር በመድፍ አላስጠጋ ስላለን ወደ ኋላ ማፈግፈግ ይዘናልና ፥ መግሪያና ወታደር ይጨመርልኝ ብሏል ብለህ ንገርልኝ ብለውኛል» አለ ።

ራስም «ሽሽት ጀምረዋል ማለት ነው?» ብለው ጠየቁት ፊታቸውን ከስኩሰው ። መልእክተኛውም ፥ «ብቻ ያው አጠገብ ለአጠገብ ናቸው ።»

«ከምን ጋር ነው አጠገብነቱ?» አሉ ራስ ።

«ወደ ኋላ ከመመለሱ ጋር ።»

«ጣሊያንስ ወደፊት ይገፋል?»

«ገና አልጀመረም እንጂ ጠንካራ የሆነ ምሽግ ይዟል ፥ መድፉም በሩቅ ይመታል ፥ አያስጠጋም» አለ መልእክተኛው ።

«ብዙ ሰው ተጉድቷል?»

«አዎ ! ቀላልም አይደለም ፤ አያል ጉዳት ባይደርስም አልቀረም ።»

«እንኳን እርሱ የሠራውን ፥ ነገደ በይጣናት የሠሩትን መድፍ ይዞ ቢሰለፍ እኔ ቱማ በኢትዮጵያ መሬት ላይ ተንሰራፍቶ አይቀመጥም!» አሉ ራስ የቁጣ እሳት—ነበልባል ከፊታቸው ላይ እየተንቦገቦገ ።

ወዲያው «ገሰ አጋፋሪ የጦር አለቆቼን አስገባቸው» ሲሉ አዘዙና ትክዝ ብለው ተቀመጡ ።

«ምነው ጌታዬ ምን ነገር ተፈጠረ?» አሉ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ፥ እንደ ገቡ የራስን ብስጭትና ትካዜ ተመልክተው ።

ራስም እንገታቸውን እየወዘወዙ ፥ «ጌኔ እንት ልጅ ወደኋላቸው ማፈግፈግ ጀምረዋል ይሉኛል» አሉዋቸው ።

«ቢሆንስ ጌታዬ ጀግና ሞልቶ እኔን በቅድሚያ ይላኩኝ» አሉ ደጃዝማች ።

«ከእንግዲህ ወዲያማ የኢትዮጵያን እንግዳ የምቀበለው ራሴ ነኝ ፤ ማንንም አልከም ፤ የጦር አለቆቹ ይሰብሰቡ» አሉና ትእዛዝ ሰጡ ።

የጦር አለቆቹ እየገቡ ቆሙ ። ራስ ከመቀመጫቸው ተነሥና እንደ መንቀራጠጥ እያሉ ፣ «እንግዲህ የምነግራችሁን በጥንቃቄ አድምጡኝ ፤ ሠራዊቱ በሦስት ይመደባል ። አንደኛዉ ዘርፍ ፊት ለፊት ያመራል ። ሁለተኛዉ በግራ በኩል ይወርዳል ። ሦስተኛው እኔን ተከትሎ ወንዛ ወንዙንና ረባዳውን ይዞ ይዘምታል ። ጨረቃዋ ስለምታነጋ ጦርነቱ ከንጋቱ ላይ ይጀመራል። የነገዋ ጨረቃ ብርሃናችንም ታዛቢያችንም ትሆናለች ። ጠላት ያሰበትን ቦታ በትክክል ለማወቅ እንድንችል ፊት ለፊት የ ሚዘምተው ጦር ምልክት ሰጭ ይሆናል ። ይህም የሚሆነው በግራና በቀኝ የተጓዘው ጦር በጠላት መድፍ እንዳይመታ ወደ ጠላት ከተቃረበ በኋላ ነው ። ጠላትን ከበን በጠመንጃና በጎራዴ ስንገጥመው የጠላት መድፍ ከኛ ውጭ ይሆናል » አሉ ። በጦር አለቆቹ መካከል ሹክሹክታና ጉርምርምታ ሆነ ። በመጠኑም ቀዝቃዛ አየር ሰፈነ ። በባሻይ ጦር ላይ የደረሰው ጉዳት ጭምጭምታው ጊንዳዕን ዐልፎ ወደ አሥመራ ለመዝለቅ በግቀብቀብ ላይ ነበረ ። የጣሊያን ጦር መድፍ በሩቅ ይመታል እሳተ—ገሞራ ይወረውራል ፤ ብዙ ሠራዊት አሰልፎአል» እየተባለ መወራት ጀምሩዋል። ያን ወሬ የሰሙ አንዳንድ የጦር አለቆችም ፣

«ለባዶ ደረቅ መሬት ለምን እናልቃለን» የሚል ሐሳብ አድርባቸዋል ። በጦር አለቆቹ መካከል የተነገው ትርምስ ጋብ እንዳለ ፣

«ተኩስ ጀማሪው በየት በኩል የዘመተው ጦር ይሆናል?» ብለው ሻለቃ አርአያ ጠየቁ ።

«ምን ጊዜም ተኩስ ጀማሪው የግንባር ዘማቹ ነው ። በተረፈ የጉደላችሁ ነገር ካለ እንወቀው» አሉ ራስ ።



የግንባር ዘማቹ ጦር ፊታውራሪ ማን ይሆን? በጣሊያን መድፍ ፊት ለፊት የሚሰለፈው ማነው ? ይህም በጦር አለቆቹ ዘንድ ከባድ ስመመን ሆነ ።

«እንግዲህ ወዳጆቼ ልጆቼ ! እስከዛሬ በፍቅርና በክብር እንደኖርን ፣ ዛሬም በክብር መሰለፍና በክብር መሞትም ግዴታችን ነው ። ምጥሞን እናስለቅቃለን ስንል የቆምንበትን ማስነካት የለብንም ።

"ነገ የምንገጥመውም ጦር ከዚህ ቀደም ከገጠምናቸው ለየት ያለ ነው ። የ ሚይዘው መሣሪያም የተለየ ነው ። የእንግሊዝ ጦር መቅደላ ድረስ ዘልቆ በመግባቱ የሀገሪቱ ክብር ተደፍሩዋል ። ይህ ደግሞ የሁላችንም ኃፍረት ነው ። ዛሬ ደግሞ የኢጣሊያ ጦር እኛን ተራምዶ ሊገባ መጥቷል ። ከእንግዲህ ወዲያ ግን የኛ ሕይወት ቁሞ ኢትዮጵያ አትደፈርም ። ሞት ላይቀር የክብር ሞት እንሙት ። የኢትዮጵያን ጀግና ሁሉ እንድናስከብር ጊዜው መጦናል ። የትውልድ መመኪያዎች እንጂ መሳለቂያዎችና ማፈሪያዎች መሆን እንዳይገባን ዕወቁ ። ሕይወታችን ቁማ ወገኖቻችን ሴቶቻችን በአረመኔ አይደፈሩም ። እንግዲህ ጀግኖቼ ልጆቼ ትላንት ከኩፊት ጦርነት በድል አድራጊነት ስንመለስ በክብር አሥመራ ስንገባ ፣ በደስታ ፈንድቶ የተቀበለን ሕዝብ ነገም እንዲኮራብን ፣ ነገም እንዲመካብን ፣ ነገም እልል ብሎ እንዲቀበለን ማንነታችንን ለጠላት እናሳየው!!» ብለው እያንዳንዱን ሲመለከቱት በጦር አለቆቹ ላይ ሰፍኖ የነበረው ቀዝቃዛ አየር እየገፈፈ ሲሔድ ፣ በርሱ ፈንታ የወኔ ትኩሳት ለክብር ቋጣ እየሠረፀ ሲሔድ ታያቸው ። ቀጠል አድርገው ፣

«ከባሕር ማዶ ተሥነቶ በሰይጣናዊ ጥበቡ ተመክቶ ጦር ጭኖ አገራችን ውስጥ ገብቶ የኛን መሬት የኛን ርስት ፣ የኛን ቤት የኛን ሚስት ሲመኝ የኛ ወንድነትስ ማንነቱን እያሳየም ! ትዕቢተኛው በቆራጥነት አንገጥመውም? ክንዱን ክንዳችን አይሰብረውም? ወንድነቱን ወንድነታችን አያሸንፈውም?›—ተበተሉልኝ እያለ ይጣራል» ብለው ሲናገሩ እንደገና የጦር አለቆቻቸውን ገጽ ሲያተኩሩበት ፣ ትካሻውን እያሳበጠ ፊቱን

እያኮሳተረ፣ የግንባሩ ቆዳ እየተሰበሰበ፣ እልህ እየተናነቀው ሲበራ ተመለከቱት ።

የጦር አለቆቹ መቁነጥነጥ፣ መገንፈል ልበ—ሙሉነት እንደዚያ ሆኖ በመቀጣጠል ላይ እንዳለ፣

«በሉ እንግዲህ ስለ አስፈላጊ ምክሩበትና ሥራዊቱ እንዲደ ለደልና ጉዞ እንዲጀምር ይሁን» ብለው አዘዙና የጦር አለ ቆቹ ሲወጡ ደጃዝማች ኃይለሥላሴን ጠርተው ፣ «እንግዲህ መቼም ጀርባዬን ለጠላቴ ሰጥቼ አልሞትም ። ትላንት ከወደ ቀት ጀግኖች ሬሳ ላይ እወድቃለሁ እንጂ አልመለስም ። ይሆን ዕወቀው ። ስለዚህ እዚህና አሥመራ ሆነው አገሩን የሚ ጠብቁ የኛን ሁኔታ እየተከታተሉ ወደ ንጉሥ ነገሥቱ የ ሚላኩ ጠንካራ ታማኞች ያስፈልጉናልና ለዚህ ማንን ትመርጣለህ?» ብለው ጠየቁቸው ።

ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴም፣ «እኛ እንዝመት እርስዎ ደጀን ሆነው ይጠባበቁን» ለማለት አሰቡና የአሉላን ቆራጥነት ፣ የአ ሉላን የጦር ገፈታ ተማሽነት ስለሚያውቁት፣ ሐሳባቸውን እንደ ማይቀበሉት ተረዱትና ሊናገሩት ያሰቡትን ዋጥ አድርገው፣

«እሺ ጌታዬ ለእስዎ ታማኞች የሚሆኑ ብዙ ጀግኖች አሉና መርጬ ሐሳቤን አቀርባለሁ» አሉ ።

«ስማህ ደጃዝማች ፣ እንዳትሳሳት አሁን የሚያስፈልጉኝ ሰዎችህ ለሀገራቱ ለራሴ ለመሬቲቱ ታማኞች የሚሆኑ ናቸው ። እኔ እንድወዳቸው፣ እኔ እንድሾማቸው፣ እኔ እንድሸልማቸው እኔን ለማስደሰት ሲሉ የሚሰለፉ አያስፈልጉኝምና ከመምረጡ ላይ ተጠንቀቅበት» አሉ ራስ ። ደጃዝማችም ፈገግታ እየታያቸው፣ «ሌላት ካየው ምን ለየው?» ይባላል «ለእርስዎ የታመኑ ለሀገሬቱ ታማኞች መሆናቸው ይቀራልን?» አሉ ።

«ለመሬትና ለሰው ታማኝነት ልዩነት አለበት ። ለኔ ታማኝ መስሎ ለመታየት የሚፈልግ እኔን ያስደስተ መስሎት ሕዝብን ይበድላል ። ሕዝብ ከበደለብኝ ደግሞ እኔና ሕዝብ ተለያየን ማለት ነው ። ሕዝብ ከራቀኝም መሬቷ ትከዳኛለች ። እኔ ትክክለኞች የም



ላቸው ለመሬቷ ፣ ለሕዝቧና በቅማንቱ መካከል ድልድል የሚሆኑትን ነውና ለዚህ ይሆናል የምትለውን ምረጥልኝ ወደም ደግሞ አንተ ከዚሁ ሆነህ በትጠባበቅ ማለፊያ ይሆናል» አሉና ራስ አማቻቸውን ትክ ብለው ተመለከቱዋቸው ።

ደጃዝማች ድንገት ብልጭ አለባቸውና ፣

«እኔ ኃይለሥላሴ ነኝ ከአሉላ ተለይቼ ተለያየ የምትረከው? ምንው ምን አጥፍቼ ምንስ ሰሙብኝ ከመቼ ወዲህ ነው እንዲህ ሆኖ የሚያውቀው» ብለው እልህ ሲተናነቃቸው ተመለከቱና ፣

«ከዚህ በትተህ የቦልጨ ትጠቀመኛለህ፣ ታገለግለኛለህ ብዬ ነው» አሉና ራስ የአማቻቸውን ቁጣ ለማብረድ ሲሉ ተነሥ ተው ፣

«ይሆን በማለቴ አትቀየመኝ ፤ ከሌላ ጠጋቢ እንድትለይ አልፈ ልልወድም ፣ ቢቸግረኝ ነው እንጂ፣ ቀኝ እጄን ልተውህ መች እመኛለሁ? የሰው ማጣት የታማኝ ማጣት ነው ይሆን ያናገረኝ፣ በል አሁንም ከጦር አለቆቹ ጋር ተመካከርና ሐሳባችሁን ንገሩኝ» አሉ፣ እንደ ሕፃን ልጅ እያባበሉ ።

ደጃዝማች ተናግረቸው የነበረውን ቁጣ ለማብረድ ሲሉም ተለማምደው ወጣ ሲሉ፣ ራስ የቤት አሽከሮቸውን ጠርተው ፣

«መኳንንቱና ሹማምቹ ሲመጡ እንዲገቡ » አሉና ከዙፋን በራቸው ላይ ተቀመጡ ። መኳንንቱ በየተራ እየገቡ ቆሙ ።

«ምክራቸውና ሐሳባቸውን ወደፊትም» ብለው እንደ ጠየቁ ዘሊያርጊል ተራቡ አሉና ፣ «ጊያዎቹ መኳንንቱ በሁለት ሐሳብ ተከ ፍለዋል ። ግማሹ ወገን 'በደረቅ መሬት ፣ ለዓይ መሬት ለምን ደግ ነው የምናልቀው' ሲል ግማሹ እንዲያውም የሚያመነው ፣ 'የጌታችን ትእዛዝ ከሆነ ሀገራችን የምትደፈርበት ከሆነ እንዘ ምታለን ፣ እናመነታም ፣ ብሏልና ምናለ ለእኔ ብናልቅ" አሉ ።

ራስ አሉላን ዝምታ አፈናቸው ፤ ለጉማቸው ፤ ሊናገሩ እያቃ ታቸው ከዓይ ዝምታ ዝም ጭጭ አደረጋቸው ።

ዐይኖቻቸው እየተጎለጎሉ ፣ እየቀሉ እየፈጠጡ ሔዱ ። ሰውነታቸው ማንቀጥቀጥ ጀመረው ። ከኩፋት ጦርነት ሲመለሱ ሹርባ ተሠርተውት የነበረው ጸጉራቸውን ፈትተው አንጐፍረውት ነበርና የግራሜ እሾህ እየመሰለ መቆም ጀመረ ።

የኢትዮጵያን ክብረ ወሰን ሲያስከብሩ ጊዜው ባስለፋቸው የጦር አሰቆች መካከል ከባድ አባዜ ወደቀ ። ለጦርነት እንግዶች አልነበሩም ። «ክተት » ሲባል ቀድመው የሚወረወሩ ነበሩ ። የጦርነት ጭምጭምታ ሲነግ ሲቃ የሚይዛቸው ነበሩ ። ራስ አሉላ ሐሳባቸውን ሰብስበው ፣ አንደበታቸውን ከፍተው ሲናገሩ ይቅርና የጦር አለቆቻቸውን ቀና ብለው ለማየት አልቻሉም ። ጦርነት ገጥመው ድል ሆነው ፣ በጠላት ወታደር ተማርከው ከጠላት ፊት የቀረቡ ነው የመሰላቸው ። የኢትዮጵያ ክብር ፣ የኢትዮጵያ ነጻነት ፣ የኢትዮጵያ ሕልውና እንኩትኩት ብሎ የወደቀባቸው መሰላቸው ።

የብላታ ገብሩ መሞት ያን ለት ተሰማቸው ። «ለምን ቀድሞኝ ሞተ? ለምን ከዳኝ? ለምን ሼሸኝ? ምን በድየው ነበር?» ብለው በልባቸው ልባቸውን ጠየቁት ። «ምናልባትስ እነዚህ ተንከለኞች ነጮች የጦር አለቆችን አባብለዋቸው ይሆን?» ብለውም ሕሊናቸውን ጠየቁት ። ከተቀመጡበት ወንበር ሥር ነጭ እሾህ እየወጣ ሊወጋቸው ሲል የድንኳናቸው ዋልታ ደም እያንዠቀዠቀ ሲያጠምቃቸው በድንኳኑ ሥር ብላታ ገብሩ ሰተት ብለው ገብተው ፣ ከፊታቸው በርከክ ብለው ቶከራውን ሲያረድሩት ፣ ባሻይ ተድላን ጣሊያን ግርኮ እግር ቀወርች ፣ አስሮ እየገረፈ ሲሣለትባቸው ፣ የጣሊያን ወታደር ሰሐጢን አይለትን ዳግስን ዐልፎ ከጊንዳዕ በር ደርሶ «ኢጅህን ስጥ» ሲላቸው ብንን ብለው ተነሡና ፣

«አሉላ ወንዱ የዮሐንስ ቀኝ እጅ!» ብለው ፎከረው ብድግ አሉና ፤ «ኢጌን ያላችሁ ተከተሉኝ ፤ ከፊታችሁ እቀድማለሁ ፤ ከፊታችሁ እጥላለሁ ፤ ከፊታችሁም እወድቃለሁ! ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ዛሬውኑ ወደ አሥመራ ተመልሰህ አገሩን እንድትጠብቅ ይሁን» ብለው ወጡ .......



# ጦ ር ነ ት

ከአሥመራ ወደ ምፅዋ ለሚወርድ መንገደኛ ምፅዋ ከመድረሱ ኻያ ኪሎ ሜትር ያህል ሲቀረው ፣ ተድአሊ የተባለችውን ቀበሌ ያገኛል ። ገና ከጊንዳዕ በታች የሚገኘውን ገደላ-ገደል ወርዶ የዳግስን ሜዳ እንዳለፈ የሚጋረፈው የቆላ ሐሩር ይቀበለዋል ። ቀበሌው ወጣ ገባ ከፍተኛ ፣ ኮረብታዎች ተቀጣጥለው ሙቀት እየፈነጠቁ ከደጋ የወረደውን መንገደኛ ሲቀበሉ በትክክል የአፍሪቃን ገጸ—ምድር የተፈጥሮ ስጦታ ይረዳዋል ።

ከሜዲትራኒያን አካባቢ የሚነሣው የክረምት ጊዜ በቀይ ባሕር አካባቢ ያሉትን አገሮች ከልሉ በሚወስድበት ወቅት ደግሞ ቃጠሎውና ደረቁ አካባቢ ወደ ለምለምነት ስለሚለወጥ ከጊንዳዕ ጀምሮ እስከ ምፅዋ ያለው ወረዳም ከጥቅምት እስከ ሚያዝያ መጨረሻ ድረስ የሚታይበት ውበት ፣ የሚገኝበት የመሬት ፍሬና የአየር ሰውጥ የማይጠገብ ነው ።

ራስ አሉላም ከጊንዳዕ ወደ ሰሐጢ የወረዱት በጥር ወር አጋማሽ ላይ ነበር ። የአየሩ ጠባይ ዐልፎ ፀልፎ ዝናብ የሚጥል መሬቱ በልምላሜ የተሸፈነ ነበር ። ስለዚህ ወራቱ ከደጋ ለወረደውም ሠራዊት የሚያስቸግር ስለሆነ ፣ ለዘመቻው መቃናት መሠረታዊ የሆነውን አስተዋጽኦ አበርክቷል ።

ራስ አሉላ ፣ በተፈጥሮአቸው ከወረሱት ጸጋ የጦር ስልት ሲያወጡ ወይም ጦርነት ለመግጠም ሲያስቡ የአየር ጠባዩንም በትድሚያ ለማወቅ የሚያደርጉት ጥረት ነው ። ሠራዊታቸው በሐሩር ፣ በጨለማ ፣ በወባ ፣ በኃይለኛ ዝናብ ጉርፍና ጉም እንዳይጠመድባቸው አጅግ ይጠነቀቁ ነበር ።

ከሙር አለቆቻቸው ጋር ድንገት በተፈጠረው የሐሳብ መለ ራት ተበሳጭ ሳይቀርጡ ወይም ሳይመጥር ወፍ ነው ሳይሉ፤ ሠራዊታቸውን እንዳለበት በሦስት መድበው የሚተማመኑባቸውን አለቆች መርጠው በኃላፊነት ከመደቡ በኋላ ጉዞአቸውን ቀጠሉ። የጊንዳዕን ገደላ-ገደል ወርደው ከዳግበ ኩሬ ብታ ላይ እንደ ሰፈሩም ከቤት አሽከሮቻቸው በድምፅ ጥራትና በግጥም ድርደራው እጅግ የሚደነቀውና በየሕዝብትም የማይለያቸው ኪዳኔ መብራቱ፣ አሉላ አርፈውበት ከነበረች ዛፍ አለፍ ብሎ ከድንጋይ ላይ ተቀምጦ አንዳንድ ጊዜ በዋሽንቱ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በድምፁ እጅግም ሳይጮህ፣

«እይዞህ ያገሬ ዱር ወንዙና ተራራው
ወላትክን ሊሰብር መጥቷል አንበሳው
ግነው የደፈረ ያገሬን ወንዝ—ወንዝ
የዓትም እሱት ወይ የሚመከት ጉብዝ
ያገሬን ተራራ ግነው የደፈረ
ጥንዲራን በቅቱ የዋለ ያደረ
እንዴት ትቃዠዉን እንተ ሽንተረር፣
ከበርህን ሊረግጠው የጠላት እግር።
አፍ አውጥቶ ጮኸ ያገሬ ምድር
ድረስልኝ ይላል ጀግና ወታደር።
ያገሩ መደፈር እሱላን ቢያስቆጣው
ተንደርድሮ መጣ፣ ጠላት ምን ይዋጠው »

እያለ ሲያቅራራ ራስ በድምፁና ሲያደምጡት ኑሮ አስጠሩትና ያስለመዱትን «የሱሩ መጣጥ» ሰሦ ቁር ኑርሻ ሰጥተው «እሰይ ያገሬ እንደሆነ ደግሞ፣ ስንመለስ ሌላ ትሸልማለህ እሱትና በተንድ ተይዞ የነበረች ጠጅ ሰጡት። ኪዳኔ ያችን ጨለጠና እንደገና ከፈታቸው ተንበርክኮ፣

«ትቆጠር ጨረታ ትታዘብ ምድር
በጥዋት ሊቆለል ነው ከምር
ነጮ ገበሬ ሲደናገር
አሉላ ደርሶ ሲያቀራምበው



የጉሙ ወታደር ቶን ሊጨልመው
የአሉላ ጀግና አረር ሲያነርሰው
ነጭ ይታያል ፈረስ ደፋር
ጀግናው ሲገባ በጠላት ላፈር»

ብሎ ፎክር ወጣ።

ሶስቱ ሌሊት ላይ የራስ አሉላ ሠራዊት በጥሩንባ ተቀሰቀሰ። ጊንዳዕ ላይ በተሰጠው ድልድል መሠረትም በየአለቃው ተከለፈ። ደረቱ ጦር ከፊት ሲቀድም ጀሌውና ሰንቅ የሚነሳው ከመካከል ኋለኛ ለፈረሰኛው ጦር የሚፈለግ በሊያም ጉዳ ሾም የነበሩት አብድል ቃድር ወደ እኩድ ኃላፊ ሆነው የመጊደ ጉዞ ተጀመረ። ራስ አሉላ በፈረሳ በቅሎአቸው ላይ ተቀምጠው የሠራዊታቸውን ጉዞ እየተቆጣጠሩ ወደፊት በሩት የሚመቱ ዘርከት ያሉ መድፎች ጠምዶ ወደሚጠብቁት ጠላት አመሩ።

ከንጋቱ ላይ ሰሐጢ አጠገብ ደርሰው የወታደራቸውን አሰላለፍ በዝርዝር መመልከት ጀመሩ። በሦስት ዘርፍ ከፍለውት የነበረውን ጦር እንደገና በአራት ከፈሉት። ሦስቱ ዘርፍ እስቀድሞ በጠዋው ሰላት መሠረት እንዲዘምት ካደረጉ በኋላ፣ አራተኛው ዘርፍ ግን የጎላ ደጀን ሆኖ ሰንቅ እየጫነ እንዲሆን እያደረገና በዋና ዋናው ግንባር ልጅ ፊንጃል ተሰማ፣ ባሻይ ተርቿ ባሻይ ተድላ ፊንጃይ፣ ባሻይ ደስታ አባጋኢ እንዲሰለፉ አድርገው ወደፊት ጉዞውና ሰሐጢ ላይ መሽጎ የነበረውን የጣሊያን ጦር ፊት ለፊት ገጠሙት። የጣሊያን ጦር ከትጠናከረ ምሽግ ውስጥ ከመግባቱም ሌላ የነበረው መድፍ የእትየጡያን ወታደር የማያስጠጋ ሆነ። ቀጥሎ ዘርከት ያለ ሠራዊት መጉዳቱን ራስ አሉላ እንደ ተረዱ ወደ ኋላ ማፈግፈግና በሌት መሰወጥ አስፈላጊ መሆኑን ተረዱት። በፈረሰኞቹ የጥንቃቄን ጦር ወደ ኋላው እንዲመለስ ካደረጉ በኋላ፣ ቀኑ ሲመሽ ሠራዊታቸውን እንደገና በሁለት ዘርፍ ከፍለው ሌት ለሌት መዝመቱ ቀርቶ በግራና በቀኝ ብቻ እንዲዘምት አደረጉና በቀኝ በኩል የሚዘምተው ጦር ራሳቸው አዝማች ሆነው ምሽጉን ከመካከል በማስጠባት ከጉንና ከኋላ ወጠሩት። በሁለተኛው ቶን የተቋቋ

ፀሐይ ስትወጣ ከጀርባቸው እንድትሆን አደረጉና ጦርነቱን ጀመሩ ።

በስሐጢ የመሸገው ጦር መከበቡንና ለመቋቋም የማይችል መሆኑን ወደ ምፅዋ ምልክት አስተላልፎ ኖሮ ፥ ተተኪ ጦር ከምፅዋ ገሥግሦ ዶጋሊ ላይ ደርሶ ሁለተኛ ምሽግ መሥራት ሲጀምር ፥ በቀኝ ዘርፍ የዘመተው የራስ አሉላ ጦር እንደገና እንደ ቀበበት ታጠፈና ከመካከሉ አስገባው ። የመድፍና የጠመንጃው ተኩስ ቀረና ውጊያው በጨበጣ ሆነ ። ራሳቸው ራስ አሉላ ከፈረሳቸው ወርደው እንደ ተራ ወታደር በተድአሊ ወንዝና ዳገት እየዘለሉ ከጠላት ጦር ጋር ተደባለቁ ። ጠላት ወንዙን ተሻግሮ ከወንዙ ወደ ላይ የሚሽቀዳደመውን የኢትዮጵያን ወታደር መትረየስ ተክሎ ማጥቃት ሲጀምር ፥ ከወንዙ በላይ ከሚገኘው ዲብ ላይ የነበሩት አሉላ ፥ በዲሞትፎር ሁለቱን መትረየስ ተኳሾች ጣሉዋቸው ። እንደገና ጠላት የመጀመሪያውን ረባዳ መሬት ለቆ ወደ ላይ ተንጋግቶ ከከፍተኛዋ ቁብታ ላይ ወጥቶ መትረየስ ለማጥመድ ከድንጋዮች መካከል ሲገባ ከእርሱ በላቀ ፍጥነት ከመጀመሪያ ምሽጉ የደረሱት አሉላ እንደገና መትረየስ ሊተኩሱ በጥድፊያ ላይ ከነበሩት ጣሊያኖች ሦስቱን አንጣጥረው ጣሉ ።

«ወዲ ቁቢ» ከመጀመሪያው ምሽግ ሁለት ፥ ከሁለተኛው ምሽግ ሦስት ነጭ ሲጥሉ ገና ገና በወጣትነታቸው ዒላማ ሲማሩ በመጀመሪያ በሁለት ቀጥሎ በሦስት ጥይት ቸመቱት ነጭ አጥንት ትዝ አላቸውና ማቅ ማቅ እያሉ ፥ ጉራዕ ላይ በግብፅ ኩፊት ላይ በድርቡሹ አንገት ላይ በደም ያጠቡትን ጉራዴያቸውን ደግሞ መዘዙና የጣሊያኑ ጦር መከላከያ ለመሥራት ሲጣደፍበት ወደነበረው ቁብታ ወጥተው ለሸለሹት ።

በሁለት ዘርፍ የተሰለፈው ያሉላ ወታደር ከዚያች ቁብታ ላይ ተገናኙና ፥ «በነውበሬ» ደም ጉራዴውን ያጥበው ጀመር ። በዚያ ጦርነት በሁለቱ ቁብታ ላይ ከአምስት መቶ በላይ የሆነ ነጭ ወታደር ሬሳ ተከመረ ። ራስ አሉላ የነጭ ሬሳ ከተቆለለበት ቁብታ አለፍ ብላ ከምትገኘው ቁብታ ላይ ወጥተው ወደ ምፅዋ የሚወስደውን መንገድ በመነጽር እየተመለከቱ ፥



«ንግ አሸከር እዚያ ማዶ ሩጥና በዚያ በኩል ያለው ጦር ወንዙን ተሻግሮ በእነዚያ ኮረብታዎች ላይ ሆና ከምጥዋ የሚመጣ ጦር እንዳለ እንዲገጥመው ንገር» ብለው አዘዙ ። በየአቅጣጫው የነበረው ሠራዊት እንዲከት ፥ ነጋሪት ሲመታ ቱልቱላው ሲነፋ ኪዳኔ መብራቱም ፥

«ጉራው ተሟሙቋል ፥ መሬት ተደባልቋል ፤
ነጩ ከምር ፈርሶ ምስቅልቅሉ ወጥቷል ።
ለዚህ ሙያ ነው ወይ የመጣው ከባሕር ፤
የአሉላ ነፍጠኛ ቀላቀለው ምድር ።
አየነው ጉልበቱን የወንድነቱን ልክ ፤
መማሪያውን ጥሎ ሸሸሸ ሲፈተለክ ።
ሚስትህ ምነው ባየች በሰማች እናትህ ፤
በአሉላ ጉራዴ ሲበጠስ አንገትህ ።
የነማን አገር ነው ብለው ሳይጠይቁ ፤
አገር የደፈሩ እነሆ ወደቁ ።
ምነው በጠየቁ የግብፅን ወታደር ፤
ምነው በጠየቁት የድርቡሽ ወታደር ፤
እንደማይደፈር የአባነጋ መንደር»

እያለ ሲያቅራራ ቆየና ከነበረበት ቦታ ራስ አሉላ ወደ ነበሩበት ቁብታ ወጥቶ ከፊታቸው በርከክ ብሎ ፥

«ፀሐይ ጨረቃ በሉ መስክሩ ፥
ነጩ ወታደር በርዶት ሐሩሩ ፥
አላረበደም? የጠላት ጦር ፤
ሐሰቱም እንደሁ ትታዘብ ምድር ።
ሦስት ምስክር አስቆጥረናል ፤
ምድር ጨረቃ ፀሐይ ቆመዋል ።
አይደፈርም ያበሻ መሬት ፤
ፍቅራቸው ጥዑም ጥላቸው ሬት ።
መራሮች ናቸው አይደፈሩም ፤
ትኩሶች ናቸው ከጋሉ አይበርዱም ።
የአባነጋ አሽከር የጦር አውራሪስ ፤

እይተ ጠላቱ ቆላ ሲደገስ ፤
እየዳለቀው በደጋ ፈረስ ።
አንች ከረብታ ብዙ ዕዳ አለብሽ ፤
የጠላት ክምር የወደቀብሽ ፤
ለመቆው ትውልድ መንገር አለብሽ»

እያለ ሲፎክር ወዲያው ደግሞ ከራስ አጠገብ ሆኖ አራት ሜዳያን ተኩሶ የጣለ አሽከራቸው ከፊታቸው በርከክ አለና ፥

«ባለማተብ ያንተ ታማኝ ፤
ምርጥ ገበሬ ጠላት በታኝ ።
የበላው ደሙ የጠጣው ወጅ ፤
ባዳይ ግራኪ የጠላት እጅ ።
ተኩሶ የማይስት ነጭ አሽባሪ ፤
መራር ለጠላት የወገን አክባሪ ፤
የሚያዳው ፈረስ የሚከው ነብር ፤
አይደፈርም ያበቸው ምድር ።
ያንተ አሽከር ያንተ መሸሬ ፤
የሚከ አንበሳ የጦር አሞራ»

ብሎ ፎከረ ።

በነጋሪቱና በጥሩንባው ጥሪ መሠረት ጦሩ ራስ ከነበሩበት ኮረብታ ተሰበሰበ ። ራስ አሉላም ዐረፍ ብለው ከነበሩበት ደንጋይ ላይ ተነሥተው ጉራዴያቸውን እንደ ያዙ ፊታቸውን ወደ ምፅዋ አዙረው ፥

«ይህን ድል ያጐናጸፈንን አምላክ ማመስገን ይገባናል ። የእ ርሱ ኃይል ፥ የእርሱ ፍርድ ነው ቀኙን የሰጠን» አሉና ወደ ልጅ ፋንታዬ ተሰግ ዘወር ብለው ፥

«የወደቁት ወታደሮቻችን ሬሳ እየተሰበሰበ ወደ ደጋው እንዲወሰድና ቤተ ክርስቲያንና መስጊድ ባለበት እንዲቀበር ፥ ቁስ ለኛው በሰውም በከብትም እየተጫነ ተደም እንዲሔድ ፥ ምርኮ ኛውም እንዲታሰረ አሥመራ እንዲሔድ ፍርዱን እዚያው እን ሰጣለን ። ግዳይና ተኩሩም እዚያው አሥመራ ላይ ይሆናል ።



ይሆን የምሥራች ለአጼ ዮሐንስ የሚነገር ፈረሰኛ አዘጋጁ ፥ ለመ ሆንስ እዚሁ ምሽቱ መጠለያዎቻችን የታረዘ ብለው ወሰኑ ።

«በጌታ ከማነው ጦር ጋር እዳይ ተርተዋል» አሉ ደጃዝ ማች ።

«ፈረሰኛ ላክና በፍጥነት አስመጣልኝ» አሉ ።

ወዲያው ልጅ ፋንታዬ ቀረብ ብለው ፥

«ወታደሩት ምፅዋ ወርደን በዚያም የመሸገውን የጠላት ጦር እንጨርስ እያሉ ተነግሥታል» አሉዋቸው ።

ራስ አሉላም ጉራዴያቸውን ወደ ምፅዋ ሰይፈው እያወዛ ወዙ ፤

«ነገሩ ይወል ያድር እንደሆነ እንጂ ሁኔታውን ለአጼ ዮሐንስ ለእታወቀን መውረዳችን አይቀርም ። አሁን ገሥግሥን በገባ ግን ሜዳያኖቹ ጦርነት ያነሡ እንደሆነ ሕዝብ ያል ቃል ። ከሕዝብ መካከል የገባ ጠላት ሕዝብ ይዞ ይጠፋል ። ስለ ዚህ ዛሬ ወደ አሥመራ እንዲመለስ ለሠራዊቱ ይነገርውላሉ»

«ወታደሩ የማረከውን መሣሪያ እንዲመርቁለትም ቃልዎን ይጠብቃል» አለ ባሻይ መርዊ ። ራስም በንቀት አመልካች ጣቸውንና ሌሎቹን እየተመለከቱ ራሳቸውንም እያወዛወዙ ፥

«መሸፍም በምርኮ ዕቃ በስመታ በገዛ በረከት ፥ በልዩ ልዩ ዜዋና ጉብረት የዳበረ ወታደር ዕለት ፥ ፍርሐትና የርስ— በርስ መናናቅ ያሸንፈዋል ። ተዚህም ተደም ከጉባኤና ከድርቡሽ ወታ ደር የተማረከው ዕቃ ሁሉ ለወታደሮቻችን ጥቂት ጥቂት እን ዲሰጣቸው እንጂ ከሺቸው የገባውን ሁሉ እንዲይወስዱ የተ ደረገው በዚህ የተነሣ ነበር ። አሁንም ተካል ተካሉ ዕቃ ተሰጥቶ ከባድ ከባዱ ዕቃና መሣሪያ በጥንቃቄ ተቆጥሮ እንዲያዝ ብለው ወሰኑ ።

በሰላይነታቸው ተይዘው በሰንሰለት ተቆራኝተው የሔዱት እኑላሲሱ ሲቀርቡም ራስ በቁጣና በንቀት እየተመለከቱ በጉ ራዴያቸው አሾቱ ።

«እዚህ የወደቀው የወገኖቻችሁ አሬሳ ዚሁ ሀሬር እንዲለብስ ይሁን ፤ እናንተም ሬሳችሁን ቅበሩ» አሉና ለባሻይ ፈንጃይ ደግሞ ፤ «ከዚያው ከወደቁበት ይቀበሩ ፤ መቃብራቸው ለወገኖቻቸው ማስጠንቀቂያ ፤ ለኢትዮጵያ መመኪያ ይሆናል ። ምርኮኞቹን አስቆፍረህ ሬሣውን አስቀብርና ጉዞ እንዲጀመር ይሁን» ብለው አዘው በጦርነቱ መጀመሪያ ላይ ቁመው ትእዛዝ ሲሰጡበት ወደ ነበረችው ከወንዙ በስተላይ ወደምትገኘው ኮረብታ ከወጡ በኋላ ፤ አሊቃን አስጠርተው «ይህን ደስታችንን ንጉሠ ምኒልክም እንዲሰሙት ወረቀት ጽፈህ ላክላቸው» ብለው አዘዙ ።

በድሉ ሣልስት ጊንዳዕ ሲገቡ የመንደሩ ሕዝብ በደስታ እየፈነደቀ ተቀበላቸው ። አቶ ዘጊዮርጊስም ፤ «ያስለ ፍልፍ ቅጠል ያለባት ርግምቷ መንደር» ብለው ጊንዳዕን ሰደቧት ፤ «ለደረቅ መሬት ለምን እንዘምታለን?» በማለታቸው አፍረው ።

ራስ አሉላ ፤ ጊንዳዕ ደርሰው በስተምዕራብ በኩል ለጦር ምሽግነት ከመረጡዋት ተራራ ላይ ወጥተው ሻለቃ አርአያን ጠርተው ፤

«ልጄ ወዳጄ ፤

እንግዲህ ከዚህች ሆነህ አገርህን ጠብቃት ፤ ከዚያች ማዶ ካለው ተራራም ታማኝ ታማኝ ሰዎችህን አስቀምጠህ ከቆላው ወደ ላይ የሚመጣውን ልብ-በለው ። ከሐባብ የሚመጡትም ወስላቶችና በጊንዳዕና በመንገደኞች ላይ ክፉ ነገር እንዳይሠሩ ከዚህ ሆነህ ተመልከታቸው ።

እስከ ዛሬ ለፈጸምከው ጀግንነትህም ዋጋህን የምትከፍልህ አገርህ ናት ። ከእንግዲህ በኋላም ጠብቃት ፤ የሀገር ጠረፍ መጠበቅ ለትውልድ ሁሉ ባላደራ መሆን ነውና የኢትዮጵያ ክብር የማይደፈርበትን ሥራ እንድትሠራ አደራውን ሰጥቾሃለሁ ። ለእሁን ሦስት መቶ ያህል ወታደር ይሰጥሃል ። ስንቅም በቶሎ ይላክልሃል ። የሚሆነውን ነገር በየጊዜው ላክብኝ ፤ የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አምላክ የዮሐንስ ጸሎት ይጠብቅህ» ብለው የራ



ሳቸውን ዲሞትፎር ሸለሙዋቸው ። ሻለቃ አርአያም ከራስ ፊት በርከክ ብለው ፤

«ጌታዬ ያሳዘንኩት ነገር ቢኖር ይቅር ይበሉኝ አሉ።»
«እስከዛሬ በቅንነት ከማገልገል በቀር የበደልከው ነገር የለም ፤ በድለህማ ቢሆን ኑሮ ለዚህ ባለአደራነት ባልተመረጥክም ነበር» አሉዋቸውና ሻለቃን አስነሥተው ስመው ወደ አሥመራ ጉዞ ጀመሩ ።

«ቱ—ቱ—ቱ—ቱ—ስማ—ቱ—ቱ—ስማ!

ከተድዓሊ የተፈተለኩት ፈረሶች 'ድል አድርገው ጠላት በታትነው ራስም በጉዞ ላይ ናቸው ! ተዘጋጁ !' እያሉ በየደረሱበት የምሥራቹን እያበሠሩ አሥመራ ገቡ ። ራስ አሉላ ለደጃዝማች ኃይለሥላሴና ለየአገሩ አስተዳዳሪዎች የላኩት ቃል እንደ ደረሰ ታላቁ ፈንጠዝያ ሆነ ። በአሥመራ አካባቢ በአካለ ጉዛይ በሠራዬ ፈረሰኞች የምሥራቹን አደረሱ ። በየቤቱም ድግስ ተጀመረ ።

«ቱ—ቱ—ቱ—ቱ—ስማ—ቱ—ቱ—ቱ ስማ ! የአሥመራ ነዋሪ ሁሉ ስማ! ብለውሃል ። ስማ! አገርህን ሊቀማ አንተን ባሪያ አድርጎ ሊገዛ የመጣብህን ጠላት ጌታ ራስ አሉላ ድል ነሥተው በጉዞ ላይ ስለሆኑ ከየቤትህ ወጥተህ እንድትቀበል ታዘሃል ። ለድል አድራጊው ሠራዊታቸውም መቀበያ እንድትደግስ ተብለሃል ።

"አገርህን ከጠላት ወረራ ያዳናትን ፤ ሚስትህን ሊቀማ የመጣብህን ፤ ክብርህን ሊነሣ የተሰለፈብህን ጠላትህን ድል ያደረገው ሠራዊት ወደ የመንደሩና ቤቱ እስቲመለስ ድረስ ስንቁን እንድትችል ተብለሃል ቱ ቱ ቱ ቱ ቱ ቱ . . . . .» ይህን ዐዋጅ እየደጋገመ ለአሥመራ ነዋሪ ያሰማ የነበረው ቱልቱላውን እያሰማ የአሥመራን ከተማ ሲያተራምሳት ፤ ሐጎስና በረሄ የተባሉ ወጣቶች ከኋላው ደረሱና ፤

«ስማ እስቲ ባለ ቱል ቱላ » ብሎ በርሄ ሲናገር ፤
«ዐዋጅ ነጋሪ ነው የምባል" ብሎ መለሰለት ።

«ወፍጮ ነጋሪ ራሱ መቼ ነው የሚመጣው » አለ ሐጎስ ።
«ዛሬ ላይ ናቸው »
«አንተ ጠላት ገድለሃል?»
«ተኳሽ ወረድና ቁጠረው »
«ስንት ማርከሃል?»
«ያየሁትን ሲመጣ ቁጠረው»
«ሬሳቸውስ ብዙ ወታደር ሞተባቸዋል?»
«ዛድያለው የሚል ጠላት ከጎኔ ጠይቀው»
«ምንው ወንድሜ! እንዲህ ትናገራለህ?»
«ሌላ ምን ዐይነት ነገር ትፈልጋለህ?»
«ለግ እኛኮ ነገ ለመዝመት የምንችል ነን»
«ትላንትና አትዘምትም ነበር? ግን ከለከሉህ?»
«ለመሆኑ እንተስ ዘምተሃል?»
«እንዳንተ ያለ አይጠይቅም »
«ታዲ ምንድነኝ?»

«የመንደር አውደልዳይ ነህ» ብሎ ወፍጮ ነጋሪው «ቱ— ቱ—ቡግ—ብለውሃል! ቡግ ወዲ መርኅቱ ያልሆኑት ዕድሜህ ከዘመር ጋሞት በላይ የሆነህ ሁሉ የምርኮ ዕቃ ትሸከማለህና ጊንባሶ ድረስ እየወረድክ ጌታ ራስ አሉላን እንድትጎበኝ ተብ ልሃል? ቱ—ቱ—ቱ—ቱ—ቡግ—ቡግ—ቡግ ብሎ ትፈጥቸው ሔደ ።

«ጉድ መጣ!» አለ ሐጎስ እጁን እያርገበገበ፣ «አንተ ሰንቱ፣ እኔ አልናቸው! አሁን ደግሞ ጊንባሶ ወርደቸው ዕቃ ተሸ ከሙ መጣ» ሲል ጓደኛው በርሄ ተበሳጭ አይረሳን ።

«በሌላ ከለተቀኝም ዕድሜኛች ነን» አለ ።
«ሌላ ምን ይመጣብናል?» አለ ሐጎስ ።

«ከጊንባሶ ያመጣችሁትን ዕቃ በየአገሩ እየወሰዳችሁ በየ ወታደሩ ቤት አስገቡ ብንባላለህ» አለ በርሄ ራሱን እንደ ጋጋሩ እየወዘወዘ ።

«እንግዲያው ተልእኮን ወደ ጊንባሶ እንውረድና ወታደር ነት እንግባ» አለ ሐጎስ በለበጣ እየጋገር ። በርሄ ከት ብሎ



ሳቀ ከንፈሩን ገለጦ ሲያስብ ቆየና ፣
«ሲያዩ ወታደርነት አንግባና ፣
የምቶ ፈረስ ጋላቢ
የጦርነት ወሬ አሩጋቢ
የጸረት ወንዝ ተሻጋሪ

የወደቀ ጠላት አባራሪ ብለን እንፎክራለን» አለውና እየተ ሣሣቁ ሲሔዱ፣ ቀለል ያለች ሰሌፍ በበትር ያንጠለጠሉ አዛ ውንት፣ አገልግል ያነገቱ ጠና ያሉ ሴትና አንድ የፍየል መንጋ የሚነዱ ወጣት ከአገር ቤት ሲገቡ አገኙዋቸውና ፣

«ሕብይ! እንተም አብይ ከየት ትመጣላችሁ?» ብሎ ጠየቃ ቸው በርሄ ።

«ከእምባስርሃ ነው የመጣነው» አሉ አዛውንቱ ።
«ወደየት ትሔዳላችሁ?» አለ በርሄ ።
«ጌታችንን እጅ ልንነሣ»
«መኳንንቱ የሚሸኙ ነው?»

«ወይስለናሽ?» አሉ አዛውንቱ እነበርሄን ከፍና ዝቅ አድር ገው እየተመለከቱ ። «መኳንንቱን ከሸኘነው ታዲያ ራሱን እንዴት እጅ እንነሣለን?» አሉት ።

«ለራስ ጉብ ማምጣታችሁ ነው?»

«አንተ ወዲ ሰበይቲ! » አሉ ሴትየዋ ድንገት ቱግ ብለው ። «ጠላት ድል አድርጎ ለመጣ አምበሳ የሚሰጥ መተበያ ጉራ ይላ ላል ያለ ማነው?» ብለው ሲያፈጠጡበት አዛውንቱም ቀበል አድርገው ፣

«አሉላ መንደር ለመንደር እየዞረ ጉብ የሚሰበስብ ይመስል ሃል? በየቤቱ በየጠረፉ እየተዘዋወረ ግብሩን፣ ድርጎቹን እየ ሰጠ ድል የሚነሣ ጀግናዎ ነው! ዛሬ ደግሞ ይሸውና ነጠላን ወታው! ለአሉላ ፍየልና ቅቤ ይበዛበታል!» አሉ ።

«ይማሩን አቦይ ፣ ይማሩን አደይ ፣ ማሩን እርሱ ተሳስቶ ነው ። ሙክትና ቅቤስ እንድታመጡ ታዛችሁ ነው?» አለ ሐጎስ ንግግር ያማመረ መስሎት ።

«ወይለየኸ እናንተ ሰዎች ለአፋችሁ ልጓም አድርጉለት ?» አሉ ሴትዮዋ እየተቆናጠሩ ።

«ስሙ ልጆቼ ስሙ!» አሉ አዛውንቱ ወደ ሐጎስ እየተጠጉ ።

«እኛኮ የባዕድ እጅ ቀምሰናል ፤ የቱርኩ የግብጡ ጦር በአገራችን ገብቶ ሳለ ፣ በሬዉን ሙክቱና ዶሮዉን ኧረ — ዕንቁላሉ ሳይቀር ነው እየቀማ የበላው ። የመንደሩን እንስሳ ቀርቶ ሕዝቡን ፈጅቶት ነው የሔደ ። ድርቡሽ መጣ ሲሉ በጣም ደንግጠን ነበርና ጌታችን 'ድል ነሡት ! አባረሩት!' ቢሉን እጅግ ተደስተን ሳለን ደግሞ ፣

እንደገና በባሕሩ በኩል ሌላ ጠላት መጣ ማለትን ሰምተን ከነገ— ዛሬ ተወረርን እያልን በሥጋት ላይ እንዳለን አሉላ ዘመቱበት ማለትን ከመስማታችን ፣ ድል ነሡት ተብሎ ትላንትና ቢነገረን ደስ ብሎን የቻልነውን ይዘን መጣን ። የመንደሩ ሰው ሁሉ እንደኛ የቻለውን ያህል እየጫነ ነው ። ይህም የመጣነው ለራሳችን ለደስታችን ለክብራችን ነው» ብለው ሲናገሩ ፣

«ለመሆኑስ ከእምባደርሆ የዘመቱ ወታደሮች አሉ ? » ብሎ ሐጎስ ጠየቀ ።

«ወይለየኸ ? ምን ጉደኞች ናችሁ ? ጀግና ጀግናው ዘምቷል ። እንደ እናንተ ቤት እውሉ ነው መንደር የቀረ?» አሉ ሴትዮይቱ ።

«እየታዘዘ ነው የዘመተ ? » አለ በረሄ ።

«ወይለየኸ ? እውነትም ጉዶች ናችሁ? ባገር ላይ ጠላት መጣ ሲባል ጀግና ይቆጣል! ይዘምታል እንጂ ደግሞ ትእዛዝ ይጠብቃል ? » አሉ አዛውንቱ ።

«አቦይ ለምን አልዘመቱም?» አለ ሐጎስ ።



«እንዶ እናንተ ኮበሌ ብነበርኩ ጊዜ ዘምቻለሁ ። ተግብጡ ጋር ተዋግተናል ። እስቲ እኔም ተራፉን ልጠይቃችሁ? እናንተስ ለምን አልዘመታችሁም ? ጠብደሎች ናችሁ» አሉዋቸው ።

«ከተማ እየጠበቅን ነዋ» አለ ሐጎስ በቀልድ አነጋገር ፤ በርሄ ደግሞ ጠጋ አለና ፣

«ይኸስ ምንድን ነው ? ብር ነው? » ብሎ ስልቻቸውን ነካ ነካ ሲያደርግ አዛውንቱ ፈንጠር ብለው ፣

«አንተ ወዲ ሰበይቲ ዐውቄሃለሁ ሰራቂ ነህ ! እኔን ነው የምታሞኘው?» ብለው ሲያፈጡበት ዐዋጅ ነጋሪው እንደገና በዚያው መንገድ ተመለሰና ፣

«ቱ—ቱ—ቱ—ስማ—ብለውሃል ስማ ያሥመራ ሰው ስማ ብለውሃል ስማ ! ቤት ያፈራውን ፣ ጕረቤት ያወቀውን ፣ ጓዳ የደበቀውን ዐውቀንብሃልና የተቻለህን ይዘህ ጌታህን ራስ አሉላን እንድትቀበል ተብለሀል ! ይህን ብትነፍጋቸው ድል ነሽው ሠራዊታቸው ጦም ቢያድር ወዮልህ ብለዋል " ጌታ ደጃዝማችና ነጋድራስ !!

«ሰምተህ እንዳልሰማህ ፣ በጓዳህ ደብቀህ እንደ ሌለህ ብትመስል ከባሕር ማዶ ወዲህ ያለ ቄስ አይፍታህ» ብለዋል አባታችን ብሎ ሔደ። በራስ አሉላ ግቢ ብቻ ሳይሆን በታወቁት የጦር አለቆች ግቢ-ሁሉ ዳስ ተጣለ ። የአሥመራ ነዋሪ ሕዝብ እንደየችሎታው እየደገሰ ወሰደ ።

ራስ አሉላ ፣ በተለመደው አለባበስና ሥርዓት አሥመራ ሲገቡ ድብልቅልቅ ያለ አቀባበል ተደረገላቸው ። ሁለት ሦስት ጊዜ ዐዋጅ አስነግረው ድግስ አስደግሰው ነበርና የገቡት የአሥመራ ነዋሪም ለሰልፉ የወጣው የቤት ሥራውን እያጠናቀቀ ቤቱን እየቆለፈ ነበርና ከኩፊት ጦርነት ሲመለሱ የደረሰው እንዳንድ መዝረክረክ አልነበረም ።

ራስ አሉላ ፣ ማዕከላዊውን አውራጃ ይዘው ሲቀመጡ የጦር አለቆቹም እንደየማዕረጋቸው ተቀመጡና ግብር ገቡ ።

የራስ ባላንጋራ ስለታወቀም ወደ ጓዳው ገብተው ጉራ ርሰው ተጉነጣጥተው ወደ አዳራሹ ገቡና፣ ጉሮሮአቸውን አሳለ ለሰው ማይገጹቸውን ቃኝተው፣ በዘለሰኛ፤

የተለመደ ነው እንዴ ባንድ መቅናቱ
ያስደንቃል እንጂ ሲወድቅ መታየቱ ።
ብዙ አሉ የቀን ባለሟ ሙሴት
ምክረውም ነበር ገላጠው ሊያዩዋት
መርገጥ ቢያቅታቸው እፊቷምን ቃመት
እሱላ በርሆን አጥብቀሀ ዝጋው
ድንገት እንዳይገባ በቀዳዳ አውሬው ።
ሊበጥስ ነበረ ማተብን አበሻ
እሱላ ደረሰ የጦሩ ወገኛ ።
ይህ ራስ እሱላ ፍርድ መስጠት ያውቃል
መሬት ለተመኙ አፈር ያሆፍራል»

የዘለሰኛውን እንጉርጉሮ ከዚህ ላይ አበቁና በሰንጎ መገን ደገሙ፤

«የባሕሩ ጦር መቀት ቢያቃጥለው
እሳት እሱላ ተደግሲ ፈጀው
መድፍ ይዘው መጡ በሩቅ ሊመቱ
እሱላ ወጣ ከጭንቅላቱ
ተራራ ይዘው ሲመሸጉ
እሱላ ወጣ ከግሩ—እስከ አናቱ
እናን ጠላቱን ሲዘፍን ባንጉቱ
ምነው ባዩቸው የርም እናቱ
ባማወቱቸው ደርሳለት እቱ»

እያሉ ከወዲያ ወዲህ ሲንጉራደዱ ቢቆዩ ደግሞ ሁለት ምንጭ ወጅን ቸላሰሉና፤

«መጣን ብለው ላኩ ድግሱ ቢያምራቸው
እኛም አልቀረንም ሔደን አየናቸው
እሱላ አባኑ አስተናገዳቸው ።



እገር ብለው መጡ እገር በሰፋቸው
የደብሙበትን አፈር አጋጥናቸው ።
ግብሮች ደጋ ወጡ ባይ ቢያቃጥላቸው
እሳት ሆኖ እሱላ እንደዶ ፈጃቸው ።
ሉዓላቸው በስበሶ ማሊያዋች ከባሕር
የዐሊይዋን መቀት ፈልገውት ነበር፤
አስጣው እሱላ ዘርር ከፈር»

ብሎ ሲያቅራራ ባሻይ ደቢታ ዲምትሮራቸውን አጽርጠው ይዘው ከራስ እሱላ ፊት ተንበርክከው፤

«ጎዳይ በሌሊት ፀሐይ ሳይወጣ
ያሉላ ታማኝ የሰማይ ቁጣ
ሰው የለም ብለው አገር ሊይዙ
ያሰቡት ጉዞ በዛ መዘዙ
ጅራት እወጡ ካንገት ቢያዩ ።
ያንተ እሽከር ያንተ ግስላ
ቁመናው የሰው ሰመሩ ሌላ
ያንተን ወታደር ጠፍቶ አሚዳኝ
ሐሰቱም እንደሁ መስከሩበኝ
አልገደልኩም ወይ አደራርቤ
ሐሰቱም እንደሁ ይታዘብ ልቤ ።
ዘራፍ ያንተ እሽከር
ያንተ ወታደር
የጠላት መቅሠፍት ታማኝ ለሀገር»

ብለው ሲፎክሩ የጦር እለቆቹም ባዉነት ነው፣ እናውቃለን፣ ካይን ያውጣው» ብለው ሲመርቁ ራስ የወገባቸውን ጉራዴ ሸለሙዋቸው ።

ባሻይ ፈንጂይም ተነሡና፣
«የጠላት ቅሌጥም ሰባሪ
እገር ጠባቂ ወገን አኩሪ
በጠላቱ ላይ ተወርዋሪ
በዲምትሮር አነጣጣሪ»

ብለው ሲፎክሩ የጦር አለቆቹ «እውነት ነው ፣ እውነት ነው ከዐይን ያውጣዎ» እያሉ ሲመሰክሩ ፣ ራስም የወገባቸውን ሸጉጥ ሸለሙዋቸው ። ቀረርቶው ፣ ፉከራው ፣ ምርኮው ሲደረደር ዋለ ። ወደ ማታ ራስ ከተቀመጡበት ሲነሡ ያዳራሹ ግብረ - በላ ተነሣ ።

«ስማችሁ ወዳጆቼ ልጆቼ —አንበሶቼ » ብለው ራስ ንግግር ሲያሰሙ ፣ አዜማሪው ማሲንቋቸው «ዝምበል — ዝምበል የሚል ዜማ ሲያስተጋቡ አዳራሹ ረጭ አለ ። እርሳቸውም በአዳራሹ ውስጥ ያለውን ሠራዊታቸውን ግራና ቀኝ ተመለካከተው፣

«ዛሬ የሠራነውን ዛሬ ዘርዝረን ተናግረን አናበቃውም ፤ ድል ሲገኝ ከልክ ዐልፎ መፈንጠዝ ፈጣሪን ወደ መርሳቱ ያደርሳልና በልኩ መሆንና ለፈጣሪም ምስጋና ማቅረብ ይገባናል።» ስለ ተማረኩት ጣሊያኖች ጉዳይ ለአጼ ዮሐንስ አስታውቄአለሁና ምላሹ እስኪመጣ እንጠብቃለን ። ያገር ልጆች የተባሉት ግን ለጠላት ገብተው ወግተውናል ። ኢትዮጵያን ወግተዋል ፣ አጼ ዮሐንስ ወግተዋል ፤ እኔን በድለዋልና ነገ ሁላችሁ የጦር አለቆችና መኳንንት ባላችሁበት እንደ በደላቸው ይፈረድባቸዋል» ብለው ሲያስታውቁ «ይገባል ! ይገባል! ማለፊያ ነው ፣ ይሁን» እያሉ የጦር አለቆቹና ወታደሮቹ እያወኩ ግብር መልስ ሆነ ።



# ች ሎ ት

በማግሥቱ በራስ አሉላ አዳራሽ የጦር አለቆቹ መኳንንትና ቀሳውስት በተገኙበት በምርኮኞቹ ላይ ለመፍረድ ችሎት ተነጠፈ ። በሥርዓቱም መሠረት ራስ አሉላ ከመካከል ፣ የጦር አለቆቹ ግራና ቀኝ ተቀመጡ ።

በሰንሰለት የተቆራኙ በርከት ያሉ እስረኞች እየገቡ መደዳውን ሲቆሙ ባሻይ ፈንጃይ ተነሥተው ፣

«አገራችሁንና መንግሥታችሁን ከድታችሁ ፣ ከጠላት ጎን ተሰልፋችሁ ወግታችሁናል ። የጌታ ራስ ትእዛዝ ሆኖ እዚህ ደረሳችሁ እንጂ እንደኛ ቢሆን ኑሮ ፣ እዚያው ተድዓሊ ላይ በፈረድንባችሁ ነበር ። አሁንም መኳንንቱ የታያችሁን እንድ ትፈርዱ እጠይቃለሁ» አሉና ሲቀመጡ ፣ ባሻይ በኩሩ ቀልጥፈው ብድግ አሉና ፣

«ሀገራቸውን ፣ ንጉሠ ነገሥታውቸን ፣ ጌታ ራስ አሉላን ከድተው ከጠላት ጋር ሁነው እኛን ከወጉን ምን ውጣ ውረድ ያስፈልጋል? በሕዝብ ፊት ሲሰቀሉ ይታየኛል » ብለው ተቀመጡ ። ከምርኮኞቹ አንዱ ።

«አቤት ! አቤት ፣ ጌታዬ አቤት ፣» ብሎ ሲጮህ ፣

«ተናገር ተብለሃል ተናገር» አሉ አጋፋሪ ።

«እኛ አገራችንን በውዴታችን አልወጋንም ፤ ተታለን ተገድደንና ሳናውቅም ነው የወጋነው ። ባላምባራስ ክፍለ የሱስ ሰብ ሰበው አታለውን ነው የተሰለፍነው ። ከድሃ ጥፋት ከጌታ ምሕረት አይጠፋምና ማሩን» ብለው መሬት ላይ ወደቁ ። በዚህ ጊዜ ሹም አብድል ቃድር ተነሥተው ፣

ብለው ሲፎክሩ የጦር አለቆቹ «እውነት ነው ፣ እውነት ነው ከዐይን ያውጣዎ» እያሉ ሲመሰክሩ ፣ ራስም የወገባቸውን ሽጉጥ ሸለሙዋቸው ። ቀረርቶው ፣ ፉከራው ፣ ምርኮው ሲደረደር ዋለ ። ወደ ማታ ራስ ከተቀመጡበት ሲነሡ ያዳራሹ ግብረ - በላ ተነሣ ።

«ለማችሁ ወዳጆቼ ልጆቼ —አንበሶቼ » ብለው ራስ ንግግር ሲያለሙ ፣ አዜማሪው ማሲንቋቸው «ዝምበል — ዝምበል የሚል ዜማ ሲያስተጋቡ አዳራሹ ረጭ አለ ። እርሳቸውም በአዳራሹ ውስጥ ያለውን ሠራዊታቸውን ግራና ቀኝ ተመለከከተው ፣

«ዛሬ የሠራነውን ዛሬ ዘርዝረን ተናግረን አናበቃውም ፤ ድል ሲገኝ ከልክ ዐልፎ መፈንጠዝ ፈጣሪን ወደ መርሳቱ ያደርሳልና በልኩ መሆንና ለፈጣሪም ምስጋና ማቅረብ ይገባናል።» ስለ ተማረኩት ጣሊያኖች ጉዳይ ለአጼ ዮሐንስ አስታውቄአለሁና ምላሹ እስኪመጣ እንጠብቃለን ። ያገር ልጆች የተባሉት ግን ለጠላት ገብተው ወግተውናል ። ኢትዮጵያን ወግተዋል ፣ አጼ ዮሐንስ ወግተዋል ፤ እኔን በድለዋልና ነገ ሁላችሁ የጦር አለቆችና መኳንንት ባላችሁበት እንደ በደላቸው ይፈረድባቸዋል» ብለው ሲያስታውቁ «ይገባል ! ይገባል! ማለፊያ ነው ፣ ይሁን» እያሉ የጦር አለቆቹና ወታደሮቹ እያወኩ ግብር መልስ ሆነ ።



# ችሎት

በማግሥቱ በራስ አሉላ አዳራሽ የጦር አለቆቹ መኳንንትና ተሳውስት በተገኙበት በምርኮኞቹ ላይ ለመፍረድ ችሎት ተነጠፈ ። በሥርዓቱም መሠረት ራስ አሉላ ከመካከል ፣ የጦር አለቆቹ ግራና ቀኝ ተቀመጡ ።

በሰንሰለት የተቆራኙ በርከት ያሉ እስረኞች እየገቡ መደዳውን ሲቆሙ ባሻይ ፈንጃይ ተነሥተው ፣

«አገራችሁንና መንግሥታችሁን ከድታችሁ ፣ ከጠላት ጎን ተሰልፋችሁ ወግታችሁናል ። የጌታ ራስ ትእዛዝ ሆኖ እዚህ ደረሳችሁ እንጂ እንደኛ ቢሆን ኑሮ ፣ እዚያው ተድዓሊ ላይ በፈረድንባችሁ ነበር ። አሁንም መኳንንቱ የታያችሁን እንድትፈርዱ እጠይቃለሁ» አሉና ሲቀመጡ ፣ ባሻይ በኩሩ ቀልጥፈው ብድግ አሉና ፣

«ሀገራቸውን ፣ ንጉሠ ነገሥታቸውን ፣ ጌታ ራስ አሉላን ከድተው ከጠላት ጋር ሁነው እኛን ከወጉን ምን ውጣ ውረድ ያስፈልጋል? በሕዝብ ፊት ሲሰቀሉ ይታየኛል » ብለው ተቀመጡ ። ከምርኮኞቹ አንዱ ።

«አቤት ! አቤት ፣ ጌታዬ አቤት !» ብሎ ሲጮህ ፣

«ተናገር ተብለሃል ተናገር» አሉ አጋፋሪ ።

«እኛ አገራችንን በውዴታችን አልወጋንም ፤ ተታለን ተገድደንና ሳናውቅም ነው የወጋነው ። ባላምባራስ ክፍሌ የሱስ ሰብስበው አታለውን ነው የተሰለፍነው ። ከድሃ ጥፋት ከጌታ ምሕረት አይጠፋምና ማሩን» ብለው መሬት ላይ ወደቁ ። በዚህ ጊዜ ሹም አብድል ቃድር ተነሥተው ፣

«ጠዋት በምፅዋ በኩል ሲገባ ያውኑ መጀመሪያው ላይ ጸለም፤ ከዚህ ቀደም ቱርክ በዚያ በኩል ገብቶ እስከ ድባርዋ ሲዘልቅ ብዙ ሕዝብ እንደ ፈጀ የታወቀ ነው። የእናንተ አባቶችም ለቱርክ እንገዛም ያሉ ሲገደሉ፤ ሐዋተ—ቢሶቹ አብረውት ተሰለፈጥል። ከምፅዋ ተነሥቶ ከረን ሲገባም እንደዚሁ ብዙ ሕዝብ ፈጀለ። ለደርቡሽ አንገዛም ብለው ከወደቁት ሐቀኞች መካከልም የእግዚአብሔር ሹም የነበሩት ደግለል ሐመድ መንበሩ ላይ ሲዋጉ በጀግንነት ሞተዋል። እንደዚሁም ከነገደ ባርያ ሼኽ አረይ አባብ ኩፊት ላይ ከደርቡሾች ጋር ሲዋጉ ወድቀዋል። አሁንም እንደሆን ትዛንት በመርኃት ድል የሆነው ጣሊያንም ምፅዋ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ብዙ ሕዝብ መፍጀቱን ታውቃላችሁ። ከዚህ በላይ ሕዝብ ፈጅቷል። እናንተም ሐገናት አይደላችሁም ይህን ሁሉ እያወቃችሁ እያያችሁና እየሰማችሁ ለጠላት አድረሳችሁ አገራችሁንና ንጉሣችሁን ከመጋችሁ ለትለቀሉ ይታያኛል» ብለው ተቆጡ።

መኳንንቱ እርስ - በርሳቸው መተያየትና መንሾካሾክ ጀመሩ። ራስ አሉላም ሁሉንም አንድ ባንድ በመመልከት ላይ እንዳሉ ደጃዝማች ኃይሉ ጦሳ ፤

«ለመሆኑ የኛ ባላባቶች ናቸሁን» ብለው ጠየቁ።

ራስ አሉላም እንደ መቆጣት አሉና ፤

«ባላባትነ ማለት ከተወላጅ ጋር ከመግኑ ጋር፤ ሆና ባዕድ ሲዳብንበት ግለት ... የሚከፍል ነው። እንዳይደፍረው ማንኛውንም መሥዋዕትነት የሚከፍል ነው። እንዲህ ሆኖቸውን ለምኣላቸው ብቻ የተሰለፉና ወገንና አገርን የዕዱ ለለም፡ ባላባትነት ቀርቶ ተወላጅነት እንደሌላቸው የነው መቆጠር ያለባቸው። አገርም ወገንም ከደዋልና ፍራኞች ናቸው።

ከዚያ በኋላ፤ መኳንንቱና የጦር አለቆች እየተነሡ እንደ ታያቸው እየተቹ ምርኮኞች እንዲሰጥሉ ፈረሱ። ተጥለው ራስ ታያቸው እየተቹ ምርኮኞች እንዲለቀቁ ፈረሱ። ተጥለው ራስ አሉላ ከመገበራቸው ሲነሡ በችሎቱ የነበሩት ሁሉ ተነሡ። ራም፤



«የኢትዮጵያ አምላክ፤ የዮሐንስ ጸሎት እመንተን ከለተላቸው ነል። ግንባቸው እጅና እግራቸው እንዲቆረጥ፤ ግንባቸው እዩ ንግሯቸው እንዲርጋን ፈርዶባቸዋል። ሩሩ ግን ምንም በደርሱ በቁመናቸው ማሰታየት አንገብ ስላይደለ ምና ምናምኞ በልቅ ባት ፤ በግዳታና እንበለ ዕውቀት የወገን ስለሰራትና በወርቅ በወርቅ ጅራፍ እንዲተው በንጉሡ ነገሥት የሐንስ ስም ፈርደ ለሁ » ብለው ፈረዱ።

የዶጋሊ ድል በተገኘ ማግሥት ራስ አሉላ ድል አድራጊ ንታቸውን ገልጸው ለአጼ ዮሐንስ የላኩት መልእክት መልሰ መጣ። ከመተሉ የነጋሡው መልእክተኛ ከራስ አሉላ ዘንድ ቀርቦ እጅ ነሥቶ በበንተር መካከል የያዛትን ወረቀት ሲሰጣቸው ከተቀመጡበት ተነሥተው ተቀበሉትና፤

“ጃንሆይ ደኅና ናቸው?” ብለው ጠየቁት።

ራስ አሉላ አጼ ዮሐንስን “ጌቶቹ ጌታዬ” እያሉ ከማቆላል በቀር “ጃንሆይ” ብለው ሲጠሩ ተሰምተው አያውቁም ነበር ይላል። በዚያች ዕለት ግን “ጃንሆይ” ብለው በመጠየ ራቸው አብረዋቸው የነበሩት መኳንንቶቻቸው በመገረም ግራ ሳይገባቸው አልቀረም ነበር። የሆነ ሆኖ ለመልእክተኛው ግራ ራያ እንዲሰጣቸው አዘዙና ወረቀቱን እንደ ቆሙ አነበቡት።

መልእክቱም እንዲህ የሚል ነበር።

“ይድረስ ተራስ አሉላ

በምፅዋ በኩል ከመጡት ጣሊያኖች ጋር ጦርነት ገጥመህ ድል መንሣትህን ገልጸህ የላከህልኝን ተመልክቼዋለሁ። ወደዚያ ሔደህ ጦርነት እንድትገጥም የፈቀድኩልህ ማን ነው? ያዘመትኩቸው ወታደሮች የኔ እንጂ ያንተ አሽከሮች አይደሉም። ይህን በማድረግህና ባለህ ጦርነት በመግጠምህ ቶሎ እጅህን እንድንቆርጠው ዕወቅ። የሐንስ ንጉሠ ነገሥት።”

ራስ አሉላ ወረቀቱን ካነበቡ በኋላ ተቀመጡና በበርቱ [illegible] ታሏት፤ በስመመንገም ውስጥ ወደቁ፤ በወረቀቱ ገለበታቸ

ውን እየጠበጠቡ መተከዝ ጀመሩ ። ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ቀስ ብለው ተጠጉና ፤

"ምነው ጌታዬ አገር ደኅናም አይደል! ጃንሆይ ደኅና አይደሉምን?" ብለው ጠየቁ ።

"ከጣሊያኖቹ ጋር ጦርነት በመግጠምህ ቀኝ እጅህን እቆርጠዋለሁ" ብለዋል ንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ" አሉና ከተቀመጡበት ድንክ አልጋ ተነሥተው ሊወጡ ሲሉ ፤ "በሚያምኑት በቅዱስ ሚካኤል ይሁንብዎ! በወደቁት ጀግኖችዎ አጥንት ገዝቼዎታለሁ ፤ ከዚህ ቤት እንዳይወጡ" አሉና ደጃዝማች ከራስ እግር ላይ ወደቁ ።

"ማነትህን እንጣልኝ ፤ ልቀቀኝ ንጹሑን ልቤን ንጹሕ ነፍስ ንጹሕ ፀሐይ ልመግበው ! ንጹሐን ዐይኖቼ ንጹሐን አገር ይመልከቱበት ! ልቀቀኝ የት እንዳልሔድ ነው?" አሉ ራስ ከግራቸው ጫማ የወደቁትን አማቻቸውን እንኳ በዐይኖቻቸው ለመመልከት ጠልተው በር—በሩን እያዩ ።

ነገሩን የተመለከቱ የቤት አሽከር ሁኔታውን ከደጅ ለነበሩ መኳንንትና የጦር አለቆች ነገረ ። እየተሻሙ ገቡ ። ምንም እንኳ ምክንያቱን ባያውቁም ፤ ሁኔታውን በመመልከት ብቻ ሁላቸውም ከራስ እግር ላይ እየተነባበሩ ወደቁ ።

ራሳቸውም ቢሆኑ ከድንክ አልጋቸው መነሣታቸውን እንጂ ወደየት እንደሚሔዱም ዓላማ አልነበራቸውም ። ከዚያ ሩጠው እንደ ወፍ በርረው ከዮሐንስ ጫማ ወድቀው ይማሩኝ ለማለት ነበር? ነበር? ወይስ ደብረቢዘን ገዳም ገብተው ለመደወል ነበር? ወይስ ምጽዋ ወርደው እጃቸውን ለጀኔራል ካርሎ ጅኒ ሰጥተው ማረኝ ሊሉ ነበር? ወይስ እንዳሉት በግቢያቸው እየተንጎራደዱ ከኩፊትና ከተደአሊ ጦርነት በድል አድራጊነት ሲመለሱ በንጹሕ ልቡ ዕልል ብሎ ፤ በንጹሕ ፍቅሩ ሆ—ብሎ የተቀበላቸውን የአሥመራን ነዋሪ ሕዝብ "ፍረደኝ" ሊሉት ነበር? ብቻ ያም ሆን ይህ በንዝር መሬት ለመራመድ አልቻሉም ነበርና ከተነሡበት መቀመጫ ላይ ዘፍ ብለው ፊታቸውን ቅጭም አድርገው ፤



"የመላዋ ትግራይ መኳንንት ፤ መላው መሳፍንት ፤ መላው የዮሐንስ ባለሟል ሁሉ መክሮ ዘክሮ ፤ 'እኛ እያለን የአንድ ገበሬ ልጅ እንዴት አገር ይገዛል ፤ እንዴትስ የራስ ወርቅ ይደፋል?' ያለው ይህን ወረቀት ለማጻፍ አይደለም ? ዳር—ዳሩን ሲል የኖረው አሾክሿኪ ሁሉ ተሳካለት አይደለም ?" አሉና ድንገት ብድግ ብለው ፤

"ይቁረጡት ፤ ነገ ካልፈለጉት ይቁረጡት ፤ ነገ ካልተዋረዱ ይቁረጡት ፤ የትላንቱን ጋሻቸውን ትላንት የሸለሙትን ነገ የማይፈልጉት ከሆነ ይጉመዱት !

"እስከዛሬም አገሬን ፤ ወገኔን ንጉሠ ነገሥቴን በድዬ ከሆነ የንጹሐን አምላክ ይፍረደኝ ። ትላንት በጉራዕ ፤ በኩፊት ፤ በተደአሊ የወደቁት ጀግኖች ንጹሕ ደም ሁላችንንም ይፋረደን ።

«ዓለም ካልጣቀባቸው ፤ ጀግና ካልታዘባቸው ፤ አገሪቱ ካልተፋረደቻቸው ይቁረጡት ! ለኔ አንድ እጅ ብዬ ፤ ለኔ ደም መፍሰስ ብዬ ፤ የኔ እጅ ይቆረጣል ብዬ አልፈራም ፤ አልሸሽም ። አገሬን አላሳፍርም ። በኔ የተነጣም የድሃ ገበሬ ዘር አይሰደብም! ገበሬም ኩሩ ነው ፤ ጀግና ነው ልበ—ሙሉ ነው ፤ መካች ነው ፤ ነጭ ከጥቁር አምራች ነው ። ለአገሩ ነጻነት ለዜግነቱ ክብር ፤ ለሰብአዊነቱ ክብር ለሕልውናው ክብር ለወንድነቱ ክብር ከጠላቱ ጋር ይዋጋል ። ጠላቱንም እየጣለ ይወድቃል ። የገበሬ ክንድ ፤ የገበሬ ልብ ፤ የገበሬ መንፈስ ፤ ብርቱ ቆራጥ ጠንካራ መሆኑን ያላወቁ ካሉ በኔ ቀኝ እጅ መቆረጥ ይረዱታል ። ስለዚህ አልሸሽም ፤ አልዋሽም ይማሩኝ ብዬም አልለምንም!

"ትላንት ጠላቶቼን የጣለው የአሉላ እጅ ዛሬ በትግራይ መኳንንት ዐድማ ቢቆረጥ የደም ጠብታው ጎርፍ ሆኖ ያጥለቀልቃቸዋል ። እሳት ሆኖ ያቃጥላቸዋል ፤ ይቁረጡት! ቀኙ ቢቆረጥ በግራዬ ያገሬን ጠላት እመክታለሁ! " አሉና ዐይኖቻቸውን አፍጥጠው አንገታቸውን እያወዛወዙ ዝም አሉ ።

ራስ አሉላ ፤ ስሐጢ ወርደው ከኢጣሊያኖች ጋር ጦርነት በገጠሙበት ቀን አጼ ዮሐንስ ለጀኔራል ካርሎ ጅኒ አንድ ደብዳቤ ጽፈው ነበር ፤ በዚያ መልእክታቸው ላይ ፤

"በመጀመሪያ ዊልጌ ያዘው አውን ደግሞ በሐረጌ ላይ ሆነው እርድ መሥራት ጀመርኩ ፤ የያዝኩው አገር የኔ እናደ ለምን በእዚህ በእስጥያል እንድትለኝ" ብለው ወይቶውትም ነበር ።

ከተድአሊ ጦርነት ሦስት ዓመታት ቀደም ራስ አሉላ ከኢጣሊያ መልእክተኞች ጋር ሲነጋገሩ ፤

"የሆነ ሆኖ ሊታገሡኝ አይገባም ፤ ጦርነቱን ከመጀመሬ በፊት ነገሩን ለንጉሠ ነገሥቱ አሳታውቄ ነበር ። ወታደሮቼ እን ደመሆኔ መጠን በተሰጠኝ ትእዛዝ መሠረት ተግባሬን ፈጽሜ አለሁ" ብለዋቸዋል ።

ራሳቸው አፄ ዮሐንስም ለንጉሠ ... በጻፉት ደብ ዳቤ ላይ ፤

"በመጨረሻው ግን ጣሊያኖቹ ሰሐጢ ድረስ መጡ ። ራስ አሉላም የያዙትን አገር እንዲለቁ ሊጠይቋቸው ቢሔዱ የኢ ጣሊያን የጦር አለቃ እምቢ ብሎ ለጦርነት በመዘጋጀቱ ጦር ነት ገጠመ" ብለዋል ።

ምንም እንኳን አፄ ዮሐንስ የቀጣ መልእክት በሰላማዊ ምክንያት የሚታይበት ነበር ። "ጦሩ ሙሉ ትቶ ሁኔታው ግልጽ ምክንያት የሚታይበት ነበር ። 'ቁርስ ዳኛ ፤ ራስ አሉላ' ተብለው ከተሾሙ በኋላ በግዛቶችና በድርቡቦች ላይ ያገ የመሰለ ታላቅ ድል በኋላ ከተጐናጸፉ በኋላ ፤ ከብራቸውን የሚቀናቀን ትልቅ በአጠገ ባቸው ብቅ ብሎ አገራቸውን ይዞ "አላፈረኝ" ሲሏቸው የሚ ገባቸው አልነበሩም ። የሚፈሩም አልነበሩም ። በተለይም ሰሐጢን ታግሠው አልነበሩም ። ለማውጣት ራሳቸው ለራ ቀርቶ ምንዳሩም ከግብጾች እጅ ነጻ ለማውጣት ግልፅ ቃል የገቡና ባለቤትም ቆራጥነት ዓላማቸውን በግልጽ ያሳወቁ ናቸው ።

እንግዲህ ያሉባን ማንነትና ዓላማ አጣርቶ ላወቀ ታሪክ ተመራማሪ የሚቀርብለት ጥያቄ ፤ "በተድአሊው ጦርነት የንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዝ የለበትም ብሎ ከመጨነቅ ፤ የኢጣሊያ ጥቅሙን ርምጃ የአሉላ ማንነት የሚቀበለውና በዝምታ ሊመ ለከተው የሚችል ነበር ወይ" የሚል ይመስላል ።



እርግጥ ነው ፤ በተድአሊው ጦርነት ንጉሠ ነገሥቱ በመ ጀመሪያ ተቆጥተዋል ።

ከጦርነቱ ቀደም በእንግሊዞች አማካይነት ነፍገ በሰላም ለመጨረስ ብርቱ ፍላጎት ነበራቸው ። በኢጣሊያኖቹ ግፈኛ እጅግ ግዝፍና መበሳጨት አሰምተው ነበር ። ታዲያ እነ ሱሉ የሚያውቁትን ጀኔራሎቻቸውን ከፍተኛ ቁጥር ለነበረው ሠራ ዊት አዛዥ አድርገው አገራቸውን የያዘውን ወገን እንዲጠ ነቀቁበት ሲላኩባቸው መልሱም ጦርነት እንደሚሆን አስቀ ድመው ባደረጉት ይተራሉ ተብሎ ይገመታል ! ያም ሆነ ይህ ንጉሠ ነገሥቱ የቀኝ እጃቸውን ቀኝ እጅ ሊቆርጡ ይችርና ሁለተኛ እንኳ ጠንከር ያለ ቃል አልተናገሩም ። እንዲያውም የጀኔራላቸውን ውለታና ሥራ ደግፈው ከሚከራከሩበት ምርጫ ላይ ደረሱ ።

በአጠቃላይ አመለካከት ግን የተድዓሊው ጦርነት በዐሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ በነበረው በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛውንና ደግሞን ምዕራፍ ይዟል ። በአፄ ዮሐንስና በኢጣሊያኖችም መካከል ብርቱ ፋክክር በመቀስቀሱ ንጉሥም ምኒልክን ሊያበረታታና ሊያነሳሳት ምክንያት ሆኗል ። የራስ አሉላም ማንነት ቆራጥነትና የጦር ስልት ችሎታ ለመ ጀመሪያ ጊዜ በአውሮፓ ጦር ላይ ድል ሊጐናጸፍ በመቻሉ ፤ ዝና ቸውን ከአድማስ እስከ አድማስ አሸጋገረው ። ለዐድዋው ጦርነ ትም የመጀመሪያው ምዕራፍ ሆኖ ለመጠቀስና የኢትዮጵያው ያንን ማንነት ለመላው ዓለም ለማሳወቅ መነሻ ሆኗል ።

ራስ አሉላ ፤ በጥር ወር ተድአሊ ላይ ያገ የመሰለ ድል ተጐናጽፈው ፤ ወዲያው በየካቲት ወር ደግሞ ፤ ምፅዋ ለነበረው የኢጣሊያ ጦር አዛዥ በአሥመራና ምፅዋ መካከል የነበረው የንግድ ግንኙነት መቋረጡ ተገቢ ያለመሆኑንና እንዲቀጥል ከልብ የሚፈልጉ መሆናቸውን ፤ ኢጣሊያኖችም ምፅዋ ብቻ ለጊዜው እንዲቀመጡ እንጂ ከዚያ ውጭ እንዲወጡና የሚያደ ርጉ ... መሆኑን ገልጸው ጽፈዋል ። እርሱም በወዳጅነትና በሰላም ለመኖር የሚፈልግ መሆኑን ፤ ለወዳጅነቱም ማስረጃ

አሉላ ያስሩዋቸው ጣሊያኖች እንዲለቀቁለት አጥብቆ የሚመኝ
መሆኑን ጻፈላቸው ።

የተድአሊ ጦርነት ያስገኘላቸውን ውጤት በቀስታ ለማጣ
ጣም የፈለጉት አሉላ እንደኛ ከመቀሌ ቤተ መንግሥት ተከታ
ትሎ የሚሰጠውን ውሳኔ መጠባበቅ ሲሆን ፣ በሌላ በኩል ደግሞ
ከኢጣሊያኖች ጋር ለመነጋገር የሚያስችላቸውን ዘዴ መቀየስ
ጀመሩ ። ስሐጢና ተድአሊ ላይ የአሉላን ክንድ የቀመሱት ጣሊ
ያኖች አግራቸውን ሰብስበው ምፅዋ ላይ ብቻ በመቀመጣቸው
ንጉሠ ነገሥቱ ሲደሰቱበት ፣ አሉላ ደግሞ ዱላቸውን ካቀመሱ
በኋላ ቀደም ብሎ ከእንግሊዞች ጋር ያደረጉት ስምምነት እንዲ
ከበር ፣ በጦርነቱም ከኢጣሊያኖች ጋር ሆነው የወጉዋቸውን ባላ
ምባራስ ክፍለ የሱስን ፣ ፊታውራሪ ደበበ አርአያንና የእነርሱም
ተከታዮች የነበሩትን የአሳውርታ ተወላጆች ከሠፈራቸው እያወጡ
ጣሊያኖች እንዲሰጡዋቸው ፣ ምናልባትም ደግሞ ጣሊያኖች
እንደገና እንሰራርተው ለጦርነት የተሰለፉ እንደሆነ በጃቸው
ያሉትን እስረኛ ጣሊያኖች ከፊት አስቀድመው ለመዝመት እን
ዲመቻቸው የጣሊያኑን የጦር አለቃ እያሰዘቡ ንጉሠ ነገሥቱ
የኢጣሊያኖችን ጠላትነት አምነውላቸው ጦርነቱን እንደገናም
ለማስነሣት እንዲፈቅዱላቸው ለማድረግ ረቂቅ ዘዴያቸውን በት
ዕግሥት ማቀነባበር መረጡ ።

የጣሊያኑ የጦር አለቃ የአሉላ ጥያቄ እጅግ ስለ አሳሰበውና
አምነው የተጠጉትን እነ ክፍለ የሱስንም አሳልፎ ለመስጠት
በመቸገሩ ክፍለየሱስን ወደ ሐልሐል እንዲሸሽ ሰደደው ።
ለክፍለ የሱስና ለተከታዮቹ ስለ አገልግሎታቸውና ወደፊትም ሲያ
ያስፈልግ ለሚሰጡት አገልጋይነት በወር አንድ ሺህ ብር
ደመወዝ መደበላቸው ። አሉላ እንዳቀዱትም አጼ ዮሐንስ በኢ
ጣሊያኖች ጠላትነት ስላመኑላቸው በመጋቢት ወር ‘ጣሊያኖች
የወጉህ እንደሆነ መጠባበቂያ እንዲሆንህ’ ብለው በርከት ያለ
ሠራዊት ላኩላቸውና ወዲያው ደግሞ ወደ መቀሌ እንዲሔዱ
በዚሁ ወር መጨረሻ ላይ ስለ ጠሩዋቸው እንኳን ቀኝ እጅ መቆ
ረጥ ገልምጫም እንደማይደርስባቸው የተማመኑት አሉላ ሳያ
ላውሉ መቀሌ ሔዱ ።



አስቀድመው ማለፊያ ማለፊያ የባሕር ዕቃዎች ገጸ—በረ
ከት ወደ ቤተ መንግሥቱ የላኩት አሉላ ፣ ከእሥመራ እንደገ
ሠገሡ መቀሌ ገብተው ልረፍ ወይም የመንገድ ልብሴን ልለ
ውጥ ሳይሉ በቀጥታ ወደ ቤተ መንግሥቱ ሔደው ጌታቸው
የሸለሙዋቸውን ዲሞትፎር ካሸከራቸው ተቀብለው ፣ ጌታቸው
ከነበሩበት እልፍኝ ገብተው መሬት ስመው ሲቆሙ ፣ “በል
ና—ሳመኝ መቼስ ምን ይደረጋል!” ብለው ሩቅ አገር ሔዶ
ተሰይቶ ኑሮ እንደ ተመለሰ የበኸር ልጅ አቅፈው ሳሙዋቸው
እንጂ ፣ ‘እንዴት ሰነበትክ’ ብለው እንኳ ዝም አላሉዋቸውም ።

ወደ እልፍኝ ከመግባታቸው በፊት ድንጋይ ተሸክመው
ገብተው ‘ይማሩኝ’ እንዲሉ ባለሙዋሎች ሲመክሩዋቸው ፣

‘እኔ አሉላ ወንዱ? ምን በበደልኩ? ያገሬን ጠላት የጌታ
ዩን ጠላት የጣልኩበት ጌታዩ የሸለሙኝን ዲሞትፎር ይዤ
እገባለሁ እንጂ ፣ እንደ ወንጀለኛ ድንጋይ ተሸክሜ አልገባም’
ብለው ነበር የገቡት ።

“በል እንኳን ደኅና መጣህ ! አሁንም ሒድና አንተም ሰው
ህም ዕረፉና ነገ እንነጋገራለን”፡ ብለው ንጉሠ ነገሥቱ ጊዜያዊ
ዕረፍት ፈቀዱላቸው ።

በማግሥቱም በመጀመሪያ ገብተው እጅ ነሥተው ሲቆሙ፣
“ዱለኛዉ ተቀመጥ”፡ ተባሉና በተለመደው የክብር ቦታቸው
ተቀመጡ’ ።

“ሁሉንም በሚገባ በዝርዝር ተረድቼዋለሁ ። ሐሳቤ በሰላም
ውል ያገኛል መስሎኝ ነበር ። ደም እንዳይፈስ መጠንቀቅ ይገ
ባል ብዬ ነበር ። መቼስ ምን ይደረጋል ። አሁንስ እንደ ቀድሞው
ወደ ላይ ብቅ ጥልቅ ይላሉ ወይንስ ምጥዋ ብቻ ናቸው ?” አሉ
አጼ ዮሐንስ “ዱለኛው” ብለው አዲስ የቅጽል ስም ያወጡላ
ቸውን ጀኔራላቸውን እየተመለከቱ ።

“ለጊዜው ከምጥዋ ብቅ ለማለት አልቻሉም ፣ ውሎ አድሮ
ግን ማስቸገራቸው የማይቀር መሆኑን ጌታዬ እንዲረዱት ያስ
ፈልጋል” አሉ ራስ አሉላ ፊታቸውን ቅጭም አድርገው ።

“ለርሱ ለርሱ መቼም እያደር ይመከርበታል ፤ አስተዳደሩም ግን መጠንቀቅና በዕለም ሊያልቅ እንዲችል መመካከር ይገባል” አሉ ንጉሡ ነገሥቱ ።

ራስ አሉላ ፣ መቀሌ ስንቅበተው ስለ ነበረ ፣ ከመቀሌ በስተቀር ከተከዜ መልስ እስከ ቀይ ባሕር ባለው አገር ሁሉ ሊሾሙ ነው እየተባለ ሲወራላቸው ሰንበቱ ። በመጨረሻም ወደ ግዛታቸው ሲመለሱ የአጼ ዮሐንስ የልብ ታማኝ የነበሩት ራስ ሐጎስ ‘አብርሀ ይበንገበት’ ተብለው የአሉላም ልዩ ተመልካችና አማካሪ ዐይነት ሆነው አብረው ሔዱ ።



# አማላጅነቱ

ምንም እንኳ ጣሊያን ተድአሊ ላይ የደረሰባትን ዱላና ውርደት ለመመለስ ጦርነት እንደምታስነሣ የማያጠራጥር መሆኑን ቢረዱትም ቶሎ ፣ በመጀመሪያ አሥመራ—ምጽዋ መንገድ እዋታው እንዲጠበቅ ፤ የእንሬታውራሩ ደበበ አርአያ እጅ እንዲሰጣቸውና ንጉሡ እንዲተማል ራስ አሉላ ቢጥሩበትም ፣ ምጽዋዕ የነበረው የጣሊያን ጦር አዛዥ ግን የራስ አሉላ ተቃዋሚዎች ከነበሩ የጐሳና የሃይማኖት ተጠሪዎች ከወገቢዶ እለቆች ጋር ጀምሮት የነበረውን ሽርክና በሰፊው በመቀጠሉ ነገሩ እያስቆጣቸው ስለ ሔደ ፣ ለሁለተኛው ዙር ጦርነት የጦር ኃይላቸውን ማጠናከር ግዴታቸው መሆኑን ተገነዘቡት ።

“ያለፈው ዐለፈ ፣ ለወደፊቱ በመካከላችን መግባባት እንዲጠናከር ንግድ እንዲስፋፋ እፈልጋለሁ” እያሉ እየላኩ የኢጣሊያንን ጦር አዛዥ ለማለዘብ ቢሞክሩም በሀገረ—ኢጣሊያ የተንጣጣው የቁጭት ግፊት መንግሥቱንም እያስገደደው በመምጣቱ ፣ “ኮርፖ ስፔዲሲዮናሌ ዲ. አፍሪካ” በሚል ሥያሜ በጀኔራል ሳሌታ ኃላፊነት የዘመቻ መምሪያ ተከፈተ ። ከሻያ ሺህ በላይ የሚሆኑ ወታደሮች ከሠላሳ ስምንት መድፎች ጋር በዘመቻው መምሪያ ሥር እንዲመደቡም ተደረገ ። በዚያም ሠራዊት ኃይል ክንድ የተማረከው የኢጣሊያ ውትድርና ስምና ክብር እንዲታደስ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን የውትድርና ባለሙያዎችም አመኑበት ። እንግሊዞችም በልዩ ልዩ ዘዴ የራስ አሉላን ቁርጠኝነትና ዝግጅት ከተረዱ በኋላ ከኢጣሊያ መንግሥት ጋር በቅድሚያ ተነጋገሩበት ። ኢጣሊያኖች ተድአሊ ላይ የደረሰባቸውን ውርደት ብድር ለመመለስ ለሁለተኛ ጊዜ በሚያስነሡት ጦርነት እንደገና ድል የሆኑ እንደሆነ የኢጣሊያ ብቻ ሳይሆን የመላው አውሮፓ ውርደት ሊሆን እንደሚችል ፣ አንዳንድ የፖ

ለቲካ ጠበብት አጥብቀው ስለ አሰቡበት ነገሩ በስምምነት እንዲወስን ውትወታቸውን ቀጠሉ ። የኢጣሊያ የውትድርና ጠበብት ደግሞ ፤ "በአንድ አፍሪካዊ ክንድ የተሰበረውን ቅስማችንን ለማደስ ይህን ሁሉ ዝግጅት ካደረግን በኋላ መመለሱ የባሰንን ውርደት ስለሆነ ፣ ዮሐንስም ሆኑ አሉላ ሊቀበሉት የማይችሉትን ጥያቄ እናቅርብና እምቢታቸውን ካገኘን በኋላ ፣ 'እርቅ ፣ ጠይቀን እንቢ አሉን' የሚል መግለጫ ሰጥተን በጦር ኃይል የምንፈልገውን ቀበሌ መያዝ እንችላለን" ብለው ሰስጠነከሩ ፣ የፖለቲካ ጠበብትም ተስማሙላቸውና ፣

1. "አሉላ በዶግአሊ ላይ ላደረሰብን ውድቀት ኢትዮጵያ ይቅርታ እንድትጠይቀን ፣

2. ሰሐጢ ዊአና አይለት የተባሉት ቀበሌዎች የኢጣሊያ የግዛት ክልል ሆነው ሐባብና አሳውርታ የተባሉት ወረዳዎች በኢጣሊያ የበላይ ጠባቂነት ሥር እንዲተዳደሩ ። ፣

3. የከረንን ምሽግ ጨምሮ የበጎስ ወረዳ የእንግሊዝና የኢጣሊያ ይዞታ እንዲሆን" የሚሉ ነጥቦች አቀረቡ ።
እንዲሁም በጽሑፍ አይሥፈር እንጂ ራስ አሉላም ከመ
ረብ ምላሽ ግዛታቸው እንዲነሡ የሚል ጥያቄም ጣሊያኖች አቀረቡ ።

እንግሊዞችም እነዚህኑ ነጥቦች ይዘው ከአጼ ዮሐንስ ጋር ለመነጋገር ፈቃደኞች መሆናቸውን ለጣሊያኖች ካስታወቁ በኋላ ፣ በኢትዮጵያና በኢጣሊያ መካከል ዕርቅና ሰላም እንዲሆን የእንግሊዝ ንግሥት የቪክቶሪያ መልእክተኛ ሆኖ ሎርድ ፖርታል የሚላክ መሆኑን ለአጼ ዮሐንስ ገልጸው ጳፉላቸውና መልእክተኞቹ ምጽዋ ገቡ ።

ሎርድ ፖርታልም ምጽዋ እንደደረሰ ይህንኑ ገልጾ ወደ አሥመራ ለመዝለቅ ፈቃድ እንዲሰጡት ለራስ አሉላ ላከባቸው። አሉላም ጥያቄውን ተቀብለው ከመኳንንቶቻቸው ጋር ከተመካከሩበት በኋላ ወደ አሥመራ እንዲመጣ ፈቀዱለት ።



በሎርድ ፖርታል የሚመራው የእንግሊዝ መልእክተኞች ቡድኑ አሥመራ ደርሶ ተገቢው አቀባበል ከተደረገለት በኋላ ከራስ አሉላ ጋር ለመነጋገር ከአረፈበት ቦታ ወደ ግቢያቸው ሲያመራ አሉላም ከነመኳንንቶቻቸው ከበር ድረስ ወጥተው ተቀበሉና ወደ አዳራሽ ይዘውት ገቡ ።

ከትውውቁም ቀጥሎ ፣

"ትላትና ያላነጋገርንዎ ከድካማችሁ ዐረፍ እንድትሉ ብዬ ነው ፣ በደኅና ገባችሁ? በመንገድስ አልተቸገራችሁም?" ብለው ራስ አሉላ ንግግሩን ጀመሩ ።

ፖርታልም መኳንንቱን አንድ ባንድ ተመለከተቶ የአፍንጫውን ሜፍ ነካ ነካ አደረገና ፣

"ገባኝ አመሰግናለሁ ! እውነት ነው ! እኛም ማታ ደክሞን ነበር ። ተቀባዮች ሰዎች፥ ስለላኩልንና እዚህም ስንደርስ ስለ ተደረገልን አቀባበል ከልብ አመሰግናለሁ ። በመንገድም ብዙም የደረሰብን ችግር የለም ። ብቻ ከእንዳንድ ቦታ ላይ እንበሶች ሳያስፈራሩን አልቀሩም ነበር" አለና ማቅ ማቅ አለ ።

"አዎ አገሬ" ብለው አሉላም ፈገግ ብለው ፖርታልንና መኳንንቱን ተመልከተው ፣ "አገሬ የብዙ አንበሶች አገር ናት። ተኩላዎች ተሹለክልከው ሊገቡባት አይችሉም" ሲሉት ፖርታል ራሱን እያወዛወዘ ማቀ ። ቀጠል አደረገናም ፈገግ ብሎ የነበረውን ገጽታውን ኮስተርተር አደረገና ፣

"በእናንተና በጣሊያኖች መካከል በተፈጠረው ግጭት በጣም አዝነናል" አለና ትክ ብሎ ተመለከታቸው ።

"እኛ ደግሞ አገራችንንና ክብራችንን የደፈረውን ጠላት ድል በማድረጋችን ተደስተናል" አሉት ከአርሱ እጥፍ በሆነ ኮስታራነት ። ፖርታል የእርሳቸውና የመኳንንቶቹ ገጽታ ሲለዋወጥበት ተመለከተና ፣

"ቢሆንም ነገሩ ለጦርነት የሚያደርስ አልነበረም" ብሎ አንገቱን ደፋ አደረገ ።

“ጊዜኛ ደግሞ ጦርነት የምንገጥመው አገራችንን ደፍሮ ነጻ ነቷን ከሚተናኮል ጠላት ጋር በመሆኑ ለጦርነት የሚበቃ ሆኖ ነው ያገኘነው” ብለው ሊመልሱለት መኳንንቱም አንገት አንገታቸውን እያወዛወዙ ፤ ያለፋን ንግግር ሊያረጋግጡላቸው ፖርታል ተመለከትና ፤ “መቼም ያለፈው አልፎአልና ምን ይደ ረጋል ለወደፊቱ ግን ይህን የመሰለ ነገር እንዳይደገም አጥግ መናለሁ” ብሎ ሐሳቡን ተቀበለውት እንደሆነ ለማረጋገጥ ሊሊ መኳንንቱን ተራ—በተራ ተመለከታቸው ።

“እንዳሬን ከደፈሩ መድገም ብቻ አይደለም ይመላለሳል” ብለው አሉላ ዐይናቸውን ጉልተው ሊመለከቱት ፤ መኳንንቱ ቁም ከመሬት ጋር ሊደባልቅ በሚችል ቁጣ ሊያፈጠጡበት ጨለፍ ጨለፍ አድርጎ እያቸውና ነገር ማጽናናቱን ተረድቶት እንገቱን እንደገና ሰበር አድርጎ ቆዩና ፤

“በውሳታችሁ መካከል ሰላም እንዲሰፍን ንጉሥ ጂኦቶ ሪያ ስለ አሰቡበት ፤ ስለዚህ ጉዳይ የዘነትን ደብዳቤ ለአጼ ዮሐ ንስ ለማድረስና ለመነጋገር ወደ መቀሌ ለመሔድ ነው የመጣ ሁት ። ስለ ጉዳዩም የእርስዎን ሐሳብ በቅድሚያ ለማወቅ እወዳ ለሁ” አሏቸው ።

“ወደ መቀሌ ለመሔድ ከሆነ ሐሳብዎ የሚያስፈልገዎ ትን ርዳታ ሁሉ አደርጋለሁ ። ግን ዋናው መልእክታችሁ ምን ድን ነው?” አሉት በጥርጣሬ ስሜት ።

“መልእክቱ ምስጢር ነው ። እንዳደርስ የታዘዝኩትም ለን ጉሡ ነገሥቱ ስለሆነ ፤ ሁሉንም ዝርዝሩ ለእርስዎ ለማስረዳት እቸገራለሁ” ብሎ መለሰ ፖርታል የእፍረትነቱን ማፍ እንደገ ከፍ እያደረገ ።

“ስሙ ወይ ጌታ ፖርታል” አሉና ራስ አሉላ አንገታቸ ውን እያወዛወዙ ቆይተው ፤ “አዬ ጌታዬ” በመጀመሪያ ምን ግን በጠባቂነት እንቀይበት ብላችሁ ስለ ጠረፋችሁን ተከታ ትን ወሰ ተቀውልን የከጠናችሁ ለእናንተ ነበር ። እናንተ ግን ከመልሱ ጋር በምሥጢር ተነጋግራችሁ መሬታችንን ለማ ችሁ” አሉና ከድንክ አልጋቸው ራስን በኩል የነበረውን



ጭራ እንሥተው ከፊታቸው የነበሩትን ዝንቦች ጨፍጭፈው ጭራቸውን መልሰው አስቀመጡና ፤ ምድሩ ላይ የሠፈሩትንም ጣሊያኖች እንደ ዝንቦቹ ለመቸብቸብ መቁረጣቸውን ለእንግ ሊዙ መልእክተኛ ለማስረዳት ከንፈራቸውን ነከስ ነከስ አድ ርገው ፤ “ይታዘቡኝ ! ዛሬ በኛ መሬት እናንተ ተመሳጥራች ሁበታል ። በግልጽ ደግሞ የምትጣሉበትና የምትዋጉበት ጊዜ ይመጣል ። የዛሬው ምስጢራችሁ በታሪክ የሚገለጽበት ጊዜ መድ ረሱ አይቀርም ። አሁንም ቢሆን ወደ አጼ ለመሔድ ከፈለጉ ወረቀቱን ያሳዩኝ ሐሳብዎንም ይንገሩኝ” አሉና ፊታቸውን ቅጭም አድርገው ተመለከቱት ።

እንግሊዛዊው መልእክተኛ ነገሩ ያለቀ የደቀቀ መሆኑን ለንደንና ሮም ያቀነባበሩት ምሥጢር መቀሌ ሳይደርስ አሥ መራ ላይ መገላለጹን ፤ የእርሱም ምሥጢራዊው ተልእኮው መክሸፉን ተረዳው ። አሉላን ተራምዶ እንኳን ጦር ምስጢ ርም ለማለፍ የማይቻል መሆኑን አመነበት ። ከዚያ በኋላ ሽን ጡን ገትሮ መከራከር እንጂ አሉላን አምልጦ በአሉላ ላይ ለመወሻከት እንደማያዋጣው በሙሉ ልቡ አመነበት ። ብቻ ምስጢሩን እንደ ጸጠረ መቀሌ አድርሶ ለመፍታት ከማንገራገሩም መረታት እንደማይገባው አመነበትና ፤

“ዋናው ሐሳባችን” አለና ራሱን ጨረፍ አድርጎ ተመልክቶ ዐይኖቹን ቁራ በተራ ወደ መኳንንቱ ወራወራቸውና ፤ “የኛ ምኞ ትማ ጣሊያኖች ከምጽዋም ወደዚህ እየወጡ ለሐጢን አልፈው እስከ ደጋው መሬት ድረስ ለመግባትና ለመኖር እንዲችሉና የታ ሰሩባቸውም ሦስቱ መሐንዲሶቻቸው እንዲለቀቁላቸው ከንጉሡ ነገሥቱ ጋር ለመወያየት ነው” አለና በዐይኑ—ሕሊናው ይማ ፀናቸው ጀመር ። ከት ከት ከት ብለው ራስ አሉላ የለበጣ ሣቅ ሲሥቁ መኳንንቱም አብረው አባጩበት ። ራስም ያስቀመጡትን ጭራ እንደገና እንሥተው እያወራጩት ፤

“ስሙ ወይ ጌታው ፖርታል! እኔ የሮማ ጠቅላይ ገዥ ሆኜ ስሔድ ያን ጊዜ ጣሊያኖችም ስሐጢ ድረስ ሲመጡ ይችላሉ ። አንድ ጊዜ ክንዴን አሳይቻቸዋለሁ ። ራሱ ቀይ ባሕር የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ወሰን ሆኖ ኖሯል ፤ ይኖራልም ።” አሉትና እርሱንም መኳንንቶቻቸውንም ተራ በተራ እየተመለከቱ ቆዩና ፤

“ሦስቱ ጣሊያኖችም ሰላዮቻቸው ናቸው ። እንዲለቀቁላችሁ ከፈለጋችሁ ደግሞ ለተደፈረው መሬትና ክብሬ ካሣ መክፈል አለባችሁ ፤ ቀጥሎም ጴጥሮስ የተባለውን ኢትዮጵያዊ የት እንዳ ደረሱት ለማወቅ እፈልጋለሁ ። በሕይወት የሚኖርም ከሆነ እርሱ ራሱ በጁ ወረቀት እንዲጽፍልኝ እፈልጋለሁ” አሉት ።

“አይደለም ልክ አይደሉም ፣ ያሠሩዋቸው ጣሊያኖች መሐንዲሶች ናቸው” አለ ፖርታል ድርቅ ብሎ ።

“ምን ሆኑብኝ?” አሉ ራስ አሉላም ከእንግሊዙ በላቀ አኳኋን ድርቅ ብለው ። “ምነው? ምን ሆኑብኝ እነሻለቃ ፒያኖ ናቸው መሐንዲሶች? እኔን ካላመኑኝማ ነገሩ በቃው እዚሁ ላይ ይብቃን ፤ ከፈለጉም ከሰላዮቹ ጋር ይነጋገሩ ። ከእነርሱው እውነቱን ያገኙታል ” አሉና ራስ አሉላ እንግሊዛዊውን እንግዳቸውን በትዝብት ተመከቱት ።

“ ማለፊያ ነው ፣ ለማንኛውም ቢሆን እነርሱን ላነጋግራቸው እፈቅዳለሁ” አለ ፖርታል ። “ ደስ ይለኛል ፣ የሚገኙትም እዚሁ ከግቢው ውስጥ ስለሆነ ይመጡልዎትና ትነጋገራላችሁ አይከፋኝም” አሉ ራስም የሰላዮችን ሰላይነትን በሚያረጋግጥ ስሜት ።

“ለመሆኑስ እስረኞች እንዲለቀቁ የሚፈልጉት ካሣ ምን ያህል ይሆናል?” አለ ፖርታል ።

“መሣሪያና ገንዘብ ነው የምጠይቀው” አሉ ራስ ።

“ ምን ምን ያህል?”

“ጣሊያኖች ከምጥዋ ለቀው እስቲወጡ ድረስ የአገሬ ነጋዴዎች ወደ ምጥዋ ሲመላለሱ ላያስቸግሩ ማንኛውም ዕቃ ሲገባና ሲወጣ ላያደናቅፉ ፣ በተጨማሪም መድፍ መትረየስ ጠመንጃና ብር ከከፈሉ ሦስቱን ሰላዮች እለቃለሁ”አሉ ራስ አሉላ እጆቻቸውን እየጨባበጡ ።

“መልካም ነው ፣ በዚህ በዚህስ እስማማችኋለሁ ፤ ሌላስ?” አለና ፖርታል ትክ ብሎ ተመለከታቸው ።

“ሌላ የሚፈልጉማ እነርሱ ናቸው” አሉ ራስ ።



“እስረኞቹንስ መቼ ላነጋግራቸው እችላለሁ?” አለ ፖርታል ።

“አሁኑኑ ሊመጡልዎ ይችላሉ” ብለው ራስ አሉላ አጨብጭበው አሽከር ጠሩና ፣

“ንሣ እባክህ ሰላዮቹ ጣልያኖች እንዲመጡ ንገር” አሉ ። በሁለቱ መካከል ለደቂቃዎች ያህል ዝምታ ሲሆን ጊዜ ፣

“የእርስዎን አስተያየትኮ አላወቅሁትም” አለ ፖርታል የዝምታውን ጭጋግ ለመግፈፍ ያህል ብሎ ።

“እኔማ” አሉ ራስ በሁለት እግሮቻቸው መሬቱን እየተመተሙ ፣ “የኔማ ሐሳቤም ሆነ ቁርጥ ያለው ቃሌ ጭብጥ ዐፈር አልሰጥም ነው ። ከዚህ ሌላ ሐሳብም ቃልም የለኝም ። ከፈለጉ ይህንኑ በመሐላ ላረጋግጥልዎ ”አሉት ።

ፖርታል ቃል መተንፈስ ተቸግሮ በሚያቅማማበት ሰዓት አጋፋሪው ገባና ፣ “እስረኞቹ ጣሊያኖች መጥተዋል” ብሎ ተናገረ ።

“አስገባቸው” አሉ ራስ ቆጣ ብለው ።

ሦስቱ ጣሊያኖች አንዳንድ እጃቸውን በድግ ተቆራኝተው ሲገቡ ፖርታል ተነሥቶ ተቀበላቸው ። ራስ አሉላ ግን ፊታቸውን ወደ ግድግዳው አዙረው ዐይናቸውን እንኳ ለማየት መፀየፋቸውን አሳዩዋቸው ።

“ይኸ በየእጃቸው ላይ የተተበተው ነገር ምንድን ነው?” አለና ፖርታል ራስን ጠየቁ ።

“አገሬን ደፍረው ገብተው ፣ እኔን አታለው ፣ እጅና እግሬን በብረት ሊያስሩኝ የመጡትን ነው እንደዚህ በጨርቅ የተበተብናቸው” አሉት ።

“ለመሆኑ የታሰራችሁበት ነገር እውነት ነው?” ብሎ ፖርታል ጣሊያኖቹን ሲጠይቅ ፣ ራስ አሉላ ቀበል አደረጉና ፣

"እንደ ልባችሁ እንድትነጋገሩ ልውጣላችሁ" ብለው ብድግ አሉ ። ፖርታልም ፈጥኖ ተነሣና ፣

"ምሥጢርኮ የለንም!" አላቸው ።

"ምሥጢራችሁንማ እምላክ ገልጦባችኋል ፤ አሁንም ቢሆን ጉዳዩንም ተነጋገሩ ፤ ስትጨርሱ እመጣለሁ ይላኩብኝ" ብለውት ወጡ ።

ፖርታልም አንገቱን ወደፊቱ እየወረወረ ነገሩን ተቀበለውና ወደ ጣሊያኖቹ ዘወር ብሎ ፣ በመጀመሪያ ማንነቱንና የተላከበትን ጉዳይ ከነገራቸው በኋላ ፣ "ለመሆን እነርሱ የሚሉትንስ ነገር ታምኑበታላችሁ? የሰጣችሁት ቃል አለ?" ብሎ ጠየቃቸው ። ሻለቃ ፒያኖም ቀበል አደረገና ፣ "ከእንግዲህ ወዲያ እውነቱን ከደን የሚሆን ነገር የለም ። ለምሥጢራዊ ሥራ መምጣታችንን ደርሰውበታል ። የመጣንበት ዋናው ተግባር ምፅዋን እንዲጎበኙ አባብለን ወስደን ቢስማሙ ከኛ ጋር ሆነው ንጉሣቸውን እንዲከዱና እንዲወጉዋቸው ፣ ይህን የሚቃወሙ ከሆነ መርከባችንን ይጎብኙልን ብለን አስገብተን አስረን ወደ ሮማ ለመውሰድና ሀገሩንም ያለ ምንም ተቃዋሚ ለመያዝ የሚቻልበትን ሁኔታ ሁሉ እንድናዘጋጅ ነበር ። ግን ገና እንዱንም ሳንጀምረው ነው ምሥጢራችንን የደረሱበት" አለ ።

"እንዴት ሊደርሱበትስ ቻሉ ? ምስጢ ውስጥ ሰላይ ይኖራቸው ይሆን? ነገሩንስ እምናችሁ!" ብሎ ፖርታል ጠየቀ ።

"ሊኖራቸው ይችላል ፤ እኛ እንደምንገምታቸው አይደሉም ፤ አስተሳሰባቸውና ዘዴያቸው ላቅ ያለ ነው ። ስለ ምሥጢር ሥራ መጣን ዐወቁብን ፤ ጦርም አሰለፍን አሸነፉን ፤ የሚያስደንቅ ችሎታ አላቸው ፤ መሳሳታችንን ያወቅነው አሁን ነው" አለ ባሊቢኒ ።

"ለመሆኑስ ያንገላቷችኋል?" አለ ፖርታል ።

"ለአሽከርና ለባላገር መቀለጃዎች ሆነናል" አለ ፒያኖ ከንፈሩን እያኘከ ።

"በሥራችን ልክ አላስቸገሩንም ፤ የበቀላም ነገር አላሳዩ ቁንም" አለ ባሊቢኒ ፣ ሻለቃ ፒያኖን እየገላመጠ ።



"ከዚህ ወዲያ ምን ሊያደርጉን ኑሩዋል!" አለ ፒያኖ ከባሊቢኒ ላይ እፍጥጦ ። "ሊገድሉንም ይችሉ ነበርኮ" አለ ባሊቢኒ ።

"ያማ የክብር ክብር ነበር ፤ በጥቁር እጅ ከመታሰር ነጭ በሠራው ጥይት መሞትን እመርጥ ነበር" አለ ፒያኖ ንዴቱ እንደገና ተቀስቅሶ ዕንባውን እያስፈሰሰው ።

"በሌላው አገርኮ ቢሆን ኑሮ ሕይወታችሁ እስከ ዛሬ አይገኝም ነበር ። መቸም ስሕተት ተሠርቷል ። አሁንም የሚጠይቁትን ካሣ ከፍለን ለማስለቀቅ እንለምናቸዋለን" አለ ፖርታል ።

"አዎ ! ለዛሬ እኛ እንከፍላለን ፣ በእጥፍ የሚከፍሉበት ጊዜ ደግሞ ይመጣል !" አለና ፒያኖ ዛተ ።

"የትላንትናው ተንኮል ዛሬ ከተገለጠ የዛሬው ደግሞ ለነገ ይጋለጣል ፤ አሁን የሚያዋጣው ይቅርታ መጠየቅ ብቻ ነው" አለ ፖርታል ።

"አዎ! ይኸው ብቻ ነው ። ሌላ ምንም ዘዴ የለም ፤ መከራችን ከከሸፈ በኋላ መግደርደር አያዋጣንም" አለ ባሊቢኒም ።

"እንግዲህ እናንተን ለማስለቀቅ እነርሱ የሚጠይቁትን ሁሉ ለመፈጸም እስማማለሁ ። እናንተም ጥፋታችሁን ማመኑና ይቅርታ መለመኑ ነው ነገሩን ከፍጻሜ የሚያደርሰው ። በመጀመሪያም አስቀድማችሁ ሳትጠይቁና ሳታጠኑ መምጣት አልነበረባችሁም ። ከዋናው ተልእኮአችሁ የሚብሰው ጥፋት ደግሞ ይኸው ነው ። አሁን እንግዲህ ለራስ ቢነገራቸውና መጥተው ማንኛውንም ነገር ብንነግራቸው ይሻላል" አለ ፖርታል ።

"የሚሻለውም ይኸው ነው" ብሎ ባሊቢኒ ሲያጨበጭብ ከበራፉ ላይ የነበረ ልጅ ገባ ። ባሊቢኒም ፣ አማርኛ ማወቁን ለማሳወቅ ሲል ፣

"መርቢል ለጌቶች ንገር" አለው ልጁ እጅ ነሥቶ መለስ እንዳለ ። ዋናው አጋፋሪ ገቡና ወደ ፖርታል ጠጋ ብለው ፣

"ጌቶች ባለ ጉዳይ እያነጋገሩ ነው፣ ለመሆኑስ አመኑልዎ? ወይስ ዐይናችንን ግንባር ያርገው ብለው ድርቅ አሉ፤ ተበድ ለናልስ አሉዎ?"ብለው ጠየቁ።

"አልካዱም፣ አላግረሩም፣ አመስግነዋል" አለ ፖርታልም።

"ምሕረት ከለመኑ የኛ ጌታ መሐሪ ናቸውና የመከራ ጨር ቃቸው ያቀልላቸው ይሆናል" ብለው አጋፋሪ ሲወጡ፣

"ሁሉምኮ ዕውቂኝ ሰገዱልኝ ባዮች ናቸው፤ አሁን እሱን ምን ያገባዋልና ነው የሚቀባጥርብን" አለ ሳሊቢኒ ብሽቅ ብሎ።

"ግዴለም ዛሬ ይለፍልፍ እኛም ጊዜ ይኖረናል" ብሎ ፒያኖ ከመናገሩ ራስ ከነመኳንንቶቻቸው ሲገቡ ፈረንጆቹ ተነሥተው ቆሙ።

"ጥፋቱና በደሉ ወደማን አዘነበለ?" አሉና ራስ ፖርታ ልን እየጠየቁ ተቀመጡ። ወዳጅዎን የእንግሊዝን መንግሥት ለማስደሰት ሲሉ ይቅርታዎን ቢለግሡልን በታሪክ ውስጥ ሲያንጸባርቅ የሚኖር ታላቅ ምሳሌ ይሆናል" አለ ፖርታል።

"ነገሩኮ በውል ማለቅ አለበት" አሉና ራስ አሉላ ቁጥ ሲማፀናቸው የነበረውን ፖርታልን አስቀመጡት።

"በውል ማለቁን አስማማበታለሁ፤ ግን ምን ዐይነት ውል ነው የሚያስፈልገዎ?" ብሎ የጭንቀት ጥያቄ ሰነዘረ።

"ቅድም ነግሬዎታለሁ፤ ገንዘብ፣ መድፍ፣ መትረየስ፣ ጠመንጃ ማምጣት አለባቸው። በተጨማሪም ነጋዴዎች ሳያስቸግሩ ጲጥ ሮስ የተባለውን ወዳጅንም የት እንዳደረሱት የሚያረጋግጡ ልኝ ከሆነ ለመስማማት እንችላለን" አሉ።

"ማለፊያ ነው፤ ይኸው ጲጥሮስ የሚሉትስ ምንዎ ነው? ከቤተሰብዎ አንዱ ነው?"

"ያገሬ ልጅ፣ ወዳጄ ወዳጄ ነው?"



"የት ይኖር ነበር?"

"ማንነቱንና ሥራውን በኋላም ያደረሱበትን እነርሱው ያውቃሉ።"

"ማለፊያ ነው፣ ጀኔራል ጅኒን እጠይቀዋለሁ" ብሎ ፖር ታል ማስታወሻ ጻፈ።

"እዎ ታስርም እንደሁ እጁን እንዲያስረክቡኝ እፈልጋ ለሁ። ገድለውትም ከሆነ ቁርጡን ያስታውቁኝ" አሉ አሉላ።

"ማለፊያ ነው፣ አሁን ለእነዚህ ይቅርታ ያድርጉልኝና ከእ ስር ነጻ ሆነው የጠየቁትን እስቲያሟሉ ድረስ በዚሁ ይቆያሉ" አለ ፖርታል ተነሥቶ።

"ማሩኝ የሚል ሰው እንዲህ ሆኖ ነው? እስረኞቹ ጥፋታ ችን ነው ብለው ከጌቶቹ እግር አይወድቁም?" አሉ ባሻይ በኩሩ ቆጣ ብለው።

"እዎ እዎ እንደ ተረዳሁት ይቅርታ መጠየቅ የሚገባችሁ እናንተ ናችሁና፤ ኑና ይቅርታ ጠይቁ" አለ ፖርታል።

ጣሊያኖቹ ተነሥተው ሳሊቢኒና ሳቦርኪስ ወደፊት ራመድ ቀረብ ብለው ጐንበስ ሲሉ፣ ፒያኖ ደግሞ በነበረበት እንደ ቆመ አንገቱን ደፋ ሲያደርግ፣ ራስ አሉላ ሲነሡ መኳንንቱም ብድግ አሉ።

"በበኩሌ የኢትዮጵያን ስምና ታሪክ ለማስከበር ስል ይቅር ብያለሁ። ልብ ይስጣችሁ፣ ለወደፊቱም ቢሆን የሰው አገርና ክብር አትድፈሩ፤ በል አጋፋሪ ድጉን አውልቅላቸው ፍታቸው፤ እኔንም ይቅር በሉኝ" ብለው ጎንበስ ብለው ቀና አሉ።

አጋፋሪው፣ የጣሊያኖቹን ሰላዮች እጅ ከፈታላቸው በኋላ ሁሉም ሲቀመጡ ግብሩው ቀረበ።

በማግሥቱ ራስ አሉላ አጃቢና ስንቅ አዘጋጅተው ከልዩ መልእክተኛ ጋር ፖርታልን ወደ አጼ ዮሐንስ ሰደዱት።

ቀጥለውም ምስቱን የኢጣሊያ ሰላዮች ለመልቀቅ ግን በቅድሚያ ጴጥሮስ የደረሰበትን ወይም ያለበትን ለማወቅ ስለፈለጉ እነሳሊቢኒ ምፅዋ ለነበረው የኢጣሊያ ጦር አዛዥ ደብዳቤ እንዲጽፉና ሁኔታውን እንዲያስታውቋቸው ጠየቋቸው ። በጉዳዩ በክረን የነበሩትም የኢጣሊያ ሚሲዮኖች ስለገቡበት ወደ አሌክሳንደሪያ መልእክተኛ ሰደው ፣ “እባክህ ደህንነትህን የሚናገር ደብዳቤ ስጠን” ብለው ጠየቁት ። እርሱም ፣ “የወረሳችሁኝን ገንዘቤን በሦስት እጥፍ አድርጋችሁ ካልሰጣችሁኝ አልጽፍም” ስለአላቸው ኢጣሊያኖች እርሱ ባመነው ልክ የወረሱትን ገንዘቡን እንደ ጠየቀው በሦስት እጥፍ ከፈሉትና ለራስ አሉላ ቀጥሎ ያለውን ደብዳቤ ጻፈላቸው ።

“ይድረስ ለአርበኞች አርበኛ ፣

ከራስ አሉላ

ዘውእቱ ቱርክ ባሻ ።

እንኳን እግዚአብሔር ዐቅፎ ደግፎ የሀገርዎን ጠላት ለመጣል አበቃዎ ። ከእርስዎ ይልቅ እኔን ደስ አለኝ ። ኢትዮጵያ እስከአሁን ድረስ በሌላ እጅ አልተገዛችም ። ዛሬም እንኳን የጠላትን ቀንበር ሰባበሩላት ። እንግዲህም አይሰነፉ ፣ ይጠንቀቁ ። እኔ በደግና በቅዱስ ማርቆስ በእስክንድርያ አለሁ ። ተወርሶ የነበረውን ገንዘቤንም በሦስት እጥፍ ተቀበልኩ ። ለእርስዎ እግዚአብሔር ይስጥልኝ ፣ በእርስዎ ዘንድ የታሠሩት ኢጣሊያኖች ሀብታሞች ናቸውና በጦርነት ያጠፉትን ገንዘብ ሳይከፍሉ አይልቀቋቸው ። ቢሆንልኝ በሽቦ አድርጌ እመጣለሁ ። በጸሎትዎ አይርሱኝ ።”

ኢጣሊያኖች ይህን የእነርሱን ወንጀለኛነትና ውርደት እንዲሁም ቅጣት የሚያስረዳውን ደብዳቤ በጥንቃቄ ወስደው ለራስ አሉላ አስረከቡ ። ጴጥሮስ ባሳሰበውም መሠረት ምስቱ ሰላዮች ሻያ አራት ፣ ያሻ አራት ሺህ ብር ሊከፍሉ በሚሲዮኖቹ ዋስትና ሳልቢኒና ፒያኖ ተራ በተራ ሲለቀቁ ፣ ሳቦሬቅስ ግን ስለሁለት ምክንያቶች በራስ አሉላ ግቢ በቁም እስረኛነት እንዲቆይ ተወስኖበት ነበር ። የነበሩትም ምክንያቶች ፣



አንደኛ ራስ አሉላ የጠየቁት ገንዘብ እስቲከፈል ፣

ሁለተኛ ፣ ቀደም ብለው ወደ ኢየሩሳሌም ሔደው የነበሩትና ወደ ኢትዮጵያ እንዳይመለሱ ኢጣሊያኖች ከልክለዋቸው የነበሩት አባ ወልደ ሰማያት በምጽዋ በኩል ገብተው አሥመራ እስኪደርሱ ድረስ ነበር ።

ነገር ግን ፣ ከብዙ ወራት በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ ተቀባይነት ያልነበረው ግን ገንዘብ በመላኩና መምህሩም ምጽዋ እንዳይገቡ ኢጣሊያኖች ከልክለዋቸው ወደ ኢየሩሳሌም በመመለሳቸው ራስ አሉላም በተፈጸመባቸው ማታለል ተቆጥተው በጉዳዩ ገብተው በዋስትና የፈረሙትን ከረን የነበሩትን ሚሲዮናውያን ለሁለት ወራት ያህል አስረው በምሕረት ለቀቋቸው ።

ለንደንና ሮም ተመሳጥረው ያረቀቁትን ውል አጼ ዮሐን ስም እንዲስማሙላቸው ፖርታል ሲያቀርብላቸው ፣

“ምጥዋንም ቢሆን እኔ አልሰጠኋቸውም ፤ እንግሊዝ ናት የሰጠቻቸው ፤ ስለሰንሒትም ጉዳይ ቢሆን ከእናንተ ጋር ባደረግነው ውል የተመለከተ ነው ። ስለዚህ አሁን አገሬን ለጣሊያን እንድሰጥ ልትጠይቁኝ አይገባም” ብለው ፊታቸውን ቅጭም አደረጉና ዘወር አሉበት ። በአዳራሹ ውስጥ ለደቂቃዎች ዕድሜ ከባድ ዝምታ ታመቀበት ። በዚያ ላይ ደግሞ የራስ አሉላን ከመረብ ምላሽ ግዛት መዛወር ማንግቱ ዋጋ እንደማይኖረው የተገነዘበው ፖርታል ፣ አጼ ዮሐንስንና የአዳራሹን ጣራ እያፈራረቀ በማመልከት ዝምታውን ለመግፈፍ በሚያውጠነጥንበት ሰዓተ—ፍጥነት ራሳቸው ንጉሠ ነገሥት ፣ “ራስ አሉላም ቢሆን የፈጸመው ስሕተት የለም ። ጣሊያኖቹ ከግዛቱ ውስጥ በመሥፈራቸው እንዲለቁ ደጋግሞ ቢጠይቅ በማስቸገራቸው ጦርነት ገጠማቸው ። ለእብነት ያህል ፣ የኢትዮጵያ ወታደሮች ወደ እንግሊዝ አገር መጥተው መሬት ቢይዙባችሁ እናንተም ዝምብላችሁ እንደማትመለከቱ ሁሉ ነው እርሱም የሠራው” ሲሉ ዝምታውን ገፈፉት ።

“መቼም ለሰላምና ለወዳጅነት የተቻለውን ያህል ጥረትና ትዕግሥት ያስፈልገዋልና ሁለታችሁም እንድታስቡበት መማከራችን አይቀርም” አለ ፖርታልም ግራና ቀኝ እየተመለከተ ።

"በሁለታችን መካከል ሰላም እንዲሆን ምኞትዎ ከሆነ እነርሱም ባገራቸው እኛም ባገሬ ሆነን መሆን አለበት እንጂ በሁለታችን መካከል ፈረስ ተጭኖ ጉራዴ ከተመዘዘ በኋላ መሆን የለበትም ። የኛም ወታደሮች ጦራቸውን እነጣጥረዋል ። ጦርነቱን የፈለጉት ግን ጣሊያኖች ናቸው ። እንግዲህ እነርሱም ይምጡ ! እኛም በጉድጓድ ውስጥ ተደብቄ አልቆያቸውም ፤ እመከታቸዋለሁ እንጂ" ሲሉት ከዚያ በኋላ ሌላ ሐሳብ መሰንዘርና ማስረዳት ዋጋ እንደማይኖረው እንግሊዛዊው መልእክተኛ ተረዳው ።

በለንደን በኩል ለኢትዮጵያ የላከችው የግዛት ማስፋፋት ጥያቄዋን መልስ ለመጠባበቅ እንኳ ትዕግሥቷ ላለቀባት ኢጣሊያ ፣ ገና እንግሊዛዊው መልእክተኛ ከአጼ ዮሐንስ ግቢ ሳይወጣ በጄኔራል ግራና ጠቅላይ አዛዥነት በአራት ጄኔራሎች የተከፈለ ኻያ ሺህ ወታደር ወደ ምፅዋ ላከች ። ጦሩም ምፅዋ እንደገባ በጄኔራል ጅኒና በጄኔራል ታጅኒ የሚታዘዝ ሁለት ክፍለ ጦር ከምፅዋ ወጥቶ ወደ ተድዓሊ አካባቢ ሔዶ ሠፈረ ። ራስ አሉላም የኢጣሊያኖችን ርምጃ ዘርዝረው ወደ አጼ ዮሐንስ አስተላለፉ ።

ምንም እንኳን የተላከበት ጉዳይ ያልተሳካለት መሆኑን ቢረዳውም ፣ በአጼ ዮሐንስ ቤተመንግሥት ውሎ ያደረው ፖርታል ዜናውን አጼ ዮሐንስ ሲነግሩት ፣ "ስምምነት እንዳይደረግ ራስ አሉላ የፈጠሩት የተንኰል ወሬ እንዳይሆን?" ብሎ ማመን አቅቶት ነበር ። አጼ ዮሐንስም ቀጥሎ ያለውን የጦርነት ክተት ዐዋጅ አናገሩ ።

የአጼ ዮሐንስ ዐዋጅ
"የኢትዮጵያ ልጅ ሆይ!
ልብ አድርገህ ተመልከት!
ኢትዮጵያ የተባለችው
አንደኛ እናትህ ናት
ሁለተኛ ዘውድህ ናት
ሦስተኛም ሚስትህ ናት
አራተኛም ልጅህ ናት
አምስተኛም መቃብርህ ናት ።



እንግዲህ የእናት ፍቅር የዘውድ ክብር የሚስት ደግነት የልጅ ደስታ የመቃብር ከባድነት እንደዚህ መሆኑን ዐውቀኸው ተነሣ" የሚል ነበር ።

ፖርታል ዐዋጅ መነገሩን ከሰማ በኋላ ፣ የተፈራው ጦርነት መነሣቱን አረጋግጦ ስለ ዝግጅቱም የበኩሉን ጥናት/አከናውኖ ወደ ሀገሩ ተመለሰ ። አጼ ዮሐንስ ከኢጣሊያኖች ጋር ጦርነት መደረጉ የማይቀር መሆኑን ተረድተውት የክተትና የዝግጅት ዐዋጅ በአደረጉበት ወቅት ፤

1ኛ. አጼ ዮሐንስ አምስት ሺህ የክብር ዘብ ።

2ኛ. ራስ አሉላ ዐሥራ ስድስት ሺህ ጦር ፣ ይበልጠው እጅ ባለብረት ።

3ኛ. በከረን ምሽግ ላይ ሠፍረው የነበሩት ራስ ሐጐስ ኻያ ሺህ ጦር ፣ የሚበዛው ባለብረት ።

4ኛ. ራስ ሚካኤል ኻያ አምስት ሺህ ጦር ፣ የሚበዛው ፈረሰኛ ።

5ኛ. ራስ መንገሻ አምስት ሺህ ጦር ።

6ኛ. ራስ ኃይለማርያም ዐሥራ ስድስት ሺህ ጦር ።

7ኛ. ራስ አርአያ ሥላሴ ዐርባ ሺህ ጦር ።

በድምሩ አንድ መቶ ኻያ ሺህ ጦር ወደ ምፅዋ ለማዝመት እንደሚችሉ አረጋገጡ ። ይሁን እንጂ ፣ በጐንደር በኩል እየገፋ የመጣው የማሕዲስቶች ወረራ ቅድሚያ ትኩረት የሚጠይቅ መሆኑን አጼ ዮሐንስ አመኑበት ። እርግጥ ነው ፣ በዚያ ወቅት ንጉሥ ምኒልክና ንጉሥ ተክለሃይማኖት በጉዳዩ እሰበውበት ቢሆን ኑሮና አጼ ዮሐንስን በመርዳት በማሕዲስቶች ላይ ዘምተው ቢሆን አጼ ዮሐንስ ወደ መተማ ባልዘመቱ ነበር ።

አጼ ዮሐንስ በሁለት ግንባር በመወጠራቸው ፣ ራስ አሉላንና ራስ ሐጐስን ከመረብ ምላሽ ጠርተው ከሌሎቹም መኳንንቶቻቸው ጋር ሆነው በጉዳዩ ላይ ውይይት በጀመሩበት ሰዓት፣

ጣሊያኖችም ከምፅዋ እስከ ለሐጢ ዘላተው የባቡር ሐዲድ ዘር
ግተው በአካባቢው ጠንካራ ጠንካራ ምሽጎች ሠርተው
መድፎች በብዛት ማጥመድ ጀምረው ነበር ። ከዚህም ሌላ
ደግሞ የራስ አሉላ ተፎካካሪዎች የነበሩትን ከየቀበሌው እየ
ለቀሙ በሚያስታጥቁበት ወቅት በእነርሱም ሠፈር ድንገተኛ
ራስ ምታት ደረሰባቸው ።

ራስ አርአያ ድምፁ ከጣሊያኖች ጉያ ተሸጉጦ የመንደር
ችግና የነጋዴዎችን ሕይወትና ንብረት ከአደጋ ላይ ጥሎት ለና
ረው ልጃቸው ለፊታውራሪ ደበበ ፣ “ልጄ ሆይ! ይኸውና እንደ
ምታየውና እንደምትሰማው ጣሊያኖች እኛን ሊወጉን መጥተ
ዋል ። አንተም ከእነርሱ ጋር አባሪ ተባባሪ ሆነህ እኛን ልትወጋን
ቆርጠህና ደፍረህ ከተሰለፍክ ረግሜሃለሁ ፤ ከቃሌ ከወጣህ ርጉም
ሁን” የሚል ቃል ላኩበት ። ይህ የርግማን ቃል ያስደነገጠው
ደበበም ፣

“በደለኛ ነኝ እሳዝንምዎታለሁ ፤ ይማሩኝና የሚወበዱኝ ወታ
ደሮች ይላኩልኝ” ብሎ ለእጼ ዮሐንስ መልእክት ሰደደ ። እጼ
ዮሐንስም በነገሩ ተደስተው ራስ አሉላ እንዲቀበሉት የምሕረት
መልእክት ሰጥተው ራስ አሉላን ወደ ሐማሴን እንዲመለሱ
አዘዙዋቸው ።

“ደበበ ዐርፎ ይቀመጣል ተብሎ ነው? እርሱ ለማጥፋት የተ
ፈጠረ ሰው ነው ። ራሱ ከሌጠፋ አገር ሰላም አይሆንም ። ብቻ
በአሁኑ ከባድ ወቅት ‘ማሩኝ’ ብሎ ከጠላቶቻችን ጉያ መውጣ
ቱም ልብ—ገዝቷል ያሰኘዋል ፤ በዚሁ ቢያዘልቅለት አይደል!”
አሉ ራስ አሉላም ትእዛዙ እንደ ተላለፈላቸው ።

ራስ አሉላ የደረሳቸውን የምሕረት ቃል ወደ ደበበ አስተ
ላለፉና እጁን እንዲሰጣቸው ጠየቁት ። እርሱም ወደ ሦስት መቶ
የሚጠጉ ኢጋሚደዎቹን አስከትሎ ገባና ራስ አሉላ ተረክበው
ወደ ዐደዋ ይዘውት ሔዱ ።

ፊታውራሪ ደበበ ፣ በእንገቱ ገመድ ዐሥሮ በትከሻው ድን
ጋይ ተሸክሞ ከአጉቱ ዘሩን ፊት ወደቀና ፣ “ሞት ይገባኛል ፣



በድያለሁ ፤ አጥፍቻለሁ ግን መሐሪ ነዎትና ይማሩኝ” [illegible]
ለመን ። እጼ ዮሐንስም ምሕረት አድርገው ሸለሙት ። [illegible]
ውም በኢጣሊያኖች ጉዳይ አማካሪያቸው እንዲሆን ሲሾሙት
ራስ አሉላም ፣

“እስቲ ይሁን! ወንበዴ የሚያቀርበው ሐሳብ የቱን ያህል እንደ
ሚበጀን እናገኘዋለን ። ምሥጢራቸውን ይልቅ ይዞባቸው እንደ
ገና ወደ ጌቶቹ እንዳይፈረጥጥ ቢያስቡበት አይከፋም” አሉ ።

## ማሕዲስቶች ፡ አሉላና መረብ ምላሽ

የማሕዲስቶች ጦር ጐንደር ከተማ ገብቶ ሕዝቡን ሲፈጅ ዐርባ አራቱን አድባራትም አቃጠለ ። ከእልቂት የተረፈው ሕዝብና ካህናትም እጅግ መራር የሆነ የኀዘን መልእክት ወደ አጼ ዮሐንስ ሰደደ ። ማሕዲስቶቹ ያደረሱትንም እልቂትና ግፍ እነዚህ ሕዝባዊ ግጥሞች በይበልጥ ያጐሉታል ።

"ተከተልኸኝ ብዬ ዞሬ ዞሬ ላይ
ወይ ጥጋብ ወይ ኩራት ጐንደር ቀረህ ወይ?
ወገራ አሳላፊ ደምቢያ እንጀራ ጣይ
ተበላህ ጐንደሬ አትነሣም ወይ?
ማር ውሃ ከሚዳው የተዘራ አዝመራ
አጫጁ ድርቡሽ ነው ሰብሳቢው አሞራ
አትከለከልሞይ ይዘህ አለንጋህን
አሞራ ሲበላው የገዛ ገላህን ።
የምትሔዱ ሰዎች የምትሻገሩ
ድመት በልታ ሞተች ብላችሁ ንገሩ ።

አጼ ዮሐንስ ፣ በጐንደር የደረሰውን እልቂት እንደ ሰሙ መኳንንቶቻቸውንና የጦር አበጋዞቻቸውን ሰብስበው ፣

"ልጆቼ ወዳጆቼ!

ሁለት ጠላቶች ተነሥተውብናል ። አንዱ አገር የሚቀማ ሁለተኛው እልጋዬን የሚፈልግ ስለሆነ ፣ የትኛውን ቀድሚ እንደምወጋ የታያችሁን ንገሩኝ" ብለው ምክር ጠየቁ ። ሁሉም እርስ—በርሳቸው ከተያዩ በኋላ ራስ አርአያ ድምፁ ተነሥተው ፣ "ለማጥፋት በመጣው ጠላት ላይ ቀድመን ብንዘምት ይታየኛል" ብለው ተቀመጡ ።



ራስ አሉላም ቀጥለው ተነሡና ፣ "ለመንግሥትዎ ብቻ ሳይሆን ለሀገርዎ ጭምር ብርቱ ጠላቶች የሆኑትን ጣሊያኖች ወደ መጡበት ሳንመልስ ወደ ጐንደር ቢሻገሩ ትልቅ ጥፋት ከኋላችን ይደርስብናል ። በጐንደር ገባ ለተባለው ድርቡሽ የሁለትና የሦስት ራሶች ጦር መስደድ ይበቃዋል" ብለው ተቀመጡ ።

ራስ ሚካኤልም ቀጥለው ፣ "ጣሊያንን ያህል አገር ፈላጊ ጠላት ከበራፋችን አስቀምጠን ወደየት ነው የምንዘምተው? አይታየኝም" ብለው ሐሳብ ሰጡ ። "ጠላታችን ዘውድዎን የሚቀናቀን ነውና በመጀመሪያ በርሱ ላይ ብንዘምት ነው የሚታየኝ" አሉ ራስ ሐጐስም ።

በዚሁ ዐይነት በስብሰባው ላይ የነበሩት መኳንንትና የጦር አበጋዞች ንጉሠ ነገሥቱ ፣

"ሁለት ጠላቶችና አንድ ተቀናቃኝ" ብለው በሠየሙዋቸው በጣሊያን በማሕዲስቶችና በንጉሥ ምኒልክ ላይ የታየውን ሁሉ ፈረደ ። በመጨረሻም ንጉሠ ነገሥቱ ፣

"ወዳጆቼ ልጆቼ!

ሁላችሁም እንደ ታያችሁ ተናግራችኋል ፤ የሁላችሁም ነገራችሁ ከልቤ ገብቷል ። ሁለቱ ጠላቶቻችን ጣሊያንና ድርቡሽ ናቸው ። የኔን ዘውድ ፈላጊው ደግሞ ምኒልክ ነው ። ድርቡሽ ጐንደርን እያቃጠለ ነው ። ሕዝቡን እየፈጀው ነው ።

ምኒልክ ወንድሜ ነው ። እግዚአብሔር ከፈቀደለት ዘውዱን ይውሰደው ። እኔ ግን ከውጭ ወደመጣብን ድርቡሽ እዘምታለሁና ተዘጋጅታችሁ ተከተሉኝ! አሉላና ሚካኤል ወደ ጣሊያን እንዝመት ብላችሁአልና ሒዱና ተከላከሉ" ብለው የመጨረሻውን ውሳኔ ሰጡ ።

ራስ አሉላ ከኢጣሊያኖች ጋር ጦርነት እንዲጋጠሙ ከንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ እንዳገኙ ከትግራይ ገሥግሠው አሥመራ ገብተው ወደ አይለት ወርደው የኢጣሊያንን ኀይልና አሰላለፉን ካጠኑ በኋላ ከምሽጉ ወጥቶ ጦርነት እንዲገጥማቸው በልዩ ልዩ

ዘዴ መተንኳኮስና ማስገደድም ጀምረው ነበር ። የኢጣሊያ ጦር ግን ከተጠናከረ ምሽጉ ንቅቶ ብቅ የማይል ሆነ ። በዚያው ወቅት ደግሞ በቤተመንግሥቱ ዙሪያ የነበሩት የአጼ ዮሐንስ ባለሟሎች በአሉላ ላይ ክሳቸውን አድሰው አቀረቡ ። የክሶቹም ዋና ዋና ነጥቦች ፥

1ኛ. አሉላ ተድኅኤ ድረስ ሔዶ ከጣሊያኖች ጋር ጦርነት ባይገጥምና ድል ባይመታቸው ኑሮ እነርሱም የተዋረደ ክብራቸውን ለማደስ ሲሉ በርካታ ጦር ምፅዋ ድረስ ባላመጡ ነበር ። እንዲያውም የኛ ዶጋሌዎች ሆነው ድርቡሾችን በወጉልን ነበር ።

2ኛ. ወንድሙም ለመሸፈት ያሰባልና እንዲያዝልን ፤

3ኛ. ወንድሙ ከተያዘ እርሱም እርስዎን ከድቶ ከጣሊያኖች ጋር ይስማማብዎታልና በሐማሴን ያከማቸውን መሣሪያ አስቆጥሮ እንዲያስረክብ” የሚሉ ነበሩ ።

አጼ ዮሐንስም የከሳሾቹን ባለሟሎቻቸውን ሐሳብ ተቀብለው የክብር ዘብ ወይም የምርጥ ጦር አዛዥ የነበሩትን የራስ አሉላን ወንድም ደጃዝማች ተሰማን ከሥልጣናቸው ሽረው ንብረታቸውን ወረሱዋቸው ።

ቀጥለውም ራስ አሉላን ከአሥመራ አስጠርተው ፥

“በሐማሴን ያከማቸኸው የጦር መሣሪያ እስከ ዐርባ ሺ ይደርሳል ተብሏል ፤ ለምንድን ነው እኔ ሳልፈቅድልህ ይህን ያህል ያከማቸኸው? ምን ተመኝተህ ነው?” ብለው መኳንንቶቻቸው ፊት ጠየቁቸው ።

“ጃንሆይ! የሚጠሉኝና የሚንቁኝ ከዚህም ሌላ የኔን ሹመት የፈለጉብኝ ጠላቶችዎ ጣሊያኖች ውስጥ ውስጡን ያታለሉዋቸው ተንኮለኞች ያቀረቡልዎ ውሸት ነው እንጂ ፥ እኔ ይህ ሁሉ መሣሪያም የለኝም ። ጌታዬ እርስዎንና አገሬን ከማገልገል በቀር ምንም ሌላ ሐሳብ የለኝም” ብለው መለሱ ።



“በል ለማንኛውም ከዚህ ከሚመረጡ ሰዎች ጋር ሔደህ ያለህን የጦር መሣሪያ ብዛትና ዐይነቱንም ቁጥር እንድታስቆጥር ዋስ ጥራ” አሉ አጼ ዮሐንስ ።

“የኔ ዋስ እጅዎ ነው እጅዎ ይጣለኝ” ብለው ራስ አሉላ የንጉሠ ነገሥቱን እጅ መትተው ምለው ከሳሾቻቸው ከመረጡዋቸው ተቆጣጣሪዎች ጋር ሆነው የጦር መሣሪያቸውን ለማስቆጠር ወደ አሥመራ ተመለሱ ።

በጥንቱ ዘመን ማለት ከራስ አሉላ በፊት በነገሥታቱ እየተመረጡ “ባሕር ነጋሽ” ሲባሉ ከነበሩት ገዥዎች እጅግ በላቀ ክብርና ሥልጣን የመረብ ምላሽ ገዥ ሆነው በአስተዳደር ችሎታቸው ፥ በዲፕሎማቲክ ስልታቸውና በጦር ዘዴ አመራራቸው ከመረብ ወንዝ ወዲህ ማዶ አልፎ በመላው አውሮፓ ዝናቸው ያስተጋባውና የአጼ ዮሐንስ ብርቱ ክንድና ጋሻ የነበሩት ሰውዬ መንፈሳቸው ኩምትርትር ብሎ ጥረታቸውና ዓላማቸው ወድሞ፥ ሙያቸውና ክብራቸው ትቢያ ለብሶ ራቁቱን ከፊታቸው ቆሞ ራሳቸውን በራሳቸው አዩትና ውርደት ራሱ ፍርሃት ለቀቀባቸው ።

እርሳቸው በአጼ ዮሐንስ ችሎት የማይታመኑ ሆነው ፥ እርሳቸው በአጼ ዮሐንስ መንግሥት ላይ ተጠርጥረው ፥ ከእርሳቸው የበለጡ ታማኞች ተገኝተው ፥ ከእርሳቸው የላቀ አገር ያገለገሉ ሰዎች ተገኝተው ፤ ከእርሳቸው የላቁ ዐዋቂዎች ተገኝተው እርሳቸውን እንዲቆጣጠሩ በእርሳቸው ላይ ልዩ ባለሥልጣኖች ተመድበው ከእርሳቸው ጋር ወደ አሥመራ በመሔዳቸው ክብራቸው ፥ ሙያቸውና አገልግሎታቸው ጥሪቸው ሲሸሽ ተሰማቸው!

አጼ ዮሐንስ ፥ እርሳቸውን ጠርጥረው በእርሳቸው ላይ ከሾሙዋቸው ተቆጣጣሪዎች ጋር ሆነው አሥመራ እንደገቡ ከሚወዱት ግቢያቸው እንኳ መግባቱን ጠልተውት ራቅ ብለው ነበር በድንኳን የሰፈሩት ። ተቆጣጣሪዎቹ ሥራቸውን እንደፈጸሙም አሉላ ዕቃቸውን አስጠቅልለው ወደ ትግራይ ሰደዱና ለግዛታቸው ሕዝብ ፥

«የሐማሴን ሕዝብ ሰማኝ!

እስከ ዛሬ በጀግንነትህና በታማኝነትህ አገርህንና ክብርህን ስትጠብቅ ኑረሃል! ከእንግዲህ ወዲህም ቢሆን ክብርህ እንዳይደፈር ፣ ኀብረትህ እንዳይጠፋ ፣ አንድነትህና ክንድህ እንዳይዝል ፣ ልብህ እንዳይሰንፍ ጠንክረህ እረስ ነግድ ። እኔም የበደልኩህ ነገር ቢኖር ለራስህ ለአንድነትህና ለክብርህ ብየነውና ከልብህ ይቅር በለኝ» ብለው ዐዋጅ አናግረው መቶ የማይሞሉ ወታደሮች ከተማቸውንና ቤታቸውን እንዲጠብቁ አሥመራ ትተው በታላቅ ሰልፍና ክብር ሲመላለሱባት ከነበረችው ከተማቸው ሾልከው ወጡ ። ዐዋጁንና ወደ ትግራይ መመለሳቸውን የሰማው ሕዝብም እጅግ አዘነ ።

«አንድ የገበሬ ልጅ ለምን የንጉሠ ነገሥት ታማኝ ሆነ?» ብለው መላ ሰውነታቸው በቅናት አብጦ ሊፈነዳ ተቃርቦባቸው የነበሩት የአጼ ዮሐንስ ባለሟሎችና የአሉላ ተቃዋሚዎች በራስ ሐጎስ አፈ ቀላጤነት ፣ በደጃዝማች ደበበ አስተባባሪነት ፣ በራስ አሉላ ላይ ነውር ነገር ተፈልጎ ክሱ ተቀነባብሮ «እጁ እንዲያዝ» ተብሎ ለአጼ ዮሐንስ ቀረበ ። ይህን ወሬ ምዕዋ የነበረው የጣሊያን ጦር አዛዥ እንደ ሰማም አሉላ እንዳይመለሱበት አጼ ዮሐንስን መወትወቱንና ማቆላመጡን ቀጠለበትና ፤

«እርስዎን እንዳልረዳዎ ከእርስዎ ጋር ያጋጩን ራስ አሉላ ናቸው ። ሀገርዎን ሐማሴንንም ለሀገሩ ባላባት ቢሰጡት እጅግ የበለጠና የተሻለ ነገር ይሆናልና ያስቡበት» ብሎ ከገለጸ—በረከት ጋር መልእክተኞች ሰደደ ።

እንግዲህ የ« ወዲ ቁቢ» ወንጀል ከባለሟሎቻቸውና ከጣሊያኖች የቀረበላቸው አጼ ዮሐንስም ክሱን ችላ የማይሉት ስለሆባቸው አሉላ በመጀመሪያ የሚችቷን ባለቤታቸውን የወዘሮ አምለሱን ሀብት የወግና የጌጥ ዕቃ ሁሉ ለወላጆቻቸው እንዲያስረክቡ ፈረዱ ። ቀጥለውም ለጣሊያኑ የጦር አለቃ ፣

«ራስ አሉላ እንደ በደለህ አድርገህ ልከህብኛል ፤ ጥፋተኛው እንዲታወቅ ካንተ በኩል ሁነኛህ የሚሆን ሹም ላክልኝና እኔም አቡኑና መኳንንቱ ባሉበት ራስ አሉላን አስቀርቤ ጉዳዩን ላስመርምረውና ጥፋተኛው በእውነት እርሱ ሆኖ ከተገኘ በሥራው ሥራ እቀጣዋለሁ» ብለው ላኩለት ። የጣሊያኑ ጦር አዛዥም በዚሁ መልእክት መሠረት ፣ የአሉላን ተቃዋሚዎች በየቀበሌው እያስጠራ አሉላ የፈጸሙትን የአስተዳደር 'ስሕተት' ሁሉ እያሰበሰበ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ መላኩን ቀጠለ ። ባንድ በኩል ደግሞ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ የሰደዱለትን መልእክት ማመንም ሆነ መቀበል እንደማይገባው እነክፍለየሱስ ይመክሩት ጀመር ።

«አሉላ ወደ ኩፊት ሲዘምቱ እናንተ ከረንንና ምፅዋን እንዳትይዙባቸው የእናንተን ወዳጅነት ለማግኘት የሚፈልጉ መስለው እንዳታለሉዋችሁ ፣ አሁንም አጼ ዮሐንስ በጐንደር በኩል ከመጣባቸው ከድርቡሽ ጦር ጋር ለመዋጋት ሲሔዱ እናንተ ወደ ደጋ ደጋው እንዳትሔዱባቸው ለማታለል ብለው አሉላ ያቀረቡላቸው ስልት ነውና በዚህ ከምትሞኙ ቀልጥፋችሁ ደጋ—ደጋውን ያዙት የሚሉ አማካሪዎች የጣሊያኑን ጦር አዛዥ ይወተውቱት ጀመር ።

የጣሊያኑም የጦር አለቃ በቀረበለት ሐሳብ ተደለቶ በአጼ ዮሐንስ ቤተመንግሥት ውስጥ የሚደረገውን ዝግጅትና የራስ አሉላንም ሁኔታ የሚከታተሉለት ተመልካቾች በሚሲዮናውያኑ አማካይነት ወደ መቀሌ ሰደደ ።

አጼ ዮሐንስ ፣ አሉላን በቤተ መንግሥታቸው ዙሪያ ሆነው በዐይኑ ቁራኛ እንዲጠበቁ ሲያደርጉ ፣ በመረብ ምላሹ ግዛታቸው ማንንም ባለመላካቸው ለጣሊያኖች ወረራ እየተጋለጠባቸው ሔደ ።

አሉላ በመረብ ምላሽ ግዛታቸው በነበሩበት የሥልጣን ዘመናቸው ሦስት መሠረታዊ ጉዳዮች ነበሩዋቸው ። እነዚህም፣

የአስተዳደርና የንግድ መዲናቸውን ከአዲ ተክላይ ወደ አሥመራ ማዛወራቸው ፣ ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ አገር ለመያዝ ብርቱ ዓላማና ክንድ የነበረው አውሮፓዊ ኃይል በቀይ ባሕር በኩል ብቅ በማለቱ ከእርሱ ላይ ማተኮር መጀመራቸው ፣ ይኸው አውሮፓዊ ኃይል ሠፍሮበት በነበረው በምፅዋ ወደብና በእርሳቸው ግዛት መካከል የወሰን ክልል ካለመኖሩም በላይ ፣ ራሳቸው እቁ

ላም ሆኑ ንጉሠ ነገሥቱ ምዕዋንም ቢሆን «ሊተቋሙን» እያሉ
ሲማጠኑበት በመቆየቱ ፣ አሉላን ከውስጥና ከውጭ ወጥረው
የያዙ ችግሮች አስከተሉ ።

እነዚህም ችግሮች አሉላ ከመረብ ምላሽ ግዛታቸው እስ
ኪፈው ፣ አዝነውና ተከዘው ወደ መቀሌ እንዲመለሱ ምክንያቶች
ሆነው ቀረቡባቸው ።

የዚያን ዘመኑን ሁኔታ የተከታተሉ አንዳንድ ተመራማሪ
ዎች በሰጡት አስተያየት ፣ «በምዕዋ የሠፈሩት ጣሊያኖች ወደ
ደጋው ብቅ እያሉ ለመሥፈር እንዲችሉ አሉላ ቢታገሡዋቸው
ኑሮ ለዕድገቱዋ እጅግ ሲጥሩላት የነበረችው አሥመራ እጅግ
ትበለጽግና ትለማም ነበር» እያሉ ተችተዋል ።

ግን አሉላ ግዛታቸውን እየቀረቡ ለንግድ ለመለወጥ ደግሞ
ሕሊናቸው ፣ ኢትዮጵያዊ ወኔያቸው የሚፈቅድላቸው አልነበ
ሩም ። በአሉላ ልበሙሉነት በአሉላ አገር አፍቃሪነት ፣ በአሉላ
ጀግንነት ፣ በአሉላ ቆራጥነት ፣ በአሉላ አትንኩኝ ባይነት ፣ በአሉላ
አይበገሬነት ፣ በአሉላ አሻፈረኝ ባይነት ፣ ሲገመገም የኢትዮጵያ
ክብረ—ወሰን በንግድ ሊለወጥ እንደማይችል አሉላን የሚያውቁና
አሉላን ያጠኑ ሁሉ ያምኑበታል ።

ኩፊት ላይ ከራስ አሉላ ጋር ጦርነት ገጥሞ ድል የሆነው
የማሕንዲስቶች መሪ ኦትማን ዲግና ዋናው ዕቅዱ በግብፆች
እግር ተተክቶ የግብፆች ጦር ሠፍሮበት የነበረውን የኢትዮጵ
ያን መሬት መያዝና እስልምናን ማስፋፋት ነበር ። ይሁን እንጂ
ይህነኑ ምኞቱንና ዕቅዱን የበላዩና የሀገሪቱም መሪ የነበረው
ኸሊፋው መክሮችና ከልክሎትም ነበር ። እርሱ ግን የአለቃ
ውን ምክር ባለመቀበሉና አሉላንም በመናቁ ኩፊት ድረስ ገብቶ
ጦርነት ገጥሞ ፣ ጦሩ እንኩትኩቱ ሲወጣበት ራሱ እምልጦ
ሱዳን ከገባ በኋላ አለቃውን ወትውቶና አሳምኖ በአጼ
ዮሐንስ ላይ ጦር ጭና እንዲዘምት ለማድረግ በመቻሉ ተንቆና
ተዋርዶ የነበረው የአሉላ ክብር እንደገና እንዲታደስ ምክንያት
ሆኖ ቀረበ ።



የማሕዲስት ጦር ጐንደር ገብቶ አጼ ዮሐንስም የእስልም
ናን ሃይማኖት እንዲቀበሉ ስለላከባቸው ፣ የከተትና የዝግጅት
ውሳኔ ቢሰጠውም ፈጥነው ወደ ዘመቻው ለመሔድ የተቸገሩባ
ቸው ምክንያቶች ነበሩ ።

ከእነዚህም ምክንያቶች አንዱ በምዕዋዕ በኩል የገባው
የጣሊያን ጦር አሥጊነት ነበር ። እርሱንም በጦርነት ለመግጠም
ዐዋጅ አናገረዋል ። ግን ፣ ወደ ምዕዋ ለመዝመትም የማሕዲስ
ቶች ፣ የንጉሥ ምኒልክና የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሁኔታ
አሥግቷቸዋል ። በዚህ ጊዜም በፀይነ ቁራኛ ሲያስጠብቋቸው
የነበሩትን ቱርክ ፓሻ ራስ አሉላን ድንገት አስጠርተው በቆ
ይታ ፣

«የእስላሙ ጦር መሪ ከሊፋው ኢትዮጵያን ሊወር ተነሥቷ
ልና ምን ታስባለህ?» ብለው ጠየቋቸው ። የአሉላ ልብ በደስታ
ፈነጠዘ ። የተዋረደ ክብራቸውን ለመመለስ የሚቀ ተፎካካሪያቸ
ውንና ከሳሻቸውን ሁሉ ለማሳፈር ፣ የዛለውን ክንዳቸውን በማ
ፈርጠም አጋጣሚ እንደ መጣላቸው ተረዱት ።

«የድርቡሽን ወንድነትና ቆራጥነትኮ ኩፊት ላይ አይተ
ነዋል ፤ የዮሐንስን ክንድ ቀርቶ የአሽከርዎን ክንድ የማይመክት
ነው ። በቅድ ሂያ ጦር ይላክበት ፤ እርስዎ ግን ከዚሁ ሆነው ጦር
እንዲዘጋጅና እንዲከት ያድርጉ ። የእርስዎን ወደ ዘመቻ መሔድ
ዐይቶ ሌላ ጠላት ከኋላ እንዳይነሣ መጠንቀቅ ይገባል» አሉ
ዋቸው ። አጼ ዮሐንስ እንገታቸውን እያወዛወዙ ቆዩና ፣ «መል
ካም ብለሃል! መቼም የልቤን የምታውቀው አንተው ነህ! በል
አንተው ወደ ሐማሴን ፈጥነህ ሔድና ጦርና ስንቅ አዘጋጅተህ
ተመለስ ፤ እስተዚያው እንዳልከው ወደ ቤገምድር ጦር ይዘም
ታል» አሉዋቸው ።

ያ—ውሳኔያቸው ከቤተ መንግሥታቸው ቀርቶ ፣ በመላዋ
ትግራይ ቀርቶ ፣ በምዕዋ የነበረውን የጣሊያን ጦር እሻገር
ኮብርቱ ድንጋጤ ላይ ጣለ ።

በአሉላ መሸር ፣ በአሉላ መከሰስና በአሉላ በአጼ ዮሐንስ
ዘንድ ሞገስ ማጣት ፣ በኢትዮጵያውያን የእርስ - በርስ ጥልና

ግጭት እጅግ ሲፋንግዝ የነበረው የጣሊያኑ የጦር አለቃ ከብርቱ
ሰመመን ላይ ወደቀ ።

የንጉሡ ነገሥቱ ገጽታ የተመለሰላቸው አሉላ ፣ ከመቀሌ ገሥ
ግሠው አሥመራ ሲገቡ ደግሞ ፣ በምፅዋ የነበረው የጣሊያኑ ጦር
አለቃ እጅግ ተደናገጠና የሚተማመንባቸውን የአሉላን ተቀ
ናቃኞች እንደ ተለመደው ሰበሰበ ፣

«ንጉሡን ማመን ችግር ነው ። በፊት እንደ ነገራችሁኝም
ያንን መልእክት የሰደዱልኝ ሊያታልሉኝ ፈልገው ነውና
ከእንግዲህ ወዲያስ ምን ታስባላችሁ?አሉላም ተመለሰ ፤ እሱ
ንስ እንዴት አድርጎ መታረቅ ይቻላል?» ብሎ ምክር ጠየቀ ።
የሰበሰባቸው ደጋፊዎቹ ግን የሰጡት ምክር ፣

«አሉላን በልዩ ልዩ ገጸ—በረከት ማታለል ነው» የሚል
ብቻ ነበር ።

አጼ ዮሐንስም ከራስ አሉላ በቀረበላቸው ሐሳብ መሠረት
ልጃቸውን ራስ አርአያ ሥላሴን ከዐርባ ሺህ ጦር ጋር ወደ ቤጌ
ምድር ሔደው ማሕዲስቶችን እንዲያስወጡ አዘመቱዋቸው ።

ዳሩ ግን ራስ አርአያ በፈንጣጣ በሽታ በመሞታቸው በቤተ
መንግሥቱ ውስጥ ታላቅ ኀዘን ሆነ ። ከሁሉም ደግሞ ራስ አሉላ
ከልባቸው አዘኑ ። ምክንያቱም ለራስ አርአያ ሞግዚት ስለነ
በሩና ሲነግሡላቸው ከትግራይ መኳንንት ክስና ንትርክ እፎይ
ብለው ለመገላገል የሚያስችል ሥልጣን ሊያስጨብጡዋቸው
እንደ ሚችሉ በተስፋ ይጠባበቁ ነበርና ነው ።

የወጣቱ የራስ አርአያ መሞት ፣ በአጼ ዮሐንስና በንጉሥ
ምኒልክ መካከል የነበረውንም የጋብቻ ክር በጠሰው ። ንጉሡ
ነገሥቱም በብርቱው በማዘናቸው ጤንነታቸው ታወከ ። ንጉሥ
ምኒልክ ከራስ አርአያ ሞት በኋላ ከሸዋ ገሥግሠው ወሎን መያዛ
ቸውን አጼ ዮሐንስ እንደ ሰሙ ፣ የማስፈራሪያ ዱላቸውንም ከአሥ
መራ ወደ መቀሌ አዛወሩ ። እንደገናም ትርክ ፓሻቸውን ማቅ
ረብ ጀመሩ ።



የንጉሥ ምኒልክና የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ስምምነትና
በአጼ ዮሐንስ ላይ ማመፃቸው ፣ ማሕዲስቶችም እንደገና ወደ
ጎንደር ለመግባት ከመተማ አያሌ ሠራዊት ይዘው መነሣታ
ቸው ፣ ጣሊያኖች በንጉሥ ምኒልክ ቤተ—መንግሥት ገብተው
ከዮሐንስ ጋር እንዲጋጩ ሲፈጽሙት የነበረው ሤራ የአጼ ዮሐ
ንስ ቤተ—መንግሥትን ጥቁር ጥላ ጣለበት ። ንጉሡ ነገሥቱ
በዘመነ— መንግሥታቸው ፍጻሜ አቅራቢያ ፊታቸውን ዘወር
አድርገውባቸው የነበሩትን ታማኝ ጀኔራላቸውን እንደገና ካቀ
ረቡዋቸውና ፊታቸውን መለስ ካደረጉላቸው በኋላ ፣ እስገምግ
መው የመጡባቸውን ችግሮች እንዳመጣጣቸው ለመቋቋም የሚች
ሉበትን ሁኔታ ከተመካከሩ በኋላ ፣ እንደገና ወደ መረብ ምላሽ
ግዛታቸው ተመልሰው የተገኘውን ያህል ወታደር ለመሰብሰብና
ስንቅም ለማዘጋጀት እንዲችሉ ተወሰነ ።

አሉላ እንደገና ወደ መረብ ምላሽ ግዛታቸው ሲመለሱም
ሞቅ ደመቅ ያለ ይዞታ ነበራቸው ። ከንጉሡ ነገሥቱ ምርጥ ጦር
አዛዥነት የተሻሩት ወንድማቸው ደጃዝማች ተሰማና የእኅታ
ቸው ልጅ ባሻይ ተድላ ከትካዜና ከብስጭት በማገገም ላይ የነ
በሩትን አሉላን አጅበዋል ። በእርሳቸው ላይ የደረሰው ብስ
ጭትና ትካዜ አብሮ አዝኖና ከሥጋት ላይ ወድቆ የነበረው
የመረብ ምላሽ ግዛታቸው ሕዝብም አብሮ ተደስቷል ።

«አሉላ አሥመራ ካለ ድርቡሽም ሆነ ጣሊያን አይደፍሩ
ንም» እያለ መተማመንና መረጋጋት ጀመረ ። አሉላ በግቢያ
ቸው ሆነው ለግብር ነጋሪት ሲያስጐስሙ ፣ ሲሸሙ ሲሸልሙ
ቅጭም ብሎ የነበረውን ገጽታቸውን በፈገግታ ለውጠው ፣
በታማኞች ወታደሮቻቸው ታጅበው ቤተ - ክርስቲያን ደርሰው
ሲመለሱ ፣ በሩቅ መመልከቻ መነጽራቸው የቀይ ባሕርን አቅጣጫ
ሲመለከቱ ቆይተው ሲመለሱ አሥመራና ነዋሪዎቿ በደስታና
እፎይታ ይዋጡ ጀመር ።

ምንም እንኳን አሉላ በአጼ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት ውስጥ
ተነሥተውባቸው የነበሩትን ተቀናቃኞቻቸውንና ከሳሾቻቸውን
ቅስም ቢሰብሩበትም ቅሉ ፣ ጠቅላላው ሁኔታ ግን እጅግ ተጫጭ
ኖአቸው ስለነበረ ወታደርና ስንቅ ከማዘጋጀቱም ጋር ትካዜና

ሰመመትንም አልለዩዋቸውም ፡ ከዕለታት አንድ ቀን እንደ ተለመደው በእልፍኛቸው ታዛ ተቀምጠው የአዲሲቱን ከተማቸውን ዕድገት በዐይነ — ሕሊናቸው እየተመለከቱ የንጉሠ ነገሥቱን ተቀናቃኞችና የሀገሪቱን ጠላቶች ተራ—በተራ በመጣል የሚችሉበትን ስልት በሐሳባቸው እየነደፉ በነበሩበት ሰዓት፣ ቀጠን ያለ የልጅ አግር ድምፅ—በሩቅ ሆኖ «አቤት!አቤት! ኧረ አቤት አቤት!» ብሎ ሲጮህ ራስ አሉላም ግንባራቸውን ኮስተር አድርገው ሲያዳምጡ ፣ በገና ደርዳሪው ከአቤት ባዩ ድምፅ ላቅ አድርገው ድምጻቸውንና በገናቸውን እያስጮሁ ፣ ሲያንጎራጉሩ ፣ ያ—ቀጭን ድምፅ እንደገና «አቤት አቤት! ኧረ አቤት አቤት» ሲል ራስ አሉላም የበገናውን እንጉርጉሮ ላለማቋረጥ ሲሉ ማዳመጡን በተመስጦ መቀጠላቸውን በገነኛው ተረዱትና ፣

«ሕዝብህ እንዳያጣ ፍትህና ፍርድ
ምሕረትክን ላክለት በጸጋ ይውረድ ።
ኢትዮጵያን የሚመኝ አረመኔው ባዕድ
ይቀጥቀጥ በክንድህ ይፍራ ይርበድበድ»

እያሉ ሲደረድሩት፣ «አቤት! አቤት!አቤት! ኧረ አቤት አቤት!» የሚለው ድምፅ የራስ አሉላን ሕሊና ቀስፎ በመያዙ ፣ እንደ መበሳጨት አሉና ሲያጨበጭቡ አጋፋሪው ጠጋ አሉ ።

«ይኸ የሚጮህ ሰው ምን ሆኖ ነው?» ብለው ጠየቁ ።

«ፍርድ ስጡን ፣ ፍርድ ተጓደለብኝ» ይላል አሉ አጋፋሪ ።

«መቼም የድሃ ረኃቡና ጥማቱ ፍርድ ነው ፤ በል አቅርበው» አሉ ። አጋፋሪ እየሮጡ ወጥተው አቤት ባዩን አቀረቡት ። ራስ አሉላ አቤቱታ አቅራቢውን ሲያዩት ደነገጡና ፣

«ዛሬስ ደግሞ ልጆች አቤት ይሉብኝ ጀመር? በል አቤቱ ምን ሆንህ ነው?» ብለው ጠየቁት ።

«አባቴ ሙቷል ! እናቴም የአባቴን ንብረት ይዛ ስድስት ልጆች ስታሳድግ አሁን በቅርቡ በመንደራችን የተሾሙት ጉበር አንች ብቻሽን እንድትከፍዪ ራስ አሉላ አዘውሻል» ብለው የመንደራችን ሽማግሌዎች ስለ አዘዙዋት ያሉንን ከብቶች በሙሉ



ለመሸጥ ነድተን ስለመጣን ፣ ሊሆን ሲሆን ፍርድ ይሰጠን ያለዚያ ከብቶቹን እርስዎ ይግዙን» አላቸው ።

ራስ አሉላ በቁጣ ጠሩና ፣

«እኔን እንደዚህ ያለ ፍርድ ፈርዷል ብለው ነው ደሃይቱን ጥሪቷን የሚያሸጧት ? ለካ የኔ ስም ማታለያ የድሃ ማንገላቻ ሆኗልና ! በኔ ስም ፍርድ ይሰጥበትና ይሸጥበት ጀመረ ? በኔ ስም ለካ ግፍና ተንኮል ይሠራበታል ? የመጣኸው ከየት ነው ?» አሉ ።

«ከሠራዬ ነው» አለ አቤት ባዩ ።

«በቅርብ እነማን ይገኛሉ?» ብለው ራስ አሉላ አጋፋሪን ጠየቁ ።

«አቶ ዘጊዮርጊስ ፣ ባሻይ በኩሩና ሻቃ አርአያ መጥተዋል» አሉ አጋፋሪ ።

«ጥሯቸው» አሉ ራስ ።

የተጠሩት መኳንንቶች እየቀረቡ እጅ እየነሡ ቆሙ ፤ ራስ በመተከዛቸው ደግሞ «ዛሬ ምን ተገኝቶ ይሆን?» እያሉ ሲያስባሉ ራስ ከመኳንንቱ ላይ አፍጥጠው ፣

«ያገር ሽማግሌዎች የተባሉ ተንኮለኞች የፈጸሙትን በደልና ማታለል ይህ ሕፃን ልጅ እንኳ እስቲታዘበውና እስቲታወመው ድረስ ! ለካ ሕዝብ ተበድሏል ? በኔ ስም ድሃ ይንገላታበት ? በኔ ስም አገር ይበደልበት ጀመር ? መሬቷስ እንዴት ትረገመን ? አገሬን ጠላት እንዳይደፍራት የምደክመው ለካ ከንቱ ነው ? ለሀገር ክብር ጀግኖች እየወደቁ ሽማግሌዎችና ባላባቶች ለካ በሕዝብ ንብረት ላይ ይጫወታሉ? እግዚአብሔር የሁላችንንም ዋጋ እንደየሥራችን ይክፈል!

«እናንተስ ብትሆኑ የኔ ባለሟሎች ፣ የኔ አማካሪዎች ሆናችሁ በድሃ ላይ እንዲህ ያለ ፍርድ ሲሰጥ እየሰማችሁ እንዴት ዝም ትላላችሁ? ደግሞስ ባትሰሙስ ሕዝቡ በየአገሩ ፣ በየመንደሩ በየቤቱ እንዴት ውሎ አደረ? ምን ችግር ደርሶበታል? እያላችሁ

አትጠይቁም? ባለሟልነታችሁ ለግብር አባይነት ነው? ግብር የሚያባላኝማ መች አጣለሁ?» አሉና ወደ አጋፋሪው መለስ ብለው፣

«በል ለዚህ ልጅ ለልብሱ መግዣ የሚሆን ዐሥር ብር ስጠው» ብለው እንደገና ወደ አቤት ባዩ መለስ አሉና፣

«አባትህ ምን ሆኖ ነው የሞተው?» ብለው ጠየቁት።

«በኩፊት ጦርነት ቆስሎ መጥቶ ለብዙ ጊዜ ታሞ ኑሮ ሞተ» አላቸው።

«አያችሁ! ሰማችሁ! ትላንት ለሀገሩ ደሙን ላፈሰሰ ጀግና የሚከፈለው ውለታው ይኸው ነው? ሀገሬን ክብሬን ነጻነቴን ብሎ ለዘመተ ብድሩ ይኸው ነው? በል ንግ አጋፋሪ ለዚህ ልጅ እናትና ለልጆቹ ልብስ መግዣ መቶ ብር ስጠው። ያመጣኻቸውን ከብቶች ቀስ አድርገህ መልሰህ ውሰዳቸው! እናንተ የምትከፍሉትን ፈሰስ ታስቦ እኔ እከፍላለሁ። በኔ ስም በድሃዋ ላይ ይህን የመሰለ አስነዋሪ ብያኔ የበየኑ ሽማግሌዎችም ተይዘው እንዲመጡና ይህን ብያኔ መስጠታቸው ከተረጋገጠ መቀጮ እንዲቀጡና ድሃዋን ደግሞ አላስቀምጣት እንዳይሉ ዋስ እንዲጠሩ ለደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ እንዲነገር» ብለው አዘዙ። አቤት ባዩ ወጣትም ዕልልታውን እያቀለጠው ከግቢው ወጣ።

ራስ አሉላ፣ አሥመራ ላይ ሆነው በርከት ያለ ጦር ለመሰብሰብ ብርቱ ጥረት አደረጉ። በደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ኃላፊነት ከረን የሰፈረው ጦር ወደ አሥመራ እንዲወጣና ከዋናው ሠራዊትም ጋር እንዲቀላቀል አደረጉ። እንደዚያ አድርገው ክንዳቸውን ካፈረጠሙ በኋላ፣ ለደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ አንድ መቶ ወታደሮች ሰጥተው አሥመራ ላይ ሆነው አገሩን እንዲጠብቁ አዘው፣ አጼ ዮሐንስ ወደ ነበሩበት አሸንጌ ተጓዙ።

ምንም እንኳን በአሉላ ዝግጁነትና በመረብ ምላሽ ባሳዩት ጀግንነት አጼ ዮሐንስ ቢኮሩበትና ቢመኩበትም ቅሉ፣ ከድርቡሾች ጋር ለመዋጋት ላቀዱት ዘመቻ አሉላን የሠራዊታቸው ጠቅላይ አዛዥ አድርገው ለመሾም ግን ዋናው ችግራቸው፣



ባለሟሎቻቸውና መኳንንቶቻቸው በአሉላ ላይ በነበራቸው የየግል ንቀትና ጥላቻ የተነሣ ነበር።

በመቀሌ ቤተ መንግሥት ሥር ሰዶ ለቆየው ጥል ክስና ንትርክ አንድ እልባት ሳይደረግለት አሉላን የሠራዊታቸው ጠቅላይ አዛዥ አድርገው ቢሾሙ፣ የትግራይ መኳንንት ዕለቱን ሰማይንና ምድርን ካላጋጠምን ብለው የከፋ ትርምስ እንደሚያስነሡ የተረዱት ንጉሠ ነገሥት፣ ራስ ኃይለማርያም ጉግሣን የሠራዊታቸው አዛዥ አድርገው ሾሙ። አዲሱ የሠራዊት አዛዥ አጼ ዮሐንስ አጐታቸው በመሆናቸው፣ ለዘውዱና ለአገሩ ከእርሳቸው የበለጠ ቀራቢና ታማኝ እንደሌለ ስለ ታመነበት፣ አልጋ ወራሽም እንዲሆኑ በመኳንንቱ ዘንድ ሙሉ ተቀባይነት አግኝተው ነበር።

አጼ ዮሐንስ፣ የጐጃሙን ራስ ተክለ ሃይማኖትን አስገብረው መቶማ ለመውረድ ከአሸንጌ ተነሥተው ወደ ጐጃም ሲሻገሩ ራስ አሉላም በደብረ ታቦርና በጐንደር አካባቢ እንዲሰፍሩ ታዘዙ። ምንም እንኳ የንጉሠ ነገሥቱ ጦር ተጠቃሎ በጐጃምና በቤጌምድር ውስጥ በመሥፈሩ፣ ሰሜን ኢትዮጵያ ቢጋለጥም በምፅዋ የነበሩት ጣሊያኖች በሰሐጢ የነበራቸውን ምሽግ ከማጠናከር በቀር ፈጥነው ወደፊት ሊገፉ አልፈለጉም ነበር። ይሁን እንጂ የራስ አሉላ ተቃዋሚዎች የነበሩትን ማደፋፈሩንና ማስታጠቁን ከመቀጠል ግን አልተገቱም ነበር። ከሁሉም ቀድመው ባላምበራስ ክፍለ የሱስ፣ "ከረን ባዶዋን ስለሆነች እንድይዛት ፍቀዱልኝ» ብለው ለጄኔራል ባልዴሴራ ጻፉለት። እርሱ ግን በነበሩበት በሐባብና በበኒዓሚር አካባቢ እየተዘዋወሩ እንዲቆዩ እንጂ ከረን እንዳይገቡ ከለከላቸው።

ይሁን እንጂ፣ የራስ አሉላ ተቀናቃኞች የነበሩት እንደ ክፍለ የሱስ የመሳሰሉ ተቃዋሚዎች በየጊዜው ሕዝቡን ማስጨነቅ ስለቀጠሉ፣ አሥመራ ለነበሩት ለራስ አሉላ ወታደሮች ም/አዛዥ የነበሩት ባሻይ ገብረማርያም ከሽፍቶቹ ጋር ሲታኮሱ ሞቱ። ከዚያ በኋላ ሁኔታው እየተበላሸ ሔደ። የአካለ ጉዛይ አገረ ገዥ ሆነው አዲስ ተሹመው ተልከው የነበሩት ፊታውራሪ ደበበም፣ እንኳ አሥመራ ገብቼ የሐማሴንንም ግዛት ደርቤ መያዝ ስላ

ሱበኩ ከተማውን እንድትለቅልኝ» ብለው ለደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ላኩባቸው ። ደበበ የአካለ ጉዛይ ገዥ የሆነውም አጼ ዮሐንስም ወደ አሸንጌ ሲሔዱ ነበር ።

ደጃዝማች ኃይለሥላሴም ፡ «የጌታየን የአሉላን ግዛትና ከተማ በጉልበት ለመውሰድ ከፈለግህ እጠብቅሃለሁ ፤ ናና ሞክረኝ» ብለው ስለላኩባቸው የደጃዝማቹን ቆራጥነት ካወቁ በኋላ ደበበ ከሰገነይቲ ወደ ዐድዋ ሔደው ሠፈሩና ምፅዋ ላይ ሆኖ ለራስ አሉላ የጦር መሣሪያ ሲያስመጣላቸው ለነበረው ግሪካዊው ነጋዴ ለእርሳቸውም እንዲያመጣላቸው መላላክ ጀመሩ ። ፊታውራሪ ደበበ ከንዳቸውን አሳብጠው ሥልጣን ለመቀማት የነበራቸው ጉጉት ከግሪካዊው ነጋዴ በቂ መልስ ባለማግኘታቸው ብቻ አልተገታም ። ከቀይ ባሕር ማዶ ተሻግር አደን ለነበረው የእንግሊዝ እንደራሴም ደረሰ ። የነበራቸውን ጉጉት ሲጽፉለትም ፡

«በምንም ነገር ከንጉሡ ጋር አይደለሁም ። ራሴ የቤተ መንግሥቱ ፡ የዘውዱ ተወላጅ ነኝ ፤ የክርስቶስ ፈቃዱ የሆነልኝም እንደ ሆን የእርስዎን ርዳታ አገኛለሁ ። ከእንግዲህ ወዲያ ምንም ዐይነት ችግር አይኖርብኝም ። ከልቤ አፈቅርዎታለሁ ፤ አምንዎትማለሁ ። እርስዎም ይመኑኝ ። አጼ ዮሐንስን ለዙፋናቸው ያበቃችኋቸው እናንተ መሆናችሁን ዐውቃለሁ ። እኔንም ለዙፋኔ እንድታበቁኝ እለምናለሁ» ብለውታል ።

ባላምበራስ ክፍለየሱስ ፡ ከረንና አሥመራን ካልያዝኩ እያሉ በሚገለገሉበት ሰዓት ደበበ ደግሞ የአሉላን ግዛት ለመያዝ ተመኝተው ካታታቸው በኋላ ፡ ዙፋን ላይ አስቀምጡኝ እያሉ የባሕር ማዶን ሰዎች መለመን በጀመሩበት ወቅት በአምባ ሰላማ ተራራ ላይ ታስረው የነበሩት ራስ ወልደጊዮርጊስ ደግሞ ያንሰራሩና ክፍለየሱስን ና ጣሊያኖች ከረንና አሥመራን እንዲይዙ ምፅዋ የነበረው የኢጣሊያ ጦር አዛዥ የጻፉት ደብዳቤ አሥመራ ሲደርስ ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ይዘው በጌምድር ለነበሩት ለራስ አሉላ ሰደዱላቸው ። ከእነዚህ ሌላ ደግሞ የአጼ ዮሐንስ የእኅት ልጅ የነበሩትና ለብዙ ዓመታት በእስር ላይ የኖሩት ደጃዝ



ማች ሥዩም ገብረኪዳን (አባ ጉበዝ) የአሉላን ግዛት ለመያዝ ታጥቀው ተነሡ ።

ደጃዝማች ሥዩም ፡ ጉጃም ውስጥ ታስረው ሲኖሩ አጼ ዮሐንስ ራስ ተክለሃይማኖትን ለማስገበር ጉጃም እንደገቡ ፡ ራስ ተክለ ሃይማኖትም ደጃዝማች ሥዩምን ፈትተው ወደ ንጉሥ ምኒልክ ሰደዱዋቸው ። ምኒልክም ደጃዝማች ሥዩምን ይቀበሉና በምን ተግባር ላይ ሊያሠማሩዋቸው እንደሚችሉ ማሰላሰል ጀመሩ ።

አጼ ዮሐንስ ፡ ጉጃምን እያስመዘበሩ ወደ ሸዋም ለመግባት ማቀዳቸውን ንጉሥ ምኒልክ እንደ ሰሙ በይበልጥ ስልታቸውን ማቀነባበር ቀጠሉና ደጃዝማች ሥዩምን አስታጥቀው ወደ እንደርታ ሰደዱዋቸው ።

የሰሜን ኢትዮጵያ ሁኔታ እንደዚያ በመሰለ ምስቅልቅል ላይ መውደቁን በጌምድር የነበሩት ራስ አሉላ እንደ ሰሙ ፡ ልጅ ፋንታንና ሻቃ አርአያን አንድ መቶ ሃምሳ ከሚሆኑ ወታደሮች ጋር ወደ አሥመራ ከመስደድ በቀር ራሳቸው ለመሔድ ወይም በርከት ያለ ጦር ለመስደድ አልተቻላቸውም ።

ይሁን እንጂ ፡ የአሉላን ከተማ ለመያዝ ደፍሮ ገቦ የጀመረ ማንም አልነበረም ። ደጃዝማች ኃይለሥላሴም ፡ «ጌታ ራስ ሊመጡ ነውና ጠጅ ጣሉ ሠንጋ ሰብስቡ» እያሉ ስለሚያዙ የአሥመራም ሕዝብ ዘወትር «መጡ መጡ እያለ የተሰፋ ወሬውን ያቀባብለው ነበርና ፡ እነክፍለ የሱስንና ጣሊያኖችን በነበሩበት ገትቷቸው ቆይቷል ። የአሉላ ምኞትና ጉጉት አሥመራ ተመልሰው የሰሜኑን በር መዝጋት ቢሆንም ፡ ንጉሥ ነገሥቱ ደግሞ ከመኳንንቶቻቸው ጋር ውስጥ ውስጡን ተበጣብጠው ነበርና ፡ ራስ ሐጎስን ከንጉሥ ምኒልክ ጋር «ተመሳጥረሃል» ፡ በጅሮንድ ለውጤን ከራስ ተክለ ሃይማኖት ጋር «ተላልከሃል» እያሉ አስረዋቸው ስለ ነበር ፡ አሉላን ከአጠገባቸው ለማራቅ አልፈቀዱም ነበር ። አሉላም እነዚሁ የመረሩ ጠላቶቻቸው ስለ ታሰሩ

ችላው በቤተ መንግሥቱ ዘንድ የነበራቸውን የተጠናከረ አቋም መጠበቅ ተገቢያቸው እንደ ነበረ እምነውበት ነበር ።

'ሃይማኖት የሚያጠፋ ጠላት መጥቶብኝ ከወንድሞቼ ጋር አልዋጋም' ብለው የተነሡት አጼ ዮሐንስ፣ ሠራዊታቸውን ጐጃምና ጐንደር አስፍረው ተክለ ሃይማኖትን አስከብበው ምኒልክን ማስፈራራቱን በመቀጠላቸው፣ ምኒልክም ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ መንልበትና ዝግጅታቸውን መጠናከር ዋና ሥራቸው አድርገው ተያያዙት ።

በተራራ ላይ ከነሠራዊታቸው ተከበው የነበሩት ራስ ተክለ ሃይማኖት ንጉሥ ምኒልክ የማይደርሱላቸው መሆኑን ተረድተው ተስፋ በቆረጡበት ሰዓት አጼ ዮሐንስ «ከነሠራዊትህ ከምታልቅ እጅህን ስጠኝ፣ ምሬሃለሁ የወንድማማች ደም አናፋስ» የሚል መልእክት ሰደዱላቸው ። ተክለ ሃይማኖትም መልእክቱን በደስታ ተቀብለው እጃቸውን ሰጡና ዕርቅ ሆነ ።

በጐጃም በኩል የነበረው ችግር በእርቅ ከተፈታ በኋላ ራስ አሉላ የዐባይን ወንዝ ተሻግረው እንዲስፋፉና በሸዋ ላይ እንዲያነጸጽሩ ቀጥሎም ንጉሠ ነገሥቱ እንዲዘምቱ ተወሰነ ። ግን ይህን ዕቅድ በመጀመሪያ ራስ አሉላ ቀጥሎም ራስ አርአያ ተቃወሙ ።

«ሃይማኖትና አገር የሚያጠፉ ሁለት ጠላቶች በስተኋላችን አሰፈሰፈው፣ ከወንድማችን ከምኒልክ ጋር ለመግጠም እንዴት እንችኩላለን? የወንድማማቾች ደም ለምን ይፈስሳል? እርስበርሳችን ከተጫራረስን አገሪቱ ባዶዋን መቅረቷን ጃንሆይ መች ይስቱታል!» ብለው ራስ አሉላ ተከራከሩ ። የእርሳቸውን ሐሳብም ትላልቆቹ መኳንንት ደገፉት ።

«እኔስ መች ደም እንዲፈስ እወዳለሁ? ከዚህ ቀደምስ የወሰንኩት ጉዳይ አይደለም? እኛ ብንጋደል፣ እኛ ብንጫረስ እኛ ብንፋጅለት ጠላት ደስ እንደሚለው መች አጣሁት! አሁንም መልካም አስባችኋል ። የድርቡሹ ጦር ጠብ ያለመፈለጉን እንዲረዳው እልክበታለሁ ። እምቢ ካለም እርሱን በጀርባዬ ትቼ ወደ ወንድሜ አልዘምትም» ብለው አጼ ዮሐንስም ተስማሙና መተማ፣



በተለይ ጋላባት፣ ሠፍሮ ለነበረው ድርቡሽ ጦር አዛዥ ለአቤ እንጃ መልእክት አስተላለፉለት ። በመልእክታቸውም ውስጥ፣

«እኔም ያገሬን ጠረፍ ዐልፌ ወደ ግዛትህ ለመግባት ሐሳብ የለኝም ፤ አንተም ካገርህ ጠረፍ ዐልፈህ ወደኔ አገር ለመግባት ምኞት ከሌለህ፣ በመካከላችን ሰላም እንጂ ጠብ አይኖርብንም። ይልቅስ የሁለታችንም ጠላት በሆኑት ፈረንጆች ላይ በአንድነት እንሰለፍባቸው» የሚል ቃል ነበረበት ። የድርቡሹ ጦር አለቃ በላከላቸው ምላሽ ላይ ግን፣

«ድፍረትና ወንድነት ካለህ ናና እንጋጠም ። ባትፈራኝ ኑሮ እንደዚህ ብለህ ከመጻፍ ትዘምት ነበር ። አሁንም ካለህበት የማትወጣ ከሆንክ ተዘጋጅተህ ጠብቀኝ እመጣልሃለሁ» የሚል ዐረፍተ ነገር ስለ ነበረበት አጼ ዮሐንስ ቀርተው አሽከሮቻቸው ሊታገሡት የማይላቸው ውርደት ሆነ ።

«እንግዲህ ከዚህ የበለጠ ውርደት መቼም አይደርስብኝም፣ ከዚህ የከፋ ጠላትም በኋላዬ ትቼ ወደ ወንድሜ አልሔድም ። ወንድሜን በጀርባዬ አዝዬ በግንባሬ ወደመጣው ጠላቴ እዘምታለሁ ። ከዚያ ከተመለስኩም ወደ ሸዋ እዘምታለሁ» ። ብለው ወሰኑና ወደ መተማ ዘመቱ ።

የአጼ ዮሐንስ ሠራዊት ደንቢያ ላይ ሲከማች በራስ አሉላም ውስጥ ከዐሥራ አምስት ሺህ በላይ የሚሆን የተጠናከረ ጦረ ተደለደለ ። ከእርሳቸው ቀጥለውም ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ራስ ሚካኤል፣ ራስ ኃይለ ማርያምና ራስ መንገሻ ብዛት የነበረው ጦር ነበራቸው ። የንጉሠ ነገሥቱ ጦር እንደዚያ ሆኖ ተጠናክሮ በነበረበት ወቅት ከአሥመራ ደግሞ አስደንጋጭ ዜና ራስ አሉላ ደረሳቸው ። የአሥመራን ከተማ ባላምባራስ ክፍሌ የሱስና ደበበ ሊቀራመቷት እንደ ከበቡዋት ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ መልእክተኛ ሰደዱ ።

ራስ አሉላም ወደ ግዛታቸው ገሥግሠው ዐመፀኞቹን አጥፍተው፣ አገሩን አደላድለው ለመመለስ እንዲፈቅዱላቸው አጼ ዮሐንስን ለመኑ ። አጼ ዮሐንስ ግን፣ «በዚህ ፈረስ ወደፈለ ግህበት አገር ዝመትበት ፣ በዚህም ጉራዴ የፈለግሽውን ቅላ

ቡት» ብለው ሾመው ወደ አካለ ጉዛይ የሰደዱዋቸው የአጎታቸው ልጅ ደበበ ይከዳኛል ብለው ስላልጠረጠሩ አሉላ ያቀረቡትን ልመና አምነው መቀበል አልቻሉም ። በመጨረሻም አሉላ ታማኞቻቸውን ባሻይ ደስታን መጠነኛ ወታደር ይዘው ወደ አሥመራ እንዲመለሱና በሁለት በኩል የተከበበችውን ከተማቸውን እንዲከላከሉ ለመላክ ተፈቀደላቸው ።

በመጀመሪያ የአሉላን ግዛት ተጥሉም የዮሐንስን ዙፋን ይመኙ የነበሩት ደበበ ግን ፣ ምፅዋ የነበረው የኢጣሊያ ጦር አዛዥ ባልዲሴራ ይቅርታ እንዲያደርግላቸውና ርዳታ እንዲልክላቸው ተማፀኑት ። በዚህም መሠረት ሁለት ሺህ ያህል ወታደር አስከትለው ወደ ሠገነይቲ ሒደው ከጀኔራል ባልዲሴራና ከሻለቃ ፒያኖ ጋር ተገናኝተው ከተመካከሩ በኋላ ወደ አሥመራ ገሠገሡ ። ወዲያውም የካቲት 3 ቀን 1881 ከደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጋር አዲ ዳር ከተባለው ቦታ ላይ ጦርነት ገጥመው ደጃዝማችን ገድለው ፣ በድል አድራጊነት አሥመራን ይዘው ከተቀናቃኛቸው ከአሉላ አባ ነጋ ቤት ገቡ ።

አሥመራን ከያዙ በኋላ ለጀኔራል ባልዲሴራ በጻፉት ደብዳቤ ፣ «ንጉሡ በጻፉልኝ ደብዳቤ ላይ 'ጣሊያኖችን ተዋቸውና ወደኔ ተመለስ ፣ የአባትህንም የራስነት ማዕረግ እሰጥሃለሁ' ብለውኛል ። ግን ፣ እስከ ዛሬ ንጉሡ የሰጡኝ ማዕረግ ደጃዝማችነት ብቻ ነው ። እኔ ግን አገር ነው የምፈልገው ! የምገዛው አገር አልሰጡኝም ! ዛሬ ግን ገሚሱ ኢትዮጵያ በእጄ ገብቷል ! እኔም እርስዎም ስላገኘነው ድል ደስ ሊለን ይገባል ። እንግዲህ መሣሪያም ሆነ ገንዘብ አልጠይቅዎትም ። ግን ወዳጅነትዎን አጥብቄ እፈልገዋለሁና እጅዎን ዘርግተው እንዲቀበሉኝ እለምንዎታለሁ» ብለዋል ።

ምንም እንኳን ደበበ በጉልበታቸው የመረብን ምላሽ ግዛት የጨበጡ መሆናቸውን አረጋግጠው ፣ ከጣሊያኖች ጋር ለመወዳጀት አስበው መልእክተኛ እየላኩ ዶጅ ጥናት ቢጀምሩም ፣ ጣሊያኖቹ ደግሞ የራሳቸው ዓላማ ነበራቸውና ደበበ አሥመራ ከመግባታቸው ሦስት ቀናት በፊት በክፍለ የቡስ መሪነት ከረን ገብ



ተው ብንዲራቸውን ሰቅለው ነበር ። ለደበበ ደብዳቤ ምላሽን ከመስጠት ፈንታም አሥመራን መያዝ በጣም ቀላል ሆነላቸው ።

ራስ ኃይለ ማርያም የአጎታቸው የአፄ ዮሐንስ ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ እንደሆኑ ወደ መተማ ጉዞ ሲጀመር ፣ የገብረ ልጅ አሉላ የማይቀበሉት ጉዳይ ሆነባቸው ። ምንም እንኳን ሹመቱ ቀደም ብሎ የተሰጠ ቢሆን ወደ አሥመራ ከመሔድ ይልቅ ከአጠገባቸው እንዳይርቁባቸው ጌታቸው ሲያዙዋቸው የጦር አበጋዝነቱን ይመልሱልኝ ይሆናል የሚል ተስፋም ነበራቸው ። በመጨረሻው ግን ንጉሠ ነገሥቱ ከሰጡት ውሳኔ የማይመለሱና የጦር አዛዥነቱን ከራስ ኃይለ ማርያም የማያነሡ መሆናቸውን ካረጋገጡ በኋላ አሉላም የጦር አለቆቻቸውን ሰብስበው ፣

«ተከታዮቼ እንጂ ተዋጊዎች እንድንሆን አልተፈለግንም ። ምንም ወዳጆቼና አሽከሮቼም ብትሆኑ በዚህ አስከፊና ዘምተን ጦርነት ገጥመን ድል ያደረግን እንደሆን ታዘቡኝ ! እንዲያውም ባልተስማማሁበትና ባልመከርኩበት ፣ መኳንንትና ባለሟሎች ተጠቃቅሰው በተሸጋሙበት ጦርነት ለምን እሰማራለሁ ! ትላንት ከፊት ላይ ቁስለኛ ሆኜ ደርቤ እጄን ለመስጠት ነው ! ወይስ ለመሸሽ ! የትውልድ ግዛቴ ጋር መታቲያ ለማግኘት ነው ? ያለኝን ወታደር ይውሰዱት ! እኔ አሉላ ግን አልነሣሣም ! እኔ የገብረ ልጅ ግን ወደ አርሻዬ እመለሳለሁ ። የመኳንንትና የባለሟል እንክርት ሰብስበው አገሬን ለማዋረድ ሲሔዱ አብሬ አልታይም» ብለው ድንኳናቸውን አስነቅለው ፣ ሠራዊታቸውን ለቀው ለመውጣት መዘጋጀት ጀመሩ ።

ይህን የተመለከቱ የጦር አበጋዞችና ባለሟሎቻቸው ደግሞ ተሰብስበው ከእግራቸው ላይ ወድቀው ፣

«ትላንት ልጃቸውን ቀብረው ፣ ጠላት በፊት በኋላ በቀኝ በግራ ተሰልፎባቸው ፣ ዛሬ እርስዎ ሲያኮርፉባቸው አገር ምን ይለዎታል ! ባይመለሱ ባይዘምቱ ነው የከዱዋቸው» ነው የሚባሉት ። ጦርነቱስ ቢበላሽ አገርና ታሪክ የሚፈርዱት በእሳቸው

ነው ፣ እስዎ ምንተዳዎ፣ አሁንም በሚያምኑት በዝቲሊው ሚካ ችል ይዘነዎታል! ሐሳብዎን ያንሡልን» ብለው ለመኑ ።

«እኔማ ምን ቸገረኝ፣ ለአገርና ለራሳቸው በይበልጥም ደግሞ በዚህ ስልትና በቅምጥል መኳንንት አዝማችነት የሚሰለፈው ሠራዊት ከንቱ እልቂት አሳርሮኝ ነው እንጂ!» ብለው ሐሳባ ቸውን አነሡና ለዘመቻዉ ተሰለፉ ።

ራሳቸው ንጉሠ ነገሥቱ የዘመቱበትን ሠራዊት ጠቅላይ አዝማችቹ ራስ ኃይለ ማርያም በሚከተለው አኳኋን መደቡት።

1ኛ. ራስ መንገሻና ራስ ኃይለ ማርያም የንጉሠ ነገሥቱን ሁለት ክፍል ሠራዊት ይዘው በራስ ኃይለ ማርያም የበላይ አዛዥ ነት በግንባር ፣

2ኛ. ራስ አሉላ ከራስ መንገሻ ጋር ሆነው በራሳቸው በአሉላ አዛዥነት በቀኝ ክንፍ እንዲሰለፉ ተወሰነ ። ይህን አሰላለፍ አሉላ ከታተቃወሙት ምክንያት አንዱም ፣

«ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ጦርነቱ ሲሔዱ ሠራዊቱ በአምስት ክፍል ተመድቦ በደጀንነት ፣ በግንባር በቀኝ በግራና ከጠላት በስተኋላ እንዲሰለፍ» ብለው ነበር ። ይህ አልሆነምና በተቃወሙት ስልት ተሰለፉ ።»

የሁለቱ ወገኖች ሠራዊት ወደፊት እየገፋ ለመጨረሻው ትንቅንቅ በሚዘጋጅበት ወቅት ደግሞ ፣ የማሕዲስቶቹ ጦር ጠቅላይ አዛዥ የነበረው ሐመዳን አቡ አንጃ በድንገተኛ ሕመም ሞተ ። ምክትሉ አዛኪ ካማል ጦሩን ባመነበት ስልት ደልድሎ አሰለፈ ። ጦርነቱ ቅዳሜ መጋቢት 1 ቀን 1881 ሲጀመር የማሕዲስቶቹ ጦር በቀኝ ክንፍ የነበረውን የኢትዮጵያን ሠራዊት መሜን በማሳየቱ ራስ አሉላ በራሳቸው ስልት ወታደር ቻቸውን ከፋፍለው መዋጋት ጀመሩ ። እየቆየም የኢትዮጵያ ጦር እያጠቃ ወደ ጠላት ምሽግ መግባት ሲጀምር የግንባር አዋጊ የነበሩት አሉላ በጥይት ተመትተው ወደቁ ። ወዲያው ቀልጥፈው ብድግ አሉና «አልተጎዳሁም ወደኋላህ ያየህ ጠላቱ ነህና ምራ አልምርም» ብለው አሰለፉ ። የተደናገጠው ሁሉ ተረጋግቶ ጦርነቱን ቀጠለና የጠላቱን ምሽግ አደበላለቀው ።



ገና ጦርነቱ ከመጀመሩ አስቀድሞ አሰላለፉንና ስልቱን አሉላ ተቃውመውት የነበረው ፣ በራስ ኃይለማርያም በኩል የነበረው ግንባር ግን እንደ ፈሩት መታጠፍ አመጣ ። አዝማቹ ራስ ኃይለ ማርያምም በጥይት ተመትተው ሲወድቁ ጦሩ መበታተን ጀመረ ።

የራስ አሉላ ስትልትና ሠራዊት ግን ፣ የጠላት ምሽግ ጥሶ መግባቱን የተመለከቱት አጼ ዮሐንስ በራስ ኃይለማርያም በኩል የተሰለፈውን ጦር ከ ጊሸሸበት እየተከላከሉ ወደፊት እንዲገፋ በሚጣጣሩበት ሰዓት «ሌኛ ምሽጉን ጥሰን ገብተናልና ወደኛ ይምጡ» ብለው ራስ መንገሻ ፈረሰኛ ላኩባቸው ። ንጉሠ ነገሥቱም እንደ አንድ ጀግና ወታደር እየተኮሱ ጠላት እየጣሉ ወደ ሬት በማምራት ላይ እንዳሉ ቀኝ እጃውን በጥይት ተመቱ። ነጠላቸውን ቀደው ቁስላቸውን አሰሩና ወደፊት ገፉ ። ወዲያው ደግሞ ግራ እጃቸውን የመታቻቸው ጥይት ደረታቸውንም አገኘቻቸው ። አሽከሮቻቸው ተሸክመው ወደ ድንኳናቸው ወሰዱዋቸው ።

የንጉሠ ነገሥቱ መቁሰል በሠራዊቱ ዘንድ እንደ ተሰማ ታላቅ ድንጋጤ ሆነ ። ወዲያውም ሲያጠቃና ሲያባርር የነበረው ጦር ወደ ኋላው መሸሽ በመጀመሩ ተባራሪ ው ጦር እየተከታተለ ፈጀው ። ጊዜው መሽቶ ሲጨልም ብቻ ለኢትዮጵያ ሠራዊት ታላቅ እፎይታ ሆነ ። ንጉሠ ነገሥቱ ግን ሲሠቃዩ ነበር ያደሩት ።

ጐህ ሲቀድ የንጉሡን ሁኔታ ለማወቅ ብለው ራስ አሉላ ሔዱና አጠገባቸው ሲቆሙ ንጉሡም ጠቀስ አድርገው በጆሮአቸው "ከምወደው ልጄ ከመንገሻ ጋር ሆናችሁ አገሬን ጠብቁ ወራሼም እርሱ ነው" ብለው ነገሩዋቸው ።

እስከዚያች ዕለት ግን ራስ መንገሻ የአጼ ዮሐንስ የወንድም ልጅ ናቸው ነበር የ ሚባሉት ። በዚያች ዕለት 'በሞት አፋፍ መያዛቸውን ያረጋገጡት ንጉሠ ነገሥት ፣ መንገሻ ልጃቸው እንጂ የወንድማቸው ልጅ ያለ መሆናቸውን አመኑ' ተብሎም በሰፊው

ይወራ ነበር ። የመንገሻን እልኃ ወራሽነት ለራስ አሉላ ካረጋገጡላቸው በኋላም ፣

“ልጄ ታማኙ አሉላ ሆይ! መንገሻን እንደ አባቱ ሆነህ ጠብቀው ። ለኔ የነበረህን ታማኝነት ለርሱም እንዳትነፍገው ፣ አደራ ሰጥቼሃለሁ” አሉና ራስ መንገሻንም አስቀርበው ፤

“ልጄ መንገሻ ፣ አሉላን አባትህ እንዲሆን ሰጥቼሃለሁ ፤ ከቃሉ እንዳትወጣ! ትእዛዙንም እንዳትጥስ አደራ ብየሃለሁ!” ብለው ኑዛዜያቸውን ፈጽመው ዐረፉ ።

ራስ አሉላና ራስ መንገሻ ተቧታትና የነበረውን ጦር ሰብስበው ለመዋጋት ያደረጉት ጥረት ከንቱ መሆኑን ተረድተው ፣ የንጉሠ ነገሥቱን አስከሬን ይዘው ፣ ወደ ኋላቸው ወደ ጐንደር ጉዞ መጀመራቸውን በሰላዩ አማካይነት የሰማው ሲሸሽ የነበረ የማሕዲስቶች ጦር መከተል ጀመረ ። የንጉሠ ነገሥቱን አስከሬን ላለማስነካትም ሲሉ ታማኞቻቸው የመጨረሻውን ውድቀት ተዋደቁ ። አትባራ ወንዝ አጠገብ ሲደርሱ በተደረገው የከፋ ፣ ጦርነት ታላቁ ራስ አርአያ ድምፁ ፣ ቢትወደድ ገብረ መስቀል ፣ ደጃዝማች ቀጸላና ሌሎቹም ታላላቅ የጦር አለቆችና ጀግኖች በንጉሠ ነገሥቱ ሬሳ ፊት ወደቁ ።

“የአቢሲኒያ ንበልባለ—አባት” እየተባሉ በውጭ ሀገር ታሪክ የሚጠሩት ራስ አሉላም የአደራ ልጃቸውን ራስ መንገሻን ይዘው ተመለሱ ። በሕይወታቸው የመጀመሪያና መጨረሻ የሆነው ‘ሽሽት’ የዚያን ዕለት ብቻ ሆነ ።

የማሕዲስቶች ጦር አዛዡም ዘኪ የአጼ ዮሐንስን ሬሳ ማርኮ እንገታቸውን ቆርጦ ፣ “የዮሐንስንና የአሉላን ጭንቅላቶች ቆርጬ ልኬልሃለሁ” ብሎ ለከሊፋው ላከ ። እርግጥ የአጼ ዮሐንስ ጭንቅላት ካርቱም ደርሷል ። የአሉላ ጭንቅላት ግን አልተገኘም ።

ከሊፋው የአጼ ዮሐንስን ጭንቅላት በገመል ላይ ጭኖ በካርቱም ገበያ ሲያዞር በንቀት ሲጥለው በዚያ ነዋሪ የነበረ አንድ ነጋዴ በድብቅ ወስዶ ኢየሩሳሌም ተቀብሯል የሚል አፈ ታሪክም አለ ።



አጼ ዮሐንስ በሞቱ ጊዜ ከሕዝብ የቀረበ እንጉርጉሮ ፤

“አጼ ዮሐንስ ሞኝ ናቸው
እኛም ሁላችን ናቅናቸው ።
ንጉሥ ቢሉዋቸው በመሻሉ
ወሰን ጠባቂ ልሁን አሉ ።
አጼ ዮሐንስ ይዋኛሉ
መጠጥ አልጠጣም እያሉ
ሲጠጡ አይተናል በርግጥ
ራስ የሚያዞር መጠጥ ።
በዶንቢያ መታረድ አዝኖ ዮሐንስ
ደሙን አፈሰሰ እንደ ክርስቶስ ።
እንዳያምረው ብሎ ደግ ወዳጁን
መተማ አፈሰሰው ዮሐንስ ጠጁን ።
ቆማ ስታለቅስ የጐንደር ሃይማኖት
እንገቱን ሰጠላት ዳግማይ ዮሐንስ ።”

የአጼ ዮሐንስ ሞት ከማንም ይበልጥ የጐዳው “ወዲ ቁቢን” ነው ። ከመተማው ጦርነት ንጉሠ ነገሥቱ በድል አድራጊነት ተመልሰው ቢሆን ኖሮ ፣ ለ“ወዲ ቁቢ” እስከ ምን ድረስ የላቀ ክብርና ሥልጣን ይመርቁላቸው ነበር? የሚል ጥያቄም በያንዳንዳችን አእምሮ ሊቀረጽ ይችላል ። ምናልባትም የመጠቀ ፣ እጅግ የላቀ ሥልጣን እያጠም ነበር የሚያሰኙን ምክንያት አሉ ። ይኸውም የመረሩ ተቃዋሚዎቻቸው መደናገጥ ነበር ። ራስ ሐጐስና በጅሮንድ ለውጤ ታስረዋል ፤ ተመሳሳዩ ርምጃም ሳይቀጥል አይቀርም ነበር ። የአሉላን ታማኝነትና ትጉ አገልጋይነት አጼ ዮሐንስ እየተረዱት መሔድ ከጀመሩም ውለው አድረው ነበርና ።

ራስ አሉላ መተማ ደርሰው እስኪመለሱ ድረስ እሥመራና ሐማሴን አልጠበቋቸውም ። ተወስደዋል ። ከዚያ በኋላ የአሉላ ጉልበት ኰሰሰ ። ጠባራው ጡንቻቸው ሰለለ ። የነቢና የኃይል ምንጫቸው ነጠፈ ። ከዚያ በኋላ ወደ ወጡበት መንደርና ቤት መመለስ ግድ ሆነ ። ከዚያም በኋላ በ“ወዲ—ቁቢ”እነታቸው የትግራይ መኳንንት የበይ ተመልካች መሆን ነበር ።

የነራስ ሚካኤል ሥሁል ፣ የነራስ አርአያ ድምፁ ፣ የነራስ ወልደ ሥላሴ ፣ የነስባጋዲስ እግዜ—ርስት በሆነችው ትግራይ

ውስጥ "ወዲ—ቁቢ" በጀግንነቱና በታማኝነቱ ተማምኖ በርካታ ሠራዊት እያስተዳደረ መኖር እንደማይችል ከማንም በፊት ከማንም ይበልጥ በቅድሚያ የተረዱት ራስ አሉላ ፣ ከመተማ ወደ ትግራይ ገና በመመለስ ላይ እንዳሉ ፣ ገና መቀሌ ሳይደርሱ ስለ ተረዱት ፣ ዐይኑን አፍጦ ጥርሱን አግጦ አፉን ከፍቶ ከጥቅጥቅ ጨለማ ውስጥ ወጥቶ ሊውጣቸው ሲሮጥባቸው ፣ ከነበረው ድህነት ለማምለጥ ሲሉ በአደራነት የተቀበሉትን መስፍን እንግሠው እንደራሴ ከመሆን ሌላ አማራጭ እንደማይኖራቸው ፈጣን አዕምሮአቸው ፈጥኖ ተረዳው ። ምናልባትም በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም ፣ ከመተማ መልስ ወጣቱን መስፍን ይዘው ወደ መቀሌ ከመሔድ ፊንታ አክሱም የገቡት ።

ከመተማ ጦርነት መልስ ፣ ራስ መንገሻን አክሱም ወስደው በኢትዮጵያ የነገሥታት ሥርዓት መሠረት አንግሠው ፣ በእንደራሴነትና በአደራ-አባትነት ጥላ ተከልለው የተቃዋሚዎቻቸውን ቅስም ለመስበር አሉላ የነበራቸውን ዕቅድ ደግሞ ራሳቸው ራስ መንገሻና የትግራይ ሁኔታ እያደነቃቀፋቸው ሔደ ።

ራስ መንገሻን በስሜን በኩል ጣሊያኖች ፣ በደቡብ ደግሞ ምኒልክ አፍጥጠው እንደ ሚመለከቱዋቸውና ለንጉሠ ነገሥትነቱ ደረጃ ሊደርሱ እንደማይችሉ ሁኔታው ራሱ ያስረዳ ጀመር ።

በሌላ በኩል ደግሞ ፣ የአጋሜ ገዥ የነበሩት ደጃዝማች ስብሐት አረጋዊ ከመተማ ጦርነት ራስ መንገሻንና ራስ አሉላን አጅበው ከተመለሱ በኋላ ፣ መቀሌ በተሰነባበቱበት ወቅት የራስ መንገሻ ታማኝ ከነበሩት ከደጃዝማች ተድላ ጋር በሐሳብ በመጋጨታቸው ፣ እንደ ማኩረፍ ብለው ለማንም ሳይናገሩ ከመቀሌ ከተማ በጠፍ ጨረቃ ወጥተው አጋሜ ገቡ ። የሰጡትም ምክንያት "ከራስ መንገሻ ጋር መግባባት እየቸገረኝ ስለሚሔድ ከኢጣሊያኖቹ ጋር መጠጋትና ራሴን ብችል ይሻላል" የሚል ነበር ።

የዚያን ጊዜዋን ትግራይን ሲያተራምሱዋት ከነበሩት መሳፍንት ደግሞ ዋናውና አንዱ ደበበ አርአያ ነበሩ ። የራስ አሉላን ግዛት ይዣለሁ ብለው አሥመራ ላይ ለጥቂት ቀናት ያህል እንደ ቆዩ ፣ ጣሊያኖች በከረን በኩል ሲገቡ ፣ ርባቸውም ወደ አካለ ጉዛይ



ሼሹና ጦር በመሰብሰብ ላይ እንዳሉ ፣ ደጃዝማች ተድላ ደግሞ አካለ ጉዛይን ለመያዝ ስለ ሔዱባቸው ሁለቱ ጦርነት ገጠሙ። ከሁለቱም በርከት ያለ ወታደር አጨራርሰው ተድላ ወደ ዐድዋ ሲመለሱ ደበበ ሰገነይቲ ላይ ሆነው የሚመጣውን መጠባበቅ ጀመሩ ።

ትልቁ ራስ አርአያ መተማ ከሞቱ በኋላ ፣ የእርሳቸውን ልጆች እየያዙ ወደ ወህኒ ቤት ካልጨመሩ አገሩ ሰላም እንዳማያገኝ ከመንገሻ ይልቅ ራስ አሉላ አምነውበት ነበርና ፣ የነ ደበበን እጅ መያዝ ከመቸውም ይበልጥ ይመኙትና ይቋምጡለት ጀመር ።

ይህንን ምኞታቸውን በልባቸው እንዳመቁ ደበበ ወደ መቀሌ እንዲሔዱና በሰላም እንዲቀመጡ የሚያግባቡ ሰዎች ሰደዱ ። ደበበም የአሉላን ሐሳብ አስቀድመው እንደ ደረሱበት ሁሉ ፣

"እኔ ከእርስዎ ከወንድሜ ርቄ መኖር አይቻለኝም ፤ ከልብ ልታረቅ እወዳለሁ ። ለእርቁና ለወንድምነቱ ሲሉ ግን የአሉላን እጅ ይዘው ይስጡኝ ፤ ከዚያ በኋላ እኔም የእርስዎ ታዛዥና ወንድምነቴን በሙሉ ፈቃዴ እቀጥላለሁ" ብለው ለራስ መንገሻ ላኩ ።

ራስ መንገሻም ፣ "አሉላ አባቴ ናቸው ፤ መካሪዬና ጠባቂዬም ናቸው ፤ ልጅ ደግሞ አባቱን መካድና ማታለል አይገባውም" ብለው ስለ መለሱላቸው የመሳፍንቱ ልጆች ትግራይን በይበልጥ ማመሳቀሉን ቀጠሉበት ።

"አገሩን እንደምን አድርገን ነው የምናረጋጋው? የራሳችን ዘመዶችኮ ከድርቡሽ የከፉ ጨካኞች ፣ ከጣሊያንም የበለጡ ተንኮለኞች ሆኑብን ፣ ምን ይታይዎታል?" ብለው ራስ መንገሻ የአደራ አባታቸውን ራስ አሉላን ምክር ጠየቁ ።

"እውነትህን ነው ፣ በመጀመሪያ አገሩ መረጋጋት ሕዝቡም አንድ መሆን ይገባዋል ። ከትግራይም ሌላ በሐማሴን በኩል የሚሰማው ምስቅልቅል ከኛ ውጭ ሊሆን በመቃረብ ላይ ነው ።

የሚያሳስበንም የዚያ ጉዳይ ነው ። ስለጠጉ አንበሳም ያልናቸው ጣሊያኖች ከረንና አሥመራን በጉልበታቸው ከያዙብን ደግሞ ጠቅላላው ሁኔታችን ሚዛን ያጣል” አሉ ራስ አሉላም ።

“በዚህ በኩል እኔ አለሁ ። በሐማሴን በኩልስ ምን ብናደርግ ይሻላል? ወይ እርስዎ ሔደው አገሩን እያደላደለውና ሰው አድርገውበት ቢመለሱ አይሻልም ይሆን?” ሲሉ ራስ መንገሻ ፣ አሉላን የሐሳብ ስንጥር ወጋቸው ። ከመቀሌ ከወጡ እንደገና ደግሞ የትግራይ መኳንንት በመንገሻ ዙሪያ ተሰብስበው በሩን ሊዘጉባቸው እንደሚችሉ ተረድተውና ፣

“እኔማ ባልከፋኝ ነበር ። ግን ካንተ ከተለየሁ ደግሞ እዚህ ያለው ነገር ያስቸግርሃል ። እኒ የሐንበሰን ሲያሳስቱ የኛ ደግሞ እንተን ገደል ይሰዱሃል ፤ ካጠገብህማ መራቅ የለብኝም” አሉና ትክ ብለው ተመለከቷቸው ።

“እሱማ እውነት ነው ። ከዚህ ያለው ሳይረጋጋ መራቅ ምላሽ ቢሻገሩ ነገሩ ሚዛኑ ያጣል ። ታዲያ በምን አኳኋን እናዘጋ ጀው ይላሉ?” ብለው ራስ መንገሻ መልሰው ጠየቋቸው ።

“እንደኔ እንደኔማ ራስ ወልደሚካኤልን ከነልጆቻቸው ፈትተን ወደ ሐማሴን ብንሰዳቸውና ባሻምባራስ ክፍለ የሱስም እርሳቸው ተላልከው ቢያስጠጉት ፣ ጣሊያኖችን መቋቋምና አገሩን ለማረጋጋት ይመቻል ይመስለኛል” አሉ ራስ አሉላ ።

“እሺ” ብለው ራስ መንገሻ ለጥቂት ጊዜ ሲያስቡ ቆዩና ፣

“እንጃ እሺ ይሉን ይሆን? ዐሥር ዓመት ሙሉ ከነልጆቻቸ እስረን ካሳዘናቸው በኋላ ፣ ዛሬ እንደገና ሐማሴን ሐደው አገር ይጠብቁ ብንል ደስ ይላል? እርሳቸውስ ያምኑናል?” አሉ ራስ መንገሻ ።

“አቡኑና ሽማግሌዎች ከለመኗቸው ይቅር ይላሉ ። ለልጆ ቻቸው ለመስፍንም አንድ አገር እንሰጣቸዋለን ። ከልብ ለመታረቃችን ምስክራችን እንዲሆን ፣ የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ሚስት የነበረች ውን ልጅን እንሰጣቸዋለን” አሉ ራስ አሉላ በራት ከሰው ያሳሉ



ንቸውን እያወጉት ከልባቸው ለመታረቅ መመኘታቸውን ለራስ መንገሻ ሲያስረዱ ።

“የሚሆን ከሆነ ምን ከፋኝ ፣ እንዳሉት ተሳውሱት ወደ አምባው ይላኩና ያነጋግሩዋቸው” አሉና ራስ መንገሻ በጉዳዩ መስማማታቸውን አስረዱ ።

የተመረጡ የሃይማኖት አባቶች በተገኙበት ሽማግሌው ራስ ወልደ ሚካኤልና ሁለቱ ልጆቻቸው መስፍንና ኃይለ መለ ኮት ከአምባ ሰላም ወርደው ይቅርታ ተጠየቁ ።

“ከእንግዲህ ወዲያ የሚቀረኝን ዕድሜ የማፍ ፍርድ በተቀበል ኩበትና እስክዛሬ በቅናና ከኖርኩበት ተራራ ወርጄ የምሠራው አንድም ነገር አይኖረኝም ። በኖርኩበት እንድኖር ከተፈቀደልኝ እንደ ትልቅ ምሕረትና ቸሮት እቆጥረዋለሁ” ብለው ራስ ወልደ ሚካኤል ቁርጥ ያለ ሐሳባቸውን አስታወቁና ወደ ተራራቸው ተመልሰው ወጡ ።

ልጆቻቸው መስፍን ግን በነገሩ መስማማታቸውን ገለጹ ። ይሁን እንጂ አባታቸው የፈጸሙባቸውን ጥቃትና በደል ከልባቸው ይቅር ለማለት ደግሞ የቀረው አልነበረም ። ቢሆንም ነገሩ ወደ ተግባር ለቀበ እንዲያመሩላቸው ሲሉ በራስ አሉላ ሐሳብ ተስማምተው ባሻምባራስ ክፍለ የሱስ ከኢጣሊያኖች ከድተው ወደ እርሳቸው እንዲመጡ ለማድረግ ደብዳቤ ላኩላቸው ። ጣሊያኖች ደግሞ በበኩላቸው ፤ እርስ በርሱ የተጣመመደው የኢትዮጵያ መኳንንት እንዲከተከት ብለው እስቲመደቅቁዋቸው ድረስ እርምጃቸውን እየቆጠቡ ከግዛቱ የተሻለ አጋጣሚ እንደሚሉ በመረጃታቸው ፣ ትኩረው ሁሉ በምሥራቅ መሣሪያ ማቀባላቸውን ዋና ተግባር አድርገው ይዘውት ነበርና ፣ በሐማሴንና በትግራይ በገንዘብ የተገዙ ሰላዮቻቸውን አመግርተው ማንኛው ንም ነገር ማስለቀም ጀመሩ ። የመስፍን ወ/ሚካኤልን ደብዳቤ ከተመለከቱ በኋላ ክፍለ ኢየሱስም ከኢጣሊያኖች ከድተው ወደ ትግራይ ለመግባት ፈቃደኛ መሆናቸውን አረጋገጡ ።

ባሻምባራስ ክፍለ የሱስ ፣ በመጀመሪያ ከረንን ይዘው የሚሊ ያንን ባንዲራ ሰቅለዋል ። ተቀባውም አሥመራን ይዘው ለሚሊ

ያን አስረክበዋል ። ይሁንና የኢጣሊያኖች ሁኔታ ደግሞ በጣም አጠራጥሩዋቸዋል ። በዚህ ሁኔታ ላይ ባሉበት ወቅት ደግሞ በድብልቅ መንፈሳቸውን የሚያስቆጣባቸው ጉዳይ ደረሰ ።

ከንቲባ ማሕሙድ የተባሉ የሐባብ ተወላጅ ከኢጣሊያኖች የተቀበሉትን አምስት መቶ ጠመንጃ አስይዘው ፣ "ሀገሬን አልወጋም" ብለው በቃሮራ በኩል ወደ ሱዳን መግባታቸውን ሰሙ ። ቀጥሎም ዓድ መድ ሼክ እኩድ ዓድ በሒት የኢጣሊያ ወታደሮች ወደ አሥመራ መግባታቸውን በመቃወማቸው ተይዘው አሥመራ ላይ መረሸናቸውን ተመለከቱ ። ሌሎች በርካታ የምፅዋ ፣ የከረን ፣ የሐማሴን ተወላጆች ኢጣሊያንን በመቃወም እየተያዙ በመረሸናቸው መደናገጥና ማሰላሰል ጀመሩ ።

ከዚያ ሌላ ደግሞ ፣ የማሕዲስቶች እንቅስቃሴ በምዕራባዊ ቆላ በኩል እየገፋ መምጣቱ አጅግ አሳስቧቸዋል ። ከኢጣሊያኖች ጋር አባሪ ተባባሪ ባይሆኑና ከረንና አሥመራን እየያዙ ባያስረክቡ ኑሮ ከማሕዲስቶቹ ጋር ለመስማማት ባልተቸገሩም ነበር ። የኢጣሊያኖች ታማኝ በመሆናቸው በማሕዲስቶች በኩል በጠላትነት መመዝገባቸውን አረጋግጠዋል ። ጣሊያኖችንም መጠራጠር ጀምረዋል ። ስለዚህ በመስፍን ወ/ሚካኤል አማካይነት ከራስ አሉላ ጋር መታረቅ እንደሚፈልጉ መልእክት በማስተላለፋቸው ራስ አሉላም የጦር አበጋዛቸውና ታማኛቸው የነበሩትን የብላታ ገብሩን ልጅ ዓለማየሁ ገብሩን በርከት ካሉ ወታደሮች ጋር ስደዱላቸው ። ባላምባራስ ክፍለ የሱስም በዚያ ወቅት ከሁለት ሺህ በላይ የሚሆን ተከታይና ስድስት መቶ ባለብረት ወታደር ነበራቸውና ከራስ አሉላ የተላከላቸው ወታደር ሲደመር ደግሞ ፣ አበጥ ጠንከር ያለ ጡንቻ እንደሚኖራቸውና ከጠላቶቻቸው አንዱን ጠንከር ያለ ክንድ ለማቅመስ እንደሚችሉ ተማመኑበት ።

ራስ መንገሻና ራስ አሉላ ፣ በትግራይና በመረብ ምላሽ የነበረውን መበጣበጥና ቀክክር አስወግደው የአገሪቱን አንድነት ለማጠናከር በሚጣጣሩበት ሰዓት ጠቅላላውን ሁናቴ ጣሊያኖች ስለ ደረሱበት፣ በርከት ያለ ጦር ይዘው ከአሥመራ ገሥግሠው ከረን ገቡና ባላምባራስ ክፍለየሱስን አዘንግተው ያዙዋቸው ። ከዚያም ወደ አሰብ ሰደዱዋቸውና በእስር ቤት እንደ ተዘጋባቸው ሞቱ ።



የባላምባራስ ክፍለ የሱስ መያዝ ከመረብ ወዲያ ማዶ የነበረውን ውስብስብ እያደር እንደ ሚያበሳጨውና ራስ መንገሻን ለማንገሥም የነበራቸውን ምኞት እንደሚያከስምባቸው የተገነዘቡት አሉላ ፣ በዚያን ጊዜ በራስ መንገሻ ዙሪያ ከነበሩት ከራስ ሐጐስ ፣ ከደጃዝማች ተድላ ፣ ከደጃዝማች ተሰማና ከሻቃ አርአያ ጋር ስለ ሁኔታው ሲመካከሩ ፣

"ዋናው ጥሪቴና ሐሳቤ ከመረብ ማዶ ያለውን አገራችንን እንደ ምን አድርገን ማረጋጋትና የገባውንም ጠላት በምን ሁኔታ ማስወጣት እንደሚገባን የታያችሁን እንድንነጋገርበት ነው" ብለው ራስ አሉላ ሐሳብ ጠየቁ ።

ራስ ሐጐስም ቀበል አደረጉና ፣ "ለመሆኑ የሁላችንስ ጦር ተዳምሮ ምን ያህል ቢሆን ነው ወደ መረብ ማዶ እንሻገር የምትለው?" ብለው ተናገሩ ።

"ከተንቀሳቀሱ ተከታይ አይገድምና ያለውን አስከትቶ መሻገሩ ይሻል ይመስለኛል" አሉ ሻቃ አርአያም ።

"ለሰው የሚሆን ቀርቶ ለእንስሳ እንኳን የሚሆን ምግብ በጠፋበት ወቅት ወደ ሐማሴን እንሻገር ማለት አወዳደቅን አለማሳመር ሆኖ ይታያኛል" አሉ ደጃዝማች ተሰማም ።

"ዋናው ችግራችን ጣሊያን ሳይሆን ድርቁና የከብት እልቂቱ ነው ። እንደምታውቁት ጣሊያኖች ምጥዋ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ የከብት በሽታም ከእነርሱ ጋር አብሮ ገብቶ ያን ሁሉ ጥፋት አድርሶብናል ። በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ረኃቡም እየጠናከረ እንዳሳሰባችሁትም ያለውን ሠራዊት አስቀጥረን ስንቁ እንዲዘጋጅ ካደረግን በኋላ እንነጋገርበታለን" ብለው ጉዳዩን ወሰኑት ። በዚያ ወቅት በራስ መንገሻ ዙሪያ የነበሩት መኳንንት የጦር አለቆችና የሁሉቱ ራሶች ማለት የራስ መንገሻና የራስ አሉላ ጦር ተደማምሮ ዐሥር ሺህ እንኳ የማይሞላ ነበር ። የቀረው በስንቅ እጥረት ተበታትኗል ። በዚህም የተነሣ ከመረብ ማዶ ተሻግሮ ለመዝመትና ከኢጣሊያ ጋር ለመዋጋት አሉላ የነበራቸውን ምኞት በልባቸው እንዳመቁ መቆየት ግዴታ ሆነ

ባቸው ። በመጨረሻም አክሱም የነበረውን የንጉሠ ነገሥቱን ግምጃ ቤት ከፍተው መሣሪያና ጥይቱን ለወታደሮቻቸው አከፋፍለው ፣

"ጊዜው ፈቅዶልን እንደገና እስክንሰባሰብ ድረስ መረብ ማዶ ተሻግራችሁ በጠላት ላይ አደጋ እየጣላችሁ ወንዝ የወለደውን ወንበዴ ሕዝቡን እንዳያስጨንቀው እየተከላከላችሁ እናንተም ወንዝ ጠባቂዎች ሁናችሁ ቆዩ" እያሉ ፈቀዱላቸው ።

ከዚያ በኋላ የዮሐንስ ክንድ አስተባብሩዋትና አጠናክሩዋት የነበረችው ትግራይ እየፈራረሰች መሔድ ጀመረች ። ከራስ አሉላ ሠፈርም ሻቃ አርአያና የራስ አሉላ ወንድም ደጃዝማች ተሰማ ተራ በተራ አሉላን እየከዱ ሔዱ ። ራስ አሉላ ከሁሉም ከሁሉም የታማኛቸው የሻቃ አርአያ ክዳት እጅግ አበሳጫቸው ። ሻቃ አርአያ ከአሉላ ከድተው ለፊታውራሪ ደበበ ግደራቸውን ሲሰሙ ደግሞ ይብልጡኑ አዘኑ ። ከዚያ አከታትሎ ደግሞ የአክሱም ገዥ የነበሩት የንቡረዕድ ወልደጊዮርጊስ ሁለት ልጆቻቸው ወደ ሁለት መቶ የሚጠጉ ወታደሮች ይዘው በመክዳታቸው ራስ አሉላ ከብስጭት ወደ ብስጭት የሚሸጋገሩ ሆኑ ። ድርቁና ረኃቡ እየረረታ በመሔዱም አሉላ ሁለት መቶ የሚሆኑ ወታደሮቻቸውን እንኳ መመገብ የተቸገሩበት ወቅት ሆነ ። የአጼ ዮሐንስም ትልቁ ችግራቸው ይኸው ነበር ። ጣሊያኖች ምፅዋ ሲገቡ በመርከብ ጭነው ያመጧቸው ፈረሶችና በቅሎዎች በበሽታ የተመረዙ ስለ ነበሩ በሽታው እየተባለሰ ብዙ የቤት እንስሳት ጨርሶ ነበር ። በተለይም ከዶግአሊ ጦርነት በኋላ የራስ አሉላ ወታደሮች ከጣሊያኖች ላይ የማረኩዋቸውን በቅሎዎች ወደ ደጋው ይዘው ስለወጡ በሽታው እየተባለሰ በሀገሪቱ ላይ ከፍተኛ እልቂት አድርሶ ነበር ። ከዚያ አከታትሎ ደግሞ ረኃቡ ሕዝብ ፈጀ ። ዮሐንስና አሉላም ወራሪዎችን የተቋቋሙት ከዚያ አስከፊ ሁኔታ ጋር እየተናነቁ ነበር ።



# ምኒልክና ጣሊያኖች

## ትግራይና ሁለቱ ራሶች

የአጼ ዮሐንስ መኳንንቶች አለመስማማታቸውን ንጉሥ ምኒልክ ከሰሙ በኋላ ፣ ራስ መንገሻን እንበለ ኃይል ማስቀረትና የራሳቸውን ጉልበት ማጠንከር እንደሚኖርባቸው ተማመኑ። ለዚህ የሚረዳቸው የጦር መሣሪያ ማስገባት ጀመሩ ።

ከኢጣሊያኖችም ጋር ውጫሌ ላይ ባደረጉት ውል በትግራይ ውስጥ ለነበሩትም ተቀናቃኞቻቸው ምንም ዐይነት እርዳታ እንዳይደረግ ፣ በምፅዋ በኩል ምንም ዐይነት የጦር መሣሪያ እንዳይገባላቸው አድርገው ፣ የእርሳቸውንም ንጉሠ ነገሥትነት በይፋ እንዲያውቅላቸው ምኒልክ ለጣሊያን ንጉሥ ኡምቤርቶ መልእክት ሰደዱ ።

ከዚያ ቀጥለው ደግሞ ራስ ሚካኤልና ንጉሥ ተክለሃይማኖት ከገቡላቸው በኋላ ፣ የኃይላቸውን መሰባሰብና መጠናከር አረጋገጡና ፣ ደጃዝማች ሥዩምን የትግራይ ገዥ አድርገው ሹመው በቂ ጦር ሰጥተው ሰደዱዋቸው ። የደጃዝማች ሥዩም ሠራዊት ብዛትና ጥንካሬ ከራስ መንገሻና ከራስ አሉላ እጅግ የተለየና የዳበረም ነበር ። በመተማ ጦርነት የተጐዳው ከዚያም የተረፈውን በሥልጣን ሹኩቻ የተከፋፈለውንና በረኃብ የተፈታውን የአጼ ዮሐንስን ሠራዊት የከዳው ከድቶ የተረፈውና በሁለቱ

ባቸው ። በመጨረሻም አክሱም የነበረውን የንጉሠ ነገሥቱን ግምጃ ቤት ከፍተው መሣሪያና ጥይቱን ለወታደሮቻቸው አከፋፍለው ።

“ጊዜው ፈቅዶልን እንደገና እስክንሰባሰብ ድረስ መረብ ግዶ ተሻግራችሁ በጠላት ላይ አደጋ እየጣላችሁ ወንዝ የወለደውን ወንበዴ ሕዝቡን እንዳያስጨንቀው እየተከላከላችሁ እናንተም ወንዝ ጠባቂዎች ሁናችሁ ቆዩ” እያሉ ፈቀዱላቸው ።

ከዚያ በኋላ የዮሐንስ ክንድ አስተባብሩዋትና አጠናክሩዋት የነበረችው ትግራይ እየፈራረሰች መሔድ ጀመረች ። ከራስ አሉላ ወፈርም ሻቃ አርአያና የራስ አሉላ ወንድም ደጃዝማች ተሰማ ተራ በተራ አሉላን እየከዱ ሔዱ ። ራስ አሉላ ከሁሉም ከሁሉም የታመኗቸው የሻቃ አርአያ ከዳት እጅግ አበሳጫቸው ። ሻቃ አርአያ ከአሉላ ከድተው ለፊታውራሪ ደበበ ማደራቸውን ሲሰሙ ደግሞ ይበልጡኑ አዘኑ ። ከዚያ አከታትሎ ደግሞ የአክሱም ገዥ የነበሩት የንቡረዕድ ወልደጊዮርጊስ ሁለት ልጆቻቸው ወደ ሁለት መቶ የሚጠጉ ወታደሮች ይዘው በመክዳታቸው ራስ አሉላ ከብስጭት ወደ ብስጭት የሚሸጋገሩ ሆኑ ። ድርቁና ረኃቡ እየረረታ በመሔዱም አሉላ ሁለት መቶ የሚሆኑ ወታደሮቻቸውን እንኳ መመገብ የተቸገሩበት ወቅት ሆነ ። የአጼ ዮሐንስም ትልቁ ችግራቸው ይኸው ነበር ። ጣሊያኖች ምፅዋ ሲገቡ በመርከብ ጭነው ያመጡቸው ፈረሶችና በቅሎዎች በበሽታ የተመረዙ ስለ ነበሩ በሽታው እየተባባሰ ብዙ የቤት እንስሳት ጨርሶ ነበር ። በተለይም ከዶጋሊ ጦርነት በኋላ የራስ አሉላ ወታደሮች ከጣሊያኖች ላይ የማረኩዋቸውን በቅሎዎች ወደ ደጋው ይዘው ስለወጡ በሽታው እየተባባሰ በሀገሪቱ ላይ ከፍተኛ እልቂት አድርሶ ነበር ። ከዚያ አከታትሎ ደግሞ ረኃቡ ሕዝብ ፈጀ ። ዮሐንስና አሉላም ወራሪዎችን የተቋቋሙት ከዚያ አስከፊ ሁኔታ ጋር እየተናነቁ ነበር ።



# ምኒልክና ጣሊያኖች

## ትግራይና ሁለቱ ራሶች

የአጼ ዮሐንስ መኳንንቶች አለመስማማታቸውን ንጉሥ ምኒልክ ከሰሙ በኋላ ፣ ራስ መንገሻን እንበለ ኃይል ማስቆረትና የራሳቸውን ጉልበት ማጠንከር እንደሚኖርባቸው ተማመኑ ። ለዚሁ የሚረዳቸው የጦር መሣሪያ ማስገባት ጀመሩ ።

ከኢጣሊያኖችም ጋር ውጫሌ ላይ ባደረጉት ውል በትግራይ ውስጥ ለነበሩትም ተቀናቃኞቻቸው ምንም ዐይነት እርዳታ እንዳይደረግ ፣ በምፅዋ በኩል ምንም ዐይነት የጦር መሣሪያ እንዳይገባላቸው አድርገው ፣ የእርሳቸውንም ንጉሠ ነገሥትነት በይፋ እንዲያውቅላቸው ምኒልክ ለጣሊያን ንጉሥ ኡምቤርቶ መልእክት ሰደዱ ።

ከዚያ ቀጥለው ደግሞ ራስ ሚካኤልና ንጉሥ ተክለሃይማኖት ከገቡላቸው በኋላ ፣ የኃይላቸውን መሰባሰብና መጠናከር አረጋገጡና ፣ ደጃዝማች ሥዩምን የትግራይ ገዥ አድርገው ሹመው በቂ ጦር ሰጥተው ሰደዱዋቸው ። የደጃዝማች ሥዩም ሠራዊት ብዛትና ጥንካሬ ከራስ መንገሻና ከራስ አሉላ እጅግ የተለየና የዳበረም ነበር ። በመተማ ጦርነት የተጐዳው ከዚያም የተረፈውን በሥልጣን ሹኩቻ የተከፋፈለውንና በረኃብ የተፈታውን የአጼ ዮሐንስን ሠራዊት የከዳው ከድቶ የተረፈውና በሁለቱ

ራሶች ዙሪያ የተከማቸው ፣ በሰሜን በኩል ፤ ጣሊያኖችና አባሪያቸው ሆነው የተሰለፉት ደበበ አርአያ ፣ በደቡብ በኩል ደግሞ አዲሶቹ ጉልበተኞች ምኒልክና ሥዩም ቀስረው ያዙት ። ጉልበቱ ያልተነካ ምርጥ መሣሪያ የታጠቀ በንቁ ያላለቀ ሠራዊት የሚመሩት ደጃዝማች ሥዩም ተቀናቃኞቻቸው የነበሩትን ዋግ ሥዩም ብሩን ለመያዝ ዋግ ሲገቡ ፣ ዋግሥዩሙም ከሰቆጣ ገሥግሠው አካለጉዛይ ገቡና ሰገነይቲ ከነበሩት ከደበበ ጋር ተቀላቀሉ ። ደጃዝማች ሥዩምም ጉዞአቸውን ቀጥለው እንደርታ ገቡ ።

አጼ ዮሐንስ ፣ ከንጉሥ ምኒልክ ጋር የነበራቸውን ትኩር ጥምድ ለመፍታት ሲሉ ልጃቸው ራስ አርአያ ሥላሴን ከወይ/ዘውዲቱ ጋር ካጋቡ በኋላ ፣ እንደርታን መተዳደሪያ ጉልት እንዲሆናቸው ለሙሽሮቹ ሰጥተው ነበር ። በዚህም የተነሣ እንደርታ ከሌሎቹ ከትግራይ አውራጃዎች ሰፋ ብላ ተደልድላ ነበረች ። የምኒልክ ሹም የሆኑት ደጃዝማች ሥዩም እንደርታ ሲገቡም የወይዘሮ ዘውዲቱ ወዳጆች የነበሩና የምኒልክንም ንጉሠ ነገሥትነት እምነው የተቀበሉ ሁሉ በደስታ ተቀበሉዋቸው ።

የሥዩምን ጉልበት ፣ የሥዩምን ሹመት ፣ የሥዩምን ግፊት ፣ የሥዩንም ድፍረት ግን አሉላና መንገሻ ሊቀበሉት የማይቻሉት ሆነ ። በሁለት ግንባሮች የተወጠሩት ሁለቱ ራሶች ቤታቸው ፣ ቤተመንግሥታቸውና የዘውድ ባለቤትነቱ ተስፋቸው ተራ በተራ እየተናደ መሔዱን በትክክል ቢረዱትም ፣ የነበሩዋቸውን ጥቂቶች ወታደሮች እንኳ እንዳይሔዱባቸው ሲሉ መላውን ትግራይን ማሰስ ዋናው የየዕለቱ ተግባራቸው ነበር ። የደጃዝማች ሥዩምን ጦር ከሠፈራቸው እስቲደርስ መጠበቁ የሚያስከትለውን ውርደት ተገንዝበውት ነበርና በጉዞ ላይ እንዳሉ ለመግጠም ሲሉ ከዐድዋ ገሥግሠው መቀሌን ዐልፈው ጠበቁት ።

በተራቸውና በዘመናቸው የምኒልክ ብርቱ ዱላ ለመሆን “ጠብ ያለሽ በዳቦ” ሲሉ የነበሩት አፍለኛው ጉልበተኛ ፣ ደጃዝማች ሥዩም “ምንም ብቀጥን ጠጅ ነኝ” የሚባለው ዘይቤትዝ አላቸውና አጼ ተክለ ጊዮርጊስን የማረከው የአሉላ ክንድትዝ አላቸውና ግብጾችን ጉራእ ላይ ፣ ጉንዲት ላይ ፣ አይለት ላይ ድርቡሾችን ኩፊት ላይ ከነዚህም ላቅ ያለውን የነጩን ጦር



ተድዓሊ ላይ የለሸለሸው የአሉላ ጉራዴ ፣ ከፊታቸው ድቅን ድንቅ እያለ እያንቦገቦገ ታያቸውና እንደ ዋግ ሥዩም ብሩ በጠፍ ጨረቃ የማይፈተለከላቸው መሆኑን አመኑበትና ወደ አሸንጌ ተመለሱ ።

ሁለቱ ራሶችም ምናልባት ሌላ ጊዜ በድንገት ይመለስ ይሆናል ወይም ሌላ የምኒልክ ጦር ይመጣ ይሆናል በሚል ሥጋት መቀሌንና ዐድዋን ለመከላከል የሚያስችላቸውን አቅጣጫ ይዘው ሠፈሩ ።

ሁለቱ ራሶች የሠራዊታቸውን መበታተን ለመከላከል የነበራቸው አማራጭ ከተረፉዋቸው የጦር አለቆች መካከል ዋና ዋናዎቹን ሹመት እየሰጡ ማባባል ነበር ። በዚህም መሠረት ደጃዝማች እምባዬ የተባሉትን የደጃዝማች ደበበን አጐት የዐድዋ ገዥ አድርገው ሾሙ ። ደጃች እምባዬ ቀደም ካለው ጊዜ ጀምረው የሁለቱም ራሶች ተፎካካሪ ቢሆኑም ፣ ጨርሰው እንዳይኮበልሉና ተጨማሪ ችግር እንዳያስከትሉ ሲባል በሥልጣን ማባበሉ ጊዜው ያመጣባቸው ውሳኔ መሆኑን ሁለቱ ራሶች አመኑበት ።

ደጃች እምባዬ ደግሞ ፣ ቂማቸውን ለመወጣት ቀን ሲጠባበቁ ኑረው መብረክረክ ሲጀምር አጐታቸው ደበበ መቀሌን እንዲይዙ ላኩባቸው ። ደበበም በምሥጢር ከሰገነይቲ ገሥግሠው እንትጮ ገብተው ከአጐታቸው ጋር በምሥጢር ተገናኙ ። ወዲያውም የደበበ አሽከሮች የዐድዋን ከተማ ያዙና የራስ አሉላ ሹመኛ ሆነው ቀረጥ ሲሰበስቡ የነበሩትን ባሻይ ገብረዝጊን ከከተማ መካከል ገደሉዋቸው ።

ይህ ሁሉ ድፍረትና ማንአለብኝነት ሲደረግ ፣ ራስ መንገሻ አንድ ሺህ ያህል ወታደሮቻቸውን ይዘው አቢይ አዲ ላይ ራስ አሉላ ደግሞ አምስት መቶ የሚሆኑ ወታደሮች ይዘው ከተወለዱባት ዝቁሊ ከምትባለው መንደር ነበሩ ።

የደበበ ግፊት ዐድዋ ላይ ብቻ አልተገታም ፤ ወደ ተንቤን ገሥግሠውና በራስ ሐጐስ ወታደሮች ላይ አደጋ ጥለው በርከት ያሉትን ገድለው ወደ ሽሬ ተጓዙ ። በዚህም ጊዜ ራስ መንገሻና ራስ አሉላ ተላልከው መቀሌ እንዳትያዝ ለመከላከል ከየነበሩበት

ሔዱ ። የሁለቱን ራሶች ጉዞ የተረዱት ደበበ ደግሞ ወደ ራስ አሉላ መንደር ገቡና ዝቅሊን እታግለውና ዘርፈው እንዲልክበ ረች አደረጉዋት ።

በተለይም አሉላ የተወለዱባትን ጉጀ ራሳቸው ነበሩ ያቃ ጠሉዋት ። እንደዚያ አድርገው አሉላን ከተበቀሉ በኋላ መቀሌን ለመያዝ ደግሞ ዝግጅት ጀመሩ ። ሁኔታውም ለሁለቱ ራሶች ከባድ ችግር የሚያስከትልባቸው ሆነ ። በዚህም ጊዜ ነበር አሉላ ደበበን በወጥመዳቸው ለማስገባት ገመድ መሸረብ የጀመሩት ። የእርሳቸውን ዘዴ ደግሞ ራስ መንገሻ ስለተቃወሙት በመካከ ላቸው የሐሳብ ግጭት ተነሣ ።

በደበበ ምክንያት ሁለቱ ራሶች የመጣላቸው ዜና ምፅዋ ሲሰማ በጣሊያኖች ዘንድ ታላቅ ደስታ ፈጠረ ። ወዲያውም የቅርብ ጉልበተኞች እርስ—በርሳቸው ተጋጥመው እንክትክት ብለው የሚወድቁበትና አገሩ ባዶ የሚሆንበት ቀን በተስፋ ይጠብቅ ጀመር ። ደበበ ደግሞ በበኩላቸው ፣ የሁለቱን ራሶች ግጭት በመስማታቸው ወደ መንገሻ ለመቅረብ ወይም መንገሻን ከአሉላ ጉያ ነጥሎ ለመውሰድ የሚችሉበት አጋጣሚ መድረሱን በመገንዘብ ለራስ መንገሻ "ከእርስዎ ጋር ለዋጋ አልፈልግም፤ ከተዋጋን ደግሞ በእርስዎ ላይ ብርቱ ጉዳት ይደርሳልና የምን ስማማበትን ብልሃቱን አስበው ይላኩብኝ" ብለው ላኩባቸው ። መንገሻም መልስ ሲሰጡ ፣ "የአጼ ዮሐንስን ግዛት ለሁለት ተካ ፍለን ብንገዛ ደስ ይለኛል" አሉዋቸው ። አዲሱ ጉልበተኛ ደበበ ግን የሚሉዋቸን ትግሬን ሳይሆን መላውን የዮሐንስን ግዛት ለመ ያዝ የሚገታቸው ምንም ኃይል እንደሌለ በመተማመን ፣ "ሁሉም ለማን ሊሆን ነው፤ የሚሉዋቸን ትግሬይን የተመኘሁ ልኝ" ብለው እንዲያውም 'አንተ' ብለው ላኩባቸው ። በዚህ ጊዜ መንገሻም አሉላ ባወጡት ወጥመድ ተስማሙና ደበበን የሚያ ንቁበትን ዘዴ አብረው ቀየሱና ለአዲሱ ጉልበተኛ የአጼ ዮሐ ንስን የፈረስ የወግና የማዕረግ ልቃ ሲልኩላቸው ፣ ደበበም ደስ ብሏቸው "ደም ከምንፋሰስ እንደዚህ አድርገህ አቅምህን አው ቀህ ስለ ተቀበልከኝ እኔም ተደስቻለሁ" ብለው ላኩባቸውና መቀሌ ገቡ ። ሦስት ቀን ሙሉም ፈንጠዝያ ሆነ ። ደበበ የንጉ



ሥነት የማዕረግ ልብስ ለበሱ ። መንገሻም የመላዋ ኢትዮጵያ ንጉሥ ነገሥት እንዲባሉ አሉላውን እንደሚልኩላቸው አረጋገጡ። ከዚያ በኋላ ደበበ ወደ አጼ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት እንዲገቡና ሥርዓተ ንግሡ እስቲፈጸም ድረስ በዚያ እንዲቀመጡ መንገሻ ለመኑዋቸው ። ወሬው መቀሌን ዐልፎ በመላዋ ትግራይ ተዳረሰ ። በአጼ ዮሐንስ ኑዛዜ መሠረት መንገሻን ባለማንገሣቸው ሕዝቡ አሉላን ነቀፈ ። ደበበም በታላቅ አጀብና ኩራት ወደ ቤተ መንግሥቱ ገቡ ። ከኋላቸውም ታማኝ ታማኝ አሽከሮቻቸው ተከ ትለዋል ። ከቤተ መንግሥቱ ገብተው ከአጼ ዮሐንስ ወንበር ላይ ሊቀመጡ ሲያጎበድዱ ፣

"ወንዱ አሉላ የዮሐንስ ቀኝ እጁ" አሉና ተወርውረው የደበ በን እጅ ያዙ ። እንደ እርሳቸው በቤተ መንግሥቱ ውስጥ አድፍ ጠው የነበሩት አሽከሮቻቸውም እየዘለሉ የደበበን አሽከሮች እየፈ ጠረቁ እግር ከወርች እያሰሩ ወደ እምባ ሰላማ ተራራ ለደጋፊዎቻቸው።

ከዚያ በኋላ በምድረ ትግራይ ታላቅ የሐሳብ መከፋፈል ሆነ ። የመኳንንቱ ዘር አሉላን ሲረግም ሕዝቡ መመረቅ ጀመረ፡ 'በሬት ራስ ወልደ ሚካኤልን አስይዞ አሳሰረ ። ዛሬ ደግሞ ደበ በን ደገመ ። ይኸ የደም የገበሬ ልጅ ትግሬይን በጠበጠ። እርሱን የሚይዝ ክንድ እንዴት ከመላዋ ትግራይ ይጠፋል?' እያሉ መኳ ንንቱና ዘር-ማንዘራቸው ሲረግም ፤ ሕዝቡ ደግሞ ፣ 'አሉላ ታማኝ ነው፤ የዮሐንስን ቃል ጠብቆ አልጋውን ለባለአጋ ሰጠ ። እንዴት በዮሐንስ ወንበር ደበበ ይቀመጣል፤ ደበበ ወንጀለኛ ነው እነሩንና ንጉሡ ነገሥቱን ሲበድል የኖረ ነው ። የሥራውን ዋጋ ነው ያገኘው' እያለ በየቤቱ በየሕሊናው ፈረደ ። እርግጥ ነው በአሉላ ላይ ብርቱ ተቃዋሚዎች ለማነሣሣት ምክንያት ሆኗል። በተለይም የአጼ ዮሐንስ እኅት ወይዘሮ ድንቅነሽ የሚባሉት የደጃች ሥዩም እናት የደበበ አክስት ፣

'እነዚህ ተንቤኖች እንዴት ይዋሻሉ?
አልጋው ለደበበ ይሰጠው እያሉ
"ወዲ-ቂቤን" ካልጋ ላይ አስቀምጠው
ደበበን ጌዶሉ እጅና እግሩን አሰረው"

ብለው ያሰሙዋት እንጉርጉሮ በእሉላ ላይ ከፍተኛ ተቃውሞ ለማስነሣት መኳንንቱን ረድቶ ነበር። ሕዝቡ ደግሞ ይህን ሲሰማ፤

"እንደ ዲያብሎስ ጌታውን የወጋ
አይበሉህ እሉላ አባነጋ
የማይለወጠው ለዓለመ—ሥጋ
አሳልፎ ሰጠ አልጋን ለባለአልጋ"

ብሎ ገጠመና በየሠርጉና በየድግሱ ቤት መዝፈን ጀመረ።

ራስ አሉላ ደበበን ከነወንድማቸውና ከነተከታዮቻቸው ይዘው ካሰሩ በኋላ፣ ራስ መንገሻ መቀሌ ላይ ሆነው ደጃዝማች ሥዩምን እንዲከላከሉ አድርገው እርሳቸው ወደ ሰሜን አመሩና ኩአቲት ሠፈሩ። ወደዚያ የገሠገሡትም ደበበ ከየነጋዴውና ከሕዝቡ እየዘረፉ ሲያከማቹት የኖሩትን ሀብት ለመውረስ ነበር። ግን ሰገነይቲ ከመድረሳቸው በፊት በጀኔራል ባልዴሴራ እዝ ሥር የነበረው የጣሊያን ጦር ከከረን ገሥግሦ ሌሊት አሥመራን ያለ ምንም ተቃዋሚ ያዘ። ጀኔራል ባልዲሴራም ተከታትሎ ደረሰና ከራስ አሉላ ቤት ገባ። ከአሥመራ ነዋሪም ቀጥሎ ያለው እንጉርጉሮ ተሰማ።

"ሰማሽ ወይ ሐማሴን፣ ሰማሽ ወይ አሥመራ
ያምርባችሁ ነበር ከአባ ነጋ ጋራ
ትላንት ቢለያችሁ አሉላ አባ ነጋ
አረመኔው ገባ በሌሊት ሳይነጋ።"

ይህን መርዶ ራስ አሉላ እንደ ሰሙ እጅግ አዘኑ፤ ተከዙ። በዚያ ወቅት የነበራቸው የወታደር ብዛት ከአንድ ሺህ የማይበልጥ ሲሆን፣ ከዚያውም ላይ ደግሞ ባለጠመንጃው ሰምንት መቶ እንኳ የማይሞላ ነበር። በዚህ ጊዜ የነበራቸው ምርጫ በጣም ጠባብ ሆነባቸው። ከጣሊያን ጋር ለመዋጋት ባይችሉም ራስ መንገሻን እንግሠው፣ ጣሊያንንና ምኒልክን ለመቋቋም መሞከር አንደኛው ምርጫቸው መሆኑን አመኑበት።

ጀኔራል ባልዲሴራ አሥመራን እንደያዘ ከራስ አሉላ ቤት ገብቶ ራስ አሉላ በሰላይነቱ ይዘው አስረውት የነበረውንና የጥቁር ጥላቻ ከደም ሥሩ ጋር ተዋህዶት የነበረውን ሻለቃ ፒያ



ኖን የኰሎኔልነት ማዕረግ ሰጥቶ የሐማሴን ም/አገረ ገዥ አድርጐ ሾመው። ራስ አሉላ ይህን ነገር ሲሰሙ ደግሞ ከመርዶ ሁሉ የከፋ መርዶ ሆነባቸው። ከዚህ በኋላ ነበር አሉላ ኢጣሊያኖችን ለማዘናጋት ልዩ ልዩ ዘዴ መቀየስ የጀመሩት። ዋናው ምኞታቸው የአደራ ልጃቸውን ራስ መንገሻን ለማንገሥ ቢሆንም የኢጣሊያኖች ርምጃ በሐማሴን ግዛታቸው ወይም ከመረብ ወንዝ ባሻገር ብቻ እንደማይገታና ትግራይን ለመያዝ እንደማያመነታ ተረዱት። ስለዚህ ያን የመረረ ጠላታቸውን ሲሆን ከሀገራቸው ጠራርገው ለማስወጣት፣ ካልሆነም በደረሰበት ለመግታትና የመረብ ምላሽን ሕዝብ በቂም በበቀል እንዳያስቃይባቸው ለማስታገሥ የጦር መሣሪያም ሊያገኙ የሚችሉበትን መንገድ ለመጥረግ ሲሉ ከጣሊያኖች ጋር ጊዜያዊ እርቅና ሰላም ለማሳየት የ ፈለጉ መሆኑን በመግንዘብ ለኰሎኔል ፒያኖ በጻፉት ደብዳቤ ላይ፣

"ከጥቂት ጊዜ በፊት እኔና ጌታዬ ራስ መንገሻ አንድ ደብዳቤ ልከንላችሁ ነበር። ከእንግዲህ ወዲያም ቢሆን የጥንቱ ጠላትነት ተረስቶ አዲስ ወዳጅነት ልንመሠርት ይገባናል። እኛና እናንተ ተባብረንም ድርቡሾችን ልንወጋው ይቻለናል። ለዚህም ማንኛውንም ነገር ከእናንተ ጋር እንዲነጋገርና እንዲጨርስ ከንቲባ ሳልህን ልኬዋለሁ ለሰላም እነሆ እጄን ዘርግቻላችኋለሁ። መልሳችሁንም እጠባበቃለሁ" ብለው ጠየቁት።

ተድዓሊ ላይ ያን ሁሉ ውርደት ካደረሱባቸው ሰውዬ ጋር ለመታረቅ ምኞት ያልነበራቸው ጣሊያኖችም፣ እርቅና ሰላም ለመመሥረት ፍላጐት አልነበራቸውምና ኰሎኔል ፒያኖ በተቻለው መጠን ያደረገውን አድርጐ አሉላን እንዲይዝ የምሥጢር ትእዛዝ ተላለፈና ለማዘንጊያ ያህል እንዲሆን ተብሎ ደግሞ ጀኔራል ባልዴሴራ ለአሉላ በጻፈላቸው ደብዳቤ፣

"እርስዎ ሁል ጊዜ ሰላም እንመሥርት እያሉ ቢጽፉልንም በሌላ በኩል የምናየውና የምንሰማው ግን የዚህን ተቃራኒ ነው። ስለዚህ ሁለታችን ለመግባባት አልቻልንም። መላው ዓለም እንደ ሊያውቀው በመጀመሪያም ምፅዋ የገባነው እንግሊዞችን ለመርዳትና ከድርቡሾች ጋር ለመዋጋት ሰንል ነበር። ግን ዶግአሊ

ላይ ያ ሁሉ እልቂት ከደረሰብን ወዲህ ከድርቡሾች ጋር ጦርነት ከመጋጠም የወታደሮቻችንን ሕይወት ማትረፍ ተገቢ መሆኑን አመንበት ። አሁንም ቢሆን ከአቢሲኒያ ጋር ሰላም ለመመሥረት እንመኛለን ። ግን ሰላምን ለማግኘት ስንል ደግሞ እንለማመጥም ። ምክንያቱም ከመጀመሪያውም ሰላምን ያበላሹና የተቃወሙ እርስዎ ነዎትና" አላቸው ። እርሳቸውም ሲመልሱለት ፣

"ሀገሬን ይዛችሁ ሰላምን ያደፈረሳችሁና የረገጣችኋት እናንተ ናችሁ ። እኛ ወዳጅነትን እንጂ ጠላትነትን የምንመኝ አይደለንም" ብለውታል ።

ራስ አሉላ ከቤታቸው ውስጥ ለገቡት ጣሊያኖች ወረቀት እየጻፉ እርቅና ሰላም በ ፈጠይቁበት ወቅት ደግሞ ፣ ከአሥመራ የሕዝብ ሮሮ ደረሳቸው ። እርሳቸው እስር ቤት በሰላይነት ተይዞ ታስሮ የነበረው ሻለቃ ፒያኖ ቂም በቀሉን ለመወጣት ሲል ቁጥሩ በትክክል ያልታወቀ ሕዝብ በመፍጀቱ ሕዝቡ ስቆቃውን እንዲህ ብሎ አሰማ ፤

"ቦሬላው በድርቡሽ ምስፈሰስ
ንጉሥ ባሕሪ ምፀ እናሐመስ
መድፍዕኒ ሮኬትኒ እናተኮስ
እልፊ ደቂ ጭዋ እሰረ ሐበስ
ንኳል ኢዱ ይመጽእ ተብሉና ቴድሮስ
ጋጽ እንኳ ይሪኡና ምድሬ መስ
ንፈርአን ዘጥፍኡት በትረ—ሙሴ
ባዕልካኸ ትፈልጥ ሥላሴ"

ምንም እንኳ በዚህ ስቆቃው እንባቸውን እያዝረከረኩ ቢያለቅሱለትም አንድ ሺህ የማይሞላ ወታደር ይዘው አሥመራ ገብተው የእሳት ራት ከመሆን ይልቅ ፣ በመረብ ማዶ ሆነው ጉልበታቸውን ማጠንከርና ማስፈራራትን መረጡና ፣ የደበበ ረዳቶች ለነበሩት ለደጃዝማች አምባዬና ለዋግ ሥዩም ብሩ ይቅርታ አድርገው ወደየፈለጉበት እንዲሔዱ ፈቀዱላቸውና በአካለ ጉዛይና በሠራዬ እየተዘዋወሩ ጦር ማዘጋጀት ጀመሩ ።



ራስ አሉላ ፣ ቀሐይን ሠፍረው በነበረበት ጊዜ የተከታያቸውም ቁጥር ወደ ሁለት ሺህ ከፍ ብሎ ነበር ። ባለ ብረቱ ግን ከአምስትና ስድስት መቶ አይበልጥም ነበር ። በዚህ ወቅት ደግሞ ያላሰቡት ራስ ምታት ደረሰባቸው ። ታማኛቸውና የእኅታቸው ልጅ ባሻይ ተድላ ፋንጃ ከእርሳቸው ከድተው አሥመራ ሔደው ለጣሊያን ገቡ ።

ሁለቱ ራሶች ከመረብ ወዲህና ወዲያ ሆነው የሰሜን ኢትዮጵያን አንድነት እንደገና ለማጠናከርና ጠላታቸውን ለመቋቋም በሚጣጣሩበት ወቅት ፣ የምኒልክ ዱላ የነበሩት ደጃች ሥዩም ከአንድ ሺህ አምስት መቶ በላይ የሆኑና በሚገባ የተደራጁ ጦራቸውን እየመሩ መቀሌ ገቡና ዐድዋ አጠገብ ከሦስት መቶ የማይበልጡ ወታደሮቻቸው ጋር ሠፍረው የነበሩትን ራስ መንገሻን ለመያዝ መዘጋጀት ጀመሩ ። ይህንም ነገር ራስ መንገሻ እንዱ ሰው በአስቸኳይ እንዲያደርሱላቸው ለደጃዝማች ተድላ አይባና ለዋግ ሥዩም ብሩ ጥሪ ላኩ ። ግን እንዳቸውም አልደረሱላቸውም ። በእነርሱ ፈንታ ግን የሐውዜን ገዥ የነበሩት ደጃዝማች ስብሐት ደረሱላቸው ። በአካለ ጉዛይ በኩል ደግሞ ደጃዝማች ባሕታ ሐጐስ ጣሊያኖች ባደረጉላቸው ርዳታ ኃይላቸውን እጅግ አዳብረው ነበሩና ራስ መንገሻን የሚደግፉ መሆናቸውን ላኩባቸው ።

ራስ መንገሻ ከሁለቱ ደጃዝማቾች ባገኙት ርዳታ ተጠናክረው ደጃዝማች ሥዩምን ወግተው ከመቀሌ ለማስወጣት በመዘጋጀት ላይ እንዳሉ ባሕታ ሐጐስ ራስ መንገሻን ከድተው የምኒልክ አሽከርና ታማኝ መሆናቸውን አስታወቁ ።

የደጃዝማች ባሕታን መነጠልና የራስ መንገሻንም ብቸኝነት ያረጋገጡት ደጃች ሥዩም ራስ መንገሻን ለመያዝ ከሚያስችላቸው ቦታ ላይ መድረሳቸውን አረጋገጡና ከመቀሌ ወደ ዐድዋ ገሥግሠው ከራስ መንገሻ ጋር ጦርነት ገጥመው ከግራቀኙም በርካታ ወታደሮች ከወደቁ በኋላ ፣ የአገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች በመካከል ገብተው ጠቡን አበረዱና እርቅ ሆነ ። ደጃች ሥዩምም የራስነት ዘውድ ደፉና "በአክሱም ካህናት አማካይነት ራስ መንገሻን ይቅርታ አድርጌለታለሁ" ብለው

ላኩበት ። ራስ መንገሻ ግን ሌሊት ከዐድዋ ወጥተው የእደራ አባታቸው ራስ አሉላ ወደነበሩበት ቆሐይን ገሠገሡ ። ደጃች ሥዩምም ራስ መንገሻን መከታተል ጀመሩ ። ራስ መንገሻም ፊጥ ነው "ይድረሱልኝ" ብለው ፈጣን ፈረሰኛ ወደ አሉላ ሰደዱ ። የእደራ ልጃቸውን የጭንቀት መልእክት ቆሐይን እንዳሉ ራስ አሉላ ሲሰሙ በቁጣ ተነሡ ። በራስ መንገሻ ላይ በደረሰውም ነገር አዘኑ ። ደጃዝማች ሥዩም ደግሞ ለራስ አሉላ እንዲህ ሲሉ ላኩባቸው ፤ "ጌታዬ ሆይ! ወደኔ ይምጡ እቀበለዎታለሁ ። የግዛቴንም ገሚስ እሰጥዎታለሁ" ራስ አሉላ ይህን ሲሰሙ ደግሞ በጣም ተቆጡና እንዲህ ሲሉ ላኩባቸው ። "ካንተ ጋር ምንም ነገር የለኝም ፤ ካንተም ጋር ግዛት አልካፈልም ። ከራስ መንገሻ በቀር ሌላ ንጉሥ የለኝም ፤ የዮሐንስ ልጅ መንገሻ ብቻ ነው ጌታዬ! አሁንም አንተ እኔ ነኝ የምትል ከሆንክ ከመረጥክበት ቦታ ጠብቀኝ መጣሁልህ" አሉና ላኩ ። ደጃዝማች ሥዩምም ወደፊት ገፍተው ራስ አሉላም ከቆሐይን ገሥግሠው አክሱም አጠገብ እንዳ አቡን ከተባለው ቦታ ጦርነት ተጋጠሙና ራስ አሉላ ድል ነሡ ። ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ተብለው በነገሡ በሦስተኛው ቀን ትግራይን ሰጥተው የላኩዋቸው እንደ ራሲያቸው ድል ሆኑባቸው ። ደጃች ሥዩም ከጦርነቱ ቦታ የፈረጠጡ የመረብን ወንዝ ተሻግረው አሥመራ ገቡና ከጣሊያኖቹ ጉያ ተሸጐጡ ። በራስና በደጃች መካከል በተደረገው ጦርነት ከራስ በኩል ከአንድ መቶ ሃምሳ በላይ ወታደር ሲሞት እስከ ሦስት መቶ የሚገመት ደግሞ ቆስሎባቸው ነበር ። በደጃች ሥዩም ላይ የደረሰው ጉዳት ግን በራስ አሉላ ላይ ከደረሰው እጥፍ ነበር ።

ራስ አሉላም ለራስ መንገሻ ፤ "ጠላታችንን ደጃች ሥዩምን ድል ነሥቼዋለሁና አንተም ተመለስ ወደ ቤትህም ግባ" ብለው ላኩባቸው ። ራስ መንገሻም በታላቅ ደስታ ወደ አባታቸው ቤት ገቡ ። መኳንንቱና የጦር አለቆቹ እስቲገረሙ ድረስም ደስታ ሆነ ። ከደስታቸውም የተነሣ ራስ መንገሻ ፤ "ጌታ ራስ አሉላ ሥራዎ ሁሉ እንደምን ያስደንቃል ። ካሉት ሰዎች ሁሉ ለማንም የማልሰጠውን ምስጋናና ሞገስ እነሆ ለእርስዎ ሰጠሁ" ብለው ላኩ ። በዚህ ነገር ሕዝቡም ሠራዊቱም ተደነቀ ።



ደጃች ሥዩም ከሁለቱ ራሶች ጋር ሲቀራቀሩ በነበሩበት ወቅት ደጃች ተድላ አባይና ደጃች ስብሐት ደግሞ አንድነት ሆነው ለኢጣሊያና ለአጼ ምኒልክ ታማኞች መሆናቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ ለጀኔራል ባልዴሴራ ጻፉለት ።

ባልዴሴራ በአጋጣሚው ተደሰተና ኰሎኔል ፒያኖንና ሌሎቹን የጦር አዛዦች ሰብስቦ ፤ ባደረገላቸው ገለጻ ፤

"ምንም እንኳን ይህን ርምጃ እንዳንወስድ ሮማ የሚገኙት አንዳንድ ባለሥልጣኖች ቢቃወሙንም በወታደራዊ ቆራጥነታችን ከዚህ ደርሰናል ። ይህም ሥራችን አሁን ወደ ተሻለ አቅጣጫ በማምራት ላይ ይገኛል ። በንጉሡ በአጼ ዮሐንስ ተከታዮችና ወራሾች መካከል መለያየትና መፋጀት ደርሷል ። ምኒልክ ሾሞ የሰደደው ሥዩም ይኸውና ርዳታ ስጡኝና በነመንገሻ ላይ እንደገና ልዝመት እያለ ነው ። የእርሱን ጥያቄ ለመደገፍ የሚያስችለን አጋጣሚ ደግሞ ደረሰ ። በዮሐንስ ግዛት በነበረው አገር በጣም የታወቁና ብዙም ተከታይ ያላቸው ሁለት ደጃዝማቾች ደብዳቤ ሰደውልኛል ። እነርሱም ተድላና ስብሐት ይባላሉ ። ስለዚህ ሥዩምን መሣሪያና ወታደር ሰጥተን ብንሰደው መንገሻንና አሉላን ሊያጠፋልን ይችላል ብዬ እገምታለሁ ፤ ምን ታስባላችሁ?" ብሎ ጠየቀ ።

ገና ንግግሩን እንዳበቃ ፒያኖ ፈጥኖ ብድግ አለና ፤

"ክቡር ጄኔራል! አስገራሚ ሐሳብና ጥናት ነው ፤ ለተድላ ለስብሐትም መሣሪያ መላክ ይገባል ። አሉላን ሲሆን ከነሕይወቱ ይዘው እጁን እንዲሰጡንና ፤ በዶግአሊ ላይ ባደረሰብን የድፍረት ሥራው ለመላው አፍሪቃ መቀጣጫ አድርገን እንድናቀርበውና በበረሃ ላይ የወደቁትን ጀግኖቻችንን ደም በእጥፍ እንድንመልስ ፤ የጣሊያን ሕዝብም በኛ ላይ ፍጹም እምነቱን እንዲያሳድርብን ማድረግ ፤ ዋናው ግባችን መሆን አለበት ። ያሲዚያ ፊማውንም ከስጡን ልባችን አፎይታና ደስታ ይሰማዋል ። ሦስቱ ደጃዝማቾች ይህን ያደረጉልን እንደሆነ ከፍተኛ ስጦታና ሽልማት እንደሚደረግላቸው ይነገራቸው" አለ ።

"በጣም ትልቅ ሐሳብ ነው ። ለሁሉቱ ደጃዝማቾች የሚላከው የጦር ማግሪያ ይዘጋጅ ፤ ሌላስ ሐሳብ ያላችሁ አላችሁ?" አለ ጀኔራሉ ።

"የአሉላን እጅ ወይም ራሱ የሚያስረክበን የሚሰጠው ሽል ማት ይነገራቸው" አለ አንድ ኰሎኔል ።

"ብር ነዋ ! ጥቁር ገንዘብ ነው የሚፈልግ ሌላ ምን ይሰጠዋል!!" አለ ፒያኖም ቶሎ ብሎ ።

"ገንዘብም፤ ልብስና የቤት ዕቃ ይጨመርላቸዋል" አለ ጀኔራሉ።

"አገር ቢሰጣቸውስ?" አለ ኰሎኔሉ ።

"ለጥቁር ሕዝብ ሥልጣን መስጠት ማሳበድ ነው፤ ጭንቅላቸውን ማቃወስ ነውና ፣ ሹመቱ አያስፈልግም" አለ ፒያኖ ።

"ዝቅተኛ ሹመት መስጠቱስ አይከፋም" አለ ጀኔራል ፒያኖን እያተመለከተ ።

"ዝቅተኛም ሆነ ከፍተኛ ሹመት ብንሰጣቸው ፣ ጥቁሮች እንዲሁ ሆኑ ያው ናቸው ። መበላለጥ ፣ መናናቅ ፣ መፋጀት ነው መያቸውና ሰላም ይነሣሉ!!" አለ ፒያኖ ።

"ይኸማ ግለፊያ ነዋ! ብራቮ ነዋ! አለና ጀኔራሉ ተነሥቶ በክፍሉ ውስጥ እየተንጐራደደ በሲያች ፍጥነት ሰዓት የተሰማውን ደስታ ሲገልጽ ፣

"የእርስ—በርሳቸው መፋጀትማ የምንመኝላቸው መጨረሻ ነው ። የእነርሱ መፋጀት ማንን ይጐዳል ብለህ ትመጋበታለህ ይጨራረሱ! ከዚያ በኋላ ከባዶ አገር ከባዶ ቤት መግባት ይቻ ገረናል ብለህ ታስባለህ? እንዲያውም ትንሹን ከፍ ፣ ትልቁን ዝቅ አድርገን ብንሾማቸው መተላለታቸውን ያፋጥንልናል ፤ አይመስል ችሁም?" ብሎ ወደ መቀመጫው ተመለሰ ።

"የክቡር ጀኔራልን ሐሳብ እደግፋለሁ" አለ ኰሎኔሉ። "እው ነት ነው የኛ ሥራችን ጠመንጃና ጥይት ማቀበልና ማቀራረብ ነው፤ መልካም አስበዋል ! ግን ከፈለገም ከደጃዝማቹ ጋር የግን



ወታደሮችም አብሮ መላክና አሉላን መያዝ ወይም መግደል አለብን ፤ እርሱ በሕይወቱ እያለ እኛ ሰላም ልናገኝና ሐሳባችን ሊሳካ አይችልም።" አለ ፒያኖ ምርር ብሎ ።

"በዚህ እስማማለሁ ። ሰላስ?" አለ ጀኔራሉ ።

"ከዚሁ ሥዩም ከሚሉት ጋርስ ልዩ ተመልካች አብረን ብንሰድስ?" አለ ፒያኖ ።

"ይህንም አስቢበታለሁ ። ግን ለዛሬው ያገር ተወላጆች ይበቁን ይመስለኛል" አለ ጀኔራሉ ።

"ያ ተወላጅ የቱን ያህል አጥጋቢ መረጃ ሊያመጣልን ይችላል? አገርን በወታደራዊ ዐይን ማስጓበስ ለሚገባን አንድ መኮንን ብንልክ ይሻላል" አለ ፒያኖ ።

ግለፊያ ነው እንግዲያው አንተ ሰው ምረጥና አዘጋጅ ፤ ለምን ሲከው የጦር መግሪያ አስረክቢ አድርገን እንልክዋለን ። አገረ— መንግዱንም የመሬቱንና የሕዝቡን ሁኔታ አጥንቶልን ይመጣል!" አለና ጀኔራሉ ስብሰባው አበቃ ። በዚሁም መሠረት ለደጃች ሥዩም ቢቂ የጦር መግሪያ ተሰጠና ወደ ትግራይ ተመለሰው ከነደጃች ተድላና ስብሐት ጋር ተቀላቅለው በሁለት ራሶች ላይ እንዲዘምቱ መመሪያ ተሰጣቸው ። ለእነርሱ ረዳት የሚሆንም የኢጣሊያ መኰንናች ያሉበት ጦር የመረብ ወንዝን ተሻግሮ ወደ እንትጮ እንዲያመራና ደጃዝማች ባሕታ ሐጐስም ወደ ደብረ ዳሞ አካባቢ እንዲዘምቱ ታዘዙ ።

ቀደም ሲል ፣ ሁለቱ ራሶች በአጼ ምኒልክ እንደራሴ ላይ በተጐናጸፉት ድል ስማቸውና ዝናቸው እየታደሰላቸው በመሔዱ ፣ የወታደራቸውም ቁጥር ከአምስት ሺህ በላይ ደረሰ ።

ኢጣሊያኖቹ ያስታጠቋቸውና ያስተባበሩዋቸው ሦስቱ ደጃዝማቾች ባንድነት ሆነው ከሦስቱ ራሶች ፣ ማለት ከመንገሻ ከአሉላና ከሐጐስ ጋር ተፋጠጡ ። እንደተፋጠጡም አልተፋቱ፤ ጦርነት ገጠሙ ። በጦርነቱም ሦስቱ ራሶች ድል አደረጉ ።

እርግጥ ነው ፤ ዘባን ላይ በተደረገው ጦርነት ሦስቱ ራሶች
ብርቱ ጉዳት ደርሶባቸው ነበር ። በተለይም እንደርታ በደጃች
ሥዩም ዘመዶች ይገዛ ነበርና ርሳቸውን የሚረዳ ብዙ ተዋጊም
አግኝተውበታል ። ሦስቱ ደጃዝማቾች ከውስጥና ከውጭ ባገኙት
ጦር ሦስቱን ራሶች ድል ለማድረግ እንዳልቻሉ ከተረዱት በኋላ
ወደ ሠፈራቸው ተመለሱ ። ደጃች ሥዩም ወደ መቀሌ ፤ ደጃች
ስብሐት ወደ አዲግራት ሲሔዱ ራስ መንገሻና ራስ አሉላም
ተንቤንን ይዘው ከሰሜን የኢጣሊያ ከደቡብ የአጼ ምኒልክ ጦር
ሲመጣባቸው ለመመከት መዘጋጀትና መጠባበቅ ቀጠሉ ።

ምንም እንኳን የአሉላን እጅ ወይም ራሣ ባያገኙም ቅሉ
ጣሊያኖችም የመረብን ምላሽ ሙሉ ለሙሉ ከሠፈሩበትና ወደ
ትግራይም እግራቸውን ካስገቡ በኋላ ፤ እ.ኤ.አ. ጥር 1 ቀን
1890 (በኛ አቆጣጠር ታኅሣሥ 24 ቀን 1882) ሰሜኑን የኢት
ዮጵያ ክፍል "ኤርትራ" ብለው ሰይመው ቅኝ ግዛታቸው
መሆኑን ዐወጁ ።

የውጫሌው ውል በቂ መሬት እንዳልሰጣቸው የተረዱት
ኢጣሊያኖች ፤ መላውን ኤርትራን እጠቃለው መያዛቸውም
ስላልበቃቸው የመረብን ወንዝ ተሻግረው ሠፈሩ ። አጼ ምኒል
ክም ይህንኑ ክልል እንዲአውቁላቸው ሮም በጉጉት መጠባበቅ
ጀመረች ። ቀጥሎም ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ትግራይ እንዲዘምቱና
ያዮሐንስን ወራሾችና አሽከሮች በተለይም ራስ አሉላን ከነተከ
ታዮቻቸው ፈጽመው እንዲያጠፉላቸው እሥመራ የነበሩት
የኢጣሊያ የጦር ባለሥልጣኖች በታላቅ ተስፋና እምነት መጠባ
በቅ ጀመሩ ።

አጼ ምኒልክ እንደራሴያቸው አድርገው የሾሙዋቸው ደጃች
ሥዩም እንዳልሆኑላቸው ካረጋገጡ በኋላ ፤ የትግራይን ጣጣ ራሳ
ቸው ለመጨረስ እሰቡና ኅዳር 29 ቀን 1882 ከአዲስ
አበባ ተነሥተው የካቲት 17 ቀን 1882 መቀሌ ገቡ ።
የእርሳቸውን መቀሌ መግባት የሰማው ጀኔራል ባልዴሴራ የመን
ገሻና የአሉላ ፍጻሜ መሆኑ ነው ብሎ እጅግ ተደሰተ ። እንዲ
ያውም አጼ ምኒልክ ትግራይ ውስጥ የኢጣሊያ ጦር ሠፍሮበት
የነበረውን ግዛት እንዲመርቁለትና ፤ የራስ አሉላንም እጅ እስረ



ኛ በሙት ጥርቅም አድርጎ እስር ወደ ኢጣሊያ እንደሚልካቸው
በመተማመን ፤ ለአጼ ምኒልክ ፤"እንኳን በደኅና የገቡ ። የሚያስፈ
ልገዎትንም ፤ ነገር ሁሉ ለመላክ ፈቃደኛና ዝግጁ ነኝ" ብሎ
ላከባቸው ።

ለሰደደው መልእክት መልስ ሳይደርሰው እንዲያውም ፈቃድ
ሳይሰጠው ጦሩን ይዞ ወደ ዐድዋ ገባና ፤ የኢጣሊያ ጦር ተድ
ጓሊ ላይ ድል የሆነበትን 'የመታሰቢያ' በዓል አከብሮዋል ።
በዚያም አልተገታም ፤ ወደ ተንቤን ለመዝመትና ሁለቱን ራሶች
ለመግጠም ተዘጋጀ ።

የጣሊያኑ የጦር አዛዥ ፤ ትግራይ ውስጥ ገብቶ የሚሠራውን
ተንኮል አጼ ምኒልክም የማይደግፉት ሆነ ። ባልዴሴራ ይረዱኛል
ብሎ ተማምኖባቸው የነበሩት ደጃዝማች ስብሐትም አገሸሹት ፤
ፊታቸውንም ወደ ንጉሠ ነገሥቱ መለሱና በሁለቱ በመረሩ
ጠላቶቻቸው በራስ መንገሻና በራስ አሉላ ላይ ብቻ ለመዝመት
ፈቃደኛነታቸውን አስታወቁ ።

ሕዝቡ የጣሊያኖችን በየቦታው መሥፈር አጥብቆ በመቃ
ወሙና እንዲያውም ወደ ሁለቱ ራሶች እየተቀላቀለ ጉልበታቸውን
ለማጠንከር መነሣሣቱን የሁለቱ ራሶች ተቃዋሚዎችና ደጋፊዎ
ችም ከተገነዘቡት በኋላ ፤ የኢጣሊያኑ ጦር ከትግራይ እንዲወጣ
ላቸው ለአጼ ምኒልክ ስላመለከቱ ፤ ንጉሠ ነገሥቱም ጣሊያኖች
የውጫሌውን ውል ጣጥሰው እስከ ዐድዋ መድረሳቸውን በመ
ቃወማቸው ኢጣሊያኖች ጉዳዩን ወደ ሮም አስተላለፉት ።

የሮም ባለሥልጣኖች ተስፋ ያደረጉት ነገር መደፍረሱንና
እንዲያውም አስከፊያቸው እየሆነ እንደሚሔድባቸው በመገንዘብ
ጀኔራል ባልዴሴራ ትግራይ ውስጥ ያሠፈረውን ጦር ወደ መረብ
ምላሽ እንዲመልስ ትእዛዝ ተላለፈለት ።

ሁለቱ ራሶች ፤ ተንቤን ላይ ሆነው በደቡብ ምኒልክ በሰሜን
ጣሊያን እየገቡ ትግራይን መያዝ መጀመራቸውን እምነው
ለመቀበል ቸገራቸው ። ሁኔታውንም በዝምታ ከመመልከት መወ
ያየት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ራስ መንገሻ ስለ ተረዱት ፤

"ከከፋ ጥፋት ላይ ከመውደቃችን በፊት ወደ መቀሌ ሔደን እጼ ምኒልክን ይማሩን ብንል ይሻል ይመስለኛል" ሲሉ ራስ መንገሻ ምክር ጠየቁ ። ራስ አሉላ ሲተክዙ ቆዩና ፤

"የምኒልክን ወንድምነት ጌታዬ አጼ ዮሐንስም ፈልገውት ስለ ነበረ 'ልጅህን ለልጄ' ብለው ለምነው ገቡ ። እግዚአብሔር ያልፈቀደው ጋብቻ ሆነና ዘር ሳያተርፉ ቀሩ ። መሸሪዋም ወደ አባቷ ቤት ተመለሰች ። ከዚያም ወዲህ የደረሰውን ሁሉ ታውቀዋለህ ። ጌታዬ አጼ ዮሐንስም 'ምኒልክ ወንድሜ ነው ፤ እግዚአብሔር ከፈቀደለት ዘውዱንም ዙፋኑንም ይውሰደው' ብለው ነበርና እነሆ ምኒልክም ነገሡ ። አሁንም እሔዳለሁ ካልክ ሒድና ግባ ። እኔ ግን አልገባም" አሉዋቸው ።

"እርስዎ ለምን አይገቡም? ከኔ ተለይተው ከምኒልክ ርቀው ከጣሊያን ጋር ተጣልተው እንዴት ሆነው ሊኖሩ ነው?" አሉዋቸው ።

"የኔማ ሐሳቤና ምኞቴ የነበረው?" አሉና ራስ አሉላ ትክዝ ብለው ቆዩና ፤ "የኔማ ምኞቴ አንተ ኮስተር ብለህ ወዳጅህንና ጠላትህን ለይተህ የዮሐንስን ዙፋን እንድትይዝልኝ ነበር ። ይህ ምኞቴ ሊፈጸም ካልተቻለ ደግሞ ገዳም ገብቼ እኖራለሁ" አሉ ።

"ይህማ እንዴት ይሆናል ብለው ያስባሉ? ከኔ ከተለዩኮ ጣሊያኖቹ አውለው አያሳድሩዎትም ፤ እጅዎን ይፈልጉታል ! ያደረሱባቸውን ይዘነጋሉ ብለው ያስባሉ?" አሉ መንገሻ ።

"ለኔ አታስብ ፤ ለኔ ብታስብማ ኑሮ ከፊት ጀምሮ የነገርኩህን ቁም ነገር ሁሉ ችላ ባላልከውም ነበር ። ከእንግዲህ ወዲያ ከዮሐንስ ወዲያ ለሌላ ጌታ አልገባም ! አንተ ግን ሒድ ፤ ከዚህ ሆነህ በሐሳብ ከምትንገላታ ከምኒልክ ጋር ታርቀህ በሚሰጡህ ትተዳደራለህ ፤ እኔን ተወኝ" አሉ ራስ አሉላ እየተከዙ ። በጉዳዩም ሊግባቡ አልቻሉም ። በአጼ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት እጼ ምኒልክ መግባታቸውን ራስ አሉላ እንደ ሰሙም እጅግ አዘኑና ፤



"የዮሐንስ ግዛት የታለ? አልፍኞቻቸውስ አሽከሮቻቸውስ የታሉ? ምልክታቸው የት ይገኛል? እንግዲህ በቃኝ ለምኒልክ እጅ አልነሣም ። የዮሐንስን ቤት ደፍረው ገብተውበታልና በቃኝ በዐይኔም አላያቸውም!" አሉ ። ራስ መንገሻ ከአደራ አባታቸው ፈቃድ ወጡ ። ከተንቤንም ተነሡና ወደ መቀሌ ሔደው 'ባጠፋሁ ይማሩኝ' ብለው ከምኒልክ ፊት ቆሙ ። "እኔን አልበደልከኝም ፤ የበደልካቸው ካሉ ቀስ—በቀስ ታረቅ ፤ እኔንም ይቅር በለኝ" ብለው አቅፈው ተቀበሉዋቸው ።

የኢጣሊያኖች ድፍረትና እስከ ዐድዋ መዝለቅ ፤ የትግራይ ሕዝብም ሆነ መኳንንቱ ያሳዩት ተቃውሞ ፤ የአጼ ምኒልክን ዐይን—ሕሊና ስቦ በያዘበት ወቅት የአጼ ዮሐንስን ወራሽ አልታረቅም አላቀርብም ለማለት ደግሞ የማያስችልና አደገኛም የሆነ ሁኔታ ሊያስከትል እንደሚችል ምኒልክ ተገንዝበውታል ። ለትግራይ ግዛት ደግሞ ፤ ከፊታቸው ከቆሙት ፤ ከመንገሻ የተሻለ ወይም የበለጠ ገዥ ሊኖር እንደማይችል አምነውበታል ። ለንጉሡ ነገሥታቸው ጽናት አንድነትና ሰላም ደግሞ ፤ የኢትዮጵያውያን አንድነትና ጥንካሬ ዋናው ምሰሶ መሆኑን ተቀብለውታል ።

የአጼ ዮሐንስ ወራሽ የሆኑትን ራስ መንገሻን አልታረቅም ማለት እና ፤ ተቀብሎ ደግሞ መላዋን ትግራይን ጠቅልሎ ለብቻቸው መስጠት ፤ ሁለቱም አደገኛ መሆናቸውን ምኒልክ ተገንዝበውት ።

ታዲያ መላዋን ትግራይን አጠቃለው 'ግዛ ንዳ' ብለው ቢሰጡ የመንገሻ ልብና ጉልበት ያብጥና 'አሻፈረኝ' ማለት እንዳይመጣ ሲሉ ደጃዝማች ሥዩምን በምሥራቅ ክፍል ፤ ደጃዝማች መሸሻ ወርቄን የአክሱም ፤ የዐድዋና የመረብ ምላሽ ወዲህ ገዥዎች አድርገው ሾሙና ፤ የቀረውን ትግራይን ለመንገሻ ሰጡ ። የትግራይ ገዥ እንዲሆኑላቸው ጣሊያኖች ደጅ የጠኑላቸውን

ደጃዝማች ስብሐትን ግን ምኒልክ ሳይቀበሏቸው ቀሩ ። በምኒልክ ቤተ መንግሥት ተሸጉጦ ሲያሸቃብጥ የነበረው የኢጣሊያ የፖለቲካ ጠቢብ አንቶኔሊም ንጉሠ ነገሥቱ ትግራይ ገብተው የእነርሱን አሙ ደጃች ስብሐትን ባለመቀበላቸውና ፣ ከትግራይም ጥቂት መሬት ቆረስ አድርገው ለጣሊያን ጦር መጣሪያ ሳይለግሱ ወደ ሸዋ በመመለሳቸው ግንባሩን በወስፈንጥር የወጉትን ያህል ተሰማው ።

አጼ ምኒልክ ትግራይ ደርሰው ሹም ሹር አድርገው ወደ ሸዋ ከመመለሳቸው በፊት ፣ አሉላ የትግራይ በራሪ ኮከብ ተዘዋዋሪ ኃይል መሆናቸውን ስለ ተረዱት ፣ የግል ሀብታቸውን ይዘው ከመኖር በቀር በአገዛዙም ሆነ በምክሩ ወይም በጦር ድልደላው ውስጥ እንዳይገቡ ራስ መንገሻን ምኒልክ አስጠንቅቀዋል ።

የጣሊያኖች ፖለቲካና ተስፋ ፣ በከፊል ውድቀት በመሆኑ አንቶኒሊ እጅና እግሩ እንደታሰረ ሆኖ ተሰማው ። እነርሱ ተስፋ እንዳደረጉት አሉላ አልተያዙም ፤ ትግራይ ውስጥ ቁራጭ መሬት ለማግኘት አልቻሉም ። እንዲያውም ራስ መንገሻ ከውድቀት ተነሥተው ሥልጣን ለመጨበጥ በቅተዋል ። ይህን ሽንፈት ቢቀበሉትም እንደገና ዕቅዳቸውንና ስልታቸውን በመለወጥ ራስ መንገሻን በመለማመጥና በማስታጠቅ ከአጼ ምኒልክ ጉያ ለማውጣት ሲያንሰላስሉ መንገሻ ደግሞ ከአሉላ ምክር የማይወጡ እየሆኑባቸው ሔዱ ። ስለዚህ መረብ-ምላሽ ላይ ተደላድለው ለመቀመጥ ፣ የፈለጉትን የትግራይን መቀራረብና በንግድ መቀራረኘት የአሉላ ምክርና ክንድ እንደሚቆራርጥባቸው በማመን ፣ 'አሉላ እያለ ቅኝ ግዛት የለም' እስከ ማለት ደረሱ ።

'በዚህም የተነሣ የአሉላን እጅ ወይም ራስ ማግኘት ካልተቻለ የአሉላን ተባባሪነት ለማግኘት ደግሞ ሙከራ መደረግ አለበት' የሚል ሐሳብ አደረባቸውና አንዳንድ ሰዎችን እየመረጡ ወደ አሉላ በምሥጢር መስደድ ጀመሩ ። "መንገሻ ከአሉላ



እጅ የማይወጣ ከሆነ ሁለቱም ተባብረው ምኒልክን እንዲቃወሙና 'ራሳችሁን ችላችሁ ተዳደሩ' ፣ ብለን መቅረብና የፈለጉትን ያህል መጣሪያ መስጠቱ የተሻለ ይሆናል" ተብሎ አሥመራ ላይ በነበሩት የኢጣሊያ የጦር አለቆች ተመከረና ስልቱ በምሥጢር ተቀነባበረ ።

ይህን ዕቅድና ስልት በሥራ ለማዋል እንዲመች ፣ ከተመረጡትና ወደ ትግራይ በምሥጢር ሲላኩ ከነበሩት አንዱ መሸሻ ወርቄ ፣ ራስ አሉላን አነጋግረው ያገኙትን ፍንጭ ለሣሊቤኒ ሲያሜውቱት ፣

"የአገሪቱን አንድነት ለመጠበቅ ቆራጥነት ያለውን ሰውዬ በመቅረብ ላይ ነው ። እርሱም በየተራራው መውጣቱና በጦርነት መኖሩ ሰልችቶታል ። ስለዚህ በተቻላችሁ ዘዴ እርሱን ማቀፍ ይኖርባችኋል" አሉት ።

እርግጥ ነው ፣ በዚያ ወቅት አሉላ ከማንኛውም አስተዳደር ተገልለው በዕረፍት ለመኖር ፈልገው ነበር ። ኢያረጁና እየደከሙ መሔዳቸውም ማንኛውንም ጉዳይ መቃወም እንደማያዋጣቸው እየተገነዘቡት ሔደው ነበር ።

ለአንድ ሰንደቅ ዓላማ ፣ ለአንድ አለቃ ፣ ለአንድ ዓላማ መቆም ዓላማቸው ሆኖ ኖሩዋል ። የሚወዱዋቸውን ጌታቸውን የአጼ ዮሐንስን አደራ እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ ለመጠበቅና ፣ ለመንገሻ ሲሉ ሌላውን አልቀበልም ያሉ ናቸው ። የንጉሠ ነገሥታቸውን አደራ እንደ ጠበቁ ለማንም እጅ ሳይነሡ ፣ 'ካንዱ ገዳም ገብቼ ዘግቼ ብቀመጥስ?' እስከ ማለትም ደርሰዋል ።

'የትግራይ መኳንንትን አስተባብር ፣ በአጼ ምኒልክ ላይ እንዲያምፁና ብጥብጡ እንዲራዘም አድርግ ፣ በመረብ ምላሽ የተጠናከረ አቋም መፍጠር የሚያዋጣ ይሆናል' ብለው የተማመኑት የኢጣሊያ ባለሥልጣኖች ፣ ግንቦት 9 ቀን 1882 ዐድዋ ድረስ ሔደው ከትግራይ መኳንንት ጋር በምሥጢር ተነጋገሩ ።

በስብሰባውም በአጼ ምኒልክ ቤተ መንግሥት አሸቃባጭ የነበረው አንቶኔሊና በሰላይነቱ ተይዞ የራስ አሉላ እስረኛ

የነበረው ግሊቢኒ በኢጣሊያ በኩል ሲገኙ ፣ ከትግራይ መኳንንት ደግሞ ራስ መንገሻና መሸሻ ወርቄ ተገኝተው ነበር ። በመካከላ ቸውም እርቅና ሰላም አድርገው ተግግለው ። በስምምነቱም ላይ መሸሻ ወርቄ ዐድዋ እንዲመናሩ መንገሻ መቀግግታቸውን አረጋገጡ ። በመካከላቸውም ወሰላቶች እንዳያስቸግሩ ለመቆጣ ጠር ወሰኑ ።

በዚህ ጊዜ አንቶኔሊ ፣ "ከራስ አሉላ ጋር መቸ ያስታር ቁናል?" ብሉ ራስ መንገሻን ጠየቁ ። "ነገ እንዲገኙና እንድት ታረቁ አደርጋለሁ" ብለው መንገሻ አረጋገጡለት ።

"እንግዲህ ጌታዬ!" አሉ ራስ መንገሻ ከስብሰባው ተመልሰው ራስ አሉላን ሲያነጋግሩ ፊራ ተባ እያሉም ፣ "መቼም ያለፈው አለፈ ። ለየሐንስ ቢሉ ለአገርዎ ቢሉ ያን ሁሉ ጀግንነት ፈጸሙ ። ከእንግዲህ ወዲያ ደግሞ ዳዊትዎን እየደገሙ ልኛ ጸሎት እያደረጉ እኛን በምክርዎ እየረዱ በሰላም እንድንኖር ከጣሊያኖቹ ጋር ይታረቁልኝ" አሉና መንገሻ ከአደራ አባታ ቸው ጉልበት ላይ ጉንበስ አሉ ።

ራስ አሉላ ፣ ብድግ ብለው መንገሻን ከጉልበታቸው ላይ አንሥተው ከወንበራቸው ላይ አስቀመጡዋቸውና እሳቸውም ተቀመጡ ። ጣቶቻቸውን እፍታትተው እንደ ማጨብጨብም አደረጉና ፣

"ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ያክብርህ ! ዓላማዬን ተናገርኸዋል ፣ ዛሬ ለጌታዬ ለዮሐንስ ሰል ነበር ያን ሁሉ የሠራሁትና ያበቃ ተርቶ የባሕር ማዶ ጠላት ያፈረሁት ። ከእ ንግዲህም በስተርጅናዬ ታረቅ ፣ በሰላም ተቀመጥ ብለህ ስት ልኝ ተቃልህ አልወጣም ። ግን እነዚህ ነጮች ተንኮላቸውን በልቦናቸው ይዘው ነውና ፣ 'እንታረቅ' የሚሉን ፣ እኛን በማያጋጭ የአገርን ክብር በማይነካ ጉዳይ ከሆነ እኔ ከቃልህ አልወጣም" አሉና በማግሥቱ ከኢጣሊያኖቹ ጋር ተገናኙ ።

በስብሰባውም ራስ መንገሻ ንግግር ሲያደርጉ ፣ "እንግዲህ በመካከላችን ሰላም መሥርተናል ፤ በሰላሙ ውላችንና ንግግራች ንም ራስ አሉላ እንዲገኙ ተደርጓል ። ያለ መታደል ሆኖብን



ከብዙ ችግሮች ላይ ወድቀናል ። አገራችን በብጥብጥና ደም በመፍሰስ ላይ ናት ። ከገራ ቀኛችንም ብዙ ሰዎች ሞተዋል ። እንግዲህ ያለፈው ዐልፏል ። ራስ አሉላም ስለ ዐለፈው ጉዳይ ሐሳባቸውን ሊነግሩን ፈቅደዋል ። ስለዚህ እናዳምጣቸው ብለው ተናገሩ ። ራስ አሉላ ተነሥተው ንግግር ሲጀምሩ ፣ ድምፃቸው የደከመና አነጋገራቸውም ያልተብራራ ነበር ። እየቆዩ እየቆዩ ግን ድምፃቸው ወሰል ብሎ የሚሰማና ግልጽም እየሆነ ሔደ ።

"...በተድዓሊ በሆነው ጦርነት ጉዳይ ጥፋቱ የጣሊያኑ የጦር አለቃ ነው ፤ በተሰጠኝ ግዛቴ ላይ ሰተት ብሎ ገብቶ ሥፈረበት ። ጌታዬ በሰጡኝ ትእዛዝ መሠረትም ተግባሬን ፈጸምኩ" አሉና በስብሰባው የነበሩትን ጣሊያኖች ትክ ብለው አፈጠጡባቸው ።

ግሌቢኒ በቅጥጥ አለ ። ከሦስት ዓመታት ተኩል በፊት በኒያ ታላቅ ጀኔራል ጫግ ሥር ወድቆ ምሕረት የለመነበቱ ጊዜ ትዝ አለው ። በዚያች ሰዓትም እነዚያኑ አሽከሮቻቸውን ጠርተው እግር ብረት የሚያጠልቁበት መሰለው ታየት ። እጃቸውንና ቁጣቸውን ያልቀመሰው አንቶኔሊ ግን በጥርጣሬ ይመለከታቸው ነበር ። በሐሳቡም 'ለምኒልክ እንኳ እጅ አልነ ሣም ብለህ አፈንግጠህ ከተቀመጥክ ይኸውና ወራት ዐልፈው ሃል ። እውነት ለኛስ ልብህን ትሰጠናለህ?' እያለ ያቅማማ ነበር ።

"ዛሬ የምኒልክ አሽከር ሆኛለሁ" ብለው አዛውንቱ ጀኔ ራል ንግግራቸውን ሲቀጥሉ አንቶኔሊ ተቁነጠነጠ ። ወደፊቱም አሰገገ ። ግሌቢኒ ደግሞ አፍጥጦ እያያቸው እጁ ብርዑን መያዝ እያቃተው ማስታወሻ መሞነጫጨር ጀመረ ።

"የመንገሻም አሽከር ነኝ ። የመንገሻ ጠላት ጠላቴ ፣ ወዳጁ ወዳጄ ነው ። በበኩሌ ግን እናንተም ከልባችሁ ሰላም ከፈለጋ ችሁ እኔም ሰላም እወዳለሁ ። ይህንኑም በመሐላ አረጋግጣ ችኋለሁ ።" በመካከሉ በራስ መንገሻ አማካይነት እርቀ ሰላም ወረደ ።

ስለ ተደረገው ዕርቅና ስምምነት ለሦስት ቀናት ያህል ዕረፍት ግብዣና በግል ውይይት ሲደረግ ቆዩና ፣ ከሦስት ቀናት በኋላ እንደ ገና ስብሰባ ተደርጐ ኢጣሊያኖች ወደ ትግራይ ገባ

ብለው ከልል እንዲሠሩ ራስ አሉላ እንዲስማሙበት ሲጠየቁ
እንኳን መሬት ዐፈር ቆንጥረው ይሰጡ ቢባሉ የሚዘገንናቸው
አሉላ ትከሻቸውን እያሰጨፈሩ፣ "ንጉሠ ነገሥቱ ያዘዙትን ሁሉ
ማክበር አለብን" ሲሉ ራስ መንገሻም ቀጠል አድርገው፣
"አዎ አዋጁ ወሳኙ ንጉሠ ነገሥቱ ናቸው። እኛ ታዛዦች ነን"
ብለው የአሉላን ሐሳብ ደገፉ። በዚያ ዕለት በዚያ ስብሰባ ላይ
ከተነሡት ነጥቦች እጅግ አከራካሪና አስቸጋሪ ሆኖ የነበረው
ደግሞ ራስ አሉላ ፎቶግራፍ እንዲነሡ የቀረበው ጥያቄ ነበር።

'የእነርሱን ምግባቸውንም መግሪያቸውንም አላምነውምና
አይሆንም' ብለው ድርቅ አሉ። ራስ መንገሻም እንደ አባት
ለምነው እንደ ሕፃን አባብለው እሺ አሰኟቸው። አሉላ እሺ
ብለው ፎቶግራፍ ተነሡ ሲባል ደግሞ የአድዋ ሕዝብ፣ 'ማን
ይሙት ጣሊያኖች ያሉላን መልክ በትክክል ያወጣሉ? ያን ሁሉ
ወታደር የፈጀባቸውን ሰው መልክ እውነት አስመስለው ያሳ
ያሉ?' እያለ መዘበቱን ጣሊያኖች ሰሙ።

እም በዚያ ዕለት የተነሡት ፎቶግራፍ ሌላውን የዕድሜና
የብቸኝነት ገጽታቸውን የ ሚያሳይ ነበር። ሠራዊታቸው በጦር
ኑ ሳይሆን በረኃብና በመከራ ተበታትኗል። ዕርቁን በብ
ቸኝነታቸው የተነካ ተገድደው ተቀብለዋል። ያን አጋጣሚውን
ግሩቡኒ ለአንቶኒሊ ሲያጫውተው፣

"ከዛሬው አሉላ ፍጹም ልዩ የሆኑት አሉላ ትዝ ይሉኛል።
ትይ ሽግ ለብሰው በበቅሎ ላይ ተቀምጠው በኩራትና በልበ—
ሙሉነት የነበሩት አሉላ ትዝ ይሉኛል። በዚያን ጊዜ ዝናቸው
የሚያስተጋባ መሸነፍ የማይታጣቸው በነበሩበት ወቅት የነበ
ረው ገጽታቸው ዛሬም ትዝ ይለኛል። ዛሬም ቢሆን አሉላ ለሰ
ላም እጃቸውን ሲዘረጉ በፍጹም ኩራትና ክብር መሆኑን ለማ
ረጋገጥ ችያለሁ። በቆራጥነትና የላቀ ወኔ ወደ ጦርነት ሲሔዱ
ጦርነትንም ሲገጥሙ የነበሩት ቆራጡ አሉላ ዛሬም በተረጋጋ
መንፈስና በፍጹም ኩራት ሰላምን ተቀበሉዋት። ታዲያ እንዲህ
ሆነው ስለአየኋቸው ዛሬም ሕሊናዬን የሚወተውቱ ጥያቄዎች
አሉኝ። ከእንግዲህ ወዲያስ ቃላቸውን ይጠብቁ ይሆን? በእርግ
ጥስ ከእንግዲህ ወዲያ ከመንገሻ በታች ሆነው ይኖራሉን? እን



ዚሆን ጥያቄዎች ያጫረብኝ ሁኔታ ዛሬ እንኳ አጋጥሞኛል።
ለምሳሌ በስብሰባው ላይ እንኳ ራስ መንገሻ ንግግር ሲያደርጉ
አሉላ አቋርጠዋቸው፣ 'ቢቃህ አነጋገርህን ቆጥብ' ሲሉዋቸው
መንገሻም ዝም አሉ። ይህም የአሉላን ፍጹም የበላይነት የሚ
ያሳየኝ ሆኗል" አለው።

ምንም እንኳ አሉላ በሙያቸውና በጀግንነታቸው ከዚያ
ከፍተኛ ደረጃ ላይ ለመውጣት ቢችሉም፣ በ"ወዲ ቁቢ" ነታ
ቸው የተነካ ሁልጊዜ ከተከታይነት ሊያመልጡ አልተቻላቸ
ውም ነበር።

ራስ አሉላ የራስ አርአያ ድምፁን ልጆች፣ በተለይም እጅግ
አምጊ የነበሩትን ደበበን ካሰሩ በኋላ፣ የትግራይ መኳንንት መቀ
ራቀፍ በመጠኑም ቢሆን እየበረደ ሔደ። ራስ መንገሻን የሚፎ
ካከሩ የነበሩት የእጋሜው ጎበዝ ደጃች ስብሐት ብቻ ሆኑ።
ስብሐት ምንም እንኳ በአስተዳዳሪነታቸው ሕዝብ ቢያከብራቸ
ውም በጦረኛነታቸው ግን ግንባረ ሰፊ ነበሩና የራስ መንገሻን
የበላይነት ሊቋቋሙት አልተቻላቸውም ነበር። እንዲያውም ዐመል
ሆኗቸው፣ 'አንድ ጊዜ እገብራለሁ' ሲሉ፣ አንድ ጊዜ ደግሞ፣
'እምቢ' እያሉ ቢያንገራግሩም ቅሉ፣ ጉልበታቸውን ተማምነው
ሙሉ ለሙሉ መንገሻንና አሉላን ሊጥሉ የሚችሉም አልነበሩምና፣
መንገሻም 'እምቢ ካልክ ወዮልህ' እያሉ ከማስፈራራት በስ
ተቀር፣ 'ከተት' ብለው ሊዘምቱባቸው አልጨከኑም ነበር።
በዚያን ጊዜም በእጋሜ በኩል ከታየው የተጋሪነት መንፈስ
በስተቀር፣ በአጼ ምኒልክ እንደራሴ ሆነው በተሾሙት በራስ መን
ገሻ የበላይነት ትግራይ መጠነኛ ሰላም እየሰፈነባት ሔደች።

ጣሊያኖችም ከራስ መንገሻ ጋር ባደረጉት ምሥጢራዊ
ወዳጅነት ሳቢያ፣ ትግራይ ገብተው የሕዝቡን ተቀባይነት ለማግ
ኘት በነበራቸው ዘዴ ለሕዝቡ እህል በነጻ ማደል ጀመሩ። አጼ
ምኒልክ ደግሞ ነገሩን ደረሱበትና ጣሊያኖች በነጻ እያደሉ
ካሉት እህል ዋጋውን ዐሥራ ስምንት ሺህ የማሪትሬዛ ብር
በመክፈላቸው፣ ከጣሊያኖቹ ይልቅ የምኒልክ ስምና ቸርነት እየ
ተጋነነ ሔደ።

ከዚያ ተዋው ደግሞ አጼ ምኒልክ ለራስ መንገሻ 'የንጉሥነት ማዕረግ ሊሰጣቸው ነው' የሚል ወሬ ከአዲስ አበባ አፈትልኮ መቀሌ ስለገባ ፣ ሕዝቡ ፣ 'ዕርቅ ሆነ ሰላም ወረደ' እያለ ደስታውን በማስተጋባቱ ፣ ራስ መንገሻ ወደ አዲስ አበባ ለመሔድና ታማኝነታቸውንና ታዛዥነታቸውን ለማረጋገጥ የማሰባቸውና የመዘጋጀታቸው ወሬ ደግሞ ፣ በተራው ከትግራይ ዋና ከተማ ገሥግሦ ሸዋ ዋና ከተማ ገባ ።

በራስ መንገሻ መሪነት የትግራይ መኳንንት አንድነት መጠንከሩ ራስ አሉላን ቢያስደስታቸውም ቅሉ ፣ ወደ ሸዋ ሔደው ለምኒልክ እጅ መንሣታቸውን ደግሞ የማይደግፉት ሐሳብ ሆነባቸው ። የመንገሻ ሐሳብና ዕቅድ ደግሞ ከአሉላ የተለየ ሆነ ። 'አጼ ምኒልክ ለራስ መንገሻ የንጉሥነት ማዕረግ ሊሰጡ አስበዋል' የተባለው ወሬ መንገሻን እጅግ አጓጉቷቸዋል ፣ ምክንያትም ነበራቸው ። የአጼ ዮሐንስ ወራሽ ሆነው የቀረቡ ያም ቀርቶ የአጼ ምኒልክ እንደራሴ የሆኑት መንገሻ ከትግራይ መኳንንት ጋር በእኩልነት ደረጃ 'ራስ' እየተባሉ መጠራቱ ሰልችቷቸው ነበር ። ምንም እንኳ የልባቸውን አፍረጥርጠው መናገሩን ባይደፍሩትም ፣ ወደ ሸዋ የመጓዛቸውን ነገር እንደ ገና ለአደራ አባታቸው ማስረዳቱን አመኑበትና ኩርፊያው አብቅቶ ምክክሩን ሲጀምሩ ፣

"እዩ ጌታ ወደ አጼ ምኒልክ ለመሔድ ያሰብኩትኮ ስለ አገሩ ስለ ሕዝቡና ስለ ሁላችንም ደህንነት ስል ነው ። አጼ ምኒልክን ያህል ሰው እዚህ ድረስ መጥቶ 'ጥፋትህን ምሬሀለሁ ብሎ እንደራሴዬ ሁን' ብሎ ይህን ያህል ሹመት ሲሰጠኝ ፣ እኔ ደግሞ በተራዬ ከዙፋናቸው ቀርቤ ማመስገንና ደስተኛነቴንም መግለጽ ይገባኛል ። ይህን ካላደረግሁ ደግሞ ያላሰብነውን አስበው ይጠሉናል" አሉ ራስ መንገሻ ።

"ዘውዱና ዙፋኑኮ ያንተ ነበር ። የዮሐንስ ወራሽኮ አንተ ነበርክ ፤ ይኸ ይበዛብህ?" አሉ ራስ አሉላ መንገሻንም ጉዞአቸውንም በንቀት እያዩ ።



"አልሆነማ ጌታ አልሆነምኮ ፤ እያወቁት? ያገሬ መኳንንትና የሥጋ ዘመዶቼ መቸ ለዚያ አበቁኝ ፤ እርስ በርሳችን አይደለም የተናከስነው?!" አሉ ራስ መንገሻም ሆድ በባሰው ስሜት ።

"እርሱማ አሁንስ የትግራይ መኳንንት መች ተኙልህ ይኸውና ስብሐትስ አጋሜን አሳድሞ ያስቸግር የለምን? ታዲያ እርሱ 'መጣሁ መጣሁ' እያለ ያንተ ወደ ሸዋ መሔድ ምን ይሉታል? ፍርሃት አይመስልብህም? አገሩንስ ለማን ሰጥተኸው ነው እምትሔደው?" አሉ ራስ አሉላ ።

"እርስዎና ራስ ሐጎስ አላችሁ አይደለም?"

"እኔንም አጼ ምኒልክ አልፈለጉኝም ። እኔን አገር ጠባቂ አድርገህ ሸዋ ብትሔድ ነገሩ ይበላሽብሃል ። ራስ ሐጎስን አደራ ብለህ ብትሔድ ደግሞ አልጋህን ይዞ እንደ ወጣህ ቅር ይልሃልና የዛሬው መንገድህ አይታየኝም" አሉ አሉላ ።

ምክሩ ከልባቸው የገባ መሆኑን ራስ መንገሻ አንገታቸውን ደፋ ቀና እያደረጉ ገለጹላቸውና ፣

"እንግዲያውማ ስብሐትን እንግጠምና እርሱን ድል ካደረግን በኋላ ብሔድ ይሻላል?" ብለው ጠየቁ ።

"ይኸማ ያምራል ፣ ይገባል ፤ ሥርዓቱም ይኸው ፤ ነው ። ተፎካካሪን ድል ነሥቶ ወደ ንጉሥ ሲቀርቡ ግርማ ሞገስም ይደምቃል" አሉ ራስ አሉላ ።

"ይሁና እንግዲያው ፤ ለራስ ሐጎስም እንላክባቸውና የሽሬን ጦር ይዘው ይምጡና ስብሐትን እንግጠመው" አሉና ራስ መንገሻ ነገሩ በዚሁ ተቋረጠ ።

ሦስቱ ራሶች እንደ ገና በአንድነት ሆነው ፣ ከአንድ ደጃዝማች ጋር ጦርነት ለመግጠም ተሰለፉ ። ስብሐት ወደ ኤርትራ ፣ እንዳይገቡ ወይም ከኤርትራ በኩል መሣሪያ እንዳያስገቡ ፣ በዚያ ጊዜ የኤርትራ ጠቅላይ ገዥ ሆኖ አዲስ ተሹሞ ለመጣው ፣ ለጀኔራል አንቶኒዮ ጋንዶልፊ ፣ ጻፉለትና ደጃች ስብሐትን ለመውጋት ዘመቱ ። ስብሐትም ፣ የሦስቱን ራሶችና የራሳቸውንም

ኃይል አመዛዝነው ፡ እጋሚ ውስጥ ምቹ ቦታ ይዘው አደፈጡ እንጂ በግልጽ ወጥተው ጦርነት ለመግጠም አልፈለጉም ነበር ። ራስ መንገሻም ስብሐትን ድል ሳያደርጉ ወደ ሸዋ መሔዱ የማያስተማምን በለሆነባቸው ፡ ትግራይ ውስጥ መቆየት ግድ ሆነባቸው ። ከደጃዝማች ስብሐት ጋር የተጀመረው ጦርነት ቀልጥፎ ያለቀ እንደሆነም መንገሻ ወደ ሸዋ የሚሔዱባቸው መሆኑን የተገነዘቡት አሉላ ደግሞ ጦርነቱ ፈጥኖ እንዳያልቅ ባቸው በለዘብታ ያዙት ።

አንቶኔሊና ሣሊምቤኒ የተባሉት የኢጣሊያ መልእክተኞች ከራስ መንገሻና ከራስ አሉላ ጋር በምሥጢር ተገናኝተው ዕርቅ እድርገው ፡ ሁለቱ ራሶች ከአጼ ምኒልክ እንዲያፈነግጡላቸው የተዋዋሏቸውን ያህል አባብለው እዋጋቢ መልስ ካጡበት በኋላ፣አዲስ አበባ ገብተው በአጼ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ብቅ ማለት መጀመራቸውን ራስ መንገሻ ከሰሙ በኋላ ደግሞ ፡ ከፍ ተኛ ሥጋት እያደረባቸው ሔደ ።

እርሳቸውን ከምኒልክ ጋር ለማስያየት ያደረጉት ሙከራ ያልተሳካላቸው ጣሊያኖች ፡ ይህን ያልሆነውን ቀባብተውና ጠን ጅለው ሌላ ርምጃ እንዳያስወስዱባቸው ስለ ሠጉ ፡ ከደጃች ስብሐት ጋር የነበራቸውን ፍጥጫ በሰላም ጨርሰው ወደ ሸዋ ለመሔድ ወሰኑ ።

ግን ፡ ይህን ሐሳባቸውን ለራስ አሉላ ቢነግሩ እንደሚታ መሙቸው በግልብ ነገሩን በምሥጢር ይዘው ፡ ሽማግሌዎች መርጠው ፡ “ወደፊት እኔ የሆንኩትን ይሆናል ፡ ለዛሬው ደግሞ ከግዛቱ ላይ ሌላ እጨምርለታለሁ ፡ እኔ ከፍ እያልኩ ስሔድ እብ ሮኝ ያድጋል” ብለው ላኩባቸው ። በዚያ ጊዜ ደግሞ ፡ ‘ንጉሥ ሊባሉ ነው’ እየተባለ ይወራ ነበርና ደጃች ስብሐትም በነገሩ ተስማምተው ዕርቅ ሆነ ። ከዚያ በኋላ በመላው ትግራይ ሰላም መስፈኑን ፡ ሕዝቡ መረጋጋቱን ካረጋገጡ በኋላ ፡ ወደ ምኒልክ ግቢ ቢሔዱ ምግስ የሚያገኙበትና የንጉሠ ነገሥቱም ተጸግቶ ባለ ሟል ሊሆኑ እንደ ጊቻሉ ተማምነውበትና ፡ ከአጼ ምኒልክ ራት ሊቀርቡ የሚያበረክቱትን ገጸ በረከት ማዘጋጀት ጀመሩ ።



‘ይህ ጅል የገድ ካስበራችሁኝ ብሎ ነው ካልሔድኩ እያለ የሚጨነቀው?’ አሉ ራስ አሉላ የመንገሻን መዘጋጀት ሰም ተው ። ‘እኔ እንኳ መሰለው! ግን ይሙት የኖሐንበን እልጋ ወራሽ ሸዋ ይዞ ይሰቃል! ራስህን ችለህ ግዛ ቢባል የገድ እሽ ከር ልሁን ብሎ ይሔዳል’ ብለው ራስ አሉላ ራስ መንገሻ ወደ ሸዋ እንዳይሔዱባቸው ለማደናቀፍ የ ሚያስችላቸውን ዘዴ ማውጠንጠን ጀመሩ ።

በመካከሉ የኢጣሊያ ንጉሥ ኡምቤርቶ በምዕዋ በኩል ለአጼ ምኒልክ የላኩት አራት መቶ ምርጥ ምርጥ ጠመንጃ ዐድዋ መድረሱን ራስ አሉላ እንደሰሙ ገሥግሠው ደረሱና ወረሱት ። የሰጡትም ምክንያት ፡ ‘ደጃች ስብሐትን እከላከልበታለሁ ። እርሱን ድል ካደረግሁ በኋላ እመልሰዋለሁ’ ብለው ነበር ።

ነገሩ የገባቸው አንድ የዐድዋ ነዋሪ አዛውንት ቃሲስ ፡ ‘የጉብዕ ፡ የድርቡሽና የጣሊያን ጦር ጭና ያመጣው መንገድ ያልበታቸው አሁን ማይሙት የምኒልክ ዕቃ ቤት ይመልባቸ ዋል ተብሉ ይታሰባል!’ ብለው አሽሟጠጡቸው ። አዛውንቱ እንዳሉትም ከአሉላ እጅ የገባው ጠመንጃ መመለሻው ራቀ ። ቀጥለው ደግሞ የአጼ ምኒልክ ታማኝ የነበሩትንና ከአሥመራ ወደ ሸዋ ለመሔድ በጉዞ ላይ የነበሩትን ደጃች መሸሻ ወርቄን ለመያዝ ማሳደድ ጀመሩ ። መሸሻም ዐድዋ አካባቢ እንደ ደረሱ ነገሩን ሰሙና ወደኋላቸው ተመልሰው አሥመራ ገቡተው ‘አሉላ ለአጼ ምኒልክ አልገዛም ብሉ ሸፈተ’ ብለው ለጣሊያ ኖቹ ነገሩ ። አሉላ ለስምንት ያህል ዐድዋንና መቀሌን እተራገ ምሰው ወደ ተንቤናቸው ሔደው እደበው ተቀመጡ ።

በዚያን ጊዜ ትግራይ ውስጥ የነበረ መርካቴሊ የተባለ የኢጣሊያ ጋዜጠኛ አሥመራ ተመልሶ ለጣሊያን ወታደሮች ሲያወራ ፣

“እንደ እውነቱ ከሆነ የትግራይ ዋናው አለቃ አሉላ ናቸው ። ይህን ማረጋገጥ የ ሚቻለው ደግሞ ለጥቂት ቀናት ያህል ትግ ራይ በመቀመጥ ነው ። ንጉሠ ነገሥቱ መተማ ዘምቱ በኋላ ፡

'የሐንስ ይሙት' የሚባለው ግረጋገጫ ቀርቶ 'ራስ ይሙ
ተብሎ ተተክቷል ። እኔህ ሰውዬ ከምቴ ትግራይ ምስቅልቅ
ይወጣል ። አሁንም ቢሆን ትግራይ ደካማ ናት ። ግን የአሉ
ዋንካሬና ቆራጥነት በሁለት እግሩዋ ቀጥ አድርጓታል" ብሏል

ኢጣሊያዊው ጋዜጠኛ ፣ የራስ አሉላ እንግዳ ሆኖ በትን
መንደራቸው ለጥቂት ቀናት ሰነባብቶ ነበርና የብቸኛው ኑሮ
ቸውን ጉዳይ አንሥቶ ለጓደኞቹ ሲያጫውታቸው ፣ "በቤታቸ
ውስጥ ከቤቷ ልጃቸው በቀር ሌላ ሴት አልነበረችም ። ባለቤ
ቸው ከሞቱባቸው ወዲህ ይህ ደካማ ባሕርይ አሉላን እንዳላ
ነፋቸው የነፍስ አባታቸው አጫውተውኛል" ብሏል ።

አጼ ምኒልክ ትግራይ ደርሰው ፣ ሹም ሽር አድርገው ከ
መለሱበት ጊዜ ጀምሮ ፣ ራስ አሉላ በሁለት ምክንያቶች የተን
ጠጠር ያለ ቅሬታና ብቸኝነት ተሰምቷቸዋል ። ከተራ ኑሮ አ
ሥተው ከዚያ ደረጃ ካደረሱዋቸውና ከሚወዷቸው ከአጼ ዮሐን
ቤተ መንግሥት ምኒልክ ሰተት ብለው ገብተው ከዙፋናቸ
ላይ በመቀመጣቸው አሉላ እጅግ ተናደዋል ፤ ተከዘዋል ። ተ
ለው ደግሞ በጉራዕ ፣ በኩፊት በተድዓሊና በሌሎቹም በታ
ጦርነት እየገጠሙ ድል ሲነሡ የኖሩትን ስመ ጥር ጀኔራ
አጼ ምኒልክ ለሙያቸው ክብር ሰጥተው ልዩ መልእክተ
ልከው ፣ "እኔ ካሉበት ድረስ እንዳልመጣ መስተንግዶው ይከ
ድዎታል ብዬ ነው ። እርስዎ የሚመጡ ቢሆን ደግሞ በደስ
በክብር ልቀበልዎ ዝግጁ ነኝ" ብለው ላኩባቸው ።

እንደ ሌሎቹ መኳንንት ፈጥነው ሔደው እጅ ነሥተው ሚ
ሰመው ሹመት ለመቀበል ደግሞ ልቡ—ኩሩነታቸው አል
ደላቸውም ። ሸዌው ንጉሠ ነገሥት ትግሬውን የጦር ሰው በ
ታቸውና በዘዴያቸው ባለማሸነፋቸው ሆድና ጀርባ ሆኑ ።
አሉላ አጼ ምኒልክን ከልባቸው ያከብሩዋቸው ስለነበሬ ፣ ተድ
ላይ ከጣሊያኖች ጋር ጦርነት ገጥመው ድል እንዳደረጉ የ
ራቹን ለአጼ ዮሐንስ ሲልኩ ለንጉሥ ምኒልክም በደብዳቤ
ታውቀዋቸው ነበር ። ምኒልክ ግን መልስ አልሰጧቸውም
ታዲያ እነዚህ እነዚህ ሁሉ ተደማምሩና አሉላን አስኮረፉ



'ለምን በምኒልክ እንገዛለን! ለምን የዮሐንስ ልጅ አይገዛም!' አሰኝተው አናገሩዋቸውና 'እሻፈረኝ' ብለው ተነሡ ።

እንደዚያ ሆነው ምኒልክን ጠልተው ፣ ከመንገሻ ርቀው ፣ ከትግራይ መኳንንት ጋር ተጋጭተው ፣ አዝነውና ተከዘው በነበረበት ሰዓት መርካቴሊ የተባለ ጣሊያናዊ ጋዜጠኛ ሊያነጋግራቸው ሔዶ ስለ ነበረ ተቀብለው ሲያነጋግሩት ፣

"ወደዚህ የምትመላለስበት ዋናው ምክንያትህ ምንድን ነው?" ብለው ጠየቁት ።

"እገርዎን ጉብኝቼ ፣ ታሪካችሁን ለሀገሬ ሰዎች ለማስተዋወቅ ነው" አላቸው ።

"የኛን ታሪክ መውሰድ ብቻ ሳይሆን ፣ ያንተንስ ሀገር ታሪክ ለምን አትነግረንም?" ብለው ፈገግ አሉስትና ቀጠል አድርገው ደግሞ ፣

"አገሬን ሐማሴንን የያዙት ወገኖችህስ ሐሳባቸው ምንድን ነው? ሸዋ ገብተው ከምኒልክ ጋር ወዳጆች እንሁን እያሉ ይወተውታሉ ፣ ነገርም ይጐነጉናሉ ። በዚህ በኩል ደግሞ ጦር ጭነው ገብተው አገር ይዘዋል ። እንዲያው ዋናው ምኞታቸው ምን ይመስልሃል!" አሉት ።

"እርስዎንና ራስ መንገሻን ለመርዳት ፣ የምትፈልጉትንም ለመስጠትና አገራችሁን ለማልማት እንደሚጥሩ ዐውቃለሁ" አላቸው ።

ራስ አሉላ ጋዜጠኛውን ትኩር ብለው ተመለከቱት ። የሐማሴን ገዥ በነበሩበት ሰዓትም ይህንኑ የመሰለ አነጋገር ከግሊ ምቤኒና ከፒያና እንደሰሙት ሰምተው ነበር ።

"እየህ ወዳጄ" አሉና ራሳቸውን እያወዛወዙ ቆይተው ንግግራቸውን በመቀጠል ፣ "ስማህ ወዳጄ! አሁን የተናገርከውን ነገር ወገኖችህም ደጋግመው የተናገሩት ነው ። ግን ወዳጆች እንሁን እያላችሁ ገብታችሁ አገር ስትይዙ ነው የምናያችሁ..." ብለው ዝም ሲሉ ጋዜጠኛው ጣልቃ ገባና ፣

"ያለፈው ፀሐፊ ከእንግሊዝ ወዲያስ ወዳጅነታችንን አይፈልጉትም?" አላቸው ።

"በራትም ቢሆን የኔ ጥፋት አልነበረም ፤ ከእንግሊዝ ወዲያም ወዳጅነትን የምጠላ አይደለሁም ። በአሁኑ ወቅት ደግሞ የኔም ምክሬም ጠላት በዝተውብናል ። አጼ ምኒልክ ደጃዝማች መሸሻ የሚባል ተንኮለኛና መሠሪ በመካከላችን አስገብተውብናል ። እርሱም በኔ ላይ ክፉ እንዳስበና እኔን ለመበደል እንደጣረ ነው ። እኔም ሆንኩ አገሬ በሁለት እሳት መካከል ገብተናል ። እስከ ዛሬ የገጠምናቸው ጦርነቶች ፣ የከብቱ በሽታና ረኃቡ በጣም ጎድተውናል ። ከእንግሊዝ ወዲያ ዕረፍትና ሰላም እንፈልጋለን ። ሀገራችንን ካልተመኛችሁብን ወዳጅነታችሁን እንቀበላለን ። አገር እናልማ ስትሉ ግን ፣ በእውነት አስባችሁ ከመጣችሁ ደስ ይለናል ። አገር ቢለማ ፣ ንግድ ቢስፋፋ እንደግፋለን ። ይህን ሁሉ አንተ ልትጨርስልን ትችላለህ?" አሉት ።

"መቼም ይህንኑ ሐሳብዎን በጋዜጣ አጽፈውና ሕዝቡ እንዲያውቅ መንግሥታችንም እንዲጠነቀቅ አደርጋለሁ" ብሏቸው ወደ አሥመራ ተመለሰ ።

በዚያው ሰሞን ደግሞ ፣ ከራስ መንገሻ ጋር ወደ አፄ ምኒልክ ለመሔድ ከአሥመራ ገሥግሠው ፀድዋ ሲደርሱ ራስ አሉላ የቆዩባቸው መሆኑን ሰምተው እንደገና ወደ አሥመራ ፈርጥጠው የነበሩት ፣ መሸሻ ወርቄ ፣ ወደ መቀሌ እንዲመለሱና አብረዋቸው ወደ አዲስ አበባ እንዲጓዙ ራስ መንገሻ ያደረጉት ጥረት ተሳክቶላቸው ፣ ራስ አሉላ እንዳይሰሙ በከፍተኛ ጥንቃቄ መቀሌ ደረሱ ። ግን ፣ ራስ መንገሻ ደግሞ ወደ አጼ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ለመጓጓዝ የነበራቸውን ዕቅድና ዝግጅት ችላ ብለውት ነበር ። ምክንያታቸውም በአጼ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ባለሟሎች የነበሩት አንቶኔሊና ግሴቢኒ የፈጸሙት ስሕተት ደግሞ በኢትዮጵያና በኢጣሊያ መካከል የነበረውን ወዳጅነት ማቀዝቀዙን ስለ ሰሙ ነበር ።

ይህንም ነገር መንገሻ ከራሳቸው ቄጽም ጋር ማገናዘብ ጀመሩ ። ከኢጣሊያ ጋር መነጋገሩና መዋዋሉ የበለጠ ራሳቸውን የመቻልና



የመጠናከር ዕድል ሊያስገኝላቸው እንደሚችልና ፣ ራስ አሉላ የለገሱዋቸውም አስተያየት ሊያጠግባቸው የሚችል እንደሚሆን አመኑበት ። በዚህም ንዋያቸውን ማዘጋጀት አንድ ፍንጭ ሊያገኙበት እንደሚችሉ ተማመኑበት ።

በዚያ ላይ እንዳሉ ደግሞ በእምባ ሰላማ ታስረው የነበሩት የራስ ወልደ ሚካኤል ትንሹ ልጃቸው ኃይለ መለኮት ከእምባው አምልጠው አሥመራ ሲገቡ ፣ በእምባው ዕቃ ቤት የነበረውን በርካታ የጦር መሣሪያና እህል በማግኘታቸው የተደሰቱት ደበበ አርአያ እንደገና ዐመፁ ። በዚህ ጊዜ ከራስ መንገሻ ጋር እርቅ አድርገው የነበሩት የሐጋሜው ገዥ ደጃች ስብሐትም ደበበን ለመደገፍ መዘጋጀታቸው ተሰማ ። ስብሐትና ደበበ ከተገናኙና በአንድነት ከተሰለፉ ደግሞ ፣ የኢጣሊያ እንደራሴ ሆነው አካለ ጉዛይን ሲገዙ የነበሩትን ባሕታ ሐጎስን ጦርነት እንደሚገጥሙና አሸንፈውም አገሩን ለመያዝ እንደሚችሉ የተማመኑት ስብሐት ፣ አካለ ጉዛይ ውስጥ የነበሩት የደበበ ደጋፊዎች ሁሉ በአስቸኳይ ደበበ ወደነበሩበት እምባ እንዲገሠግሡ አደረጉ ።

ቀጥሎ ደግሞ የጥጀራቱ ገዥ ደጃች ተድላ ዋህድና ደጃች እምባዬ በራስ መንገሻ ላይ የመነሣሣታቸው ወሬ መቀሌ በሰ ደረሰ ፣ የራስ መንገሻም ጉዞ እየተሰናከለ ትግራይም እንደገና ወደ በደድ እሳትነት እየተሸጋገረች መሔድ ጀመረች ።

ራስ መንገሻ የተነሣሣባቸውን ዐመፅ ብቻቸውን ሊደቁሙት እንደማይችሉ በመረዳታቸው ራስ አሉላን ከተንቤን አስጠሩ ። ምንም እንኳ አሉላ ሊይዟቸው ቢመኙም ፣ መሸሻ ወርቄም ከራስ መንገሻ አስፈቅደው ወደ ሸዋ ተጓዙ ።

ሁለቱ ራሶች እንደገና ለትግራይ አንድነትና ሰላም ተሰለፉ ። ሕዝቡም እንዲከተላቸውና በሁለቱም መካከል ፍቅርና ሰላም እንጂ ቅያሜ ያለመኖሩን ለማረጋገጥ ሲሉ ፣ ዐድዋ ገበያ ላይ ሁለቱም በአንድነት ቆመው ለሕዝብ ታዩ ። ዐማፅያኑም አስነገኑ ።

በእምባ ሰላማ የተነሣው ዐመፅ ደግሞ እየተጋጋለ ሔደ ። የእምባው አውራሪብ ሆነው የተነሡት ደበበ ፣ ታማኞቻቸው ያቀ

በሉዋቸውን አርጌ መድፎች ጠምደው ፣ የመንገሻንና የአሉላን ጦር ማጥቃት ጀመሩ ። የእርሳቸውን ማመፅና የመድፍ ባለቤትነት የሰሙት ሌሎች የትግራይ መኳንንትና የመንገሻ ተቃዋሚዎች ደግሞ መቀሌን እንዳይዙ ለመከላከል ፣ መንገሻ ወደ ዋና ከተማቸው ሲመለሱ ፣ አሉላ ታማኞች ወታደሮቻቸውን ብቻ ይዘው ጦርነቱን ቀጠሉ ።

በአሉላ ወታደሮች የተከበቡት ደበበ ፍጻሜያቸው እንደማያምር ከተረዱት በኋላ ከሉበት ቦታ እንዲወጡና በሠራዬ ፣ በአካለ ጉዛይና በአማውርታ ላይ የነበራቸውን ሥልጣን እንዲያጸድቁላቸው ወደ ራስ መንገሻ አማላጅ ላኩ ። ይህ ጥያቄያቸው ደግሞ አሥመራ ስለ ተሰማ ፣ በጣሊያኖቹ በኩል ያልታሰበ ዱብ—ዕዳ ሆነ ፤ በጣሊያኖቹ ላይ ያስከተለው ሥጋትም ፣ 'የደበበን ጥያቄ መንገሻ ከተቀበሉ ፣ ትግራይንና ኤርትራን ማቆራኘት ብቻ ሳይሆን ፣ የአጼ ምኒልክንም እግር ሊያስገባ የሚችል ስለሚሆን ፣ ሦስቱ የትግራይ ዋልታዎች ፣ ማለትም የደጃች ሰባጋዲስ ፣ የራስ አርአያ ድምፁና የአጼ ዮሐንስ ወራሾች የሚያደርጉት ኅብረትና ውል አደገኛ ስለሚሆን ማፈራረስ አለብን' የሚል ነበር ።

ምንም እንኳን ከኢጣሊያኖቹ ጋር ባይነጋገሩበትም ቅሉ ፣ ራስ መንገሻ ከሰባጋዲስና ከአርአያ ልጆች ጋር የጀመሩት ኅብረት እነርሱንም የሚጐዳቸው መሆኑን ስለአመኑበት ፣ ኅብረቱን ራስ አሉላ ራስ ሐጐስና ራስ ወልደ ሚካኤልም ተቃወሙት ፤ በተጨማሪ ደግሞ ፣ ደበበ የራስ አሉላን እጅ እንዲያበረክቡዋቸው ራስ መንገሻን በምሥጢር መጠየቃቸውን ራስ አሉላ ስለ ደረሱበት ፣ የመሳፍንቱን ሹክሹክታ በጥብቅ ይከታተሉት ጀመር ። የመኳንንቱን ትርምስ በጥብቅ ሲከታተሉ የነበሩት ጣሊያኖች ደግሞ ፣ "ከእንግዲህ ወዲያ የያዝናትን 'ኤርትራን' ከኛችን እንዳትወጣ ሊረዳን የሚችለው የራስ አሉላ ሁኔታ ብቻ ስለሆነ ፣ ወደ መንገሻ ክበብ እንዳይገቡ ማድረግና ማባባልም ይገባናል" ከሚል ውሳኔ ላይ ደረሱ ። ይህንኑ ውሳኔያቸውን በሥራ ለመተርጐም ሲሉም የጣሊያኑ ጦር አዛዥ ለጦር አለቆቹ ፣ "ራስ አሉላ በጠቅላላው የአውሮፓውያን በተለይም የኛ ብርቱ ጠላት



መሆናቸው አይካድም ። ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ኢጣሊያ 'በኤርትራ' ላይ ያላትን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ የምትችለው እሳቸውን ሰውቆ በማቅረብና በማቀፍም ነው ። በዚህ ረገድ ከፍተኛ ዋጋ የሚኖረው ውጤት ሊያስጨብጡ ይችላሉ ። ደበበንም የሸዋ ደጋፊዎች የሆኑትንም ሁሉ በመቃወም ላይ ስለሆኑ ፣ ፈጽመው ሊያጠፏቸውም እንደሚችሉ ይተማመናሉ ። መንገሻን ከምኒልክ ጋር ለማስተባበር የሚጥሩትንም ይቃወማሉ ። ስለዚህም ያለፈው ተረስቶ ወዳጅነትና ስምምነት ብንመሠርት ይሻላል" ብሎ አስረዳ ።

የትግራይ ሁኔታ በዚህ ገጽ ይታይ በነበረበት ወቅት ደግሞ ፣ 'የኤርትራን ጉዳይ' የሚያጠና ቡድን ከሮም ተልኮ አሥመራ ሲገባ ፣ የትግራይን መኳንንቶች ፍጥጫና ጠብ ሲያጠና የነበረው ጋዜጠኛ ሜርካቴሊ ፣ ከዐድዋ ወደ አሥመራ ተጠራና ከቡድኑ ጋር ሆኖ እንዲሠራ ተመደበ ። ከሮም የተላከው ቡድን በምሥጢር ከትግራይ ራሶች ጋር የሚገናኝበትን ዘዴ ፡ በዚያን ጊዜ ዐድዋ ተቀማጭ ከነበረው ዶ. ማርቲና ከሚባለው ጣሊያን ጋር ሆኖ እንዲያከናውን ታዘዘ ። በዚያን ጊዜ ኢጣሊያኖች ያመኑበትም ጉዳይ በትግራይ ውስጥ እግራቸውን ማስገባቱን ለጊዜው ገታ በማድረግ ፣ የመረብ ወንዝ ወሰን ሆኖ ፣ 'የኤርትራ ቅኝ ግዛትነታቸውን' የትግራይ መኳንንቶች አምነው እንዲቀበሉላቸውና ይህንንም በውል እንዲያጸድቁላቸው መለመን ነበር ።

ማንኛውንም ነገር እንዲያዘጋጅና ስብሰባውን ተግባራዊ እንዲያደርግ ጋዜጠኛው ሜርካቴሊ ከአሥመራ ወደ ዐድዋ ተላከና ራስ አሉላ ከኢጣሊያኖቹ ጋር እንዲገናኙለት ጠየቃቸው ። ምንም እንኳን አዲስ የተጀመረው የራስ መንገሻና የደበበ ኅብረት ቢያሳስባቸውም ቅሉ ፣ ከኢጣሊያ መልእክተኞች ጋር ለመገናኘትና ለመዋዋል ፈጥነው መልስ አልሰጡትም ነበር ። እርሱም የተላከበትን ተግባር በሥራ ላይ ሳያውል ወደ አሥመራ ፈጥኖ መመለሱን አልወደደውም ነበርና እዚያው ዐድዋ ሰነባበተ ።

የእርሱን ሙጭጭ ብሎ መቀመጥ ለመገላገል ሲሉም አሉላ ጋዜጠኛውን አስጠርተው ፣

“ከመጀመሪያው ጀምሮ የነገርኩኝ ነገር ማስፈታ ነው ብየ የለው። ይሁን እንጂ፣ በአሁኑ ወቅት እጅግ አስቸጋሪ ከሆነ ሁኔታ ላይ በመድረሳችን ነገሩን ከጌታቹና ከስሉጮም ጋር መወያየት አስፈላጊ ሆኗል። የመልእክተኞቹ ዋናው ኃላፊ ስለኛ ጉዳይ ለመነጋገር ፈቃደኛ ከሆኑ እኔም ለመነጋገር ፈቃዱ ነው። ግን ሁኔታውን ለራስ መንገሻ አስታውቄ መልስ እስካገኝ ድረስ ታገሡኝ” አሉት። ራስ አሉላ ሁኔታውን አብራርተው እንዲያስረዱ ደጃች ወልደ ጊካኤልን ወደ ራስ መንገሻ ላኩዋቸው። ራስ መንገሻም በበኩላቸው፣ ጣሊያኖቹ ኤርትራን እንደያዙ ለጊዜው እንዲቆዩ የሚሰጣቸው መሆናቸውንና ስለ እርሳቸውም ሆነው ጣሊያኖቹን እንዲያነጋግሩ ላኩባቸው። ይሁን እንጂ ምንም እንኳን ራስ አሉላ ከኢጣሊያኖቹ ጋር እንዲነጋገሩ በፈቃዳቸውም ቢሉ፣

“የሚሉትን ሰምተው ይላኩብኝ፤ ሐሳባቸውን ካወቅሁ በኋላ መልሴን በወረቀት አስታውቃለሁ” የሚል ውሳኔም ወስነው ሰደዋል።

የትግራይ መኳንንት የሚጐተጐቱዋቸው ራስ መንገሻ፣ ደበበ ከጣሊያን ጋር እንዋጋ በሚሉበት ወቅት የጣሊያን የመረሩ ጠላት የነበሩት አሉላ ደግሞ ከጣሊያን ጋር እንነጋገርና ሐሳባቸውን እንወቀው ብለው ስለላኩባቸው ከሁለቱ የማንኛቸውን ሐሳብ በመቀበል ማስላሰል ጀመሩ። ከመረብ ማዶ ሆነው ሁኔታውን ሲከታተሉና ሲጠባበቁ በነበሩት ጣሊያኖች መካከልም ተመሳሳይ የእርስ—በርስ ንትርክ ተጀመረ። ራስ አሉላ ከኢጣሊያ መልእክተኞች ጋር ለመነጋገር የፈለጉት በዐድዋና በመረብ ወንዝ መካከል በሚገኘው ዓዐር ተክላይ በተባለው ሥፍራ እንዲሆን ለጋዜጠኛው ጣሊያን ነግረውት ስለነበረ፣ ከርም የተባ ከው የመልእክተኞች ቡድን መረብን ተሻግሮ ወደ ትግራይ ለመግባት ሲዘጋጅ የኤርትራ አገረገዥ የነበረው ጋንዶልፊ ደግሞ፣ “የትግራይ ተጠሪና ዋናው፣ ራስ መንገሻ ናቸው እንጂ አሉላ አይደሉም። እናንተም የኔን ኃላፊነትና ሥልጣን ችላ ብላችሁ ውስጥ ውስጡን መላላክ አይገባችሁም ነበር። አሁንም እኔ እስቀድሜ ባልወቅሁትና ባልተስማማሁበት ጉዳይ መረብ ምላሹን መሻገር የለባችሁም” ብሎ ወረፋቸው።



በመጨረሻ ደግሞ፣ ራስ አሉላ ለመልእክተኞቹ መሬ ዝንቦ ረው በርትተው፣ “ተያዩኝችሁን ተቀብያለሁ። ለመንግሥቴ ለመነጋገርም ፈቃዱ ነው፣ ለሰላምና ወዳጅነትም ለመመሥረት ዝግጁ ነኝ” ሲሉ ላኩበት። የመረብን ወንዝ ተሻግሮ ከአሉላ ጋር እንዳይነጋገር የኤርትራው አገረ ገዥ የከለከለው በርትኒ ግን፣

“እኔና ጓደኞቼ በጠና ስለ ታመምን፣ ወደ አገራችን መመለስ ባችን ነው። ሰላምታዬን ለራስ መንገሻ እንዲያስተላልፉልኝ እጠይቀዎታለሁ” ብሎ ወደ ኢጣሊያ ተመለሰ። የመልእክተኞቹ ቡድን ኢጣሊያ እንደ ገባ ራስ አሉላ፣ ከመረብ ምላሽ ባለው በትግራይ ውስጥ ብቻ ተገትተው የመረብ ምላሽን ጸጥታ በማስከበሩና ከኢጣሊያም ጋር ዕርቅና ሰላም መሥርተው ለመኖር ፈቃደኛ የሆኑላቸው እንደሆነ፣ ኢጣሊያ በየወሩ አንድ ሺህ ብር ደመወዝ ልትከፍላቸው ፈቃደኛ ሆና እንደ ነበረ፣ አንዱ መልእክተኛ ለጋዜጠኞች በመናገሩና ምሥጢሩም በጋዜጣ በመውጣቱ በዐገሩ ኢጣሊያ ከፍተኛ ቅሬታና ውዝግብ አስነሣ።

አሥመራ በነበሩት የኢጣሊያ ባለሥልጣኖች፣ ዐድዋ በነበሩት ራስ አሉላና መቀሌ በነበሩት ራስ መንገሻ መካከል የነበረው ጉዳይ እንደዚህ ሁኖ ተጠላልፎ በነበረበት ወቅት ደግሞ፣ ደበበ አርአያ ዘራፊዎችን ከተከበቡበት ከአምባ ሰላም አምልጠው የጅራት ገበና ሲጠባበቁዋቸው ከነበሩት ከአምስት መቶ በላይ ከሚሆኑት አሽከሮቻቸውና ከተባባሪያቸው ከደጃዝማች ተድላ ዋህድ ጋር ተቀላቀሉ። ወዲያውም የተከታዮቻቸው ብዛት ከሦስት ሺህ በላይ ደረሰ።

የደበበን ማምለጥ ራስ መንገሻ እንደ ሰሙ፣ ነገሩን ችላ አሉት እንጂ እንደ ተለመደው ራስ አሉላን ድረሱልኝ ብለው አልጠየቁም። ምክንያቱም ከደበበና ከሰባሐት ጋር ዕርቅና ሰላም ከመመሥረቱ፣ ትግራይን በአንድነቱ አረጋግተው ለመግዛት እንደሚችሉ ያመኑበትና የተቀበሉትም ጉዳይ በመሆኑ ነበር። ከዚያ ሌላ ደግሞ በዙሪያቸው የነበሩት አዳዲስ አማካሪዎች የእጨጌ ምኒልክ ደጋፊዎችና የአሉላ ጠላቶች ስለ ነበሩ፣ መንገሻ ወደ ሸዋ ሒደው ለአጼ ምኒልክ ታማኝነታቸውን እንዲያረጋግጡና

የንጉሥነት ማዕረግ እንዲያገኙ የሚወተውቱ እንጂ ፣ የእሱላን ምክር ሰምተው እንዳያፈነግጡ የሚመክሩ ነበሩ ።

ደበበና ስብሐትም ባንድነት ሆነው ለራስ መንገሻ ታማኞች መሆናቸውን አረጋግጠው ራስ አሉላን ግን ከማንኛውም መንግሥታዊ ጉዳይ እንዳያስገቡ አጥብቀው ለመኑዋቸው ። ራስ መንገሻ ግን ፣ የራስ አሉላን መወገድ የማይስማሙበት መሆኑን አስረድተው ፣ ለደበበ ስለ ታማኝነታቸው የደጃዝማችነት ማዕረግ ስለ ፈቀዱላቸው ፣ ደበበና ስብሐት መቀሌ ገብተው ከራስ መንገሻ ጋር አንድነታቸውን በመሐላ አጸደቁላቸው ።

ከዚያ በኋላ ደጃች ደበበ ለኤርትራው አገረ ገዥ ለጋንዶልፊ ፣ የዕርቃቸውን ዋና ነጥብ ሲገልጹለት ፣ "እኔና መንገሻ ስንታረቅ ሁለታችንም የነገሥታት ልጆች እንደ መሆናችን መጠን አሉላም የኛ አሽከር እንዲሆን እንዲያገለግለን ነው" ብለው ላኩለት ።

አሉላ ደግሞ ይህንኑ የመሳፍንት አንድነት አጥብቀው መቃወም ጀመሩ ። እርሳቸውን ያገለለ ማኅበር ፣ የእርሳቸውን ማንነት የናቁ ማኅበርተኞች ስምምነት አደረጉ ። ደግሞ ፣ ደጃች ደበበ የሠራዊቱን ፣ የአክለጉዛይንና የአማውርታን ግዛት የትግራይን መኳንንት አስተባብረው ለመውጋት ጣሊያኖችንም ለመቃወም እንደሚፈልጉ ለማኅበርተኞቻቸው አረጋገጡ ። አሉላ ደግሞ ይህን እንደ ሰሙ ፣ "የእኛ አንድነትና ጉልበት ሳይጠነክር ጣሊያኖችን ጦርነት መግጠም በትግራይ ብቻ ሳይሆን በመላ ኢትዮጵያ ላይ ጠቅላላ ጥፋት ያመጣል" ብለው የመሳፍንቱን ኅብረትና ዓላማ ተቃወሙትና የመሳፍንቱን አንድነት ለመበታተን ቢሉ ጦራቸውን አስከትተው ሰተት ብለው መቀሌ ሲደርሱ ፣ የሃይማኖት አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎችም በጉዳዩ ገቡበት ። ሦስቱንም ለምነው አስታረቋቸው ።

ከወጣትነታቸው ጊዜ ጀምረው ሲተናነቁ የኖሩትን አሉላንና ደበበን አስታርቀው ተከታዮቻቸው ለማድረግ የቻሉት ራስ መንገሻ ፣ አዲስ የመሠረቱትን አንድነትና ፍቅር ሕዝቡም እንዲያውቅላቸው ሲሉ ፣ በሁለቱ ተናናቂዎች ታጅበው የትግራይ



አምባርትና መኩሪያ ወደ ነበረችው ዐድዋ ሲገቡ ፣ የሦስቱን አዲስ ማኅበር የተቃወሙት ደጃች ስብሐት ደግሞ ፣ ብቻቸውን አፈንግጠው በግዛታቸው እንደሆኑ የአዲሱን ማኅበር አዲስ ፍሬ መጠባበቅ ጀመሩ ።

ሁለቱ ራሶች ከአንድ ደጃዝማች ጋር ወይም ሁለቱ የነገሥታት ዘሮች አንድ 'ወዲ ቁቢ' አስከትለው ዐድዋ ሲደርሱ ፣ ሕዝቡ የነርሱን ኅብረት ግድነትና የአጼ ዮሐንስን ዘውድ እንዲያስመልሱ ምኞቱን መግለጽ ጀመረ ። በኢጣሊያና በምኒልክ መካከል የነበረው ስምምነት በመደፍረሱ ፣ ትግራይን እንበል ፈላጭ ቆራጭ እንደ ልባቸው ለመግዛት ይመኙ የነበሩት ራስ መንገሻም ፣ 'ከጣሊያኖች ጋር እንስማማ' እያሉ ባለሟሎቻቸው ሲወተውቷቸው የነበረውን ጉዳይ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስቡበት ብቻ ሳይሆን የሚገፋበት እንደሚሆን ፣ አዲሱን ማህበራቸውን ለሚመርቁላቸው ሁሉ ያረጋግጡ ጀመር ።

ራስ መንገሻ ወደ ኢጣሊያ በመለሱት ገጽታቸውና ፈቃደኝነታቸው ላይ ደጃች ደበበ ሲጨመሩ ደግሞ ፣ ምን ሊመስል እንደሚችል የአዲሱን አንድነት እርምጃ በየዕለቱ በልዩ ተመልካቾቻቸው ዐይነ ሕሊና ሲመለከቱት የቆዩት ጣሊያኖችም ፣ 'ሁለቱ ራሶች የኛን ርዳታ ሲያገኙ ከሚችሉበት ወቅትና ምክንያት ላይ ደርሰውልናልና የምኒልክ እጅ ሳይደርስባቸው ማጠናከር ነው' ከሚል ውሳኔ ላይ ደረሱ ።

ሁለቱ ራሶችና ደጃዝማቹ ፣ በአዲሱ ማኅበራቸው ጥላ ለጥቂት ሳምንታት ያህል ተጠልለው ከቆዩ በኋላ ፣ ደጃች ደበበ ከመረብ ወንዝ ማዶ እየተሻገሩ ዝርፊያ በመጀመራቸው እድራጎቱ ከኢጣሊያ ጋር የሚያጣላቸው መሆኑን የተረዱት ራስ መንገሻ ከወረራው እንዲገቱ ደበበን አዘዙ ። ቀጥለውም ብቻቸውን ተኮፍሰው ከግዛታቸው ተቀምጠው የነበሩትን ደጃች ስብሐትን ለመያዝ ሁለቱ ራሶች ተነሡ ።

የሁለቱንም ራሶች ሁለት ውሳኔ ደጃች ደበበ በጥብቅ ተቃወሙትና ንትርክ ተጀመረ ። የአዲሱን ማኅበር ርምጃ በየዕለቱ ሲከታተሉት የነበሩት ጣሊያኖች ደግሞ ፣ ሁለቱ ራሶች በደበበና

በተከታዮቻቸው ላይ የመሰዱትን ርምጃ በመደገፍ በርካታ የጦር
መሣሪያ ላኩላቸው ። ከዚያ በኋላ ነገሩ እየከረረ ሲሔድ ማገበሩ
ፈረሰኛ ለጦርነት ተሰላለፉ ። ሁለቱ ራሶች በድምሩ ሁለት ሺህ
የሚሆን ወታደር አከማችተው በአሉላ አዝማችነት ሲነሡ ደጃች
ደበበ ደግሞ አንድ ሺህ የሚሆን ወታደር ይዘው በራሳቸው
አዝማችነት መስከረም 19 ቀን 1883 አዲነፋስ ከሚባ
ለው ቦታ አጠገብ ከ ጀንግ ተራራ ላይ ጦርነታቸውን ገጠሙ ።
ምንም እንኳን ራስ መንገሻ በዙር ሐረጋቸው በደበበ ላይ ለመ
ጨከን ባለመቻላቸው 'ደበበን ከነሕይወቱ ይዞ ላመጣልኝ
ወታደር ሁለት መቶ ብር ጉርሻ እሰጣለሁ' ብለው በጦርነቱ
ቦታ ላይ ቢያስለፍፉም ፣ ራስ አሉላ ደግሞ ፣ የራሳቸውን ታማኝ
ታማኝ ወታደሮች ይዘው በተለመደው የወጊያ ስልታቸው የደ
በበን ጦር ከበው ማስጨነቁን አምርረው ገፍተውበት ነበርና ፣
የደበበን እጅ በሕይወት ለመያዝ አልተቻለም ነበር ። ደበበ በአ
ሉላና በወታደሮቻቸው መከበባቸውን እንዳረጋገጡ እርድ እርድ
ይዘው ሲታኮሱላቸው በነበሩት ታማኞቻቸው መካከል ሆነው

"ይህን የድሃ ገበሬ ልጅ ! ይህን የአገሬ አማቢ የነበረ
ይህን የመላው ትግሬ መኳንንትና የጨዋ ልጅ ሁሉ ጠላት
የሆነ እጁን ይዞ ለሚሰጠኝ የማዛቱን ግማሽ እሰጣለሁ" እያሉ
ራሳቸው ሲጮሁ ፣ አሉላ ደግሞ በታማኞቻቸው መካከል እየተ
ዘዋወሩ ፣

"ያው በዚያ በኩል ራጋው ባስቷል በዚህ በኩል ጠንክሩ
ያ ሥፍራ ያዙ ፣ ያኛውን ልቀቁ ! በዚያ በኩል ባሉት ተኳሾ
ላይ አነጣጥሩባቸው ። ይህን ርምጃ ፣ በተረገመች ዕለት የተወለ
ርጉም ግንባሩን ብቻ ካላሳረፍኩት በርሱ የተነካ አገሬ ሰላ
ሙ ሕዝብ ሲተላለቅ አይኖርም" እያሉ ደበበ የቀደበበት
እርድ ማንጸጸር ጀመሩ ።

ተራ ወታደር ባለመገደል በደበበ ላይ ብቻ የዲሞትሬ
ቸውን እረር ለማሳረፍ በሚያነጣጥሩበትም ወቅት ደበበ በወ
ትነቱ ወቅት በአባቱ ቤት ሳሉ የሰደባቸው ትዝ አላቸው
በርግጫ መትቷቸው ገብገብ ሲጋጠሙ ከመሬት ላይ ዘርረው
ታያቸው ። የሚወዷቸውን ባለቤታቸውን ንብረት ምዕም አከባ



ዘርፎ ከመሰደ በኋላ አሹፎ የላከባቸው ቃልና በዚያም ምክንያት
ባለቤታቸው ያዘኑት ዝገን ትውስ አላቸው ፣ ወዲያው ደግሞ
ባለቤታቸው እምስሉ ፣ 'ከጠቀመው ይውሰደው ተወው
ቂም አትያዝበት'' ያሉዋቸው የጉባዔ ቃል ትዝ አላቸው ። ያ
ትዝታ ገፍቶ የሚል የደበበ ወንጀል ደግሞ ተራራ ያህል ሆኖ
ከፊታቸው ታያቸው ። ደበበ ከጣሊያኖች ጋር ፣ ደበበ ከሚሲዮናዊ
ጋር ፣ ደበበ ከትግራይ መኳንንት ጋር ፣ ደበበ ከአማውርታ ሽፍ
ቶች ጋር ሲመራው የነበረው ተንኮልና ሤራ ታያቸው ።
እንደገና ደግሞ ከዮሐንስ ዙፋን ላይ ሊቀመጥ ሲያጉበደድ
ታያቸው ። ይህን ሁሉ ጥቦ ደግሞ 'አወይ ትዳሬ! ክብሬ ማዕ
ረጌ በደበበ ጥጋብ ፣ በደበበ ማን አለብኝነት ፈረሰ' ብለው የደ
ጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ሚስት የነበሩት ያለቀሱት ፣ ልጃቸው
ከፊታቸው ቆመባቸው ። 'የኔን ግዛት ተመኝቶ በኔ ወንበር ላይ
ለመቀመጥ ሲል አይደለም ታማኙን ኃይለ ሥላሴን ከነጆንግዬ
የገደለብኝ ። እኔን የበደለ መስሎት አይደል በሚሲዮናዊች [illegible]
ራን የሰጠብኝ' ብለው አጉረመረሙና ፣ 'ሚካኤል አይማረኝ
ብምረው' ብለው ከንፈራቸውን ነክሰው ትንፋሻቸውን እያ
ቁው ዲሞትፈራቸውን አነጣጥረው ዐይናቸውን ተራ በተራ
ጭፍን ክፍት ፣ ጭፍን ክፍት ፣ እያደረጉ ሲጠባበቁ ራስ እር
እያ ደምቶ ደግሞ የአጼ ዮሐንስን ራስ አላስማርከም ብለው
ከእኅታቸው ልጅ ራስ አጠገብ ወድቀው ፣ 'በዮሐንስ ዙፋን
ልቀመጥ አለ? ቃላቸውን ማስ[illegible] ያዘውና ገረፈው!' ብለው ሲል
ምንአቸው ደበበ ተንበርክከው ሲታኮሱበት ከነበረው እርድ
እንገታቸውን ቀና አድርገው ፣ "ወዲ ቁቢ ዛሬ የማርከህ እንደሁ
አይማረኝ ! ዛሬ ያመለጥኸኝ እንደሆን ቆዊ ብቻ ሽንቻለሁ!
ዛሬ ..." ብለው ተናግረው ሳይጨርሱ ፣ 'እኔም የማርከህ እን
ደሁ አይማረኝ' ብለው አሉላ የዲሞትፈራቸውን ምላጭ
ሳቡት ። የአሉላ ዲሞትፈርም የወነጨፈችው እረር ከደበበ ግን
ባር ላይ ስታርፍ ጦርነቱ ቆመ ።

ራስ መንገሻ ፣ የዙር ሐረጋቸውንና የማኅበርተኞቻቸውን የደጃ
ዝማች ደበበን አስከሬን አሸከመው ዐድዋ ገቡና ሁለቱም
ራሶች በተገኙበት በክብር ተቀበረ ።

የመኳንንቱ ዘርም አሉላን 'ዐይንሀ ኣፈር' እያለ ተራገሙ። 'ዘራፎች ኃይለ ሥላሴ ቢሉ ጸበበን ገደሉት' እያለ አማቸው። በየቤቱ ሲያጉረመርምና ጉልበቱን ሲተገምግም የነበረው የትግራይ መኳንንትም አሺሱን የአሉላን ዱላ በመፍራት በመንገሻ ዙሪያ መሰብሰብ ጀመረ። ከዚያም በኋላ የራስ መንገሻ ልብና ጉልበት እየጠነከረ ሔደና የአጼ ምኒልክንም ጥሪ ችላ ማለት አመጣ።

ትግራይ ውስጥ የነበረው ኢጣሊያዊው ጋዜጠኛ አሥመራ ተመልሶ ባቀረበው አስተያየት ፥

“በአሁኑ ወቅት ያለው የራስ መንገሻ ሥልጣንና ኃይል ፍጹም ተፎካካሪም የሌለበት ነው። የትግራይም መኳንንት የዮሐንስ ወራሽነታቸውን ሙሉ ለሙሉ አምነው ተቀብለው ይሰግዱላቸዋል። አሉላም ቢሆኑ ታላቅ አክብሮትና ትሕትና ያሳዩዋቸዋል። መንገሻን የሚጻረር ማንም የለም” አለ። ትእሉላ ምክር የሚያዋጣቸው እንደሚሆንላቸው ራስ መንገሻ የተገመተበትን ያህል ደግሞ ፥ አሥመራ የነበሩትና የሮም የፖለቲካ ጠበብትም ምኞታቸው ወደ መልካም ፍጻሜ መቃረቡን በመገመት ፥ ከሁለቱ ራሶች ጋር የሚነጋገሩ መልእክተኞች ወደ ትግራይ ለመላክ ወሰኑ። በዚህም መሠረት ዶክተር ነራዚኒና ሲ. ማርቲና የተባሉ ኢጣሊያውያን ወደ ትግራይ ከመሔዳቸው በፊት በጉዳዩ ላይ የኤርትራው አገረ ገዥ ባለበት ምክክር ሲደረግ ፥

“ከሦስቱ አንዱ ተገድሏል ፥ አሁን እንግዲህ ሁለቱን እንደ ምን አድርገን እንደምንቀርባቸው ወይም እንደምናርቃቸው ወይም ከምኒልክ ጋር እንደ ጊጋው ዘዴውን ብንመክርበት ይሻላል” አለ አገረ ገዥው ጋንዶልፊ። “ለዛሬው መቀራረቢያ የሚሆነን መግቢያ አዘጋጅተናል። ለራስ መንገሻ ባለፈው መሠረት ንጉሣችን የላኩትን ደብዳቤና ልዩ ልዩ ገጸ-በረከት ይዘናል። እንግዲህ በዚህ ከቀረብናቸው በኋላ የ ሚቀጥለውን ጉዳይ ደግሞ እንደዚሁ እንመክርበታለን” አለ ነራዚኒ።

“ልክ ነው ፤ የእሙኑ ርምጃችን ይኸው ነው። ሌላው ነጥብ ግን የሁለቱ ራሶች የእርስ በርስ ጉዳይ ነው። አሉላ ፥ ምኒልክ



ስለ አላተረፉት አኩርፈ ፤ ዘመዱን ለመንገሻ አስመልሰው ይላል። ትግራይም ለጥ ሰጥ ብላ በመንገሻ ሥር እንድትገዛ ብርቱ ጥረት ያደርጋል። የጦር መሣሪያም እንደልቡ ለማግኘት እንደሚፈልግ ተረድተነዋል። ይህን መሣሪያ የሚፈልገው ለምን ሊያደርገው ነው? እኛን ሊወጋበት ነው? ወይስ ምኒልክን? እነ ዚህን ነጥቦች በጥንቃቄ ማጥናት ይኖርብናል። እናንተም ትግራይ እንደ ገባችሁ እነዚህን ጉዳዮች እንድታተኩሩባቸው ያስፈልጋል” አለ ጋንዶልፊ መልእክተኞቹን ተራ በተራ እየተመለከተ።

“ምናልባት ሱዳኖቹን ለመከላከል ብለውስ እንደሆነ?” አለ ነራዚኒ።

“ሱዳኖቹ ለኛም አስቸጋሪዎች ሊሆኑብን ይችላሉ ፤ ስለዚህ ሁለቱም ቢፋጁ እኛ የምንፈልገው ጉዳይ ነው። መሣሪያ የፈለጉት በእርግጥ ለዚህ ከሆነ ነገሩ ገፍቶ ሲመጣባቸው የ ፈለጉትን ያህል መሣሪያ ልንሰጣቸው እንደምንችል ልታረጋግጡላቸው ትችላላችሁ” ብሉ አገረ ገዥው መልእክተኞቹንና ከፊቱ የነበረውን ማኅደር እያስተያየ ሲመለከቱ ቆየና ፥

“አሉላ ከሌሎቹ ራሶች ለየት ያለ ስለሆነ ፥ ከተቻለ ሌላ የንግድ ጉዳይ ያሳስበዋል። ንግድ በማስፋፋት ረገድ ቀደም ያለ ፍላጎት እንዳለው የተጠና ነው። አሁንም ይህን ነጥብ ሊያነሣባችሁ ስለሚችል ፤ ከዐጽዋ እስከ ምፅዋ ንግዱን ለመዘርጋትና ለማስፋፋት እንደምንፈልግ አረጋግጡለት። የንጉሡ ወራሽ የሆነው መንገሻ ደግሞ እንደ አጼ ዮሐንስ ጠበቅ ያለ እምነት ያለው መሆኑ ስለ ታወቀ ፥ አንድ ቤተ ክርስቲያንና አንድ ቤተ መንግሥት ልናሠራለት እንደምንችል አረጋግጡለት። ለጊዜው በእነ ዚህ ነጥቦች ለመቀራረብና ለመስማማት እንችላለን” አለ።

“ከአሉላ ጋር ዕርቅ ማድረጋችንን የኢጣሊያ ሕዝብ ቢሰማ ከፍተኛ ችግር እንዳያስነሣብን ለጊዜው ከመንገሻ ጋር ብቻ በግልጽ ተነጋግረን ከአሉላ ጋር ደግሞ በነባብተን በምሥጢር ብንስማማስ?” አለ ፒያና።

"ምንጊዜም እርግጥ ይመጋኛል ፤ ግን ፣ ድንገት ተጓዥ በመንገድ ታቅዶ በአል ታጠቀ ፣ አሉላ በዶጋሊ ላይ ላደረሰብን ጥቃት ካሳ ሊሆን የሚችለው ከመረብ ወንዝ ወዲህ ያለው አገር የኛ ይዞታ መሆኑን አምኖ የተቀበለና ፣ ትግራይ ውስጥ ብቻ ለመቀመጥ መስማማቱ ነው ፤ በቂ ሊሆን ይችላል ተብሎ ታምኖበታል። በዚህ አሁን ከመንገሻ ጋር ተነጋግረን እርሱን ችላ ብንለው ፣ እርሱ ደግሞ ወደ ባለ ብሶቶች ያመራና መንገሻን ለበር ወይም ደግሞ ከምኒልክ ጋር የታረቁብን እንደሆነ ፣ ከዶጋሊ የከፋ ውድቀት ሊደርስብን ይችላልና ፣ ከሁለቱም ጋር በአንድነት መነጋገርና መስማማቱ ነው የሚያዋጣን" አለ ኑራዚኒ በስብሰባው ላይ የነበሩትን ተራ በተራ እየተመለከተ ።

"እኔም በዚሁ ነው የምስማማው ና ጉዞአችሁን ቀጥላችሁ ከአሉላ ጋር ከተከገመ በኋላ ከኔ ጋር ደግሞ በምሥጢር የም ንግግሮችን ሁሉ ትቀይሳላችሁ" አለና አገረ ገዥው ጉዳዩን አጠቃለለው ።

ከዚህ በኋላ ከርሞ የተላኩት መልእክተኞች ወደ ትግራይ ተጓዙና ከሁለቱ ራሶች ጋር ተገናኙ ። አስቀድመው ጣሊያ ኖች የተሰጡትንም ነጥቦች አሰሙ ። በነጥቦቹ ሲስማሙ አሉላ እንደ ማኩረፍ አሉና ፣

"ከዚህ እስከ ምጥዋ ገባድ እናስፋፋለን ያላችሁትን አል ስማማበትም ። የመሣሪያውን ጉዳይ ግን ልታስቡበት ይገባል ከወደታች በኩል ድርቡሽ እያስቸገረ ነው ። አጤ ምኒልክም ርቀውናል ። ለዚህ ለዚህ ሁሉ መሣሪያ ያስፈልገናልና ም ላይ የራሳችን ሰው አስቀምጠን ከእናንተም ሆነ ከሌላ አገ በተገዛችሁን እያስገባን የምናስመጣው መሣሪያ ያለ ችግር እን ገባ እናንተም ምከሩበት" አሉ ።

"ይሁን ፣ ይህንኑ ሐሳብዎን ለመንግሥታችን እናቀርባለን ግን ፣ ሁላችሁ በእናንተ ላይ ከዘመቱ እኛ በገዛ እንችልም ። ምኒልክም ቢሆን ስንት መሣሪያ እንዳላቸው እና ቃለን ። በእናንተ ላይ የሚዘምቱባችሁ ከሆነ እኛም የሚቻለን ያህል እንረዳለን" አለ ማርቲኖ ።



ምንም እንኳን ነገሩ ከልባቸው ባይገባም ፣ አሉላ ለጊዜው ሐሳቡን ተቀበሉትና 'ከኤርትራው አገረ ገዥ' ጋር ለመገናኘት ፈቃደኛች መሆናቸውን ካረጋገጡላቸው በኋላ መልእክተኞቹ ጉዳዩን ወደ አሥመራ አስተላለፉ ።

ራስ አሉላ ፣ የጦር መሣሪያ የማግኘቱ ጉዳይ እየራቀባቸው መሔዱን ተገነዘቡት ። እጃቸው በደብልዮ እየታሰረ ጉልበታቸው እየደከመ ሕልናቸው እየቆሰለ እንደሚሔድ አመኑበት ። በዚያም ወቅት ነበር ከዕለታት አንድ ቀን ከራስ መንገሻ ጋር ሲነጋገሩ ፣

"እንዲያው ነገሩን በጥሞና ስታስበውኮ አገራችን ኢትዮጵያ እያነሰች እጇና እግርጋ እየታሰሩባት መሔዷ ነው ። እስቲ ተመልከተው! እነዚህ ተንኮለኞች በመጀመሪያ የደንከልን የባሕር በር ቀጥለው የምጥዋን በሮች ያዙ ። ከዚያ ተንፏቀው ተንፏቀው ደግሞ ሐማሴንን ይዘው የመረብን ወንዝ ግዶ አጠቃለው መሬቱበት ። የልባቸውን ካደረሱ በኋላ የጦር መሣሪያ እናስገባለቸሁም አሉን ። እኛም እርስ በርሳችን ስንባላ እያደር እየተመናመን ሔድን ። ከአጤ ምኒልክ ጋር ጦርነት በንጋጠም ደግሞ በደብልዮ እየተጐዳን ልንሔድ ነው ። ታዲያ እስቲ አስበው? ኢትዮጵያ እያነሰች እያነሰች እጅ እግሩዋ እየታሰረባት መሔዱ እርድ ለምን ወይኔ አሉላ! ያገሬ መሳፍንት ነገር በሩቅ አልታየው ብሎ አገሬን ሊያጠፏት ነው!" አሉዋቸው ።

ምንም እንኳን ሁለቱ ራሶች አፍጥጦ የመጣባቸው ጉረት የፒያቢልትለውን ጣጣ አስቀድመው ሊረዱት ቢችሉም ፣ ከቀረ በላቸው አገራቸው መውጣት ስላልተቻላቸው ደካማነታቸውን በልባቸው አምነው 'ከኤርትራው አገረ ገዥ' ጋር ለመገናኘትና ለመነጋገር ተገደዱ ።

የሁለቱ ወገኖች ስብሰባ ኢጣሊያኖች ሠፍረውበት በነበረው መረብ ግዶ እንዲሆን ተስማሙ ። በዚሁ መሠረት ራስ መንገሻ ከራስ አሉላ ፣ ከራስ ሐጐስና ከራስ ወልደ ሚካኤል ጋር ፣ 'የኤርትራው አገረ ገዥ' ጋንዶልፊ ደግሞ ከባለሟሎቻቸው ጋር ሆነ ቀረበ ።

በመጀመሪያ ራስ መንገሻ የመረብን ወንዝ ሲሻገሩ 'የኤርትራው አገረ ገዥ' በታላቅ ክብር ተቀበላቸው ። ተቀባዩም ራስ መንገሻ በዶጋሊ ላይ የደረሰውን እልቂት ከልቡ የረሳው መሆኑን ጋንዶልፌ በመሐላ እንዲያረጋግጥላቸው ጠይቀውት ፣ እርሱም ከልቡ ይቅር ያለ መሆኑን በመሐላ ከአረጋገጠ በኋላ ፣ ራስ አሉላም እንዲሻገሩ ተላከባቸውና ተሻገሩ ።

የጋንዶልፌና የተከታዮቹ ዐይኖች መንፈስ እንደሚያዩ ሁሉ ግልብጥብጥ ብለው ፈጠጡ ። ቀዩ ቆዳቸው ጥላሼት እየለበሰ ሔደ ። አንዳንዶቹ ከንፈር ከንፈራቸውን ሲነክሱ ፣ ጋንዶልፌ ራሱን ቅጭም እንዳደረገ ወደፊቱ ራመድ ራመድ አለና ቆም ብሎ ሲጠጋቸው ፣ አሉላም ቆም ብለው ፊታቸውን እንዳስቀሙ ከጋንዶልፌ ላይ አተኮሩበት ። ከበስተ ኋላው በነበሩትም ላይ የዐይኖቻቸውን እሳት ነበልባል ለቀቁባቸው ።

ራስ መንገሻ ከነበሩበት ወደ ፊታቸው ራመድ ራመድ ብለው ከራስ አሉላ ጐን ቆም ብለው ፣

"ይበሉ ይቅር በለኝ ይበሉት" አሉዋቸው ።

"እርሱው 'ይቅር በሉኝ' ይበለኝ እንጂ ፣ እኔ ምን በደልኩና ቀድሜ እጠይቀዋለሁ" አሉ ። ራስ መንገሻም እንደገና ወደ ጋንዶልፌ ሔደው ፣

"ይበሉ 'ይቅር በለኝ' ይበሉዋቸው" አሉት ።

ጋንዶልፌ ጥቂት ርምጃዎች ወደፊት ሔዶና አንገቱን ደፋ አድርጐ ፣

"ይቅርታዎን እጠይቃለሁ" ሲል ፣

"እርስዎም ይቅር ይበሉኝ" አሉ አሉላም ።

ከዚያ ቀጥሎ ሁለቱ በመጀመሪያ ከተጨባበጡ በኋላ ፣ ጋንዶልፌ ከኋላው የነበሩትን ተከታዮቹን እያቀረበ አስተዋወቃቸውና የእጅ ሰላምታ ተለዋወጡ ።



"በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ የአውሬ እጅ መጨበጤ ነው" አለና አንዱ ጣሊያን ለጓደኛው ሹክ አለው ።

"ዶጋሊ ላይ የወደቁት ጀግኖቻችን ደምና አጥንት መቼም ይፋረዱናል" አለ ጓደኛየውም ።

ራስ መንገሻ በመካከል ፣ አሉላ በስተቀኝ ፣ ጋንዶልፌ በስተ ግራ ሆነው ወደፊት አምርተው ከተዘጋጀው ዳስ ውስጥ ገብተው ሲቀመጡ ጋንዶልፌ ተነሣና ፣

"ክቡር ራስ መንገሻ ፣
"ክቡር ታላቁ ጀኔራል ራስ አሉላ ፣

"ክቡራን ወዳጆቻችን ፤ በዛሬው ቀን ከዚህች ቦታ ለእርቅ ለሰላምና ለወዳጅነት በመገናኘታችን በመንግሥቴና በራሴ ስም የተሰማኝን ደስታ እገልጻለሁ ። ማንኛውም ጀግና የጦር ሰው እንደሚያደርገው ሁሉ ፣ ክቡር ራስ አሉላም የንጉሡ ክ[illegible]ታቸውን አደራና ትእዛዝ ለማስከበርና ሀገራቸውን ለመጠበቅ ሲሉ ከኛ ጋር ባደረጉት ጦርነት የደረሰብንን ጉዳት ረስተን ዛሬ ለእርቅ በቅተናል ። እኒህ ታላቅ ጀግና ስለ ሀገራቸው ፍቅር ሲሉ ከግብጾችና ከማሕዲስቶች ጋር ባደረጉዋቸው ጦርነቶች ያገኙዋቸውን ድሎች ከልብ አደንቃለሁ ። በእውነት አስደናቂ የጀግንነት ሥራዎች ነበሩ" ብሎ ሁለቱን ራሶችና የራሱንም ባለሥልጣኖች ተራ በተራ ተመለከተና ንግግሩን በመቀጠል ፣

"ከእንግዲህ ወዲያ ግን ታላቁ ጀኔራል በመግባባትና በፍቅር እንደሚኖሩ እየተመኘሁ ፣ ዳግመኛ ምን ደም የለመደ ጉራዴያቸውን እንደማይመዙ ተስፋ አደርጋለሁ" ብሎ ሲቀመጥ ፣ ከባዱን ዝምታ መጠነኛ ፈገግታ ገፈፈው ።

"እርስዎም ከልብዎ ይቅር ያሉ መሆንዎን ቢያሳውቋቸው መልካም ይሆናል" ብለው ራስ መንገሻ ፣ ራስ አሉላን ሹክ አሉዋቸው ።

"ምን ከፋኝ" ብለው አሉላ ሲነሡ ራስ መንገሻም አብረው ብድግ ሲሉ ፣ ራስ አሉላ አስቀመጡዋቸውና ግራና ቀኙን ቃኝ ብለው አስተውለው ፣

ክቡር አገሬ ዓኘ!

እንደሚያውቁት ጀግና ወታደር አገሩን ሲደፍሩበት ልቡ
ይቆጣል። ክብሩ ይዋረዳል። ያገሬ ሕዝብ ደግሞ በባህሉ ወታ
ደር ነው። አገሩ ሲነካበት የሚቆጣውም ሁሉም ነው! እኔም
በዚያ ጊዜ ከወገኖቻችሁ ጋር ጦርነት የገጠምኩት በዚሁ
መሠረት ነው። ግን አስቀድሜ ወረቀትም ሰውም እየላክሁ የጦር
አሊቃውን ለምኜው ነበር። 'ከምጥዋ እየወጣህ አገር መያዝህ
ተገቢ አይደለምና አገሬን ልቀቅልኝ' እያልኩ በለምነው፤ ቁስጠ
ንቅቀው አልሰማም ብሎ አስቸገረኝ! የርሱ አንሶ ወንበዴና
ወሰላታ እየሰበሰበ መግሪያ እየሰጠ ሰላም ነሣኝ! ያን እያየሁና
እየሰማሁ ዝም ብል ደግሞ ያገሬን ሕዝብ እጅግ የሚያሳዝነውና
የሚያስቆጣው ይሆን ነበር። ስለዚህ የሚገባኝን ሥራ መርቻለሁ።
አሁን ግን እናንተም ሰላም ፈላጊዎች ከሆናችሁ እኔም ሰላም
ፈላጊ ነኝ! ጥናው ሐሳቤ ሰላም ነው። አገሬንና ክብሬን የሚደ
ፍር ካልመጣም ጉራዴዬን አላነሣም" ብለው ተቀመጡ።

ከዚያ ሥነ ሥርዓቱ ተፈጸመ ፤ ራስ መንገሻ ለጀኔራል
ጋንዶልፊ የራስነት ማዕረግ ሰጡት። ከዚያ በኋላም ሁለቱም
ወገኖች ወደየሠፈራቸው ከመመለሳቸው በፊት ስምምነታቸውን
በመሐላ ሲያጸድቁ ራስ አሉላም ፤ 'የመንገሻ ጠላት ጠላቱ ፤
የመንገሻም ወዳጅ ወዳጁ' ነው ብለው ቃላቸውን ሰጡ። ራስ
መንገሻ ራሳቸው ከራስነት ማዕረግ ያላለፉ ሆነው ሳሉ ፤ ለባዕድ
ተወላጅ የራስነት ማዕረግ በመስጠታቸው እጼ ምኒልክን ለማስ
ቆጣት ሲሉ የወሰዱት የተጋፊነት ምልክት መሆኑንም ብዙዎቹ
መኳንንቶቻቸው ተረድተውት ነበር። ከዚያ በኋላ ራስ መንገሻ
ከኢጣሊያኖች በኩል በቂ የጦር መግሪያ ለማግኘትና ለእጼ
ምኒልክ 'አልገብርም ፤ አልገዛም ፤ አላንኑበስም' ለማለት የሚችሉ
በት ወቅት እየቀረበላቸው እንደሚሔድ እያመኑበት ሔዱ።

በዚያ ወቅት ከራስ መንገሻ አፈንግጠው የነበሩ ደጃ
ዝማቾች ስብሐት ስለነበሩ ፤ እርሳቸውንም በሹመትና በጋብቻ
መቀራረብ እንደሚሻል ራስ አሉላ ስለመከሩበት ፤ በጉዳዩም ራስ
መንገሻ ስለተስማሙበት ፣ የራስ አሉላ ወንድም የባሻይ ገብረ
ማርያም ልጅ ወይዘሮ ሸዋንሽን ለደጃዝማች ስብሐት ወንድም



ለደጃዝማች ዐባይ መርዐድ ፤ የራስ አሉላን ልጅ ወይዘሮ ደመቀችን
ከራስነት ማዕረግ ጋር ሰጥተው ፤ ነገሩ በእርቅ አለቀ። ከዚያ
በኋላ ፤ የራሳቸው የራስ መንገሻ ፤ የራስ አሉላ ፤ የራስ ሐጐስና
የራስ ስብሐት ጦር ተደምሮ ከዐሥር ሺህ በላይ መድረሱን
መንገሻ ከረጋገጡ በኋላ ፤ 'ጃንሆይ' እየተባሉ እንዲጠሩ አዘዙ።
ተጣለውም ፤

'ከምኒልክ ወታደር የበለጠና የተሻለ ሠራዊት አዘጋጅ
ተን ወደ ሸዋ እንዘምታለን። ሸዋ ገብቼ ዘውዱን እጭናለሁ'
ብለው ለመኳንንቶቻቸው ቁርጥ ያለ ሐሳባቸውን አስታወቁ።

ከሁሉም ከሁሉም በዚህ ሐሳባቸው ራስ አሉላ እጅግ
ተደሰቱ።

'አንተ ቆራጥ ከሆንክ ፤ አንተ ለአባቴ ዘሩን አብቂኝ ብለህ
ከተነሣህ ፤ መግሪያም ሠራዊትም አይጠፋም። የኔ ጥናው ሐሳቤም
ይኸው ነው። ጉልበታችንና አንድነታችን እንደበረቱ ከተመለስ
ከመረብ ምላሽ ያለውን የተቀማነውን አገራችንን እናስመልሳ
ለን። ከምኒልክ ዘውድህን ፤ ከጣሊያኖች አገርህን ካስመለስን፤
እያነሰች ፤ እየተቀረበች የሔደችውን ኢትዮጵያን ወደ ታላቅነቷ
እንመልሳታለን። ከዚያ በኋላ ድርቡሽ ቀርቶ ማንም አይጠጋ
ንም ፤ ከሰላምም በአንድ ራስ ጦር ማስመለስ እያቅተንም'
ብለው ልባቸው እምቆት የኖረውን ምሥጢራቸውን ገለጹላ
ቸው።

ራስ መንገሻም የመኳንንቶቻቸው አንድነት የተጠናከረ
የእጆሬ አባታቸው የራስ አሉላ መንፈስ የታደሰላቸው መሆኑን
ከረጋገጡ በኋላ ፤

"የጦር መግሪያ ከሰጣችሁኝ ወደ ሸዋ ዘምቼ የወሰደብ
ኝን ዘውድ ለማስመለስ እችላለሁ። ከዚያም በኋላ ከእናንተ ጋር
የጸና ወዳጅነት እንመሠርታለን" ብለው ለጋንዶልፊ ላኩ።

"የትግራይ ራሶች አንድነት የተጠናከሩ ይመስላል ፤ ወደ
ሸዋም ዘምተው ከምኒልክ ጋር ጦርነት ለመግጠም መዘጋ
ጀታቸውን ልከውብኛል ፤ መግሪያም እንድንሰጣቸው ጠይቀዋል።

ምን ብናደርግ ያዋጣናል?" ብሎ 'የኤርትራው አገረ ገዥ' ጀኔራል ጋንዶልፊ የረዳቶቹን ምክር ጠየቀ።

"መሣሪያ ቢያገኙስ በየትኛው ስንቅ ነው ሸዋ ድረስ የሚሄዱት? ትግራይ በከፍተኛ ረኃብ ላይ ናት፤ ይህን እንዴት መገመት አልቻሉም?" አለ ምክትሉ።

"ይህ እኛን የሚያሳስበን ጉዳይ አይደለም፤ ዞር ዞር የሚፈለገው መተላለቃቸው ነው። የእነርሱ የዕለት ምግብም ሆነ የዓመት ልብስ ያው ዝርፊያ ነው። ከዚህ ተነሥተው አገር እየዘረፉ ሸዋ ይደርሳሉ" ብሎ ጋንዶልፊ ተናግሮ ሳያበቃ ምክትሉ አቋረጠውና፣ "እና ምኒልክን ጦርነት ገጥመው ያሸንፋሉ ማለት ነው?" አለና ጠየቀ።

"ይህም አያሳስበንም፤ ምኒልክም ቢያሸንፉ መንገሻም ቢያሸንፉ እኛን እንደሆነ ከዚህ አያነቃንቁንም። ከሁለቱም ጋር ያለንን ስምምነት ምክንያት ፈልገው ስምምነቱን አፍርሰናል ቢሉን፣ እኛም በጦር ኃይላችን እንደ ርምጃ ወደፊት መራመድ አያቅተንም። አሁን ችግር ሆና የታየን ግን ምን ያህል መሣሪያ ለትግሬዎቹ ራሶች እንስጥ ለማለት ነው የጠራኋችሁ" አለ ጋንዶልፊ።

"መሣሪያ መስጠታችንን ምኒልክ የሰሙብን እንደሆንስ?" አለ የፖለቲካ አማካሪዉ።

"በተቻለ መጠን ምሥጢሩ እንዲጠበቅ እንጠነቀቃለን። ወይም 'ለአጼ ምኒልክ የሚላክ ነው' በሚል ምክንያት እንልከውና አሉላ እንዲዘርፈው አስቀድመን እናስታውቀዋለን። አሉላ ደግሞ ከሰማው ከአየው እንደማይለቀው የታወቀ ነው። ዘርፎ ያስቀረዋል። ከዚያ በኋላ 'ተዘረፍን' ብለን ለምኒልክ መልእክተኛ እንሰዳለን" አለ ጋንዶልፎ።

"በጣም ጥልቅና ክቡር ሐሳብ ነው። እንግዲያው በዚሁ ዘዴ መሣሪያው ይላክላቸው" አለ ምክትሉ።



ምክክሩ በዚሁ አበቃና ለመጀመሪያ ጊዜ ከመላስ አምስት ሺህ በላይ የሆነ ክርታ ጥይት ለአጼሱ 'ጃንሆይ' ተላከ። እርዳታውም እንደሚቀጥል ጭምር የሚያረጋግጥ ቃል አብሮ መቀሌ ገባ።

አጼ ምኒልክ በእነራስ መንገሻና በጣሊያኖች መካከል የተጀመረውን ሽርክና እንደ ሰሙ፣ 'የመንገሻን ከዳተኝነት ራሴ ሔጄ አረጋግጠዋለሁና ጦር ይዘጋጅ' ብለው እንደ ወሰኑ መኳንንቶቻቸው በጉዳዩ እጅግ ስለ ተቸገሩበት፣

'እንዴት እርስዎን ያህል ሰው ከዮሐንስ ወራሽ ጋር ጦርነት ይገጥማል? ለአገራቸውና ለሃይማኖታቸው ክብር ትላንትና አንገታቸውን ለጠላት የሰጡት የዮሐንስ ዓፅም ይፋረደናል። ትላንት የሞቱት ሰው ቢሳሳትስ ሰው ልክ ማስመከር ነው እንጂ እንዴት ይወጉታል? እምቢ ካለም ደግሞ አገር እንዳያበላሽ ሕዝብ እንዳያሳስት ያንድ ደጃዝማች ጦር ማዝመት ይበቃል፣ የእርስዎን መዝመት አንደግፍም' ብለው ለመኑዋቸው።

"እንዳላችሁት ይሁን! የዮሐንስን ወራሽ ትላንት ሹሜ ዛሬ ብወጋው አገር ይታዘበኛል፤ ወገን ያዝንብኛል፤ እግዚአብሔር ባይጨምርበት ነው እንጂ ተጋብተንስ አልነበር? ብቻ መንገሻን የሚያሳስተው አሉላ መሆኑን ሰምቻለሁና ተላልካችሁ ሁለቱንም አስመክሩ። አሉላም የሠራው ሙያ ሳያንሰው እኔን አላይም አልቀርብም ያለበት ምክንያትስ ምንድነው? የአባቴን ዙፋን እንጂ የአባቱን አልወረስኩም! ምናለ ጀግንነቱንና ታላቅ ሰውነ ባያበላሸው? እኔ አልቀበልሁም አላልኩትም፤ መንገሻን መሣሪያ አድርጎ የሚያሳዝነኝ ለምንድን ነው? እርሱንም ቢሆን ላኩበት" ብለው ነገሩን በይደር አቆይተውት ነበር።

መኳንንቱና ጳጳሳቱም በዚሁ ጉዳይ ላይ ተመካክረው ሽማግሌዎች መርጠው ወደ ትግራይ ለመላክ በዝግጅት ላይ እንዳሉ ከአሥመራ የተጫነው የጦር መሣሪያ መቀሌ መድረሱን አጼ ምኒልክ ሰሙ።

"ጣሊያኖች ባገሬና በሕዝቤ ላይ እንደዚህ ይጫወቱ ጀመር? መንገሻና አሉላን እያባበሉ በጉን መሣሪያ እያቀበሉ፣ እኔን ደግሞ

በዚህ እያታለሉ አገሬን ለከፋ ሊዳርጉኝ ያሰቡት ! ለካ የእነርሱ ወዳጅነት እንደዚህ ነው ለ” ብለው ተቆጡ ፡ ቀጥ ያለው መልእክታቸውም ከአዲስ አበባ ተነሥቶ ሮም ደረሰና በኢጣሊያ የፖለቲካ ጠቢባት ላይ ራስ ፍልጠት ለቀቀባቸው ፡ ምሥጢራቸው የተጋለጠባቸው የኢጣሊያ ባለሥልጣናትም ጋንዶ ልፊ የሠራው ሥራ ፍጹም ስሕተት መሆኑን አምነው የይቅርታ መጠየቂያ መልእክት ወደ አጼ ምኒልክ ሰደዱ ፤ ጋንዶልፊን አንሥ ተው ጄኔራል አረስቴ ባራቴሪን ሰደዱ ፡

ባራቴሪ ፡ አሥመራ እንደ ገባ በጉዳዩ ላይ ከሹማምንቱ ጋር ከመከረበት በኋላ ፡ “መቼም የቅርብና የሩቅ ግዛቶች አሉን፤ ከአሰብ ምፅዋ ፡ ከረን ፡ ከከረን አሥመራ ለመድረስ ብዙ ጊዜ ወሰ ደብናል ፡ ብዙም ሕይወትና ንብረት ከስክሰናል ፡ ዛሬም ከዚህ ተነሥተን ወደፊት ለመራመድ ሰአትና ጊዜ ይጠይቀናል ፡ ምንም እንኳን በዓላማው ባይሳሳትም በሰአትና በጊዜው ግምገማ ረገድ ጋንዶልፊ በመጠኑ ተሳስቷል ፡ አሁን እንግዲህ ከትግሬው ራስ ጋር የተጀመረው ግንኙነት እንዳይቋረጥ በመጠኑ አለዝበን እን ይዘዋለን ፡ ቀጥለንም አጼ ምኒልክን እንዲያስታግሡልን ከራስ መኮንን ጋር እንነጋገራለን ፡ የትግሬው ራስ የጠየቁትን የጦር መሣሪያም ሆነ እህል የማንልክ መሆናችንን እናረጋግጥላቸዋለን ፡ ራስ መኮንንም የኛ ተባባሪ የሚሆኑበትን ዘዴ እንቀይሳለን” ብሎ አዲሱን መመሪያውን አስረዳ ፡

በዚሁ መሠረት ወደ መቀሌና አዲስ አበባ መልእክተኞች ገጸ በረከት እያስያዘ መስደድ ጀመረ ፡ እንደ ተመኘውም የራስ መኮንንና የአጼ ምኒልክን ወዳጅነት አለዝቦ ለመያዝ ከቻለበት ወቅት ላይ ደረሰ ፡ ከዚያ ቀጥሎም በትግሬይ ውስጥ የነበረውን ሁኔታ የሚያጠኑለት ሰዎች በልዩ ልዩ ምክንያት እየሰደደ ያገኛ ቸውን መረጃዎች ከሁኔታዎች ጋር ካገናዘበ በኋላ ፡

“አሉላ መቼም ወመኔ ነው ፤ ለምኒልክም ሆነ ለኛ ጠላት ነው ፡ አሉላ መንገሻን ከራሱ አስቀድሞ ይሆን ሁሉ ዘራፊ ጥሙ የሚ ፈልገው ለኛም ለበላ ሆኖ ለመታየት የሚመከረውና ይሆን ሁሉ ይቀበለዋል የሚሉት ፤ ከእኛ በሚያገኘው ሆነ በመንገሻ ስም የሚሰጠውን የጦር መሣሪያ ሰብስቦ በኛ ላይ ከንቱን እንደገና



ለማገልገልና አሥመራን ለመያዝ መሆኑን በትክክል ደርሼበታ ለሁ ፡ ትግሬዎቹንም እርስ በእርሳቸው እያጋጩ ዕረፍት የነሣ ቸው እርሱ ነው ፡ ስለዚህ በተቻለ መጠን በርከት ያለ የጦር መሣሪያ ወደ ትግራይ እንዳይገባ በብርቱ መጣር አለብን ” ብሎ ለሹማምንቱ አስረዳ ፡

በዚህ መመሪያ መሠረትም ራስ መንገሻ ፡ ‘መሣሪያ ላኩ ልኝ’ እያሉ ለሚሰዱት መልእክተኛ ሁሉ ፡ ‘በመካከላችን ያለው ወዳጅነት እንዲቀጥል እደርጋለሁ ፡ የጦር መሣሪያ ለመላክ ግን አለቆቼን ጠይቄያለሁና ይታገሡኝ’ እያለ ከመመለስ በቀር ጠመ ንጃ ቀርቶ ጥይት ጠብ የማይለው ሆነ ፡

በዚያው ወቅት ልጅ በየነ የሚባሉ የጉበዝ አለቃ በርከት ያሉ ኮበሌዎች ሰብስበው ሠራዬ ውስጥ ከመንደር መንደር እየ ተዘዋወሩ ጣሊያኖችን ማስቸገር በመጀመራቸው ጣሊያኖቹም ‘በየነን አብልታችኋል ፡ አጠጥታችኋል ፡ አሳድራችኋል ’ እያሉ ሕዝቡን ክፉኛ ይቀጡት ጀመር ፡ በዚህ ጊዜም ራስ አሉላ ልጅ በየነን አስጠርተው ፡

“በማህ ልጅ ሐሳብህንና ሥራህን ወድጄዋለሁ ፡ ግን አንተ በተንኮሰካሰቸው ቁጥር ጣሊያኖቹ ደግሞ ሕዝቡን እያሰቃዩት ነው ፡ አንተ ጣሊያኖች ሠራዬን አይነኩብኝ ነው የምትለው ፡ እኔ ደግሞ ምፅዋንም ጭምር ለማስለቀቅ ነው ምኞቴ ፡ ለዚህ ሁሉ የሚረዳን ደግሞ የጦር መሣሪያ ስናገኝ ነው ፡ መሣሪያ እንዲሰጡንና እንደዚሁም በምፅዋ በኩል ለማስገባት እንዳያስ ቸግሩን መንገዱን እያመቻቸን ነው ፡ በዚህ የተነሣ አሁን እነርሱን መነካካቱን አልፈቀድኩትም ፡ አንተም አንድ ቀን አገርህ ታላቅ ሙያ ትሠራለታለህና እንዳትቀጭ ተጠንቀቅ ፡ እስ ከጊዜው ድረስ ከዚሁ ከኔ ቤት ዐርፈህ ተቀመጥ” ብለው ልጅ በየነን እንደቁም እስር አድርገው በቤታቸው አቆዩዋቸው ፡ ባራቴሪ ግን ፡ ‘በየነ ብዙ በደል ፈጽሞብኛልና እጁን ሰጥቶኝ ለፍርድ አቅርበዋለሁ’ ብሎ ለራስ አሉላም ሆነ ለራስ መንገሻ መልእክት ሰዶ ነበር ፡ ግን እርሱ የጦር መሣሪያ እንደ ከለከለ ሁሉ ራስ አሉላም ፡ ‘የበየነን እጅ አሳልፌ አልሰጥም’ ብለው እምቢ አሉ ፡

# መንገሻ አሉላና ምኒልክ

ወደ ትግራይ ምንም ዐይነት የጦር መሣሪያ እንዳይገባ ኢጣሊያኖች መከልከላቸውንና ፣ ራስ አሉላም የአደራ ልጃቸውን ለማንገሥ የጀመሩት ዝግጅት እየተሰናከለባቸው መሔዱን ፣ አጼ ምኒልክ በልዩ ልዩ መንገድ ካረጋገጡ በኋላ ፣ የትግራይ መኳንንት እርስ በርሳቸው እንዳይጣሉ ወይም እንዳይሸፍቱና ሕዝብ እንዳያስቸግሩ ፣ ያለዚያም ደግሞ ፣ ወደ አሥመራ ሔደው ለጣሊያኖች እጃቸውን እንዳይሰጡና ጠቅላላ የሆነ ውርደትና ውድቀት እንዳይደርስ ስለ ሥጉበት ሽማግሌዎች በአስቸኳይ ወደ መቀሌ እንዲሔዱ አዘዙ ።

ለዚህም መልእክትና ኃላፊነት ብላታ ተሰፋይ ሕንጣሉ የተባሉ አዛውንት ተመረጡ ። ይህን ነገር ራስ አሉላ እንደ ሰሙ ደግሞ ተቆጡ ። በጉዳዩም ከራስ ስብሐት ጋር ተነጋገሩበትና መንገሻ ወደ ሸዋ ከመሔድ የማይገቱ ከሆነ እርሳቸውን አስወግደው 'ጃንሆይነቱን ከነጣጣው ለራስ ስብሐት' ለመስጠት ማሰባቸውን ለስብሐት ነገሩዋቸው ።

በዚያን ጊዜ ሁለቱ ራሶችም ከስባት ሺህ የሚበልጥ ወታደር ነበራቸው ። ነገር ግን ራስ መንገሻን ጦርነት ከመግጠም ፣ ለመበቀል ግብር ሲያገቡ በድንገት መድረስና ስልፋቸውን አሳይተው ታማኝነታቸውንም ለጌታቸው ከገለጹ በኋላ ፣ ከጉዞአቸው እንዲቀሩ ለመጠየቅ አሉላና ስብሐት ተስማሙ ።

በተባለው ዕለት ያወጡትን ስልት ለመፈጸም የነታቸው ሁኔታ ደግሞ ደረሰ ። ራስ ሐጐስ በርከት ያለ ጦራቸውን አስልፈው በድንገት መቀሌ ገቡ ። በዚያ ላይ ነገር ቢያነሡ ሁኔታው የማያምር እንደሚሆን በማወላወል ላይ እንዳሉም ራስ መንገሻ መኳንንቱንና የጦር አለቆቹን ሰብስበው ፣ "አባቶቼ ወንድሞቼ



እስከ ዛሬ ድረስ የአናንተን ምክር በማዳመጥ የአጼ ዮሐንስን ዘውድና ዙፋን ለመያዝ አቅደን ነበር ። ግን እግዚአብሔር ያልፈቀደውን መመኘት በሀገር ላይ ብርቱ ጉዳይ እንደሚያመጣ በመረዳት አጼ ምኒልክ ለመቅረብና ሰላም እጃቸውን ስለ ዘረጉልኝ መሔዴን እንድታውቁት" ብለው ተናገሩ ። እጨጌ ቴዎፍሎስም ተከትለው "እግዚአብሔር በቀመን እርቁን ልኮልዎታል ። ከታገሡ ፣ በጸሎት ከለመኑትም ያሰቡትን ይሰጥዎታል ። ያባትዎን አያሳጣዎትም' ፣ አሁንም ከወንድሞ ጋር ልታረቅ ብለው ንጉሠ ነገሥቱ ሲጠይቁ ገሸሽ ማለት ከአምላክ ትእዛዝ መውጣት ነውና መልካም አይደለም ። እግዚአብሔር ይከተልዎ" አሏቸው ።

ራስ ሐጐስም ፣ "አገርዎንና አልጋዎን እንጠብቅታለን ፤ ይሔዱ ማለፊያ ሥራ ነው" ብለው ደገፉ ። ይህን ከሰሙ በኋላም ራስ ስብሐት አጋሜያቸው ሲገቡ ፣ አሉላ ብቻ መቀሌ ቀርተው እደ ፋና መንገሻ ወደ አዲስ አበባ እንዳይሔዱ እየፎከሩም እየሰደቡም ቢቀሩ መንገሻ ዝግጅታቸውን ከመቀጠል በቀር አሉላን ሊያዳምጡ የማይፈልጉ ሆኑ ።

ራስ መንገሻ ፣ ከአጼ ምኒልክ ዘንድ ይቅርታ ፣ ሹመትና ሽልማትም ሲፈልጉ ከባራቴሪ ጋር የጀመሩት ወዳጅነትም እንዳይቋረጥባቸው ጽኑ ምኞት ነበራቸውና ፣ እርሱን ለማስደሰት ቢሉ ልጅ በየነን እንዲልኩለት ራስ አሉላን አዘዙ ። አሉላ ግን ፣ 'አገርና ሕዝብ እንዳያስቸግር ብዬ እኔ ብይዘውም ፣ ወገኔን አሳልፌ ለጣሊያንስ አልሰጠውም' ብለው እምቢ አሉ ። ራስ መንገሻ ግን የባራቴሪን ወዳጅነት ፈልገውታልና ራስ ሐጐስን ከነወታደሮቻቸው ወደ ራስ አሉላ ሠፈር በድንገት እንዲሔዱና ልጅ በየነን ከአሉላ ቤት አውጥተው ለባራቴሪ እንዲልኩለት አዘዙዋቸው ።

ራስ ሐጐስም እንደ ታዘዙት በርከት ያሉ ወታደሮቻቸውን አስልፈው ፣ ራስ አሉላ ወደ ቤተ ክርስቲያን በሔዱበት ሰዓት ከግቢያቸው ሰተት ብለው ገብተው ልጅ በየነን አውጥተው ወደ ኤርትራ ሰደዱትና ከጠላቶቹ እጅ ገባ ። ከዚያ በኋላ ራስ አሉላም በነገሩ እጅግ ተናደዱና የራስ መንገሻን አሽከሮች እያስያዙ አሳሰሩ ። ተገለውም ራስ መንገሻን ከሥልጣናቸው ለማ

ውረድ ማሰባቸውን ለራስ ስብሐት አስረድተው፣ ዐድዋ ላይ ነጋሪታቸውን ማስጐሰምና ሠራዊታቸውን ማስከተት ጀመሩ።

ራስ ስብሐትም ከአጼ ዮሐንስ ወራሽ ጋር ጦርነት መግጠሙ በትግራይ ሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ ተቃውሞ እንደሚያስነሣባቸውና፣ መንገሻንም ለመደገፍ ሲል ባራቴሪ ከፍ ያለ ርዳታ ሊያደርግ እንደሚችል በማመን፣ የአክሱም ካህናት፣ እጨጌውና የሌሎቹም አድባራት መሪዎች፣ በድንገት ቱግ ያለውን የአሉላን ቁጣ እንዲያበርዱላቸው ማስለመን መረጡ። ካህናቱም የራስ ስብሐትን ሐሳብ በመደገፍ ዐድዋ ሔደው አሉላን ለመኑ። የቀሳውስቱን ልመና መቃወም የማይቻላቸው አሉላም፣ ሲያስጐስሙ የነበሩትን ነጋሪታቸውን ከነዱላው አሸከመው፣ ተንቤናቸው ገቡና ዝቀሊ በሚገኘው ምሽጋቸው አደፈጡ።

አሉላ ከዐድዋ ወደ ተንቤን ሲሔዱ ነጋሪታቸውን ብቻ አልነበረም የወሰዱት። ዐድዋ ተቀማጭ የነበረውን ዲ.ማርቲኖንና ሌሎች አምስት ጣሊያኖችንም እየነዱ ወስደው ነበር።

ዝቀሊ ከምሽጋቸው ገብተው፣ 'የመንገሻን የበላይነት አላውቅም፤ ጣሊያኖቹን እንድፈታላችሁ ከፈለጋችሁም ከቤቴ ነጥቃችሁ የወሰዳችሁትን የሠራዊቱን ጀግና በየነን መልሱልኝ' ብለው አሻፈረኝ አሉ።

ከዚያ በኋላ "ወዲ ቁቢ" እና የአጼ ዮሐንስ አልጋ ወራሽ ለዱላ ተሰላለፉ። የትግራይ ሕዝብም ምንም እንኳን ለአሉላ ጀግንነትና ሙያ ታላቅ አክብሮት ቢኖረውም፣ ከራስ መንገሻ ጋር ለጦርነት መሰለፋቸውን አልወደደላቸውም ነበር።

ራስ መንገሻም ቢሆኑ የአደራ አባታቸውን ቢያከብሩዋቸውና ከቃላቸው ላለመውጣት ቢጠነቀቁም፣ እስከዚያ ድረስ 'ማን አለብኝ' ማለታቸውን በቸልታ ሊያልፉት የሚቻላቸው አልሆነላቸውም። በዚያ ወቅት የአሉላን ውድቀት የማይመኝ አልነበረም ለማለት ይቻላል። አጼ ምኒልክ 'መንገሻን የሚያሳስተው አሉላ ነው' ይላሉ። ባራቴሪ፣ 'አሉላ እንደገና አሥመራን ለመያዝ የረቀቀ ዘዴውን እያውጠነጠነብኝ ነው'' ይላል። የትግራይ መኳንንትም 'ወዲ ቁቢን' የሚይዝ ወንድ እንዴት ጠፋ፤ይላሉ። ራስ



መንገሻም 'ብችላቸው ብችላቸው የምፈራ መስላቸው !?' ማለት ጀምረዋል።

ሐጐስም ቂማቸውን ሁሉ አደሱና ተነሡ። 'የአጼ ዮሐንስ ዘመን መንግሥት እንደዚህ ፈጥና የወደቀው በወዲ ቁቢ የተነሣ ነው፤ መክረን መክረን አልሰማን ብለው ነው፣ ስለዚህ የደረሱትና አሁንም ይፍቅዱልኝ እጁን እንጠልጥዬ ላምጣልዎ' ብለው መንገሻን ለመኑ። 'ራሴም እዘምታለሁ' ብለው ራስ መንገሻም ነጋሪታቸውን አስደለቁና ከሁለት ሺህ በላይ የሆነ ወታደር ሰብስበው፣ ራስ ሐጐስንም አዝማች አድርገው፣ አሉላንና ከመቶ የማይበልጡ ወታደሮቻቸውን ደብቃ ወደ ነበረችው ዝቀሊ ዘመቱ፤ የአሉላ መንደር በመንገሻና በሐጐስ ሠራዊት ተከበበች። የምስቱ ማኅበርተኞች መፋጠጥ በመላዋ ትግራይ እጅግ ከባድ ጨለማ ጣለ።

ራስ አሉላም ከእርዳቸው ወጥተው፣ በኩፊት ጦርነት ጊዜ የማሕዲስቶችን የጦር አሰላለፍ ወለል አድርጎ ባሳያቸው መነጽራቸው የሁለቱን ራሶች ጦር አሰላለፍ ተመለከቱት። ያች ቁብታ መንደራቸው ተከባለች። መነጽራቸውንም ለአሽከራቸው ሰጡና፣ "ዮሐንስ አደራ በሰጡን ሰው ላይ አልጨክንም እንጂ የሠፈረበትን ቦታ ለይቸዋለሁ። እርሱን ብቻ አጥፍቼም ልጠፋ ይቻለኝ ነበር። ግን አላደርገውም፤ እንደ ሐጐስ የመሰለ ከንቱ ሰው የሚመራኝ አይደለም። በኔ የተነሣ የዝቀሊ መንደር አይቃጠልም። ክብሬንና ስሜን እንደ ጠበቅሁ ዐልፋለሁ። አይ አገሬ! አይ ኢትዮጵያ እያነሰሽ መሔድሽ ሲያንገበግበኝ፣ ብለን ብለን ደግሞ እኛው በኛ እንተላለቅብሽ ?ጠላት እኛን እያፋጀ እኛን እያታለለ፣ በእኛ እየማቀ ለተት ብሎ ሊገባ ነው ? የሚመክተው ከንዴ ሊጠፋ ነው?" ብለው ሊተክዙ ቆዩና፣ ደጃዝማች ዐባይንና ደጃዝማች ተድላ ፈንጃን አስጠርተው፣

"በኛ አገር ጠላት መደሰቱ ነው። አገር ወገንና ታሪክም አንገቱን መድፋቱ ነው። አጼ ዮሐንስን ወትውተው ወትውተው ሳይሳካላቸው የኖሩት እነሐጐስ፣ መንገሻን አባብለው አሸንፈው ጦር ጭነው መጡብኝ። እኔ እንደነርሱ አይደለሁም፤ ያገር ግፈረያ አልሆንም፤ በመንገሻም ላይ ጥይት አልተኩስም።

የዮሐንስ ዐፅም ይፋረደኛል ። እንግዲህ ተዘጋጁና ወደ በረሃችን እንገባለን ። እነዚህንም መዘዞች ጣሊያኖች አቆራኝታችሁ አስተድሙአቸው" ብለው ትእዛዝ ሰጡና መቶ የማይሞሉ ታማኝ ወታደሮቻቸውን አስከትለው ፣ እስረኞቹን ጣሊያኖች አስተድው ከመንደራቸው በእኩለ ሌሊት ወጥተው ወደ አበርገሌ ሲጓዙ ፣ ደጃዝማች ዐባይ እስረኞቹን ጣሊያኖች እንደ ያዙ ከድተው ከራስ መንገሻ ሠፈር ገቡና እጃቸውን ሰጡ ። ራስ አሉላም ከተራራ ላይ ወጥተው የመጨረሻ ምሽጋቸውን ማዘጋጀት ጀመሩ ።

የሦስቱን ራሶች ለዳላ መሳሳለፍ ባራቴሪ በሰላዮቹ አማካይነት እንደ ሰማ በደስታ ፈነደቀና ፣ ለራስ መንገሻ ፣ "የእርስዎን የበላይነት የሚገነቀው የአገርዎ ጠላት የሆነውንና ለኢትዮጵያም እንቅፋት የሆነው አሉላ የሚሠራውን ድፍረት ሰምቻለሁና ተከታትለው ማጥፋት ይገባዎታል ። እርሱን ካጠፉ ከእኛም ጋር የማይናወፅ ወዳጅነት ልንመሠርት እንችላለን" ብሎ ላከባቸው ።

ለራስ ሐጎስም ፣ "አሉላ ካመለጠዎ የታወቀው ጀግንነትዎና ዝናዎም መገቢያ መሆኑን እንዳይዘነጉት ፤ እርሱን ካጠፉ እኔም የምችለውን ያህል እረዳዎታለሁ ። ራስ መንገሻ እንኳ ችላ ቢሉት እርስዎ መበርታት እንደሚገባዎት አምናለሁ" ብሎ በምሥጢር ላከባቸው ።

ራስ መንገሻና ራስ ሐጎስ ፣ አሉላ ከተከበቡበት ማምለጣቸውን ሰምተው ሠራዊታቸውን ወደ አበርገሌ ለማዝመት በተነሡበት ሰዓት ደግሞ እጨጌ ቴዎፍሎስና የአገር ሽማግሌዎች በመካከሉ ገብተው ከወታደሮቹ ቀድመው በሦስቱ ራሶች ሠፈር መጓጓዝ ጀመሩ ።

ከራስ አሉላ ዘንድ 'ይቅር በለኝ' የሚል ቃል ይዘው ከራስ መንገሻ ሠፈር ደረሱ ። "እኔማ መቼስ ከእናንተ ቃል መች እወጣለሁ ፤ የእርሳቸውንስ ልመና እንዴት እምቢ እላለሁ ፤ እርሳቸውንም ምከሩልኝ ። ዐድዋ የነበሩትን ጣሊያኖች በግዛታቸው አሥመራ የሚገኙት ጣሊያኖች በሙሉ አዝነዋል ፤ ጀኔራል ባራቴሪም እጅግ ተቆጥቷል ። ከእንግዲህ ወዲያ መቼም ከእነርሱ ጋር መተያየት አይችሉም ። እኔም ቀኑን እጠብቃለሁ እንጂ ከእጼ



ምኒልክ ጋር ጦርነት አልገጥምም ። እርሳቸውም ከእንግዲህ ወዲያ በአባትነታቸውና በክብራቸው ተከብረው ዐርፈው ይቀመጡ እንጂ በኔና በእጼ ምኒልክ መካከል እንዳይገቡ ምከሩልኝ" ብለው እርቁን ተቀበሉ ።

ሁለቱ ራሶች ዐድዋ ሥላሴ ተገናኝተው በመሐላ ፣ 'ይቅር ይቅር' ተባባሉ ። ከዚህ በኋላ የወረዳ ገዥነት ሹመትና ሁለት መቶ ጠመንጃዎች ራስ መንገሻ ለራስ አሉላ ሰጧቸው ። የሁለቱ ራሶች እርቅ ፣ በአራተኛው ቀን አሥመራ ደርሶ ከባራቴሪ ጆሮ እንደ ገባ በንዴት ጦፈ ።

'አሉላ ከመንገሻ ጋር ከታረቀ ነገሩ በቃው አለቀለት ፤ ከእንግዲህ ወዲያ ጦርነት እንጂ ሰላም የለም ። አሉላ እኛን ወግቶ ምፅዋንም ለመያዝ የማይተኛ ምኞት እንዳለው በየጊዜው አረጋግጦልኛል ። የእርሱን የሩቅ ዕቅድም መንገሻም ሆነ ምኒልክ አልደረሱበትምና ለመንገሻ የፈለገውን ሁሉ ሰጥተን የአሉላን እጅ መረከብ አለብን' ብሎ ለሹማምንቶቹ ቁርጥ ያለ ሐሳቡን ገለጸላቸው ።

ከአንዲት ወረዳ ፣ ያውም የከብት እልቂትና ድርቅ ከገረፋት ወረዳ በሚገኝ ገቢ ፣ ከሁለት መቶ በላይ የሚሆኑ ወታደሮች ለማስተዳደር ደግሞ አሉላ የማይቻላቸው እየሆነ ሔደ ። ማዘን መተከዝና መበሳጨትም የዘወትር ጓደኞቻቸው ሆኑ ። እንደ መኳንንቱ ርስት ጉልት የላቸውም ፤ በገቢው የሚተዳደሩበት ከዘር የወረሱት አውራጃም የላቸውም ፤ ከገበሬ አብራክ የተገኙ በዕውቀታቸው ፣ በቆራጥነታቸውና በችሎታቸው ብቻ የንጉሥ ነጋሪት እንደ ራሱ እስከ መሆን የደረሱ ቢሆኑም ፣ የነበራቸውን ገንዘብ ሁሉ ለአክሱም ጽዮንና ለሌሎችም ገዳማት ሰጥተው በዕለት ጉርስ ብቻ የሚኖሩ መሆናቸውን መላው ትግራይ ዐውቋቸዋል ። ከደረሰባቸው ችግር የተነሣ ፣ 'ምነው ከጌታዬ ጋር ድር ቡሽ አስቀርቶኝ ቢሆን ኖሮ!! አዬ ፈጣሪዬ ፣ እጄ እስኪ ታሰር ድረስ ፣ ዕድሜ ትሰጠኝ !?' ብለው እስኪማረሩም ችግር ይገርፋቸው ጀመር ። ድንገት ወጥተው ወደ ሐዲቡት አዘቅዝቀው ወርደዋል ። ያውም ፣ በአስደናቂ ፍጥነት ድህነቱ ደግሞ መከተሉ!

ብቻውን አልሔደባቸውም ፤ ውርደት አስከትሎ ኃፍረት አዝ
ታዝሎባቸዋል ።

‘ወዲያልኝ ወዲያ ! ለዚህ ነው ያቆየኸኝ ?’ ከአበርገሌ ተራራ
ከወረዱበት ዕለት ጀምሮ የሚያሰሙት ሙሾአቸው ነበር ።

ነገሩ ሁሉ እየከበዳቸው ፣ ቀንና ሌሊት አንድ እየሆነባቸ
ሔደ ። የትግራይ መኳንንትም ‘የድሃ ልጅ ጥጋብ አይችልም
በድህነቱ በሰላም ይኖራል ’ እያሉ እንዲሚዘብቱባቸው አሉ
ሰሙ ።

ያች በአምስትና በዐሥር ሺህ ወታደር ስትርመሰመስ የነ
ረችው ዝቋሊ ጭር ብላለች ። በአሉላ ግቢ ሃምሳ የማይሞ
ወታደሮች ውር ውር ይላሉ ። ከጡዋት እስከ ማታ ግብር እን
ገባበት የሚውለው የአሉላ አዳራሽ የዝንብ ገበያ ሆኗል ። በ
ሲማታ የነበረው የአሉላ እጅ ተሰብስቧል ። በጠጅ ሲራጭ
በረው አሳላፊ ውሃ ማቅረብ አቅቶታል ። ‘ይኸው ነው ኑሮ
እኔ አሉላ እንደዚህ ሁኜ ነው የምኖረው አውሬ ገድየስ ብበላ
እያሉ በሚያቅማሙበት ወቅት አሽከራቸው እየሮጠ ጠጋ ብሎ
“ኧረ! ጌቶች ተከበብን ፣ ይነሡ እንውጣ!” ሲላቸው “አሉ
ወንዱ ! የዮሐንስ ቀኝ እጅ !!” አሉና ዲሞትፈራቸውን ይዘ
ወጡ ። በርካታ ጦር አውራውን መንገድ ይዞ ሲያመራ ‘በሩ
ይታያል ። ወዲያው ጥሩምባ አሰነፉ ። እነዚያው ውርው
የሚሉት ወታደሮቻቸው ከተቱ ። መቶ የማይሞሉ ነበሩ ። እነዚያ
አሰለፉና ወደ ሚጓዘው ጦር ገሥግሠው ገጠሙት ። ያ በግ
የነበረ ወታደር ተበታተነ ። የራስ መንገሻ ጦር ነበር ። ወ
ሸዋ የሚጓዝ ነበር ። እግረ መንገዱንም አሉላን ወደ መቀ
ለመውሰድ ታዞ ነበር ። የአሉላ ማመፅ እንደገና በዐድዋ
በመቀሌ ሲሰማ ታላቅ ድንጋጤ ፈጠረ ። ከሁሉም ከሁሉ
ዐድዋ የነበረው ዲ.ማርቴና እጅግ ፈራ ። ገሥግሠው እ
እንደገና የሚይዙት መስሎት እጅግ ተደናገጠ ። ዐድዋ ጠበ
ችው ። ወደ ቤተ ክርስቲያን ሩጦ ገባ ፣ ቀሳውስቱ አባረሩት
ከዚያ ወጥቶ ቲ.ጂ.ቤንት ወደ ተባለ እንግሊዛዊ የቅርስ ጥና
ባለሙያ ቤት ሔደ ። እንግሊዛዊውም በደረሰው ነገር ተደናግ
ስለ ነበር ፣ “የከተማው ሕዝብ ምስቅልቅሉ ወጥቷል ፤ በ



በት ይራራጣል ፤ አሉላ የመንገሻን ጦር መግጠማቸው እንደ ተሰማ ፣ ‘አንዳንዱ ዐድዋ ሊገቡ ተቃርበዋል ፣’ እያለ ወሬውን ያነጉ ደዋል ። ከዚህ ከገቡም ‘የከዱዋቸውን ጠላቶቻቸውን ሁሉ እጅና እግር እየቆረጡ ሊቀጡ ወስነዋል’ እየተባለ ይወራል ። ምን ይሻላል ?’ ብሎ ሲያማውተው ያ ዐድዋ ተቀማጭ የነ በረ ማሊያንም በፍርሃት እየተርበደበደ ፣ “የድሮ ጠላታቸው እኔ ስለሆንኩ አይለቁኝም ይቆርጡኛል” እያለ ያለቅስ ነበር ። ‘ራስ አሉላ ከተራራ ጫፍ ላይ እንደ ጥቁር ጢስ ተመስለው የሚ ወጡ ሰይጣን ናቸው’ እየተባለ ይነገር ስለ ነበረ ፣ የዐድዋው አገር ገዥ ደጃች አምባዬም ሰይጣኑ አሉላ ወደ ቤታቸው እንዳ ይደርሱባቸው ከበራፋቸው ላይ መስቀል ሰቀሉ ። በዚያ ወቅት ዐድዋ በታላቅ ሽብር ብትመታም ፣ አሉላ መቀሌን ወይም ዐድዋን ለመያዝ በቂ ጉልበትም አልነበራቸው ። ጉልበታቸው እንኳ እንደ ዱሮው ባይጓሸሽ ኑሮ ፣ መንገሻን ለመያዝ ወደ መቀሌም ቢያመሩ ባራቴሪ በዝምታ አይመለከታቸውም ነበር ። ራስ መንገሻም ዱሮ የራስ አሉላ አሽከር የነበሩትንና ለእርሳቸው ገብተው የነበሩትን ደጃች ዐባይን በርከት ያለ ጦር ሰጥተው አሉላን እንዲወጉ አዘመቱ ።

ራስ አሉላም ነገሩን ሰሙና ፣ ‘ምንስ ቀን ቢከዳኝ አንተም ልትወጋኝ ትሰለፋለህ ?ያሳደግሁህና ለዚህ ማዕረግ ያደረስኩህ እኔ አሉላ አይደለሁም! ከጨከንክ አልወጋህም ናና ያዘኝ’ ብለው ላኩባቸው ። ዐባይም በድሮው ጌታቸው ላይ የሚጨክን አንጀት አልነበራቸውምና ከነሠራዊታቸው ወደ አሉላ ተጠቃ ለው ገቡ ።

ከዚያ በኋላ አሉላ ከሁለት መቶ የሚበልጡ ወታደሮች ለመሰብሰብ ቻሉና እንደ ተለመደው ወደ አበርገሌ ተራራቸው ወጡ ። የዚህም ወሬ አሥመራ ደረሰና ፣ “የእርስዎና የትግራይ ዕድል የሚወሰነው ከእንግዲህ ወዲያ ነው ። ርኩሱ ሰይጣን እንዳያመ ልጠዎ!! ከዚያ ተራራ ላይ እጁ ካልተያዘ ወይም ሬሳው ካልተ ገኘ በእርስዎ ሕይወት ላይ መጥፎ ነገር ሊደርስ እንደሚችል፣ በኤርትራ ከሚገኙ ታላላቅ ቤተ ክርስቲያኖች የተላኩ ፣ ምሥጢሩ በርእይ የተገለጸላቸው አባቶች ልከበውብኛልና ፣ አሉላ መቀጣጫ

ካልሆነ ፣ ለእርስዎ ያሠጋዎታል” ብሉ ባራቲሪም መልእክተኛ ነጋሪ መንገሻን አስጠነቀቁ ።

“ከእንግዲህ ወዲያማ መቀጣጫ ካልሆነ በቀ ለቀ ብሉል... የነበረው መኳንንት ሁሉ በረሃ መግባቱን እንዳይዘነጉ ። ... ቀዱልኝ እጁን ወይም ራሣውን ካላረከቡዎ ። ለእሱላ ምሕ... ማድረግ ወይም ጊዜ መስጠት አገር ማበላሸት ነው” ብለው ... ሐጐስም መንገሻን መወትወት ጀመሩ ። የትግራይ መኳን... ተራ በተራ እየገቡ ፣ “ወይ እኛን ያለዚያ አሉላን ይምረ... እያሉ እቅጩን መናገር ቀጠሉ ። ‘አሉላን ዛሬ ካላጠፉ የ... ወትሮ ፍጻሜ መታረቡን ይወቁ’ ተብሉ ከታወቁ ባሕታው... ተልኳል የሚለው ማስጠንቀቂያ ዕለት ዕለት የሚሰማ ሆነ ። “አሉላን ለመያዝ ወይም ለማጥፋት ለሚያደርጉት ዘመቻ ... መግሪያ ልኬልዎታለሁ ። ለወያራቱም የፈለጉትን ያህል ር... እልክልዎታለሁ” የሚል ማበረታቻ ከባራቲሪ ከደረሳ... በኋላ ፣ “ምንም እንኳ እጁ የሐጎስ ኪታሉ አትወጣ በ... ኝም ከዚህ ይበልጥ መቻል አይሆንልኝም ። ስለዚህ እሉ... እጁን ሰጡኝ ያለዚያ ራሣውን አሳዩኝ” ብለው መንገሻ ... ጐስ ትእዛዝ ሰጡ ። ራስ ሐጐስም ከራሳቸው ጦር ሌላ የ... መንገሻንና የሌሎቹንም መኳንንት ወታደር አስከትለው አ... የነበሩበትን ተራራ ዙሪያውን ማስከበብ ጀመሩ ። በዚህ ጊዜ... ‘ትግሬዎች አንድ ጀግና ማሳደር ፣ አንድ ባለወኔ ወረኛ ማ... አቅቷቸው የኢትዮጵያን ስምና ክብር በባሕር ማዶ ያስወቀ... እንዱን አሉላን ካላጠፉን ብለው ከበቡቸዋል’ የሚለው ... ከትግራይ እየበረረ አዲስ አበባ ገባ ። አጼ ምኒልክም ነገሩን ሲሰ... እጅግ አዘኑና ፣ በነገሩም ከመኳንንቱ ጋር ከተመካከሩበት በኋ...

“ምንም እንኳን እኔን ባይወደኝም ፣ ትናንት በኢትዮ... ጠላቶች ላይ ያን ሁሉ ድል ያስገኘውን አሉላ መንካት ፣ የሁላ... ንም ውርደት ነው ! ያገር ውርደት ነው ! ነገ ደግሞ ለክፉ ... ይሆነናልና ፣ አንተን ካስቸገረህ እኔ ዘንድ ላከልኝ ! እኔ በመሉን ... እንደ ብጤቱ አሳድረዋለሁ” ብለው እምዬ ምኒልክ መልእ... ወደ ራስ መንገሻ ሰደዱ ።

አሉላን ለማጥፋት የቸኰሉት የትግራይ መኳንንትና ባ... ቲሪ ደግሞ ተጋግዘው ውርንቱን ጀመሩ ። ሁለት ወር ታ...



ወታደሮች ይዘው ተራራ ላይ ወጥተው በረሃብ ሲገረፉ የከረመት እሉላም ፣ በወኔ ስለ ወኔ ብቻ እየተከላከሉ ለንዋብተው ድል ሆኑ ። ወዲያውም “መንገሻ ይቅር የሚለኝ ከሆነ መማሪያዬን እንደ ያዘኩ መቀሌ ልግባ ! ያለዚያ ራሣዬን ትትታችሁ ውሰዱለት እንጂ ከነሕይወቴ እጄን አልሰጥም ! የኔ መጥቶ ደለ የሚላችሁ ያገሬ መኳንንት! ነገ ታፍራላችሁ ። ጣሊያን ግን ! ድርቡሽ ግን ፣ ጉበጡ ግን ይሰቅባችኋል ፣ ይገታችኋል ፣ ዘርም ያፍርሳችኋል” ብለው መልእክት ወደ መቀሌ ዐድዋና አክሱም ሰደዱ ።

እጨጌ ቴዎፍሎስ ፣ ከአክሱም ገሥግሠው መቀሌ ገብተው ለሰው ተኍ አሉላ ምሕረት እንዲያደርጉ ፣ ራስ መንገሻን እያማገሱና እያወገዙ በሚለማመኑበት ሰዓት ፣ ከአጼ ምኒልክ የተላኩት መልእክተኞች ቀንና ሌሊት ገሥግሠው መቀሌ ደረሱና የንጉሠ ነገሥቱን መልእክት ለራስ መንገሻ ነገሩ ።

የዐድዋና የአክሱም ካህናትም ፣ “የወንድምዎን የምኒልክን ልመና ይቀበሉ ። ለባራቲሪና ለሐጐስ ብለው ፣ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር መቀያየምዎን እንደማናየም” የሚል ሐሳብ አቀረቡና እዉጌው መኳንንቱና ካህናቱ በተገኙበት ሁለቱ ራሶች ታረቁ ። ወዲያውም በቂ የሆነ መተዳደሪያና አምሳት መቶ ወታደር ለራስ አሉላ ተሰጠ ።

“ሰይጣኑ አሉላ ብቻም አይደለ ። ቄሱም ፣ አቡኑም ፣ መንገሻም ፣ ምኒልክም ፣ መኳንንቱም ፣ ሌቱም ፣ ወንዱም አበሻ በሙሉው ሰይጣን ነው !! ዲያብሎስ ነው ። በዓለም ላይ ተመሳሳይ የሌላቸው ሰይጣኖች ናቸው ! በታኝ እንግዲህ በታኝ ያበሻ ነገር በታኝ ምኒልክ አሉላን ከሰፈሩ ፣ ለአፍሪካ አግባጅ ከሆኑ በታኝ! ሰይጣኑን አሉላን እያስጋበዙ እኛ ያስገቡታል በታኝ” እለ ጀኔራል ባራቲሪ ዲ.ማርቲኖ የሳበሩትን ወረቀት ማመን አቅቶት አፍጥጦ ከተመለከተችው በኋላ ። ጠረጴዛውንም በቡጢ ጠብ ቀውና ከተቀመጠበት ተነሥቶ ከቤቱ በረንዳ ላይ ሆኖ ፣ “አሉላ ይገባበታል” ብሉ የሚጠራጠረውን የአሥመራን ደቡብ አቅጣጫ እየተመለከተ በጥብቅ እንዲጠበቅ ትእዛዝ ሰጠ ።

ሁለቱ ራሶች ከታረቁና አሉላም በቂ ኃይል ይዘው በሠ
ራቸው ሆነው እንዲጠብቁ አደራ ከተባሉ በኋላ ፣ መንገሻም ወ
ሸዋ ለመጓዝ ዝግጅታቸውን ቀጠሉ ። "ከእንግዲህ ከእንግዲህ በኋ
ትግሬም መንገሻም የዮሐስም ኑዛዜም ምኑም አይደሉ ። በተዋረ
ኩበት ትግሬ አልኖርም ። የመንገሻ አገር ጠባቂና አማካ
ከምሆን የምኒልክ ግብረ በላ ሆኜ ደጅ እጠናለሁ ። ሲሆንም የ
ረብ ምላሽ ግዛቴን አስመልሳለሁ" አሉ ራስ አሉላ ከአጨ
ቴዎፍሎስ ጋር ሲጫወቱ ።

"ማለፊያ አስበዋል ። በእውነቱ ከአምላክዎ ጋር የሚታረ
ቁበትን መንገድ ነው ያመለከተዎትና ፣ ይሔዱ እስማማለሁ" አለ
አጨጌውም ።

"እርሱም ብቻውን መሔዱ አያምርበትምና አብሬው እ
ድሔድ ይለምኑልኝ ፤ የርሱን አገርና እልጋ ለሚያስጠብቀው ያበ
ጠብቅ ፤ ከእንግዲህ ወዲያ ትግራይ በቃኝ ፤ ቁራሽ እንጀራ የነፈ
ገኝ አገር ነው ፤ በቃኝ!' አሉ አሉላ ምሬት እያንገፈገፋቸው ።
ግንቦት 26 ቀን 1886 ራስ መንገሻ ከዐሥራ ሁለት ሺህ
በላይ በሆነ ሠራዊት ታጅበው አዲስ አበባ ገቡ ። አብረዋቸ
ውም ራስ አሉላ ፣ ራስ ሐጎስና ራስ ወልደሚካኤል ነበሩ ።

አጼ ምኒልክ በዙፋናቸው ላይ ሆነው ዘውዳቸውን ደፍተው
ራስ ዳርጌ ፣ ራስ ሚካኤል ፣ ራስ ወሌና ሌሎቹም መኳንቶቻቸውና
የውጭ አገር መልእክተኞችም በተገኙበት አራቱን የትግራይ
ራሶች ተቀበሉ ።

አራቱ ራሶች ደንጋይ ተሸክመው ከንጉሠ ነገሥቱ ፊት
ወድቀው ፣ 'ባጠፋን ይማሩን' ብለው ጠየቁ ። 'ምሬአችሁአለሁ
ደንጋዩን አንሡላቸው!' አሉና ምኒልክ ተነሥተው ፣ "እናንተም
ይቅር በሉኝ" አሉና ጉንበስ ካሉ በኋላ እያንዳንዳቸውን እየ
ቀፉ ስመው ተቀመጡ ።

በዚህ ጊዜ የአጼ ምኒልክ አጋፋሪ ራስ መንገሻን በተዘጋ
ጀላቸው ወንበር ያስቀምጡና ሦስቱን ራሶች ሲያስወጡ ፣

"ከፈረንጆቹ እንኳን አንሰን ነው እኛ እምንወጣ" ብለው
ራስ አሉላ በአጋፋሪው ላይ አፈጠጡ ።



"መልስ—መልስ— አስገባ—" ብለው አጼ ምኒልክ ተቆጡ።
ሦስቱ ራሶች ከመንገሻ ቀጥለው ሲቀመጡ ያሉላ ቁጣ እየበረደ
እየበረደ ሲሔድ ያስተዋሉት ንጉሠ ነገሥት ምኒልክም በለሆ
ሳስ አነጋገር ፣

'ከጣሊያን ጋር እየተጣላሁ እንዳንተ ያለውን ጀግና የማስ
ቆጣ ምኔ ሞኝ ነው!' ብለው በልባቸው በጉጉት ተመለከቱዋቸው ።

አሉላም ፣ 'ያደራ ልጁ ከተቀናቃኞቹ ጋር ተመሳጥር ሊያ
ጠፋኝ ሲል ነፍሴን የታደግሃት ምኒልክ በሩቁ ስጠላህ ፣ በሩቁ
ስንቅህ ኑሬአለሁ ። በሩቁ ሆነህ ነፍሴን አተረፍካት ! ከውርደቱ
አወጣኸኝ ! ከእንግዲህ ወዲያ ከግቢህ አልወጣም' እያሉ ከሐ
ሳባቸው ጋር ሲጨዋወቱ ፣ በአዳራሹ ከነበሩት መኳንንት ይልቅ
ምኒልክና አሉላ ዐይን ለዐይን እየተያዩ ልብ ለልብ ይጨዋ
ወቱ ነበር ።

በዚያች ፍጥነት-ሰዓት በዚያ አዳራሽ ውስጥ ለደቂቃዎች
ያህል በነበረው ዝምታ ልብ—ለልብ ከሚጨዋወቱትም ከም
ኒልክና ከአሉላ በቀር ሁሉም ወለል—ወለሉን የሚመለከት ነበር።

ከዚያ በኋላ ስለ እንግዶቹ ክብር ታላቅ ግብር ተደረገ ።
ራስ መንገሻም አንድ መቶ ምርጥ ምርጥ ጠመንጃዎችና ስድ
ስት ሺህ ብር ለንጉሠ ነገሥቱ ግምጃ ቤት አስረከቡ ።

ከሦስት ቀናት በኋላ ንጉሠ ነገሥቱና ጥቂቶች መኳንንቶች
ባሉበት አራቱም ራሶች ቀርበው የእርቁ ሐሳብ ቀረበላቸው ።
ነጥቦቹም ፤

አንደኛ፣—የራስ ሐጎስ ግዛት የነበረው ጠለምቲ አውራጃ
በእቴጌ ጣይቱ የበላይነት እንዲተዳደር ፤

ሁለተኛ፣—የአክሱም ንቡረዕድ በንጉሠ ነገሥቱ እንዲሾም ፤

ሦስተኛ፣—ከትግራይ የሚሰበሰበው ግብር ለንጉሠ ነገሥቱ
ግምጃ ቤት ፈሰስ እንዲሆን ፣

አራተኛ፣— የወይዘሮ ዘውዲቱ ርስተ—ጉልት የነበረው እንደ
ርታ እንዲመለስላቸው የሚሉ ሲሆን ፣ ራስ መንገሻ ከመኳንንቶ

ቻቸው ጋር ሆነው በእነዚህ ነጥቦች ላይ መክረው የበኩላቸውን ሐሳብ እንዲያቀርቡ ታዘዙ ።

እራሱ ራሶች አዲስ አበባ ከመግባታቸው በፊት ጀምሮ የአጼ ምኒልክ መኳንንትና የጦር አበጋዞች ራስ አሉላን ለማየት ለመተዋወቅና ለማነጋገር ጓጉተውበት ነበር ። አጼ ምኒልክ እራሱ ራሶች ካነጋገሩ በኋላ በየተዘጋጀላቸው ቦታ እንዲሰፍሩና መስተንግዶም እንዳይጓደልባቸው አዘዙላቸው ።

መኳንንቱና የጦር አበጋዞቹ ግን ፣ ከራስ መንገሻ ይልቅ ወደ ራስ አሉላ ሠፈር እየሔዱ ልዩ ልዩ ገጸ—በረከትና መስተንግዶ ያበረክቱላቸው ጀመር ። ሁለት ጊዜ ከግብፅ ጦር ጋር ፣ ከማሕዲስቶችና ከጣሊያኖች ጋር ስለ አደረጉዋቸው ጦርነቶችና ስለአገኙዋቸው ድሎች እንዲያጫውቷቸው መኳንንቱ ይጠይቋቸው ጀመር። መኳንንቱ ብቻም ሳይሆኑ እቴጌ ጣይቱም ልዩ ልዩ ስጦታ ላኩላቸው ። ከየመኳንንቱና ከየጦር አበጋዞቹ ቤት እየተዘጋጀ የሚላከው መስተንግዶ የአሉላን ሠፈር ፍተንገዝግዞን አወጣው ። ከጠዋት እስከ ማታ ድግሱ የማያቋርጥ ሆነ ። የአሉላ የጦር አለቆች በሽልማት ተንቆጠቆጡ ።

በዚህ ወቅት ደግሞ በአዲስ አበባ ውስጥ አንድ ግቢን ቶኛ ፣

“አሉላ የሚሉት ጀግና ገባ ዛሬ
ደስ ይበልሽ ሸዋ እልል በይ አገሬ
ግብጦን የማረከ ድርቡሾን የነዳ
ጣሊያንን የወጋ ደርሶ በማለዳ
የራሶች ራስ ነው የጀግኖችም ጀግና
የምኒልክ ግቢ ደመቀ እንደገና ።
አሉላ አባነጋ የሙሉ ትንታግ
ደርሶ የሚያቃጥል የጠላት ምሽግ
ማንን እፈራለሁ ከማን እሸሻለሁ
የሳቱን ነበልባል አሉላን ይዣለሁ
የበደድ እሳት ነው አሉላ አባ ነጋ
ጠላት የሚነዳ ፣ ጠላት የሚያንጋጋ



አገሩ የረገጠው እጁ የጨበጠው
ይፋጃል አሉላ ለጠላቱ እሳት ነው”

እያለ በማስተጋባቱ የአሉላ ዝና እየገነነ ሔደ ። አሉላ በየዕለቱ እርዳታ ፣ በየሰዓቱ ፈገግታ የማይለያቸው ሆኑ ። እስከዚያ ወቅት ድረስ ያልታየባቸው የደስታ ኑሮ አጋጠማቸው ።

“የምወዳትና ያገለገልኳት አገሬ እኔነቴን ዐውቃልኝ የቆሰለውን መንፈሴን አደሰችልኝ” እያሉ ለወዳጆቻቸው ማጫወትም ጀመሩ ።

ከዕለታት አንድ ቀን በሠፈራቸው ውስጥ እየተዘዋወሩ ወታደሮቻቸው የሚበሉትንና የሚጠጡትን ተመለከቱና ፣ ትክዝ ብለው ፣

“እኮ ገብሩ ይህን ታሪክ ባታይ በመሞትህ አዘንኩ ። በምኒልክ ግቢ ይህ ሁሉ መስተንግዶ ፣ ይህ ሁሉ ስጦታ ፣ ይህ ሁሉ ክብር ሲደረግልኝ አንተ ባየኸው ኑሮ እንደ ምን ደስ ባለኝ ነበር?” እያሉ ተናገሩ ።

እንዲያውም የመስተንግዶው ድግስ ከአሉላ ሠፈር እየተትረፈረፈ ወደነ ራስ መንገሻና ራስ ሐጐስ ሠፈር ይላክ ነበር ። በዚሁም ጊዜ አሉላ ፣ “እናንተ ልታጠፉኝ ስታሙኑ ምኒልክ ከዚያ አውጥተው ለዚህ አበቁኝ ፤ እንኳን አገሬ በእናንተ መዳፍ ያልገባች’’ ብለው እነራስ ሐጐስን ወቀሱ ።

በዚሁም ነገር ምክንያቱ ራሶችና አሉላ እንደገና ሆድና ጀርባ ወደ መሆን ተዳረሱ ። የእነርሱ ሠፈር እንደ ነገሩ ሆኖ የአሉላ ሠፈር በተላከ ድግስ ግብር ሲበላ በምኒልክ ግቢ ቀርቶ በአዲስ አበባ ከተማ የአሉላ ዝና ሲያስተጋባ ፣ የአሉላ ስም ሲሞገስ ፣ የአሉላ እሽኮር እየተፈለገ ሲሸለምና ሲጋበዝም ሰቱ ራሶችና ወታደሮቻቸው ጥርሳቸውን መንከስ ጀመሩ ። በዚህ ጊዜ ነበር ከአራት መቶ በላይ የሆኑ ወታደሮች ከራስ መንገሻና ከራስ ሐጐስ እየከዱ ወደራስ አሉላ የገቡት ። አጼ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱም በእራሱ ራሶች ሠፈር የደረሰውን መቀትና ትዝታዉ ከተረዱ በኋላ ፣ “ሆን ተብሎ የተደረገ ነገር እንዳይመስል ለነራስ መንገሻም መስተንግዶውና ሽልማቱ እንዳይጓደል” ብለው አዘዙ ።

በመከከላቸው የነበረው ሁኔታ እንደዚያ ተራርቆ በነበረ በት ወቅት ራስ መንገሻ ፣ ራስ ሐጐስን ለብቻ ጠርተው ሲያነጋ ግሩዋቸው ፣ "የራስ አሉላ ምክር ዛሬ ነው የገባኝ ። ስተት ብለን መጥተን ባንገታችን ገመድ አስገባን አይደለም ?" አሉ ራስ መንገሻ ። "አሉላ የጦር ሰው ብቻም አይባል ነቢይ ነው" አሉ ራስ ሐጐስም ። "የሆነ ሆኖ ስለ ጉዳዩስ ምን ያስባሉ!" አሉ ራስ መንገሻ ፤ "አሁንማ ነገሩ አልቆ ሌላ ምን ሐሳብ ይኖረናል ? ከእጃ ቸው ከገባን በኋላ ፣ ከቃልዎ አንወጣም ነው እንጂ ሌላ ምን ቃል ይወጣናል" አሉ ሐጐስም ። "እንግዲህ ራስ ወልደሚካኤ ልን ጨምረን እንመከከርበትና መልሱን እንስጥ እንጂ" አሉ መንገሻ ።

"አሉላስ" አሉ ሐጐስ ።

"ከእርሳቸው ጋርማ ከእንግዲህ ይብቃን" አሉ ራስ መን ገሻ እየተ ከዙ ።

"ለምን ? ምክንያቱስ" አሉ ራስ ሐጐስ ደንገጥ ብለው ።

"ከእንግዲህ ወዲያ አሉላ የልባቸውን ይነግሩናል ብለው ያስባ ሉን !" አሉ ራስ መንገሻ እንደ መናደድ ብለው ።

"ስለ ምን ይደብቀናል ?"

"ከአጼ ምኒልክ ጋር በቆይታ መነጋገር ጀምረዋል ፤ ለኛ አይ ጠቅመንም" አሉ ራስ መንገሻ እየተከዙ ።

"አይሆንም፣ እዚ ያ ሳለን ስንጣላ የኖርነው አንሶ ደግሞ፣ እዚህ ተጣልተን የሸዋ መሣቂያ እንሁን!" አሉ ሐጐስም ኮስተር ብለው ።

"ታዲያ የምኒልክን ታማኝ ከመከከላችን አስቀምጠን ምን ምን እንድንነጋገር ያስባሉ?" አሉ መንገሻ ።

"ባላስረገጡት ነገር እንደዚህ አይባልም ። ነውር ነው ፣ አይገ ባንም!" አሉ ሐጐስ ።

"ምኑን ነው ያላረጋገጥኩት?" አሉ መንገሻ ።
"አሉላ ወደ ምኒልክ ማድላቱን!"



"በቆይታ ተነጋግረዋል ፣ ይመኑኝ ።"

"እንዴት ዐወቁት!"

"የወይዘሮ ዘውዲቱ አሽከር ከኛ ጋር የነበረ እኔንም የሚያው ቀኝ አጫውቶኛል" አሉ መንገሻ ።

"ቢሆንስ ታዲያ" ብለው ራስ ሐጐስ ፊታቸውን ቅጭም አድርገው አንገታቸውን አወዛወዙና ፣

"ቢሆንም ነገሩን ማወቃችን ማለፊያ ነው ። ግን በዚህ አኩርፈን አሉላን ማግለልማ ከዚሁ እስሩን ማለት ነውና እሉ ላም ይጠሩና ተመካከረን ፣ 'ጃንሆይ ከፈቀዱ እኛም ፈቅደናል' ብለን እንስማማላቸውና ከተመለስን በኋላ የሚሆነውን እናደርጋ ለን ፤ ምክር በራስ ቤት ነው ከሰው ቤት ሆኖ ! ማንገራገር አያዋ ጣም" አሉ ።

ከዚያ በኋላ አራቱም ራሶች በተሰጡዋቸው የስምምነት ነጥቦች ላይ ተመካክረው 'ይስማማናል' ብለው ለንጉሠ ነገ ሥቱ አቀረቡ ።

ራስ አሉላ የአጼ ምኒልክን ቤተ መንግሥት የጦር ኃይላ ቸውን ሚዛን የመኳንንቶቻቸውን ኑሮና ሁኔታ የአስተዳደራቸ ውንና የፖለቲካ ሚዛናቸውን ለማጥናት ብዙ ጊዜ አልፈጀባ ቸውም ። ከዚያ በኋላም ነበር ፣

"ወይ ልቢቱ! ወይ አለማወቂቱ! ባናውቅ ለካ ተታለናል፤ እኛን እኛን ተውን ፣ የኢትዮጵያ መመኪያ ምኒልክ ናቸው!' ብለው ተናገሩ ።

ራስ መንገሻ ፣ ወደ ትግራይ ለመመለስ ከተዘጋጁ በኋላ ራስ አሉላ ፣ 'እውነተኛውን ጌታ ፣ እውነተኛውን የኢትዮጵያ ጋሻ አግኝቻለሁና መንገሻን ተከትዬ አልሔድም' ማለታቸውን አጼ ምኒልክ ሰምተው አስጠሩዋቸውና ፣

"አጼ ዮሐንስም አደራውን የሰጡት ለአንተ ነው ። አሁን አልሔድም ማለትህ መንገሻን ያሳዝነዋል ፤ ብቻውንም ይሆናልና

ባይሆን አብረኸው ሔደና ካልተስማማችሁ ተመልሰ እንጂ እን
ዴት ትተራለህ!" ብለው ጠየቋቸው።

"እስቲ መክረቧት ለመለስ ይፍተዱልኝ" አሉ አለቃ።

"ግለሬያ ነው! ያዋቂ ሰው መልስ ነውና መክረሀቧት ተመልሰ" ብለዋቸው አለቃ ሲወጡ፣ እቴጌ ጣይቱ ነገሩን ከሥር ከመሠረቱ ይከታተሉት ኑሮ ከእልፍኛቸው ወጥተው ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ነበሩበት እልፍኝ ገቡና፣

"የመንገሻንና የአለቃን ነገር ምን አልባት አገኙልትን?" ብለው ጠየቋቸው።

"እብረችሁ ሔዱ፣ አትነጣጠሉ ብዬያለሁ አለቃን" አሉ አጼ።

"ቢታ በዚሁ አለቀ? አለቃስ እሺ አለም?"
"መክረቧት ለምጣ ብለዋል።"
"ከሆድዎ ከልብዎ ነው፣ አለቃን ሔድ የሚሉትን?"
"አይ መቼ፣ ምመቼም..." አሉ አጼ እንደ መተከዝ ብለው።

"እይሆንም ጌታ! አይሆንም ያስቡበት! አለቃን ያህል ጀግና፣ 'ያባድሩኝ ያስጠጉኝ' ሲሉዎት 'ሔደና ከመንገሻ ጋር ወይም ከማሊያን ጋር ሆነህ ውጋኝ ነው የሚሉት?" ብለው ተግ አሉ።

"እኔማ ነገሩ ትድመንም ከልቢ ተብቷልኮ! እንዲያው ነጣጠላን እንዳይሉኝ ብዬ ነው እንጂ" አሉ አጼ።

"ማነው ነጣጠሉ የሚለዎት? ርስ—ብርሳቸው የተነጣጠሉ፣ እርስበርሳቸው የሚናከሱ መኳንንቶች አይደሉም? ለሁንም በነገሩ እርስዎ ሳይገቡበት እኔ እጨርስዋለሁ። ለሀገራችን ያን ሁሉ ሙያ የሠራ ሰው ከሀገራችንም ዐልፎ በባሕር ዳር ግዶ እንደዚሁ ሰው የተጠራ ሰው ከእርስዎ እንዲርቅ ሲደረግ አይታየኝም። ነገም ለሀገር የሚጠቅም ነገር መሥራቱ አያጠራጥርምና፣ እኔ ነገሩን እጨርሰዋለሁ!" ብለው እቴጌይቱ ሲወጡ "እንዲታየሽ አድርጊ! ጀግና እጠላ መስለሽ!" አሉ ምኒልክም ራሳቸውን ደፋ ቀና እያደረጉ። እቴጌ ጣይቱም ራስ አለቃን ወደ እልፍኛቸው አስጠርተው፣



"እጼ የሐገሰ የእርስዎን ምክር ሲሰሙ ኑሮ ድርቡሽ ባለ ተጫወተብን ነበር። ግዛትምንም ባላው ነበር። እጼ የሐሰበን ከው በኋላ ደግሞ ትግሬ ውስጥ መቀየት ባላስፈለገም ነበር። ነገር ግን ሲመጡ ሁላችንም አክብረን በተቀበልንም ነበር። ያም ሁሉ ችግር ባልደረሰብም ነበር። አሁንም መንገሻ ከመኳንንቱ ጋር እንደ ፈለገው ይሁን። አጼ ምኒልክ ለእርስዎ አገርና ሹልግት መስጠት የሚሳናቸው አይደሉምና እዚሁ ይሰንብቱ" አሉዋቸው።

ራስ አለቃ የእቴጌይቱን ንግግር ከልባቸው ሲያዳምጡ ነበርና፣ "እግዚአብሔር ይስጥልኝ! እግዚአብሔር ያክብርልኝ፣ ምክርዎ በልቤ ውስጥ ያደረውን ነው ያስታወሱኝ! እኔም በዚሁ ቆርጫለሁ" አሉዋቸው።

ራስ መንገሻ የአድራ አባታቸውን መልሰው ለመውሰድ ባለመቻላቸው እያዘኑ ወደ ትግራይ ሲመለሱ ደግሞ፣ በርከት ያሉ ወታደሮቻቸው፣ 'አለቃን የሚያህል ጀብ ይዛላን' ብለው ከድተው ከራስ አለቃ ጋር ተሩባቸው።

ምስቱ ራሶች መቀሌ እንደ ገቡም መንገሻ የአድራ አባታቸውን ለመጀመሪያ ጊዜ 'አንተ' ብለው "አለቃ እኔንና አገሩን ትግራይን ጠልቶ ሸዋ ገብቶ ከድቶናል። እንግዲህ የእርሱ ወገኖች ሁሉ ጠላቴ፣ ጠላቴም ወገን መሆኑን እንድታውቁት" ብለው ለመኳንንቱና ለቀሳውስቱ ተናገሩ።

የአለቃ ሸዋ መቅረት ከመቀሌ ይልቅ በአሥመራና በርም ታላቅ ድንጋጤ ፈጠረ። 'አሥመራን ብቻ ሳይሆን ምፅዋንም መልቀቃችን ነው፤ ያ ሰይጣን አመለጠን' ብለው ጣሊያኖችም ሐሳባቸውን ደመደሙ።

ራስ አለቃ፣ አዲስ አበባ ውስጥ ተቀማጭ ሆነው በምኒልክ ግቢ በታላቅ ክብር በሚታዩበት ሰሞን ደግሞ፣ አሥመራ ባሉ ያውታቸው የነበረ ዋይልድ የተባለ እንግሊዛዊ ነጋዴ አዲስ አበባ መጥቶ ወደ ቤታቸው ሔዶ ሲያነጋግራቸው፣

"ሰሞን ሸዋ ቀሩ! ከአጼ ምኒልክ ጋር እንዴት ታረቁ?" ብሎ የጭውውቱን መግቢያ ከፈተ።

"ሸዋ የቀረሁበት ራስ መንገሻና መኳንንቱ አላበተም
በላሉኝ ነው ። እኔ የማስበው ሌላ ነበር ። የኔን ሐሳብ ደገ
ያገሬ መኳንንቶችና ጊዜው የማይደግፉት ሆነ ። እጼ ምኒልክ
ቀረብኳቸው ። ከልብ ደስ ብሏቸውም ተቀበሉኝ ። እቴጌም በ
ነት ለሀገር የሚያስቡና የሚደክሙ መሆናቸውን ተረዳሁት
እጼ ምኒልክ ሕግንና ሰላምን የሚወዱ ፣ የአገርን አንድነት የሚ
ብቁ መሆናቸውንም አመንኩበት ። የኢትዮጵያን ትልቅነትና አ
ድነት ለማጠንከር በሚያደርጉትም ድካም ሁሉ ዐቅሜ የቻለው
ያህል ላገለግላቸው ወደድኩ" አሉት እትኩረው እየተመለከቱት

"ከጣሊያኖች ጋር ጀምረውት የነበረውን ወዳጅነትስ ይ
ጥሉበታል!" አላቸው ።

"ከእነርሱ ጋርማ ወዳጅነትም አንድነትም የሚኖራች
እናንተ ናችሁ ! ከነርሱ ጋር ወዳጅነት ጀምሬ የነበረውም ለ
ሐሳብና ዓላማ ስለነበረኝና ለራስ መንገሻም ከል ነበር ፤ ከእ
ግዲህ ወዲያ ቢሆን የምከተለው የእጼ ምኒልክን ሐሳብ ነው
ንጉሠ ነገሥቱ 'ይሁን' ከሚሉት አልወጣም! እናንተ ግን…"
ብለው ራሳቸውን ነቀነቁና ፣

"እድራችሁ ውላችሁ ከጣሊያኖቹ ጋር እንዳትጣሉ እ
ጠራጠር" አሉት ።

ራስ አሉላ ፣ ከመንገሻ ጋር ተኳርፈው ሸዋ ከቀሩ ጀም
እጼ ምኒልክ በታላቅ እንክብካቤ ይዘዋቸዋል ። ከኢጣሊያ ጋ
ለነበራቸው ያለመግባባት ምርጥ ዱላ አግኝተዋል ። ሽልማቱ
ጌጡ ፣ ስጦታው ከእጼ ምኒልክ ፣ ከእቴጌ ጣይቱ ፣ ከወይዘሮ ዘ
ዲቱ ከራስ መኩንንና ከሌሎቹም መኳንንት በየጊዜው ይላክሉ
ዐሰሜን ኢትዮጵያ ተራራ ለተራራ ፣ ሸለቆ ለሸለቆ ፣ ሜዳ ለሜ
ከጦርነት ወደ ጦርነት ሲሸጋገሩ ሲቆስሉ ሲራቡ ሲጠሩ ሲ
ድቁና ሲነሡ የኖሩት ፣ በትግሬይ መኳንንት ዘንድ ፣ "የድሃ ልጅ
የገበሬ ልጅ ፣ የሴት ልጅ ፣ የሰይጣን ቁራጭ ከሀዲ…" ሲባ
የኖሩት "ወዲ ቁቢ" በእምዩ ምኒልክ ቤተ መንግሥት መ
ሽንሽ ፣ መዘባነን ጀመሩ ። በዚያን ዘመን ከእጼ ምኒልክ ጋር ለ
ነጋገር ከሮም ወደ አዲስ አበባ ሲመላለሱ የነበሩት መልእክተኞ



ራስ አሉላንም ለማነጋገር እንዲፈቀድላቸው እጼ ምኒልክን ጠይቀው ፣ ተፈቀደላቸውና ወደ ቤታቸው ሔደው ሲያነጋግሯቸው ፣

"ከሀገራችን ምን እንላክልዎ?" ብለው ጠየቋቸው ።

"ሁሉንም እጼ ምኒልክ ሰጥተውኛል ፤ የምፈልገው ነገር የለኝም" ይላሉ ። ጣሊያኖቹም ድርቅ ይሉና ፣

"ይኸማ እኛ ዕርቅ ስንፈልግ እርስዎ እምቢ ማለትዎ መቀየምዎ ነውና አንድ መታሰቢያ የሚሆን ነገር እንድንልክልዎ ይፍቀዱልን" ብለው አጥብቀው ይለምናሉ ።

"እንግዲያው" አሉና አሉላ አሽከራቸውን ጠርተው የእደን ጠመንጃቸውን እንዲያመጣላቸው አዘዙትና ፣ ጠመንጃውን ለጣሊያኖቹ እያሳዩ ፣ "ለዚህ የሚሆን ጥይት ላኩልኝ" ይላሉ ። ጣሊያኖቹም ተስማምተው ተሰነባበቱ ። አገራቸው እንደ ደረሱም ሁለት ሺህ ጥይት ላኩ ። አሉላም ዒላማ ሲመቱ ጥይቶቹን ከጠመንጃቸው ሲያጐርሱ ሲሞክሩ ጊዜ የማይገጥም ንምራው የተለያየ ሆነባቸውና ፣

"ዱሮውንስ ቢሆን ከነርሱ ጋር ልብ ለልብ ሳንገናኝ ጥይታቸው ከጠመንጃዩ እንዴት ሊገጥም ይችል ኑሯል!" ብለው የተላከላቸውን ጥይት በሙሉ አቃጠሉት ።

እጼ ምኒልክም ነገሩን ሰሙና አሉላ በጣሊያኖች ላይ ባላቸው ጥላቻ ለዒላማቸው መምቻ እንደሚሆኑዋቸው ተማመኑባቸው ። በቅጽበታዊ ድንጋጤ ቁጡነት 'የበዝብዝ አሽከር' ቢሉም በጭውውት ጊዜ ደግሞ ፣ 'የምኒልክ ያሰሀ' ሲሉም ተሰምተዋል ።

የመረብ ምላሽ ግዛታቸው ከእጃቸው ወጥቶ በመቆየቱ ከሁሉም ይበልጥ እጅግ የሚያሳስባቸውና የሚያስተክዛቸው ከመሆኑም ሌላ ፣ የምኞት የቅንጦትና የመንደላቀቅ ልማድና ፍላጐትም ስላልፈጠረባቸው ፣ የምኒልክ ቅምጥልነቱ እየሰለቻቸው በመምጣቱ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ መገሥገሥና መረብን መሻገር ደግሞ የሌሊትና የቀን ሐሳባቸው ፣ የንግግር መጀመሪያ

ቸው የኢትዮጵያን ታሪክና አንድነት የማስተዋወቂያቸው ጦርነት ስለት የማስተማሪያቸው እየሆነባቸው ሔደ ።

ስለዚህ ንጉሡ ነገሥቱ የሰሜን ኢትዮጵያን ጉዳይ ትኩ ረት እንዲሰጡትና ሙርሽ ምኞቻቸን በጦርነት ነጻ ማውጣት እንደ ሚቻል በየጊዜው እያነሡ የሚያጠኑት ጉዳያቸው ሆነ ።

'አሉላ የምኒልክ ቀራቢ ሆኖ አሉላ በምኒልክ ቤተ መን ግሥት ተቀምጦ 'ኤርትራን' ይዘን እንቆያለን ማለት ዘበት ነው ። ምኒልክ አሉላን ማስጠጋታቸው በእኛ ላይ ለመዝመት በመሰ ናዶ ላይ ለመሆናቸው በቂ ማረጋገጫችን ሊሆን ይገባል' እያለ ባራቲዬሪ በየሰንቱ የሚያሳዝንበት መቀተን ሆነ ።

ራስ አሉላ የሰሜን ኢትዮጵያ ጉዳይ ሲወዘውዛቸው በነበ ሩበት ወቅት ደግሞ ፣ አጼ ምኒልክ ወደ ወላይታ መዝመት አስፈ ላጊያቸው ሆኖ ቀረበ ። በዚያም ዘመቻ አሉላ ሰባት መቶ ወታ ደሮች ተደልድለውላቸው ለስንቅም ማዘጋጃ የሚሆናቸው በቂ መገሪያና ገንዘብ ተሰጣቸው ። በዚህም ጊዜ ፣ 'ይኸኛው ዘመቻ የአንድ ፣ ቢበዛም የሁለት ራሶች ጦር ይበቃው ነበር ። ብርቱ ክንድ የሚያስፈልገው ጠላት ያለው ግን በሰሜኑ በኩል ነው' ብለው ነበር ።

አጼ ምኒልክ በሰሜን ኢትዮጵያ ሲደረግ የነበረውን የውጭ ወረራና ግፊት የሕዝብ እንዲወጡት ጠብ ርግፍ አድርገው ትተውላቸው እንደ ነበረና ፣ የእርሳቸው ትኩረት ደግሞ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ እንደ ነበረ አሉላ በደብዳቤ የተገነዘቡት ወቅትም ሆነ ። ስለዚህ 'ከወላይታ ሲመለሱ የሰሜኑን ጉዳይ እከራከርበ ታለሁ' በሚል እምነት ወደ ወላይታ አብረው ሔዱ ።

* * *

አጼ ምኒልክ በደቡብ ኢትዮጵያ የነበረባቸውን ችግር ለማ ቃለል የኢጣሊያኖች የመረሩ ጠላት የነበሩትን አሉላን አስከት ለው ግዛታቸውን ለማስፋት ሲታገሉ ፣ ኢጣሊያኖች በሰሜን በኩል ገፍተው ገብተው ፣ ከራስ መንገሻ ጋር ጦርነት መግጠማቸውን ሰምተው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ ።



ጣሊያኖች ፣ ወደ ምዕራብ ቀኝ ወርደው ማሕዲስቶችን ድል ነሥተው ከሰላን ከያዙ በኋላ ፣ ከራስ መንገሻ ጋር ውጊያውን ከፈ ቱባቸው ምክንያቶች አንዱም ፣ መንገሻ ከመሐዲስቶች ጋር ተባብረው ሊወጉን የአካለ ጉዛይ ገዥ የነበሩትንም ባሕታ ሐጎስን አባብለው የእርሳቸው ተባባሪና የኛ ተቃዋሚ ለማድረግ ስምምነትና ዕቅድ እንደ ነበራቸው ከማሕዲስቶች ላይ ከማረክ ነው ሰነድ አረጋግጠናል ፣ ብለው ነበር ።

ስባራ ስንጣራ ምክንያቶቹን ሰብስቦ ትግራይን ለመያዝ ሲያሰላስል የነበረው ባራቲዬሪ ዐድዋ ሲደርስ ፣ ሕዝቡ ብርቱ ተቃውሞ በማሰማቱ ፣ ያልጠበቀው ሁኔታ ሆነበትና ከአራት ቀናት በኋላ ጓዙን ጠቅልሎ ከዐድዋ ወጣና አክሱም ገባ ።

ምንም እንኳን አሉላን ያህል ታላቅ አዝማች ባይኖራቸ ውም ቅሉ ፣ የአገራቸው መደፈር እጅግ ያንገበገባቸው ራስ መን ገሻ ዐሥር ሺህ የሚሆን ጦር አሰልፈው እርሳቸውም በፈንታቸው የመረብን ወንዝ ተሻገሩና ኩአቲት ላይ ጦርነት ገጠሙት ።

ባራቲዬሪ ከዐድዋ በወጣ በዐሥር ቀናት ውስጥ ራስ መንገሻ ዐሥር ሺህ ጦር አስከትተው ሁለት ቀናት ሙሉ ተኩ አድርገው ቡተው በሚያስደንቅ ጀግንነት ከተዋጉ በኋላ ድል ሆኑ ። ከኩአቲት ተመልሰውም ሰንዓፌ ላይ እንደ ሰፈሩ የጣሊያን ጦር ሌሊቱን ሲገሠግሥ አድሮ ደረሰባቸውና እንደ ገና ተዋጉ ። በዚህ ኛውም ጦርነት መንገሻ ድል ሆነው ወደ ትግራይ ሲሸሹ ደጃች ተድላ ዐባይ ሞቱ ።

“ወይኔ አሉላ! ወይኔ የበዝብዝ አሽከር! ወይል ወንዱ! እንዴት እኔ እዚህ ተቀምጬ ባራቲዬሪ አገሬን ይደፍራል? እርሱም ወንድ ሆኖና ጦርነት ገጥሞ ድል ነሣ? ምን ያድርግ? ምድረ እንኩቶ እዚያ ተሰብስቦ እስ በሱ እየተባላ አገር አስደፈረ?” አሉ ራስ አሉላ የጦርነቱን ነገር እንደ ሰሙ ።

ከንዴታቸውም ተነሡና ወደ ቤተ መንግሥት ሔደው እቴጌ ጣይቱ ዘንድ ገብተው ፤ “በራቸንም በእያሰው ተነጋገረናል ። አሁንም ይኸውና እንዲህ ሆነ ፣ ተቸገረድን ጀግና ባይጠፋ ለበ— ሱ ወንድ ሞልቶ እንዴት አገራችን ይደፈር? አሁንም እባክዎ

ያማልዱኝና ልሒድ ። እሥመራ ያልገባሁ እንደሁ ይታዘቡኝ እንጂያወም ቤ. . . ." አሉና ነገሩን ቀጥ አደረጉት ። 'ቤት ብለው ይጥሩኝ' ሲሉ ነበር ። ግን ከፊታቸው ተቀምጠው ዐይናቸቸውን አፍጥጠው ይመለከቱዋቸው የነበሩት ጣይቱ ደግሞ ከወንድም ወንድ መሆናቸውን ዐውቀዋል ። ሁልጊዜም 'ጣሊያንን ከገራችን ማስወጣት አለብን' እያሉ የሚከራከሩ መሆናቸውን ያውቃሉና ነገሩን ቀጥ አድርገው ፤

"በሚያምኑዋት በእንጦጦ ማርያም ይዠዋታለሁ ፤ ያማልዱኝና ልሒድ" ብለው በእልህ ሲንቀጠቀጡ እቴጌይቱ ተመለከቱዋቸውና ፤

"ግዴለዎትም የኔም እምነት እንደ እርስዎ መሆኑን ያውቁ የለም? አብረን እንነግራቸዋለን ይሔዳሉ ፤ ግዴለዎትም ይዘዋታሉ" አሉዋቸው ።

አጼ ምኒልክም ነገሩን በችሎታ ለማለፍ ወይም በዲፕሎማቲክ ብቻ ለመፍታት እንደማይቻል ከተረዱት በኋላ ራስ ወሌን ፤ ራስ ሚካኤልንና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ከነሠራዊታቸው በራስ አሉላ አዝማችነት ወደ ሰሜን ለመላክ ማዘጋጀት ጀመሩ ።

ነገር ግን በዚህ ዕቅድ ላይ ደግሞ ብርቱ ውዝግብ ተነሣበት ። አንዳንዶቹ መኳንንት ፤ 'ይህን ሁሉ ሠራዊት በአንድ ጊዜ ከመላክ ለራስ አሉላ ጦር ተጨምሮላቸው ቢሔዱ ይሻላል' ሲል በአዲስ አበባ ኑዋሪ የሆኑ የሚጠጏቸው የትግራይ ተወላጆች ደግሞ ፤ 'አሉላ በትግራይም ሆነ በሐማሴን የተጠሉ በመሆኑ በእርሳቸው መሪነት ጦር ማዝመት ጨርሶ እንዲከዳ ማድረግ ይሆናልና ይታሰብበት' ማለት ጀመሩ ። በተለይም የአጼ ምኒልክ መልእክተኛ ሆነው ወደ ትግራይ ሲመላለሱ የነበሩትና ራስ መንገሻን ለምነውና አባብለው ያመጡት ፤ ተሰፋይ ሕንጻሉ ከጥላቻቸው የተነሣ የአሉላን አዝማችነት በመቃወም አጥብቀው ተከራከሩበት ። በዚህም ሁሉ ምክንያት የሦስት ራሶች ሠራዊት ጠቅላይ አዝማች ሆነው ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ለመዝመት ታጭተው የነበሩት ፤ የአሉላ አዝማችነት ለጊዜው እንዲቆይ ሆነ ።



ነገር ግን ፤ ከሰሜን ኢትዮጵያ ወደ አጼ ምኒልክ ቤተመንግሥት ይጐርፍ የነበረው ዜና ፤ የኢጣሊያኖችን ዝግጅትና ትግራይን ካልያዙ የኤርትራ ግዛታቸው ሊረጋጋላቸው እንደማይችል ያመኑበት ጉዳይ በመሆኑ ፤ ባልታሰበ ቀን መቀሌ ሊገቡ እንደሚያስቡ የሚያመለክት ስለ ነበረ ፤ አጼ ምኒልክም በጥብቅ እያሰቡበት ሔዱና የጣሊያኖች ማስፈራሪያ የሆኑትን አሉላን የማዝመቱን ጉዳይ እያመኑበት ሔዱ ።

ራስ ሚካኤልና ዋግ ሥዩም ብሩ ምክትሎች ሆነው በራስ አሉላ ጠቅላይ አዝማችነት ከዐሥራ ሁለት ሺህ በላይ የሆነ ሠራዊት እንዲዘጋጅና ፤ ለዚህም ዘመቻ ሃምሳ ሺህ ብር ተመድቦለት ለሠራዊቱ ስንቅ ሀገራቸውንም እየከዱ ወደ ኢጣሊያ ለገቡት ማባበያ እንዲሆን ተወሰነ ።

የአሉላ ጦር ትግራይ ከመድረሱ በፊትም ለማባበያና ለስንቅ ማሰናጃ የሚሆን ዐሥራ ሁለት ሺህ ብር በአስቸኳይ ለራስ መንገሻ ተላከ ። በተጨማሪም አሸንጌና ዞብል በቀጥታ በራስ አሉላ አስተዳዳሪነት እንዲመደቡና ለጦርነቱ ስንቅና ወታደር የሚዘጋጅባቸው እንዲሆኑ ታዘዘ ።

ምንም እንኳን በአሉላ አዝማችነት ጦር ለመላክ ቢዘጋጅም ፤ ፈረንሳዮች ደግሞ ነገሩን በሰላም ለመጨረስ እንዲያመች ዘመቻው እንዲዘገይ አጼ ምኒልክን መወትወት በመጀመራቸው ፤ ነገሩ እየዘገየ ሔደ ። ባራቴሪ ግን የምኒልክን ዝግጅትና በተለይም የአሉላን አዝማችነት ከሰማ በኋላ 'የተድባሊው ዱላ' ትግራይ ከመግባቱ በፊት መቅደም እንደ ሚያዋጣው ስላመነበት ፤ አደግራትን ፤ ዐድዋንና መቀሌን እያከታተለ ያዘ ።

አሉላ ገና ከአዲስ አበባ ሳይወጡ ፤ የመቀሌን መያዝ እንደ ሰሙ ቁጣና እልህ እንደ ተናነቃቸው ወደ ቤተ መንግሥቱ ሔዱና "ጃንሆይ ቁርጡን ልወቀው ። ኢትዮጵያኮ ዐይናችን እያየ ተወሰደች ። ምን እስኪሆን ነው ጥበቃው? እኔን አላመኑኝ እንደሆነ ጀግና ሞልቶዎታልና የሚያምኑትን ይላኩ" ብለው አቤቱታ አቀረቡ ።

"እንተን ወንድሜን እንዴት አላምንም ! 'ፈረንሳዮች ከነ ሩን በሰላም እንጨርሳለንና ወዳጆቼን' እያሉ ነው እንጂ" አሉ ምኒልክ ።

"እኛ ጃንሆይ ፈረንሳዮችን ፡ እንግሊዞችን ፡ ጣሊያኖችን ፡ ግብፆችንም ሆነ ደርቡሾችን አሳምረን ዐውቃቸዋለሁ ። በእኛ ላይ ለነርሱ በሩን ልቡን የከፈተ የለም ። 'እኔ ላምነው እንተ በጭተው' ነው ብለዋታቸው ። ለመሆኑስ ፈረንጅና ቅንቅን ይታመናል? እውነት እንግዲህ ታሪኩ የሚለን ወለላ ውል እኮ ነው የሚሆነው?" አሉ አሉላ ።

"በምን ዐይነት ውል? ይሆናል" አሉ ምኒልክ ።

"መቸም መቀሌን ይዘዋልና መቀሌን እናስለቅቃቸዋለን ፤ ዐድዋን ለተቀላቸውና ደንበራቸው እዚያ ይሁን ነው የሚለን ። ይህን ያላሉም እንደሆነ ይታዘቡኝ" አሉ አሉላ ።

"እኔ ምኒልክ በሕይወቴ ቆሜ ይህ ይሆናል ብለህ ታስባ ለህ!"

"እኔማ አላስብም ፤ በሕይወቴ ቆሜ መቀሌ መያዙን ሰምቻለሁና ይፍቀዱልኝ ለዘመቻ" አሉ አሉላ ።

"እንግዲህ መቀሌን ከያዙብህ በየት ትገባለህ" አሉ ምኒልክ ።

"በራያና አዘቦ በሩ አካለ ጉዛይንና ሐማሴንን ለይዘበት እችላለሁ ፤ ብቻ ይፍቀዱልኝ" አሉ አሉላ ።

"ጉዳዩ ይሰርክህ ግለፊያ ስሌት ነው ፤ በሌላ በኩልም ጦር መግባት ያስፈልጋል ፤ አንተ ብቻህን ከሆንክ ያጠቃሃል" አሉ ምኒልክ ።

ራስ አሉላም ጥቂት አሰብ አደረጉና ፡ "እንግዲያውማ የአ ገድ ራስ ጦር በቤገምድር በኩል ታጥር ከራሳ መንገሻ ጋር ተቀናትሎ ወደ መቀሌና ዐድዋ ቢያመራ የበለጠ ይሆናል" አሉ አሉላ ።



"ጉዳዩ ግለፊያ ነው ይሰርክህ ፡ እንግዲያው በቤገምድር በኩል ራስ ወሌ ይሻገራል" አሉ ምኒልክ ።

በዚሁ ነገሩ አለቀ ። ራስ አሉላ ከምስት ሺህ በላይ የሚ ሆን ወታደር አሰልፈው ሚያዝያ 25 ቀን 1887 ከአንጦጦ ተነሡ ። በሠራዊታቸውም ደጃች እንዳርጋቸው ፡ ቀኝ ጌታ ጉብዜ ፡ ደጃዝማች ጋይለግርያም ፡ ፊታውራሪ ገነሙ ፡ አዝማች አበራና ደጃች ተድላ ጥሁድ ተደለደሉ ። አሉላ ጉግቶዊ ሲታ እየተናነቁቸው ጉዞአቸውን ተጠሉና በወረኢሉ በኩል ተጉ ዘው ቡሩ ሜዳ ደረሱ ። ቀናው ጉዳያቸውም በዚያን ጊዜ የጀን አጨታለው ይዘው ከንበሩት ከራስ ወሌ ጋር ተገናኙትው ፡ በወሎ ዐትድ መሥረት ዮብልን ከራስ ወሌ ለማሬከብ ነበረ ።

በዚያን ጊዜ ለእጼ ምኒልክ ዘንድ ተደማጭነት ከነበራቸው መኳንንት አንዱ ራስ ወሌ ነበሩ ። የእቴጌ ጣይቱም ወንድም ናቸው ። ታዲያ ነገሩን ከራስ አሉላ እንደ ሰሙ ጠቅላላውን ዘመቻውን ተቃውመው በጫራቂቴራና በአጼ ምኒልክ መካከል ገብተው ነገሩን በሰላም ለመጨረስ እንደሚችሉ አስረዱዋቸው ።

ራስ አሉላ ምርር ብለው አዘኑ ፤ ተከዙ ።

"አውሬ እያደንኩ በረሃ በተቀመጥኩ በተሻለኝ ነበር ። የጉበዝ አለቃ ሆኜ በተኛሁ ቁጭቴን በተወጣሁት ነበር" ብለው ሲያዝኑ አዝማች አበራ ለመኗቸውና ፡

"ከዚህ ሌላ ምን እናደርጋለን ! የጦሩንስ ቤት እንደው ተርቷል ። እንደ ልብም አይናገሩ ፤ አይከራከሩ ፤ የሸዋው ነገር አይ ታወቅም ፤ ትዕግሥትን ከነርሱ ተምሬአለሁ ። መታገሥ ነው" አሉ አዝማች በምኒልክ ቤት መንገሥ ለብዙ ጊዜ የቆዩ መሆናቸውን ለማሳወቅ ያህል ።

"አዬ ኢትዮጵያ አዬ አገሬ! አዬ የጀግኖች አገር ! እኛ እየ ተናከስን ፡ እኛ እየተባላን ጠላት በትሻ ግቢ ውሰ ይደር? አዬ የኛ መኳንንት!" ብለው ሲተክዙ ቆዩና ፡

"ባንተ ውስጥ ታማኝ ታማኝ አሽከሮች አሉህ አይደ ለም?" ብለው አዝማች አበራን ጠየቁ ።

"ለምን ሥራ የሚሆኑ?" አሉ አዝማች ።

"ወደ ሀገርህ የምንልካቸው?"

"ወደ ሐማሴን የሚሔዱ ?" ብለው ጠየቁ አዝማች ።

"አዎ ፤ ወደ ሐማሴን ሔደው ካንተ ቤት ገብተው ፣ ከዘመዶ ችህ ጋር ተገናኝተው የሚመለሱ ።" አዝማች አበራ በሐሳባቸው ከአሽከሮቻቸው መካከል ታማኞች ለመምረጥ ሲያምሰለስሉ፣ እሉላም ዒላማቸውን መምታቸውን በማረጋገጥ በጉጉት ይመ ለከቱዋቸው ጀመር ።

"አዎ እንዴታ ! አሉኝ እንጂ አይሳነኝም" ብለው አዝማች አበራ የታማኝ አሽከሮቻቸውን ብዛት በሐሳባቸው እየቆጠሩ ጣቶቻቸውን ተራ በተራ ሲያጣጥፉ ቆዩና ፣

"አንድ ዐሥር የሚሆኑ በጣም ታማኞች" አሉኝ አሉ ።

"የተወለዱትስ የት ነው?" አሉ እሉላ ።

"ከኔው ጋር ነው ፣ ሐማሴኖች ናቸው" አሉ አዝማች ።

"መልካም ነው ፣ መሸት ሲል ለብቻ አምስቱን አምጣልኝ ፤ ጉዳይ አለኝና ወደ ሐማሴን እሰዳቸዋለሁ" አሉ እሉላ ። ሁለቱ ይህን በሚነጋገሩበት ሰዓት ደግሞ ደጃች ተድላ ዋህድ ገቡና ፣

"እንግዲህ ውሰን ማደራችን ነው መሰለኝ ። ምናልባትም ራስ ወሌ ነገሩን ካስረዱት ክረምቱን ወደየአገራችን ከርመን ብንመለስ አይከፋም" አሉ ።

"ተወኝ እስቲ! ተወኝ ፣ ትጥቃችሁንም አታላሉ ! መዝመታ ችን የማይቀር ነው" አሉ እሉላ ።

"ራስ ወሌኮ እኔ አስታርቃለሁ ብለው ተማምነዋል" አሉ ደጃች ተድላ እንደ ማሾፍ እያሉ ።

"ምኒልክን ያህል ሰው ፈረንጎችን አስታርቁኝ ብለው አማላጅ ልከው ያልሆነውን ጉዳይ ፣ አሁን ማን ይሙት አንድ



ወሌ ማሊያንን ሸንገሎ ነገር ይጨርሳል ብለህ ታምናለህ ? ይል ቅስ እንዳትዘናጉ!" አሉ እሉላ ።

"እንግዲህ መቼም አቸላለሁ ብለዋል ። ታዲያ ወደየት ነን? ወደ አዲስ አበባ ልንመለስ ነው? ወይስ . . ." ብለው ተና ገረው ሳይጨርሱ ፣

"እሱማ አጼ ምኒልክም ወደዚሁ እየመጡ ናቸው ፤ ጠብቀን የሚሉትን መስማት ነው እንጂ!" አሉ እሉላ ።

መሸትሸት ሲል አዝማች አበራ ታማኞቻቸውን መርጠው ወደ ራስ እሉላ ድንኳን ወስደው አቀረቡዋቸው ። ራስም የተመ ረጡትን አሽከሮች የትውልድ መንደራቸውን ፣ ወላጆቻቸውንና የዘር ሐረጋቸውን እየጠየቁ አጣርተው ካወቋቸው በኋላ ፣ "ልጆቼ ፣ ጉብዞቼ!

አባቶቻችሁ አያቶቻችሁ ዘር ማንዳችሁ ታማኝ ነው ። እኔም በዝናም ፣ በተግባርም ዐውቃችኋለሁ ። ቀደም ብላችሁ ወን ድሞቻችሁን አበራን ተከትላችሁ ሸዋ ገብታችሁ የኖራችሁም ለጠላት እንዳዛም ብላችሁ መሆኑን አላጣሁትም ። አሁን እን ደምታዩት ጠላታችሁን ከአገራችሁ አስወጥተን ለመግባት ይኸውና ጉዞ ጀምረናል ። ስለዚህ እናንተም ነጋዴዎች ተመ ስላችሁ ፣ አገራችሁ ገብታችሁ ከዘመዶቻችሁ ጋር ከተገናኛ ችሁ በኋላ ፣ በነጋዴ መልክ አሥመራ ገብታችሁ ፣ አንደኛ ፣ በጠቅላላው ማሊያን የሚሠራውን ሥራ ፣ ሁለተኛ ፣ ወታደሩ የት እንደ ሠፈረ ፣ ሦስተኛ ፣ ከየት ተነሥቶ በየት በየት በኩል አድርጎ ወደ ትግራይ እንደ ገባ ፣ አራተኛ ፣ ትግራይ የገባውን የጦሩን ብዛትና ሠፈር ። አምስተኛ ፣ መድፉን የጠመደበትን ቦታ ቦታውን ፣ ብዛቱን ልቅም አድርጋችሁ አጥርታችሁ እንድታመ ጡልኝ መርጫችኋለሁ ። ስትመለሱ የድካማችሁን ዋጋ እከፍላ ችኋለሁ» ብለው እጃቸውን እያስሙቱ አስምለው ለየአንዳንዳ ቸው ሁለት ሁለት መቶ ብር ሰጥተው ሲያሰናብቷቸው ፣

"ግዴለዎትም አይጠራጠሩ ፣ ታማኞቹ ናቸው ፤ ጠንካሮች ናቸው ፣ ያሰቡትን ልቅም አድርገው ያመጣሉ" ብለው አዝማችም ጽኑ እምነታቸውን አረጋገጡላቸው ።

ትግራይ ገብተው ባራቲየሪን ለማተራመስ ሻንተው የነበሩት አሉላ ፣ ወረኢሉ መፍረው ከሰነባበቱ በኋላ አጼ ምኒልክም ወደዚያው ተጉዘው እንደ ደረሱ ጉዳዩን አቀረቡላቸው ።

አጼ ምኒልክ ከጠባብ ምርጫ ላይ ወደቁ ። እዲሱ የማስፈራሪያ ዱላቸው ከአማቻቸው ጋር አንጃ ግራንጃ ገጥመው እጀ ታው ተይዞ ቆያቸው ። ሁሉቱም እንዳያኮርፉ ምኒልክ ዘዴ ፈጠሩና ፤

“ክረምቱ መግቢያው ነው ። በዚህ ክረምት ወታደሩን ማገገሚያትና እነሩንም ስንቅ አቅርቦ ማበት ብርቱ ችግር መሆኑን ሁላችሁም ታውቁታላችሁና ፣ አሉላም ወደ ዋግ ሐይና በዚያው ብንህ ተጠባበቅ ። ተሰፋይ ሕንጣሉ ደግሞ ትግራይ ተቸገርና መንገሻን እየረዳህ ሁኔታውን እየተከታተልክ ብትቆይ . . .” ብለው ተናገሩ ።

አሉላ በዚኢ ወር ዋግ ገቡና ፣ “የመንደርን ክረምት እጋሜ ባልሰላፍ ቤት እያላችሁ ተሩኝ” እያሉ እየዋቱ የዋራሪንና የላምሪን ወገኖች ተቸገረው ለመዝመት እንዲፈቅዱላቸው አጼ ምኒልክን በመልእክት መወትወት ጀመሩ ።

በዚህ መንገዱ በኩል ደግሞ የአጼ ምኒልክ የቅርብ አማካሪዎችና እቴጌ ጣይቱ ጭምር ሌላ ሐሳብ አቀረቡ ።

“አሉላን የመሰለ ጦረኛ ሰው ካጠገብዎ ለምን ይርቃል? ትግሬስ ከገባ በኋላ ከመንገሻ ጋር ሆኖ ቢወጋንስ? ያለዚያም ደግሞ ቸኩሉ ጦርነቱን ገጥሞ በለስ ቢቀናው የሰጠው እንደሆነስ እንኳን እኛን እርስዎን መናቁ አይደለም? ደግሞ ጣሊያን በብዙ እንተቶ በደዘውስ ታላቅ ውርደትና ሞት አይደለም? ለማንኛውም በውስጡ ካለው ወታደር ተጊሉን ወደ ራስ መንገሻ መስደድና አሉላን ካጠገብዎ ማስቀመጥ ይሻላል” የሚለው ምክር አሸነፈና የራስ አሉላ ጦር ተጊሉ ወደ ራስ መንገሻ ተልኮ አሉላም ተጊሉን ጦራቸውን ይዘው ከዋግ ወደ ምንጃር እንዲመለሱና ክረምቱን በዚያው እንዲያሳልፉ ታዘዙ ።



የጣሊያን ጦር በትግራይ ውስጥ መንበሬቱን እየተጠለ ሰለ ሔደ ምኒልክም የተጠናከረ ጦር ማዝመት የግድ ተደረገባቸው እየሆነ ሔደ ። በዚሁ ጊዜም ነበር አሉላን ጠርተው ፣

“እንተን ዘማች ከማድረግ ራሴ እንድትሆንኝና ራሴ ለምዘምትበት ጦርነት ከቅርቤ እንድትሆን ፈልጌ ነው ያስቀረሁህ ። አሁንም ራስ መኮንን እንዲዘምት ታዝዞልና ሰልቱን መንገዱን ሁኔታውን ተሰ ጋር ተመካከሩበት” ብለው ከራስ መኮንን ጋር አገናኟቸው ።

“ምን ከፋኝ! ሲሆን ሲሆን ከጌታዬ ከራስ መኮንንም ጋር ብዘምት ባልጠላሁ ። ካልሆነም መንገዱንና ብልሃቱን እመሰክታለሁ ፤ ስለዚሁ የሚረዱም ሰዎች እሰጣቸዋለሁ” አሉ ትእዛዛቸው እንዲያጋልጣቸው እየተናነቃቸው ።

ገና ወረኢሉ መፍረው በነበሩበት ጊዜ ፣ ወደ ሐማሴን የሰደዷቸው አምስቱ “ምርጥ ምርጥ ” ሐማሴኖች በተነገራቸው ሰአት መሠረት አምባ ገብተው በአካለ ጉዛይ ፣ በአዲ ግራት ፣ በዐድዋ ፣ በመቀሌና አምባላጌ በማምሬ በኩል አድርገው በየገበሩ አቆራርጠው አሉላ ከጠበቁት በላይ መረጃ አቀረቡ ። አሉላም ከጠበቁት በላይ ጀለሟቸው ። እነዚያ ልዩ ተመልካቾች ለላም መርዶ ነገረዋቸዋል ። አምባሪ የነበረችውን እልፍኛቸውን ጣሊያኖች አቃጥለው ፣ ‘አበቶች ልባቸው ወግ እን ዲሆን ፣ የአሉላ ቤት በነበረበት ቦታ ላይ እነሆ የወግ ጋጋ ሠራ ንበት’ ብለው መናገራቸውንና ነገሩም እውነት መሆኑን ሲነገ ራቸው ፣

‘የእርሱን ልብ ደግሞ አታጥፋቸው’ አሉ ።

አምባላጌ ላይ በተደረገው ጦርነት እንደገናም መቀሌን መክበብ የተደረገውን ሰልት ያቀነባበሩት ራስ አሉላ ነበሩ ።

በመኳንንት ቹኩት በተከፋፈለችው ትግራይ ፣ አንበሳ ሹመት ... በሹመትም ለመተመተ የተንገላታት አሉላ ፣ ጣሊያንን ... ድረገው ከሰሜን ኢትዮጵያ አስወጥተው የመረብ ማዶ ግዛ ቶቻቸውን መመለስ ፣ ያለዚያም የምኒልክ የጦር አበጋዝ መሆን

ዋናው ዒላማቸው ከሆነበት ጊዜና ውሳኔ ላይ ደርሰዋልና ፡ ያጠ
ኑትን ያህል ፡ ያመኑበትን ያህል ፡ የሚያውቁትን ያህል ፡ የችሎታቸ
ውን ያህል ፡ ጣሊያንን የመዋጋታቸውን ያህል ፡ አሥመራ ከተማ
ላይ የነበራቸውን ኀጀአቸውን የናፈቁትን ያህል ፡ የልብ ምክራ
ቸውን ለራስ መኰንን አበርክተው ፡ አስዘምተው ፡ በመጀመሪያ
አምባላጌ ላይ ድል አስገኝተው ፡ ቀጥለው መቀሌን ካስከበቡ
በኋላ ፡ "ሰበይቲ ሽዋ ሽህ ትውለድ" እሉና ያረረ አንጀታቸውን
ቅቤ አጠጡት ። ከኩፊት ጦርነት ሲመለሱ እንደ ተሠሩትም
ሹርባ ተሠርተው ጸጉራቸውን አንድ ጥዋ ቅቤ ተቀቡት ።

መቀሌ የነበረው የጣሊያን ጦር እንደ ተከበበ ጣሊያንም
መልእክተኞቹን ወደ አዲስ አበባ በመላክ ነገሩን በእርቅ ለመ
ጨረስ ጠየቀ ። እምዩ ምኒልክም "እኔ የሰላም ተጋፊ አይደለ
ሁም ። ሰላም ያበጠላችሁ እናንተ ናችሁ ፡ አሁንም ሰላም ከተመ
ኛችሁ እሺ" ብለው አንደገና የሰላም እጃቸውን ዘረጉ ።

እጼ ምኒልክ ለዚያ ጦርነት በአዝማችነቱ በራስ መኰንን
ፊንታ አሉላን ልከው ቢሆን ኖሮ ለሰላም ድርድር የሚያደርስ
ጊዜና ነጥብ ጣሊያኖች ባላገኙ ነበር !

ጣሊያኖች በሰላም ከመቀሌ ለመውጣት በ ሂቻከሉበት
ወቅት ደግሞ ፡ "ምኒልክ ያን ሰይጣን ፡ ያን አሉላ የሚሉትን
ምትሐት የሐማሴንና የሠራዩ ገዥ አድርገው ሊሰዱት ነው"
የሚል ወሬ አሥመራ ገባና ጣሊያኖችን ማሸበር ጀመረ ። እው
ነት ያለመሆኑን ባራቴየሪም በሰላዮቹ አማካይነት ካረጋገጠ
በኋላ ወደ ሀገሩ በአስተላለፈው ማብራሪያው ላይ ፡

"የኛ ጥላቻ በደም ሥሩ የሠረፀበትንና መራራ ጠላታችንን
አሉላን አጼ ምኒልክ ከግንባር መሥመር ወደ ኋላ መልሰውልናል ።
ምክንያቱም ግልጽ ነው ። ያ—ገዴለሽ ሰውዬ ጦርነት ከገጠመ
ከትእዛዝ ውጭ ሆና ወደፊት በመግፋት ለሰላማዊ ንግግርና
ውል በርና ጊዜ ሊሰጥ የማይፈልግ መሆኑን በመገመታቸው
ነው" ብሏል ።



ይሁን እንጂ ሲጨነቁ 'እርቅ' ፡ ተንፈስ ሲሉ ገፊት ሲያ
የነበሩት ጣሊያኖች ነገሩን በእርቅ ለመጨረስ በማስቸገ
ው ፡ ምኒልክም አዲሱን የማስፈራሪያ ዱላቸውን ጀንፎና ጦር
ልቁለት ጀመር ። ያሉላ መታጠቅ ጣጣውን የሚያከትምላቸው
ነት እንደሚሆን ምኒልክ ያመኑበት ጉዳይ መሆኑን የሚያ
ክት ዝግጅት ሆነ ።

# እሉላ በዐድዋ ጦርነት

የኢጣሊያ ወታደሮች ምፅዋ ከደረሱበት ዕለት ጀምሮ ፣ ራስ አሉላ የፈሩትና አስተድመውም የተከላከሉት ጉዳይ እየገፋ መጣና ዐድዋ ላይ ትልቁን ጦርነት አስነሣ ።

ከኢጣሊያኖች ጋር በሰላም ለመኖር ታላቅ እምነትና ተስፋም የነበራቸው አጼ ምኒልክ ፣ ዝነኛውን የውጫሌን ውል ሲፈራረሙ ዐሥራ ሰባተኛው አንቀጽ አከራካሪ ብቻ ሳይሆን ጦርነትም አስከተለ ። ያ ጣጠኛ አንቀጽ የሚለውም ፣

"የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ፣ ከአውሮፓ ነገሥታት ለሚፈልጉት ጉዳይ ሁሉ በኢጣሊያ መንግሥት አጋዥነት መላክ ይቻላቸዋል" ነበር ። ይህም አንቀጽ በአማርኛው ቋንቋ "ፈቃዱ የሆነ እንደሆነ" የሚል ቃል ያለው ሲሆን ፣ በኢጣሊያንኛው ቋንቋ ደግሞ "ይገባዋል" የሚል የግዴታ መንፈስ ያዘለ ኖሮ ሁለቱ ሳይገጣጠሙ ቀሩ ።

ራስ አሉላ ግን ፣ የውሉን ነገር እንደ ሰሙ ፣ 'ጠመንጃችን ካልመከተ ፈረንጂን በወረቀት ለመከላከል እንዴት ይቻላል?' ብለው ነበር ። የፈሩት አልቀረላቸውም ለጦርነቱ ከምኒልክ ጋር ሆነው ተሰለፉ ።

በጄኔራል ባራቲዬሪ አዝማችነት ፣ ሃያ ሺህ ወታደር አሰልፎ ከስድሳ በላይ መድፍ ጭኖ ከአሥመራ ተነሥቶ ትግራይ የገባው የኢጣሊያ ጦር ፣ በመጀመሪያ እምባላጌ ፣ ተከትሎ መቀሌ ላይ ከሆነ በኋላ እንደገና ኃይሉን ጨምሮ በአራት ጀኔራሎች አዋጊነት መድቦ ወደፊት ገፋ ።

አጼ ምኒልክም በራሳቸው አዝማችነት ፣ ከእቴጌ ጣይቱ ጀምሮ በአንድ ንጉሥ ፣ በሰባት ራሶች ፣ በአንድ ዋግ ፣ ሥዩምና በአንድ



ፊታውራሪ አዋጊነት ከሰባ ሺህ በላይ የሆነ ጦር አሰልፈው ወደ ዐድዋ ገሠገሡ ።

ሁለቱም ወገኖች ለታላቅ ጦርነት መሰላለፋቸውን የተመለከቱት እውነተኞቹ ዜጎች ደግሞ ፣ የግል ጠባቸውንና ኩርፊያቸውን ጠብ ርግፍ እያደረጉ ወደ ወገን ጦር ተቀላቀሉ ።

ከእነዚያም ቁርጠኞች ወገኖች ፣ ደጃዝማች ባሕታ ሐጐስ ራስ ስብሐትና ራስ ሐጐስ ተፈሪ ዋና ዋናዎቹ ነበሩ ። በተለይም ደጃዝማች ባሕታ ሐጐስ ቀደም ብለው የኢጣሊያኖች ደጋፊ ሆነው በማገልገላቸው የአካለ ጉዛይ ገዥ ሆነው ነበር ። በዚህም ጊዜ በግዛታቸው ውስጥ የሚገኘው ለም መሬት ተቆጥሮና ተከልሎ ለኢጣሊያኖች እንዲሰጥ እንዲያደርጉ ታዘዙ ። ቀጥሎ ደግሞ ፣ በግዛታቸው ውስጥ የሚገኙትን ቆነጃጅት እየመረጡ ለኢጣሊያውያን ወታደሮች እንዲሰጡ ታዘዙ ። በዚህ ጊዜ ባሕታ ሐጐስ አሻፈረኝ ብለው ይነሣሉ ። ባለቤታቸውም ፣

"ምነው እነርሱ ያዘዙህን ብትፈጽም" ይሏቸዋል ።

"እሽ እንግዲያው በመጀመሪያ ያንችን ልጆች ልስጣቸዋ!" ይላሉ ባሕታ ሐጐስ ።

"እዋይ! ይህስ አይሆንም!!" ይላሉ እናት ።

"ነገሩ ባንች ላይ ሲመጣ የእናትነትሽ ልብ ተነካ ። ሌሎች እናቶችም ልባቸው እንደሚነካ አስቢ" ብለው ባሕታ ፣ "የወገኖቼን መሬትና ቆነጃጅት ለቀይ መርዘኛ እባብ አሳልፌ አልሰጥም" ብለው 'አሻፈረኝ' ይላሉ ።

ወዲያው የበላያቸውና ተቆጣጣሪያቸው የነበረውን ኢጣሊያዊ የመቶ አለቃ ራሳቸው ጉረሮውን አንቀው ይጥሉና በእግራቸው ረግጠው በጉራዴያቸው ሲወጉት የመቶ አለቃው ፣

"ኢጣሊያኮ ኃያል ናት" እያለ ሲጮህ ባሕታም ጉሮሮውን በጉራዴያቸው እንደ ወጉ ፣ "ኢትዮጵያም ከኢጣሊያ የበለጠች ኃያል ናት" ብለው ረሸኑት ። ቀጥለውም ሐላይ በተባለው ቀበሌ ከነበረው የኢጣሊያ ጦር ጋር ገጥመው ከፍተኛ ጀብዱ ፈጽመው በቆራጥነት ተሠዉ ። ሕዝቡም ፣

"ባሕታ ባሕታ ሰገነይቲ
አንበሳይ ትውልድ ሰበይቲ
በሐንቲ ጠመንጃ ቀታሊ ምእቲ"

ትርጉሙም

"የሰገነይቲው ጀግና ባሕታ
እናትህ አንበሳ ወልዳ አሳደገች ወይ አጥብታ!
በአንድ ጠመንጃ መቶውን የምትመታ!"

ይህ የጀግንነትና የአንድነት ዜና በያለበት ማስተጋባት ጀመረና በሹመትና በልዩ ልዩ ምክንያት አኩርፈው የነበሩት መኳንንትና ወታደሮች ሁሉ ከኢጣሊያኖች አካባቢና ከየነበሩበት እየወጡ ወደ አጼ ምኒልክ ገሠገሡ። ከኢጣሊያ ጦር ጋር ተሰልፈው የነበሩትና በቅጽል ስም "ባሻ ባዙቅ" እየተባሉ ይጠሩ የነበሩት የኤርትራ ተወላጆችም ፤ "እንጀራቸውን ብንበላም ለነሱ ብለን ፤ አገራችንና ንጉሠ ነገሥታችንስ አንወጋም" ብለው ውስጥ ውስጡን ዐድመው ብዙዎቹ በጦርነቱ ሳይዋጉለት ቀርተዋል ።

አጼ ምኒልክ ኅዳር 19 ቀን 1884 ውጫሌ ላይ ከኢጣሊያ መንግሥት ወኪሎች ጋር በተፈራረሙት ውል መሠረት ፤ ዐሥራ ፬ኛውን አንቀጽ አጼ ምኒልክ እንዳለ እንዲቀበሉ ለማግባባትና ለማስፈራራትም የኢጣሊያ መንግሥት ልኮት አዲስ አበባ መጥቶ የነበረው አንቶኔሊ የተባለው ኢጣሊያዊ ከአጼ ምኒልክ ፤ ከእቴጌ ጣይቱና ከመኳንንቱ ፊት ቀርቦ ፤

"ይህን ነገር እምቢ ካሉ ጦርነት መነሣቱን እንዲያውቁት ያስፈልጋል!" ብሎ ቢደነፋ ፤ እቴጌ ጣይቱ ደግሞ ከእርሱ እጥፍ ጊዜ ቱግ ብለው ተቆጡና ፤

"እኛ ለራሳችን እንበቃለን ፤ የሀገራችንንም ክብር እንጠብቃለን ፤ እንፈራችሁም በፈቀድነው ጊዜ ከመሬታችን ከሀገራችን ተራራ እንደ ድንጋይ እንፈነቅላችኋለን" አሉ ።



እርሱም ከአዳራሹ ሲወጣ ከምክረ በኋላ እንደገና መለስ ብሎ ፤ "የምንገጥመውኮ ጦርነት ነው ፤ ወንድ በሆነላቸው እንኳን ሴቲቱ" አላቸው ።

"የእኔ ሴትነትና ያንተ ወንድነት የሚለካው እዚያው ጦር ሜዳ ነውና እንዳትቀር" ብለው ሲመልሱለት ራስ አሉላ በምተው ነበርና ፤

"እኔም የእቴጌ ጦር አበጋዝ እሆናለሁ" ብለው ነበር ። ምኒልክ ግን አሉላን የእርሳቸው የቅርብ ረዳትና አማካሪ የስልትም አስተባባሪ አደረጉ እንጂ ለእቴጌ አልሰጧቸውም ። አሉላ ከአማካሪነታቸው ሌላ ፤ በጠላት እንቅስቃሴ ላይ በስልት አስተባባሪነትታቸውም ማተኮር ዋናው የጦርነት መቅድም መሆኑን ስለሚያውቁ ፤ ቀደም ብለው በጣሊያኖች ሠፈርና እንቅስቃሴ ላይ አሠማርተዋቸው የነበሩ የመረጃ ሠራተኞቻቸው ያስገኙላቸው ውጤት ለጦርነቱ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ሊያበረክት ችሏል ።

የካቲት 22 ቀን 1888 ቅዳሜ ሌሊት በኢጣሊያ የጦር ሠፈር ውስጥ የነበሩት ሁለት የመረጃ ሠራተኞቻቸው ከኢጣሊያ የጦር ሠፈር ሾልከው ወደ ዐድዋ ገሥግሠው በራስ አሉላ ሠፈር ደርሰው ከራስ ዘንድ ቀረቡና ፤

"ጣሊያን ከንጋቱ ላይ ወደዚህ ሊመጣ ተዘጋጅቷል ፤ በምን እዚህ የነበሩት ሰላዮቹ ባቀረቡለት ወሬም መሠረት የአጼ ምኒልክ ሠራዊት ስንቁን ሊፈልግ መበታተኑንና ንጉሠ ነገሥቱ ከጥቂት ወታደሮች ጋር ብቻቸውን የቀሩ መሆኑን ደርሶበታልና ተጠንቀቁ" ብለው ነገሩዋቸው ።

ከእነዚህኞቹ መልእክተኞቻቸው ቀደም ብሉ ደግሞ ፤ በዚሁ በዐድዋ ጦርነት ታሪክ ምዕራፍ ውስጥ ስማቸው ሲወሳ የሚኖረውን ፤ ባሻይ አውአሎም ሐረጐትን ወደ ሐማሴን ዘመዶቻቸውን ለመጠየቅ እንደሚሔዱ ተመስለው ፤ ገብተው የኢጣሊያንን ሠፈር ሰልለው እንዲመለሱ በራስ መንገሻና በራስ አሉላ አማካይነት ከንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ቀርበው ፤ ጣሊያኖችን እንደምን አድርገው ሰልለው እንደሚመለሱ ስልታቸውን ተናግረው አጼ ምኒልክም ተስማምተውበት ተልከው ነበር ።

ባሻይም ከዐድዋ ገሥግሠው ከኢጣሊያኖችቹ ሠፈር እን
ደረሱ ፤ የአጼ ምኒልክ ጥላቻ ያላቸው መሆናቸውን ተናገረው
የጣሊያኖች ፈቃድ ከሆነም የምኒልክን ሁኔታ ሊሰልሉ
እንደሚችሉ ያመለክታሉ ። ጣሊያኖቹ የጦር አዝማችም የበ
ይን ሐሳብ ይቀበልና ሌሎች ሰላዮችም ጨምር ወደ ዐድ
መልሶ ይልካቸዋል ። ባሻይ ዐድዋ ከገቡ በኋላ 'ዘመድ ጠይ
ልምጣ እናንተ እዚሀ ጠብቁኝ' ብለው ከእነዚያ ከእውነተኛ
የኢጣሊያ ሰላዮች ተለይተው በምሥጢር ከሁለቱ ራሶች ጋ
ተነጋግረው ከጨረሱ በኋላ ፤ ከእርሳቸው ጋር የተላኩት እው
ተኞቹ የኢጣሊያ ሰላዮች እንዲያምኑ ተብሎ ፤

"በንቅ ያስቀብሀ ሁሉ ወደ አገርህ ሔደህ ስንቅህን
ጋጅተህ እንድትመለስ ተብለናል" የሚል የማስመሰያ ዐዋጅ
ዚያ ሰላዮች በነበሩበት አካባቢ ይለፈፋል ። ወዲያው ደግሞ በ
ሥጢር ለየጦር አበጋዞቹ ትእዛዝ ይተላለፍና ሠራዊቱ የውጊ
መሥመሩን እንዲይዝ ይደረጋል ።

ይሀ ከሆነ በኋላ ባሻይና የጣሊያን ሰላዮች ከዐድዋ
ከው ይወጡና ወደ ኢጣሊያ ሠፈር ሲገሠግሡ ሔደው የሰ
ትን 'ዐዋጅ' ይናገራሉ ።

የጣሊያኑ ጦር አዝማች በዚሀ መረጃ መሠረት እንቅስቃ
ውን ሲጀምር ፤ ራስ አሉላ ደግሞ ባሻይንም ጭምር የሚከታተ
ሁለቱን ሰላዮቻቸውን ወደ ኢጣሊያ ጦር ሠፈር አካባቢ ፤ '
ገደኞች' አስመስለው ልከው ነበር ። በዚህም መሠረት በሁ
አቅጣጫ ከተላኩት ሰላዮች ትክክለኛውን የጠላት እንቅስ
ዜና አግኝተው ፤ ለአጼ ምኒልክ አስረዱ ። ቀጥለውም አ
ላይ የሠሩዋቸውን እልፍኝ ከአዳራሽ ቤቶቻቸውን ያቃጠሉ
ውን የመረሩ ጠላቶቻቸውን ለሁለተኛ ጊዜ የሚያቃጥሉበ
የውጊያ ስልት አውጥተው መሥመራቸውን ይይዛሉ ።

በቀረበላቸው መረጃ መሠረትም የኢጣሊያ ጦር አ
ገሠ በዐድዋ ተራራዎችና ኮረብታዎች መካከል ከንጋቱ
ገባ ።



[illegible] ግራኪና ተግራኪን ለማስተናበርና ለመቆጣጠር [illegible]
[illegible] ።

ኢትዮጵያውያንን በመከፋፈልና ውለታ በማዋረስ ግዛት
እናስፋፋለን ፤ የቅኝ ግዛት ባለቤቶች እንሆናለን ፤ ብለው የተስ
ፈሩት ኢምፔሪያሊስቶች መኳንንቱን እርስ በርሱ ለማጋጨት
ራስ መንገሻን በስጋን ፤ ራስ መኩንን በምሥራቅ በኩል በም
ኒልክ ላይ እንዲያምፁ እንዲዋጉ ፤ ምኒልክ ከወደቁም በኋላ መኳ
ንንቱን እየገጠሉ በመውጋት ኢትዮጵያን ለመውረር ሲያስ
ጠነቅቁት የነበረው ሤራ ከሽፎ ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድ
ነቱን አጠንክሮ ወኔውንና ክንዱን አስቀድሞ በአንድ አዝማች
ትእዛዝ ፤ በአንዲትም ሰንደቅ ዓላማ ጥላ በመሰለፉ ፤ ሊከፋፍሉት
ሊያበጣብጡትና ሊገዙት በተነሡበት ጠላቶቹ ላይ ብርቱ ክን
ዱን ማለባቸው ።

እሑድ የካቲት 23 ቀን 1888 ከንጋቱ ዐሥራ ሁለት
ሰዓት ላይ የተጀመረው ጦርነት ፤ ቀኑን ሙሉ ውሉ ወደ ማታ
ሲያበቃ ፤ ድሉ ሙሉ ለሙሉ የኢትዮጵያውያን ሆነ ። በጦርነቱም
ከወራሪው ጠላት በኩል ዐሥር ሺህ ወታደሮች ሲሞቱ አንድ
ሺህ አምስት መቶ ቆሰሉ ሦስት ሺህ ተማረኩ ።

ከኢትዮጵያም በኩል እስከ ስድስት ሺህ የሚገመቱ ሲሞቱ
ስምንት ሺህ የሚሆኑ እንደ ቆሰሉ ተገምቷል ።

ራስ አሉላ ፤ በድሉ ማግሥት ከአጼ ምኒልክ ዘንድ ቀርበው ፤
"ጃንሆይ! ድላችን ገና ነው ፤ ጠላት ከማንሰራራቱ በፊት ወደ
አሥመራ እንገሥግሥ ! ያለዚያ እኛንም ሆነ ልጆቻችንን ለዘምና
ፈሬት የሚነግ ፤ አንድነታችንን የሚከፋፍል ጠንቅ ደግሞ ይተክ
ልብናል" ብለው አመለከቱ ።

"ማለፌ ነው ፣ ሐሳብህን ወድጄዋለሁ ። ግን ከመኳንንቱና ከጦር አበጋዞቹ ጋር ብንመክርበት ይሻላል" አሉ አጼ ምኒልክ ።

"እንግዲያው እስኪ መክርበትና ጦሩ እስቲዘጋጅ ድረስ ጃንሆይ ይፍቀዱልኝና እኔ የመረብን ወንዝ ተሻግሬ ልሥፈርና ከአሥመራ የሚመጣ ጦር ቢኖር ልከላከል" አሉ አሉላም፣ ንጉሠ ነገሥታቸውን በዐይነ—ሕሊናቸው ጭምር እየተማፀኑ ። በሐሳባቸው ደግሞ ፣ 'የመረብን ወንዝ ከተሻገርኩ የማደርገውን ዐውቃለሁ' እያሉ ።

"አንተ በሌለህበትስ ምን ተብሎ ይመከራል፤ ከመረብ ምላሽ ያለውን አገርም ሆነ ጣሊያኖቹ የሠፈሩበትን ሁሉ የምታውቀው አንተ ነህ ። ማናቸውንም ነገር ማስታወቅ ይገባሃልና ከመኳንንቱ ጋር እንምከርበት" አሉ አጼ ምኒልክም ።

በዚህ መሠረት አጼ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱ ባሉበት ፣ መኳንንቱና የጦር አበጋዞች ቹ ተጠርተው አሉላ ያቀረቡት ሐሳብ ለምክክር ቀረበ ።

'አገሩ ስለ ተራበ ለሠራዊቱ የሚሆን ስንቅ የለም ። ሠራዊቱም በጉዞና በረሃብ ተጎድተውቷል፤ በደረሰውም እልቂት አዝኗል ።

"እንደዚህ የተጎዳውን ሠራዊት ወደ መረብ ምላሽ ብናዘምተው ደግሞ ፣ ጣሊያኖች ያደረሱበት ችግር አንሶ ሕዝቡ በይበልጥ ይጎዳብናል ። ምናልባትም የጣሊያን ጦር ያለ የሌላ ኃይሉን ይዞ ከመጣብን ጦርነትም ገጥመን ድል የሆን እንደሆነ መላውን ኢትዮጵያን ይይዝና ነጻነቷ ጨርሶ ሊጠፋ ይችላል ።

"ስለዚህ ባይሆን ሠራዊቱ ካረፈና ከገገመ በኋላ ፣ አገሩም ጸጥ ያለ አዝመራ ሲያገኝ በቂ ስንቅና ዝግጅት አድርገን ብንመለስበት ይሻላል እንጂ ፣ አሁኑኑ ወደ መረብ ምላሽ መዝመራችን ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝንብናል" የሚል ሐሳብ ከመኳንንቱ ስለ ተሰነዘረ ፣ አጼ ምኒልክም ይህንኑ አስተያየት ተቀብሉትና የአሉላ ሐሳብ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ ።



አጼ ምኒልክ በጦርነቱ የወደቁባቸውን ጀግኖቻቸውን በክብር አስቀብረው ፣ ቁስለኞቹንም በእንክብካቤ እንዲጠበቁ ከአደረጉ በኋላ ወደ መናገሻ ከተማቸው ጉዟቸውን ሲጀምሩ ፣ የትግራይም መኳንንቶች በቂ መተዳደሪያ ፣ ሹመትና ሽልማት ሰጥተው

ራስ መንገሻም የራስ ወሌን ልጅ ወይዘሮ ከፈይን እንዲያገቡ አጼ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱ ፈቅደው ፣ ለሠርጋቸው መቋቋሚያ የሚሆንም ከፍ ያለ ገንዘብ መደቡላቸው ። ቀጥሎም የትግራይ መኳንንት ከራስ መንገሻ ጋር ከልብ እንዲታረቁና አገራቸውን በአንድነት እንዲጠብቁ ፣ 'ከእንግዲህ ወዲያ ነገር እንዳላስማባችሁ አደራ' ብለው ፣ የስሜን ግዛታቸውን እንደየትውልድ ዘርፋቸውና እንደየአገልግሎታቸው አከፋፈሉ ። በዚህም መሠረት ራስ መንገሻ ፣ ቀጥሎ ራስ ሐጎስና ደጃዝማች ሐድጉ ተንቤንንና ሽሬን ፣ ተበሩቀ ሕንጣሎ ዋጅራትንና አፎንጎን ፣ ራስ ሰብሐት አጋሜን እንዲገዙ ተሾሙ ።

በትግራይ ነገሥታት መሳፍንትና መኳንንት የዘር ሐረግ ውስጥ በቀጥታ ክር እንኳ ያልተያያዙት አሉላ በትግራይ ውስጥ ታላቅነትና ስልጣን ግዛት ተሰጡ ። ዋና ከተማቸው ዐድዋ ሆኖ እስከ መረብ ወንዝ ድረስ ያለውን ሰፊ ግዛት ሲገዙ በትግራይ ታሪክ ውስጥ አንድ የገበሬ ልጅ ከዚያ ደረጃ ላይ ሲወጣ የመጀመሪያው በመሆናቸው በትግራይ ውስጥ 'ጉድ' ተባለ ።

በሹመቱ የትግራይ መኳንንትና መሳፍንት አንገታቸውን ቢደፉበትም ፣ የገበሬው ልጅ ሁሉ ደግሞ የጊዜብትና የሚመኘው ሹመት ሆነ ። እንደ ርስተ ጉልቱ ሁሉ ፣ መኳንንቱ ቢደሙበትም ፣ ገበሬውና ነጋዴው እየተቀኘ ወንድ ልጅ በተወለደ ቁጥር "አሉላ" እያለ ስሙን ይሠይም ጀመር ። በአሉላ የላቀ ሹመትና ማዕረግ እንደገና ቅናት ያቃጠላቸው እነራስ ሐጎስ በአዝማሪዎቻቸው አፈ ቀላጤነት ፣

"እኒህ የሸዋ ሰው እንዴት የዋህ ናቸው፣
የነገሥታት ሐረግ መምዘዝ ተስኗቸው
አገር ለገበሬ ግዛ ማለታቸው ።
'ወዲ ቁቢን' አምነው ዐድዋን መስጠታቸው፣"

እያለች ግጠሙላን በመጀመሪያቸው ሕዝቡ ደግሞ ፣

"እኔህ የሸዋ ሰው አገር ይወዳሉ
መሬት ለገበሬ እያሉ ደላሉ ።
ጀግና የሚወዱ የሚሾሙ ጀግና
ምኒልክ የሚሉ ንጉሥ አጣ ገና ።
የትግራይ መኳንንት ምነዋ አያለቅሱ
ገበሬ ሲሾሙ ዐድዋ ላይ ንጉሡ!"

እያለች በማሲንቆኞች አማካይነት በየደጋጉና በየወንዙ እያስዘፈነ በይበልጥ አሳረራቸው ።

የምኒልክ ታማኝና ባለሟል የሆኑት አሉላ ፣ ትግራይ ውስጥ በፈለጋቸው ቀን ፣ ወደፈለጋቸው ቦታ እንደልባቸው የሚዘዋወሩ መንገሻንም ሆነ ሌሎቹን የማይፈሩና ለማንም የማያገበድዱ ሆኑ ። የትግራይ መኳንንትም ሆዳቸው እያረረ አሉላን በአክብሮትና በፍርሃትም መመልከት ከተገደዱበት ሁኔታ ላይ ደረሱ። አሉላ መቀሌ ከምትገኘው ጉጀአቸው ፍል ያለች አዲስ ቤት አዘሉም ውስጥ በማሠራታቸውም ፣ የትግራይ መኳንንት ፣ 'ሌላ ጎን አበባ እንደሆን' እያሉ የጥላቻና የንቀት ወሬ ማሰተጋባት ጀመሩ ።

እርግጥ ነው ፣ አሉላ መረብ ወንዝን ተሻግረው ጣሊያኖችን እየገፉ አስወጥተው ግዛታቸውን በእጃቸው ለማስገባት ብርቱ ምኞት ነበራቸው ። ለዚያ ዕድል የ ሊያበቃቸውንም ጊዜ በጉጉት ነበር የሚጠባበቁት ። ግን ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ከሚከተሉት አሠራር ማፈንገጥ እንደማይገባቸው እያመኑበት ሔደዋል ። ቢሆንም አዲሱን ግዛታቸውን ከዱሮው ግዛታቸው ጋር በማገድ ለማቀራረቡ ሕዝቡም ከሥር ከመሠረቱ የነበረውን አንድነት መተሳሰብ እንዳይቀዘቅዝ በተቻላቸው መጠን ይጥሩ ነበር ።

ከመረብ ወንዝ ማዶ በመገዛት ላይ የነበሩትንም ኢጣሊያኖች ሁኔታ በየዕለቱ እየተከታተሉ ፣ 'እስከ መቼ ነው በዝምታ የምናያቸው?' እያሉ መተከዝም ፣ እለታቸውን አስጨ ንቆ የያዛቸው ጉዳይ ሆነ ።



# የሁለቱ ራሶች ፍጻሜ

፩.

ራስ ምኒልክ ትግራይ ውስጥ ያደረጉት ሹም ሽር ፣ የአጼ ዮሐንስ ወራሽ ሆነው መላውን ኢትዮጵያን ለመያዝ ሲመኙ የነበሩትንና ትግራይን እንደ ግል ርስታቸው ሲቆጥሩት የነበሩትን መንገሻን ቅር እያሰኛቸው ሔደ ። ከዚያ ሌላ ደግሞ ፣ 'ወደ ቀበ' በረውን ግዛት ይዘው የምኒልክ ባለሟል ሆነው ዝዋ የነበረው ክንዳቸው ፈርጥሟል ። የሥልጣናቸው መወበና የአደራ አባታቸው ግፈንገፍ የልባቸውን ቁስል እየወጋባቸው ዕረፍት በማጣታቸው ፣ ከኢጣሊያኖች ጋር ታርቀው የሚፈልጉትን የጦር መሣሪያ አግኝተው ፣ ሲሆን ሲሆን የምኒልክን ያለዚያም በምኒልክ ሹማምንት የተከፋፈለባቸውን ትግራይን አስታለው ይዘው 'አሻፈረኝ' ለማለት ፣ ከሚያመቻቸው ደረጃ ላይ ለመውጣት ሲሉ የእንግሊዝ ንግሥት ቪክቶሪያ ከኢጣሊያኖች ጋር ከልብ እንዲያስታርቋቸው በምሥጢር ደብዳቤ ሰደዱ ።

ሁኔታቸውን በቅርብ ርቀት ሲከታተሉ ከነበሩት የውጭ አገር ተወላጆች አንዱ የሆነው ዋይልድ የተባለው እንግሊዛዊ ፣ ወደ ትግራይ ሔዶ ፣ ከራስ አሉላ ጋር ተገናኝቶ በሚጫወቱበት ሰዓት ነገሩን አነሣቶ ፣

"ራስ መንገሻ በእንግሊዝ አማካይነት ከኢጣሊያኖች ጋር ቢታረቁ እርስዎስ አይታረቁም ወይ?" ብሎ እንደ ዋዛ ሲጠይቃቸው ፣ ራስ አሉላ ክት ብለው ሣቁና ፣

"ከእንግሊዝ ወዳጅ ምን ሊሆን ነው? ከጣሊያኖች ጋር የሚታረቀው? ከመረብ ማዶ ከያዙት አገር ቁራጭ መሬት አይለቁትም ፣ የአርበኑን ለመውሰድ ይፈልጋሉ እንጂ ምን ሊያገኙበት ይችላሉ?" አሉት ።

"ከጣሊያኖቹ ጋር ከታረቁን የጦር መሣሪያ ለማግኘት ይመቸናል ይሆናል?" አለ ዋይልድ። "የጦር መሣሪያ ቢያከማችስ ምን ሊሆን ነው፤ ምኒልክን ወግቶ ዘውድ ሊያስመልስ ነው፤ ወይስ ጣሊያኖችን ወግቶ ከሐማሴን ሊያስወጣ ያስባል? ምንድን ነው ዓላማው?" ብለው መልሰው ጠየቁት።

"ምናልባት ትግራይንስ እንደ ድሮው በሙሉ ሥልጣን ለመግዛት ቢችሉስ?" አላቸው።

"ይህም አይሆንለትም፤ ከእንግዲህ ወዲያ ትግራይንም ቢሆን አጠቃሎ ሊይዝና ብቻውን ሊፈነጭ አይችልም። እኔም ራሴ ብሆን አልደግፈውም። ትግራይ በእጁ አልነበረችም፤ ራሱ እየደለ ነገሩን አበላሽቶ ከእጁ ያስወለቃት፤ እንዲያውም ትግራይን አሁን የሰጡትንም ግዛት ማስተዳደር አልሆነለትም። በአንድ በኩል ሐጎስ፤ በሌላ በኩል ሰባሐት፤ ደግሞ በሌላ አቅጣጫ ሌላው ይንቀሳቀሳል። ይኸው አንተም ራስህ ሸዋ ድረስ ሔደሃል፤ በያገሩ የተሾሙት መኳንንት ግዛታቸውን በሚገባ ይዘው ይኖራሉ። በሥራቸው ያሉትን ሹማምንትና መኳንንት እንደ ባሕሪያቸው ችሎታ ያስተዳድራሉ። በውስጣቸው ብጥብጥና ንትርክ የለባቸውም። ትግራይ ግን ያልታደለች ናት፤ ከባዕዳኑ ወረራ ሌላ መንገሻና መኳንንቱ በንትርክና በንትርክ ምስቅልቅል አድርገውባታል መሰለህ? ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲያ ዐርፎ ቢቀመጥ ነው የሚሻለው፤ ይህንንም ደግሞ ደጋግሜ ነግሬዋለሁ፤ እስመክረዋለሁ" አሉት።

"ለመሆኑስ ራስ መንገሻ ከኢጣሊያኖች ጋር ለመታረቅ ማሰባቸውንና ለንግሥት ቪክቶሪያም መላካቸውንስ ምኒልክ ሰምተዋል?" ብሎ ጠየቃቸው።

"መሰማታቸው የት ይቀራል? አገር አጠፋለሁ ብሎ ቢነሣባቸውስ ዝም እንላለን? መክረን እምቢ ካለኮ እኔም ራሴ ብሆን ዝም ብዬ አላየውም። ከእንግዲህ ወዲያ ራሱንና አገሩን ቢያውቅ ካልሆነ በቀር ምንም ነገር ሊያገኝ አይችልም። [illegible] ራሴ ሆን ብሎ ሊትዋጋ የሚሻለት ምኒልክ መሆናቸውን [illegible] አምነዋታለሁ። እርሱ ግን ገና ከኢጣሊያኖች ተጣላ እንደ[illegible]



ወጣም፤ [illegible] ባሕርይው ነው። የሆነ ሆኖ በተቻለኝ [illegible] እመክረዋለሁ አስመክረዋለሁ" ብለውት ነበር።

ምንም እንኳን ራስ መንገሻ ከዘር ሐረጎቻቸው ጋር እየተመላለሱ ወደ [illegible] እያሉ ቢሔዱም፤ የአጼ ዮሐንስን አደራ ከልባቸው ሳይረሱ፤ ከጣሊያኖቹም አጥብቀው ለማስወጣት ያልተቻላቸው ሲሆን ግን፤ መንገሻ ሊከተሉት ካሰቡት መንገድ እንዲመለሱ ለማድረግ የከረረው የማይሳካላቸው መሆኑን ከተገነዘቡ በኋላ፤ መንገሻን ፈንግለው የምኒልክ እንደራሴ ሆነው ትግራይን አጠቃለው ለመያዝ ምኞታቸው ከፍ ብሎ በነበረበት ወቅት ደግሞ፤ አጼ ምኒልክ ራስ መንገሻን እንሥተው ትግራይን ከሁለት ከፍለው ለራስ አሉላና ለራስ ሰባሐት ሊሰጡ ነው የሚል ወሬ ተሰራጨ።

ለወሬው መነሻና መገሥገሻም የነበረው ምክንያት፤ ራስ አሉላ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በቀጥታ ይጻጻፉ ስለ ነበረ አጼ ምኒልክ ከኢጣሊያ ጋር ያደረጉትን ሁለተኛውን የ[illegible]ና የስምምነት ውል መንገሻ ሳያውቁና ሳይሰሙ አሉላ አስቀድሞ እንዲያውቁት በመደረጉ፤ ከመንገሻ ይልቅ የንጉሠ ነገሥቱ የቅርብ ምስጢረኛ ሆነው በመገኘታቸው ነበር።

በተለይም አጼ ምኒልክ ራስ መንገሻ ወደ ሸዋ እንዲሔዱ በመጥራታቸው፤ ጉዳዩ አጠራጣሪ እየሆነ ልዩ ልዩ ወሬና ትርጉም እያዘለ ሔደ፤ ትግራይ ውስጥ የሚደረገውን ማንኛውንም እንቅስቃሴ በየፈረጁና በየመልኩ ይከታተሉት የነበሩት ጣሊያኖችም በሰላዮቻቸው አማካይነት እንዲት ፍንጭ ከአሉላ እንደ ወጣ ለማግኘት ቻሉ።

ራስ አሉላ ከሚያምኑዋቸው ሁለት መኳንንቶች ጋር ሲነጋገሩ በነበረበት የቆይታ ጨዋታ ላይ፤

"ራስ መንገሻን አጼ ምኒልክ ጠርተዋቸዋል የሚል ወሬ ሰምተን ለእንስናበት ገብተን ነበር። እርሳቸውም፤ 'እኔ የንጉሠ ነገሥት ግብር ሊሰጡኝ ጠርተውኝ መሔዴ ነው ብለዋል፤ እኔ

ት ይሆን' ብለው መነኩሴው አሉላን ይጠይቃሉ ። ራስ አሉ ላም መነኩሴዎቹን ያምኑዋቸው ነበርና ፤

'እኮ አባቴ ንጉሥነት የሚመኝ ሰው እንዲዚህ እየዋለለ መታየት ይገባዋል ብለው ነው? ነገሩ በኛው መካከል ይቅር እንጂ ፤ ንጉሥነቱ ቀርቶበት በያዘው ሹመትም መኖሩን እንጃ ለት ። የሆነ ሆኖ በርሱ እግር ራስ መኰንን ትግራይን ቢበጉ ቀው ባይመጡ አይቀሩም' ብለው ይነግሩዋቸዋል ። መነኩ ሴዎቹም ያችን ፍንጭ ወደ አሥመራ አስተላልፈዋት ኮር ማሊያኖች ጉዳዩን አስተድመው በለንቁበት የራሳቸውን ስልት መቀየስ ይጀምራሉ ።

ራስ ሐጎስ ከመተማ ጦርነት በፊት አንድ ደሃ ገበሬ ተከሶ ከችሎታቸው ሲቀርብ በገበሬው አነጋገር ተቆጥተው ኖር ፤

'ውሰደና ዐርባ ጅራፍ ግረፈው' ብለው ይፈርዳሉ ። ያ ደሃ ገበሬም ፤ 'በዮሐንስ አምላክ አልበደልኩም ፤ አልተመሰከ ረብኝም ይመስክርብኝ' እያለ እየጮኸ ተወስዶ ይገረፋል ። በኋላም ያ ደሃ ገበሬ ከአጼ ዮሐንስ ችሎት ቀርቦ ፤

"በዮሐንስ አምላክ እያልኩ ራስ ሐጎስ ገርፈውኛልና ፍርድ ይሰጠኝ" ብሎ አመለከተ ። አጼ ዮሐንስም ቱግ ብለው ይቆ ጡና ፤ ራስ ሐጎስ ከችሎቱ ላይ በለነበሩ 'መልስ ስጥ' አሏ ቸው ።

'አስመስክሬበት ነው ያስገረፍኩት ፤ ቢሆንስ ለአንድ ገበሬ ትግሬ እኔ እንዴት በችሎት ላይ እጠየቃለሁ' ብለው ይናገራሉ።

"ምናልክ አንተ ነህስል? ቢሆንስ በዮሐንስ አምላክ እያ ለሁ ትገርፈዋለህ? እሱን አይደለም የገረፍከው ፤ እኔን ነው የገረፍ ከኝ ንጉሥ እጋፋሪ ፤ ሐጎስንም ያዝና ወስደህ ግረፈው' ብለው ይፈርዳሉ ።

ወዲያው ነገሩን ለማተዝተዝ ሲባል ጥቂቶቹ መኳንንቶች ከራስ አሉላ ጋር ሆነው ራስ ሐጎስ ወደታሰሩበት ይሔዱና እጋፋ ሪውን ፤



'ምንስ ቢሆን ግርፊቱ የሐጎስ በሐጎስ ላይ ይወሰን ብለህ ነው? ተበሳጭተው ነውና እንዳትነካው ! እኛ የሚሆን እናስታርቃቸዋለን' ብለው እጋፋሪውን አዘው ሔዱ ።

በሦስተኛው ቀን እነራስ አሉላ ከአጼ ዮሐንስ ዘንድ ቀር በው በራስ ሐጎስ ምሕረት ሲለምኑ ፤ አጼ ዮሐንስም ፤ እጋፋ ሪያቸውን ጠርተው ፤

'ሐጎስ አልተደበደበም ወይ?' ብለው ቢጠየቁ እጋፋ ሪውም ፤ 'ይቅር ብለዋል ጃንሆይ ፤ እንዳትነኩዋቸው' ብለው እነ ዚያ ራስ አሉላ ስለ ነገሩኝ አልተገረፉም' ይላሉ ።

'እውነቱን ነው ወይ? እኔ እንዳትነኩ ብያለሁ?' ብለው አጼ ዮሐንስ ከነራስ አሉላ ላይ ያፈጣሉ ።

'ውሸት ነው አላልነውም' ይላሉ አሉላ ።

'እንግዲያው የኔን ፍርድ አውለህ አሳድርሃልና በገመዱ አንተ ገብተህ ትገረፋለህ' ብለው እጋፋሪያቸውን እንዲገረፉ ይፈርዳሉ ። ወዲያውም ሐጎስ ተፈትተው እጋፋሪው ተገረፉ ።

በዚያ ፍርድ ልባቸው የቆሰለው አሉላ 'ንጹሕ ደም አስ ፈብኝ ! ደሃውን ገበሬ የገረፈውን የመሳፍንት ወገበዱ አድና ለሁ ብዬ የሸሜ ንጹሕ ደም አስፈሰሱኝ" እያሉ ሲተክዙ ኖሩ ።

ራስ መንገሻ ፤ ተከፋ እንዳደረጉት ሸዋ ገብተው ከአጼ ምኒልክ ዘንድ የንጉሥነት ማዕረግ ለማግኘት ጉዞ በጀመሩበት ሰሞን ደግሞ ፤ የአሉላ መንደር ሰዎች የሆኑ ተንቤናውያን ወደዋ ሐጀው ፤ ሽንሩዋን በሙሉ የተሸለተች ዶሮ አቀረቡላቸው ።

'ምንድነው ነገሩ?' ብለው ራስ ጠየቁ ።

'ራስ ሐጎስ አሽከሮቻቸውን እየላኩ እንደዚህች ዶሮ ገፈ ፉን ፤ ባዶአችንን አስቀርተውናል ፤ ግብር መክፈል ያልቻለ ውን ደሃውን ገበሬ እየገረፉ አሠቃዩት ! ምነው ከዮሐንስ ጋር ዘምተናል ፤ ለአገራችን ተዋግተናል ፤ ምነው መላው አገር እርይ ብሎ በሚዋርብት ጊዜ እኛ መሠቃየታችን! ምነው በምግባሩን ። ራስ መንገሻም አልሰማን እሱ! ለማን እናት ንገባ!' ብለው አቤቱታ አቀረቡላቸው ።

'ደግሞን ገበሬ እየገረፉ አሥታዬትን' አሉና አሉላ የተገቢ የጦያግን አቡቴዎ ደጋውትና ፣ 'ምንው ቢያግልኝን' አሉና ደጋዎቸውን አስቆጠሩ ። 'ምን አግልጋችኋለሁ ? አግማግችኋለሁ እንጂ' አሉና 'ግልፈደ ነው አብረን እንሐዳለን' አሉዋቸው ለአቡቴዎ አትራቢያቹ ።

አሉላ ጥር 12 ቀን 1889 ሦስት መቶ የሚሆኑ ወታደሮች አስከትለው ወደ ሽሬ ተጓዙና ራስ ሐጐስን አስከበቡ፣

'አገሩን ለቀቅልኝ ፣ እጅህንም አስረክበኝ' ብለው ሽግ ግሉ በደላ ። 'ምንም የሚኒልክ ባለሟል ብትሆን እኔ ሐጐስ ለእንግሊዝ ያለ የደጃ ልጅ ግዛቴን ለቅቄ እጄን የምሰጥ አይደለሁም' ብለው መለሱላቸው ። እነዚህ ሁለት ራሶች ከዚያች ዕለት በፊት ቢካሰሱ ኖረዋል ። ሁለት ጊዜ ተዋግተዋል ። በዚያች ዕለት ደግሞ እንደ ተለመደው ትዕግሥታቸው በልቆ ኑሮ ተቈጡ ።

'እኔኮ የምኒልክ አሽከር ነኝ ፤ አንተ ግን ለጣሊያኖች ባሪያ ሆነህ መዋጋትህን ደርሼበታለሁና እጅህን ስጠኝ ይሻል ሃል' ብለው አሉላ መልሰው ላኩ ። የራስ ሐጎስ መልስ ሌላ ሆነ ። መንገሻ የሰጡዋቸውን አንድ አርጊ ቀላል መድፍ ደግነው አስተኩሱ ። የሠራዊታቸውም ብዛት ከአሉላ ወታደሮች እጥፍ ነበር ። ወጊያው ተከፈተ ሆነ ። በመጀመሪያ ከቀበሌው መካከል አሉላ አንዱ ሆኑ ። ቅልጥማቸውን ተመቱ ። ቀጥሎ የወንድማቸው ልጅ ባሻይ ገብረ እግዚአብሔር ተማረኩና ሐጎስ ገደሉዋቸው ።

አሉላ ቅልጥማቸውን በራሪ ጨርቅ አስሩና ወታደሮቻቸውን በቍልቍላ አስከትተው ወጊያውን በሌታቸውን ለቀውና የጠላታቸውን እርድ ጥሰው ገብተው ሐጎስን ከእርሻቸው ውስጥ እንዳሉ ማረኩዋቸውና ፣

'አንተ ብትማርከኝ ኖሮ ምን ታደርገኝ ነበር?' ብለው ጠየቁዋቸው ።

'እሰርህ ነበር' ቢሉዋቸው !

'ባንተ ስለብኩ ንጉሕ ደም አፍስሻለሁ ! ያ ደም ሁላችንንም እነሆ ተፋርዶናል' አሉና ፣ 'የአጼ ዮሐንስ ፍርድ እኮ



ነበር ፣ መግደል ነበረብህ ። ያ ፍርድ ዛሬ ይፈጸምብሃል" ብለው ወዲያውኑ አስገደሉዋቸው ። እባቸውንም አሽከሮቻቸው ተሸክመው ወደ አኩስም ወስደዋቸው ከዐሥር ወራት በላይ ለሆነ ጊዜ ታመው ቆይተው ፣ በዚሁ ቁስል የተነሣም የካቲት 9 ቀን 1889 በተወለዱ በስሳ ዓመታቸው ዐርፈው ዐድዋ በሚገኘው አባ ገሪማ በሚባለው ገዳም ተቀበሩ ። አዲኳላ የነበረው የጣሊያን አገረ ገዥም ፣ 'አሉላ ሞተ ! ትግራይም ከብጥብጥ ውስጥ መግቢያ ነው' ብሎ ወደርም ባስተላለፈው ዜና መሠረት የጣሊያን ጋዜጣም ፣ 'ጉራዴውን በኛ ላይ እንደ መዘዘ ወደ አፎቱ ሳይመልሰው አሉላ ሞተ' ብሎ ጻፈ ።

ራስ አሉላ ከሞቱ በኋላ ከተገጠሙ
ከሕዝባዊ እንጉርጉሮዎች ሁለቱ ፤
እነዚህ ጣሊያኖች እጅግ ተደሰቱ
የአሉላ ጉራዴ ሲበርድ ሰለቱ ።
በርም አደባባይ መድፍ ተተኩሶ
ምጽዋም ተሰምቶ መድፍ ተተኩሶ
አሥመራም ተሰማ መድፍ ተተኩሶ
የተደላሊ ደሙን ብድሩን መለሰ ።
ዐድዋ ያረረውን እንጀቱን አራሰ ።
አሉላ አባነጋ ክንዱን ተንተራሰ ።
ጣሊያን እልል አለ የልቡ ደረሰ ።

* * *

ወልደሚካኤልን አሸንፈው ገብተው ፤
ሰብስበውን ነበር ገበያ መሥርተው ።
በከሰላም በኩል ገበያ አሥርተው
በሐጢም ላይ አየን ገበያ አቋቁመው
በየደረሱበት ጠመንጃ እየመጡ
ራስ ያለ ዋጋ ለሕዝባቸው ሰጡ ።
ጠመንጃውም ቀረ ገበያው ተዘጋ
ምሰሶው ወደቀ አሉላ አባነጋ !
ሁሉንም ሰብስቦ ተሸክሞት ነበር
ሁሉም ተበተነ ምሰሶው ሲሰበር ።

## ትውልድ የሚከፍለው ውለታ ።

በዘመናት ውስጥ ለየሀገራቸውና ለየወገናቸው ታላላቅ አስተዋጽኦ ላደረጉ ዜጎች ትውልድ ውለታቸውን እየከፈለ ስለመኖሩ ከየአገሮቹ ታሪክ ላይ ይገኛል ። በሥነ ጥበብ ግለትም ፣ በተግባረ ዕድ ፣ በሥዕል ፣ በሙዚቃ ፣ በሥነ ጽሑፍ ፣ በፍልስፍና በሕክምና በልዩ ልዩ ሙያዎች ለየሀገራቸው የተቻለውን ያህል ላበረከቱ ትውልድም ሥራቸውን እየመዘነ ተገቢውን ዋጋቸውን ይከፍላል ። መታሰቢያቸው እንዲታወቅ በስማቸው መንገድ ፣ ትምህርት ቤት ሆስፒታል ድርጅት እንዲሠየምላቸው ሐውልት እንዲሠራላቸው ያደርጋል ።

ከኅብረተሰብ አገልግሎታቸው ለየት ያለ አገልግሎት የሰጡም አሉ ። የሀገራቸውን ጦር እየመሩ የዘመቱ ፤ የተዋጉና ያዋጉ ጀግኖች ደግሞ ለየት ያለ ባለውለታነት አላቸው ፤ እንደዚህ የመሰሉ ጀግኖች ደግሞ ትውልድ ዋጋቸውን በዕጥፍ ይከፍላል ።

ራስ አሉላ አባ ነጋ ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ባለውለታ መሆናቸውን እነሆ ከታሪካቸው ላይ ለመረዳት ችለናል ። ግን ለዚሁ ውለታ አገልግሎታቸው ኢትዮጵያውያን የከፈልነው ውለታ ሳይኖር ቆይቶ ፣

ለታላቁ ጀግና ጀኔራል ለራስ አሉላ አባ ነጋ ታላቅ ጀግንነትና የሥራ ዋጋ ለመክፈል የመጀመሪያው ርምጃ በ1974 ተጀመረ ።

አብዮታዊት ኢትዮጵያ በፊውዳላዊ ግዞት ተይዛ በነበረችበት ክፍለ ዘመን የሰሜኑን ግዛቷን አስከብረው ላለፉት ጀግናዋ ጥር 18 ቀን 1974 የሐውልታቸውን መሠረት አኖረች ።



በሐውልቱ መሠረት ላይ የተቀረጸው ጽሑፍም ፣

"የኢትዮጵያን ነጻነትና አንድነት ለመጠበቅ በዚህች ምድራና በጉንደት ፣ በጉራዕና በዶጋሊ ላይ በመላው ዓለም የታወቀ የማይረሳ ጀግንነት ለፈጸሙት ለራስ አሉላ አባ ነጋና ለሠራዊታቸው መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ጓድ ሊቀ መንበር መንግሥቱ ኃ/ማርያም የዚህን ሐውልት መሠረት ጥር 1974 አኖሩ" ይላል ።

በሐውልቱ መሠረት ላይ ቀጥሎ ያለው የራስ አሉላ ንግግር ተቀርጾበታል ። "አንድ ጊዜ ክንዴን አሳይቻቸዋለሁ ፤ እንደገናም ከመጡ እደግማቸዋለሁ ፤ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ወሰን ቀይ ባሕር ነው ። አሉላ አባ ነጋ 1880 ።"

ከላይ በተጠቀሰው ዕለት ጥዋት ተድአሊ በመጀመሪያ የደረስኩም ራሴ ነበርኩ ። በዚያች ዕለት ለአሉላ አባነጋ ሐውልት መሠረት እንደሚቀመጥ ከጥቂት ቀናት በፊት ጀምሮ ዐውቄው ስለ ነበረ ፣ የዕለቱዋን መድረስ በጉጉት ስጠባበቅ ሰንብቸ ነበርና የዋዜማው ሌሊት አልነጋልኝ ብሎ ስገላበጥ ነጋልኝ ። አሉላን በዐይደ ሥጋ አገኛቸው ይመስል ፣ ከነጋቱ በዐሥራ ሁለት ሰዓት ምጽዋ ተነሥቼ ተድአሊ በአንድ ሰዓት ደረስኩ ።

የፀሐይዋ ኃይል ለሰስ ያለ ነበር ። በአንድ ሰዓት ተኩል ከአዲስ አበባ የሔዱ የኪነት ባለሙያዎች ደረሱ ። ቀጥሎ ጋዜጠኞች ፣ ቀጥለውም ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ከሕዝባውያን ድርጅቶች የተወከሉ የቀይ ኮከብ ሁ ለገናር ተካፋዮች ደረሱ ።

ጓድ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በሦስት ሰዓት ላይ ደርሰው ከቁብታዋ ግርጌ ሲደርሱ አንድ የኪነት ባለሙያ በነጭ ፈረስ ላይ ተቀምጦ አሉላን ተመስሎ አጭር ድራማ አሳየ ። ከዚያም በኋላ ጓድ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ወደ ኮረብታዋ ወጥተው ለራስ አሉላ አባነጋ ሐውልት መሠረት የሆነውን ድንጋይ አስቀመጡ ።

[illegible] [illegible] በብሔራዊ ደረጃ ታሪኩ [illegible] መታሰቢያ ሲባል፣ በሥነ ሥርዓቱና በቦታው ለመገኘት በመቻሌ ነው። በሬትም ሆነ በኋላ የራስ አሉላን ታሪክና ለአገሩ ሕዝብ ለማቅረብ ላደረገው መከራ ማበረታቻ ሆኖኛል።